## ምዕራፍ ፡ ፴፫ ።

## ስለ ፡ አቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ መንግሥትና ፡ ስለ ፡ መታሰራቸው ።

ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ በመንግሥታቸው ፡ የሚከተል ፡ ከደን በኛ ፡ ሚስታቸው ፡ ከእቴጌ ፡ ማርያም ፡ ሥና ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ አልነበራቸውም ። ነገር ፡ ግን ፡ እመቤት ሐረጎ ፡ (ሐርጓ) ፡ ከሚባሉ ፡ ቍባታቸው ፡ ከስሜን ፡ ሴት ፡ ያዕቆብን ፡ ወልደው ፡ ነበር ፡ (1)። ስለዚህ ፡ እቴጌ ፡ ማርያም ፡ ሥና ፡ የልጆቻቸው ፡ ባሎች ፡ ራስ ፡ አትናስዮስ ፡ የበጌምድር ፡ ገዥ ፡ ራስ ፡ ክፍለ ፡ ዋሕድ ፡ የትግሬ ፡ ገዥ ፡ መክረው ፡ የ፯ቱን ፡ ዓመት ፡ ወጣት ፡ ያዕቆብን ፡ በራስ ፡ አትናስዮስ ፡ ሞግዚትነት ፡ አነገሡዋቸው ። ዙፋንን ፡ የሚቀናቀኑትን ፡ ዘድንግል ፡ የሚባሉትን ፡ የዐፄ ፡ ሚናስን ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ አስረው ፡ ከጣና ፡ ደሴት ፡ አጠገብ ፡ ሐይቅ ፡ ወስደው ፡ አሰሯቸው ። ታላላቆቹ ፡ መኳንንት ፡ ዘድንግልን ፡ አስረው ፡ ያዕቆብን ፡ ማንገሣቸው ፡ ዘድንግል ፡ የነገሡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዕድሜ ፡ሙሉና ፡ ዐዋቂ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሥልጣኑን ፡ በሙሉ ፡ ይዞ ፡ አያስገዛንም ፤ ያዕቆብ ፡ ግን ፡ ሕፃን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለስሙ ፡ እርሱን ፡ አንግሠን ፡ እኛ ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እየሾምን ፡ እየሻርን ፡ ለመግዛት ፡ እንደ ፡ ልባችን ፡ እንችላለን ፡ ብለው ፡ ነው ፡ ይባላል ።

እንደዚሁም ፡ የዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ ልጅ ፡ የአቤቶ ፡ ያዕቆብን ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ የአቤቶ ፡ (የገራም) ፡ ፋሲልን ፡ ልጅ ፡ ሱስንዮስን ፡ ይፈሩ ፡ ነበርና ፤ ይዘው ፡ ለማሰር ፡ ሲያስቡ ፡ ሱስንዮስ ፡ ከበጌምድር ፡ አምልጠው ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ወደ ፡ ጋላው ፡ አገር ፡ ሸሽተው ፡ ተቀመጡ ። ሱስንዮስና ፡ ዘድንግልም ፡ በዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ቤት ፡ አብረው ፡ ስላደጉ ፡ በጣም ፡ ይዋደዱ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

እነዚህ ፡ መንግሥትን ፡ የሚቀናቀኑት ፡ አንደኛው ፡ ከሸሸና ፡ ሁለተኛውም ፡ ከታሰረ ፡ በኋላ ፡ ዙፋኑን ፡ ለስሙ ፡ ለያዕቆብ ፡ ሰጥተው ፡ እቴጌ ፡ ማርያም ፡ ሥና ፤ ራስ ፡ ክፍለ ፡ ዋሕድ ፤ ራስ ፡ አትናስዮስ ፤ ደጃች ፡ ዘሥላሴ ፡ (ደጃች ፡ ዘሶ) ፡ አገሩን ፡ ተከፋፍለው ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ይገዙ ፡ ጀመር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ንጉሡ ፡ ያዕቆብ ፡ የንጉሥነት ፡ ሥልጣናቸው ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ ሆኖ ፡ መኖር ፤ ለሕሊናቸው ፡ ደስ ፡ ስላላላቸው ፡ እነዚህን ፡ ገዥዎች ፡ በበታቻቸው ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ አባቶቻቸው ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ለመግዛት ፡ የሚችሉበትን ፡ መንገድ ፡ ማዘጋጀትና ፡ በቀጥታ ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ ማድረግ ፡ ጀመሩ ። በመጀመሪያ ፡ ደጃች ፡ ዘሥላሴን ፡ ላዩን ፡ በግዛት ፡ አስመስለው ፡ ውስጡን ፡ በግዞት ፡ አድርገው ፡ ወዳገራቸው ፡ ወደ ፡ እናሪያ ፡ ላኳቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ገዥዎቹ ፡ እነራስ ፡ አትናስዮስ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ዕጣ ፡ በተራችን ፡ ለኛም ፡ ሳይደርሰን ፡ አይቀርም ፡ ብለው ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ተነሡባቸው ፤ ወዲያውም ፡ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ ሕፃን ፡ ነውና ፤ ለንጉሥነት ፡ አይበቃም ፤ እንዲያውም ፡ አብዷል ፡ ብለው ፡ በገሃድ ፡ እየተናገሩ ፡ ሕዝቡንም ፡ በዐድማ ፡ አሥነሡባቸው ። ዐድማውም ፡ መበርከ

(1) አቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ የእቴጌ ፡ ማርያም ፡ ሥና ፡ ልጅ ፡ ናቸው ፡ የሚሉ ፡ አሉ ።

ቱን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ያዕቆብ ፡ መኳንንቱ ፡ ይዘው ፡ እንዳያስሯቸው ፡ ፈርተው ፡ ከዚያ ፡ ሸሽተው ፡ ወደ ፡ እናታቸው ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ስሜን ፡ ተራራ ፡ ለመቀመጥ ፡ ሲሄዱ ፡ ከመንገድ ፡ ተያዙና ፡ በግዞት ፡ ወደ እናሪያ ፡ ተላኩ ።

## ምዕራፍ ፴፮ ።

ስለ ፡ ዐፄ ፡ ዘድንግል ፡ መንግሥት ፤ – ሐሰተኛው ፡ ክርስቶስ ፡ – የሃይማኖት ፡ ጦርነት ፤ ዐፄ ፡ ያዕቆብ ፡ ፪ኛ ፡ ከዙፋን ፡ እንደ ፡ ወጡ ፤ — የዐፄ ፡ ያዕቆብና ፡ የሱስንዮስ ፡ ጦርነት ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዘድንግል ፡ ከታሰሩበት ፡ ከጣና ፡ ሐይቅ ፡ አምልጠው ፡ በጐጃም ፡ አገር ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ተደብቀው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፤ እቴጌ ፡ ማርያም ፡ ሥናና ፡ መኳንንቱ ፡ ያለንጉሥ ፡ ሕዝቡ ፡ እንደማይገዛላቸው ያውቃሉና ፡ ከታሰሩበት ፡ አምጥተው ፡ ዘድንግልን ፡ ለማንገሥ ፡ ሰዎች ፡ ቢልኩ ፡ አልተገኙም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በመጨረሻ ፡ መልእክተኞቹ ፡ ከብዙ ፡ ድካም ፡ በኋላ ፡ በጠቋሚ ፡ አግኝተው ፡ ነገሩም ፡ ለሰላም ፡ መሆኑን ፡ አስረድተው ፡ አመጧቸውና ፡ በያዕቆብ ፡ ሥፍራ ፡ «አጥናፍ ፡ ሰገድ» ፡ ተብለው ፡ ነገሡ ።

፨ ፨ ፨

በዐጼ ፡ ዘድንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከአማራ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ ክርስቶስ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ሐሳዌ ፡ መሲሕ ፡ ሆኖ ፡ ተነሣ ፤ እናቱም ፡ መርዓተ ፡ ወንጌል ፡ ትባላለች ። ብዙ ፡ ሰውም ፡ ለጊዜው ፡ ተከተለው ። እንደ ፡ ክርስቶስም ፤ ፲፪ ፡ ሐዋርያት ፡ ፸፪ ፡ አርድእት ፡ (ደቀ ፡ መዛሙርት ) ፡ ፴፮ ፡ አንስት ፡ (ሴቶች) ፡ መረጠ ፡ ይባላል ። ዐጼ ፡ ዘድንግል ፡ ይኸን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ልከው ፡ አሲያዙት ፤ በተያዘም ፡ ጊዜ ፡ ጭፍሮቹ ፡ ተበታተኑ ። ሐሳዌ ፡ መሲሑ ፡ (ሐሰተኛው ፡ ክርስ ቶስ) ፡ እንደ ፡ ተያዘ ፡ ዐጼ ፡ ዘድንግል ፡ ፊት ፡ ቀረበ ። በቀረበም ፡ ጊዜ ፡ ቢጠየቅ ፡ አወን ፡ ከድንግል ፡ ማርያም ፡ የተወለድኹ ፡ የሞትኹ ፤ የተነሣኹ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ያረግኹ ፡ እኔ ፡ ክርስቶስ ፡ ነኝ ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከቤተ ፡ አሕዛብ ፡ ከመርዓተ ፡ ወን ጌል ፡ ተወለድኹ ፡ ምክንያቱም ፡ ከቤተ ፡ እስራኤል ፡ ተወልዶ ፡ እኛን ፡ ባዕድ ፡ አደ ረገን ፡ እንዳይሉኝ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ መልስ ፡ ሰጠ ። ንጉሡ ፡ ይኸን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ «ሰይጣን ፡ በሰው ፡ እያደረ ፡ እንዴት ፡ ይጫወትብናል» ፡ ሲሉ ፡ በመገረም ፡ ከተና ገሩ ፡ በኋላ ፡ እንዲገደል ፡ አዘዙና ፡ በሰይፍ ፡ ተገደለ ፤ ሬሳውንም ፡ አሞራና ፡ ዥብ ፡ በላው ።

፨ ፨ ፨

ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ የተባሉት ፡ ግን ፡ በሸሹበት ፡ ቦታ ፡ ሆነው ፡ መሞቱን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከሙታን ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወጣ ፡ እያሉ ፡ ማስተማር ፡ ዠመሩ ፤ እንደዚሁም ፡ ቍርባን ፡ እያደረጉ ፡ «ሥጋሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ ዘነሥአ ፡ እመ ርዓተ ፡ ወንጌል ፡ እግዝእትነ» ፡ አሉ ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህንም ፡ ጭፍራ ፡ እየተከታተለ ፡ ፈጃቸው ፤ ሐሳዌ ፡ መሲሕም ፡ በመሆኑ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ተከታይ ፡ አላገኘም ።

የዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ቀድሞ ፡ መጥተው ፡ የነበሩት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሚሲዮናውያን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከፍተን ፡ ብዙ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ ከፖርቱጊዞች ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ደባልቀን ፡ እያስተማርን ፡ ለቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አገልጋይ ፡ የሚሆኑ ፡ ልጆች ፡ እናዘጋጅ ፡ ብለው ፡ አስቀድሞ ፡ ከዐጼ ፡ ያዕቆብ ፡ ጋራ ፡ ተነጋግረው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ይኸንኑ ፡ እፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ ሚሲዮኖቹ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የንጉሥታቱ ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ወደ ፡ ደንቀዝ ፡ ቢመጡ ፡ ያዕቆብ ፡ ቃስረው ፡ ዘድንግል ፡ ነግሠው ፡ ቢያገኙ ፡ አስቀድሞ ፡ ንግግራቸው ፡ ከያዕቆብ ፡ ጋራ ፡ ነበርና ፡ ደነገጡ ፡ ይባላል ። ቢሆንም ፡ አሳባቸው ፡ ይከናወን ፡ እንጂ ፡ የንገሥታቱ ፡ መለዋወጥ ፡ እነሱን ፡ የሚያገባቸው ፡ ነገር ፡ የለምና ፡ አሳባቸውን ፡ ላዲሱ ፡ ንጉሥ ፡ ለዐጼ ፡ ዘድንግል ፡ አቀረቡላቸው ።

ዐጼ ፡ ዘድንግልም ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ጉዳይ ፡ እስኪመከርበት ፡ ድረስ ፡ ይቈይ ፡ አሉና ፡ ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ መልክተኛ ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ጳጳስ ፡ ወደ ፡ ክሌማንት ፡ (ቀሌምንጦስ፡) ፰ኛና ፡ ወደ ፡ ኤስፓኙ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ፡ ፊልጶስ ፡ ፫ኛ ፡ የወዳጅነት ፡ ደብዳቤ ፡ ጨምረው ፡ ላኩ ።

አሳባቸውም ፡ እንደ ፡ አባቶቻቸው ፡ እንደነ ፡ ዐጼ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ እንደነ ፡ ዐጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ የሚያስተምሩ ፡ ኤስፓኞችና ፡ ፖርቱጊዞች ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለማስመጣት ፡ ነበር ። ንጉሡም ፡ የዚህኑ ፡ መልስ ፡ በተስፋ ፡ ሲጠብቁ ፡ ቈዩ ፤ ይልቁንም ፡ ቀድሞ ፡ ዐጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግልንና ፡ ዐጼ ፡ ገላውዴዎስን ፡ ፖርቱጊዞች ፡ እንደ ፡ ረዷቸው ፡ እንደዚሁም ፡ የኤስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ እንደ ፡ ፖርቱጋል ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ እንደ ፡ አሜሪካ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ እንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በዓለም ፡ ላይ፡ኃይሉ ፡ የገነነ ፡ ነበርና ፡ ከውጭም ፡ ከውስጥም ፡ ጠላት ፡ ቢነሣብኝ ፡ የኤስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ ይረዳኛል ፡ እያሉ ፡ ተስፋ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ። ሚሲዮኖቹም ፡ ይኸንኑ ፡ ተስፋቸውን ፡ በንግግራቸው ፡ ስላፀኑላቸው ፡ ሚሲዮኖቹን ፡ ወዳጅ ፡ አድርገዋቸው ፡ ነበር ። በመጨረሻም ፡ ካቶሊኮችንና ፡ ኮፕቶችን ፡ እያከራከሩ ፡ አሳባቸውን ፡ ከካቶሊኮቹ ፡ ጋራ ፡ አደረጉ ፡ ይባላል ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ከጦር ፡ አለቃው ፡ ከደጃች ፡ ላእከ ፡ ማርያም ፡ ጋራ ፡ ተስማምተው ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ለውጠው ፡ ወደ ፡ ካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘረዋል ። እየተባለ ፡ በቀሳውስቱም ፡ በሕዝቡም ፡ ዘንድ ፡ ተወራ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ የነበሩት ፡ ከእስክንድርያ ፡ የመጡት ፡ ጳጳሱ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ለንጉሡ ፡ ለዘድንግል ፡ የሚታዘዘውን ፡ ገዝቻለሁ ፡ ብለው ፡ መኳንንቱንም ፡ ሕዝቡንም ፡ አወገዙ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከእናሪያ ፡ የተመለሰው ፡ ደጃች ፡ ዘሥላሴ ፡ ራስ ፡ ዘሥላሴ ፡ ተብሎ ፡ የጐጃምን ፡ ሕዝብ ፡ ይዞ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ተነሣ ። ንጉሡም ፡ ወታደሮቻቸውን ፡ አስከትለው ፡ ሄደው ፡ ደምቢያ ፡ ውስጥ ፡ ባርጫ ፡ ከሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ከደጃች ፡ ዘሥላሴ ፡ ጋራ ፡ ለጦርነት ፡ ተሰለፉ ። በዚህም ፡ ጦርነት ፡ የቤተ ፡ ክህነትና ፡ የሃይማኖት ፡ ጥብቅነት ፡ (ፋናቲክነት ፡) ያለው ፡ ወገን ፡ ከራስ ፡ ዘሥላሴ ፡ ጋራ ፡ ሆነ ።

በዚያ ፡ ዘመን ፡ የነበሩ ፡ ፪፻ ፡ የሚሆኑ ፡ ብረት ፡ የያዙ ፡ ፖርቱጊዞችና ፡ ሚሲዮ ኖች ፡ ግን ፡ ታማኝ ፡ ከሆኑት ፡ ከንጉሡ ፡ አሽከሮች ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ በዐጼ ፡ ዘድን ግል ፡ ጐን ፡ ተሰልፈው ፡ እፊትዎ ፡ እንሞታለን ፡ እያሉ ፡ ያደፋፍሯቸው ፡ ነበር ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ጦርነቱ ፡ እንደ ፡ ተዠመረ ፡ ከንጉሡ ፡ ከዘድንግል ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ እየ ከዳ ፡ ወደነዚያ ፡ ዞረ ፤ ቢሆንም ፡ የቀሩት ፡ በገርግንነት ፡ ይዋጉ ፡ ዠመር ። በጦርነቱም ፡ ውስጥ ፡ የንጉሡ ፡ ታማኝ ፡ የጦር ፡ አዛዦቸው ፡ ደጃች ፡ ላእከ ፡ ማርያም ፡ ባንካሴ ፡ ተወግቶ ፡ ወደቀ ። ንጉሡም ፡ ወጊውን ፡ ተጠባብቀው ፡ ለመግደል ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ በወደቁ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚሁ ፡ ሌሎቹ ፡ በተቀባው ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ እጅህን ፡ አትዘርጋ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ አልፈው ፡ በጦርና ፡ በአንካሴ ፡ ወጓቸው ፤ ዋናው ፡ አዝማች ፡ ራስ ፡ ዘሥላሴም ፡ አነጣጥሮ ፡ ግንባራቸውን ፡ መታና ፡ ሲጥላቸው ፡ ከወደቁ ፡ በኋላ ፤ ወታደሮቹ ፡ ጨረሷቸው ። በሞቱም ፡ ጊዜ ፡ ፫ ፡ ዓይነት ፡ ግፍ ፡ ተደረገባቸው ፤ ፩ኛ ፡ ከጣታቸው ፡ ላይ ፡ አልማዝ ፡ ያለበትን ፡ ወርቅ ፡ እንወስዳለን ፡ ብለው ፡ ጣታ ቸውን ፡ አብረው ፡ ቈረጡት ፤ ፪ኛ ፡ ዓይናቸውን ፡ በዘንግ ፡ ወጓቸው ፤ ፫ኛ ፡ በሬ ሳቸው ፡ ላይ ፡ የፈረስ ፡ አጐዳ ፡ ተነዳባቸው ፡ ይባላል ። ሬሳቸውም ፡ እንዳለፉት ፡ ነገሥታት ፡ በክብሬታ ፡ ሳይቀበር ፡ ባንድ ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ ተጥሎ ፡ በኋላ ፡ ባላገሮች ፡ አግኝተው ፡ ቀብረዋቸው ፡ ነበርና ፤ ከርሳቸውና ፡ ከያዕቆብ ፡ ቀጥለው ፡ የነገሡት ፡ ኋደኛቸው ፡ ዐጼ ፡ ሱስንዮስ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ሬሳቸውን ፡ ከዚያ ፡ አስመጥተው ፡ ጣና ፡ በደሲት ፡ ዳጋ ፡ በክብሬታ ፡ አስቀበሯቸው ። ታሪክ ፡ ነገሥታቸውን ፡ በየሥፍ ራቸው ፡ ተመልከት ።

ዐጼ ፡ ያዕቆብ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ከዙፋን ፡ ወርደው ፡ በግዞት ፡ ወደ ፡ እናሪያ ፡ ተልከው ፡ ስለ ፡ ነበር ፤ እቤቶ ፡ ሱስንዮስም ፡ በሸዋ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፤ ዘድንግልም ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ደጃች ፡ ዘሥላሴ ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ ይዘው ፡ ይገዙ ፡ ዠመር ። እንዲያውም ፡ ራሳቸው ፡ ለመንገሥ ፡ አስበው ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ እርሳቸውም ፡ እንዳይነግሡ ፡ የእናሪያ ፡ የድኻ ፡ ልጅ ፡ እንጂ ፡ የን ጉሥነት ፡ ዘር ፡ ስለሌላቸው ፡ ሕዝቡም ፡ ያለንጉሥ ፡ መገዛትን ፡ አለመውደዱን ፡ ስለ ፡ ተገነዘቡ ፡ በመጨረሻ ፡ ያዕቆብን ፡ ጠርቼ ፡ ባነግሥ ፡ ይሻላል ፡ አሉና ፤ ዐፄ ያዕቆብን ፡ ከእናሪያ ፡ አስመጥተው ፡ ሁለተኛ ፡ በዙፋን ፡ ላይ ፡ አስቀመጧቸው ።
በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ የዘድንግልን ፡ ሞት ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ የጋ ላና ፡ የሸዋ ፡ ጦራቸውን ፡ አስከትለው ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ሄዱ ። በዚያም ፡ ያማ ረውን ፡ ገዥ ፡ ራስ ፡ አትናስዮስን ፡ እንድ ተመጣ ፡ ብለው ላኩባቸው ። ራስ ፡ አትናስዮስም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ሄደው ፡ በሰላም ፡ ተገናኙ ። በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ ዘሥላሴ ፡ መልእክተኛ ፡ ላኩ ። ደጃች ፡ ዘሥላሴ ፡ ግን ፡ ላዩን ፡ እሺ ፡ እመጣለኹ ፡ እያሉ ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ለጦርነት ፡ ይዘጋጁ ፡ ዠመር። ከያዕቆብና ፡ ከጳጳሱ ፡ ከቡነ ፡ ጴጥሮስም ፡ ተገናኝተው ፡ በሱስንዮስ ፡ የሚደረ ገውን ፡ ጦርነት ፡ በስምምነት ፡ ጨረሱ ። ለሱስንዮስም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ገብተው ፡ የነበሩት ፡ ራስ ፡ አትናስዮስ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ከድተው ፡ ወደ ፡ ያዕቆብ ፡ ተመለሱ ።

ቢሆንም ፡ የአቤቶ ፡ ሱስንዮስ ፡ አኳኋን ፡ [illegible]ርቶ ፡ ነበርና ፡ ዐፄ ፡ ያዕቆብ ፡ ለሱስንዮስ ፡ ካማራ ፡ ገሚሱን ፡ አገር ፡ ሸዋንና ፡ ወለጋን ፡ ጭምር ፡ ልስጥኸና ፡ ታርቀን ፡ አብረን ፡ እየገዛን ፡ እንቀመጥ ፡ ብለዋቸው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሱስንዮስ ፡ የግዛት ፡ ጊዜያቸው ፡ እንደ ፡ ደረሰና ፡ በጠገባቸው ፡ ያለውም ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ የዐፄ ፡ ያዕቆብን ፡ ወታደር ፡ ለማሸነፍ ፡ በቂ ፡ መሆኑን ፡ ስለ ተረዱት ኢትዮጵያ ፡ በሙሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተሰጥታኛለችና ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ዕርቅ ፡ አልቀበልም ፡ የሚል ፡ ምላሽ ፡ ሰጡ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ በዐፄ ፡ ያዕቆብና ፡ በደጃች ፡ ዘሥላሴ ፡ መካከል ፡ በሥልጣን ፡ የተነሣ ፡ ቅያሜ ገብቶ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ለሱስንዮስ ፡ ተመቻቸው ። ቢሆንም ፡ ከዐፄ ፡ ያዕቆብ ፡ ተለይተው ፡ ደጃች ፡ ዘሥላሴ ፡ ለብቻቸው ፡ ከሱስንዮስ ፡ ተዋጉና ፡ ሠራዊታቸው ፡ አልቆ ፡ ብቻቸውን ፡ አምልጠው ፡ ከሸሹ ፡ ወዲህ ፡ ታርቀው ፡ ለሱስንዮስ ፡ ገቡላቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሱስንዮስና ፡ የቀረው ፡ የዐፄ ፡ ያዕቆብ ፡ ጦር ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ደራስያን ፡ ጐጃም ፡ ውስጥ ፡ ናዝሬት ፡ እንደ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ መገርመሪያ ፡ ጨጨሆ ፡ በር ፩ ፡ ጎል ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ተጋጥሞ ፡ ይዋጋ ፡ ገርመር ፤ በጦርነቱም ፡ መገርመሪያ ፡ ዐፄ ፡ ያዕቆብ ፡ ሞቱ ። አነጣጥረው ፡ የመቷቸውም ፡ ሱስንዮስ ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። ቢሆንም ፡ ሠራዊቱ ፡ በሌሎቹ ፡ መኳንንት ፡ እየተመራ ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ። ይልቁንም ፡ ጳጳሱ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ በቀኝ ፡ እጃቸው መስቀላቸውን ፡ ጨብጠው ፡ ወታደሩን ፤ ግፋ እያሉ ፡ ያበረቱ ፡ ነበርና ፤ የጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ረዘመ ። በኋላ ፡ ግን ፡ በሱስንዮስ ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ አንድ ፡ ዐረብ ፡ አነጣጥሮ ፡ ተኵሶ ፡ በጠመንዣ ፡ ጳጳሱን ፡ ገደላቸው ። በሩቅም ፡ የተኰሰባቸው ፡ የቱርክ ፡ ወታደር ፡ መስለውት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጳጳስ መሆናቸውን ፡ ቢያውቅ ፡ አይገድላቸውም ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ምክንያት ፡ የመጣው ፡ ሱስንዮስ ፡ ጳጳሱን ፡ አስገደሏቸው ፡ እያሉ ፡ ሕዝቡና ፡ ቀሳውስቱ ፡ ስላጕረመረሙ ፡ የዚህን ፡ ወሬ ፡ ለማስወገድ ፡ የተፈጠረ ፡ ምክንያት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ሲዋጉ ፡ ውለው ፡ ጊዜው ፡ መሽቶ ፡ ነበርና ፡ ከመካከላቸው ፡ አንዱን ፡ ብቻ ፡ ዕንጨት ፡ አንጠልጥሎ ፡ ሲያተርፈው ፡ ብዙ ፡ የዐፄ ፡ ያዕቆብ ፡ ፈረሰኞች ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ሲሸሹ ፡ ገደል ፡ እየገቡ ፡ ሞቱ ፡ ይባላል ። ገላውዴዎስ ፡ የሚባለውንም ፡ የዐፄ ፡ ያዕቆብን ፡ ልጅ ፤ ሱስንዮስ ፡ አሳንቀው ፡ ገደሉት ፡ ይባላል ። ጺጋ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚባለው ፡ ሌላው ፡ ልጃቸው ፡ ግን ፡ ከጦርነቱ ፡ አምልጦ ፡ ወደ ፡ ስናር ፡ ሄዶ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ። በዚያም ፡ ሳለ ፡ ባላባቱ ፡ ኑርባት ፡ ልጇን ፡ ልዳርልህና ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ተቀመጥ ፡ ብሎት ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ጺጋ ፡ ክርስቶስ ፡ እንቢ ፡ ብሎ ፡ ያገኘውን ፡ ጦር ፡ ሰብስቦ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ከዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ወይም ፡ ከመኳንንቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ ተዋግቶ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ስላልቀናውና ፡ ይልቁንም ፡ ስለ ፡ ቈሰለ ፡ ከዚያ ፡ ተመልሶ ፡

ወደ ፡ ሱአኪም ፡ (የሱዳን ፡ ወደብ) ፡ ሄደ ። የኩልቦ ፡ መጽሐፍ ፡ በ፲፰፻፳፱ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ እንደሚገልጸው ፡ ጳጳ ፡ ክርስቶስ ፡ ከ፴ ፡ ጓደኞቹ ፡ ጋራ ፡ ከሱአኪም ፡ ወደ ፡ ካይሮ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ በካይሮ ፡ የሚገኙት ፡ የኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖት ፡ ሹማምቶች ፡ የቱርክ ፡ ባሻ ፡ ሳይቀር ፡ ላንድ ፡ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ የሚገባ ፡ የክብር ፡ አቀባበል ፡ አደረጉለት ። ከካይሮም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተሻገረ ፤ በዚያም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ገዳም ፡ ከጐበኘ ፡ በኋላ ፡ ከካቶሊኮች ፡ ቀሳውስት ፡ ጋራ፡ ግንኙነት ፡ አድርጎ ፡ አብሮ ፡ ሰነበተ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ናዝሬት ፡ በለው ፡ ቢካቶሊኮቹ ፡ ገዳም ፡ ከኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖት ፡ ወደ ፡ ካቶሊክ ፡ መዞሩን ፡ በገሀድ ፡ አስታወቀ ። የዚህንም ፡ ወሬ ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አላቸው ። ወደ ፡ ሮማም ፡ እንድትመጣ ፡ የሚል ፡ መልክት ፡ ላኩበት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ በክርፋ ፡ በናፕል ፡ በኩል ፡ አልፎ ፡ ሮማ ፡ ደረሰ ። በየደረሰበትም ፡ የክብር ፡ አቀባበል ፡ አልጐደለበትም ። በኋላም ፡ ከሮማ፡ ወደ ፡ ፓሪስ ፡ ተሻገረ ። በፓሪስም ፡ በሰሙ ፡ አገር ፡ የሚደርሰው ፡ ደስታና ፡ ኀዘን ፤ እየተፈራረቀበት ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፤ የፈረንሳዊ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ካርዲናል ፡ ሪሸሊዩ ፡ እየደገፉት ፡ ኖሮ ፡ በመጨረሻ ፡ ታሞ ፡ በሺሕ ፡ ፲፮፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ አቈጣጠር ሞተና ፡ በረይ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተቀበረ ።

## የዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።


### ምዕራፍ ፡ ፴፯ ።

### ስለ ፡ ዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡-የዐፄ ፡ ሱስንዮስና ፡ የእቴጌ ፡ ማርያም ፡ ሥና ፡ ዕርቅ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ቅያሜ ።

ገራም ፡ ፋሲል ፡ የዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ የአቤቶ ፡ ያዕቆብ፡ ልጅ ፡ ናቸው ። ወደ ፡ ወንድሜ ፡ (1)ወደ ፡ ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ልሂድ ፡ ብለው፡ ከሸዋ ፡ ተነሥተው ፡ ጐንደር ፡ ሄደው ፡ በዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ቤት ፡ ተቀመጡ ። ገራም ፡ መበላቸውም ፡ ውስጡን ፡ ብልኅ ሆነው ፡ ሳለ ፡ በነጋገራቸው፡ ሞኝና ፡ ባላገር ፡ ስለ ፡ ሚመስሉ ፡ ነው ፡ ይባላል ።

ያገራችን ፡ ታሪክ ፡ እንደሚተርከው ፡ ገራም ፡ ፋሲል ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ለእቴጌ ፡ ማርያም ፡ ሥና ፡ ኮሶ ፡ ተጣባኝ ፡ ብለው ፡ ቢነግሯቸው ፤ እቴጌም ፡ ምንስ ፡ ሞኝ ፡ ቢሆን ፡ የነጋሢ ፡ ልጅ አይደለምን ፡ በገረድ ፡ እጅ ፡ አይጠጣም ፡ ብለው ፡ ሐመልማላዊት ፡ የሚባሉ ፡ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ በእልፍኛቸው ፡ ተጠብቀው ፡ የሚኖሩ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ፋሲልን ፡ ኮሶ ፡ አጠጭው ፡ አሏቸው ፤ ሐመልማላዊትም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ከሚቀመጡበት ፡ እልፍኝ ፡ ወስደው ፡ አጠጧቸው። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ገራም ፡ ፋሲል ፡ የጐልማስነታቸው ፡ ጊዜ ፡ ደርሶ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ተገናኝዋቸውና ፡ በዚሁ ፡ ግንኙነት ፡ ሱስንዮስ ፡ ተፀነሱ ፤ ከ፫ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ የፅንስ ፡ መልክ ፡ ይታወቃልና ፡ እቴጌ ማርያም ፡ ሥና ፡ "አንቺ ፡ ሐመልማላ

፩) ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ለገራም ፡ ፋሲል ፡ የአጎታቸው ፡ የዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ልጅ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ቀጥታ ፡ ወንድም ፡ አይደሉም ።



በደብረ ፡ መይ (መዊእ) ፡ ኦዲት ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ (ጐጃም) ፡ የሚገኘው ፡ የፀዒ ፡ ሱስንዮስ ፡ የቤት ፡ ፍራሽ ፡
(ከአናራቶሪ ፡ መጽሐፍ) ። ፲፻፶፭

ዊት ፡ የዕንስ ፡ መልክ ፡ አየሁብሽ ፡ ነገሩ ፡ ምንድነው ፡ ብለው ፡ ቢጠይቋቸው» ፡ እቴጌ ፡ እኔ ፡ የምኖር ፡ ከእርስዎ ፡ እልፍኝ ፡ ነው ፡ ትንኝን ፡ ሆኖ ፡ ገባን ፡ አሏቸው ፤ እቴጌዪቱም ፡ «በዩ ፡ እስቲ ፡ ጊዜ ፡ ይግለጠው» ፡ ብለው ፡ ዝም ፡ አሉ ። ከ፯ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ዕንሱ ፡ እየገፋ ፡ ሄደ ።

እቴጌም ፡ «ትንኝን ፡ ሆኖ ፡ ገባ ፡? አላልሽም ፡ ነበር ፡ እውነቱን ፡ ንገሪኝ ፡ አለዚያ ፡ አስገርፍሻለሁ» ፡ ቢሏቸው ፡ እሳቸውም ፡ ከገሩም ፡ ፋሲል ፡ መዕነሳ ቸውን ፡ ገለጹ ። እቴጌም ፡ ከቤትዎ ፡ የሚወለድ ፡ ልጅ ፡ መንግሥትዎን ፡ ይወ ርሳል ፡ የሚል ፡ ንግር ፡ ይሰሙ ፡ ነበርና ፡ ፋሲል ፡ ሞኝ ፡ መስሎ ፡ መጥቶ ፡ የኔን ፡ መንግሥት ፡ ሊያፈርስ ፡ ነውን ፤ ፋሲልን ፡ ቶሎ ፡ ፈልጉ ፡ ቢሉ ፤ ፋሲል አስቀድሞ ፡ ነገሩን ፡ ሰምተው ፡ ነበርና ፡ ከዚያ ፡ ሸሽተው ፡ ወደ ፡ አያታቸው ፡ ወደ ፡ እቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ተሻገሩ ። ከዚህ ፡ በኋላ እቴጌ ፡ ማርያም ፡ ሥና ፡ ወይዘሮ ፡ ሐመልማላዊትን ፡ ሆዷን ፡ እሽዋት ፡ ብለው ፡ የጤፍ ፡ ገለባ ፡ ሙቅ ፡ ውሃ ፡ እያስነከሩ ፡ ሆዳቸውን ፡ አሳሹዋቸው ። ምክንያ ቱም ፡ ሱስንዮስ ፡ ዕውር ፡ ሆነው ፡ እንዲወለዱ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ሐመልማላዊ ትም ፡ ወደ ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ጐጃም ፡ ተላልከው ፡ ኖሮ ፡ ከጐጃም ወገኖቻቸው ፡ መጥተው ፡ ሠርቀው ፡ ግንደ ፡ በረት ፡ ወስደው ፡ አስቀመጧቸው ። በዚያ ፡ ሱስ ንዮስ ቢወለዱ ፡ ዕውር ይሆናሉ ፡ የተባሉት ፡ ዓይናቸው ፡ የአጥቢያ ኮከብ መስሎ ፡ ተወለዱ ። ከደጉም ፡ በኋላ ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ዘድንግልን አሸንፈው ፡ በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ ያይናቸውን ፡ ማማር ፡ ለማስደነቅ ፡ በዘመኑ ፡ የነበረ ፡ ባለቅኔ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ተቀኘ ፡ ይባላል ።

ምስለ ሰብአ ፡ ሮሜ ፡ ወጽርእ ፡ ለእመ ፡ ነበርከ ፤
እምአምለኩ ፡ በኮከብ ፡ ዓይንከ ።

ትርጓሜ ።

የጽርዕና ፡ የሮም ፡ ሰዎች ፡ በወንጌል ፡ ሳያምኑ ፡ በኮከብ ፡ ያ ፡ መልኩ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ ሱስንዮስ ፡ ከነሱ ፡ ጋሩ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ብትኖር ፡ ኖሮ ፡ ዐይንኽን ፡ ኮከብ ፡ መስሏቸው ፡ ባመለኩበት ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ።

ወደ ፡ ቀድሞው ፡ ታሪክ ፡ ዕንመለስ ፡ ሱስንዮስ ፡ ባለፈው ፡ እንደተባለው ፡ ከደጉ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻም ፡ ደጃች ፡ ዘሥላሴን ፡ ዐፄ ፡ ያዕቆብን ፡ ወግተው ፡ አሸንፈው ፡ ወዲያው ፡ ሳይውል ፡ ሳያድር ፡ ጐጃም ፡ ቀራንዮ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ «ሥልጣን ፡ ሰገድ» ፡ ተብለው ፤ ነገሡ ። የነገሡበትን ፡ ዘመን ፡ የብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ዋዜማ ፡ ሺህ ፡ ፭፻፺፭ ፡ ያደርገዋል ። የውጭ ፡ አገር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ደግሞ ፡ እንዳገራቸው ፡ አቈጣጠር ፡ ሺህ ፡ ፮፻፯ ፡ ያደርጉታል ፡ ይኸውም ፡ ሲሆን ፡ ሺሕ ፮፻ ፡ ወይም ፡ ሺህ ፡ ፭፻፺፱ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዐፄ ፤ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የዕረፍት ፡ ዘመን ፡ ከሺሕ ፡ ፭፻፴፫ ፡ ላይ ፡ የገ

ላውዴዎስን፡ ፲፱ ፡ የሚናስን ፣ ፬ ፡ የሠርፀ ፡ ድንግልን ፣ ፴፬ ፣ የያዕቆብን ፣ ከዘ ድንግል ፡ ጋራ ፡ ፯ ፡ ወይም ፡ ፰ ፡ የጨመርን ፡ እንደሆነ ፡ የሱስንዮስ ፡ ንግሥ ፣ ሺህ ፡ ፭፻፺፯ ፡ ወይም ፡ ፰ ፡ ዓ፡ ም፡ ይሆናል ።

ዐፄ ፡ ሱስንዮስም ፡ ከደብረ ፡ ታቦር ፡ ጋራ ፡ ፳ ፡ የሚሆን ፡ ከተማ ፡ ቈርቈረዋል ፡ ይባላል ፣ ዋናውን ፡ ከተማቸውን ፡ ግን ፡ ደንቀዝ ፡ አደረጉ ። የደንቀዝ ፡ በታ ፡ ዙሪያው ፡ እንደ ፡ አምባ ፡ ገደልነት ፡ ያለው ፡ ላዩ ፡ ሜዳ ፡ ላገሩ ፡ ሁሉ ፡ አማካይ ፡ ነው ፡ ሱስንዮስም ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ረዥም ፡ ግንብ ፡ አሠርተው ፡ ከግንቡ ፡ ላይ በመነጥር ፡ ሲመለከቱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ትግሬ ፣ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ጐጃም ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ የመተማ ፡ አፋፍ ፡ ጭልጋ ይታያል ።

ዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ እንደ ፡ ነገሡ ፡ ጠበኞቻቸው ፡ ወደ ፡ ነበሩት ፡ ወደ ፡ እቴጌ ፡ ማርያም ፣ ሥና ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ባለቤት ፡ ሄደው ፡ በለፈው ፡ ጥፋቴ ፡ ምሕረት ፡ ያድርጉልኝና ፡ ከልብዎ ፡ ይታረቁኝ ፡ ብለው ፡ ለመኗቸው ። እቴጌይቱም ፡ «ከያዕቆብ ፡ ተዋግተኸ ፡ መግደልኸና ፡ መንግሥቱንም ፡ መያዝኸ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ ነው ፣ አንተስ ፡ ቢሆን ፡ ከነያዕቆብ ፡ ከነዘድንግል ፡ ጋራ ፡ በቤቴ ፡ ያደግኸ ፡ (1) ልጄ ፡ አይደለህምን ፣ አሁንም ፡ ምሬኸለሁ ፣ ነገር ፡ ግን ፡ አንተም ፡ የያዕቆብን ፡ መኳንንቶች ፡ በቂም ፡ እንዳታጒላላቸው ፡ ከማዕርጋቸውም ፡ እንዳታወርዳቸው ፡ ርስታቸውንም ፡ እንዳትነቅላቸው ፣ እኔም ፡ በሞትሁ ፡ ጊዜ ፡ በደከምሁበት ፡ ገንዘቤን ፡ በጨረስሁበት ፡ በማኅደረ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንድታስቀብረኝ ፡ ቃል ፡ ግባልኝ» አሏቸው ። ዐፄ ፡ ሱስንዮስም ፡ ይኸን ፡ ያሉኝን ፡ ሁሉ ፡ እፈጽማለሁ ፡ ሲሉ ፡ ቃል ፡ ገቡላቸው ፣ እቴጌዪቱም ፡ ከልቤ ፡ ምሬኸለሁ ፡ መንግሥትንም ፡ ከልጅ ፡ ልጆችኸ ፡ አያውጣው ፡ ብለው ፡ መረቋቸውና ፡ ተራረቁ ።

እንደዚሁም ፡ በእቴጌዪቱ ፡ አማካይነት ፡ የጌታቸው ፡ ሞት ፡ ጸጸቱ ፡ ያልበረደላቸው ፡ የዐፄ ፡ ያዕቆብ ፡ ሹማምንቶች ፡ እየታረቁ ፡ ገቡላቸውና ፡ በማዕርግ ፡ አስቀመጧቸው ። ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ሹመትና ፡ ማዕርግ ፡ ግን ፡ ለወንድሞቻቸው ፡ ለመልክአ ፡ ክርስቶስ ፣ ለአፈ ፡ ክርስቶስ ፣ ለሣህለ ፡ ክርስቶስ ፣ ለየማነ ፡ ክርስቶስ ፣ አደላድለው ፡ ሰጡ ።

ነገር ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጳጳስ ፣ የነበሩት ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዐፄ ፡ ሱስንዮስና ፡ ዐፄ ፡ ያዕቆብ ፡ በተዋጉበት ፡ ቀን ፡ አቡኑ ፡ በዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ወታደር ፡ እጅ ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ወገን ፡ በዚሁ ፡ ቂም ፡ አድርጎ ፡ ነበርና ፣ በመንገሣቸው ፡ ደስ ፡ አላለውም ፣ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ንጉሡ ፡ የብዙ ፡ ሠራዊት ፡ ጌታ ፡ በመሆናቸው ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ ከእቴጌና ፡ ከመኳንንቱም ፡ ስለ ተስማሙ ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ (ዐላዊ ፡ ንጉሥ) ፡ እያለ ፡ ከማማት ፡ በቀር ፡ ለጊዜው ፡ የጐዳቸው ፡ ነገር ፡ የለም ።

(፩) በቤቴ ፡ ያደግኸ ፡ ሲሉ ፡ ግን ፡ በጐጃም ፡ በግንደ ፡ በረትና ፡ በሸዋ ፡ አድጉ ፡ ከሚለው ፡ ጋራ ፡ ይፋለሳል ፣ ነገር ፡ ግን ፡ ግማሹን ፡ ጊዜ ፡ በዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ቤት ፣ ግማሹን ፡ ጊዜ ፡ በሸዋና ፡ በጋላ ፡ አገር፡አድገው ፡ ይሆናል ።

ጋሎችም ፡ አስቀድሞ ፡ በስደታቸው ፡ ጊዜ ፡ ኋላም ፡ ከዐፄ ፡ ያዕቆብ ፡ በተዋጉ ፡ ጊዜ ፡ በጦርነትም ፡ በምክርም ፡ እየረዱ ፡ ደስ ፡ አሰኝተዋቸው ፡ ነበርና ፤ ተከትለው ፡ ከመጡት ፡ በቀኛ ፡ ሌሎችንም ፡ ከሸዋና ፡ ከወለጋ ፤ ከግንደ ፡ በረት ፡ በጥሬ ፡ እያስመጡ ፡ በዳሞት ፤ በጉጃም ፤ በአገው ፡ ምድር ፤ በመተከልና ፡ በባንጃ ፡ ርስተ ፡ ጉልት ፡ እየተከሉ ፡ አሰማሯቸው ። ዐፄ ገላውዴዎስ ፡ የተከሉትን ፡ የመካነ ፡ ሰማዕታት ፡ ቅዱስ ፡ ገላውዴዎስንና ፡ እቴጌ ፡ ሥሉስ ፡ ኅይላ ፡ የተከሉትን ፡ የማኅደረ ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቀፈፍ ፡ (ርስተ ፡ ጉልት) ፡ ሳይቀር ፤ ሚሶውን ፡ እየተዉ ፡ ሁለት ፤ እጁን ፡ እየወሰዱ ፡ ለጋሎቹ ፡ ሰጡቸው ፡ ይባላል ። በዚህም ፡ ሁሉ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሰዎች ፡ ቅያሜ ፡ እየበረከተ ፡ ሄደ ።

በሌላው ፡ የክርስቲያን ፡ አገርና ፡ ሕዝቡ ፤ ቤተ ፡ ክህነትን ፡ በሚያከብርበት ፡ መንግሥት ፡ እንደሚደረገው ፡ በኢትዮጵያም ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ ለመግዛት ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ድጋፍ ፡ ቀላል ፡ አይደለም ፤ ስለዚህ ፡ ዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ በቤተ ፡ ክህነቱ ፡ በኩል ፡ እንደተጠሉ ፡ ያውቁ ፡ ነበር ፤ ሕዝቡም ፡ በቤተ ፡ ክህነቱ ፡ ስብከት ፡ (ፕሮፓጋንዳ) ፡ እንደሚነሳባቸው ፡ ተጠራጠሩ ። ባንድ ፡ ወገንም ፡ ከሰሜን ፡ ቱርኮች ፡ በዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ጊዜ ፡ ተዋግተው ፡ ኅይላቸው ፡ ደክሞ የነበሩት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መንግሥት ፡ በተለዋወጠ ፡ ጊዜ ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ የሚደረገው ፤ ጦርነት ፡ አግዟቸው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መልሰው ፡ ቀድሞ ፡ ይዘውት ፡ የነበረውን ፡ ስለ ፡ ያዙ እነሱንም ፡ ወግቶ ፡ ለመመለስ ፡ ቤተ ፡ ክህነቱና ፡ ሕዝቡ ፡ ካላበረላቸው ፤ ወይም ፡ ከውጭ ፡ መንግሥት ፡ የበቃ ፡ ርዳታ ፡ እንደ ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ካላገኙ ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ አመዛዘኑ ።

ስለዚህ ፡ ከቤተ ፡ ክህነቱ ፡ ጋራ ፡ ያላቸው ፡ ቅያሜ ፡ እየባሰ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ ባጠገባቸው ፡ ያሉትን ፡ ሚሲዮኖችና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ባለሟል ፡ አደረጓቸው ፤ ለካቶሊክ ፡ ሚሲዮኖቹም ፡ የራሳቸውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚተክሉበትና ፡ የሚተዳደሩበት ፡ ሰፊ ፡ መሬት ፡ ከደንቢያ ፡ ሰጡቸው ። ፖኤዝ ፡ የሚባለውን ፡ የካቶሊኮችን ፡ አለቃ ፡ ከፍሬሞና ፡ ወደ ፡ ደንቀዝ ፡ አስመጥተው ፡ ባጠገባቸው ፡ አስቀመጡት ፤ ደንበኛ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሣቸውን ፡ ለማክበር ፡ አኵስም ፡ ጽዮን ፡ በብሩ ፡ መኳንንትና ፡ ቀሳውስት ፡ ታጅበው ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ ፖኤዝንም ፡ ስለ ፡ ፍቅሩ ፡ ይዘውት ፡ ሄደው ፡ ነበር ። እርሱም ፡ በዚያው ፡ በጐንደር ፡ ተምሮ ፡ አማርኛና ፡ ግዕዝ ፡ ያውቅ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

ከዚያም ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ በሺህ ፡ ፮፻ ፡ ዓ፡ ም፡ ለኢስፓኝና ፡ ለፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ለዶን ፡ ፊልጶስና ፡ ለሮማው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ለጳውሎስ ፡ ፭ኛ ፡ ደብዳቤ ፡ አዘጋጅተው ፡ በዚሁ ፡ በፖኤዝ ፡ እጅ ፡ ላኩ ፤ በዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ውስጥ ፡ የዝምድናና ፡ የወታደር ፡ ጥየቃ ፡ ሲኖርበት ፡ እንደዚሁም ፡ በሮማ ፡ የካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንተዳደራለን ፡ የሚል ፡ ጽሕፈት ፡ ነበረበት ፡ ይባላል ።

እሁን ፡ ግን ፡ ለጊዜው ፡ ይኸን ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ አድርገን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ የፖርቱጋልን ፡ መንግሥት ፡ ትተው ፡ ፊትም ፡ ዐፄ ፡ ዘድንግል ፡ አሁንም ፡ ዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ከኤስፓኝ ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ የተላላኩበትን ፡ ምክንያት ፡ ለመግለጽ ፡ እንዲረዳ ፡ ስለ ፡ ኤስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ ባጭሩ ፡ እንጠቅሳለን ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፫ ።

## ስለ ፡ ኤስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ ገናናነት ፡ ባጭሩ ።

ባ፲፮ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ፡ ም፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የኤስፓኝን ፡ መንግሥት ፡ ገናናነት ፡ ከመጥቀስ ፡ በፊት ፡ ስላለፈ ፡ ታሪኩ ፡ ባጭሩ ፡ እንጽፋለን ።

ዛሬ ፡ ኤስፓኝ ፡ በሚባለው ፡ መንግሥት ፡ ውሥጥ ፡ ቀድሞ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ኢበር ፡ ይባሉ ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ ጥንት ፡ በእስያ ፡ ውስጥ ፡ በካውካዝ ፡ ደቡብ ፡ ይገኝ ፡ የነበረ ፡ ያንድ ፡ አገር ፡ ስም ፡ ነው ።

በዚህ ፡ አገር ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፊንቃውያን ፡ በኋላም ፡ ግሪኮች ፡ ገብተው ፡ ተመሥርተውበት ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የነበራቸውን ፡ ሥልጣኔ ፡ ትተውላቸው ፡ እንደዚሁም ፡ በስመ ፡ ጥሩው ፡ በአኒባልና ፡ ባባቱ ፡ በአሚልካር ፡ ባርካ ፡ ጊዜ ፡ ካርታገሮች ፡ ከአፍሪካ ፡ ሰሜን ፡ ተሻግረው ፡ ይዘውት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሮማውያን ፡ ከካርታገሮች ፡ ጋራ ፡ ባፍሪካና ፡ በሲሲል ፡ ግዛት ፡ ሁሉ ፡ ይዋጉ ፡ በነበረና ፡ አፍሪካዊው ፡ ሺፒዮን ፡ አኒባልን ፡ በሸነፈው ፡ ጊዜ ፡ ካርታገሮች ፡ በፍጹም ፡ ኤስፓኝን ፡ ለቀው ፡ የኤስፓኝ ፡ ግዛት ፡ ወደ ፡ ሮማውያን ፡ ዞረ ። የሮም ፡ ግዛት ፡ እሁለት ፡ ከተከፈለ ፡ በኋላም ፡ ኤስፓኝ ፡ በምዕራቡ ፡ የሮማ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ይተዳደር ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቫንዳል ፡ አሌን ፡ ስዌብ ፡ ዊዚጎት ፡ የሚባሉት ፡ ነገዶች ፡ በየጊዜው ፡ እየወረሩ ፡ የዛሬዩቱን ፡ ኤስፓኝ ፡ ይዘዋት ፡ ነበር ። በ፮ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ሌዎቪጂልድ ፡ የሚባለው ፡ የኤስፓኝ ፡ ሰው ፡ ያገር ፡ ተወላጆቹን ፡ ሰብስቦ ፡ ወራሪዎቹን ፡ ተዋግቶ ፡ አሸነፈና ፡ የኤስፓኝን ፡ ነፃነት ፡ በደንብ ፡ አቋቋመ ። ከተማውንም ፡ ቶሌዶ ፡ (በታጎ ፡ ወንዝ ፡ አቅራቢያ ፡ ከማድሪድ ፡ ደቡብ ፡ ምዕራብ) ፡ አደረገ ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ዐረቦች ፡ በሰባተኛውና ፡ በስምንተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ኀይል ፡ አግኝተው ፡ የአፍሪካን ፡ ሰሜን ፡ በወረሩበት ፡ ጊዜ ፡ ከአፍሪካ ፡ ሰሜን ፡ ተሻግረው ፡ ኤስፓኝንም ፡ ያዙትና ፡ እስከ ፡ ፲፩ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መገምመሪያ ፡ ድረስ ፡ ገዙት ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የኤስፓኝ ፡ ዘር ፡ ከነዚሁ ፡ ከዐረቦቹ ፡ ተዋልዶ ፡ የተደባለቀ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ባሥራ ፡ አራተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ የኤስፓኝና (የካስቲይ) ፡ የፖርቱጋል ፡ ሕዝቦች ፡ ኅብረት ፡ አድርገው ፡ በፈረንሣይ ፡ መን

ሥትም ፡ ርዳታ ፡ ዐረቦችን ፡ ወግተው ፡ አስወጡና ፡ የኤስፓኝን ፡ መንግሥት ፡ ራሱን ፡ አስቻሉት ። መንግሥቱም ፡ እያደር ፡ ኀይለኛ ፡ ሆነ ። ይልቁንም ፡ በሻርል ፡ ፭ኛና ፡ በልጁ ፡ በፊልጶስ ፡ ፪ኛ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ በመርከብም በወታደርም ፡ ከሌሎቹ ፡ መንግሥታት የበረታ ፡ ሆነና ፡ ከኤውሮፓ ፡ ሳርዴኝን፡ ሲሲልን ፡ ሚላንን ፡ ናፕልን ፡ የፈረንሣይን ፡ ደቡብ ፡ ሉክሳምቡርግን ፡ ሆላ ንድን ፡ በጠገቡ ፡ የሚገኘውን ፡ ትልቁን ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፤ ከአሜሪካን፡ አብዛኛውን ፡ የደቡብ ፡ አሜሪካንን ፡ ከእስያ ፡ በትልቁ ፡ ውቅያኖስ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ደሴቶች ፡ በማሌዚያ ፡ ያለውን ፡ አሜሪካኖች ፡ ይገዙት ፡ የነበረ ውንና ፡ አሁን ፡ የለቀቁትን ፡ አገር ፡ ፊሊፒን ፡ ይገዙ ፡ ነበር ። ፊሊፒን ፡ የተ ባለውም ፡ አገር ፡ በኦኤስኝ ፡ ንጉሥ ፡ በፊሊፕ ፡ ፪ኛ ፡ ስም ፡ ተሰይሞ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ ኤስፓኝ ፡ በዘመኑ ፡ ተፎካካሪው ፡ ነን ፡ ከሚሉት ፡ ከቱርክ ፡ ከፈረንሣይ ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ እየተዋጋ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ ማድ ረጉ ፡ በሌላው ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ታወቀ ፡ እንዲሁም ፡ ጐንደር ፡ ባሉት ፡ ፖር ቱጊዞችና ፡ ይልቁንም ፡ በፖኤዝ ፡ አፍ ፡ እየተነገረ ፡ በዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ዘንድ፡ ይሰማ ፡ ገ፦መር ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ በሺህ ፡ ፲፻ኛ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ «የማይሸነፈው ፡ ጦር» ፡ የሚባ ለው ፡ የኤስፓኝ ፡ ጦር ፡ በንግሥት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ የሚመራውን ፡ የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ ለመውጋት ፡ በመርከብ ፡ ሲሄድ ፡ ድንገተኛ ፡ ማዕበል ፡ ተነሥቶ ፡ ስላበላ ሸው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የተበላሸው ፡ መርከብና ፡ ያለቀው ፡ ወታደር ፡ የኤስፓኝን ፡ መንግሥት ፡ ኀይል ፡ ከቀድሞው ፡ ቀነሰው ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ አሁንም ፡ ይኸው ፡ መንግሥት ፡ ከገናንነቱ ፡ አልተዋረደም ። በዚህም ፡ ላይ ፡ የኤስፓኝ ፡ ነገሥታት ፡ በካ ቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ ፍቅር ፡ የተቃጠሉ ፡ የሮማን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳቱን ፡ በጣም ፡ የሚያከብሩ ፡ ነበሩ ። የሮማ ፡ ጳጳሳትም ፡ ከነልዩንና ፡ ከነጎርጎ ርዮስ ፡ ትልቁ ፡ ዠምሮ ፡ በኤውሮፓ ፡ የካቶሊክ ፡ ነገሥታት ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ እስከ ፡ መሸም ፡ እስከ ፡ መሻር ፡ እየደረሱ ፡ ክብርና ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ የኤስፓኝ ፡ ነገሥታት ፡ በራሳቸውም ፡ ሥራ ፡ በሊቃነ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ድጋፍ ፡ ገናናነታቸውን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ነበር ። ዐፄ ፡ ሱስንዮ ስም ፡ ወደ ፡ ኤስፓኝ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ፊልጶስ ፡ ፫ኛና ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ወደ ፡ ጳውሎስ ፡ ፭ኛ ፡ ደብዳቤ ፡ ልከው ፡ ዝምድና ፡ ለመመሥረትና ፡ ርዳታ ፡ ለማግኘት ፡ ያሰቡት ፡ የንጉሡንና ፡ የጳጳሱን ፡ ተሰባበሪነት ፡ በዓለምም ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ መፈ ራት ፡ በፔር ፡ ፖኤዝ ፡ አመልካችነት ፡ ከተረዱት ፡ በኋላ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፱ ።

### ሐሰተኛው ፡ ያዕቆብና ፡ አርዘ ፤ -በካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ ምክንያት ፡የተነሣው፡ ጦርነት።

ነገሥታት ፡ በሚገዙበት ፡ ጊዜ ፡ በውስጣቸው ፡ አንዳንድ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ እንደሚገኝ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይኸም ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ በንጉሡ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ በእንደራሴነት ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ ባነሰ ፡ ሥልጣን ፡ ይኖራል ፤ ሲመቸውም ፡ ዙፋን ፡ ለመነቅነቅ ፡ አይመለስም ። በዚሁ ፡ አያያዝ ፡ አሁን ፡ ትዝ ፡ የሚለን ፡ ራስ ፡ ዘሥላሴ ፡ የሚባለው ፡ ነው ።

ራስ ፡ ዘሥላሴ ፡ ከዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ እየታሰረ ፡ በሌላውም ፡ ጊዜ ፡ በከበሬታ ፡ የነበረ ፡ ሰው ፡ ነው ። በመካከሉም ፡ ሕዝቡና ፡ መኳንንቱ ፡ የነጋሢነት ፡ ዘር ፡ የለህም ፡ እያለ ፡ ባያውከው ፡ እንደርሱ ፡ አሳብ ፡ ለመንገሥም ፡ ያሰበበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። አሁንም ፡ በዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ባለፈው ፡ ጥፋቱ ፡ ይቅርታ ፡ ተደርጎለት ፡ ሲኖር ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንደሚባለው ፡ በመጠጥ ፡ ምክንያት ፡ ሰክሮ ፡ «ያዕቆብንና ፡ ዘድንግልን ፡ ከዙፋን ፡ እንዳወረድኳቸው ፡ ሱስንዮስንም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሳላዋርደው ፡ አልቀርም» ፡ ብሎ ፡ ተናግሮ ፡ ኖሮ ፡ ይኸውም ፡ በንጉሡ ፡ ጆሮ ፡ ስለደረሰ ፡ ተይዞ፡ በአምባ ፡ ኡሬ ፡ ታሰረ ። ከዚያም ፡ አመለጠና ፡ ከሽፍቶች ፡ ጋራ ፡ ተደባልቆ ፡ ጐጃምን ፡ ይዘርፍ ፡ ዠመር ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ ለንጉሡ ፡ ታማኝ ፡ የሆኑ ፡ ጋሎች፡ በጫካ ፡ አድፍጠው ፡ ገደሉትና ፡ ራሱን ፡ ቈርጠው ፡ ለንጉሡ ፡ ላኩላቸውና ፡ የሕይወቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ሆነ ።

※ ※ ※

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ የመጠሪያ ፡ ስሙ ፡ ዐምዶ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ፊቱን፡ በጦርነት ፡ እንደ ፡ ቆሰለ ፡ ሰው ፡ ተሸፋፍኖ ፡ ሄዶ ፡ ለደብረ ፡ ቢዘን መነኰሳት፡ እኔ ፡ ንጉሥ ፡ ያዕቆብ ፡ ነኝ ፤ ከሱስንዮስ ፡ በተዋጋሁበት ፡ ቀን ፡ ከሞት ፡ እግዚአብሔር ፡ በተአምራት ፡ አድኖኝ ፡ እናንተ ፡ አባቶቼ ፡ ዘንድ ፡ ለመድረስ ፡ አበቃኝ፡ ብሎ ፡ ነገራቸው ። መነኰሳቱም ፡ የሚናገሩት ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ተደማጭነት ፡ ስላለው ፡ በነሱ ፡ ስብከት ፡ ይህ ፡ መንግሥትን ፡ ይይዛል ፡ እያለ ፡ ተስፋ ፡ ያደረገ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ገብቶለት ፡ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ በስሜን ፡ ግዛት አስቸግሮ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ትግሬን ፡ የሚገዛው ፡ ሣህለ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚባለው ፡ የንጉሡ ፡ ወንድም ፡ ተዋግቶ ፡ አሸነፈውና በአምባ ፡ ላይ ፡ አሰረው ። በኋላም ፡ ከዚያ ፡ አምልጦ ፡ ወደ ፡ ሐማሴን ፡ ሄዶ ፡ በኋላም ፡ ንጉሡና ፡ ሣህለ ፡ ክርስቶስ ፡ መረዋ ፡ ከሚባሉት ፡ ጋሎች ፡ ጋራ ፡ በሚዋጉበት ፡ ጊዜ ፡ ይኸው ፡ ሐሰተኛው ፡ ያዕቆብ፡ ሽሬ ፡ ድረስ ፡ መጥቶ ፡ አገር ፡ ዘርፎ ፡ ሲመለስ ፤ በትግሬ ፡ ያገር ፡ ጠባቂው ፡ (የሹሙ) ፡ አሽከሮች ፡ አግኝተው ፡ ገደሉት ። ይህም ሰው ፡ የግብጽ ፡ ተወላጅ ፡ ነው ፡ ይባላል ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ በግራም ፡ በቀኝም ፡ ያለው ፡ አገር ፡ ለጊዜው ፡ ረግቶ ከተገዛላቸው ፡ በኋላ ፡ በሺሕ ፡ ፮፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የዘውድ ፡ በዓላቸውን ፡ ለማክበር ፡ ወደ ፡ አኵስም ፡ ሄደው ፡ አክብረው ፡ ተመለሱ ።

ከዘውድ ፡ በዓላቸውም ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ቃመው ፡ እቤት ፡ ውለው ፡ ነበርና ፤ ሞተዋል ፡ እየተባለ ፡ ተወራ ። መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ የሚባለው ፡ የወገራ ፡ ገዥ ፡ ከዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ዘር ፡ የተወለደውን ፡ አቤቶ ፡ አርዞን ፡ አነገሥና ፡ ሸፈተ ፤ መልከ ፡ ጼዴቅም ፡ እስከ ፡ ንጉሡ ፡ ሠፈር ፡ ድረስ ፡ እየመጣ ፡ ከወታደሮቹ ፡ አለቆች ፡ ከነሲናዳ ፡ እየተዋጋ ፡ ድል ፡ እያደረገ ፡ ያበርራቸው ፡ ዠመር ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ራስ ፡ የማነ ፡ ክርስቶስ ፡ (የንጉሡ ፡ ወንድም) ፡ መልከ ፡ ጼዴቅን ፡ አባሮ ፡ ያዘውና ፡ ከአቤቶ ፡ አርዞ ፡ ጋራ ፡ ተገደሉ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ጳጳስና ፡ ወደ ፡ ኤስፓኝ ፡ ንጉሥ ፡ ተልኮ ፡ የነበረው ፡ ፖኤዝ ፡ ሌሎችም ፡ ሰዎች ፡ ጨምሮ ፡ መልስ ፡ ይዞ ፡ ከኤውሮጳ ፡ መጣ ።

ንጉሡም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አቸፈር ፡ (አገው) ፡ ነበሩና ፡ መላክተኞቹ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በፍቅርና ፡ በከበሬታ ፡ ተቀበሏቸው ። እነሱም ፡ ከንጉሣቸውና ፡ ከጳጳሳቸው ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቍጥር ፡ በሺሕ ፡ ፮፻፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መጋቢት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ የተጻፈውን ፡ ደብዳቤ ፡ አስረከቡ ፡ የደብዳቤው ፡ ሙሉ ፡ ቃል ፡ አልተገኘም ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የፖርቱጊዝ ፡ መንግሥት ፡ ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ቃል ፡ ተቀብሎ ፡ ርዳታ ፡ ከላከላቸው ፡ በኋላ ፤ ልጃቸው ፡ ገላውዴዎስ ፡ ያባታቸውን ፡ ቃል ፡ ተቀብለው ፡ ስላልፈጸሙ ፡ አሁንም ፡ እርስዎ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የካቶሊክን ፡ ሃይማኖት ፡ ተቀብላ ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ የቤተ ክህነቱም ፡ ሃይማኖት ፡ ካቶሊክ ፡ መሆኑን ፡ በግልጽ ፡ ለማወቅ ፡ ካልተቻለ ፡ በደብዳቤ ፡ የጠየቁትን ፡ ጉዳይ ፡ ለመፈጸም ፡ ያዳግታል ። የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከተደረበ ፡ ግን ፡ ማናቸውንም ፡ ርዳታ ፡ እናደርጋለን ፡ የሚል ፡ መሆኑ ፡ ርግጠኛ ፡ ሳይሆን አይቀርም ።

ንጉሡም ፡ መልሱ ፡ ይህ ፡ መሆኑን ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ ይኸንኑ ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ደብዳቤ ፡ ጨምረው ፤ ፍቁረ ፡ እግዚእንና ፡ ከሚሲዮናውያኖቹ ፡ አንዱን ፡ አንቷን ፡ ፈርናንዲዝን ፡ መልሰው ፡ ላኳቸው ፡ ይባላል ። መልክተኞቹም ፡ በምጥዋና ፡ በዘይላ ፡ በኩል ፡ እንዳይሄዱ ፡ ቱርኮችን ፡ ስለ ፡ ፈሩ ፡ ቃቹን ፡ በደቡብ ፡ በእናሪያና ፡ በከምባታ ፡ በኩል ፡ ሄዱ ፤ ከዚያም ፡ አልፈው ፡ አላባ ፡ ሲደርሱ ፡ ባላባቱ ፡ አስሯቸው ፡ ሲኖር ፡ በኋላ ፡ ለቀቃቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እነርሱ ፡ ሄደው ፡ መልሱን ፡ ከማምጣታቸው ፡ በፊት ፡ ባገሩና ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተው ፡ አሳዛኝ ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ ደረሰ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱሳውያን ፡ የሚባሉት ፡ እነዚሁ ፡ ሚሲዮኖች ፡ የንጉሡን ፡ ልብ ፡ ስላገኙ ፡ በዋና ፡ በዋና ፡ መደባቸው ፡ በፍሬሞና ፡ (በትግሬ) ፡ በጐርጐራ ፡ (ደምቢያ) ፡ በሌላውም ፡ ከተማ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ልባቸው ፡ የካቶሊክን ፡ ሃይማኖት ፡ በየጉባኤው ፡ በየገበያው ፡ በየመኳንንቱም ፡ ቤት ፡ እየሰበኩ ፡ በካቶሊክነት ፡ ያጠምቁ ፡ ዠመር ። ይልቁንም ፡ ፖኤዝ ፡ የሚባለው ፡ ሚሲዮናዊ ፡ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ ዠምሮ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በመቀመጡ ፡ አማርኛና ፡ ግዕዝ ፡ ከማወቁ ፡ በላይ ፡ ለንጉሡ ፡

ባለሚል ፡ ሆኖ ፡ ይወጣ ፡ ይገባ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ የሱ ፡ ስብከት ፡ ከሌሎቹ ፡ ይበልጥ ፡ ይሠራ ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለኦርቶዶክሳዊ ፡ ሃይማኖት ፡ የተቈረቈሩትና ፡ በሹመት ፡ ምክንያትም ፡ ቀድሞ ፡ የተቀየሙት ፡ መኳንንቶች ፡ ሕዝቡንና ፡ ካህናቱን ፡ እያሳደሙ ፡ ንጉሡ ፡ ካቶሊክ ፡ ሆነዋል ፤ ለክርስቶስም ፡ ሁለት ፡ ባሕርይ ፡ አለው ፡ ብለው ፡ በአዋጅ ፡ አናግረዋል ፡ እያሉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እያወሩ ፡ ለመሸፈት ፡ አቄበቄቡ ።

በንጉሡና ፡ እርሳቸውን ፡ በተከተሉ ፡ መኳንንት ፡ በነአዛዥ ፡ ጢኖ ፡ (ተክለ፡ ሥላሴ) ፡ በወንድማቸው ፡ በራስ ፡ ሣህለ ፡ ክርስቶስ ፡ መሪነት ፡ ቀድሞውኑ ፡ የነበረው ፤ የሚሲዮኖቹ ፡ መሪ ፡ እላይ ፡ ስሙን ፡ የጠራነው ፡ ፔር ፖኤዝ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ከሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ዘንድ ፡ ፓትሪያርክ ፡ ተብሎ ፡ ከ፲፰ ፡ ሚሲዮናውያን ፡ ጋራ ፡ የመጣው ፡ ሜንዴዝ ፡ አልፎንሱ ፡ ያዲሱ ፡ ሃይማኖት ፡ መሪ ፡ ሆነው ፡ የቀረቡትውን ፡ በካቶሊክነት ፡ ሲያጠምቁ ፡ አዲስ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ ሲያበጁ ፤ የቀድሞውን ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ሃይማኖት ፡ ለመከላከል ፡ በየጊዜውና ፡ በየሥፍራው ፡ የተነሡት ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ።

እነዚህም ፡ ግብጻዊው ፡ ጳጳስ ፡ አቡነ ፡ ስምዖን ፡ የታወቁት ፡ መምህር ፡ አባ ፡ ዲዮስቆሮስ ፤ ከመኳንንት ፡ የዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ወንድም ፡ ራስ ፡ የማነ ፡ ክርስቶስ ፡ የልጃቸው ፡ የወይዘሮ ፡ መለኮታዊት ፡ ባል ፡ ራስ ፡ ዩልዮስ ፡ ዮናኤል ፡ የዳሞት ፡ ገዥ ፡ ጌዴዎን ፡ የፈላሾች ፡ ባላባት ፡ አቤቶ ፡ የማነ ፡ አብ ፡ አቤቶ ፡ መልከ ፡ ክርስቶስ ፡ አቤቶ ፡ ዘመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (የሚቹ ፡ የአቤቶ ፡ አርዞ ፡ ልጅ) ፡ ናቸው ።

ሌሎችም ፡ ብዙ ፡ ቀሳውስትና ፡ ካህናት ፡ ስለ ፡ ሃይማኖታችን ፡ እንሞታለን ፡ እያሉ ፡ ባንድነት ፡ ዐድመው ፡ በዐፄ ሱስንዮስ ፡ ላይ ፡ ሸፈቱ ። መሸፈታቸውም ፡ በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ይዘው ፡ እነዚህኑ ፡ ለመውጋት ፡ ከደንቀዝ ፡ ወደ ፡ ጸዳ ፡ ሄደው ፡ ተሰለፉ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ጳጳሱ ፡ አቡነ ፡ ስምዖን ፡ ንጉሡ ፡ ሱስንዮስ ፡ የእስክንድርያን ፡ ኦርቶዶክሳዊትና ፡ ያባታችንን ፡ የማርቆስን ፡ ሃይማኖት ፡ ለውጠው ፡ ወደ ፡ ካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ ገብተዋልና ፤ እሳቸውን ፡ ተከትሎ ፡ የወጋን ፡ ውጉዝ ፡ ከመ ፡ አርዮስ ፡ ብለው ፡ ገዘቱ ። ንጉሡንም ፡ አስቀድሞ ፡ ገዝተዋቸው ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ግዝቱ ፡ ጦርነቱን ፡ ለማቆም ፡ አልቻለምና ፤ ከወዲህ ፡ ከንጉሡ ፡ ወታደር ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ሚሲዮኖችና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ተጨምረው ፤ ከወዲያም ፡ ጳጳሱና ፡ ቀሳውስቱ ፡ ሆነው ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ እየተዋጉ ፡ ወታደሩንም ፡ ያዋጉ ፡ ጀመር ። በጦርነቱም ፡ ውስጥ ፡ አዝማች ፡ የነበሩት ፡ ዋናው ፡ ዩልዮስና ፡ አባ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ከብዙ ፡ ወታደርና ፡ ካህናት ፡ ጋራ ፡ በጥይትና ፡ በጦር ፡ ተመተው ፡ ወደቁ ። ጳጳሱም ፡ አቡነ ፡ ስምዖን ፡ እንደ ፡ ሹመት ፡ አባታቸው ፡ እንደ ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ መስቀላቸውን ፡ በእጃቸው ፡ ጨብጠው ፡ አይዞችሁ ፡ ለሃይማኖታችሁ ፡ ብትሞቱ ፡ ሰማዕትነት ፡ ትቀበላላችሁ ፡ እያሉ ፡ እያደፋፈሩ ፡ እጦርነቱ ፡ መካከል ፡ ገብተው ፡ ሲዋጉ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡

ያልታወቀ ፡ ወታደር ፡ በጦር ፡ ወግቶ ፡ ገደላቸውና ፡ ንጉሥ ፡ ዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ድል ፡ አደረጉ ። ራስ ፡ የማነ ፡ ክርስቶስና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የተማረኩት ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ በዚያው ፡ አውራጃ ፡ እንዲታሰሩ ፡ ተፈረደባቸው ። ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ በያለበት ፡ ጋሎችም ፡ አማሮችም ፡ በስሜንም ፡ በዳሞትም ፡ በየጁም ፡ ቢሸፍቱ ፡ ኀይልም ፡ ዕድልም ፡ የሚያልቀው ፡ ከዘመን ፡ ጋራ ፡ በመሆኑ ፡ ርሳቸውም ፡ እግዚአብሔር ፡ የወሰነላቸው ፡ ጊዜ ፡ አላለቀም ፡ ነበርና ፤ ሰውም ፡ እየላኩ ፡ ራሳቸውም ፡ እየሄዱ ፡ ሁሉንም ፡ ለጊዜው ፡ ድል ፡ እያደረጉ ፡ በደስታ ፡ ተመለሱ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቤተ ፡ ሰቦቻቸውን ፡ አስከትለው ፡ በሚሲዮናዊው ፡ በፔር ፡ ፖኤዝ ፡ እጅ ፡ ተጠምቀው ፡ ካቶሊክነታቸውን ፡ በገሃድ ፡ አስታወቁ ። በዚህም ፡ ቀን ፡ ምሳሌያቸውን ፡ እየተከተሉ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችና ፡ ቤተ ፡ ሰቦቻቸው ፡ ወንድማቸው ፡ ራስ ፡ ሥዕለ ፡ ክርስቶስም ፡ በካቶሊክነት ፡ ተጠመቁ ።

በእስክንድርያ ፡ ሃይማኖት ፡ የተጠመቃችሁ ፡ ሁሉ ፡ በሮም ፡ ሃይማኖት ፡ ተጠመቁ ፡ ሥርዐተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑና ፡ በዓል ፡ አከባበሩም ፡ እንደ ፡ ሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሁን ፡ የሚል ፡ ትእዛዝም ፡ አወጡ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ በትግሬ ፡ በላስታ ፡ በበጌምድር ፡ በጐጃም ፡ ያሉ ፡ ሊቃውንት ፡ ደንቀዝ ፡ እየመጡ ፡ ሰማዕትነት ፡ አያምልጥኽ ፡ እየተባባሉ ፡ ፓትርያርክ ፡ ተብሎ ፡ ከሮማ ፡ ጳጳስ ፡ በተላከው ፡ በሜንዴዝ ፡ አልፎንሱ ፡ ትእዛዝ ፡ ተደብድበው ፡ ሞቱ ፡ ይባላል ። በዚሁ ፡ አያያዝ ፡ አባ ፡ እፌ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚባሉ ፡ ስለ ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ በጥብቅ ፡ ይከራከሩ ፡ የነበሩት ፡ መላሳቸው ፡ በንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ ተቆረጠ ፡ ይባላል ።

ዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ከሺሕ ፡ ፻፰ ፡ ዓመት ፡ ይበልጥ ፡ ዠምሮ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነገሥታትና ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ጸንቶ ፡ የኖረውን ፡ የኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖትን ፡ ለውጠው ፡ ወደ ፡ ካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ የዞሩበትና ፡ ሕዝቡም ፡ እንዲከተላቸው ፡ በጠርነት ፡ ለማስገደድ ፡ የሞከሩበት ፡ ምክንያት ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ለመረዳት ፡ ለአንባቢ ፡ ሳይቸግረው ፡ አይቀርም ፤ ቢሆንም ፡ የጊዜውን ፡ ያገሩን ፡ የውጭና ፡ የውስጥ ፡ ታሪክ ፡ ስንመለከተው ፡ የምክንያቱ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ነገሮች ፡ እነዚህ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በ፫ ፡ ክፍል ፡ የጠቀስናቸው ፡ መስለው ፡ ይታያሉ ።

፩ኛ ፡ ከዐፄ ፡ ያዕቆብ ፡ በተዋጉበት ፡ ቀን ፡ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡ በወታደራቸው ፡ እጅ ፡ በመሞታቸው ፡ ከዚያ ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ በዐፄ ፡ ሱስንዮስና ፡ ዐላዊ ፡ ንጉሥ ፡ እያለ ፡ በሚያማቸው ፡ በቤተ ፡ ክህነት ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ቂሙ ፡ ስላልተፋቀ ።

፪ኛ ፤ ክርስቶስ ፡ ባምላክነቱ ፡ ሙታንን ፡ አነሣ ፤ ለምጽን ፡ አነጻ ፤ ውሃን ፡ ወይን ፡ አደረገ ፤ በሰውነቱ ፡ ግን ፡ ተራበ ፤ ተጠማ ፤ በተሰቀለም ፡ ቀን ፡ ከጻዕር ፡ የተነሣ ፡ አምላኬ ፡ አምላኬ ፡ ለምን ፡ ተውኸኝ ፡ ብሎ ፡ አለቀሰ ። ስለዚህ ክርስቶስ ሰውነታዊና ፡ አምላካዊ ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ የተለያዩ ፡ ባሕርያት ፡ አሉት ፡ እያሉ ፡ እነ ፡ ፖኤዝ ፡ እነ ፡ አልፎልንሱ ፡ ስለ ፡ ነገሯቸው ፡ በነርሱ ፡ ስብከት ፡ ከልባቸው ፡ ተረትው ፡ ይሆናል ።

ሮኛ ፤ በስሜን ፡ ፈላሾች ፤ በዳሞትና ፡ በጐጃም ፡ ጋሎች ፤ በሐማሴን ፡ ቱር ኮች ፤ በሌላውም ፡ ሥፍራ ፡ የሚነሣባቸውን ፡ የውስጥ ፡ ጠላታቻቸውን ፡ የሚያጠቁ በት ፡ ወታደርና ፡ መሣሪያ ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ግራኝን ፡ ለመጣል ፡ በቻሉበት ፡ መንገድ ፡ በጊዜው ፡ ከገነነው ፡ ከኤስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ ርዳታ ፡ ማግኘት ፡ ስላስ ፈለጋቸው ፡ ይኸንንም ፡ ፈትነው ፡ ከርዳታው ፡ በፊት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ወደ ፡ ካቶሊክ ፡ መለወጢን ፡ በግልጽ ፡ አስቀደመን ፡ ካላወቅን ፡ ለመ ላክ ፡ አይቻልም ፡ ስላሏቸው ፡ ርዳታውን ፡ ለማግኘት ፡ ይሆናል ።

በዚህም ፡ እላይ ፡ በተባለው ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ካቶሊክ ፡ መሆናቸውን ፡ በግልጽ ፡ ባስታወቁበት ፡ ቀን ፡ ይቅርና ፡ በዚህ ፡ ሃይማኖት ፡ እንኳን ፡ ቢጠረጠሩ ፡ ሕዝቡ ፡ እንደሚሸፍት ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ የጠየቁት ፡ ርዳታ ፡ አስቀድሞ ፡ በእጃቸው ፡ ሳይገባ ፡ በገሃድ ፡ በካቶሊክነት ፡ የራሳቸወ ና ፡ የቤተ ፡ ሰባቸው ፡ መለወጥ ፡ አንሶ ፡ ሕዝቡንና ፡ ካህናቱን ፡ በግድ ፡ ካቶሊክ ፡ እንዲሆኑ ፡ ቀድሞ ፡ በኦርቶዶክስነት ፡ የተጠመቁት ፡ በቂ ፡ አይደለምና ፤ እንደገና ፡ በካቶሊኮቹ ፡ ቄሶች ፡ እጅ ፡ እንዲጠመቁ ፡ ዐርብና ፡ ረቡም ፡ መጾሙ ፡ ቀርቶ ፡ ቅዳሜ ፡ እንዲጾም ፡ የቅዳሜ ፡ ሰንበትነትም ፡ እንዲሻር ፡ የቅዳሴውም ፡ የማኅሌ ቱም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተለውጦ ፡ በ፩ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ካቶሊክ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲ ሆን ፡ ትእዛዛቸውን ፡ በዋጅ ፡ አወጡ ። ዐዋጁንም ፡ የፈራ ፡ ሲፈጽም ፡ ለቄየው ፡ ሃይማኖት ፡ ቀናተኛ ፡ የሆነው ፡ የቤተ ፡ መንግሥትና ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ወገን ፡ እንቢ ፡ ብሎ ፡ ሲዋጋ ፡ ሲማረክ ፡ ሲቀጣ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ቈየ ።

በአገው ፤ በጐጃም ፤ በትግሬ ፤ በሸዋ ፤ ገሚሶቹ ፡ ይኸንኑ ፡ የቆየ ፡ ሃይማኖት ፡ ለመከላከል ፡ የቀረውም ፡ ከብትና ፡ ገንዘብ ፡ ለመዝረፍ ፡ ፈላሾቹም ፡ ነፃ ፡ ለመሆን ፡ በየመሪዎቻቸው ፡ ተነሡና ፡ ከሺሕ ፡ ፮፻፲፩ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፮፻፲፫ ፡ ዓ፡ ም ድረስ ፡ ባገሩ ፡ ዘረፋና ፡ እልቂት ፡ ሆነ ። ንጉሡም ፡ ወታደሮቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ሽቅ ብና ፡ ቍልቍል ፡ እየሮጡ ፡ ሲዋጉ ፡ ሲያዋጉ ፡ ትርፉ ፡ ከወዲያም ፡ ከወዲህም ፡ ያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ማለቁ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ እየሆኑ ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ድል ፡ ቢያደርጉ ፡ የሃይማኖቱ ፡ ጦርነት ፡ ሊቆምና ፡ አገሩ ፡ ሰላም ፡ ሊሆን ፡ አልቻለም ።

## የዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡

## ምዕራፍ ፡ ፴ ።

### ፋሲል ፡ ይነግሥ ፤ ሃይማኖት ፡ ይመለስ ፡ የዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ዕረፍት ፤—አልፎ ንሱና ፡ ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ።

በዚህ ፡ በሃይማኖት ፡ ጦርነት ፡ ምክንያት ፡ አገሩ ፡ ታውኮ ፡ ሳለ ፡ በሺሕ ፡ ፮፻፲፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ልጃቸው ፡ ማርቆስና ፡ ሴት ፡ ልጃቸው ፡ ወይዘሮ ፡ መለኮታዊት ፡ በዚሁ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱም ፡ ተከታትለው ፡ ስለሞቱ «ካቶሊክ ፡ ከመሆና ቸው ፡ የተነሣ ፡ እግዚአብሔር ፡ መዓት ፡ አወረደባቸው» ፡ እየተባለ ፡ ተወራባቸው ።

ፋሲል ፡ (ፋሲለደስ) ፡ የሚባሉት ፡ ልጃቸው ፡ በዚህ ፡ በሃይማኖት ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ተቸግረው ፡ ነበር ፤ ምንም ፡ እንኳን ፡ ከባታቸው ፡ ጋራ ፡ እየሆኑ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ የሸፈቱትን ፡ ሰዎች ፡ ቢወጉ ፡ ከጦርነቱ ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሲገቡ ፡ ግን ፡ የሞቱትን ፡ ሰዎች ፡ ሬሳና ፡ ቍስለኛ ፡ እያሰበሰቡ ፡ ያባቶቻችንን ፡ ሃይማኖት ፡ በመለወጥዎ ፡ ምክንያት ፡ ለምን ፡ የገዛ ፡ ሕዝብዎን ፡ እርስ፡ በርሱ ፡ ያስተላልቍታል ፡ እያሉ ፡ ከባታቸው ፡ ጋራ ፡ ይጨቃጨቁ ፡ ነበር ። አሁንም ፡ ተመልሻለሁ ፡ ይበሉ ፡ ሕዝቡም ፡ ወደ ፡ ጥንት ፡ ሃይማኖቱ ፡ እንዲመለስ ፡ ዐዋጅ ፡ ያድርጉለት ፡ እያሉ ፡ ያባብሏቸው ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በመጨረሻም ፡ በነገሡ ፡ በ፳፯ኛው ፡ ዓመት ፡ ዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ቃመው ፡ አንደበታቸው ፡ ተዘጋ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥታቸው ፡ እንደሚለው ፡ ልጃቸው ፡ ፋሲል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ መዓት ፡ ያመጣባቸው ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ቢለውጡ ፡ ይሆናል ፡ ሲሉ፡ በየገዳማቱና ፡ በየአድባራቱ ፡ በጸሎታችሁና ፡ በኀዘናችሁ ፡ አባቴን ፡ አድኑልኝ ፡ እኔም ፡ ያላችሁኝን ፡ አደርጋለሁ ፡ እያሉ ፡ ብዙ ፡ መባእ ፡ ላኩ ፡ አባ ፡ ዓምደ ፡ ሥላሴ ፡ የሚባሉ ፡ ከሸዋ ፡ ሄደው ፡ መተማ ፡ አጠገብ ፡ ከበረሓው ፡ የማኅበረ ፡ ሥላሴን ፡ ገዳም ፡ አዲስ ፡ ቈርቍረው ፡ በበረሓ ፡ የሚኖሩ ፡ የበቁ ፡ መነኰሴ ፡ ነበሩ ። እርሳቸውም ፡ ለቈረቈርሁት ፡ ገዳም ፡ ፵፬ ፡ ጕልት ፡ ልትሰጠኝ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ግባልኝና ፡ አባትኽን ፡ እኔ ፡ እፈውሳለሁ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ አቤቶ ፡ ፋሲል ፡ ላኩ ። አቤቶ ፡ ፋሲልም ፡ እሺ ፡ ያሉኝን ፡ አደርጋለሁና ፡ መጥተው ፡ አባቴን ፡ ይፈውሱልኝ ፡ ብለው ፡ መልሰው ፡ ላኩ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አባ ፡ ዓምደ ፡ ሥላሴ ፡ ከገዳማቸው ፡ ተነሥተው ፡ መነኰሳትን ፡ አስከትለው ፡ ደንቀዝ ፡ ሄዱ ። በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ አቤቶ ፡ ፋሲል ፡ በክብር ፡ ተቀብለው፡ በመልክት ፡ የተነጋገሩትን ፡ በቃል ፡ አጽድቀው ፡ አባ ፡ ዓምደ ፡ ሥላሴም ፡ መነኰሳትን ፡ ጨምረው ፤ ፫ ፡ ሱባኤ ፡ ቀን ፡ በጸሎት ፤ ሌሊት ፡ በሰዓታት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለምነው ፡ አጥምቀው ፡ ስላቈረቧቸው ፡ ዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ የተዘጋ ፡ አንደበታቸው ፡ ተከፈተና ፡ የእስክንድርያ ፡ ሃይማኖት ፡ ትመለስ ፡ የሮም ፡ ሃይማኖት ፡ ትርከስ ፡ ፋሲል ፡ ይንገሥ ፡ ብለኽ ፡ ዐዋጅ ፡ አናግር ፡ ብለው ፡ ለልጃቸው ፡ ለአቤቶ ፡ ፋሲል ፡ ተናገሩ ፡ ይባላል ። እርሳቸው ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖት ፡ ተመልሰው ፡ ወይም ፡ በካቶሊክነት ፡ ጸንተው ፡ ይሙቱ ፡ የልባቸው ፡ አልታወቀም ። ከታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ካቶሊክነት ፡ ያለው ፡ በዚያው ፡ በካቶሊክነታቸው ፡ ጸንተው ፡ ሞቱ ፡ ሲል ፤ ኦርቶዶክስነት ፡ ያለው ፡ ግን ፡ ንስሓ ፡ ገብተው ፡ ወደ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተመልሰው ፡ ሞቱ ፡ ሲል ፡ ይገኛል ።

ይህም ፡ ዐዋጅ ፡ ተነግሮ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በየዋሻው ፡ በየበረሓው ፡ የተሰደዱት ፡ ሊቃውንትና ፡ መነኰሳት ፡ መጻሕፍቶቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደየቤታቸው ፡ ተመለሱ ፡ ይባላል ።

አባ ፡ ዓምደ ፡ ሥላሴም ፡ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ከጣቀሱ ፡ ፵፬ ፡ ጕልት ፡ ስለ ፡ ሰጧቸው ፡ ተመልሰው ፡ ማኅበረ ፡ ሥላሴን ፡ ገዳማቸውን ፡ አቀኑ ። ማኅበረ ፡ ሥላሴም

የተባለው ፡ የአባ ፡ ዓምደ ፡ ሥላሴ ፡ ገዳም ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ዐፄ ፡ ሱስንዮስም ፡ በነገሡ ፡ በ፳፫ ፡ ዓመታቸው ፡ በሺሕ ፡ ፮፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ ስላረፉ ፡ ልጃቸው ፡ ፋሲል ፡ ነገሡ ፡ ስመ ፡ መንግሥታቸውም ፡ (ዓለም ፡ ሰገድ) ፡ ተባለ ። ሕዝቡም ፡ ካህናቱም ፡ ባባታቸው ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ መለወጥ ፡ ውስጡን ፡ መቈርቈራቸውን ፡ ያውቅ ፡ ነበርና ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ንግሣቸውን ፡ በደስታ ፡ ተቀበለው ።

፨ ፨ ፨

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሊቃውንቱ ፡ በዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ መሪነት ፡ ፳፱ ፡ ምእመናን ፡ በከንቱ ፡ ደማቸው ፡ ፈሷልና ፡ ከሮማዊው ፡ ጳጳስ ፡ ከአልፎንሱ ፡ ጋራ ፡ ተከራክረን ፡ ደማቸውን ፡ እንበቀላለንና ፤ ለጉባኤው ፡ ዐዋጅ ፡ ይነገርልን ፡ ብለው ፡ ለዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ቢነግሯቸው ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ዐዋጅ ፡ አናገሩላቸው ፤ ሊቃውንቱም ፡ ከያገሩ ፡ ተሰበሰበና ፡ ጐንደር ፡ ላይ ፡ ጉባኤ ፡ ተደረገ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የተማሩ ፡ ሊቅ ፡ ነበሩና ፡ ለሊቃውንቱ ፡ አፈ ፡ ጉባኤ ፡ ሆነው ፡ ቆሙ ። ሜንዶዝ ፡ አልፎንሱም ፡ ወንጌቹን ፡ እነ ፡ ፖኤዝን ፡ ይዞ ፡ ቆመ ። በመጀመሪያ ፡ አልፎንሱ ፡ ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስን ፡ «የአብ ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ታሞ ፡ ሞቶ ፡ ዓለምን ፡ አዳነ» ። የሚል ፡ ንባብ ፡ ከብሉይና ፡ ከሐዲስ ፡ ማስረጃ ፡ ስጡኝ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። ዕጨጌም ፡ ጳውሎስ ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ በጻፈው ፡ መልክቱ ፡ ‹እግዚአብሔር ፡ ጠላቶቹ ፡ ስንሆን ፡ በልጁ ፡ ሞት ፡ አዳነን› ፡ ይልብኛል ፡ ቢሉት ፡ መልስ ፡ አጥቶ ፡ ዝም ፡ አለ ።

ቀጥሎም ፡ ማሸነፊያ ፡ ያገኘሁ ፡ መስሎት ፡ «የእግዚአብሔር ፡ ፊቱ ፡ ወዴት ፡ ነው» ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ በጉባኤው ፡ መብራት ፡ አስበርተው ፡ ‹የዚህ ፡ መብራት ፡ ፊቱ ፡ ወዴት ፡ ነው» ? እያሉ ፡ መልሰው ፡ ጠየቁት ፤ ለዚሁም ፡ መልስ ፡ አጣ ፤ ዕጨጌም ፡ የዚህ ፡ መብራት ፡ ፊት ፡ በዚህ ፡ ገጽ ፡ ነው ፡ እንደማይባል ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ባራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ረቱት ። ይልቁንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፊቱ ፡ ክፉ ፡ ወደሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ የዳዊትን ፡ ቃል ፡ ጠቅሰው ፡ ፊታቸውን ፡ ወደ ፡ አልፎንሱ ፡ አዙረው ፡ በጥፊ ፡ መቱት ፡ ይላል ። ከዚህ ፡ አያይዞ ፡ አንዱ ፡ ሊቅ ።

ወረከብናሁ ፡ ለበትር ፡ ዘያደክማ ፡ ለሮሜ ።
ጽኑብ ፡ በንባብ ፡ ወቅኑጸ ፡ በትርጓሜ (1) ።

ብሎ ፡ ቢቀኝ ፡ ሊቃውንቱ ፡ ንሴብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እያሉ ፡ በያሬድ ፡ ማኅሌት ፡ ባደባባይ ፡ አሸበሸቡ ፡ ሲል ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ይገልጻል ።

(1) ትርጓሜው ፡ የዕጨጌው ፡ ስማቸው ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ (የጊዮርጊስ ፡ በትር) ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ ሮሜን ፡ ያደከማት ፡ በትር ፡ በንባብ ፡ የተጸረበ ፡ በትርጓሜ ፡ የተቀረጸ ፡ ሆኖ ፡ አገኘነው ፡ ማለት ፡ ነው ።

ካገራችን ፡ ሊቃውንት ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ የተጻፈውን ፡ ስን መለከት ፡ አልፎንሱ ፡ ሜንደዝ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ራሱ ፡ የጻፈውን ፡ ተመልክ ተን ፡ በፍርድ ፡ መንገድ ፡ ሁለቱን ፡ ለማመዛዘን ፡ አልቻልንም ። ይሁን እንጂ ፡ በዚሁ ፡ በታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ እንጋገር ፡ ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ጠቅሰው ፡ ራሳቸውም ፡ በመብራት ፡ ያመጡት ፡ ምሳሌ ፡ የሊቅነት ፡ መንገድ ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጥቅስ ፡ በኋላ ፡ ያስከተሉት ፡ ጥሬ፡ ከወንጌል ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ በፍጹም ፡ አይስማማም ። በወንጌል ፡ ጌታችን ፡ ለሐዋ ርያት ፡ ሲያስተምር ፡ ያላመናችሁን ፡ በጥፊ ፡ በትር ፡ አሰምኑት ፡ አላለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እናንተን ፡ አስተማሪዎቼን ፡ ሰው ፡ አንደኛውን ፡ ጉንጫችሁን ፡ ቢመታ ችሁ ፡ ሌላውን ፡ አዙራችሁ ፡ ስጡት ፤ ክፉ ፡ ለሚያደርግባችሁ ፡ ደኅንነት ፤ ጸልዩ ፤ የሚጠሏችሁን ፡ ውደዱ ፡ የሚወዷችሁን ፡ ከወደዳችሁ ፤ የሚጠሏችሁን፡ ከጠላችሁ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አላችሁ ፤ ይኸንንማ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ይሠሩት ፡ የለ ምን ?፡ ብሏል ። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ፈንታ ፡ ሜንደዝ ፡ አልፎንሱም ፡ በዐፄ ፡ ሱስ ንዮስ ፡ ጊዜ ፤ ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ባሁኑ ፡ በዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ጊዜ ፤ የበ ትር ፤ ደም ፡ የማፍሰስ ፤ የበቀል ፡ ሥራ ፡ ሊሠሩ ፡ ባልተገባቸውም ፡ ነበር ። ዕጨጌም ፡ ለጥፊው ፡ በትር ፡ ያመጡት ፡ የብሉይ ፡ (የዳዊት) ፡ ጥቅስ ፡ በሐዲስ፡ (በወንጌል) ፡ ትእዛዝ ፡ ሊለወጥ ፡ ይገባው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የካህን ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡ መሃይምን ፡ ደካማ ፡ በመሆኑ ፡ መንፈሳዊውን ፡ ትእዛዝ ፡ መፈጸም ፡ ስለሚያውከው ፤ ዕጨጌም ፡ ፊታቸውን ፡ ለመቺ ፡ በመስጠት ፡ ፈንታ ፡ የሰው ፡ ፊት ፡ በጥፊ ፡ ለመምታት ፡ ተገደዱ ። እንዲያውም ፡ ዕጨጌው ፡ ጥፊ ፡ ሳይ በቃ ፡ ቀርቶ ፡ «ዐፄ ፡ ሆይ ፡ አልፎንሱ ፡ ያስገደላቸውን ፡ የምእመናኑን ፡ ደም ፡ እበቀላለሁና ፡ ይስጡኝ ፡ ላስደብድባቸው» ፡ ሲሉ ፡ ንጉሡን ፡ ለመኑዋቸው ። ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ግን ፡ «የሞቱት ፡ የሰማዕትነት ፡ ዋጋ ፡ አግኝተዋል ፤ አሁን፡ የነዚህ ፡ ደም ፡ ቢፈስ ፡ ምንም ፡ አይጠቅማቸውም ። ደግሞም ፡ አባቴ ፡ ዐፄ፡ ሱስንዮስ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ምጥዋ ፡ ድረስ ፡ አሸኝተህ ፡ ወዳገሩ ፡ ስደድልኝ ፡ ብለው ፡ ተናዘዋልና ፡ አልችልም» ፡ ብለው ፡ መለሱላቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ በዚያ ፡ ወረዳ ፡ ያሉትን ፡ የውጭ ፡ አገር፡ ሚሲዮኖችንና ፡ ካቶሊኮችን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጠብ ፡ የተነሣው ፡ በናንተ ፡ ምክን ያት ፡ ነውና ፤ ይኸን ፡ ሥፍራ ፡ (በጌምድርን) ፡ ለቃችሁ ፡ ወደ ፍሬሞና ፡ (ትግሬ) እንድትሄዱ ፡ ይልቁንም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ከእስክንድርያ ፡ አዲስ ፡ ጳጳስ ፡ ስለሚ መጡ ፡ እርሳቸውም ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ባንድ ፡ ከተማ ፡ ለመቀመጥ ፡ አይፈልጉምና ፡ በጃችሁ ፡ ያለውን ፡ ብረትና ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ አስረክባችሁ ፡ በቶሎ ፡ እንድትነሡ ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ ለካቶሊኮቹ ፡ ዋና ፡ ቄስ ፡ ለሜንደዝ ፡ አልፎንሱ ፡ ላኩበት ፤ ሚሲዮኖቹም ፡ በዚሁ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ሊሄዱ ፡ ተነሡ ። እነሱንም ፡ የሚሸኙ ፡ ወንድማቸውን ፡ ገላውዴዎስን ፡ አደረጉላቸውና ፡ ወደ ፡ ፍሬሞና ፡ ሄዱ ። ፍሬሞና ፡ በትግሬ ፡ ውስጥ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የካቶሊኮቹ ፡ መደብ ፡ ነው ። ከፖርቱጊዞቹም ፡ ውስጥ ፡ ሲሞት ፡ የሚቀበረው ፡

በዚያው ነበር ፤ ከዚያም ፡ ሚሲዮኖቹ ፡ ወደ ፡ ምጥዋ ፡ እንዲሄዱ ፡ ታዘዙ ። ነገር ፡ ግን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ፡ እያበጁ ፡ ሳይሄዱ ፡ ለንጉሡ ፡ ገና ፡ ወዳል ተገዛው ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ዮሐንስ ፡ አካይ ፡ የሚጠብቀን ፡ ሰው ፡ ላክልንና ፡ ወዳንተ ፡ ለመምጣት ፡ እንፈልጋለን ፡ ብለው ፡ በስውር ፡ ላኩ ። እሱም ፡ በመልክት ፡ እተቃጠሩበት ፡ ሥፍራ ፡ ድረስ ፡ በቶሎ ፡ ተቀባይ ፡ ላከላቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሚሲዮናውያኖች ፡ ወደ ፡ ምጥዋ ፡ ለመሄድ ፡ እንፈልጋለን፡ ብለው ፡ ለንጉሡ ፡ በመልክት ፡ አመለከቱ ። እነሱም ፡ ይኸን ፡ ያደረጉበት ፡ ምክንያት ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ከደንቀዝ ፡ ከተማና ፡ ከንጉሡ ፡ሩቅ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ ለጊዜው ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ከንጉሡ ፡ ስምምነት ፡ የለውምና ፡ በግዛቱ ፡ ላይ ፡ አስቀምጦን ፡ ሥራችንንና ፡ ስብከታችንን ፡ እንደ ፡ ልባችን ፡ ለማስኬድ ፡ እንችላለን ፡ ብለው ፡ ነው ። ዐፄ ፡ ፋሲልም ፡ ውስጡን ፡ ከባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ዮሐንስ ፡ ጋራ ፡ መላላካቸውን ፡ ስላላወቁ ፡ በቀጥታ ፡ በምጥዋ ፡ በኩል ፡ አድርገው ፡ ወዳገራቸው ፡ የሚገቡ ፡ መስሏቸው ፡ ነበርና ፡ ጠባቂ ፡ ጨምረው ፡ ወደ ፡ ምጥዋ ፡ እንዲሄዱ ፡ አሰናበቷቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሚሲዮኖቹ ፡ ተጉዘው ፡ እቀጠሮው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ የባሕር ፡ ነጋሽን ፡ ሰዎች ፡ ባገኙ ፡ ጊዜ ፡ ከንጉሡ ፡ ሰዎች ፡ ዕጅ ፡ አምልጠው ፡ ወደነዚያ ፡ ተደባለቁ ፤ በኋላም ፡ ከባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ጋራ ፡ ተገናኙ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አብረው ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ ንጉሡ ፡ መልሰኽ ፡ ላክ ፡ ወይም ፡ ካገርህ ፡ አባር ፡ ብለው ፡ በትእዛዝ ፡ አስፈራርተውት ፡ ነበርና ፤ በንጉሡ ፡ ፍራቻ ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ ማስቀመጥ ፡ ትቶ ፡ ካገሩ ፡ አሥነሥቶ ፡ ወደ ፡ ምጥዋ ፡ ላካቸው ፤ በምጥዋም ፡ የቱርኮች ፡ ሹም ፡ ለጊዜው ፡ በመልክም ፡ ተቀብሏቸው ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ኃያላን ፡ ተፎካካሪ ፡ የነበሩት ፡ የቱርክና ፡ የኤስፓኝ ፡ መንግሥታት ፡ በምጥዋና ፡ በሌላውም ፡ ግዛት፡ እየተከራከሩ ፡ ጠበኞች ፡ ስለነበሩ ፡ ከምሲዮኖቹም ፡ ይበልጦቹ ፡ እስፓኞችና ፡ ፖርቱጊዞች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ሱአኪም ፡ ደሴት ፡ ወስዶ ፡ የያዙትን ፡ ዕቃ ፡ ነጥቆ ፡ አሠራቸው ። በመጨረሻም ፡ ፫ ፡ ሺሕ ፡ ፒያስትር ፡ (የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ገንዘብ ፡) አስከፍሎ ፡ ወደ ፡ ህንድ ፡ ላካቸው ፡ ይባላል ።

እንዲሔዱ ፡ ከታዘዙት ፡ ውስጥ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ፡ በመደበቅም ፡ ሁለት ፡ ሚሲዮናውያን ፡ ቀርተው ፡ ነበር ። ከነዚህ ፡ አንዱን ፡ ኑጊራ ፡ የተባለውን ፡ አንታቸው ፡ ራስ ፡ ሣህለ ፡ ክርስቶስ ፡ በቤቱ ፡ አስቀምጦት ፡ ሁለቱም ፡ ርኅታ ፡ ይላክልን ፡ እያሉ ፡ ከሮማ ፡ ጳጳስ ፡ ጋራ ፡ ሲላላኩ ፡ ስለ ፡ ተገኙ ፡ ተያዙና ፡ ርሱና ፡ ሚሲዮናዊው ፡ ተሰቀሉ ። አንደኛውንም ፡ በጣና ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ መነኮሳት ፡ አግኝተው ፡ ገደሉት ፡ ይባላል ።

የሚሲዮኖቹ ፡ ከበጌምድር ፡ ወደ ፡ ምጥዋ ፡ መሔድ ፤ የኩልበ ፡ የፔሩሾን ፡ የሳቤሊ ፡ የታሪክ ፡ መጻሕፍቶቻቸው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ዐይነት ፡ ሲተርኩ ፡ ያገራችን ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፤ አሳቡን ፡ ከነዚሁ ፡ ሳይለይ ፡ ባጭር ፡ መንገድ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ይገኛል ።

ዐፄ ፡ ፋሲለደስ ፡ (ዓለም ፡ ሰገድ ፡) አልፎንሱን ፡ በምጥዋ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ሐማሴን ፡ ብሰደዱት ፡ ጊዜ ፡ ሐማሴን ፡ ሲደርስ ፡ አመመኝ ፡ ብሎ ፡ ተኝቶ ፡ የቅ ባቶችንና ፡ የጸጎችን ፡ ሃይማኖት ፡ ከርሱ ፡ ሃይማኖት ፡ ጋራ ፡ አመሳስሎ ፡ «ክር ስቶስ ፡ በቅብዐተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከብሮ ፡ እንደኛ ፡ የጸጋ ፡ ልጅ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ የጸጋ ፡ ልጆችን ፡ ሃይማኖት ፡ በጕልህ ፡ አስተምሮ ፡ ጨረሰ ። አስተም ፡ ሮም ፡ በጨረሰ ፡ ጊዜ ፡ «ቅባትንና ፡ ጸጋን ፡ ሁለት ፡ እሾኽ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተከ ልሁባት» ፡ ብሎ ፡ ፎክሮ ፡ በምጥዋ ፡ በኩል ፡ ወዳገሩ ፡ ገባ ፡ ይባላል ፡

ነገር ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ ዘመን ፡ ሲቀዘቅዝ ፡ ባንድ ፡ ዘመን ፡ ሲገን ፡ የቈየ ውን ፡ ይህን ፡ የጸጋና ፡ የቅባት ፡ ሃይማኖት ፡ መሥራቹ ፡ አልፎንሱ ፡ መሆኑን ፤ የተመሠረተበትም ፡ ጊዜ ፡ ይኸው ፡ ዘመን ፡ መሆኑን ፡ አላረጋግጥም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ይኸንኑ ፡ አዲስ ፡ የጸጋ ፡ ትምህርት ፡ ለመንቀፍ ፡ ከተዋሕዶዎቹ ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ ሊቅ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ተቀኘ ።

ቃለ ፡ እምነ ፡ ሥጋ ፡
በአፍአ ፡ ፈለጡ ፡ ውሉደ ፡ ሮሜ ።
ዘንተኒ ፡ ልማደ ፡ ዘአፍአ ፤ ከመ ፡ ኢንግበር ፡ ልማደ ፡
ዋሕድና ፡ ክልኤቱ ፡ በታቦር ፡ ተግህደ ።
ዘሰገደሂ ፡ ለቃል ፡ እንዘ ፡ ይሬሲ ፡ አሐደ ፡
ለሥጋ ፡ ሰገደ ፡ ኀበ ፡ ሰገደ ።
ባዕደ ፡ አብ ፡ እስመ ፡ ኢወለደ ።
ወድንግል ፡ ኢወለደት ፡ ባዕደ ።

የቅኔ ፡ ትርጓሜ ።

የሮሜ ፡ ልጆች ፡ ቃልን ፡ ከሥጋ ፡ ለዩ ። ይህነን ፡ መለየት ፡ ልማድ ፡ እን ዳናደርግ ፡ የቃልና ፡ የሥጋ ፡ መዋሐድ ፡ አብ ፡ ይህ ፡ ልጄ ፡ ነው ፡ ባለው ፡ ምስክርነት ፡ ተገለጠ ። ቃልን ፡ ከሥጋ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ለቃል ፡ የሰገደ ፡ ለሥጋ ፡ መስገዱ ፡ ነው ። አብ ፡ ሌላን ፡ አልወለደምና ፤ ድንግልም ፡ ሌላን ፡ አልወለደችምና ፡ ያንኑ ፡ አንድ ፡ አካልን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የእጅ ፡ ሥራንና ፡ የንግድን ፡ ጕዳይ ፡ ከመነጋገር ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጕዳይ ፡ እንዳሁኑ ፡ ጊዜ ፡ አይጣጣሩም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የግራኝ ፡ ጦርነት ፡ የካቶ ሊኩን ፡ የፖርቱጋልን ፡ መንግሥት ፡ ርዳታ ፡ ሲስብ ፤ እንደዚሁ ፡ ይህ ፡ ርዳታ ፡ የካቶሊክነት ፡ ዋጋ ፡ አስጠየቀ ።

የሮማ ፡ ሊቀ ጳጳሳት ፡ በመንበረ ፡ ጴጥሮስ ፡ ተቀምጠው ፡ ቀሳውስቶቻቸ ውን ፡ ደግሞ ፡ በአሜሪካን ፡ በእስያ ፡ በአፍሪካ ፡ እየተዘዋወሩ ፡ የካቶሊክን ፡ ሃይማኖት ፡ እያስተማሩ ፡ የሮማ ፡ ካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንድትስፋፋ ፡

በያለበት ፡ ይልኩ ፡ ነበር ። የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትና ፡ የኤውሮፓ ፡ ነገሥታትም፡ በሃይማኖትም ፡ በግዛትም ፡ ሥራቸውና ፡ ስብከታቸው ፡ የተደገፈ ፡ በመሆኑ ፡ አንደኛው ፡ ለቤተ ፡ ክህነቱ ፣ ሁለተኛው ፡ ለቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ መስፋፊያ ፡ የሚሆነውን ፡ ጥቅም በኅብረት ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ። በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ቀድሞ ፡ የፖርቱጋል ፣ በኋላም ፡ የኤስፓኝ ፡ ነገሥታት ፡ ከሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ጋራ ኢትዮጵያን ፡ ወደ ፡ ካቶሊክነት ፡ ለውጦ ፡ የዚህ ፡ መለወጥ ፡ የሚሰጠውን ፡ የየክፍላቸውን ፡ የግዛት ፡ ድርሻ ፣ ለመካፈል ፡ ተስማምተው ፡ ነበር ፣ ነገሩም ፡ መገዠመሪያ ፡ በዐፄ ፡ ዘድንግል ፣ ፪ኛም ፡ በዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ይበልጥ ፡ ዘለቄታ ፡ አግኝቶ ፡ ፩ ሺሕ ፡ ፫፻ ፡ ዓመት ፡ የጸናችውን ፣ የእስክንድርያ ፡ ኦርቶዶክሳዊትን ፡ ሃይማኖት ፡ ሊገለብጥ ፡ ጥቂት ፡ ቀርቶት ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን በዴሞክራሲ ፡ መንፈስ ፣ መንግሥት ፡ ማለት ፡ ሕዝብ ፡ ማለት፡ ሲሆን ፡ በዲክታተርነት ፡ «መንግሥት ፡ ማለት ፡ እኔ ፡ ነኝ» ብሎ ፡ የፈረንሳዊ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፬ኛ ፡ ሉዊ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ሳይሆን ፡ ቀርቶ ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ሱስንዮስና ፡ ቤተ ፡ ሰቦቻቸው ፡ ምንም ፡ ካቶሊክነትን ፡ ቢቀበሉ ፡ ሌላውም ፡ ሕዝብ ፡ እንዲቀበል ፡ ባዋጅ ፡ ቢያዙ ፣ ዐዋጁንም ፡ የተቃወመውን ፡ በጦር ፡ ኀይል ፡ ለማሳመን ፡ ቢዋጉ ፡ ሕዝቡ ፡ የቈየውን ፡ ሃይማኖት ፡ ለማጽናት ፡ እንቢ፡ ብሎ ፡ የመጣውን ፡ ነገር ፡ በጥብቅ ፡ መከተ ። ስለዚህ ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የዠመረችው ፡ ዐላማ ፡ ወደ ፡ ግቡ ፡ ሳይደርስ ፡ ቀረና ፡ የነበረው ፡ ሃይማኖት ፡ ረጋ ። ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ መፍሰሱ ፡ ያሳዝናል ።

ዛሬ ፡ የአውሮፓ ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ለመሆን ፡ እንደሚመኙ ፡ እንደዚሁም ፡ ከመዠመሪያው ፡ ከሐዋርያት ፡ ጉባኤ ቀጥሎም ፡ ከሦስቱ ፡ ምእት፡ ወዲህ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በትርጓሜና ፡ በሥርዐት ፡ በመለያየት ፡ በመከራከር ፡ ፈንታ ፣ አንድ ፡ ለመሆን ፡ ቢጥሩ ፡ ኖሮ ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ይኸን ፡ ያኽል ፡ የክርስቲያን ፡ ደም ፡ አይፈስም ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ መንግሥታት ፡ እንደሚለያዩ ፣ የሰውም ፡ ጠባይና ፡ መልክ ፡ የልብ ፡ አስተያየትና ፡ የአእምሮ ፡ ዕውቀትም ፡ በተለያየበት ፡ መንገድ ፡ የሃይማኖት ፡ ነገርም ፡ በዚያው ፡ በኩል ፡ መለያየት ፡ ግድ ፡ ሆነበት ። አንድነት ፡ ለማድረግም ፡ ልበ ፡ ቅኖች ፡ ቢጥሩ ፡ ቅን ፡ አሳባቸው ፡ ሳይፈጸም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ቈየ ። ምናልባት ፡ ባለፈው ፡ የፈሰሰው ፡ ደም ፡ ትምህርት ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ ፊት፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በፍጹም ፡ ደም ፡ እንዳይፈስ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሪዎች ፡ ዘዴ ፡ ይፈጥሩለት ፡ ይሆናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፵፩ ።

## የዐፄ ፡ ፋሲልና ፡ የቱርኮች ፡ ስምምነት ፤-በተዋሕዶዎችና ፡ በቅባቶች ፡ መካከል፡ ስለ ፡ ተነሣው ፡ ክርክር ።

ከፍ ፡ ብሎ ፡ ከዐፄ ፡ እስክንድር ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከሺሕ ፡ ፬፻፸ ዓ ፡ም፡ ግድም ፡ ዠምሮ ፡ በፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ጠባቂነት ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ፡ የፖርቱጋልና፡ የኢጣሊያ ፡ , . . . ተወላጆች ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከተላመዱ ፡ በኋላ ፡ ቀጥለው ፡ በነገሡት ፡ ነገሥታት ፡ ዘመን ፡ በየጊዜው ፡ ግንኙነቱ ፡ እየ ጠበቀ ፡ መሄዱን ፡ ከዚሁ ፡ ግንኙነት ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ደብዳቤ ፡ መለዋወጣቸ ውን ፡ የግራኝንም ፡ ወረራ ፡ ለማስወገድ ፡ ርዳታ ፡ መምጣቱን ፡ ከርዳታውም ፡ በኋላ ፡ ብዙዎች ፡ ሚሲዮናውያን ፡ መምጣታቸውን ፡ እነሱም ፡ ከእስክንድር ፡ ዠምሮ ፡ የተመኙት ፡ የሃይማኖት ፡ የጥቅም ፡ ምኞት ፡ በዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ጊዜ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በልጃቸው ፡ በዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ጊዜ ፡ መውደቁን ፡ ያለፉት ፡ ምዕራፎች ፡ ገልጸውልናል ።

ስለዚህ ፡ ከፋሲል ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥትና ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ እናገኛለን ፡ በማለት ፡ የፖርቱጋልና ፡ የኤስፓኝ ፡ ነገሥ ታት ፡ እንዲሁም ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ደክመውበት ፡ የነበረው ፡ ፖለቲክ ፡ በፍጹም ፡ ተበላሸ ። ዐፄ ፡ ፋሲልም ፡ እነሱን ፡ ትተው ፡ ግንኙነታቸውን ፡ ወደ ፡ ቱርኩ ፡ ፓሻ ፡ ወደ ፡ ምጥዋ ፡ ሹም ፡ አዞሩ ።

የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ሰዎች ፡ ከጠ ባያቸው ፡ ዐዋቂዎችና ፡ ብልኆች ፡ መሆናቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ ከዚያ ፡ በፊትና ፡ በኋላ ፡ የተነሡትን ፡ ሳንዘረዝር ፡ ባለፈውና ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የሆነውን ፡ ማስታ ወስ ፡ ይበቃል ። ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ የቱርክንና ፡ የየ መንን ፡ መንግሥት ፡ ድጋፍ ፡ አድርጎ ፡ ተነሥቶ ፡ አገራቸውን ፡ በጠፋ ፡ ጊዜ ፡ ከክርስቲያኑ ፡ ከፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ተላልከው ፡ ባገኙት ፡ ርዳታ ፡ ልጃ ቸው ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ የግራኝን ፡ ኀይል ፡ ለማጥፋት ፡ ቻሉ ። አሁን ፡ ግን ፡ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ከካቶሊኮች ፡ ጋራ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጠብ ፡ ስለ ፡ ተለያዩ ፡ የኤ ስፓኝና ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥታት ፡ እንዳያጠቋቸው ፡ ከነዚሁ ፡ መንግሥቶች ፡ ባለጋራና ፡ ካባታቸው ፡ ባለጋራ ፡ ከነበረው ፡ ከቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ መስማ ማት ፡ ለመንግሥታቸው ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ተረዱት ። ትላንት ፡ ጠላት ፡ የነበረውን ፡ ለዛሬ ፡ ጥቅም ፡ ሲያስፈልግ ፡ መልሶ ፡ ወዳጅ ፡ የማድረግ ፡ ፖለቲክ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ባሉት ፡ መንግሥታት ፡ እየተደጋገመ ፡ ተሠ ርቶበታል ፡

ስለዚህ ፡ ዐፄ ፡ ፋሲልና ፡ የቱርኮች ፡ ሹም ፡ (የሱአኪምና ፡ የምጥዋ ፡ ፓሻ) ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ስምምነትና ፡ ወዳጅነት ፡ አደረጉ ። ፓሻውም ፡ ንጉሡ፡ ያልፈቀዱላትን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመግባት ፡ በም

ጥዋ ፡ በኩል ፡ ሲመጣ ፡ ሊከለክል ፡ ቃል ፡ ገባላቸው ። እንደዚሁም ፡ ወደ ፡ የመን ፡ ተሳልከው ፡ ወዳጅነት ፡ ወጡ ። ይኸውም ፡ ድንገት የኢስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ በሚሲዮኖቹ ፡ መበረር ፡ ተቀይሞ ፡ ጦርነት ፡ ያነሣ ፡ እንደሆነ፡ የጦር ፡ ጓደኛ ፡ ለማግኘት ፡ የተደረገ ፡ ዘዴ ፡ ነው ።

፨ ፨ ፨

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ በሻቹ ፡ ጳጳስ ፡ በአቡነ ፡ ስምዖን ፡ እግር ፡ ጳጳስ ፡ እንዲላክላቸው ፡ ከእስክድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ከአቡነ ፡ ማቴዎስ ፡ ጋራ ፡ ተላላኩ ። በመካከሉም ፡ አንድ ፡ ሐሰተኛ ፡ ግብጻዊ ፡ ተል ኬአለሁ ፡ ብሎ ፡ መጥቶ ፡ ሥራ ፡ ዠምሮ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን፡ ጓደኛው ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሐሰተኛ ፡ መሆኑን ፡ ገለጸበትና ፡ ተያዘ ፡ በደቅ፡ ሐይቅ ፡ ታሰረ ። በኋላ ፡ ግን አባ ፡ አርሜኖስ ፡ ይባሉ ፡ የነበሩት ፡ አባ ፡ ማርቆስ ፡ ተብለው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጡና ፡ እንደተለመደ ፡ ሥራቸውን፡ ያከሂዱ ፡ ዠመር ። ንጉሡና ፡ ጳጳሱም ፡ ባንድነት ፡ ተማክረው ፡ ከእንግዴህ፡ ወዲህ ፡ ማንም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ከየትም ፡ አገር ፡ ያለ ፡ ፈቃድ ፡ መጥቶ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቢገኝ ፡ መጪውና ፡ ተቀባዩ ፡ ይታሰራሉ ፡ ወይም ፡ ይስቀላሉ ፡ የሚል ፡ ዐዋጅ ፡ አናገሩ ።

የሮማ ፡ የካቶሊክ ፡ ቄሶችም ፡ በነቤርሙዴዝ ፡ በነኤዝ ፡ በነአልፎንሱ ፡ ተዠምሮ ፡ የነበረው ፡ የሃይማኖት ፡ ስብከታቸው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ በፍጹም ፡ በመቅረቱ ፡ በጣም ፡ አዝነውበት ፡ ነበር ። ከነሱም ፡ ውስጥ ፡ ፫ደፋሮች ፡ የሆኑትና ፡ ሰማዕትነት ፡ የተመኙት ፡ በፓሻና ፡ በዐፄ ፡ ፋሲል ፡ መካከል ፡ የተደረገውን ፡ ስምምነት ፡ ያውቃሉና ፡ የምጥዋን ፡ በር ፡ ትተው ፡ በመቃድሾ ፡ በኩል ፡ መጥተው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመግባት ፡ ሲጓዙ ፡ ሱማሌዎች ፡ በጫካ ፡ አግኝተው ፡ ገደሏቸው ። ሌሎችም ፡ ፫ ፡ ሚሲዮናውያን ፡ በምጥዋ ፡ በኩል ፡ መጥተው ፡ የቱርኮቹ ፡ ሹም ፡ አስሮ ፡ ራሳቸውን ፡ ቈርጦ ፡ ገደላቸው ። ከራሳቸውም ፡ ላይ ፡ ቈዳቸውን ፡ አስገፍፎ ፡ የካቶሊክ ፡ ቄስ ፡ አለሚጨት ፡ መሆኑን ፡ አይተው ፡ ደስ ፡ እንዲላቸው ፡ ለዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ላከላቸው ፡ ይባላል ።

የኢትዮጵያም ፡ ካህናትና ፡ ሕዝብ ፡ የሚጠሉትና ፡ የተጋደሉበት ፡ የካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ በዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ መሞትና ፡ በዐፄ ፡ ፋሲል ፡ መንግሥ ፡ በሚሲዮኖቹ ፡ መጥፋት ፡ ከተወገደላቸው ፡ በኋላ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ሃይማኖት ፡ ውስጥ ፡ ከራና ፡ ጸጋ ፡ ቅባት ፡ የሚባሉት ፡ ወገን፡ ለይተው ፡ ክርክር ፡ ስለ ፡ አነሡ ፡ ለሕዝብና ፡ ለመንግሥት ፡ አስፈላጊ ፡ የነበረው ፡ ሰላም ፡ በሙሉ ፡ አልተገኘም ፡ ነበር ።

የነዚህንም ፡ የሦስቱን ፡ እምነት ፡ ልዩነት ፡ በትክክልና ፡ በዝርዝር ፡ የሚያውቁት ፡ ከፍ ፡ ያሉት ፡ ሊቃውንቶች ፡ ናቸው ። ቢሆንም ፡ አሳቡ ፡ ባጭሩ ፡ እንደዚህ ፡ ይመስላል ።

፩ኛ ፡ ክርስቶስ ፡ በተዋሕዶ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ተዋሕዶ ፡
ማለትም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የኛን ፡ ሥጋ ፡ በአካሉ ፡ ከፍሎ ፡ ቢዋ
ሐደው ፡ በሰውነቱ ፡ እንደ ፡ አብ ፡ እንደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያለ ፡ ፍጹም ፡ አም
ላክ ፡ ሆነ ፡ የሚሉ ፡ ተዋሕዶዎች ፡ ናቸው ።

፪ኛ ፡ የሥጋና ፡ የቃል ፡ መዋሐድ ፡ ሁለትነትን ፡ አጠፋ ፡ እንጂ ፡ ቃል ፡
የለበሰውን ፡ ሥጋ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክነት ፡ ክብር ፡ ያከበረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ነው ፡ የሚሉ ፡ ቅባቶች ፡ ናቸው ።

፫ኛ ፡ ቃል ፡ በለበሰው ፡ ሥጋ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደኛ ፡ የጸጋ ፡
ክብር ፡ አግኝቶ ፡ ክርስቶስ ፡ ተባለ ፡ የሚሉ ፡ የጸጋ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

ከነዚሁ ፡ ከሦስቱ ፡ ወገኖች ፡ ማናቸው ፡ እውነትን ፡ የያዙ ፡ መሆኑን ፡
ለማረጋገጥ ፡ የያውሬጃው ፡ ሊቃውንት ፡ በራሻና ፡ በአሬንጎ ፡ ላይ ፡ ተሰብስበው ፡
እንዲከራከሩ ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ፋሲልና ፡ ጳጳሱ ፡ አቡነ ፡ ማርቆስ ፡ አዘው ፡ ነበር ።

ከጐጃም ፡ ከቅባቶች ፡ ወገን ፡ ዋናው ፡ ተከራካሪ ፡ ዘኢየሱስ ፡ የሚባ
ለው ፡ ነው ። ከደብረ ፡ ሊባኖሶች ፡ (ተዋሕዶዎች) ፡ ወገን ፡ አዳም ፡ ዘእምፍራግዝ ፡
የሚባለው ፡ ሆኖ ፡ ብዙ ፡ ጥቅስ ፡ እየጠቀሱ ፡ ተከራከሩ ። በመጨረሻ ፡ አዳም ፡
ዘእምፍራግዝ ፡ (ተዋሕዶ) ፡ አሸነፈ ፡ ዘኢየሱስ ፡ (ቅብዐት) ፡ ተሸነፈ ፡ ተብሎ ፡
ጉባኤው ፡ ተፈታ ።

የቅባቶችም ፡ ወገን ፡ ከጐጃም ፡ በተለይ ፡ ደብረ ፡ ወርቆች ፡ ናቸው ።
ተዋሕዶ ፡ ግን ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ በሸዋ ፡ በጐንደር ፡ በትግሬ ፡ ነው ፡ ጸጋ
ዎች ፡ ግን ይበልጥ ፡ የሚገኙት ፡ በሸዋ ፡ ነው ፡ ይባላል ።

## ምዕራፍ ፴፪ ።

### ስለ ፡ መልክአ ፡ ክርስቶስና ፡ ዘማርያም ፡ መሸፈት ፡— ስለ ፡ ጐንደር ፡ ቤተ መንግሥትና ፡ ስለ ፡ ዐባይ ፡ ድልድይ ፡ መሠራት ።

ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ መልክአ ፡ ክርስቶስ ፡ የተባለ ፡ የላስታ ፡ ባለ
ባት ፡ አስቀድሞ ፡ በዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ጊዜ ፡ በሃይማኖት ፡ ምክንያት ፡
ሸፍቶ ፡ ሲኖር ፡ በዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ጊዜ ፡ የእስክንድርያ ፡ ሃይማኖት ፡ ከተመለሰ ፡
በኋላ ፡ የሃይማኖቱን ፡ ምክንያት ፡ ዘሩን ፡ ወደ ፡ መፈለግ ፡ አዘረና ፡ ለጦር
ነት ፡ ይዘጋጅ ፡ ገመር ። ጦርም ፡ ከበረለት ፡ በኋላ ፡ በሺሕ ፡ ፲፻፷፯ ፡ ዓ ፡ ም
ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ወደ ፡ ነበሩበት ፡ ወደ ፡ ሊቦ ፡ (በጌምድር) ፡ መጥቶ ፡ በንጉሡና ፡
ባሽከሮቻቸው ፡ ላይ ሳይታሰብ ፡ አደጋ ፡ ጣለ ። አሳቡም ፡ ንጉሡን ፡ ለመማረክ ፡
ነበር ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ንጉሡ ፡ በፈረስ ፡ ሆነው ፡ ስላመለጡ ፡ ሊያገኛቸው ፡
አልቻለም ፡ መልክአ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሠፈር ፡ በገባ ፡ ገዜ ፡ ብዙ ፡ ዕቃ ፡ አገኘ ፡
ወዲያውም ፡ ነግሻለሁ ፡ ብሎ ፡ ዐዋጅ ፡ ነገረ ፡ ይባላል ።

በኋላ ፡ ግን ንጉሡ ፡ ከጐጃም ፡ ከዳሞት ፡ የራስ ፡ ዘቅዱስን ፡ ከሰሜን ፡ የወንድማቻቸውን ፡ የገላውዴዎስን ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ሄደው ፡ ያለበትን ፡ ሶፍራ ፡ ዙሪያውን ፡ ከበቡና ፡ ጦርነት ፡ ተዠመረ ፤ በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ ከንጉሡ ፡ ተዋጊ ዎች ፡ ወገን ፤ ቆዘሮ ፡ የሚባለው ፡ የገላውዴዎስ ፡ ወንድም ፡ መልክአ ፡ ክርስ ቶስን ፡ ገደለው ፤ እርሱም ፡ ሲሞት ፡ ጭፍራው ፡ ተሸንፎ ፡ ሸሸ ።

ደግሞ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የመልክአ ፡ ክርስቶስ ፡ ልጅ ፡ መልክአ፡ ማርያም ፡ ያባቱን ፡ ደም ፡ ለመበቀል ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ጦር ፡ ሰብስቦ ፡ በዚያው ፡ በባቱ ፡ አገር ፡ በላስታ ፡ ተነሣና ፡ ከንጉሡ ፡ ሹማምንቶች ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ዠምሮ፡ ክፍሌ ፡ የተባለውን ፡ ሹም ፡ ማረከው ። ብዙ ፡ ቀን ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ድሉ ፡ ለማንኛው ፡ ወገን ፡ መሆኑ ፡ ሳይለይ ፡ በመክከሉ ፡ ክረምት ፡ ረኀብና ፡ በሽታ ፡ አንድነት ፡ በገሩ ፡ ስለ ፡ ገባ ፡ የንጉሡ ፡ ጦር ፡ ከላስታ ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ መመለስ ፡ ግድ ፡ ሆነበት ።

በዚህ ፡ ላይ ፡ አቤቶ ፡ ዘማርያም ፡ የተባለው ፡ የተንቤን ፡ ገዥ ፡ እንዲሁ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሸፈተ ፡ የላስታው ፡ መልክአ ፡ ማርያም ፡ የጦር ፡ ጓደኛ ፡ ስላገኘ ፡ ደስ ፡ አለውና ፡ ሁለቱም ፡ ተስማሙ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አቤቶ ፡ ዘማርያም፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ ቀን ፡ ሳይቈይ ፡ ተሸነፈ ። እርሱም ፡ ንጉሡ ፡ ከገር ፡ እንዲወጡ፡ ካሰናበቷቸው ፡ ውስጥ ፡ ብሩናና ፡ ኮርዲሬያ ፡ የሚባሉትን ፡ ኢየሱሳውያን ፡ በአ ምባ ፡ ሰላም ፡ ደብር ፡ ላይ ፡ ደብቆ ፡ አስቀምጦ ፡ ኖሮ ፡ ከንጉሡ ፡ አሽከሮች ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ በሞተበት ፡ ቀን ፡ ሚሲዮናውያኑም ፡ ተይዘው ፡ ተገደሉና ፡ የተ ንቤኑ ፡ ሽፍትነት ፡ በቶሎ ፡ ተፈጸመ ።

ገላውዴዎስም ፡ ክረምቱ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ከበጌምድር ፡ ወደ ፡ ላስታ ፡ ሄዶ ፡ የመልክአ ፡ ማርያምን ፡ ጦር ፡ ወግቶ አሸንፎ ፡ ከበታተነ ፤ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በተደረገው ፡ ጦርነት ፡ ተማርኮ ፡ የነበረውን ፡ ክፍሌን ፡ ከታሠረበት ፡ ቦታ ፡ ነፃ ፡ አውጥቶ ፡ ይዞ ፡ በደስታ ፡ ተመለሰ ።

፨ ፨ ፨

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ አገሩ ፡ ሁሉ ፡ ሰላም ፡ ሆኖ ፡ ሰዉም ፡ የራሱን ፡ ተግባር ፡ እንደልቡ ፡ እየሠራ ፡ ኖረ ፤ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ፋሲልም ፡ ከግራኝ ፡ ጦርነት ፡ ወዲህ ፡ ያሉት ፡ ነገሥታት ፡ ለኑሮም ፡ ሆነ ፤ ወይም፡ ለጦርነት ፡ ለጊዜው ፡ ደስ ፡ በሚያሰኛቸው ፡ ሥፍራ ፡ ምሽግ ፡ ወይም ፡ ቤት ፡ እየሠሩ፡ አለዚያም ፡ በየድንኳናቸው ፡ ? ይቀመጡ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፤ የታወቀ ፡ ታላላቅ ፡ ከተማና ፡ ቤት ፡ መንግሥት ፡ ገና ፡ አልተሠራም ፡ ነበር ፡ የጐንደር ፡ መንግሥ ትም ፡ በዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግልና ፡ በዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ዘመን ፡ ተመሠረተ ፡ ቢባል፡ ወደ ፡ ትግሬም ፡ ወደ ፡ ሸዋም ፡ ወደ ፡ ጐጃምም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ እየተዘዋወሩ፡ የትም ፡ ሄደው ፡ ተመልሰው ፡ መቀመጫውን ፡ በዚያው ፡ በጐንደር ፡ አቅራቢያ ፡ በደንቀዝ ፡ ስላደረጉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ የታወቀ ፡ ትልቅ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሠር ተው ፡ ከተማውን ፡ በሰፊ ፡ አልከተሙትም ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ የፈላሾችንና ፡ የህንዶችን ፡ አናጢዎችና ፡ ግንበኞች ፡ ሰብስበው ፡ (ፖርቱጊዞች ፡ አሉበት ፡ የሚሉ ፡ አሉ) ፤ በጐንደር ፡ ከተማ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የፋሲል ፡ ግንብ ፡ እየተባለ ፡ የሚታየውን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አሠሩ ። ያሠራሩንም ፡ አኳኋን ፡ ከሌሎቹም ፡ እየተማከሩ ፡ ዐይነቱን ፡ የሰጡ ፡ ራሳቸው ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። ቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ ተሠርቶ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ዙሪያውን ፡ ሰፊ ፡ ግንብ ፡ አሠሩ ፤ በዙሪያውም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አሳነፁ ፡ በዚህም ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የንጉሡ ፡ ለብቻ ፡ የጳጳሱ ፡ ለብቻ ፡ ግብር ፡ ማብሊያውና ፡ ችሎት ፡ ማስቻያውም ፡ እየተለየ ፡ በየክፍሉ ፡ ስለ ፡ ተሠራ ፡ በጣም ፡ አምሮ ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ያሠሩት ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ እላይ ፡ እንዳልነው ፡ «የፋሲል ፡ ግንብ» ፡ እየተባለ ፡ ታሪካዊ ፡ የሆነ ፡ ምልክቱ ፡ ስማቸውን ፡ እያስጠራ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ይታያል ።

ለመንግሥታቸውና ፡ ለሕዝባቸውም ፡ በሰፊው ፡ ከማሰባቸው ፡ የተነሣ ፡ ከር ሳቸው ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ያልሠሩትን ፡ የዐባይን ፡ ድልድይ ፡ አን ሩን ፡ በዐፈረዋናት ፤ አንዱን ፡ በአዳቤት ፡ ሁለት ፡ ድልድይ ፡ አሠርተውለት ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ነጋዴውም ፡ መንገደኛውም ፡ ሲያልፍ ፡ የፋሲልን ፡ ነፍስ ፡ ይማር ፡ እያለ ፡ ያርፍ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ሙኻል ፡ በጌምድርም ፡ የርብን ፡ ድል ድይ ፡ ከጐንደር ፡ አጠገብ ፡ የአንገረብን ፡ ድልድይ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አሠርተውት ፡ የነበረው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ፍራሹ ፡ አለ ፡ ይባላል ። እኔ ፡ ግን ፡ ጊዜ ፡ አጋጥሞኝ ፡ ባይኔ ፡ አላየሁትም ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ዘፋኝ ፡ እንዲህ ፡ አለች ፡ ይባላል ።

ርብና ፡ ዐባይ ፡ መንጠቅ ፡ የለመዱ ፡
እንደ ፡ ልማዳቸው ፡ ስውን ፡ እንዳይገድሉ ፡
በፋሲል ፡ ዳኝነት ፡ ተፈጥመው ፡ ሄዱ ።
ርብና ፡ ዐባይ ፡ ሸፍተው ፡ ሲኖሩ ፡
አላፊ ፡ አግዳሚውን ፡ ከጕራ ፡ እያሰሩ ፡
በትላልቅ ፡ ድንጋይ ፡ ተደብድበው ፡ ቀሩ ።
አብርሃም ፡ ነው ፡ ጣና ፡ እንግዳ ፡ ተቀባይ ፡
ከቤቱ ፡ ቢመጡ ፡ ርብና ፡ ዐባይ ፡
ሌቦች ፡ ናቸው ፡ ሳይል ፡ ግብራቸውን ፡ ሳያይ ፡
መንገዱን ፡ መራቸው ፡ እንዳይሄዱ ፡ በላይ ።

የግጥሙም ፡ ምክንያት ፡ ዐባይ ፡ በጣና ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ሄዶ ፡ የሚለይበት ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ ጊዮርጊስ ፡ ስለ ፡ ሆነና ፡ ርብም ፡ የሚገባው ፡ ጣና ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፵፫ ።

### አዳኙ ፡ ዐፄ ፡ ፋሲልና ፡ ቈለኛው ።

ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ እንደ ፡ ነገሥታት ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ከአእምሮና ፡ ከመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ጋራ ፡ ውሃ ፡ ዋና ፡ አደን ...... ሲማሩ ፡ አድገዋል ። ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ግን ፡ አጥብቀው ፡ ይወዱ ፡ የነበረው ፡ አደንን ፡ ነው። አደንም ፡ ሲባል ፡ በተለይ ፡ የሚወዱት ፡ ሊያስፎክሩ ፡ ከሚችሉት ፡ አራዊት ፡ ውስጥ ፡ አንበሳና ፡ ዝሆንን ፡ ነው ። ከመውደዳቸውም ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ አደን ፡ ሊሄዱ ፡ በሰቡበት ፡ ቀን ፡ ሌሊቱን ፡ እንቅልፍ ፡ አይወስዳቸውም ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በታሪከ ፡ ነገሥታቸው ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ዠግኖችን ፡ አስከትለው ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ የቈላ ፡ በረሓ ፡ ላደን ፡ ሄዱ ። በበረሓም ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ሲፈልጉ ፡ አንድ ፡ ባለትልቅ ፡ ጥርስ ፡ ዝሆን ፡ አገኙና ፡ በትልቅ ፡ ጨሬ ፡ (ረዥም ፡ ጦር) ፡ ከእልቀቱ ፡ ላይ ፡ ፈለሙት ። ቀጥሎም ፡ ሩጫ ፡ ቢዠምር ፡ በፈረሳቸው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ደግመው ፡ በወጉት ፡ ጊዜ ፡ ዝሆኑ ፡ ደም ፡ እያቦረረው ፡ ወደ ፡ በረሓ ፡ ገብቶ ፡ ላይን ፡ ጠፋ ። ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ፋሲልም ፡ የተንጠባጠበውን ፡ የደም ፡ ምልክት ፡ እየተከታተሉ ፡ ካሽከሮቻቸው ፡ ተለይተው ፡ ብቻቸውን ፡ በግልቢያ ፡ ዝሆኑን ፡ ይፈልጉ ፡ ዠመር ። ነገር ፡ ግን ፡ ዝሆኑ ፡ ድቡሽትና ፡ ረግረግ ፡ ባለበት ፡ ሥፍራ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ የደሙን ፡ ምልክት ፡ ለመከታተል ፡ አልቻሉም ። ለመከታተልም ፡ ቢችሉ ፡ የረግረጉ ፡ ሥፍራ ፡ ፈረሳቸውን ፡ እስከ ፡ ለከው ፡ ድረስ ፡ እየዋጠ ፡ መሄድ ፡ አቃታቸው ። ቢሆንም ፡ ካንዱ ፡ ማጥ ፡ ወዳንዱ ፡ ማጥ ፡ ሲደርሱና ፡ ሲሰር ፡ በመከራ ፡ ሲወጡ ፡ በመጨረሻው ፡ መግቢያ ፡ መውጫው ፡ ወደማይታወቅ ፡ ጭው ፡ ያለ ፡ በረሓ ፡ ገቡ ። የመጡበትም ፡ መንገድ ፡ በፍጹም ፡ ጠፍቶ ፡ የሚያደርጉት ፡ ግራ ፡ ገባቸው ። ብዙ ፡ ሰዓትም ፡ ብቻቸውን ፡ ዝሆኑን ፡ ፍለጋ ፡ ትተው ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ ለመፈለግ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ከባዘኑ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ በወጣው ፡ ያውጣኝ ፡ ብለው ፡ ወዳንዱ ፡ አቅጣጫ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ይጋልቡ ፡ ዠመር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንዳጋጣሚ ፡ አንድ ፡ ከበረሓው ፡ ጌሾ ፡ ቈርጦ ፡ ተሸክሞ ፡ የሚሄድ ፡ ቈለኛ ፡ ስላዩ ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ አመስግነው ፡ ወደርሱ ፡ ግልቢያቸውን ፡ ቀጠሉ ፤ በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ ‹እባክህ ፡ መንገድ ፡ ምራኝ› አሉት ፡ ቈለኛውም ፡ «እዬ ፡ ወንድሜ ፡ እግረኛ ፡ ከፈረሰኛ ፡ ጋራ ፡ መቼ ፡ ትክክል ፡ ይሄዳል› ሲል ፡ መለሰላቸው ፤ ዐፄ ፡ ፋሲል« ፡ የጌሾ ክን ፡ ዋጋ ፡ ያልኸኝን ፡ ያኸል ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ጌሾውን ፡ ተውና ፡ ሳይመሽ ፡ ተፈናጠጥ ፡ በቶሎ ፡ እንጋልብ» ፡ አሉት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቈለኛው ፡ ጌሾውን ፡ ጥሎ ፡ እፈረሱ ፡ ላይ ፡ ተፈናጠጠና ፡ በሚያውቀው ፡ መንገድ ፡ እያመለከተ ፡ ግልቢያቸውን ፡ ዠመሩ ። በመንገድም ፡ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ እንዳንድ ፡ ተራ ፡ ወታደር ፡ መስለው ፡ ከቈለኛው ፡ ጋራ ፡ እያወሩ ፡ መንገዳቸውን ፡ ቀጠሉ ። መኳንንቱና ፡ ወታደሩ ፡ በየፊናው ፡ ተበታትኖ ፡

በኋላም ፡ ግማሹ ፡ ተገናኝቶ ፡ ስለ ፡ ንጉሡ ፡ መጥፋት ፡ አጥብቀው ፡ ሲጨነቁ ፡ ነበርና ፤ አሁን ፡ ሲመጡ ፡ ስላዩዋቸው ፡ ሁሉም ፡ በደስታ ፡ ለመቀበል ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ይጓዙ ፡ ገሮመር ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ‹ይህ ፡ ወደኛ ፡ የሚመጣው ፡ ሠራዊት ፡ ንጉሡን ፡ የሚቀበል ፡ ነው› ፡ አሉት ። ቈለኛው ፡ ለድኻ ፡ አዛኝ ፡ የሆኑትን ፡ ንጉሥ ፡ ባይኔ ፡ ባይ ፡ ምንኛ ፡ ደስ ፡ ባለኝ ፡ አላቸው ። ዐፄ ፡ ፋሲልም ፡ ስለ ፡ ወረታኽ ፡ ያልኽኝን ፡ ሁሉ ፡ ሰጥቼ ፡ ከንጉሡም ፡ አገናኝቼ ፡ ባልደረባ ፡ አሰጥኻለኹ ፡ አሉት ። ሕዝቡም ፡ እያደር ፡ ሲጠጋ ፡ ንጉሡ ፡ ለቈለኛው ፡ እንደዚህ ፡ አሉት ፡ ‹ከከብት ፡ የማይወርደው ፡ ንጉሡ ፡ ነውና ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ወርደኽ ፡ እጅ ፡ እንድትነሣ› ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዐፄ ፡ ፋሲልን ፡ ሲያዩ ፡ መኳንንቱ ፡ ከበቅሎም ፡ ከፈረስም ፡ እየወረዱ ፡ እጅ ፡ መንሣት ፡ ሲዠምሩ ፡ ፪ቱ ፡ ብቻቸውን ፡ በፈረስ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተፈናጠጡ ፡ ቀሩ ። የቀረው ፡ ሁሉ ፡ ዐፄ ፡ ፋሲልን ፡ እጅ ሲነሣ ፡ ቈለኛው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ደነገጠ ። ዐፄ ፡ ፋሲልም ፡ ንጉሡን ፡ አየኽን ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ፡ ‹ከሁለታችን ፡ በቀር ፡ ከፈረስ ፡ ወርዶ ፡ እጅ ፡ ያልነሣ ፡ የለም ፡ እንግዲያው ፡ ንጉሡ ፡ ወይ ፡ እርስዎ ፤ አለዚያም ፡ እኔ ፡ መሆኔ ነዋ› ፡ ሲል ፡ መለሰ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ በቈለኛው ፡ አነጋገር ፡ ሥቀው ፡ ከፈረሳቸው ፡ ወርደው ፡ ለዚሁ ፡ ቈለኛ ፡ ባላገር ፡ ፈረስና ፡ በቅሎ ፡ ከሙሉ ፡ መጓሪያው ፡ ጋራ ፡ ሸልመው ፡ አስደስተው ፡ ወዳገሩ ፡ ሰደዱት ።

ይህ ፡ ታሪክ ፡ ሐንሪ ፡ አራተኛ ፡ የሚባለው ፡ የፈረንሣይ ፡ ንጉሥ ፡ ከደረገው ፡ ጋራ ፡ በፍጹም ፡ ይጋጠማል ።

## ምዕራፍ ፡ ፵፬ ።

ስለ ፡ ኑብያና ፡ ስለ ፡ ስናር ፡ መገዛት ፤ ስለ ፡ ገላውዴዎስ ፡ መሸፈት ፤

## ስለ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ዕረፍት ።

ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ታሪክ ፡ ነገሥታቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምዕራብ ፡ ስናርንና ፡ ኑብያን ፡ እንደ ፡ ገዙ ፡ ይገልጻል ። በኑብያም ፡ በበታቻቸው ፡ ጊዮርጊስ ፡ የሚባል ፡ ንጉሥ ፡ አንግሠው ፡ እስከ ፡ ምድረ ፡ ግብፅ ፡ ጠረፍ ፡ ገዝቷል ፡ ይላል ። የፈረሰቻቸውም ፡ መታሠሪያና ፡ መቀለቢያ ፡ ስናር ፡ ነበር ። ከርሳቸው ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ኑብያንና ፡ ስናርን ፡ ቢበረታ ፡ መውረር ፡ እንጂ ፡ እንደርሳቸው ፡ አልገዙትም ፡ ነበርና ፡ ባለቅኔ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ይባላል ።

እንዘ ፡ ኢተአምር ፡ ባዕደ ፡ ኑብያ ፡ ድንግል ፤ ወለደቶ ፡ ለፋሲል ፡ ቃል ።

ትርጓሚው ፡

ድንግል ፡ ወንድ ፡ ሳታውቅ ፡ ቃልን ፡ እንደ ፡ ወለደች ፡ ኑብያም ፡ ሌላ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ሳይገዛት ፡ ፋሲልን ፡ ወለደች ፡ (ወይም ፡ ተቀበለችው ፡ ማለት) ፡ ነው ።

አዝማሪ ፡ ደግሞ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ገጠመ ፤
ጐንደር ፡ ቢያጕረመርም ፡ ፋሲል ፡ ፈረስኽ ፡
ኑብያና ፡ ስናር ፡ ወርቁን ፡ ጫኑልኽ ።
ሣሩን ፡ ተጠየፈ ፡ የፋሲል ፡ ፈረሱ ፤
ክምር ፡ የሱዳን ፡ ወርቅ ፡ ገፈራው ፡ ነው ፡ ለሱ ።

፨ ፨ ፨

በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሰላምና ፡ ደስታ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከቈየ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ በፍቅር ፡ ያገለገሏቸው ፡ ወንድማቸው ፡ ገላውዴዎስ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ሸፈቱባቸውና ፡ የሚያሳዝን ፡ ሆነ ። ገላውዴዎስ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ የሸፈቱትን ፡ ሁሉ ፡ እየተከታተሉ ፡ ስላጠፉ ፡ ዝናቸው ፡ በያለበት ፡ ተሰምቶ ፡ ነበር ፤ በዚህም ፡ ላይ ፡ የንጉሥ ፡ ዘር ፡ በመሆናቸው ፡ መንግሥትን ፡ ከዐፄ ፡ ፋሲል ፡ በኋላ ፡ ወይም ፡ በዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ጊዜ ፡ ለመያዝ ፡ አስበው ፡ ነው ፡ ይባላል ።

በዚህም ፡ ጊዜ የቀድሞው ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ማርቆስ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ተመልሰው ፡ የጳጳስነቱ ፡ ሥፍራ ፡ ባዶውን ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ከእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ጋራ ፡ ተላልከው ፡ በኑብያና ፡ በስናር ፡ በኩል ፡ አቡነ ፡ ሚካኤልን ፡ ሲያስመጡ ፡ እንዲሁም ፡ ገላውዴዎስ ፡ ውስጡን ፡ ለኔም ፡ ጳጳስ ፡ እንድትልኩልኝ ፡ ብለው ፡ ኖሮ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ የሚባሉት ፡ በአውሳ ፡ በኩል ፡ መጡ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ያቡኑን ፡ ሥፍራ ፡ በጠቅላላው ፡ ርሳቸው ፡ ላስመጧቸው ፡ ጳጳስ ፡ ለአቡነ ፡ ሚካኤል ፡ ሰጧቸው ፡ በገላውዴዎስ ፡ ስም ፡ የመጡት ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ ግን ፡ ከንጉሡ ፡ ሸሽተው ፡ ላስታ ፡ ገብተው ፡ ነበርና ፤ ካሉበት ፡ ተይዘው ፡ በወሀኒ ፡ አምባ ፡ (ከጣና ፡ ባሕር ፡ በስተምሥራቅ) ፡ ታሠሩ ፤ በኋላም ፡ ያመለጡ ፡ እንደሆነ ፡ አገር ፡ ማሸፈታቸው ፡ አይቀርም ፡ ተብሎ ፡ ከእስሩ ፡ ወጥተው ፡ በንጉሡ ፡ ትእዝዛ ፡ ተገደሉ ፡ ይባላል ።

ገላውዴዎስ ፡ ያስመጧቸው ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ በሸፈቱ ፡ ጊዜ ፡ ከበጌምድር ፡ ወደ ፡ ላስታ ፡ የሔዱበት ፡ ምክንያት ፡ የላስታ ፡ ባላባት ፡ መዠመሪያም ፡ መልክአ ፡ ክርስቶስ ፤ ሁለተኛ ፡ ልጁ ፡ መልክአ ፡ ማርያም ፡ ለንጉሡ ፡ ለዐፄ ፡ ፋሲል ፡ አልገዛም ፡ ብለው ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ፍቅር ፡ ስላልነበራቸው ፡ ነው ።

ይኸውም ፡ መልክአ ፡ ማርያም ፡ ንጉሡ ፡ በዳሞትና ፡ በጣና ፡ አጠገብ ፡ ከጋሎች ፡ ጋራ ፡ በሚዋጉበት ፡ ጊዜ ምቹ ፡ ሰዓት ፡ እየፈለገ ፡ ከላስታ ፡ እስከ ፡ ጐንደር ፡ እየመጣ ፡ አገር ፡ እያሸበረ ፡ ከብትም ፡ ሲዘርፍ ፡ ራስ ፡ ብዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚባለው ፡ የንጉሡ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ እየወጋ ፡ ይመልሰው ፡ ነበር ።

በመጨረሻም ፡ ንጉሡ ፡ ራሳቸው ፡ የላስታን ፡ ሽፍትነት ፡ በፍጹም ፡ ለመለመደምሰስ ፡ በሺህ ፡ ፲፮፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወደ ፡ ላስታ ፡ ዘመቱ ። መልክአ ፡ ማርያም ፡ ይኸንኑ ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ ኃይሉ ፡ በንጉሡ ፡ ሹማምን

ቶች ፡ ውጊያ ፡ ተዳክሞ ፡ ነበርና ፤ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ራሳቸው ፡ ከመጡ ፡ መጥ ፊያው ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ ያኽል ፡ ስለ ፡ ተረዳው ፡ ውጊያውን ፡ ትቶ ፡ ከልብ ፡ ይማሩኝና ፡ ታርቂ ፡ ልግባ ፡ ብሎ ፡ አማላጅ ፡ ላከ ። የሸፈተውን ፡ ከመውጋት ፡ በቀር ፡ ልታረቅ ፡ የሚለውን ፡ አልምርም ፡ ማለት ፡ የማይጠቅም ፡ መሆኑን ፡ ንጉሡ ፡ ስለ ፡ ተረዱ ፡ ጥያቄውን ፡ ተቀብለው ፡ ምሕረት ፡ አደረጉለትና ፡ ታርቆ ፡ ገባ ።

እንዲያውም ፡ ታርቆ ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ልጃቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ትውክልያን ፡ በሚስትነት ፡ ዳሩለት ። እርሱም ፡ በዚሁ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ያባቱን ፡ ግዛት ፡ አስመርቆ ፡ በደስታ ፡ ወደ ፡ ላስታ ፡ ተመለሰ ።

ከዚህም ፡ በፊት ፡ አገዎችና ፡ ጋሎች ፤ ሻንቅሎችም ፡ በውስጣቸውም ፡ ያሉ ፡ አገው ፤ ዚጋም ፤ ሕንካሳ ፤ ሞትቃል ፤ ወንበርያ ፡ ዋቆ ፡ የሚባሉት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገዶች ፡ ዘራቸው ፡ ጣም ፡ በርክቶ ፡ ወደ ፡ ላይም ፡ እየወጡ ፡ የጐጃምንና ፡ የበጌምድርን ፡ አገር ፡ ጊዜ ፡ ሲመች ፡ በመውረር ፡ አስቸግረው ፡ ነበር ።

በተረፈም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እየተዋጉ ፡ አገር ፡ ሰላም ፡ አጥቶ ፡ ነበርና ፡ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ በባሰበት ፡ ወገን ፡ ራሳቸው ፡ እየሄዱ ፡ በተረፈ ፡ የጦር ፡ አለቆቻ ቸውን ፡ ራስ ፡ ብዕለ ፡ ክርስቶስን ፤ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስን ፤ ደጃዝማች ፡ ማኅ ደረ ፡ ክርስቶስን ፤ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ላቶስን ፤ ደጃዝማች ፡ መልክአ ፡ ባሕርን ፤ ፊታውራሪ ፡ ማሞን ፡ እየላኩ ፡ ሲያስወጓቸው ፡ የጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ዓመታት ከፈጀ ፡ በኋላ እነዚሁ ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ እየተደመሰሱ ፡ በመጨረሻ ፡ አገሩ ፡ ሰላም ፡ ሆነ ። ከዚህ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ፴፯ ፡ ዓመት ፡ ከገዙ ፡ በኋላ ፡ ሰውነታቸውም ፡ ሸመ ገለ ፡ በሽምግልናቸውም ፡ ላይ ፡ ጽኑ ፡ ሕመም ፡ አደረባቸው ፡ በታመሙም ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡና ፡ መኳንንቱ ፡ በጣም ፡ ተጨነቀ ። ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ መል ክአ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚባለው ፡ እንደራሴያቸው ፡ በጣም ፡ ይወዳቸው ፡ ነበርና ፡ በን ጉሡ ፡ ሕመም ፡ እጅግ ፡ አዝኖ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ሰሞኑንም ፡ በጾምና ፡ በጸሎት ፡ ለድኾች ፡ ምጽዋት ፡ በመመጽወት ፡ ስለት ፡ በማድረግ ፡ ይደክምላቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥታቸው ፡ ይገልጻል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሕመማቸው ፡ እየጸና ፡ ሄዶ ፡ በሺሕ ፡ ፲፻፶፱ ፡ ዓ፡ ም ፡ በጥቅምት ፡ ወር ፡ ማክሰኞ ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ ዐረፉ ። ዘመነ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ግማሹ ፡ ፴፭ ፡ የቀረው ፡ ፴፯ ፡ ያደርጉታል ። ዙፋንም ፡ ልጃቸው ፡ ዮሐንስ ፡ እስኪቀመጡ ፡ ድረስ ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ ሁከት ፡ እንዳይነሣ ፡ ሞታቸው ፡ ለሕዝብ ፡ እንዲደበቅ ፡ የነጋሢ ፡ ዘሮችም ፡ ለጊዜው ፡ እንዲታሰሩ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ መልክአ ፡ ክርስቶስ ፡ አዘዘና ፡ ከያለበት ፡ እየተያዙ ፡ ታሰሩ ።

## የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ፩ኛ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

## ምዕራፍ ፡ ፵፫ ።

## የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥና ፡ ያወጡት ፡ ደንብ ።

በታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ እንደምናነበው ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ መልክአ ፡ ክርስቶስ ፡ አገር ፡ እንዳይታወክ ፡ የዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ሞት ፡ እንዲሰወር ፡ አድርጎ ፡ የነጋሢ ፡ ዘሮችንም ፡ ካሳሰረ ፡ በኋላ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዙን ፤ ዐቃቤ ፡ ሰዓቱን ፤ ሊቀ ፡ ማእምራኑን ፤ ጽራግ ፡ ማሰሬውን ፤ ቄስ ፡ ዐፄውን ፤ አዛዦቹን ፡ ሰበሰበና ፡ አቤቶሁን ፡ ዮሐንስ ፡ ቢነግሥ ፡ ይሻላል ፡ ሲል ፡ ምክር ፡ አቀረበላቸው ። እነሱም ፡ በነገሩ ፡ ከተስማሙበት ፡ በኋላ ፡ ጽራግ ፡ ማሰሬው ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ እግዚኦ ፡ በኃይልከ ፡ ይትፌሣሕ ፡ ንጉሥ ፡ . . . . . የሚለውን ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ፡ እየደገመ ፡ አክሊሉን ፡ ለአቤቶሁን ፡ ዮሐንስ ፡ ደፋላቸው ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጥተው ፡ እንደ ፡ ዘመኑ ልማድ ፡ «ንጉሣችን ፡ ዐፄ ፡ ፋሲለደስ ፡ ዐርፈዋል ፤ ልጃቸውን ፡ አቤቶሁን ፡ ዮሐንስን ፡ አንግሠናል ፤ የሞትንም ፡ እኛ ፡ ያለንም ፡ እኛ ፡ ጠላታችንን ፡ ይዘን ፤ ወዳጃችን ፡ ደስ ፡ ይበለው» ፡ ብለው ፡ በነጋሪት ፡ ዐዋጅ ፡ አናገሩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ሟቹ ፡ ንጉሥ ፡ ኀዘን ፡ ስለ ፡ ነጋሢውም ፡ ክብረ ፡ በዓል ፡ በገሃድ ፡ ተደረገ ። በታላቅ ፡ ኀዘንና ፡ ለቅሶ ፡ የዐፄ ፡ ፋሲልም ፡ ሬሳ ፡ አዘዞ ፡ (ደብረ ፡ ሊባኖስ) ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (1) መጥቶ ፡ በአባቶቻቸው ፡ መቃብር ፡ አጠገብ ፡ ተቀበሩ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ስመ ፡ መንግሥታቸውን ፡ (አእላፍ ፡ ሰገድ) ፡ አሰኝተው ፡ ያባታቸውን ፡ መንግሥት ፡ ይዘው ፡ ሥራቸውን ፡ ማከኼድ ፡ ዠመሩ ። እንደ ፡ ዠመሩም ፡ ለብላቴን ፡ ጌታን ፡ መልክአ ፡ ክርስቶስ ፡ ርእሰ ፡ መኳንንት ፡ አሰኝተው ፡ ሙሉ ፡ የእንደራሴነትን ፤ ለራስ ፡ (ወህኒ) ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የራቅ ፡ ማሰሬነትን ፡ ሹመት ፡ ሰጡ ። ቀጥሎም ፡ የነጋሢዎቹ ፡ ልጆች ፡ ብቻ ፡ በወህኒ ፡ አምባ ፡ ሲታሰሩ ፡ ለቀረው ፡ እስረኛ ፡ ሁሉ ፡ ሙሉ ፡ የምሕረት ፡ ዐዋጅ ፡ አደረጉ ።

ወደ ፡ ጐጃም ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ ለጐጃም ፡ ካህን ፡ የሚሰን ፡ መሬት ፡ የጠም ፡ ቄሎ ፡ ሰጥቻለሁ ፡ አሉ ። በተመለሱም ፡ ጊዜ ፡ የክርስቲያንና ፤ የእስላም ፤ የፈላሻ ፡ ሠፈር ፡ የተለየ ፡ ይሁን ፡ ወንድና ፡ ወንዱም ፤ ሴትና ፡ ሴቱም ፡ አይ[illegible]ኝ ፡ ሁሉም ፡ ለየብቻ ፡ መንደሩን ፡ እየሠራ ፡ ይቀመጥ ፡ ፈረንጅም ፡ ይ[illegible] ፡ የኛን ፡ ሃይማኖት ፡ ተቀብዬ ፡ በክርስትና ፡ ተጠምቄ ፡ እቀመጣለሁ ፡ የሚለው ፡ ይቀመጥ ፤ ያልፈለገ ፡ ወዳገሩ ፡ ይመለስ ፡ ሲሉ ፡ ይኸን ፡ የመሳሰለውንና ፡ የጋብቻ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መስከረም ፡ ፳፲ ፡ ቀን ፡ በጉባኤ ፡ ሊቃውንቱና ፡ መኳንንቱ ፡ ባሉበት ፡ ተመክሮ ፡ ሕጉ ፡ በዐዋጅ ፡ እንዲወጣ ፡ አደረጉ ። በጉባኤውም ፡ የነበሩ ፡ ጳጳሱ ፡ አባ ፡ ክርስቶዶሉ ፡ (ክርስቶስ ፡ ደወሉ) ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ (ቢቶደድ) ፡ መልክአ ፡ ክርስቶስ ፤ ብላቴን ፡

(1) የዜጋመሉ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ አይደለም ።

ጌታ ፡ ገብረ ፡ ልዑል ፤ የስሜን ፡ አጋፋሪ ፡ አሥራት ፤ ግራዝማች ፡ ሚካኤል ፤ ቀኛ ዝማች ፡ ሐዋርያ ፤ ሊቀ ፡ ጉባኤ ፡ መምህር ፡ ዘድብረ ፡ ሊባኖስ ፡ አባ ፡ ሕርያቆስ ፤ ዐቃቤ ፡ ሰዓት ፡ አባዲር ፤ ቄስ ፡ ዐፄ ፡ አሥረ ፡ ክርስቶስ ፤ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ወልደ ሃይማኖት ፤ ሊቀ ፡ ማእምራን ፡ ዘጊዮርጊስ ፤ (ማሞ) ፡ ጽራግ ፡ ማሰሬ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፤ (በኋላ ፡ የተሾሙ) ፡ . . . . . . . ናቸው ። እነዚህ ፡ ባሉበት ፡ የላይኛው ፡ ሥርዓትና ፡ ሕግ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በዐዋጅ ፡ ተነገረ ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ወዳገራቸው ፡ ሳይ ሄዱ ፡ በያለበት ፡ የነበሩት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ይገድሉናል ፡ ብለው ፡ ፈር ተው ፡ በአሪንጎ ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ። በዚያም ፡ ሳሉ ፡ ሊይዙን ፡ የመጡ ፡ እንደሆነ ፡ ሳንዋጋ ፡ እጃችንን ፡ አንሰጥም ፡ ብለዋል ፡ የሚሉ ፡ ወሬ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ተሰምቶ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ከመኳንንቱ ፡ መካከል ፡ ፊሊጥና ፡ ንግግር ፡ ዐዋቂ ፡ ግራ ዝማች ፡ ሚካኤል ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ተመርጦ ፡ ፈረንጆቹ ፡ ወዳሉበት ፡ ሄዶ ፡ የንጉ ሡን ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲነግራቸው ፡ ታዘዘ ። እርሱም ፡ ከጐንደር ፡ ወደ ፡ አሪንጎ ፡ ሄዶ ፡ ከፈረንጆቹ ፡ ጋራ ፡ በሰላም ፡ ተገናኝቶ ፡ በቈላ ፡ ወይም ፡ በደጋ ፡ በፈቀዳችሁት ፡ በኩል ፡ በሰላም ፡ ወዳገራችሁ ፡ እንድትመለሱ ፡ ንጉሡ ፡ አዘዋችኋል ፡ ሲል ፡ አስ ረዳ ። እነርሱም ፡ በቈላ ፡ በኩል ፡ በስናር ፡ አድርገን ፡ ወዳገራችን ፡ እንገባለን ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት ። በዚህም ፡ ግራዝማች ፡ ሚካኤል ፡ ተስማምቶ ፡ እነርሱም ፡ ወደ ስናር ፡ (ሱዳን) ፡ ሄዱ ። ግራዝማቹም ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ተመለሰ ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፮ ።

## ስለ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ጻድቅነትና ፡ ስለ ፡ ተደረገላቸው ፡ ታምራት ።

ዮሐንስ ፡ አንደኛ ፡ ከልጅነታቸው ፡ ዠምሮ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ ስላ ደጉ ፡ እንደ ፡ ባለቤታቸው ፡ እንደ ፡ እቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ጸሎተኛና ፡ ለድኻ ፡ አዛኝ ፡ ነበሩ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ «ጻድቁ ፡ ዮሐንስ» ፡ ይላቸው ፡ ነበር ።

ከጸሎት ፡ የተረፈውንም ፡ የበለጠ ፡ ጊዜያቸውን ፡ መጽሐፍ ፡ በመመልከት ፡ ከሊ ቃውንት ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ በመነጋገር ፡ ያሳልፉ ፡ ነበር ። ከመንግ ሥቱ ፡ ቀረጥና ፡ ግብር ፡ አልበላም ፡ ብለው ፡ ራሳቸው ፡ ሰሌን ፡ እየሠሩ ፡ ይበሉ ፡ ነበር ። ከጒሮሯቸው ፡ የተረፈውንም ፡ ለድኻ ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ስለ ፡ ትዕግ ሥታቸውም ፡ ብዛት ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የንስሐ ፡ አባታቸውን ፡ ከባለቤታቸው ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ አድርጎ ፡ ቢያገኙት ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ከማዕርጉም ፡ ሳይሽሩ ፡ ምሕ ረት ፡ አድርገው ፡ አስቀመጡት ፡ ይባላል ። በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ ጻድቁን ፡ ዮሐ ንስን ፡ ያገራችን ፡ ታሪክ ፡ ቄስ ፡ ነበሩ ፤ በመጨረሻም ፡ በቅተው ፡ ነበር ፤ እያለ ፡ ይና ገርላቸዋል ። ለዚሁ ፡ ማስረጃ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ይጽፋል ።

«ከልፍኛቸው ፡ ደጃፍ ፡ ከመድረኩ ፡ አጠገብ ፡ እንደ ፡ ሰሎሞን ፡ ባሕር ፡ አስበ ጅተው ፡ በባሕሩም ፡ ላይ ፡ ዓሣ ፡ አስረብተው ፤ ከዚህም ፡ ዓሣ ፡ ውስጥ ፡ ተመርጦ ፡ እየተሠራ ፡ ለግብር ፡ ይቀርብ ፡ ነበር ። እንደዚሁ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ግብር ፡ ገብቶ ፡ ከባ

ለቤታቸውና ፡ ከንስሐ ፡ አባታቸው ፡ ጋር ፡ ተቀምጠው ፡ የተጠበሰ ፡ ዓሣ ፡ ከማዕዱ ፡ ቀርቦ ፡ ሳለ ፡ የባለቤታቸውንና ፡ የንስሐ ፡ አባታቸውን ፡ መፈላለግ ፡ አውቀው ፡ «ሦስታችን ፡ እውነት ፡ ብንናገር ፡ ይህ ፡ የተጠበሰ ፡ ዓሣ፡ በሕያውነት ፡ተነሥቶ ፡ እባሕሩ ፡ውስጥ፡ ይገባ ፡ ነበር» ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እቴጌዪቱ ፡ ቄሱን ፡ አግብቼ ፡ ብኖር ፡ እወዳለሁ ፡ አሉ ፤ ቄሱም ፡ እቴጌን ፡ አግብቼ ፡ ብቀመጥ ፡ እወዳለሁ ፡ አሉ ንጉሡ ፡ ግን ፡ ይችን ፡ ከንቱ ፡ዓለም ፡ ንቄ ፡ ብመንን ፡ እወዳለሁ ፡ ብለው ፡ ሦስቱም ፡ እውነተኛውን ፡ የየምኞታቸውን ፡ ተናግረው ፡ ሲጨርሱ ፡ የተጠበሰው ፡ ዓሣ ፡ ተነሥቶ ፡ ዘሎ ፡ እባሕር ፡ ገባ ።

ዛሬም ፡ በጣና ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ክንፍ ፡ የሌለው ፡ የተጠበሰ ፡ የሚመስል ፡ ዓሣ ፡ በመረብ ፡ የተያዘ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የጻድቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ዓሣ ፡ ነው ፡ እየተባለ ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ይመልሱታል ፡ እንጂ ፡ አይበሉትም ፡ ይባላል ።

ስለዚህ ፡ ይህነኑ ፡ ምክንያት በማድረግ ፡ የዚያ ፡ ጊዜ ፡ ባለቅኔ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ሥላሴ ፡ ቅኔ ፡ ተቀኘ ።

አእዳው ፡ እለ ፡ ጴጥሮስ ።
እምክልኤ ፡ ዓሣት ፡ ወእምኃምስቱ ፡
አስፈሬዳተ ፡ ፍት ፡ ዐሥረ ፡ ወክልኤ ፡ እምድኅረ ፡ ተርፉ ፡ አግሐሣ ፡
ኢየሱስ ፡ አመ ፡ አጽገበሙ ፡ ለዘምእት ፡ ኃምሳ ።
ለመንኖሰ ፡ ዓለመ ፡ አመ ፡ ዮሐንስ ፡ ኀሠሣ ፤ አእዳዊሁ ፡ ቅድመ ፡ ይግሥሣ ፡
ድኅረ ፡ ሞት ፡ መልአ ፡ ለባሕር ፡ እስከነ ፡ ከርሣ ፡
በፈቃዱ ፡ ዘተግሕሠ ፡ ዓሣ ።

ትርጓሜው ፡ ባጭሩ ።

ኢየሱስ ፡ ላ፭ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ባጠገበ ። ጊዜ ፡ የጴጥሮስ ፡ እጆች ፡ ከ፪ ፡ ዓሣና ፡ ካ፭ ፡ እንጀራ ፡ የተረፈውን ፡ ፲፪ ፡ እንቅብ ፡ አነሡ ፡ ዮሐንስ ፡ ዓለምን ፡መናቅ ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ እጆቹ ፡ ሳይዳስሱት ፡ የተነሣ ፡ ዓሣ ፡ ባሕርን ፡ መላት ።
ያማርኛ ፡ ገጣሚ ፡ ደግሞ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

የደጉ ፡ ዮሐንስ ፡ ደግነት ፡ ቢነሣ ፡
ዘሎ ፡ ገባ ፡ እባሕር ፡ የተጠበሰ ፡ ዓሣ ።
ዓለምን ፡ቢመኙ ፡ ንጉሥ ፡ ጠርተውት ፡
ያ ፡ የሞተ ፡ ዓሣ ፡ ተነሣ ፡ ከሞት ።
ጻድቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘውድ ፡ ይዞ ፡ ብቃት ፡
ልበ ፡ አምላክ ። ሆነ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ።
የዓሣውን ፡ መነሣት ፡ በማሰብ ፡ ልጆቿ ፡ የሞቱበት ፡ ሴት ፡ የገጠመችው ።
ልጆቼ ፡ አልቀውብኝ ፡ ትንሹ ፡ ትልቁ ፡
የልጆቼን ፡ ማለቅ ፡ ንጉሥ ፡ ቢጠይቁ ፤
ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ልጆቼ ፡ ካለቁ ፡
ያሥነሡልኝ ፡ ነበር ፡ ዮሐንስ ፡ ጻድቁ ።

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ መጻፉችን ፡ ያገራችን ፡ ታሪክ ፡ የሚለውን ፡ ለማስረዳት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ተጠብሶ ፡ ለመብል ፡ እማዕድ ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ ዓሣ ፡ ነፍስ ፡ ዘርቶ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ መመለሱን ፡ ወይም ፡ አለመመለሱን ፡ ለይተን ፡ ላንበቢ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ደንበኛ ፡ መንገድ ፡ አናገኝም ።

## ምዕራፍ ፵፺ ።

## በተዋሕዶና ፡ በቅብዐት ፡ መካከል ፡ የተነሣው ፡ ክርክር ፤ — ስለ ፡ ንጉሡ ፡ ዕረፍት ።

በጻድቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚሁ ፡ የሃይማኖት ፡ ክርክር ፡ አላቋረጠም ፡ ነበር ። ንጉሡ ፡ የማይወዷቸውን ፡ ጳጳስ ፡ በዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ጊዜ ፡ መጥተው ፤ የነበሩትን ፡ አቡነ ፡ ክርስቶዶሉ ፡ ፪ኛን ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ልከው ፡ አቡነ ፡ ሲኖዳን ፡ አስመጡ ፤ ዕጨጌነቱንም ፡ ከአባ ፡ ዘክርስቶስ ፡ ላይ ፡ ወስደው ፡ ለአባ ፡ ሕርያቆስ ፡ ሰጧቸው ።

በዘመናቸው ፡ እንደዚሁ ፡ እነዚያ ፡ ባባታቸው ፡ ጊዜ ፡ ያውኩ ፡ ከነበሩት ፡ ነገዶች ፡ ውስጥ ፡ የሻንቅላ ፤ የሐንጋዝ ፤ የባንጋ ፤ የጋላ ፤ የዋጅራት ፡ ነገዶች ፡ ሸፈቱባቸው ። እርሳቸውም ፡ በየክፍሉ ፡ እንደራሴያቸውን ፡ ራስ ፡ (1) መልክአ ፡ ክርስቶስን ፡ የጦር ፡ አለቃቸውን ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ገብረ ፡ ልዑልን ፡ ሹማምንቶቻቸውን ፡ እነደጃዝማች ፡ አንስጣስዮስን ፡ እነደጃዝማች ፡ ሎሬንስን ፡ እነደጃዝማች ፡ ዘማርያምን ፡ ልከው ፡ እያ ዋጉ ፡ ራሳቸውም ፡ እነአቤቶ ፡ ዮስጦስ ፡ እነፊታውራሪ ፡ ወልዴ ፡ ቡሩክን ፡ እያስከተሉ ፡ ሄደው ፡ ካገር ፡ ወዳገር ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ሲዋጉ ፡ ሲያዋጉ ፡ ሰንብተው ፡ በመጨረሻ ፡ ጐንደር ፡ ገቡ ፤ ልጃቸውም ፡ አቤቶሁን ፡ ኢያሱ ፡ ተጣልተው ፡ ሸፍተው ፡ ነበር ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ ታርቀው ፡ ገቡ ።

በተረፈ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ (አእላፍ ፡ ሰገድ) ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ሲገዙ ፡ ከጦርነትና ፡ ከሌላ ፡ የተረፈውን ፡ ጊዜያቸውን ፡ ቅባቶችንና ፡ ተዋሕዶዎችን ፡ በማከራከር ፡ ያሳልፉ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

ዐፄ ፡ ዘድንግልና ፡ ሱስንዮስ ፡ ለካቶሊኮች ፤ ዐፄ ፡ ፋሲልና ፡ አብዛኞቹ ፡ የኢትዮ ጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ለተዋሕዶዎች ፡ ካሮች ፤ እነዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ እነዐፄ ፡ በካፋ ፡ ለጸጋ ፡ ልጆች ፡ ያደሉ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፤ እንደዚሁ ፡ ጻድቁ ፡ ዮሐንስ ፡ እምነታ ቸው ፡ ቅብዐት ፡ በመሆኑ ፡ ለነርሱ ፡ ያደሉ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በሳቸው ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ የጐጃም ፡ ቅባዐቶች ፡ እንደ ፡ ልባቸው ፡ ኖሩ ፡ ይባላል ። ለዚሁም ፡ ማስረጃ ፡ ዘታየስ ፡ ሣህሉ ፡ የሚባል ፡ የአኰስም ፡ ሰው ፡ ጐንደር ፡ መጥቶ ፡ ተምሮ ፡ በጣም ፡ ሊቅ ፡ የነ በረ ፡ ሃይማኖቱም ፡ ተዋሕዶ ፡ የሆነ ፤ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ጻድቁ ፡ ዮሐንስ ፡ በጉ ባኤ ፡ ተቀምጠው ፡ ቅባቶችና ፡ ጸጎች ፡ የሃይማኖታቸው ፡ ባህል ፡ ልዩ ፡ ሲሆን ፡ በቅብ ዐት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከበረ ፡ በማለት ፡ አንድ ፡ ናቸውና ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ ተዋሕዶ ዎች ፡ ከሌላው ፡ ወገን ፡ ሆነው ፡ እንዲከራከሩ ፡ ተደረገ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዘታየስ ፡ ሣህሉ ፡ ለተዋሕዶዎች ፡ አፈ ፡ ጉባኤ ፡ ሆኖ ፡ ቆመ ።

(1) መልክአ ፡ ክርስቶስን ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ በቢቶደድነት ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ በራስነት ፡ ይጠ ራቸዋል ፤ ይኸውም ፡ የራስ ፡ ቢቶደድነት ፡ ማዕርግ ፡ ለእንደራሴ ፡ የሚሰጥ ፡ ስም ፡ መሆኑ ፡ በራስ ፡ ቢቶ ደድ ፡ ተሰማ ፡ ሹመት ፡ ይታወቃል ።

እሱም ፡ እንደ ፡ ጳውሎስ ፡ ፊሊጥ ፡ ዐዋቂ ፡ ነበር ፡ ከዋናው ፡ ነገር ሳይደርስ ፡ ቅባቶችንና ፡ ጸጎችን ፡ ሃይማኖት ፡ አንዲት ፡ ናት ፡ ወይስ ፡ ሁለት ፡ ናት ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ።

እነሱም ፡ ዐውቀውበት ፡ አንዲት ፡ ናት ፡ ብንለው ፡ የናንተ ፡ ሃይማኖታችሁ ፡ ሁለት ፡ ነው ፡ ሊለን ፡ ነው ። ሁለት ፡ ናት ፡ ብንለው ፡ ጳውሎስ ፡ ሃይማኖት ፡ አንዲት ፡ ናት ፡ ብሏልና ፡ በዚህ ፡ ሊረታን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የሚሰጡት ፡ መልስ ፡ ተቸግረው ፡ ዝም ፡ ቢሉ ፤ ንጉሡ ፡ ለነሡ ፡ አድልተው ፡ ይህን ፡ ተውና ፡ ሌላ ፡ የሚገባ ፡ ጥያቄ ፡ አምጣ ፡ አሉት ። እሱም ፡ ማድላታቸውን ፡ ዐውቆ ፡ የሚገባ ፡ ጥያቄ ፡ እስከመጣ ፡ ቀን ፡ ይስጡኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። ንጉሡም ፡ ለዛሬ ፡ ሳምንት ፡ ብለው ፡ ቀጠሯቸውና ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሲመለሱ ፤ የጐንደር ፡ የከተማው ፡ መንገድ ፡ ጠባብ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ቅባቶችና ፡ ጸጎች ፡ በዚሁ ፡ መንገድ ፡ ሲያልፉ ፡ እንደ ፡ ዳኛ ፡ ማጣት ፡ መልከም ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ዛሬ ፡ ንጉሡ ፡ የኛ ፡ ወገን ፡ ባይሆኑ ፡ እውነተኛ ፡ ዳኛ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ዘታየስ ፡ ሣህሉ ፡ አስቀጥቶን ፡ ነበር ፡ እየተባባሉ ፡ ሲጫወቱ ፡ ዘታየስ ፡ ሣህሉ ፡ ከነሰዎቹ ፡ በዚሁ ፡ መንገድ ፡ ሲያልፍ ፡ ሰምቶ ፡ በነገሩ ፡ ስለ ፡ ተበሳጨ ፤ በዚያ ፡ ሌሊት ፡ መጽሐፎቹን ፡ አስጭኖ ፡ ተማሮቹን ፡ ይዞ ፡ ወገራ ፡ ደርሶ ፡ አደረ ። ከዚያ ፡ አገሩ ፡ አኰስም ፡ ገብቶ ፡ ተቀመጠ ፡ ይባላል ፡ ቢሆንም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ካሮች ፡ አሸናፊነትና ፡ በሕዝቡም ፡ ዘንድ ፤ መሰማት ፡ ነበራቸው ። በዚያም ፡ ወራት ፡ የነበረ ፡ ባለቅኔ ፡ በቅባቶች ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ተቀኘ ፡ ይባላል ።

መንበረ ፡ ኪሩባዊ ፤

እመ ፡ በቅብዐት ፡ ወረሰ ፡ ፍሬ ፡ ክርሥቲ ፡ ዕጹብ ፡
ዘቤተ ፡ ድንጋሌ ፡ ማርያም ፡ ርግብ ።
እስመ ፡ ከማሁ ፡ ኰልነ ፡ ሱቱፋነ ፡ ቅብዐት ፡ ሕዝብ ፡
እስፍንተ ፡ ይጸውር ፡ መንበሩ ፡ ለአብ ።
ወእስፍንተ ፡ ያገምር ፡ ኪሩብ ።

ትርጓሜ ።

የድንግልና ፡ ቤት ፡ ርግብ ፡ ማርያም ፡ ሆይ ፡ የማሕፀንሽ ፡ ፍሬ ፡ ክርስቶስ ፡ የኪሩቤልን ፡ ዙፋንነት ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዐት ፡ ካገኘ ፤ ሁላችንም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተቀብተናል ፡ የአብ ፡ ዙፋኑ ፡ ስንቱን ፡ ይሸከማል ፤ ኪሩብስ ፡ ስንቱን ፡ ይችላል ፤ ብሎ ፡ የቅብዐቶችን ፡ ሃይማኖት ፡ ነቀፎ ፡ ተገኘ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ከሺሕ ፡ ፯፻፳ ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፯፻፹፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ ገዝተው ፡ ሞቱ ። መንግሥታቸውንም ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፡ ልጃቸው ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፡ ያዙ ።

## የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ (አድያም ፡ ሰገድ ፡) ዘመነ ፡ መንግሥት ።

### ምዕራፍ ፡ ፵፰ ።

### የታላላቅ ፡ መሳፍንት ፡ መኳንንትና ፡ ሊቃውንት ፡ ዝርዝር ፡ – ስለ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አነጋገሥ ።

የቀዳማዊ ፡ ዮሐንስ ፤ የአድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፤ የበካፋ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ እንደ ፡ ቀሩት ፡ ነገሥታት ፡ በዘመናቸው ፡ በጸሐፌ ፡ ትእዛዛቸው ፡ በነወልደ ፡ ሃይማኖት ፡ (ሐዋርያ ፡ ክርስቶስ ፡) በነሲኖዳ ፤ በነአዛዥ ፡ ዘወልድ ፡ እንደዚሁም ፡ በንዳንድ ፡ ሊቃውንት ፡ እጅ ፡ እየተጻፈ ፡ ዛሬም ፡ በጐንደር ፡ በትግሬ ፤ በጐጃም ፤ በሸዋ ፤ በገዳም ፡ በደብር ፡ ወይም ፡ ባንዳንድ ፡ ታላላቅ ፡ መኳንንትና ፡ ሊቃውንት ፡ እጅ ፡ መገኘቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ከዚሁ ፡ ውስጥ ፡ በግዥም ፡ በዘረፋም ፡ ሄዶ ፡ በፓሪስና ፡ በሎንዶን ፡ በቤርሊንም ፡ መጻሕፍት ፤ ቤት ፡ የጥርቅም ፡ ተርታ ፡ (የኮሌክሲዮን ፡) ቍጥር ፡ እየተሰጠው ፡ በደንብ ፡ ተቀምጧል ። ኢኛሲዮ ፡ ጉዪዲ ፡ (IGNAZIO GUIDI) የነዚህን ፡ እላይ ፡ በስማቸው ፡ የተጠቀሱትን ፡ የሦስት ፡ ነገሥታት ፡ የዮሐንስን ፤ የኢያሱን ፤ የበካፋን ፡ ታሪክ ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈውን ፡ ታሪካቸውን ፡ እንዳለ ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ በማሳተም ፡ አሳትመውታል ። እኝህም ፡ ሊቅ ፡ እንዲታተምና ፡ እንዲራባ ፡ በማድረጋቸው ፡ ይመሰገናሉ እንጂ ፡ የግዕዙ ፡ ታሪክና ፡ የእጁ ፡ ጽሑፍ ፡ ግን ፡ እላይ ፡ እንደ ፡ ገለጽነው ፡ ባገራችን ፡ በያለበት ፡ አለ ።

እንግዴህ ፡ ስለ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አነጋገሥ ፡ ከመጻፋችን ፡ በፊት ፡ በዚህ ፡ ዘመንና ፡ ባባታቸው ፡ ዘመን ፡ የነበሩትን ፡ የመሳፍንት ፤ የመኳንንት ፤ የሊቃውንት ፡ ስምና ፡ ማዕርጋቸውን ፡ ከዚሁ ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ከተጻፈ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እየተ ፈላለግን ፡ የለቀምነውን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ በረድፍ ፡ ጽፈነዋል ። ይኸም ፡ ታሪኩን ፡ ስናነብ ፡ ስማቸውን ፡ ለመለየት ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ የዚያ ፡ ጊዜ ፡ የሹመትና ፡ የስም ፡ አጠራር ፡ ከዛሬው ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንደሚለያይ ፡ ለመገመት ፡ ያኸል ፡ ይረዳል ፡ በማለት ፡ ነው ።

### ንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ።

አቤቶ ፡ (ተ) ፡ ሁን ፡ ዮስጦስ ፡ (የአድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፡ ታላቅ ፡ ወንድም ፡)
  የሞቱ ፡

አቤቶ ፡ ወልደ ፡ ክርስቶስ ።
" አምባ ፡
" ድልበ ፡ ኢየሱስ ፡
" ሥዕለ ፡ መለኮት ፡
" ቴዎፍሎስ ፡
" ቅላዥ ፡ .....

<u>በቤተ ፡ መንግሥት ፡ በኩል ፡ ያሉ ፡ መኳንንት ።</u>

ራስ ፡ ቢቶደድ ፡ መልክአ ፡ ክርስቶስ ፡ (ብላቴን ፡ ጌታ ፡ የነበረው ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ቢቶደድ ፡ በመጨረሻ ፡ ራቀ ፡ ማሰሬ ፡ የተባለው ፡)
ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ገብረ ፡ ልዑል ፡ የታላላቅ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፤
የታላላቅ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ አካለ ፡ ክርስቶስ ፡ የጥቃቅን ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡
አይገበዝ ፡ (ግብዝ ፡ አይሁን ፡ ማለት ፡ ነውን ?)
ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ወልደ ፡ ሃይማኖት ፡ ሐዋርያ ፡ ክርስቶስ ።
ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ወልደ ፡ ክርስቶስ ፡
ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የሠራተኞች ፡ አለቃ ፡ ራሱም ፡ ሠሪ ? ፡

ደጃዝማች ፡ ሎሬንስ ፡
" አኖሬ ፡
" አልባስጥሮስ ፡
" ዘማርያም ፡
" አዳዎ ፡
" እንስጣስዮስ ፡ (ወደ ፡ ፊት ፡ ራስ ፡ ቢቶደድ ፡ የተባለው ፡)
" ፋሬስ ፡ (ከራስ ፡ ቢቶደድ ፡ አንስጣስዮስ ፡ በኋላ ፡ የእንደራሴነትን ፡ ማዕርግ ፡ የወሰደው ።
" ድልበ ፡ ኢየሱስ ፡ (አቤቶ የተባለው ፡ ይሆን ፡ ?

አሥራት ዘስሜን ፡ አጋፋሪ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ የተባለው ።

ደጃዝማች ጣሚ ፡ የጐጃም ፡ ገዥ ።
" ድምያኖስ ፡ የአማራ ፡ ሣይንት ፡ ገዥ ።
" ድሜጥሮስ ፡ የሸዋ ፡ ገዥ ።

አዛዥ ፡ ወልደ ፡ ትንሣኤ ።
" ዘመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (ልጃቸው ፡)
" ዘወልድ ፡
" ከናፍሮ ።

አዛዥ ፡ ሐዋርያ ፡ እርሱም ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ገ/ንጥራር ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ የሆነው ፡ ይመስላል ።
ፊታውራሪ ፡ ፍሣ ፡ ክሶስ ፡ (ፍሥሐ ፡ ክርስቶስ) ።
ፊታውራሪ ፡ ያዕቆብ ።
" ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡
ቀኛዝማች ፤ ዘወልድ . (ወልድ) ፡
" ሐዋርያ ፡ (ሐዋርያ ፡ ክርስቶስ) ፡
" አትናቴዎስ ፡
" ገቾ ፡

ግራዝማች ፡ ሚካኤል ፡ (ዘሚካኤል) ፡
፡፡ ጥቍሬ ፡
፡፡ አቤትዬ ፡
በትረ ፡ ኀይል ፡ በኋላ ፡ ቀኛዝማች ፡ የተባለው ።
በጅሮንድ ፡ ዐስበ ፡ (የአንበሳ ፡ ቤት ፡ ኀላፊ) ፡
ባሻ ፡ ልሳነ ፡ ክርስቶስ ፡
ባሻ ፡ ሩሩ ፡
ማኀደሮ ፡ ውዝፍ ፡ ጠባቂ ፡ (ሒመተ ፡ እብሬት ፡ ወርተረኛን ፡ አስተዳዳሪ) . . . . . . . ።

## የቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣኖች ።

ከአባ ፡ ክርስቶዶሉ ፡ (ክርስቶስ ፡ (ደወሉ ?) ፡
በኋላ ፡ የተሾሙት ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ።
ከአባ ፡ ክርስቶስ ፡ በኋላ ፡ የተሾሙት ፡ ዕጨጌ ፡ ሕርያቆስ ፡

| | |
|---|---|
| ቄስ ፡ ዐፄ ፡ (ቀይስ ፡ ዐፄ) ፡ አባ ፡<br>አሠረ ፡ ክርስቶስ ፡<br>ዐቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ቄስጠንጢኖስ ።<br>ጽራግ ፡ ማሰሬ ፡ መልክአ ፡ ክርስቶስ ፡<br>ጽራግ ፡ ማሰሬ ፡ ቀውስጦስ ፡<br>ሊቀ ፡ ካህናት ፡ አባ ፡ ዘወልድ ፡ . . . . . . ፡ | ሥራቸው ፡ ከቤተ ፡ ክህነትና ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፤ |

ደግሞ ፡ የታላላቅ ፡ ገዳማት ፡ የቤተ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትና ፡ የቤተ ኤውስጣቴዎስ ፡ የመጉዳና ፡ አበ ፡ ምኔቶችና ፡ መምህራን ፡ መነኰሳትና ፡ ቀሳውስት ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

እነዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፉት ፡ የቤተ ፡ መንግሥትና ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሹማምት ፡ ግማሾቹ ፡ ከዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ዠምረው ፡ ሲሻሩ ፡ ሲሾሙም ፡ እስከ ዚህ ፡ ጊዜ ፡ የደረሱ ፤ ግማሾቹ ፡ ባሁኑ ፡ በአፄ ፡ ዮሐንስና ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ዘመን ፡ የተነሡ ፡ ናቸው ፤ እነሱም ፡ በየጊዜው ፡ ሹመት ፡ ለሹመት ፡ እየተቀያየሩ ፡ የተሰጣቸውን ፡ ሥራ ፡ የሚያስኬዱ ፡ ገሚስቹም ፡ በየጊዜው ፡ ማዕርግ ፡ የጨመሩ ፡ ገሚሶቹም ፡ የታሰሩ ፡ የተጋዙ ፡ ናቸው ፤ የያንዳንዳቸውን ፡ ተግባር ፡ ባለፈው ፡ በምዕራፍ ፡ ፲፱ ፡ በመጠኑ ፡ ገልጸናልና ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ እንመለስ ።

አድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፡ አባታቸው ፡ እኙሁ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስና ፡ ቀዳማዊ ፤ እናታቸው ፡ እቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ናቸው ፤ የእቴጌይቱ ፡ አባት ፡ የመደበዩ ፡ ባላባት ፡ አቤተሁን ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ይባላሉ ።

ታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ ስለ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፤ እንደዚህ ፡ ይላል፡ አእላፍ ፡ ሰገድ ፡ ዮሐንስና ፡ እቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ኢያሱን ፡ በወለዱ ፡ ጊዜ ፡ እነሱ ፡ ራሳቸው ፡ ንጹሐንና ፡ ጻድቃን ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ልጃቸውንም ፡ ኢያሱን ፡ መጻሕፍት ፡ ቅዱሳትን ፡ እያስተማሩ ፡ በተግሣፅ ፡ በጥበብ ፡ በንጽሕና ፡ በቅድ ስና ፡ .... አሳደጓቸው ። ከዚያም ፡ ፈረስ ፡ ግልቢያን ፡ ጦርነትን ፡ ውሃ ፡ ዋናን ፡ ..... አስተማሯቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡ ተገለጸው ፡ አባታቸው ፡ ዐፄ፡ ዮሐንስ ፡ በሺሕ ፡ ፯፻፳ ፡ ዓ ፡ ም ሐምሌ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ሲሞቱ ፡ ታላላቆቹ ፡ ሹማ ምቶች ፡ እነብላቴን ፡ ጌታ ፡ አካለ ፡ ክርስቶስ ፡ እነደጃዝማች ፡ አንስጣስዮስ ፡ ስመ ፡ መንግሥታቸውን ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ አሰኝተው ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ ሥርዐተ ፡ ንግሡም ፡ ዐዋጁም ፡ ተፈጽሞ ፡ አነገሧቸው ። ሲነግሡም ፡ ኻያ ፡ ዓመ ታቸው ፡ ነበር ፡ ይባላል ፡ በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ በከተማም ፡ በባላገርም ፡ ግርግርታ ፡ አልተደረገም ። ነገር ፡ ግን ፡ ወንድሞቻቸው ፡ አቤቶ ፡ ሁን ፡ ቴዎፍሎስና ፡ አቤቶ፡ ሁን ፡ ቅላዣ(ዥ) ፡ በከተማ ፡ ነበሩና ፡ ለጊዜው ፡ ስለጸጥታው ፡ ሲባል ፡ በነሐሴ፡ ወር ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ወዳሉበት ፡ ወደወህኒ ፡ አምባ ፡ ሄደው ፡ በመልካም ፡ አኗኗር፡ እንዲኖሩ ፡ ተደረገ ።

ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ወዲያው ፡ የንጉሥነት ፡ ሥራቸውን ፡ እንደ ፡ ዠመሩ ፡ በ፫ኛው ፡ ወር ፡ በመስከረም ፡ ለእህታቸው ፡ ለወይዘሮ ፡ እሌኒ ፡ ስሜ ንን ፤ ለደጃዝማች ፡ አንስጣስዮስ ፡ የራስ ፡ ቢቶደድነት ፤ (የእንደራሴነት) ፡ ማዕ ርግ ፡ ጨምረው ፡ የዳሞትን ፡ ግዛት ፤ ለፊታውራሪ ፡ ፍሥሐ ፡ ክርስቶስ ፡ ጐጃምን፡ ለአጋፋሪ ፡ አሥራት ፡ በጌምድርን ፤ ለፋሬስ ፡ የእብናትን ፤ የማያን ፡ የቆላ ፡ ግዛ ትን ፡ ለዐስበ ፤ በጅሮንድነትን ፡ ለማሞ ፤ የጥቃቅን ፡ ብላቴን ፡ ጌትነትን ፡ ለማ ኅደሮ ፡ ውዝፍ ፤ (እብሬት ፡ ጠባቂነትን ፡ የተረኛን ፡ አስተዳዳሪነት ?) እንደዚሁ ፡ በቤተ ፡ ክህነት ፡ ክፍል ፡ በአባ ፡ ዘክርስቶስ ፡ ፈንታ ፡ እጨጌ ፡ ሕርያቆስን ፤ በዐ ቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ፈንታ ፡ አባ ፡ አሠረ ፡ ክርስቶስን ፡ የሾሙት ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ይኸንም ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ ሲያደርጉ ፡ የቀሩት ፡ ነገሥታት ፡ እንደሚያደርጉት ፡ የማይስማሟቸውን ፡ ርስት ፡ ጕልት ፡ በመስጠት ፡ እየተው ፡ የሚስማሟቸውንና ፡ የሚወዷቸውን ፡ እየመረጡ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፵፱ ።

## ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ በየጊዜው ፡ የፈጸሙት ፡ ሥራ ።

ታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ወሩንና ፡ አበቅቴውን ፡ እንጂ ፡ ዓመ ቱን ፡ እየለየ ፡ ለሚሰጠው ፡ አሳብ ፡ በነቀፋና ፡ በምስጋና ፡ በማመዛዘን ፡ ሰፊ ፡ ሐተታ ፡ መስጠት ፡ ባይመቸውም ፡ ንጉሡ ፡ በየጊዜው ፡ የፈጸሙትን ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ይዘረዝራል ።

፩ኛ ፡ በጥቅምት ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ቤተ ፡ ኤውስጣቴዎስና ፡ ቤተ ፡ ተክለ ፡ ሃይ ማኖት ፡ የሚባሉት ፡ የቀሳውስት ፡ ወገኖች ፤ በሃይማኖት ፡ ተጣልተው ፡ ያከራክ

ሩን ፡ ሲሉ ፡ ቢመጡባቸው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በባቴ ፡ በአእላፍ ፡ ሰገድ ፡ ጊዜ ፡ ዐቃቤ ፡ ሰዓት ፡ አባ ፡ አሰረ ፡ ክርስቶስና ፡ ቄስ ፡ ዐፄ ፡ አባ ፡ ማቴዎስ ፡ ባሉበት ፡ ተከራ ክራችሁ ፡ እንደ ፡ ተወሰነው ፡ በዚያው ፡ እንዳለ ፡ ይቆይ ፡ ሲሉ ፡ ፈርደው ፡ አሰ ናበቷቸው ።

፪ኛ ፡ እጨጌ ፡ አባ ፡ ሕርያቆስ ፡ ከመጉና ፡ አስመጥተው ፡ የደብረ ፡ ሊባ ኖስን ፡ መምህርነት ፡ አክሊልና ፡ ሽልማት ፡ ሰጥተው ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ሾሟ ቸው ። ዕጨጌው ፡ የማዕርግ ፡ ልብሳቸውን ፡ ለብሰው ፡ አክሊላቸውን ፡ ደፍተው ፡ በካህናትና ፡ በቀሳውስት ፡ ታጅበው ፡ እፊት ፡ እፊት ፡ ሲሄዱ ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ዘውዳቸውን ፡ አድርገው ፡ በትረ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ይዘው ፡ በፈረስ ፡ ሆነው ፡ ከመኳንንቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ በስተኋላ ፡ ያጅቧቸው ፡ ነበር ። ይኸንንም ፡ ያደረጉት ፡ ከልባቸው ፡ የሚወዷቸውን ፡ አቡነ ፡ ተክለ ሃይማኖትን ፡ ለማስደሰት ፡ ሲሉ ፡ ነው ።

፫ኛ ፡ ባለፉት ፡ ነገሥታትና ፡ በርሳቸውም ፡ ጊዜ ፡ እየሸፈቱም ፡ እየተጠረጠ ሩም ፡ ዳግም ፡ ሳይሸፍቱም ፡ ሳይጠረጠሩም ፡ ድንገት ፡ ሰው ፡ ይዘው ፡ ግርግር ፡ እን ዳያነሡ ፡ ለጸጥታ ፡ ጥበቃ ፡ ሲባል ፡ እንደዚያ ፡ ጊዜ ፡ ልማድ ፡ እየተሰበሰቡ ፡ በወህኒ ፡ አምባ ፡ የተቀመጡትን ፡ የነጋሢ ፡ ዘሮች ፡ እወህኒው ፡ አምባ ፡ ድረስ ፡ ራሳቸው ፡ ሄደው ፡ ስጦታም ፡ ግብዝም ፡ አደረጉላቸው ። ከዚሁም ፡ ውስጥ ፡ የራሳቸውን ፡ ወን ድሞች ፡ አቤቶሁን ፡ ቴዎፍሎስንና ፡ አቤቶሁን ፡ ቀላዝ ፡ (ዢ)ን ፡ የዐፄ ፡ ሱስንዮስንና ፡ የዐፄ ፡ ፋሲልንም ፡ ተወላጆች ፡ ከወህኒው ፡ ወደ ፡ ከተማቸው ፡ አውርደው ፡ እማዕ ርግ ፡ በታ ፡ አስቀምጠው ፡ ታላቅ ፡ ግብር ፡ አደረጉላቸው ፤ ከግብርም ፡ በኋላ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሽልማት ፡ አስደሰቷቸው ። እነሱም ፡ (እኛን ፡ በወህኒ ፡ አምባ ፡ ተረስተን ፡ የነ በርነውን ፡ ሰዎች ፡ ፈተኸ ፡ ለዚህ ፡ ደስታና ፡ ማዕርግ ፡ እንዳበቃኸን ፡ እግዚአብሔ ርም ፡ መንግሥትኸን ፡ ከልጅ ፡ ልጅኸ ፡ አያውጣው) ፡ እያሉ ፡ መረቋቸው ።

፬ኛ ፡ ከጐንደር ፡ ተነሥተው ፡ በቃሮዳ ፡ በሐመድ ፡ በር ፡ አድርገው ፡ አሪንጎ ፡ ከነጓዛቸው ፡ ሠፈሩ ። በዚያም ፡ በጥር ፡ ፬ ቀን ፡ ታማኛቸውንና ፡ ዐዋቂውን ፡ ተስፋ ፡ ልዑልን ፤ ያምባሰሉን ፡ ዠንጥራር ፡ (ጽራር) ፡ ሐዋርያን ፡ ይዘኸ ፡ እሠር ፡ ሲሉ ፡ ማኅ ተማቸውን ፡ ሰጥተው ፡ ላኩት ። እርሱም ፡ አምባሰል ፡ ሄዶ ፡ ያለውጊያ ፡ በብልሃት ፡ ዠንጥራር ፡ ሐዋርያን ፡ ከነገንዘቡ ፡ ከነመሣሪያው ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አመጣውና ንጉሡ ፡ በደባባይ ፡ ወቅሰው ፡ ወደ ፡ ሠራዊ ፡ ልከው ፡ በግዞት ፡ አስቀመጡት ። ከዚ ያም ፡ ተነሥተው ፡ ንጉሡ ፡ በመጋቢት ፡ ፪ ቀን ፡ በአምባ ፡ ጐንዳ ፡ በጥንጁት ፡ አል ፈው ፡ ጀፍጀፍ ፡ ደረሱ ፡ በዚያም ፡ በመጋቢት ፡ ፰ ፡ ቀን ፡ የአቡነ ፡ ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በዓል ፡ አክብረው ፡ ከጀፍጀፍ ፡ በታምሬ ፡ በኩል ፡ አድርገው ፡ ይባባ ፡ ገቡ ፡ በዚያም ፡ በመጋቢት ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ አክለ ፡ ክርስቶስንና ፡ አዛዥ ፡ ከናፍሮን ፡ ሽረው ፡ ለባሻ ፡ ሩሩ ፡ የብላቴን ፡ ጌትነትን ፤ ለጴጥሮስ ፡ ራቅ ፡ ማሰሬነትን ፡ ሰጥ ተው ፡ ከዚያ ፡ በየደሴቱ ፡ ያሉትን ፡ ያበቶቻቸው ፡ ትክል ፡ የሆኑትን ፡ አብያተ ፡

ክርስቲያናት ፡ ጐብኝተው ፡ ወደ ፡ ይበባ ፡ ተመለሱ ፡ በግንቦት ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ከይበባ፡ ተነሥተው ፡ በዲማ ፡ ባመዳሚት ፤ በጕምብሌ ፡ በኩል ፡ አልፈው ፡ ቡጥላ ፡ ሠፈሩ ። በዚያም ፡ በግንቦት ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ በዓል ፡ አክብረው ዋሉ ፤ ከቡጥላ ፡ በየሌማት ፡ በኩል ፡ አልፈው ፡ መራሪት ፡ ሠፈሩ ።

፰ኛ ፤ መራሪት ፡ ሠፍረው ፡ ሳሉ ፡ በዐባይ ፡ ዳር ፡ አጠገብ ፡ ደበል ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ የጐሽ ፡ መንጋ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ፩ ፡ ዐዋቂ ፡ ተናገረ ። ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ይኸን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ አያታቸው ፡ እንደ ፡ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ አደን ፡ ማደን ፡ ይወዱ፡ ነበረና ፡ ከጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ በቶሎ ፡ ወደዚሁ ፡ ሥፍራ ፡ ሔዱ ። እንደ ፡ ደረሱም ፡ አንድ ፡ ጐሽ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ በትር ፡ በጦር ፡ ወግተው ፡ ገደሉ ፤ ቀጥለው ፡ ከሰዎቻቸው ፡ ተለይተው ፡ እያባረሩ ፡ አንድ ፡ ሴት ፡ ጐሽ ፡ አግኝተው ፡ ቢወጓት ፡ ኀይለኛ ፡ ጐሽ ፡ ነበረችና ፡ እንደ ፡ ቈሰለች ፡ ተናንቃ ፡ ከፈረስ ፡ ላይ ፡ ገለበጠቻቸው ። ወዲያውም ፡ እርሷ ፡ እንደ ፡ ቈሰለት ፡ እርሳቸውንም ፡ እግራቸውን ፡ ወግታ ፡ አቈሰለቻቸው ፤ እንዲያውም ፡ ልትገድላቸው ፡ ምንም ፡ አልቀራትም ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን፡ ከጉታ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ጐር ፡ ድፍጫ ፡ የሚባል ፡ ድንገት ፡ ደርሶ ፡ (1) ጐሿን ፡ ገድሎ ፡ እርሳቸውንም ፡ ከወደቁበት ፡ አንሥቶ ፡ ከሞት ፡ አዳናቸው ።

፱ኛ ፤ ግንቦት ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ከመራሪት ፡ ተነሥተው ፡ በደምበጫ ፡ አልፈው ፡ ቊልቢጥ ፡ ደረሱ ። በዚያም ፡ በሰነበቱበት ፡ ጊዜ ፡ ከጨዋ ፡ ክፍል ፡ አንድ ፡ የወታደር፡ መኰንን ፡ ቀርቦ ፡ የሊበን ፡ ጋሎች ፡ ጐጃምን ፡ ወረሩት ፡ ሲል ፡ ለንጉሡ ፡ ተናገረ። ንጉሡም ፡ ይኸን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከነመኳንንቶቻቸው ፡ በግሥጋሤ ፡ ደሆ ፡ ደረሱ ። ጋሎቹም ፡ ይኸን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ የማረኩትን ፡ ከብትና ፡ ዕቃ ፡ ትተው ፡ ዐባይ፡ (ዊ)ን ፡ ተሻግረው ፤ በሽሽት ፡ ወዳገራቸው ፡ ተመለሱ ፡ ንጉሡም ፡ ከደሆ ፡ ወደ፡ ሠፈራቸው ፡ ወደ ፡ ቊልቢጥ ፡ ሄደው ፡ ከጓዛቸው ፡ ተገናኙ ። ከዚያም ፡ በያገሩ ፡ ዘረው ፡ ሲጨርሱ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ቀን ፡ በሰላምና ፡ በደስታ ፡ ጐንደር ፡ ከዋና ፡ ከተማቸው ፡ ገቡ ።

፲ኛ ፤ ጐንደር ፡ እንደ ፡ ገቡ ፡ በ፱ኛው ፡ ወር ፡ በመስከረም ፡ ጳጳሱን ፡ አባ ፡ ሲኖዳን ፡ ዕጨጌውን ፡ አባ ፡ ሕርያቆስን ፡ አስጠርተው ፡ በነርሱ ፡ አማካይነት ፡ መጽሐፈ ተክሊል ፡ ተነበ ፡ ሥርዓተ ፡ ጋብቻ ፡ በደንብ ፡ ተፈጽሞ ፡ ወለተ ፡ ጽዮን ፡ የምትባለውን ፡ ወጣት ፡ በሠርግ ፡ አገቡ ። ወለተ ፡ ጽዮን ፡ በሐማሴን ፡ በተለይ ፡ ምድረ ፡ በቊላ ፡ ከሚባለው ፤ አገር ፡ ከደቀ ፡ አስገዴ ፡ ነገድ ፡ የሆነው ፡ የሀብተ ፡ ኢየሱስ ፡ ልጅ ፡ ናት ። ወለተ ፡ ጽዮንም ፡ ከሐማሴን ፡ ለዚሁ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ጋብቻ ፡ ስትመጣ ፡ በአኵስም ፡ በኩል ፡ ስታልፍ ፡ ካህናቱ ፡ መርቀው ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ እንደ ፡ ሰደዷት እርሷም ፡ መልክ ፡ መልካም ፡ ቆንጆ ፡ እንደ ፡ ነበረች ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ይነግረናል ።

(1) የግዕዙ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ (ይእተ ፡ ጊዜ ፡ አብጽሖ ፡ እግዚአብሔር ፡ በክንፈ ፡ መልአኩ ፡ ገብርኤል ፡ ለጐር ፡ ድፍጫ ፤ . . . . . . ወቀተላ ፡ ለይእቲ ፡ ጐሽ ፡ —በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ በገብርኤል ፡ ክንፍ፡ጐር፡ ድፍጫን ፡ አመጣው ፡ እርሱም ፡ ጐሽዋን ፡ ገደላት) ፡ ይባላል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፱ ።

### ስለ ፡ ወሬኛ ፡ ይስሐቅ ፡ ጦርነትና ፡ ስለፍጻሜው ።

በዚህ ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ ዓይነት ፡ በየቀኑ ፡ ንጉሡ ፡ የሄዱበትን ፡ አገር ፡ እየጠቀስን ፡ ያደረጉትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መጻፍ ፡ ሥራው ፡ ቀላል ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ላንባቢ ፡ እንደሚሰለችና ፡ እንደማይጥም ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በታሪከ ፡ ነገሥቱና ፡ በሌሎችም ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፎች ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ እያጋጠመን ፡ በጠቅላላው ፡ ለመጻፍ ፡ ስንል ፡ አሁን ፡ ንጉሡ ፡ በጋሎች ፡ ላይ ፡ ሁለተኛ ፡ ያደረጉትን ፡ ጦርነት ፡ እንጽፋለን ።

እንደ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ አቈጣጠር ፡ በነገሡ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ደጃዝማች ፡ ጣሜ ፡ በሚገዛበት ፡ በጐጃም ፡ በኩል ፡ የቱለማ ፡ ጋሎች ፤ በወሎ ፡ ደግሞ ፡ የውጫሌና ፡ የከረዩ ፡ ዘሮች ፡ ተነሥተው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አገር ፡ ወረሩ ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ መጣ ። ንጉሡም ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ የዳሞቱን ፡ ገዥ ፡ እንደራሴያቸውን ፡ ራስ ፡ አንስጣስዮስን ፡ ልከው ፡ ርሳቸው ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ሄዱ ። ጋሎቹ ፡ ግን ፡ አሁንም ፡ የንጉሡን ፡ መምጣት ፡ ቢሰሙ ፡ የዘረፉትን ፡ ዘርፈው ፡ ሸሹ ፤ ንጉሡም ፡ ከዚያ ፡ ተመልሰው ፡ የጋላ ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ በረታበት ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ ሄዱ ። በዚያም ፡ በራስ ፡ አንስጣስዮስ ፡ የሚመራው ፡ ጦር ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ንጉሡ ፡ ከሠራዊታቸው ፡ ጋራ ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ ሲዋጉ ፡ ዋሉ ። በጦርነቱም ፡ ውስጥ ፡ ንጉሡ ፡ ራሳቸው ፡ ገብተው ፡ ሲዋጉ ፡ አንድ ፡ ኀይለኛ ፡ የጋላ ፡ ቀስተኛ ፡ በዛፍ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ በቀስት ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ሲፈጅ ፡ አይተው ፡ በጠመንዣ ፡ አነጣጥረው ፡ ቢመቱት ፡ ከዛፍ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ወደቀ ፡ ይባላል ። በዚህም ፡ ጦርነት ፡ ምንም ፡ የከረዩና ፡ የውጫሌ ፡ ጋሎች ፡ በኃይል ፡ ቢዋጉ ፡ ከመሸነፍ ፡ አልዳኑምና ፤ ሁሉም ፡ በያለበት ፡ ሸሹ ። ንጉሡም ፡ የግንቦት ፡ ማርያም ፡ ለት ፡ ሺህ ፡ ፯፻፸፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጋሎችን ፡ ስላሸነፉ ፡ ለመርጡለ ፡ ማርያም ፡ ብፅዓት ፡ አድርገው ፡ የነበረውን ፡ ለመፈጸም ፡ ሲሉ ፡ አዛዥ ፡ ዘመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ጠርተው ፡ የተለየ ፡ ጕልት ፡ ለታቦቷ ፡ እንዲሰጥ ፡ አዘዙና ፡ በደስታ ፡ ምርኳቸውን ፡ ይዘው ፡ ጐንደር ፡ ተመለሱ ። ቢሆንም ፡ ከዚህ ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ ሰላም ፡ ገና ፡ አልተገኘም ።

የጐጃም ፡ ካህናትና ፡ ቀሳውስት ፡ ከዚያውም ፡ በተለይ ፡ ደብረ ፡ ወርቆች ፡ ቅባቶች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ በዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ባለሟል ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፤ የጐጃምና ፡ የዳሞት ፡ ገዥዎችም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በቅብዐት ፡ ሃይማኖት ፡ ያሉት ፡ እየተመረጡ ፡ እየተሾሙ ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ሕይወት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ በደስታ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ እርሳቸው ፡ ሞተው ፡ ልጃቸው ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፡ ስለ ፡ ነገሡ ፡ የርሳቸውም ፡ ሃይማኖት ፡ እንደ ፡ ግማሾቹ ፡ ጸጋ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹም ፡ ታሪክ ፡ ተዋሕዶ ፡ (ካራ) ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በጐጃሞቹና ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ መካከል ፡ ቅያሜ ፡ አደረ ።

ስለዚህ ፡ በሹመት ፡ ቅያሜ ፡ የነበረው ፡ ደጃች ፡ ወሌ ፡ እነአባ ፡ ተድባበን ፡ ይዞ ፡ የጐጃምን ፤ የሜጫን ፤ የጉዱሩን ፤ የጃዊን ፤ የጠብደንን ፡ ተወላጆች ፡ አሳ ድሞ ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ተነሣ ፡ ሲነሣም ፡ የዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ የሚለውን ፡ ወሬኛ ፡ (1) ፡ ይስሐቅ ፡ አሰኝቶ ፡ አነገሠው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ አድርገው ፡ የጐጃምን ፡ አውራጃ ፡ በግዛት ፡ ተከፋፈሉት ። ከዚህ ፡ እነዚሁ ፡ ለጦርነት ፡ እሦስት ፡ ላይ ፡ ተከፍለው ፡ ግማሾቹ ፡ በዋሚት ፤ ግማሾቹ ፡ በሙተራ ፤ ግማሾቹ ፡ በባሶ ፡ አድርገው ፡ ጕዞ ፡ ዠመሩ ። የጐጃምን ፡ ግዛት ፡ ከዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ተሾሞ ፡ የሚገዛው ደጃች ፡ ጣሜ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ያውቅ ፡ ነበርና ፤ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ለንጉሡ ፡ በመልክት ፡ አስታ ወቀ ። ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ይኸን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ሠራዊታቸውን ፡ አስከትተው ፡ በቶሎ ፡ አዲስ ፡ (በጐዛም) ፡ ወደሚባለው ፡ መሬት ፡ ቀትን ፡ በፀሐይ ፡ ሌሊቱን ፡ በፋና ፡ (በሙብራት) ፡ ገሥግሠው ፡ ጎሕ ፡ ሲቀድ ፡ (ሲነጋ) ፡ ደረሱባቸው ። እንደ ፡ ደረሱም ፡ ሠራዊታቸውን ፡ በያለቃው ፡ ከፋፍለው ፡ በሰንተራ ፡ ሜዳ ፡ አሰልፈው ፡ ለውጊያ ፡ ተዘጋጁ ። በዚሁ ፡ ሜዳ ፡ ሰልፍ ፡ ሲያደራጁ ፡ የወታደሮቻቸውና ፡ የሹ ማምንቶቻቸው ፡ የወርቅና ፡ የብሩ ፡ ጋሻና ፡ ጥሩር ፡ ጐራዴና ፡ ጦር ፡ ከጧቱ ፡ ጮራ ፡ ጸዳል ፡ ጋራ ፡ እየተያየ ፡ ሲያብረቀርቅ ፤ የነጋሪቱና ፡ የመለከቱ ፡ ድምፅ ፤ የመድፉ ፡ ጩኸት ፡ እንደ ፡ ነጐድጓድ ፡ ሲጮኽና ፡ ሲያስተጋባ ፡ የሽፍቶቹ ፡ ወገኖች ፡ በሰሙትና ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ መብረቅ ፡ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ መስሏቸው ፡ በድንጋጤ ፡ ተሸበሩ ። (2) ፡ ቢሆንም ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ተጽናንተው ፡ ትንሽ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተዋጉ ፡ ሸሽት ፡ ዠመሩ ። ይኸውም ፡ በንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ በታ ወቀ ፡ ጊዜ ፡ እነሱን ፡ በየሸሹበት ፡ እየተከታተለ ፡ እንዲዋጋ ፡ ራሱም ፡ የጐጃም ፡ ገዥ ፡ ደጃች ፡ ጣሜ ፡ ከጭፍራ ፡ ጋራ ፡ ታዘዘ ። እርሱም ፡ ዱካ ፡ በዱካ ፡ እየተከ ታተለ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ፈጀ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ደጃች ፡ ጣሜ ፡ የዐባይ ፡ ወንዝ ፡ ከሸሺዎቹ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ጨረሰ ። በዐባይ ፡ ዳርና ፡ ዳር ፡ ያለው ፡ የጕመ ሮና ፡ የቀንጠፋ ፡ እሾኽ ፡ የብዙዎቹን ፡ ጋሎች ፡ ልብስ ፡ እየገፈፈ ፡ አስቀረ ።

በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ደጃች ፡ ጣሜ ፡ የገደለውን ፡ ገድሎ ፡ የማረከውን ፡ እሬት ፡ እሬት ፡ እየነዳ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጥቶ ፡ ግዳይ ፡ ጣለላቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ እንዶድ ፡ መሬት ፡ ሄደው ፡ የጋሎቹ ፡ መምጫ ፡ ነው ፡ የተባለውን ፡ በር ፡ አዘግተው ፡ ከዚያ ፡ በየጫካው ፡ ዝሆን ፡ እያደኑ ፡ አል ፈው ፡ ዱቂ ፡ ሠፈሩ ። በኋላ ፡ ከወሬኛ ፡ (ይስሐቅ) ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ደጃች ፡ ወሌና ፡ ጠብዱ ፡ ግን ፡ ውለው ፡ አድረው ፡ ጳጳሱን ፡ አባ ፡ ሲኖዳን ፡ አማላጅ ፡ ልከው ፡ ከንጉሡ ፡ ታርቀው ፡ ገቡ ።

(1) ነጋሢ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ እያስወራ ፡ የሸፈተ ው ፡ ሁሉ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወሬኛ ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ ይሰጠዋል ።

(2) ታሪክ ፡ ነገሥቱን ፡ የጻፈው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የንጉሡ ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ በመሆኑ ፡ የዚህኑ ፡ ጉዳይ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ለማጋነን ፡ ሲፈልግ ፡ ይኸን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ዳታንና ፡ አቢሮን ፡ መሬት ፡ ተከፍታ ፡ በዋጠችን ፡ ሰማይም ፡ በተደፋብን ፡ አሉ ፡ ብሎ ፡ ጽፎታል ።

ይስሐቅ ፡ ተብሎ ፡ የነገሠው ፡ ወሬኛ ፡ ግን ፡ ከጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ ከጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ አምልጦ ፡ ወደ ፡ አማራ ፡ ሣይንት ፡ ኖሮ ፡ ከዚያም ፡ ካገረ ፡ ገዥው ፡ ከደጃች ፡ ድምያኖስ ፡ ጋራ ፡ የተከተሉትን ፡ አማሮችና ፡ ጋሎች ፡ ይዞ ፡ ተዋግቶ ፡ አሁንም ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ካስጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ዞረ ። በዚያም ፡ አንድ ፡ ከጐንደር ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ የመጣ ፡ አውስግንዮስ ፡ የሚባል ፡ በጣም ፡ የተማረ ፡ ሊቅ ፡ በምንኵስና ፤ በመምህርነት ፡ ይኖር ፡ ነበር ። እርሱም ፡ ወሬኛ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እያለ ፡ ሰውን ፡ ሲያሳድም ፤ ሃይማኖትንም ፡ ሲያስክድ ፡ አግኝቶ ፡ በሃይማኖቱም ፡ ክርክር ፡ ረቶ ፡ ገርፎ ? ወደ ፡ ቀናችው ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲመለስ ፡ አደረገው ። ቢሆንም ፡ ወሬኛ ፡ ከአውስግንዮስና ፡ ከሸዋ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ከደጃች ፡ ድሜጥሮስ ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ዜጋመል ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሄዶ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተቀመጠ ። በዚያም ፡ ሳለ ፡ እኔ ፡ የነገሥታት ፡ ዘር ፡ ስለሆንኩ ፡ እነግሣለሁና ፡ ተከተሉኝ ፡ እያለ ፡ እየሰበከ ፡ በርሱ ፡ ስብከት ፡ ባላገሮችና ፡ ወስላቶች ፡ እንዲከተሉት ፡ አደረገ ። በዚህም ፡ ሳለ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በጐጃም ፡ እንዳደረገው ፡ ድባብ ፡ (ትልቅ ፡ ጃንጥላ) ፡ እያስያዘ ፡ ነጋሪት ፡ ያስመታ ፡ ጀመር ።

የዚህንም ፡ ነገር ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ በአሪንጎ ፡ ሳሉ ፡ ይሰሙ ፡ ነበርና ፡ እንደ ፡ ምንድነው ፡ የወሬኛ ፡ ነገር ፡ ያለበትስ ፡ ትክክለኛ ፡ ሥፍራ ፡ ወዴት ፡ ነው ? ለመያዝስ ፡ የሚቻልበት ፡ መንገድ ፡ እንደምን ፡ ይመስልኻል ? ስለዚህ ፡ እኛም ፡ ብንመጣ ፡ ሰውም ፡ ብንልክ ፡ ለመያዝ ፡ የሚቻልበትን ፡ ብልኀት ፡ አጥንተኽ ፡ ላክብን ። እስከዚያም ፡ አንተ ፡ ራስህ ፡ በጥበብና ፡ በብልኀት ፡ ወሬኛን ፡ ለመያዝ ፡ ብትችል ፡ የያዝከውን ፡ የሸዋን ፡ ግዛት ፡ ካንተና ፡ ከዘርኽ ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ እንዳይወጣ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እናደርጋለን„ ። ሲሉ ፡ ለዚሁ ፡ ለሸዋ ፡ ገዥ ፡ ለደጃች ፡ ድሜጥሮስ ፡ ላኩ ።

ደጃች ፡ ድሜጥሮስ ፡ ይኸን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ልብስ ፡ አሲዞ ፡ ወደ ፡ ጻሕፈ ፡ ላም ፡ አእጋሮ ፡ (የጻሕፈ ፡ ላሕም ፡ ልሳኖ ፡ ልጅ) ፡ ቤት ፡ ሄደ ። በገናውም ፡ ጊዜ ፡ ለጋሎች ፡ ልብስ ፡ ለመስጠት ፡ ከንጉሡ ፡ ታዝዤ ፡ ወዳንተ ፡ መጣሁ ፡ አለው ፡ አእጋሮም ፡ ወጥቶ ፡ ይኸንኑ ፡ በየወረዳው ፡ ላሉት ፡ የቱለማ ፡ ጋሎች ፡ በነገረ ፡ ጊዜ ፤ ጋሎቹ ፡ ከያለበት ፡ ተሰብስበው ፡ መጡ ። እነሱም ፡ ከመምጣታቸው ፡ በፊት ፡ ደጃች ፡ ድሜጥሮስ ፡ ነፍጥ ፡ (ጠመንዣ) ፡ የያዙትን ፡ ወታደሮች ፡ የጥይት ፡ ድምፅ ፡ ለምልክት ፡ ስትሰሙ ፡ ወደኔ ፡ ሮጣችሁ ፡ እንድትመጡ ፡ ብሎ ፡ በጫካና ፡ በሌላ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ደብቋቸው ፡ ነበር ። ጋሎቹ ፡ ነገሩን ፡ ሳያውቁት ፡ በልበ ፡ ገርነት ፡ የተባለውን ፡ ልብስ ፡ ለመቀበል ፡ ተሰብስበው ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ድሜጥሮስ ፡ የጥይት ፡ ድምፅ ፡ ለወታደሮቹ ፡ አሰማ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጭፍሮቹ ፡ እየተሯሯጡ ፡ መጥተው ፡ ጋሎቹን ፡ ከበቧቸው ። ወዲያውም ፡ ሁሉንም ፡ ካሰሯቸው ፡ በኋላ ፡ በጋሎቹ ፡ ፊት ፡ ደጃች ፡ ድሜጥሮስ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፤ «እናንተ ፡ እዚህ ፡ ያላችሁ ፡ ጋሎች ፡ ሁሉ ፡ የምነግራችሁን ፡ ደኅና ፡ አድርጋችሁ ፡ ስሙኝ ፡ በናንተና ፡ በኛ ፡ መከ

ከል ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ውጊያና ፡ ጠብ ፡ የለብንም ፤ በመካከላችን ፡ ገብቶ ፡ የበጠ በጠን ፡ ወሬኛ ፡ የተባለው ፡ እናንተ ፡ ያስቀመጣችሁት ፡ ነው ፤ አሁን ፡ እርሱን ፡ ይዛችሁ ፡ ስጡንና ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ኢያሱ ፡ እንውሰደው ፤ እንቢ ፡ ያላችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ እናንተን ፡ እንደዚሁ ፡ እንደ ፡ ታሰራችሁ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ እወ ስዳችሁና ፡ ትገደላላችሁ ፡ ይኸንን ፡ መክራችሁ ፡ በቶሎ ፡ ንገሩኝ ፡ አላቸው ።

ጋሎቹም ፡ ይኸንን በሰሙ ፡ ጊዜ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይከራከሩ ፡ ዠመር፡ ግማሾቹ ፡ እኛን ፡ እንደ ፡ ፈቀዱ ፡ ይፍጁን ፡ እንጂ ፡ እኛን ፡ አምኖ ፡ በባታችን ፡ በቱለማ ፡ ደንብ ፡ ተማፅኖ ፡ የተቀመጠውን ፡ እጁን ፡ ይዘን ፡ አሳልፈን ፡ አንሰ ጥም ፡ አሉ ። ግማሾቹ ፡ ግን ፡ ብዙዎቹ ፡ የቱለማ ፡ ሕዝቦች ፡ ከሚያልቁ ፡ አንድ፡ ወሬኛ ፡ ብቻውን ፡ ቢሞት ፡ ይሻላል ፡ ሲሉ ፡ ለነዚያ ፡ መለሱላቸው ፤ ድምፃቸ ውም ፡ በነዚያ ፡ ላይ ፡ ብልጫ ፡ አገኘ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከነዚህ ፡ ከቱለማ ፡ ወገኖች ፡ ያብቹና ፡ የገላን ፡ ፹ ፡ ሰዎች፡ ተመርጠው ፡ በፈረስ ፡ ሆነው ፡ አለበት ፡ ድረስ ፡ ሄደው ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ ወሬኛን ፡ ያዙት ። በተለይ ፡ የያዘውም ፡ አባ ፡ ጋዳ ፡ ጪቆ ፡ የሚባለው ፡ የግም ብቹ ፡ ተወላጅ ፡ ነው ። ወሬኛም ፡ እንደ ፡ ተያዘ ፡ ሶምሳ ፡ ወደሚባለው ፡ ደጃች፡ ድሜጥሮስ ፡ ወዳለበት ፡ ሥፍራ ፡ ወሰዱትና ፡ አስረከቡት ።

ዐፄ ኢያሱ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከአሬንጎ ፡ ወደ ፡ ደራ ፡ ተሻግረው ፡ ከዚያም ወደ ፡ አማራ ፡ ሣይንት ፡ አልፈው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አለቃቸውን ፡ ብላቴን ጌታ ፡ ዮሐንስን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እየላኩ ፡ ከዚያም ፡ በፈለገ ፡ ዠራ ፡ በቄል ቄል ፤ በሸዋ ፡ ገደል ፤ በማን ፡ ሐራ ፤ በቡሽ ፡ ቄለሌ ፡ አድርገው ፡ ደማስቆ ፡ ገቡ።

በዚህ ፡ ሳሉ ፡ ወሬኛ ፡ ከታሰረበት ፡ አምባ ፡ መጥቶ ፡ እንደ ፡ ታሰረ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ቀረበ ። ንጉሡ ፡ ፍርዱ ፡ በደንብ ፡ እንዲፈጸም ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ የሚ ቀመጡትን ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ እየጠቀሱ ፡ የሚፈርዱትን ፡ አዛዦች ፡ ከነርሱም ፡ በቀ፤ ፡ መኳንንቱና ፡ ቀሳውስቱ ፡ በጉባኤ ፡ እንዲቀመጡ ፡ አድርገው ፡ ነበር።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከአዛዦች ፡ (ከፈራጆች) ፡ አንዱ ፡ "አንተ ፡ ማነኽ ፡ አገር ኽስ ፡ ነገድኽስ ፡ ወዴት ፡ ነው" ፡ ሲል ፡ ወሬኛ ፡ ይስሐቅን ፡ ጠየቀው ፤ እርሱም፡ "ዛሬ ፡ ከባለጌ? ፡ ወገን ፡ ነው ፡ በጐጃም ፡ በተለይ ፡ በደብረ ፡ ወርቅ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ተቀምጫለሁ» ፡ አላቸው ፡ እነርሱም ፡ "የመጣኽበትን ፡ አገርና ፡ ትው ልድኽን ፡ ሳትደብቀን ፡ እውነቱን ፡ እንድትነግረን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ አምለን ኻል" ፡ አሉት ። እርሱም ፡ "በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ካማላችሁኝስ ፡ እውነቱን ፡ ነው ፡ የምነግራችሁ ፤ እኔ ፡ በደብረ ፡ ወርቅ ፡ በብር ፡ አንጥረኞችና ፡ በብረት ፡ ቀጥቃጮች ፡ ቤት ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ ብረት ፡ በመቀጥቀጥ ፡ ነው ፡ የኖርኩት ፤ ዘሬም ፡ የዦን ፡ ሸላሚ ፡ ወገን ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ችግር ፡ ስለ ፡ በዛብኝ ፡ የብረት ፡ ቅጥቀጣውን ፡ ሥራ ፡ ትቼ ፡ ከጐጃም ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ሄድሁ" ፡ ሲል ፡ መለሰ ። አዛዦችም ፡ "እንግዲያው ፡ ከነገሥታት ፡ ወገን ፡ ሳትወለድ ፡ ድባብ ፡ ማሲያዝኽ፡ ነጋሪት ፡ ማስጮኽኽ ፡ አገር ፡ ላገርስ ፡ እየዞርኽ ፡ ሕዝብ ፡ ማስጨረስኽ ፡ ስለ ፡

ምንድነው ? ፡ "ሲሉ ፡ መልሰው ፡ ጠየቁት ፤ በዚህ ፡ ምንም ፡ የሚመልሰው ፡ አጣና፡ ዝም ፡ አለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አዛገሮቹ ፡ ሁሉም ፡ በንድ ፡ ቃል ፡ ተስቅሎ ፡ መሞት ፡ ይገባዋል ፡ ሲሉ ፡ ፈረዱበት ። ወዲያው ፡ ያደረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ምት ሐተኛና አስማተኛ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ያመልጣል ፡ ተብሎ ፡ የዕለቱ ፡ ለት ፡ ተሰቀለና ፡ ሞተ ። ይኸ ፡ ሁሉ ፡ የሆነው ፡ በሺሕ ፡ ፯፻፳ ፡ ፳፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነው ። ዐፄ ፡ ኢያሱም ፡ በጣም ፡ አስፈሪቶና ፡ አስቸግሮ ፡ የነበረውን ፡ የወሬኛን ፡ ጉዳይ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ከደማስቆ ፡ ተነሥተው ፡ ጫካ ፡ ሲያገኙ ፡ አደን ፡ እያደኑ ፡ ሽፍታ ፡ ሲያገኙ ፡ እየቀጡ ፡ ገዳምና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲያገኙ ፡ እየተሳለሙ ፡ ጸሎት ፡ እያደረሱ ፡ በሽ ፡ መከር ፡ አምባ ፡ በምንጋሽ ፡ አምባ ፤ በአባ ፡ ጉንዳ ፤ በቃሮዳ ፤ በመንዝሮ ፤ በጻዳ ፡ በኩል ፡ አድርገው ፡ በሐምሌ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ መዲናቸው ፡ (መናገሻ ፡ ከተማቸው) ፡ ጐንደር ፡ ገቡ ።

## ምዕራፍ ፡ ፭ ።

## ወደ ፡ አኵስም ፡ የተደረገ ፡ ጕዞ ፤—ስለ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴ ፤–ክፍለ ፡ ዮሐንስ፡ ስለሚባለው ፡ ሊቅ ።

በዚሁ ፡ ዘመን ፡ በሺሕ ፡ ፯፻፳፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እደ ፡ ክርስቶስ ፡ የአማራ ፡ ጸሐፊ ፡ ላሕምና ፡ ዐቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ይልቁንም ፡ እንደራሴያቸው ፡ ቃማኛቸው ፡ ራስ ፡ አንስጣስዮስ ፡ ሞቱና ፡ ታላቅ ፡ ኀዘን ፡ ተደረገ ። በሟቹም ፡ በራስ ፡ አንስጣስዮስ ፡ እግር ፡ ደጃች ፡ ፋሬስ ፡ ራስ ፡ ተብሎ ፡ እንደራሴነቱን ፡ ተሾመ ። እንዲሁም ፡ በ፪ኛው ፡ ዓመት ፡ የሚወዷቸው ፡ እናታቸው ፡ እቴጌ ፡ ሰብለ፡ ወንጌል ፡ የአእላፍ ፡ ሰገድ ፡ ዮሐንስ ፡ ባለቤት ፡ ስለ፡ሞቱ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ፡በኀዘን፡ ላይ ፡ ኀዘን ፡ ደረሰባቸው ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ለወጥ ፡ የተሠራው ፡ ዓሣ ፡ ተነሣ ፡ በተባለ ፡ ጊዜ ፡ ከንስሓ ፡ አባታቸው ፡ ጋራ ፡ ያሰብ ፡ ወይም ፡ የሥጋ ፡ ግንኙነት፡ አድርገዋል ፡ የተባለውን ፡ እንደ ፡ ተረት ፡ በመቍጠር ፡ እውነትም ፡ ሆኖ ፪ ሆን ፡ እሱን ፡ ሳንከተል ፡ እቴጌዩቱ ፡ በጠባያቸው ፡ ደግነትና ፡ ርኅራኄ ፡ የመላቸው ፤ ይልቁንም ፡ ባለቤታቸው ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ሁሉንም ፡ ትተው ፡ በጸሎትና ፡ በስግደት ፡ ተጠምደው ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አጠገብ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ሁለተኛ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ አሳብ ፡ አልተመለሱም ፡ ሲል ፡ ታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ አጋኖ ፡ ጽፎላቸዋል ። በሞቱም ፡ ጊዜ ፡ ልጃቸው ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ በታላቅ ፡ ክብርና ፡ ፍታት፡ ጣና ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ ምጽራሐ ፡ ማርያም ፡ በሚባለው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስቀበሯቸው ።

፨ ፨ ፨

ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ በጐንደር ፡ ከተማቸው ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ በመጨረሻ ፡ በስሜን ፡ በኩል ፡ አድርገው ፡ ወደአኵስም ፡ ለመሄድ ፡ አሰቡ ። ስለዚህ ፡ በሺሕ ፡ ፯፻፳፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በደባርቅና ፡ በለማልሞ ፡ በኩል ፡ አድ

ርገው ፡ ስሜን ፡ ደረሱ ፤ ደርሰውም ፡ ከመነው ፡ ላይ ፡ ግብርና ፡ መጥን ፡ እየተ ቀበሉ ፡ ያላመነውን ፡ በጦር ፡ እያስገበሩ ፡ መረብ ፡ ወንዝ ፡ ደረሱ ። በዚያም ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ እየተላለፉ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገድም ፡ እያሳመኑ ፡ የጥምቀትንም ፡ በዓል ፡ መረብ ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ አክብረው ፡ ዋሉ ። የርሳቸውም ፡ ገሚስ ፡ ጭፍራ ፡ በንድ ፡ ወገን ፡ ወደ ፡ ከሰላ ፡ ሄዶ ፡ እስከ፡ ስና ፡ ደረሰ ፤ ይኸንንም ፡ ወረዳ ፡ ከያታቸው ፡ ከዐፄ ፡ ፋሲል ፡ በቀር ፡ ያለፉት ፡ ነገሥታት ፡ በጐንደር ፡ መንግሥት ፡ ዘመን ፡ አልደረሱበትም ፡ ይባላል ። ዐፄ ፡ ኢያ ሱም ፡ ይኸንኑ ፡ አገር ፡ አቅንተው ፡ ግዛታቸውን ፡ ከምዕራብ ፡ እስከ ፡ ስናር ፤ ከሰሜን ፡ የከረንን ፡ የሐበብን ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ እያስገበሩ ፡ ጨርሰው ፡ እስከ ፡ ላይኛው ፡ የባርካ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ አቅንተው ፡ በገበረው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሹም፡ ሽር ፡ አድርገው ፡ በእንበ.ልታና ፡ በመለከት ፡ በብዙ ፡ ሠራዊትም ፡ ታጅበው ፡ ተመልሰው ፡ አኵስም ፡ ደረሱ ። በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ የአኵስም ፡ ጽዮን ፡ ካህናት፡ እንደ ፡ ተለመደ ፡ በንሴብሖ ፡ እያሸበሸቡ ፡ በላገሩ ፡ በሆታ ፡ ሴቱም ፡ በእልልታ፡ ተቀበላቸው ።

ንጉሡም ፡ አኵስም ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ደጃዝማች ፡ ጥሥሐ ፡ ክርስቶስ ፡ የት ግሬን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ይዘ ፡ ስሜን ፡ በዘመተ ፡ ጊዜ ፡ ተከበ ፡ ሳለ ፡ ደጃ ዝማች ፡ ገላውዴዎስ ፡ የሚባለው ፡ የሺሬ ፡ ገዥ ፡ እርሱን ፡ በመርዳት ፡ ፈንታ፡ ከነጭፍራው ፡ ከዘመቻው ፡ ከድቶ ፡ ወዳገሩ ፡ ተመልሷል ፡ ተብሎ ፡በዚሁ ፡ ተይዞ ፡ ለፍርድ ፡ ቀረበ ።

በችሎቱም ፡ ነበሬው ፡ ሁሉ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ፈረደበት ፤ ንጉሡ ፡ ግን ፡ ከሹመ ቱና ፡ ከማዕርጉ ፡ በጭራሽ ፡ ይሻርና ፡ ሞቱ ፡ ይቅርለት ፡ ብለው ፡ ምሕረት ፡ አደ ረጉለት ። ከዚሁ ፡ የተነሣ ፡ ቀድሞ ፡ የነጋሪት አገር ፡ የነበረውም ፡ ሽሬ ፡ የነጋሪት፡ አገር ፡ መባሉ ፡ ቀርቶ ፡ ትግሬ ፡ መኰኔ ፡ (ትግሬ ፡ መኰንን) ፡ በሚባለው ፡ አገር ፡ ገዥ ቈራጭነት ፡ ውስጥ ፡ እንዲተዳደር ፡ ተወሰነ ።

፨ ፨ ፨

በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ዘመን ፡ ጥንተ ፡ ዘሩ ፡ አርመን ፡ የሆነ ፡ ሙራድ ፡ የሚባል፡ የግብጽ ፡ ተወላጅ ፡ ከግብጽ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ህንድ ፡ እየተመላለሰ ፡ ሲነግድ ፡ በዚያውም ፡ ምንጣፍ ፡ ከባ ፡ በተረፈም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሸቀጥ ፡ እያመጣ ፡ ንጉሡንና ፡ መኳንንቱን ፡ ደስ ፡ ስላሰኘ ፡ በለሟል ፡ ሆኖ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ናይብ ፡ ሙሳ ፡ (ወልደ ፡ እመርቁኑ) ፡ የሚባለው ፡ በምጥዋና፡ በአርኪቆ ፡ ያለው ፡ የቱርኮች ፡ ሹም ፡ ብዙ ፡ ሸቀጥ ፡ ይልቁንም ፡ የንጉሡን ፡ ዕቃ ፡ ከሙራድ ፡ ላይ ፡ ቀምቶ ፡ የሐማሴንና ፡ የምጥዋ ፡ ሕዝብ ፡ ንግድ ፡ እንዳ ይነግድ ፡ ቀረጥ ፡ እያበረከተ ፡ ማስቸገሩን ፡ ሙራድ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ላከ ። በዚህ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ተቈጡ ፤ ወዲያው ፡ ወደ ፡ ሐማሴን ፡ አውራጃ ፡ ገዥዎችና፡ በለባቶች ፡ ወደ ፡ አብ ፡ ሥሉስና ፡ ወደ ፡ ዘርዐ ፡ ቡሩክ ፡ ልከው ፡ «ቅቤ ፡ ማር ፡

እኽል ፡ ይዞ ፡ ከሐማሴን ፡ ወደ ፡ ምጥዋ ፡ ለንግድ ፡ ማንም ፡ እንዳይሄድ ፡ የሄደ ፡ ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ ያገኘዋል» ፡ ሲሉ ፡ በመልእክት ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ። በዚህ ፡ ዐዋጅ ፡ የምጥዋና ፡ የአርኪቆ ፡ ሕዝብና ፡ ቱርኮች ፡ እታላቅ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ወደቁ ። ናይብ ሙሳም ፡ ዘመቻ ፡ አድርጎ ፡ ዐዋጁን ፡ በኀይል ፡ እንዳያስፈርስ ፡ የንጉሡ ፡ የዐፄ ኢያሱ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በአኵሱምና ፡ በሐማሴን ፡ ውስጥ ፡ መኖሩን ፡ ከዚህ ፡ ቀደምም ፡ በዙሪያው ፡ አገር ፡ ያደረገውን ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ ስለሚያውቅ ፡ ከሙ ራድ ፡ በቀረጥ ፡ ምክንያት ፡ የቀማውን ፡ ሸቀጥ ፡ ራሱ ፡ ናይብ ፡ ሙሳ ፡ ይዞ ፡ መጥቶ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ አኵሱም ፡ ላይ ፡ ተገኘ ። እንደ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ አነጋገር ፡ በተ ገናኘም ፡ ጊዜ ፡ በግንባሩ ፡ ተደፍቶ ፡ ንጉሡን ፡ ይቅርታ ፡ ለመነ ፤ የቀማውንም ፡ የንጉሡን ፡ ዕቃና ፡ ሸቀጥ ፡ ከራሱም ፡ እንደ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃ ፡ ጨምሮ ፡ ለንጉሡ ፡ አቀረበ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሐማሴን ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ምጥዋ፡ የምጥዋ ፡ ሕዝብም ፡ ወደ ፡ ሐማሴን ፡ ወደ ፡ ትግሬም ፡ እየመጣ ፡ እንደ ፡ ቀድ ሞው ፡ ሲነግድ ፡ እንዳይከለከል ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ስምምነት ፡ አድርገው ፡ ከጨ ረሱ ፡ በኋላ ፡ ናይብ ፡ ባሻ ፡ ተሰናብቶ ፡ በሰላም ፡ ወደ ፡ ሥፍራው ፡ ተመለሰ ።

ንጉሡም ፡ ከአኵሱም ፡ ተነሥተው ፡ በሽሬ ፡ በኩል ፡ አድርገው ፡ ተከዚን ፡ ተሻግረው ፡ የላስታን ፡ አገርና ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አይተው ፡ መገመሪያ ፡ አሪንጎ ፡ ደርሰው ፡ ከዚያ ፡ ጐንደር ፡ እከተማቸው ፡ ተመለሱ ።

፨ ፨ ፨

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ጐንደር ፡ የሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕንፃው ፡ ተሠርቶ፡ አልቆ ፡ ነበርና ፡ ታቦቱን ፡ ከአባ ፡ ሲኖዳ ፡ በኋላ ፡ የተሾሙት ፡ ጳጳሱ ፡ አቡነ፡ማር ቆስ ፡ ዕጨጌው ፡ ጸጋ ፡ ክርስቶስ ፡ ከቀሳውስቱ ፡ ጋራ ፡ ይዘው ፡ እፊት ፡ እፊት ፡ ሲሄዱ ፤ ንጉሡ ፡ «ጐቤን» ፡ በሚባለው ፡ ፈረሳቸው ፡ ተቀምጠው ፡ በመኳንንቶቻ ቸው ፡ ታጅበው ፡ ታቦቱን ፡ ከኋላው ፡ ይከተሉ ፡ ነበር ። በኋላም ፡ ታቦቱ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ደጃፍ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ታቦቱን ፡ ከቄሱ ፡ ተቀብለው ፡ (ገና በጳጳሱ ፡ አልተባረከም ፡ ነበርና) ፡ በራሳቸው ፡ ተሸክመው ፡ ቅድስት ፡ ድረስ ፡ አገቡ ከዚያ ፡ ቄሱ ፡ ተቀብሎ ፡ ከቅድስት ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ካገባው ፡ በኋላ ፡ በጳጳሱ ፡ ተባርኮ ፡ ቅዳሴ ፡ ቤቱ ፡ ተቀደሰና ፡ የታቦቱ ፡ አገባብ ፡ በታላቅ ፡ በዓል ፡ ተከበረ።

በዚህም ፡ ቀን ፡ ለካህናትና ፡ ለወታደር ፡ ለመኳንንትና ፡ ለሊቃውንት፡ትልቅ ግብር ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ አደረጉ ። አዛዥ ፡ ሐዋርያ ፡ ክርስቶስም ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ መወድስ ፡ ተቀኘ ።

ሕዝበ ፡ ነገደ ፡ ሴም ፡ ያብእ ፡ ውስተ ፡ ርእሰ ፡ ሴም ፤
አመ ፡ ፀኢቱ ፡ ምስሌኪ ፡ እምነ ፡ ሴይር ።
ዘእም ፡ ገጸ ፡ ግርማኪ ፡ ጐየት ፡ እንተ ፡ ርእየተኪ ፡ ባሕር ።
ወእንፈርዐጹ ፡ ከመ ፡ ሐራጊት ፡ ቅድሜኪ ፡ አድባር ።
አ ፡ ሠናይት ፡ ዝክር ።

ኅበ ፡ ኢያሱ ፡ እሙሴ ፡ ተመጠውኪ ፡ በክቡር ።
ዘመንየ ፡ እስመ ፡ ኅዳጥ ፤ ወዕለትየ ፡ ኅጹር ።
እስፍንተ ፡ እዜኑ ፡ ሠናተ ፡ ተድላ ፡ ወምንተ ፡ እነግር ።
አኮኑ ፡ የኀብር ፡ ቀሥም ፡ ምስለ ፡ ማእረር ።
ታቦተ ፡ ሕጉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ታቦተ ፡ ሕጉ ፡ ለእግዚአብሔር ።
በመዋዕልኪ ፡ መዋዕለ ፡ ሰላም ፡ ወፍቅር ።
ታቦተ ፡ ሕጉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ታቦተ ፡ ሕጉ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ሌሎችም ፡ ደግሞ ፡ ስማቸው ፡ ያልታወቀ ፡ ሊቆች ፡ (1)እንደዚህ ፡ ሲሉ ፡ ተቀኝተዋል ።

ከመኒ ፡ አግመረ ፡ ለባሕረ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ከርሡ ፡
እንዘ ፡ በ ፡ ዮሐንስ ፡ በስምዐ ፡ ርእሱ ፡
ዘመነ ፡ ኪሩብ ፡ ገብረ ፡ ደብረ ፡ መቅደሱ ፡
ዘሐነፀ ዳግማይ ፡ ኢያሱ ።

የዚህኛው ፡ ትርጓሜ ።

ዮሐንስ ፡ በማጥመቁ ፡ ምስክርነት ፡ ሳለ ፡ የሥላሴን ፡ ሦስትነት ፡ የዮርዳኖስ ፡ ባሕር ፡ እንደ ፡ ቻለ ፡ ፪ኛው ፤ ኢያሱ ፡ የሠራውን ፡ የመቅደሱን ፡ ደብር ፡ ሦስትነት ፡ ያለበት ፡ የኪሩብን ፡ ዙፋንነት ፡ አደረገ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሥላሴ ፡ ቅኔ ።

አምላክ ፡ ዘኢፈቀድከ ፡

ደቂቀ ፡ ቆሬ ፡ ወዖዝያን ፡

ሶበ ፡ ማዕጠንተ ፡ ወርቅ ፡ ነሥኡ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ካህናተ ።

ነሥኡ ፡ ተቀሥፎ ፡ ወለብሱ ፡ እሳተ ።

እለ ፡ ይፈርሁከ ፡ ሰብአ ፡ ባሕቱ ፡ እምኀበ ፡ ረከብከ ፡ አንተ ።

በዘወሀብከሙ ፡ ትእምርተ ።

አመ ፡ ርኅበ ፡ በልዐ ፡ ዳዊት ፡ መሥዋዕተ ።

ወኢያሱ ፡ አንሥአ ፡ ጽላተ ።

ትርጓሜ ።

የዖዝያንና ፡ የቆሬ ፡ ልጆች ፡ ካህናት ፡ ለመሆን ፡ አስበው ፡ አምላክ ፡ ያልፈቀድኸውን ፡ የወርቅ ፡ ጥና ፡ በወሰዱ ፡ ጊዜ ፡ ተቀሥፈው ፡ እሳት ፡ በላቸው ። አንተን ፡ ከሚፈሩህ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ በሰጠኸቸው ፡ ምልክት ፡ ተመርተው ፡ ዳዊት ፡ ቢራብ ፡ መሥዋዕትን ፡ በላ ፤ ኢያሱም ፡ ጽላትን ፡ አነሣ ።

(1)ምናልባት ፡ ከዛገሮቹ ፡ ወይም ፡ ከጸሐፍት ፡ ትእዛዛቱ ፡ ውስጥ ፡ ይሆናሉ ።

ያማርኛ ፡ ግጣሚ ፡ ደግሞ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።
ወይት ፡ ሄዶ ፡ ኖሯል ፡ ሰሞነኛው ፡ ቄሱ ።
ታቦት ፡ ተሸከመ ፡ ዘውዱን ፡ ትቶ ፡ ኢያሱ ።
የተሸሸገውን ፡ ያባቱን ፡ ቅስና ፡ (አባታቸው ፡ ዮሐንስ ፡ ቄስ ፡ ነበሩ ፡ ስለሚባል) ፡
ገለጠው ፡ ኢያሱ ፡ ታቦት ፡ አንሣና ።
አየነው ፡ ኢያሱን ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ቆሞ ።
ከኪሩቤል ፡ ጋራ ፡ ሦስቱን ፡ (ሥላሴን) ፡ ተሸክሞ ።
ሰውነቱን ፡ ትቶ ፡ መልአክ ፡ ሆነ ፡ ደግሞ ።
ሥላሴን ፡ ቢሸከም ፡ ኢያሱ ፡ ገነነ ፤
ላራቱ ፡ ኪሩቤል ፡ አምስተኛ ፡ ሆነ ።

ታቦቱ ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አገልጋዮች ፡ ከያለበት ፡ ተጠራቅመው ፡ መሉት ። ንጉሡም ፡ በጊዜያቸው ፡ የተሠራ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመሆኑ ፡ ርስትም ፡ በመትከል ፡ አበልም ፡ በማብዛት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ አገልጋዮች ፡ አበርክተዋቸውና ፡ አክብረዋቸው ፡ ነበር ፤ አለቃውም ፡ «መላከ ፡ ብርሃናት ፡ የሚባል ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ተሰጠው ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከነበሩ ፡ ከጐንደር ፡ ሊቆች ፡ ውስጥ ፡ ስሙ ፡ የታወቀው ፡ የክፍለ ፡ ዮሐንስ ፡ ነበር ፤ እሱም ፡ መጻሕፍት ፡ ዐዋቂ ፡ ከመሆኑ ፡ ሌላ ፡ በቅኔ ፡ ደግሞ ፡ የተመሰገነ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሊቅ ፡ የሚያስተምርበት ፡ ሥፍራ ፡ ከዚሁ ፡ ከደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አጠገብ ፡ ካለው ፡ ወይራ ፡ ውስጥ ፡ ነበር ። አንድ ቀን ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሳልመው ፡ ሲመለሱ ፡ መጻሕፍት ፡ ሲያስተምር ፡ ለማየት ፡ ባጠገቡ ፡ ሲያልፉ ፡ በቅኔ ፡ አሳብ ፡ ልቡ ፡ ተመስጦ ፡ ሳያያቸውና ፡ ሳይነሣ ፡ ቢቀር ፡ በወርቅ ፡ ዘንግ ፡ ራሱን ፡ ነካ ፡ አደረጉት ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ አይቶ ፡ ተነሥቶ ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ወዲያው ፡ ዘርፎ ፡ ተቀኘ ፡ ይባላል ። ደግሞ ፡ ገሚሶቹ ፡ ንጉሡ ፡ ባጠገቡ ፡ ሲያልፉ ፡ ቆም ፡ ብለው ፡ ለርሱ ፡ እንደ ስጦታ ፡ እንዲቈጠር ፡ አንድ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ወርውረው ፡ ስለ ፡ መቱት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በወርቅ ፡ ዘንግ ፡ አልመቱትም ፡ ይላሉ ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዘርፎ ፡ የተቀኘው ቅኔ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

በእስጢፋኖስ ፡ አዕባን ፡ እመ ፡ የኀልቁ ፤
ዘበጠኒ ፡ ኢያሱ ፡ በወርቁ ።

## ትርጓሜ ።

እስጢፋኖስን ፡ አይሁድ ፡ በደንጊያ ፡ ደብድበው ፡ ስለ ፡ ገደሉት ፡ ደንጊያዎች ፡ በእስጢፋኖስ ፡ ላይ ፡ ቢያልቁ ፡ ኢያሱ ፡ በወርቁ ፡ ደበደበኝ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ክፍለ ፡ ዮሐንስ ፡ ያገራችን ፡ ባለታሪክ ፡ እንደሚለው ፡ ንጹሕና ፡ ድንግል ፡ ነው ። በኑሮውም ፡ ያገኘውን ፡ ከተማሪዎቹ ፡ ጋራ ፡ ተሳትፎ ፡ (ተካፍሎ) ፡ መኖር ፡ ነው ። እንጂ ፡ ለራሱ ፡ ትዳር ፡ የለውም ። ልብሱም ፡ እንደ ፡ መናንያን ፡ ነጭ ፡ ዐጽፍ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ዐጽፍ ፡ በጐንደሮች ፡ አነጋገር ፡ ማስ ፡ ይባላል ። ባጥቂ

ንቱና ፡ ባገልግሎቱም ፡ ያገኘውን ካባና ፡ ድርብ ፡ ያስቀምጠው ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በበዓል ፡ ቀን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንኳ ፡ አይለብሰውም ፡ ነበር ፡ ይባላል ። የቀ ሩት ፡ ሊቃውንት ፡ ግን ፡ ጥንግ ፡ ድርብ ፡ ቋሬ ፡ ነጠላ ፡ የሚባለውን ፤ በዚያ ፡ ጊዜ የተከበረውን ፡ ልብስ ፡ ሲለብሱ ፡ እሱ ፡ በመካከላቸው ፡ እንደ ፡ ንቀት ፡ ዘወትር ፡ ዐጽፍ ፡ ብቻ ፡ ስለሚለብስ ፡ ሊቃውንቱ ፡ ተቀይመው ፡ ነበር ፤ እርሱም ፡ ይኸንኑ ፡ እየቀጠለ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ ሊቃውንቱ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ገብተው ፡ እኛ ፡ የማዕርግ ፡ ልብስ ፡ ለብሰን ፡ በቅኔ ፡ ማኅሌት ፡ ስንቆም ፡ እርስዎ ፡ የሸለሙት ፡ የማዕርግ ፡ ልብስ ፡ ሳለ ፡ ዳባ ፡ እየለበሰ ፡ ከመካከላችን ፡ ይቆማል ፤ ይህም ፡ አኳኋን ፡ የርስ ዎን ፡ ደብር ፡ ማዋረድና ፡ እኛን ፡ በትምህርት ፡ መናቅ ፡ ይመስላል ፡ ብለው ፡ ነገሯቸው ። ንጉሡም ፡ «ለዚህ ፡ የሚሻለውን ፡ ምክር ፡ አምጡ» ፡ ቢሏቸው ፡ እነሱም «ዳባ ፡ የለበሰ ፡ እቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ አይግባ ፡ ብለው ፡ ዐዋጅ ፡ ያስነግሩ ልን» ፡ አሏቸው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በንጉሡ ፡ ፈቃድ ፡ የጐንደር ፡ ገበያ ፡ በሚውል በት ፡ በቅዳሜ ፡ ቀን ፡ ይኸው ፡ ዐዋጅ ፡ ተነገረ ። ክፍለ ፡ ዮሐንስም ፡ ሌሊቱን ፡ የማዕርግ ፡ ልብሱን ፡ ለብሶ ፡ ተማሪዎቹን ፡ አስከትሎ ፡ መወድስ ፡ ለመቆም ፡ እቤተ ክርስቲያን ፡ ሲገባ ፡ ካህናቱ ፡ በክብሮ ፡ ሲዘምሩ ፡ ቢያገኛቸው ፡ እናንት ፡ ዐዋጅ ፡ አፍራሾች ፡ ትላንት ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ዳባ ፡ የለበሰ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አይግባ፡ ብለው ፡ ዐዋጅ ፡ አስነገሩ ፤ አሁን ፡ እናንተ ፡ ዳባ ፡ የለበሰውን ፡ ክብሮ ፡ ትደበድባላ ችሁ ፡ ቈዳ ፡ የለበሰውን ፤ መጽሐፍ ፡ ትደግማላችሁ ፡ ብሎ ፡ ተማሪዎቹን ፡ ነጋሪቱ ንም ፡ ከበሮውንም ፡ መጻሕፍቱንም ፡ ሳይቀር ፡ እያወጣችሁ ፡ ጣሉ ፡ አለ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ መወድሱ ፡ ታጐሎ ፡ አደረ ፡ ይባላል ፤ በማግስቱ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ መጥ ተው ፡ የሁሉንም ፡ ክርክር ፡ ሰሙና ፡ እንደነበረው ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ ዐዋጁን ፡ በት እዛዝ ፡ ሻሩትና ፡ እሱም ፡ ያንኑ ፡ የቀድሞውን ፡ ዐጽፍ ፡ ይለብስ ፡ ዠመር ፡ ይባላል።

## ምዕራፍ ፡ ፶፪ ።

### ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ሸዋ ፡ ስለ ፡ መምጣታቸው ፤ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ዐድማ ።

ለበጌምድርና ፡ ለከተማቸው ፡ ለጐንደር ፡ ጠባቂ ፡ እንደራሴያቸውን ፡ ራስ ፡ ፋሬ ስን ፡ ትተው ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ለመምጣት ፡ በሺህ ፡ ፯፻፹፰ ፡ ዓ ፡ ም ጕዞ ፡ አደረጉ ፡ መጥተውም ፡ ተድባበ ፡ ማርያም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ካህናቱ ፡ ልብሰ፡ ተክህኗቸውን ፤ ወታደሩ ፡ የበዓል ፡ ልብሱን ፡ ለብሶ ፡ በሰልፍ ፡ ተቀበሏቸው ። ንጉሡም ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ የቀድሞዎቹን ፡ ነገሥታት ፡ የነዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፤ ፩ኛን የነዐፄ ፡ ይስሐቅን ፤ የቅርቦቹን ፡ የነዐፄ ፡ ገላውዴዎስን ፤ የነዐፄ ፡ ሚናስን ፤ መቃ ብር ፡ ጎበኙ ፤ ለእመቤታችንም ፡ ራሳቸው ፡ ይለብሱት ፡ የነበረውን ፡ የወርቅ ፡ ካባ ፡ ሰጡ ።

ወደ ፡ ሸዋ ፡ ለመምጣት ፡ ያሰቡበት ፡ ምክንያት ፡ ሸዋን ፡ ተከፋፍለው ፡ የሚገ ዙት ፡ ባላባቶች ፡ በወሰንና ፡ በሌላም ፡ ነገር ፡ ክርክር ፡ ማድረጋቸውን ፡ አስቀድ መው ፡ ልከውባቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነው ። እነኚህን ፡ ጐንደር ፡ በመጥራት ፡ ፈንታ ፡

እዚሁ ፡ እሥፍራው
በግድም ፡ በውድ

ለዚሁም ፡ «
ያለውን ፡ ደብዳ
ቋንቋ ፡ ጽፈው ፡
ነገሥት ፡ ኢያሱ ፡
ሰላም ፡ ለክሙ ፤
ኀዳጠ ፡ እስከ ፡ እ
ዓ ፡ ም ፡ »(ሺሕ ፡

በታሪካችን ፡
እናውቃለን ፡ የማ
በፊትና ፡ በኋላ ፡ የ

፩ ፤ በአንጾኪያ ፡
፪ ፤ በኤፍራታ ፡
፫ ፤ በግድም ፡ ለ
፬ ፤ በመንዝ ፡ ማ
፭ ፤ ደግሞ ፡ ባ
፮ ፤ በግሼ ፡ አው
፯ ፤ በዶባ ፡ ጌታ
፰ ፤ በደብብ ፡ ጸ
፱ ፤ በምሖይ ፡
፲ ፤ በመርሐ ፡ ቤ
፲፩ ፤ በሞረት ፡
፲፪ ፤ በተጕለት ፡
፲፫ ፤ በወግዳ ፡ ሕ

ይህነንም ፡
ከነዚህ ፡ ባላባቶች
የተነሡ ፡ ናቸው ፡
ባ፲፯፻፹፰ ፡ ዓ ፡ ም
ርገው ፡ ሸዋ ፡ ሲ
ደስታ ፡ ተቀበላቸ
ፀዋቂ ፡ ነበሩና ፤

በአስትዓ ፡ ማ
ኢያሱ ፡ ንጉሥ ፡ ተ
እስመ ፡ ይደሉ ፡ እ
ወእምረሰይናከ ፡ እ

እዚሁ ፡ እሥፍራው ፡ ላይ ፡ መጥተው ፡ አገሩንም ፡ ጐብኝተው ፡ የተጣሉትንም ፡ በግድም ፡ በውድም ፡ ለማስማማት ፡ አስበው ፡ ነው ፡ ይባላል ።

ለዚሁም ፡ «መጥቼ ፡ እስክጐበኛችሁ ፡ ድረስ ፡ ታገሡ ፡ » የሚል ፡ ከዚህ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ደብዳቤ ፡ ቀድሞ ፡ ከሸዋ ፡ በተላኩት ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ጽፈው ፡ ልከው ፡ ነበር ፡ «ዛቲ ፡ ጦማር ፡ ዘተፈነወት ፡ እምኀበ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ኢያሱ ፡ ዘተሰምየ ። አድያም ፡ ሰገድ ፡ ትብጻሕ ፡ ኀበ ፡ መኳንንተ ፡ ሸዋ ። ሰላም ፡ ለክሙ ፤ እስመ ፡ እመጽእ ፡ ኀቤክሙ ፡ በቅሩብ ፡ መዋዕል ፤ ተዐገሡ ። ኀዳጠ ፡ እስከ ፡ እመጽእ ፡ ወእሔውፀክሙ ። ተጽሕፈ ፡ ጐንደር ፡ በ፲፻ወ፯፻፸ወ፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ »(ሺሕ ፡ ፯፻፹፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም) ።

በታሪካችን ፡ እንደ ፡ ተጻፈና ፡ ዛሬም ፡ የመንዝ ፡ ተወላጆች ፡ የሸዋን ታሪክ እናውቃለን ፡ የሚሉት ፡ በቃል ፡ እንደሚዘረዝሩት ፡ በሸዋ ፡ ከአቤቶ ፡ ነጋሢ ፡ በፊትና ፡ በኋላ ፡ የነበሩት ፡ ባላባቶችና ፡ ያገሩ ፡ ስም ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

፩ ፤ በአንጾኪያ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ ዘሜ ፡ (ዘሚካኤል) ፡
፪ ፤ በኤፍራታ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡
፫ ፤ በግድም ፡ ለታ ፡
፬ ፤ በመንዝ ፡ ማማ ፡
፭ ፤ ደግሞ ፡ ባ፩ ፡ ወገን ፡ መንዝ ፤ ባላምባራስ ፡ ላሎ ፡
፮ ፤ በግሼ ፡ አውሳብዮስ ፡
፯ ፤ በዶባ ፡ ጌታቸው ፡
፰ ፤ በደብብ ፡ ጸጋ ፡
፱ ፤ በምሑይ ፡ አዛዥ ፡ መሐዴ ፡
፲ ፤ በመርሐ ፡ ቤቴ ፡ በከራ ፡ ወልዱ ፡
፲፩ ፤ በሞረት ፡ ጥዱ
፲፪ ፤ በተጕለት ፡ ይገብዋል ፡
፲፫ ፤ በወግዳ ፡ ሕርያቆስ ፡

ይህንንም ፡ መጻፋችን ፡ የባላባቶቹን ፡ ዝርዝር ፡ ለመግለጽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከነዚህ ፡ ባላባቶች ፡ አንዳንዶቹ ፡ ከዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በኋላ ፡ የተነሡ ፡ ናቸው ። ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ በነገሡ ፡ በ፲፬ኛው ፡ ዓመት ፡ በ፲፮፻፹፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከጐንደር ፡ ተነሥተው ፡ በማኀደረ ፡ ማርያም ፡ በኩል ፡ አድርገው ፡ ሸዋ ፡ ሲገቡ ፡ መኳንንቱም ፡ ሕዝቡም ፡ ካህናቱም ፡ በታላቅ ፡ ክብርና ፡ ደስታ ፡ ተቀበላቸው ። ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ ዘሚካኤል ፡ ቅኔ ፡ ዐዋቂ ፡ ነበሩና ፤ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቅኔ ፡ ለንጉሡ ፡ አበረከቱ ፡ ይባላል ።

በአስትዓ ፡ ማኅሌት ፡ ወይባቤ ፡
ኢያሱ ፡ ንጉሥ ፡ ተቀበልናከ ።
እስመ ፡ ይደሉ ፡ እግዚአ ፡ እምወሀብናከ ፡ ሰጊደ ፤
ወእምረሰይናከ ፡ አምላከ ፡ ዋሕደ ።

ባሕቱ ፡ አምላክ ፡ ዘእምቤትከ ፡ ተወልደ ፡
ውስተ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ አመ ፡ ወረደ ፡
በቅድመ ፡ ሙሴ ፡ ወአሮን ፡ ይቤ ፡ ገሃደ ፡
እንበሌየ ፡ ኢታምልኩ ፡ ባዕደ ።

ትርጓሜውም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ከለው ፡ ብላቴን ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ በዋዜማ ፡ መጽሐፋቸው ፡ ከተረጐሙት ፡ ልዩነት የለውም ።

ከወገንኽ ፡ የተወለደው ፡ አምላክ ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ በሙሴና፡ በአሮን ፡ ፊት ፡ ከኔ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አታምልኩ ፡ ብሎ ፡ በግልጽ ፡ ባይናገር ፡ ኖሮ ፡ አንተን ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱን ፡ አምላክ ፡ አድርገን ፡ በሰገድንልኽ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ።

ንጉሡም ፡ በሸዋ ፡ በሰነበቱ ፡ ጊዜ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በግዛትም ፡ በሌላም ፡ ይጣሉ ፡ የነበሩትን ፡ የግድምን ፡ የመንዝን ፡ የግሼን ፡ የመርሐ ፡ ቤቱን ፡ የተጕለትን ፡ ባላባቶች ፡ አስማምተው ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ የአቤቶ ፡ ሥግወ ፡ ቃልን ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ አቤቶ ፡ ነጋሢን ፡ የበላይ ፡ መስፍን ፡ አድርገው ፡ ሾመው ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ጕዟቸውን ፡ ዠመሩ ። በመንገዳቸውም ፡ የጎነተ ፡ ጊዮርጊስን ፡ የመካነ ፡ ሥላሴን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሳልመው ፡ አለፉና ፡ ጐንደር ፡ እከተማቸው ፡ በደስታ ፡ ተመልሰው ፡ ገቡ ።

※ ※ ※

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ አምነው ፡ የሾሟቸው ፡ አደራና ፡ አኖሪ ፡ (1) ፡ የሚባሉት ፡ ሹማምንቶች ፡ ለመሸፈትና ፡ ይልቁንም ፡ በንጉሡ ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ የመቃወም ፡ ዐድማ ፡ አድርገዋል ፡ ተብሎ ፡ ተወሬባቸውና ፡ ወዲያው ፡ ከያለበት ፡ ተይዘው ፡ ታሰሩ ። አፍርድም ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ በምርመራው ፡ ንጉሡን ፡ ከፍየል ፡ ሐሞትና ፡ ከመብል ፡ ጋራ ፡ መድኀኒት ፡ ሊያበሉ ፡ ከቤት ፡ አሽከር ፡ ጋራ ፡ አድመው ፡ ኖሮ ፡ ይኸው ፡ ስለ ፡ ተመሰከረባቸው ፡ ዋነኞቹ ፡ በፍርድ ፡ ዐይናቸው ፡ ታውሮ ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ ተላኩ ።

ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ዮሐንስንም ፡ ፳ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ የሚያወጣ ፡ ሰይፍ ፡ መማለጃ ፡ ተቀብለኻል ፡ ብሎ ፡ ደጃዝማች ፡ ሕዝቅያስ ፡ ከሶ ፡ እንጉሡ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ረታው ፡ ታሰረ ። እንደዚሁም ፡ በሺሕ ፡ ፲፻፹፱ና ፡ ፺ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ላይ ፡ ከመኳንንትም ፡ ከቤተ ፡ ክህነትም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ዐድማ ፡ አድርገዋል ፡ ተብለው ፡ ስለ ፡ ተከሰሱ ፡ ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ አዛዥ ፡ ቄርሎስ ፡ ከሹመቱ ፡ ተሻረ ። ዕጨጌ ፡ ጸጋ ፡ ክርስቶስ ፡ ተሽረው ፡ በርሳቸው ፡ ምትክ ፡ ዕጨጌ ፡ ተብለው ፡ አባ ፡ ዘሚካኤል ፡ ተሾሙ ። በዚሁ ፡ ዐድማ ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ ደጃዝማች ፡ ጊዮርጊስ ፡ የሚባለው ፡ የራስ ፡ አንስጣስዮስም ፡ ልጅ ?

(1) የግዕዙ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ፭ኛውን ፡ ወልደ ፡ ተላይ ፡ ወልደ ፡ ያፍ ፡ አይሮ ፡ ፬ተኛውን ፡ ወልደ ፡ ሹም ፡ ዘእምነገደ ፡ አገው ፡ ጊሲ ፡ ወውላጅ ፡ አድጎ ፡ ይላቸዋል ።

ከዐድመኞቹ ፡ ውስጥ ፡ ገሚሶቹ ፡ ሲታሰሩ ፤ ገሚሶቹም ፡ ሲሸሹ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ከጐንደር ፡ አምልጦ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ አዲስ ፡ እተሾሙት ፡ ዕጨጌ ፡ ዘንድ ሄዶ ፡ ደውሎ ፡ ገባ ።

ንጉሡም ፡ «ወንጀለኛውን ፡ እጄን ፡ ይዛችሁ ፡ መልሳችሁ ፡ ላኩልኝ ፡ ድን ገት ፡ ከእጃችሁ ፡ አምልጦ ፡ የጠፋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ዠምሮ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በመካከላችን ፡ ጸንቶ ፡ የኖረው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ፈርሶ ፡ ጠብ ፡ መከተሉን ፡ እንድታውቁት ፡ ይሁን» ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ዕጨጌ ፡ ላኩ ። ቃል ፡ ኪዳን፡ ይፈርሳል ፡ ማለታቸውም ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከመራ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትና ፡ ከልጁ ፡ ከይትባረክ ፡ ተነጋግረው ፡ መንግሥቱን ፡ ወደ ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘር ፡ ወደ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ስለአስመለሱ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክም ፡ ለዚሁ ፡ ውለታ ፡ የመንግሥቱን ፡ ሢሶ ፡ በቃል ፡ ኪዳን ፡ ለቤተ ፡ ክህነት ፡ የሰጡትን ፡ ሲጠቅሱ ፡ ነው ።

ቀሳውስቱም ፡ መልእክቱን ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ ምሕረት ፡ እንዲደረግለት ፡ የልመና ፡ ደብዳቤ ፡ አስቀድመው ፡ ደጃዝማች ፡ ጊዮርጊስን ፡ እንደ ፡ ታሰረ ፡ ለንጉሡ ፡ አስረከቡት ፤ ንጉሡም ፡ ክተማዬን ፡ ትቶ ፡ ከሹመቱም ፡ ወርዶ ፡ አገሩ ፡ ገብቶ ፡ ይቀመጥ ፡ እንጂ ፡ ለናንተ ፡ ላባቶቼ ፡ ስል ፡ ቅጣቱን ፡ ምሬዋለሁ ፡ ብለው ፡ ላኩባቸው ።

እንደዚሁም ፡ በ፪ኛው ፡ ዓመት ፡ ጳውሎስ ፡ የሚባል ፡ የብላቴን ፡ ጌታ ፡ ገብረ ፡ ልዑል ፡ ልጅ ፡ ንጉሡን ፡ ከዙፋናቸው ፡ ለማውረድ ፡ ከብዙ ፡ መኳንንቶች ፡ ጋራ ፡ ማደሙ ፡ ተሰማና ፡ ታሰረ ፡ እንደ ፡ ታሰረም ፡ እችሎት ፡ ቀርቦ ፡ ሲመረመር ፡ የራሱን ፡ ዘመዶችና ፡ አንድ ፡ አዝማሪ ፡ እመስክ ፡ ላይ ፡ ሌሊት ፡ በጨረቃ ፡ ከሰዎች ፡ ጋራ ፡ ለመሸፈትና ፡ ከጋሎች ፡ ጋራ ፡ ለመደባለቅ ፡ ሲያድም ፡ አይተነዋል ፡ ብለው ፡ መሰከሩ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዐድማው ፡ የተባበሩት ፡ ተይዘው ፡ ታሠሩ ። እሱ ፡ ግን ፡ የጋርማ ፡ (አገው ፡ ምድር) ፡ ባላባት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አስረው ፡ ለወገኖቹ ፡ ያውላችሁ ፡ እናንተ ፡ እንደ ፡ ፈቀዳችሁ ፡ አድርጉት ፡ ብለው ፡ ሰጧቸውና ፡ እነርሱ ፡ ተቀብለው ፡ አገራቸው ፡ ወስደው ፡ ሰቀሉት ፡ ይባላል ።

## ምዕራፍ ፶፫ ።

### ስለ ፡ ምክር ፡ ቤትና ፤ ስለ ፡ ደረጃ ፡ ስለ ፡ ሰልፍና ፡ ጉዞ ፡ ስለ ፡ ንግድ ፡ መስፋፋትና ፡ ስለ ፡ ኬላና ፡ ቀረጥ ፡ ውሳኔ ።

አፄ ፡ ኢያሱ ፡ ከቀድሞ ፡ ዠምሮ ፡ በቅባትና ፡ በተዋሕዶች ፡ መካከል ፡ ክርክር ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ለተዋሕዶች ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ቀሳውስት ፡ እያደሉ ፡ ቅባቶችን ፡ የደብረ ፡ ወርቅን ፡ ካህናት ፡ ይጫኑ ፡ ነበር ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖሶችም ፡ ፍቅራቸውን ፡ ለመግለጽና ፡ ወዳጅነውም ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመሳለም ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መጥተው ፡ ርዳታ ፡ አደረጉ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐባይ ፡ አጠገብ ፡ ጉድሩ ፡ ከሚባሉ ፡ ጋሎች ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ገጠሙ ፤ በጦርነቱም ፡ ጊዜ ፡ ከጋሎቹ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡ የሚመራቸው ፡ ነበርና ፡ ጦሩን ፡ እሁለት ፡ ከፍሎ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ አስቀምጦ ፡ የቀረውን ፡ ራሱ ፡ ይዞ ፡ ውጊያ ፡ ዠመረ ። ንጉሡንም ፡ ለመግደል ፡ ራሱ ፡ ጦሩን ፡ እየሰበቀ ፡ ሲመጣ ፡ ንጉሡም ፡ በያዙት ፡ ጠመንጃ ፡ ተኩሰው ፡ ጣሉት ፤ ሰዎቹም ፡ ሸሹ ።

የንጉሡም ፡ አሽከሮች ፡ ጋሎቹን ፡ ያባርሩ ፡ ዠመር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ተጠባቂ ፡ የነበረው ፡ የጋላ ፡ ጦር ፡ ደረሰና ፡ ባባራሪዎቹ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ጥሎ ፡ ፈጃቸው ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ አኖሬዎስ ፡ የሚባለው ፡ የደጀን ፡ ጦር ፡ አዛዥ ፡ ብቻ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ሲያመልጥ ፡ ብዙ ፡ መኳንንቶችና ፡ ወታደሮች ፡ እዚያው ፡ እጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞቱ ። ይልቁንም ፡ ፋሲል ፡ የተባለው ፡ የንጉሡ ፡ ልጅ ፡ አብሮ ፡ ስለሞተ ፡ ንጉሡ ፡ ጐንደር ፡ ገብተው ፡ ታላቅ ፡ ኀዘን ፡ አድርገው ፡ ሰነበቱ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ንጉሡ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ጦር ፡ ሰብስበው ፡ በሺሕ ፡ ፲፻፺ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እነዚህኑ ፡ የሚሚና ፡ የጉድሩን ፡ ጋሎች ፡ ለመበቀል ፡ ጉዞ ፡ አደረጉ ። የጐጃሙ ፡ ገዥ ፡ ደጃዝማች ፡ አኖሬና ፡ የዳሞቱ ፡ ገዥ ፡ ደጃዝማች ፡ ቱሉ ፡ አማረ ፡ አብረው ፡ ነበሩ ። ንጉሡም ፡ በይባባ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ እስካራት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ የሚበቃኽን ፡ ሥንቅና ፡ ጋሻ ፡ ጦር ኽን ፡ ይዘህ ፡ ያልተከተልከኝ ፡ በብርቱ ፡ ትቀጣለኽ ፡ የሚል ፡ ዐዋጅ ፡ ነግረው ፡ ዐባይን ፡ ተሻግረው ፡ ወደ ፡ ጋሎች ፡ ሠፈር ፡ አቅጣጫ ፡ መጡ ። የጋሎቹም ፡ አለቃ ፡ ዲላሞ ፡ በወገኑ ፡ ያለውን ፡ ጦር ፡ ሰብስቦ ፡ ደጃዝማች ፡ ቱሉ ፡ በተሰለፈበት ፡ በኩል ፡ መጥቶ ፡ ጦርነቱን ፡ ዠመረና ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በኀይል ፡ ይዋጉ ፡ ዠመር ። ቢሆንም ፡ ከንጉሡ ፡ ወገን ፡ ብዙ ፡ ጠመንዣ ፡ ስለነበረ ፡ በተኵሱ ፡ ብዛት ፡ ጋሎቹ ፡ ተሸብረው ፡ ሽሽት ፡ ዠመሩ ። ይልቁንም ፡ የዠግና ፡ መሪ ፡ የነበረው ፡ አለቃቸው ፡ ዲላሞ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ከጋሎቹ ፡ ወገን ፡ ቆሞ ፡ የሚመክት ፡ ጠፋና ፡ ሁሉም ፡ መውጫውን ፡ እየፈለገ ፡ ይሸሽ ፡ ዠመር ። ዲላሞንም ፡ የገደለው ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ የነበረው ፡ ባዘ የሚባል ፡ ጋላ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የንጉሡ ፡ ወታደሮ ፡ አገሩን ፡ ዘረፈው ።

ንጉሡም ፡ ከዚያ ፡ አልፈው ፡ የእናሪያን ፡ አገርና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጐበኙ ፤ እናሪያም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ የእናሪያና ፡ የወለጋ ፡ ባላባቶች ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ለዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ አድርገውት ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ መታያ ፡ እየያዙ ፡ መጥተው ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፡ ተገናኝዋቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ለመመለስ ፡ ጉዞ ፡ ዠምረው ፡ ሳለ ፡ ከልባቸው ፡ የሚወዷቸው ፡ የልጅነታቸው ፡ እናት ፡ ወይዘሮ ፡ ቅድስቴ ፡ በጠና ፡ ታመዋል ፡ ብለው ፡ በጉዞ ፡ ላይ ፡ ነገሯቸው ። ንጉሡም ፡ በነፍስ ፡ ለመድረስ ፡ ጢትና ፡ ማታ ፡ ይገሠግሡ ፡ ዠመር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሞተው ፡ አገኝዋቸውና ፡ መሪር ፡ ኀዘን ፡ አዘኑ ፡ ይባላል ።

ዐፄ ፡ እያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰፊ፡ ከመሆኗ ፡ የተነሣ ፡ ባንዳንድ ፡ ሥፍራ ፡ ሽፍታ ፡ መነሣቱ ፡ ባይቀር ፡ ረዥም፡ ጊዜ ፡ ባለው ፡ ዘመን ፡ መንግሥታቸው ፡ ከጦርነት ፡ ይልቅ ፡ ይበልጥ ፡ ጊዜ፡ ዕረፍት ፡ ሰላም ፡ ሆኖ ፡ ነበር ። በዘመናቸውም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፤ በሹማምን ቶቹ ፡ በኩል ፡ ካለቃ ፡ ወዳለቃ ፡ በምክርና በደረጃ ፡ እየተላለፈ ፡ እንዲፈጸም፡ ያደርጉ ፡ ነበር ። ተራውም ፡ ከዛገሮቹ ፡ (ከሕግ ፡ ዐዋቂዎቹ) ፡ ተነጋግረው ፡ እንደ ፡ ተስማሙት ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ያዳል ፡ ጭፍራ ፡ የሻለቃ ፤ እንዲመ ክር ፡ ቀጥለው ፤ በየክፍላቸው ፡ ያሉት ፡ የጦር ፡ ሻለቆች ፡ እንዲመክሩ ፡ ከዚያ፡ በጠጅ ፡ አዛዥ ፡ በሊቀ ፡ መኳስ ፡ በባላምባራስ ፡ (ሐምበል ፡ ራስ) ፡ በበዥሮንድ ፡ የዕቃ ፡ ቤት ፡ በበዥሮንድ ፡ (የዙፋን ፡ ቤት ፤ የአንበሳ ፡ ቤት)፤ በራቱ ፡ ሊቀ ፡ መጣኒዎች ፡ በ፬ቱ ፡ አዛገሮች ፡ በ፪ቱ ፡ ጸሐፍያን ፤ ወይም ፡ ጸሐፍት ፡ ትእዛዞች፤ በገንደረባ ፡ አዛዥ ፡ በፊታውራሪ ፡ በግራዝማች ፡ (1) በቀኛዝማች ፡ በጥቃቅን ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ መከዳንና ፡ ዙፋንን ፡ በሚጠብቀው ፡ ነጋድራስ ፡ በጠረይሰንበ ፡ (የጉበዛዝት ፡ ጋሻ ፡ ዣግሬዎች ፡ አለቃ) ፡ አዛዥ በራቅ ፡ ማሰሬ ፤ በደጃዝማች፤ በታላቅ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፤ በዳሞት ፡ ጻሕፈ ፡ ላም ፤ በጐጃም ፡ ነጋሽ ፤ በአማራ፡ ጻሕፈ ፡ ላም ፡ በበጌምድር ፡ አዝማች ፡ በበትረ ፡ ያሬክ ፤ በወርተረኛው ፡ ሊቀ ፡ ካህን ፤ በሰሜን ፡ አጋፋሪ ፡ በትግሬ ፡ መኰንን ፤ በአኵስም ፡ ንቡረ ፡ እድ ፤ በዓድዋ ፡ ደጃዝማች ፡ (በመኻል ፡ ትግሬ ፡ ገዥ)፤ በዐቃቤ ፡ ሰዓት ፡ በራስ፤ በራስ ፤ ቢቶደድ ፡ በኩል ፡ እየተመከረና ፡ እየተላለፈ ፡ በመጨረሻ ፡ ንጉሡ ፡ ይወስናል ። የነዚህም ፡ የሹማምንትና ፡ የመኳንንት፡የደረጃና ፡ የተርታ ፡ ማዕርግ፡ ከዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ በፊት ፡ በነበሩት ፡ ጊዜ ፡ በርሳቸውም ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ ፊትም፡ በተነሡት ፡ ነገሥታት ፡ ጊዜ ፡ በከፍታና ፡ በዝቅታ ፡ ሥልጣናቸው ፡ ይለያያል ። ለምሳሌ ፤ በዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ በመጨረሻ ፡ የሚመክ ረው ፡ ዐቃቤ ፡ ሰዓት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይገልጽልናል ፤ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ከን ጉሡ ፡ በፊት ፡ ከሌሎቹ ፡ በመጨረሻ ፡ የሚመክረው ፡ እንደራሴው ፡ ራስ ፡ ቢቶ ደዱ ፡ መሆኑን ፡ ይገልጻል ። የዚህም ፡ አንዱን ፡ የማዋረድና ፡ ሌላውን ፡ የማክ በር ፡ የማስቀደምና ፡ የመለዋወጥ ፡ ምክንያት ፡ ከታሪኩ ፡ ስንፈልግ፡ የምናገኘው፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ አኳኋን ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፡ ዳሞት ፤ ጻሕፈ ፡ ላም ፡ ከነሕዝቡ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ራስ ፡ እያመጠ፡ ያስቸገረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ወሬኛን ፡ (እነግሣለሁ ፡ ብሎ ፡ የተነሣውን) ፡ ብገሩ፡ ላይ ፡ ተቀብሎ ፡ ያስተናገደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የዳሞት ፡ ጻሕፈ ፡ ላምነት ፡ ማዕርግ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ይወርዳል ። የአማራ ፡ ሣይንት ፡ ጻሕፈ ፡ ላም ፡ ወይም ፡ ትግሬ ፡ መኰንን ፡ አለዚያም ፡ የዐድዋ ፡ ደጃዝማች ፡ በታማኝነት ፡ ለንጉሡ ፡ ያገለገለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የንጉሡን ፡ ጠላት ፡ በመዋጋት ፡ ማርኮ ፡ እጁን ፡ በመስጠት ፡

(1) የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ግራዝማች ፡ ከፊታውራሪ ፡ ይበልጥ ፡ ነበር ፤ ይኸም ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒልክና ፡ በንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ጊዜ ፡ የፊታውራሪ ፤ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ማዕርግ ፡ ከራሶች ፡ እንደሚበልጠው ፡ ማለት ፡ ነው ።

ወይም ፡ ራሱን ፡ ቈርጦ ፡ ግዳይ ፡ በመጣል ፡ ደስ ፡ ያሰኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ደረጃውና ፡ ክብሩ ፡ ከፍ ፡ ይደረግለታል ። እንዲሁም ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ሲሸፍት ፡ ትግሬ ፡ መኰንን ፡ ሲታመን ፡ ትግሬ ፡ መኰንኑን ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ድረስ ፡ እንዲገዛ ፡ ያውጁለታል ። ትግሬ ፡ መኰንኑ ፡ አምጦ ፡ ባሕር ፡ ነጋሹ ፡ የታመነላቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የግዛቱ ፡ ሥልጣን ፡ ከባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ማኽል ፡ ትግሬ ፡ ድረስ ፡ እንዲዘረጋ ፡ ያደርጉታል ። ደግሞ ፡ ፩ ፡ ንጉሥ ፡ ከመንግሡ ፡ በፊት ፡ የነበረበትን ፡ አገር ፡ እዙፋን ፡ ለመውጣት ፡ የረዳውን ፡ መኰንን ፡ ማሳደግ ፡ ማክበር ፡ ይወዳል ።

ደግሞ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ መንፈሳዊነት ፡ ያጠቃው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዐቃቤ ፡ ሰዓቱ ፡ ራቅ ፡ ማሰሬው ፡ ቄስ ፡ ዐጼው ፡ ከፍ ፡ እንዲል ፡ ያደርጋል ። ንጉሡ ፡ የዠግንነትና ፡ የጦርነት ፡ የድል ፡ አድራጊነት ፡ ጠባይ ፡ እንዳለው ፡ ሊቀ ፡ ዐቢያን ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ራስ ፡ ቢቶደድ ፡ የሚባሉትን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አለቆችና ፡ እንደራሴዎች ፡ ከፍ ፡ እንዲሉ ፡ እያደረገ ፡ ባለሟልነትንና ፡ ሞገስንም ፡ በፊቱ ፡ እንዲያገኙ ፡ ያደርጋቸዋል ። ሁሉም ፡ በሁሉም ፡ የሚሆነው ፡ ንጉሡ ፡ በልቡ ፡ ደስ ፡ ያለውና ፡ ባይኑ ፡ ፊት ፡ የተወደደው ፡ ነው ። ግማሾቹ ፡ ነገሥታት ፡ ግን ፡ ዠግንነትንም ፡ መንፈሳዊነትንም ፡ አስተዳዳሪነትንም ፡ አጣምረው ፡ የመያዝ ፡ ጠባይ ሲኖርባቸው ፡ ወዳንደኛው ፡ ወገን ፡ ጨርሰው ፡ ሳያዘነብሉ ፡ ያባቶችን ፡ ወግና ፡ ሥርዐት ፡ ከሊቃውንቱና ፡ ካዛዦቹ ፡ (ከሕግ ፡ ዐዋቂዎቹ) ፡ ጠይቀው ፡ ባለፈው ፡ በዘረዘርነው ፡ ደረጃ ፡ ያለአድልዎ ፡ በትክክል ፡ መሥራት ፡ እስከ ፡ ተቻለ ፡ ድረስ ፡ ይሞክራሉ ። ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ የነዚህ ፡ አያያዝ ፡ የተሻለ ፡ መሆኑን ፡ አንባቢ ፡ እንደ ፡ ሚረዳው ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

አሁን ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ጕዳይ ፡ ትተን ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ በፊትና ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ባሉት ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ በሚነሡት ፡ ነገሥታት ፡ ዘመን ፡ የሚደረገውን ፡ ከታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ የምናገኘውን ፡ የሰልፍና ፡ የጕዞ ፡ ሥርዐት ፡ እንመልከት ።

ንጉሥ ፡ በጦርነትም ፡ በሰላምም ፡ ጊዜ ፡ ታጅቦ ፡ ሲጓዝ ፡ በፊትና ፡ በኋላ ፡ ካሉት ፡ ሹማምንትና ፡ ወታደር ፡ እርቆ ፡ በመከከል ፡ በበቅሎ ፡ በፈረስ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በእግርም ፡ ይሄዳል ። ሲሄድም ፡ ከስተ ፡ ፊቱ ፡ ራቅ ፡ ብለው ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ የያዙ ፡ ነጋሪት ፡ የጫኑ ፡ ቀጥለው ፡ የነፍጠኛ ፡ ጭፍሮች ፡ ከነርሱም ፡ ቀጥሎ ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ (መደቡት ?) ከርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ፬ ፡ የሚያማምሩ ፡ በቅሎዎች ፡ ንጉሣዊ ፡ ዕቃ ፡ የተጫኑ ፡ እፊት ፡ ፊት ፡ ይሳባሉ ። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ሥዕለ ፡ ኵርዐተ ፡ ርእስ ፡ (የአክሊለ ፡ ሦክ ፡ ሥዕል ፡) ከድባብ ፡ ጋራ ፡ በ፬ ፡ ሰይፍ ፡ ዠግሬ ፡ ታጅቦ ፡ ይሄዳል ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ሆነው ፡ ከንጉሡ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይሄዳሉ ።

ከንጉሡ ፡ በስተኋላ ፡ (ወይም ፡ ባጠገብ) ፡ ግራዝማችና ፡ ቀኛዝማች ፡ የሆኑ ፡ የሰይፍ ፡ ዠግሬ ፡ ሹማምት ፡ የሐር ፡ መነሳንስ ፡ (ጭራ)ና ፡ ድባብ ፡ ይዘው ፡ ይሄ

ዳሉ ። ከነርሱ ፡ በስተኋላ ፡ ሁለት ፡ ባልደራሶች ፡ ሁለት ፡ ፈረሶች ፡ እየሳቡ ፡ ሲሄዱ ፡ ከነርሱ ፡ በስተኋላ ፡ ደግሞ ፡ ዙፋንና ፡ መከዳ ፡ ያዥዎች ፡ ይሄዳሉ ። ከነርሱ ፡ በኋላ ፡ ራቅ ፡ ብለው ፡ የጋሻ ፡ ዠግሬ ፡ ጭፍሮች ፡ ከነርሱ ፡ በኋላ ፡ ራሶች ፡ ከነርሱ ፡ በኋላ ፡ ቢቶደድ ፤ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ መኳንንቱ ፡ በሙሉ ፡ ከመኳንንቱ ፡ በኋላ ፡ ሠራዊቱ ፡ ይሄዳል ። ከሁሉ ፡ መጨረሻ ፡ ደግሞ ፡ ደጀን ፡ ሆኖ ፡ ሠፈር ፡ የሚጠብቀው ፡ አዝማች ፡ ከነጭፍራው ፡ ይከተላል ። ይነስ ፡ ይብዛ ፡ የጕዘው ፡ ሁኔታ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ መሆኑን ፡ ታሪክ ፡ ነገሥቱን ፡ ተመልከት ።

ይህን ፡ ከቀድሞ ፡ ዠምሮ ፡ የነበረውን ፡ ጕዞ ፡ ከተመለከትን ፡ በኋላ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ጕዳይ ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ዘመንና ፡ ታሪክ ፡ ላይ ፡ እንመለስ ።

※ ※

ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ በዘመናቸው ፡ ጣልቃ ፡ እየገባ ፡ ከሚደረገው ፡ ጦርነት ፡ በቀር ፡ በተረፈ ፡ አገሩ ፡ ሰላማዊ ፡ በመሆኑ ፡ እርሻና ፡ ንግድ ፡ በጣም ፡ ተስፋፍቶ ፡ ነበር ። በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ከስናር ፡ ከካይሮ ፡ ከምጥዋ ፡ ብዙ ፡ ሸቀጥ ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ወደ ፡ ሌሎችም ፡ አውራጃዎች ፡ እየገባ ፡ እንደዚሁም ፡ ከጐንደርና ፡ ከውራጃው ፡ እኽል ፡ ቅቤ ፡ ቡና ፡ ቈዳ ፡ ከብት ፡ ወደ ፡ ውጪ ፡ እየወጣ ፡ ይሸጥ ፡ ነበር ፤ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱም ፡ የወግና ፡ የሥርዐት ፡ ደንብ ፡ ለማበጀት ፡ ከመጣራቸው ፡ ጋራ ፡ የንግዱም ፡ ጕዳይ ፡ በደንብ ፡ እንዲሆን ፡ ይጥሩ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ንግዱ ፡ በኬላና ፡ በቀረጥ ፡ ብዛት ፡ እንዳይቸገር ፡ አስበው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ የቀረጥ ፡ ደንብ ፡ ካማካሪዎቻቸው ፡ መክረው ፡ ዐወጁ ።

፩ኛ ፡ በንድ ፡ አውራጃ ፡ አንድ ፡ ኬላ ፡ ብቻ ፡ እንዲሆን ።

፪ኛ ፡ በ፫ ፡ በቅሎ ፡ ጭነት ፡ አንድ ፡ አሞሌ ፡ ጨው ።

፫ኛ ፡ በ፰ ፡ አህያ ፡ ጭነት ፡ አንድ ፡ አሞሌ ፡ ጨው ፡ እንዲከፍል ።

፬ኛ ፡ በትከሻ ፡ የሚነግደው ፡ ቀረጥ ፡ እንዳይከፍል ።

፭ኛ ፡ በጐንደር ፡ መከከል ፡ ባለው ፡ ገበያ ፡ የሚውለው ፡ የበግና ፡ የፍየል ፡ ነጋዴ ፡ በጭራሽ ፡ ድላል ፡ (ቀረጥ) ፡ እንዳይከፍል ፡ አደረጉ ።

ይኸውም ፡ ንግድ ፡ በደንብ ፡ እንዲካሄድ ፡ የዚሁ ፡ ልማድ ፡ ያላቸውን ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ነጋድራስ ፡ ሆነው ፡ እንዲሠሩ ፡ ሾሟቸው ። ከነዚህም ፡ አንደኛው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስሙን ፡ የጠቀስነው ፡ ሙራድ ፡ የተባለውን ፡ የአርመን ፡ ተወላጅ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ በኩል ፡ ከህንድ ፡ ከየመን ፡ የሚመጣውን ፡ ሸቀጥ ፡ ተቆጣጣሪ ፡ ሁለተኛው ፡ ሃጂ ፡ ዐሊ ፡ የተባለውን ፡ ከሱዳን ፡ ከግብጽ ፡ ከኑብያ ፡ ለሚመጣው ፡ ሸቀጥ ፡ ተቆጣጣሪ ፡ አድርገዋቸው ፡ ነበር ። ሙራድና ፡ ሃጂ ፡ ዐሊም ፡ ከንግዱ ፡ በቀር ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የፖሊቲክ ፡ ግንኙነት ፡ ይረዷቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በነርሱ ፡ አማካይነት ፡ ከፈረንሳዊ ፡ ንጉሥ ፡ ከሉዊ ፡ ፲፬ኛና ፡ ከህንድ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ጋራ ፤ ተዋውቀው ፡ ይላላኩ ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የህንድን ፡ አብዛኛ ፡ ክፍል ፡ የሆላንድ ፡ መንግሥት ፡ ይገዛ ፡ ነበርና ፡ የህንድ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ በንጉሡ ፡

ስም ፡ አድርጎ ፡ በሺሕ ፡ ፯፻፺፪ ፡ ዓ፡ ም፡ የወዳጅነት ፡ ደብዳቤ ፡ ሌላም ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ጨምሮ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ደወል ፡ ልኮላቸው ፡ ነበር ፡ ንጉሡም ፡ ይኸንኑ ፡ ደወል ፡ ጐንደር ፡ ራሳቸው ላሠሩት ፡ ለደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰጡ ። የደወሉም ፡ ድምፅ ፡ ከጐንደር ፡ እስከ ፡ ደምቢያ ፡ ይሰማ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። የደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴንም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሥዕል ፡ ውስጡን ፡ በጣም ፡ አሳምረውት ፡ ነበር ፡ ይባላል ። የሆላንድ ፡ መንግሥት ፡ ይኸንን ፡ ደወልና ፡ ሌላም ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ መላኩ ፡ ከፈረንሣዊ ፡ መንግሥት ፡ በፊት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለመግባትና ፡ ለመፎካከር ፡ ሲል ፡ ነው ይባላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፶፬ ።

## በመጠጥ ፡ የተሸነፈው ፡ ሰውዬና ፡ የንጉሡ ፡ ፈረስ ፡- የቁም ፡ ጸሐፊና ፡ የንጉሡ ፡ በግ ።

ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ፍርድ ፡ አዋቂነታቸውንና ፡ መሐሪነታቸውን ፡ የሚያስረዳውን ፡ በዘመናቸው ፡ የሠሩት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የሚነገርላቸውን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንጽፋለን ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በጥቂት ፡ የልፍኝ ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ታጅበው ፡ ጐንባሲት ፡ በምትባለው ፡ በር ፡ ወጥተው ፡ ፈረሳቸው ፡ በወርቅ ፡ መጣብር ፡ አጊጠ ፡ ባማረ ፡ የወርቅ ፡ ዕቃ ፡ ተጭኖ ፡ እፊታቸው ፡ እየተሳበ ፡ ሲሄድ ፡ አንድ ፡ መጠጥ ፡ ያሸነፈው ፡ ሰው ፡ እመንገድ ፡ አገኛቸውና ፡ ይህ ፡ ፈረስ ፡ ይሸጣልን ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸውና ፡ አለፈ ። ንጉሡም ፡ በትዕግሥት ፡ ከኋላው ፡ ተከትላችሁ ፡ የሚገባበትን ፡ ቤቱን ፡ እዩ ፡ ብለው ፡ ስላዘዙ ፡ የታዘዘው ፡ አሽከር ፡ በመጠጥ ፡ የተሸነፈው ፡ ሰውዬ ፡ የገባበትን ፡ ቤት ፡ አይቶ ፡ ተመለሰ ፤ በማግሥቱ ፡ ልብሰ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ለብሰው ፡ ግሩማን ፡ (ዠርጋዶች) ፡ የሆኑትን ፡ ጋሻ ፡ ዣግሬዎቻቸውን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ አቁመው ፡ እችሎት ፡ ተቀመጡ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያን ፡ ሰው ፡ አስጠርተው ፡ ያንኑ ፡ ፈረስ ፡ ቀድሞ ፡ ተጭኖ ፡ የነበረውን ፡ የወርቅ ፡ ዕቃ ፡ እንደተጫነ ፡ እመካከል ፡ አስቁመው ፡ ያውልኽ ፡ ትላንት ፡ ልትገዛው ፡ ጠይቀኽ ፡ የነበረውን ፡ ፈረስ ፡ አሁን ፡ ግዛው ፡ አሉት ። ይኸንንም ፡ ማለታቸው ፡ ግዥውን ፡ እንደ ፡ ትላንትናው ፡ በድፍረት ፡ የገፋበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ መልስ ፡ ያጣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለመቅጣት ፡ ይመስላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሰውዬው ፡ ጮሌ ፡ የነገር ፡ መላ ፡ ዐዋቂ ፡ ኖሮ ፡ ትላንት ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ከነበሩት ፡ ባልንጀሮቼ ፡ መክሬ ፡ ነው ፡ የምገዛው ፡ ሲል ፡ መለሰ ።

ንጉሡም ፡ «ትላንትና ፡ ስናይህ ፡ ብቻህን ፡ አልነበርህምና ፡ ምን ፡ ባልንጀራ ፡ ነበረኽ» ፡ ቢሉት ፡ «ትላንትና ፡ የነበሩት ፡ ባልንጀሮቼ ፡ ከጠላና ፡ ከጠጅ ፡ የሚገቡት ፡ ሥሮች ፡ እነጌሾ ፡ እንግራዋ ፡ እነብቅል ፡ ናቸው» ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ፡ ንጉሡም ፡ የንግግሩ ፡ አካሄድ ፡ ስላማቃቸው ፡ ቍጣቸውን ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ መልሰው ፡ በሰላም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ እንዲሄድ ፡ አሰናበቱት ፡ ይባላል ።

ደግሞ ፡ የድቍስ ፡ ቀንድና ፡ ቢላዋ ፡ ከነማኅደሩ ፡ ባንገቱ ፡ ያንጠለጠለ፡ የንጉሡ ፡ የበግ ፡ ሙክት ፡ ነበር ። እሱም ፡ በከተማው ፡ እየዞረ ፡ የተሰጣውን ፡ የመንደር ፡ እኽል ፡ ይበላ ፡ ነበር ፤ ሰውም እንዳይመታው ፡ የንጉሥ ፡ በግ ፡ በመ ሆኑ ፡ ይፈራ ፡ ነበር ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ የጐንደር ፡ ቄም ፡ ጸሐፊ፡ ካህን ፡ ቍጭ ፡ ብሎ ፡ ሲጽፍ ፡ ይኸው ፡ በግ ፡ መጥቶ ፡ አጠገቡ ፡ ያሰጣውን ፡ እኽል ፡ በላበት ፤ ካህኑም ፡ ተነሥቶ ፡ ይዞ ፡ እቤቱ ፡ አግብቶ ፡ አርዶ ፡ አንገቱ ፡ ባለው ፡ በራሱ ፡ ድቍስ ፡ በላው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ካህኑ ።
ዕድሜ ፡ እለምናሁ ፡ ለንጉሥ ፡ ኢያሱ ፤
ያንን ፡ የበግ ፡ ሙክት ፡ ቢሰደው ፡ ንጉሡ ፡
በገዛ ፡ ቢለዋው ፡ በገዛ ፡ ድቍሱ ፤
አመስግኜ ፡ በላሁ ፡ ከነራስ ፡ ምላሱ ።
(ማነኽ? ፡ እንጃልኽ) ፡ የሚል ፡ ጽፎ ፡ በጕፋያ ፡ መስጫ ፡ ሜዳ ፡ ጥሎት ፡ ተገኘ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መዠመሪያ ፡ ጽሑፉ ፡ ፪ኛ ፡ በብዙ ፡ ምርመራ ፡ ከህኑ ተገኝቶ ፡ ተይዞ ፡ እንጉሡ ፡ ፊት ፡ ቀረበና ፡ ይኸን ፡ የጻፍክ ፡ አንተ ፡ አይደለኽምን ፡ እውነቱን ፡ ንገረኝ ፡ ብለው ፡ ንጉሡ ፡ ጠየቁት ፤ እሱም ፡ እተቀበው ፡ ንጉሥ ፡ ፊት ፡ ቀርቤ ፡ ውሸት ፡ አልናገርም ፤ መቸገር ፡ ያስደፍራልና ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ የንጉ ሡን ፡ በግ ፡ ሲፈራ ፡ አርጄ ፡ የበላሁ ፤ ወረቀቱንም ፡ የጻፍኩ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ሲል ፡ በድፍረት ፡ ተናገረ ።

ንጉሡም ፡ በሐቀኝነቱ ፡ አመስግነው ፡ የገንዘብ ፡ ጕርሻ ፡ ሰጥተው ፡ በሰላም ፡ አሰናበቱት ፡ ይባላል ። ይኸንን ፡ የመሳሰለ ፡ ነገር ፡ በሌሎቹ ፡ ነገሥታት ፡ እንደሚደረ ገው ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱም ፡ ጊዜ ፡ የተደረገ ፡ አለ ። ይኸውም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ባንድ፡ ፊት ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ባይጠፋበት ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ የቀልድና ፡ የጨዋታ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ቀልዱን ፡ እቁም ፡ ነገር ፡ ላለመደባለቅ ፡ አኳኋኑም ፡ እላይ ፡ በተባለው ፡ አኳኋን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እዚህ ፡ ውስጥ ፡ አበርክቶ ፡ ለመጻፍ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ አል ታየንም ።

## ምዕራፍ ፡ ፶፭ ።

## ስለ ፡ ዓለም ፡ ሁኔታና ፡ - ስለ ፡ ፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ትልቅነት ፡ ባጭሩ ።

ነገድና ፡ ዘር ፡ እየለየ ፡ ለድል ፡ አድራጊው ፡ እየራቀ ፡ ለብቻው ፡ አም ልጦ ፡ ከሚኖረው ፡ በቀር ፡ አብዛኛውን ፡ የምዕራብና ፡ የምሥራቅ ፡ አገር ፡ ፩ ፡ ኃይለኛ ፡ እየተነሣ ፡ በውስጡ ፡ አድርጎ ፡ ይገዛው ፡ ነበር ። ኃይለኛም ፡ ተብለው ፡ በጥንትና ፡ በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩት ፡ ቂሮስ ፡ የፋርሱ ፡ ናቡከደነፆር ፡ የባቢሎኑ ፤ እስክንድር ፡ የመቄዶንያው ፤ ቄሣር ፡ የሮማው ፡ አኒባል የካርታገፁ ፤ አቲላ ፡ የሑኑ ፤ ሻርለማኝ ፡ የፍራንኩ ፤ ፍሬዴሬክ ፡ ባርባሩስ ፡ የጀር

መኑ ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ መሪዎች ፡ ከተፈጥሯቸው ፡ ባገኙት ፡ ዕድል ፡ በሕዝባቸው፡ ዘንድ ፡ በጣም ፡ የሚፈሩ ፡ ነበሩ ። የጦር ፡ ሠራዊታቸውም ፡ በፍርሃትም ፤ በፍቅርም ፡ ላዋሉት ፡ ጉዳይ ፡ እየተከተለ ፡ ይውልላቸው ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ በየጊዜያቸው ፡ ከራሳቸው ፡ አገር ፡ ድንበር ፡ ውስጥ ፡ እያለፉ ፡ ሌላውን ፡ ሰፊ ፡ ግዛት ፡ አስገብረው ፡ ብዙ ፡ ታሪክ ፡ ትተው ፡ አልፈዋል ።

የሮማን ፡ ግዛት ፡ ጀርመኖች ፡ ከአውሮፓ ፡ ሰሜን ፡ ዐረቦች ፡ ከደቡብ ፡ ወገን ፡ መጥተው ፡ በየጊዜው ፡ እየወጉ ፡ ካደከሙት ፡ በኋላ ፡ እሁለት ፡ ተከፈለ ። ከሁለቱ ፡ የሮማ ፡ ግዛት ፡ ሙስጥ ፡ እነዚህ ፡ የጀርመን ፡ ዘር ፡ የሆኑት ፡ ነገዳቸውን፡ እየለዩ ፡ ለየራሳቸው ፡ መንግሥትን ፡ስላቆሙና ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ጉልበት ፡ ስላበጁ፡ ብዙዎቹን ፡ አንድነት ፡ አድርጎ ፡ ለመግዛት ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ አልቻል ፡ አለ ። ስለዚህ ፡ ከሮማ ፡ ውድቀት ፡ በኋላ ፡ ሻርለማኝ  የፍራንኮች ፡ ንጉሥ ፡ የምዕራብ ፡ አገሮች ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተብሎ ፡ እሱና ፡ ተከታዮቹ ፡ ከ፯፻፺፱ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ፰፻፹፰ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ቈይቶ ፡ ወደቀና ፡ እሱ ፡ ባንድ ፡ በትረ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ያስተዳድራቸው ፡ የነበሩት ፡ የጀርመን ፡ የፈረንሳዊ ፡ የኤስፓኝ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥቶች ፡ ተከፋፍለው ፡ መንግሥታቸውን ፡ ለብቻ ፡ ማቆም ፡ ዠመሩ ።

ከምዕራብ ፡ የሻርለማኝ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ውድቀት ፡ በኋላ ፡ ከኢጣሊያ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ያሉት ፡ ጀርመኖች ፡ በኦቶንና ፡ በፍሬዴሬክ ፡ ባርበሩስ ፡ ጊዜ ፡ ኀይል ፡ አገኙና ፡ የኢጣሊያንንና ፡ የኦትሪሺን ፡ በቅራቢያው ፡ ያሉትን ፡ አገሮች ፡ ወደ ፡ ራሳቸው ግዛት ፡ ደባልቀው ፡ «የተቀደሰው ፡ የሮማና ፡ የጀርመን፡ ግዛት» ፡ እየተባለ ፡ እስከ ፡ ፲፮ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ቈየ ።

የሻርለማኝ ፡ የምዕራቡንና ፡ የፍሬዴሬክን ፡ «የቄሣር ፡ግዛት» ፡ (አምፒር) ፡ በመሆኑ ፡ ለይተን ፡ ተናገርን ፡እንጂ ፡ ከሻርለማኝ ፡ በኋላ ፡ ከፍሬዴሪክ ፡ቀደም፡ ብሎ ፡ የእንግሊዝ ፡ የፈረንሳዊ ፡ የኤስፓኝ ፡ የፖርቱጋል ፡ የስዊድን ፡ የኖርቬዥ ፡ ሕዝቦች ፡ . . . . መንግሥታቸውን ፡ በደንብ ፡ አቁመዋል ። ከነዚሁም ፡ ስለ ፡ ኤስፓኝና ፡ ስለ ፡ ፖርቱጋል ፡ ስለ ፡ ቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ባለፈው ፡ ጽፈናል ። የቀሩትም ፡ የሞስኰ ፡ ትልቅ ፡ የመስፍን ፡ ግዛት ፡ (ግራን ፡ ዱክ ፡ ደ ፡ ሞስኩ)፡ የሊቷኒ ፡ ትልቅ ፡ የመስፍኑ ፡ ግዛት ፡ (ግራንድ ፡ ዱክ ፡ ደ ፡ ሊቷኒ) ፡ እየተባሉ፡ ለብቻ ፡ነጻ ፡ ሆኑ ። የባልካንና ፡ የታናሽ ፡ እስያን ፡ ግዛቶች ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደ ፡ ተተረከው ፡ መዠመሪያ ዐረቦች ፡ ከዚያም ፡ ሞንጎሎችና ፡ ቱርኮች ፡ እንደ ፡ ያዟቸው ፡ ነው ። ከነዚህ ፡ ከዘረዘርናቸው ፡ መንግሥታት ፡ ውስጥ ፡ እንግሊዝና፡ ፈረንሳዊ ፡ በግዛት ፡ የተነሣ ፡ የበረታ ፡ ጠብ ፡ አደረጉ ። የመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ታሪክ ፡ እማለቂያው ፡ ላይ ፡ ከሺሕ ፡ ፫፻ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፬፻፶ ፡ ዓመት ድረስ ፡ የፈረንሳዊና ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ባንድ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ሲቀጥሉ ፡ ሲያቋሙ ፡ ረዥም ፡ ጦርነት ፡ አደረጉ ። እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ መንግሥታቶች ፡ ከዚህ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ በወሰንም ፡ በንግድም ፡ ሲጋጩና ፡

ሲዋጉ ፡ ጠላትነታቸው ፡ እየበረታ ፡ ሄደ ። በመጨረሻም ፡ ለዚህ ፡ ለመቶ ፡ ዓመት ፡ ጦርነት ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ኤድዋርድ ፡ ፫ኛ ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ ከፊልጶስ፡ አራተኛ ፡ ከፈረንሳዊ ፡ ንጉሥ ፡ በናቴ ፡ በኩል ፡ እወለዳለሁና ፡ የፈረንሳዊ ፡ ዙፋኑና ፡ ዘውድ ፡ ይገባኛል ፡ ሲል ፡ ከስድስተኛ ፡ ፊልጶስ ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ቀሰቀሰና ፡ እንግሊዞች ፡ ፈረንሳዮችን ፡ በባሕርም ፡ በመሬትም ፡ ጦርነት ፡ አሸነፏቸው ። ፈረሳንዮችም ፡ ከእንግሊዞች ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሲመክቱ ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ የፈረንሳዊ ፡ ሕዝብ ፡ ውስጣዊ ፡ ጦርነት ፡ እያነሣ ፡ ስለ ፡ ተቸገሩ ፡ በሺሕ ፡ ፫፻፰ ፡ ዓመት ፡ ብሬቲኝ ፡ ላይ ፡ ከግዛታቸው ፡ አብዛኛውን ፡ ለእንግሊዞች ፡ ለቀው ፡ ታረቁ ።

ይህ ፡ ዕርቅ ፡ ደጉ ፡ የሚባለው ፡ በዮሐንስ ፡ ሁለተኛ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ የተነሣው ፡ (ዐዋቂው ፡ ሻርል ፡ አምስተኛ) ፡ የፈረንሳዮችን ፡ የተዋጊነት ፡ መንፈስ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ቀስቅሶ ፡ እንግሊዞችን ፡ ወግቶ ፡ ቀድሞ ፡ ከገቡበት ፡ ከማኽል ፡ ፈረንሳዊ ፡ አስወጥቶ ፡ ወደ ፡ ካሌ ፡ አስጠጋቸው። ነገር ፡ ግን አንዱ ፡ ንጉሥ ፡ ለዠግንነትና ፡ ለዐዋቂነት ፡ ሲታደል ፡ ሌላው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አይታደልምና ፡ ከሻርል ፡ ፭ኛ ፡ ቀጥሎ ፡ የተነሣው ፡ ሻርል ፡ ፮ኛ ፡ አገዛዝ ፡ ባለማወቁ ፡ የፈረንሳዊ ፡ ሕዝብ ፡ አንደኛው ፡ አርማኛክ ፡ አንደኛው ፡ ቡርጊኞ ፡ እየተባለ ፡ ወገን ፡ ለየና ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ይዋጋ ፡ ዠመር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንግሊዞች ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ስላገኙ ፡ ከደሴታቸውና ፡ ከካሌ ፡ እየተደራጁ ፡ መጥተው ፡ ኤዚንኩር ፡ ላይ ፡ ፈረንሳዮችን ፡ ወግተው ፡ አሸነፉ ። በኋላም ፡ የእንግሊዙ ፡ ንጉሥ ፡ ሐንሪ ፡ ፭ኛ ፡ የፈረንሳዊውን ፡ ንጉሥ ፡ የሻርል ፡ ስድስተኛውን ፡ ልጅ ፡ አገባና ፡ የፈረንሳዊ ፡ ንጉሥ ፡ ተባለ ። የፈረንሳዊ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ የነበረው ፡ ዳልፊን ፡ ሻርል ፡ ፯ኛው ፡ የፈረንሳዊ ፡ ንጉሥ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ከእንግሊዞች ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ይቀጥል ፡ ዠመር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እንግሊዞች ፡ በማናቸውም ፡ ግንባር ፡ እያሸነፉ ፡ ፓሪስ ፡ ከተማና ፡ እማኽል ፡ ገብተው ፡ ፈረንሳዊን ፡ ይዘው ፡ ይገዙ ፡ ዠመር ። በዚህ ፡ መካከል ፡ በሺህ ፡ ፬፻፳፱ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ዣን ፡ ዳርክ ፡ (የቀስት ፡ ዮሐና) ፡ የምትባል ፡ ልጃገረድ ፡ በምትሠራው ፡ የቅድስና ፡ ሥራ ፡ ቀሳውስትም ፤ መሃይምንም ፡ ይቺ ፡ ከእንግሊዞች ፡ ቀንበር ፡ ታድነናለች ፡ እያለ ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋት ፡ ዠመር ፤ ፈረንሳዊንም ፡ ለማዳን ፡ ቅዱስ ሚካኤል ፡ ተገልጦ ፡ አነጋገረኝ ፡ ያለችውም ፡ መዠመሪያ ፡ ጥርጣሬን ፡ ቢያሳድር ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ይፈተን ፡ ተብሎ እርሷ ፡ እንደ ፡ ጠየቀችው ፡ ከፈረንሳዊ ፡ ንጉሥ ከሻርል ፡ ፯ኛ ፡ ጦር ፡ ተቀብላ ፡ በፓቴይ (patay) ፡ እንግሊዞችን ፡ ተዋግታ፡ አሸነፈች ፤ ከፓሪስም ፡ እንግሊዞችን ፡ ለማስወጣት ፡ ስትዋጋ ፡ ቈስላ ፡ ሳለች ፡ ጦርነቱን ፡ በዠመረች ፡ በመቱ ፡ ተማርካ ፡ በእንግሊዞች ፡ እጅ ፡ ወደቀች ። አሳልፈው ፡ እንድትማረክ ፡ ያደረጓትም ፡ ወገኖቿ ፡ ናቸው ፤ ፈረንሳዮች ፡ በቅድስና ፡ በብፅዕና ፡ ታምራት ፡ አደረገች ፡ ይሏት ፡ የነበረውን ፡ እንግሊዞች ፡ ወደ ፡ ጥንቈላ ፡ ወደ ፡ አስማት ፡ አዞሩና ፡ ከሰይጣን ፡ ጋራ ፡ እየተነጋገረች ፡ ታምራት ፡ ታደርጋለች ፡ ብለው ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ አቃጠሏት ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ እንግሊዞች ፡ አልቀናቸውም ሻርል ፡ ፯ኛ ፡ ጦሩን ፡ እያደር ፡ አደ

ረጅ ፡ በውስጡም ፡ ርስ ፡ በርስ ፡ ይጣሉ ፡ የነበሩትን ፡ አስማምቶ ፡ እንግሊዞችን ፡ በማባረር ፡ እንዲያብሩ ፡ አደረገ ፤ ፈረንሳዮችም ፡ ባንድነት ፡ በንጉሣቸው ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ተሰብስበው ፡ በሺህ ፡ ፬፻፶፫ ዓመት ፡ ላይ ፡ ተዋግተው ፡ በጭራሽ ፡ ከካሌ ፡ በቀር ፡ ከቀረው ፡ የፈረንሳዊ ፡ ግዛት ፡ እንግሊዞችን ፡ አስወጧቸውና ፡ የመቶ ፡ ዓመት ፡ ጦርነት ፡ ባጭሩ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ተፈጸመ ።

ፈረንሳዮችም ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፤ እያደር ፡ እየበረቱና ፡ እያየሉ ፡ እስከ ፡ ሐንሪ ፡ ፬ኛውና ፡ እስከ ፡ ልጅ ፡ ልጅ ፡ እስከ ፡ ፲፬ኛው ፡ ሉዊ ፡ ደረሱ ። በ፲፬ኛው ፡ ሉዊ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ከአውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ውስጥ ፡ በኀይልም ፡ በጥበብም ፡ በውቀትም ፡ በጽሑፍም ፡ በለጠ ። በአሜሪካ ፡ የእስፓኝ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ በነበረውም ፡ አገርና ፡ በሌላውም ፡ አውራጃ ፡ እየተተካ ፡ ግዛቱን ፡ አስፋፋ ፤ ቀድሞ ፡ በእንግሊዞች ፡ ይጨነቁ ፡ የነበሩት ፡ ፈረንሳዮች ፡ እንዲያውም ፡ በ፲፬ኛው ፡ ሉዊ ፡ ዘመን ፡ (ሺህ ፡ ፮፻፸፫ ፤ ሺህ ፡ ፮፻፲፯ ፡ ዓ ፡ ም) ፡ የኤስፓኝን ፡ ዘውድ ፡ የሆላንድንና ፡ የአትሪሽን ፡ ግዛት ፡ ለመውሰድ ፡ በእንግሊዝም ፡ ዙፋን ፡ የኛ ፡ ወገን ፡ ያዕቆብ ፡ ፪ኛ ፡ የሚባለው ፡ ይቀመጥ ፡ በማለት ፡ በጦርነት ፡ አስጨነቁ ፡ በማስጨነቃቸውም ፡ በርግጥ ፡ ፈረንሳዮች ፡ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ የቀድሞ ፡ ግሪኮችንና ፡ ሮማውያኖችን ፡ ፍራንኮችንና ፡ ጀርመኖችን ፡ የጓለኞችን ፡ ቱርኮችንና ፡ ፖርቱጋሎቹን ፡ ኤስፓኞችንም ፡ መሰሉ ። ሉዊ ፡ ፀሥራ ፡ አራተኛው ፡ በኃያልነቱ ፡ ምክንያት ፡ «በምድር ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወኪል „ ተባለ ፤ “ ትልቁ ፡ ሉዊ ፡ ─ፀሐዩ ፡ ንጉሥም» ፡ የሚባል ፡ ስያሜ ፡ ወጣለት ፤ የርሱም ፡ የመዠመሪያ ፡ ሚስቱ ፡ የአትሪሽና ፡ የሆንግሪ ፡ ንግሥት ፡ ማሪ ፡ ቴሬዝ ፡ ነበረች ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ በስውር ፡ የገጣሚው ፡ የስካሮ ፡ ባለቤት ፡ የነበረችውን ፡ ማዳም ፡ ሜንቴኖን ፡ አግብቷል ። በርሱ ፡ ዘመን ፡ የግዛት ፡ ማስፋፊያ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በጥበብና ፡ በጽሕፈትም ፡ ፈረንሳዮች ፡ ከዓለም ፡ የመዠመሪያውን ፡ ደረጃ ፡ ያዙ ። እነኮርኔይ ፡ እነራሲን ፡ እነፎንቴን ፡ እነስፓስካል ፤ የነበሩት ፡ በሱ ፡ ዘመን ፡ ነው ። እስከ ፡ ዛሬ ፡ የሚያስደንቀው ፡ የቤርሳይ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ በዚያም ፡ የተደረገው ፡ የጌጣጌጥ ፡ የልብስ ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተድላና የደስታ ፡ ሁኔታ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ አልተደረገም ፡ ይባላል ። ሉዊ ፡ ፲፬ኛ ፡ በተወለደ ፡ ባ፭ ፡ ዓመት ፡ ነግሦ ፡ አነስተኛውን ፡ ጊዜ ፡ በሞግዚት ፡ ይበልጡን ፡ ዘመን ፡ እርሰው ፡ ራሱ ፡ በቀጥታ ፡ ፸፪ ፡ ዓመት ፡ ገዝቶ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ እዱኛ ፡ እንደ ፡ ሰሎሞን ፡ አይቶ ፡ በተወለደ ፡ በ፸፯ ፡ ዓመቱ ፡ ሞተ ።

ወደ ፡ ፊት ፡ ተጽፎ ፡ እንደምናየው ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የሆኑት ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ካይሮ ፡ ባለው ፡ በፈረንሳዊ ፡ ቆንሲል ፡ በደማዬ ፡ አማካይነት ፡ የወዳጅነት ፡ ደብዳቤ ፡ የተላላኩት ፡ ከዚሁ ፡ ከሉዊ ፡ ፲፬ኛ ፡ ጋራ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፶፮ ።

### የንጉሡ ፡ ሕመምና ፡ የዶክተር ፡ ፖንሴ ፡ ሕክምና ፤ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድና ፡ ፲፬ኛው ፡ ሉዊ ።

ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ በ፩፻፹፫ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ነገሡት ፡ እንደ ፡ ዐፄ ፡ ካሌብ ፤ በሺህ ፡ ፩፻፷፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እንደ ፡ ነገሡት ፡ እንደ ፡ ዐፄ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፤ ከሺህ ፡ ፯፻ኛ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ በጐንደር ፡ ከነገሡት ፡ ነገሥታት ፡ ውስጥ ፡ ከገናናዎቹ ፡ ያንዱ ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ስም ፡ በሸዋም ፡ በትግሬም ፡ በጋላም ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ የገነነ ፡ ነበር ። ግዛታቸውም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ከሰሜን ፡ ኤርትራን ፡ አልፈው ፡ ከሰላን ፤ ከምዕራብ ፡ እስከ ፡ ስናር ፡ ድረስ ፡ ይገዙ ፡ ነበር ። የኢትዮጵያም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ስም ፡ የገነነው ፡ በርሳቸው ፡ ጊዜ ፡ ነው ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያን ፡ እስከ ፡ ፳፬ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ገዙ ፡ ሕመም ፡ አደረባቸው ። ከሕመማቸውም ፡ ለመዳን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስሙን ፡ ያነሣነውና ፡ በጠገባቸው ፡ ያለው ፡ ሃጂ ፡ ዐሊ ፡ የሚባለው ፡ ግብጻዊ ፡ በካይሮ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እኔን ፡ አክሞ ፡ ያዳነኝ ፡ የፈረንሳዊ ፡ ሐኪም ፡ አለና ፡ እርሱን ፡ ቢያስመጡና ፡ ቢታከሙ ፡ ይሻላል ፡ ብሎ ፡ መከራቸው ። የርሱንም ፡ ምክር ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ ካይሮ ፡ ያለውን ፡ ደ ፡ ማዬ ፡ (Demaillet) ፡ የሚባለውን ፡ የፈረንሳይን ፡ ቆንሲል ፡ ፖንሴ ፡ የሚባለውን ፡ ሐኪም ፡ እንዲልክላቸው ፡ በሃጂ ፡ ዐሊ ፡ አማካይነት ፡ ደብዳቤ ፡ ላኩበት ፤ ደ ፡ ማዬም ፡ ገና ፡ አስቀድሞ ፡ በቀይ ባሕር ፡ በኩል ፡ የፈረንሳይ ፡ ንግድ ፡ ከሆላንድና ፡ ከቱርክ ፡ ይልቅ ፡ እንዲስፋፋ ፡ ምኞት ፡ ነበረውና ፤ መልክቱ ፡ እንደ ፡ ደረሰው ፡ ይኸንኑ ፡ ሻርል ፡ ጃክ ፡ ፖንሴ ፡(Charles-Ja-cques poncet) ፡ የተባለውን ፡ ሐኪም ፡ ካንድ ፡ ሚሲዮናዊ ጋራ ፡ ላከው ።

እነሱም ፡ ከካይሮ ፡ ተነሥተው ፡ ሲመጡ ፡ ብሬቬዳንት ፡ (Brevedant) ፡ የሚባለው ፡ ይኸው ፡ ሚሲዮናዊ ፡ ጐንደር ፡ ሊደርስ ፡ ጥቂት ፡ ሲቀረው ፡ ታሞ ፡ ሞተ ። ዶክተር ፡ ፖንሴ ፡ ግን ፡ በደኅና ፡ ጐንደር ፡ ደረሰና ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ተገናኝቶ ፡ ያክማቸው ፡ ገመር ። በርሱም ፡ ሕክምና ፡ ንጉሡ ፡ ከሕመማቸው ፡ ተሻላቸው ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ዶክተር ፡ ፖንሴ ፡ ለንጉሡ ፡ ባለሟል ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ ይወጣ ፡ ይገባ ፡ ገመር ። በኋላም ፡ ከሆላንድም ፡ ከኤስፓኝ ፡ መንግሥትና ፡ ከሌሎቹ ፡ ነገሥታትም ፡ ከሚበልጠው ፡ ከፈረንሳይ ፡ ንጉሥ ፡ ከ፲፬ኛ ፡ ሉዊ ፡ ጋራ ፡ ተላልከው ፡ ወዳጅ ፡ ቢሆኑ ፡ መልካም ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ መከራቸው ፡ ንጉሡም ፡ ምክሩን ፡ ሰምተው ፡ የሾቹን ፡ የሙራድን ፡ ዘመድ ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ መስቀል ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ፈረስ ፡ አንድ ፡ የዝኆን ፡ ግልገል ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጌጥ ፡ የተጠለፈ ፡ ልብስ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ባሮች ፡ ጨምረው ፡ ደብዳቤ ፡ አሲዘው ፡ ላ፲፬ኛ ፡ ሉዊ ፡ እንዲሰጥላቸው ፡ ላኩት ። ርሱም ፡ ይኸንኑ ፡ ዕቃ ፡ በያይነቱ ፡ ከደብዳቤ ፡ ጋራ ፡ ተረከበና ፡ ከንጉሡ ፡

ተሰናብቶ ፡ ወደ ፡ ምጥዋ ፡ ሄደ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥትና ፡ የውጭ ፡ መንግሥት ፡ ወዳጅ ፡ እንዲሆኑ ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ አይፈቅድም ፡ ነበርና ፤ መላክተኛው ፡ ምጥዋ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ ያለው ፡ የቱርኮች ፡ ሹም ፡ አግኝቶ ፡ የያዘውን ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ቀምቶ ፡ መለሰው ፤ ዝናኑም ፡ ምጥዋን ፡ ሳያልፍ ፡ ሞተ ። በካይሮ ፡ ያለውም ፡ ካራ ፡ ሚሐሜት ፡ የሚባለው ፡ ፓሻ ፡ ከኮስታንቲኖፕል ፡ በተቀበለው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ከፈረንሳዊ ፡ ንጉሥ ፡ ከ፲፬ኛ ፡ ሉዊና ፡ ከበታቾቹ ፡ ሹማምት ፡ ወይም ፡ ከሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ እንደዚሁም ፡ ከኢትዮጵያው ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ አገር ፡ ሰውም ፡ ገጸ ፡ በረከትም ፡ ደብዳቤም ፡ እንዳይተላለፍ ፡ ጥብቅ ፡ ትእዛዝ ፡ ለምጥዋው ፡ ፓሻ ፡ አስተላለፈ ። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ በምጥዋ ፡ በኩል ፡ መተላለፍ ፡ ችግር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በኑብያና ፡ በስናር ፡ በኩልም ፡ አንዳንድ ፡ ቄራጦች ፡ መልእክተኞችና ፡ ሚሲዮኖች ፡ በድፍረት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመግባት ፡ ቢያስቡ ፡ ሱዳኖች ፡ እየያዙ ፡ ስላጉላሏቸው ፡ በንግድና ፡ በማናቸውም ፡ ሊወዳጁ ፡ የነበሩት ፡ የፈረንሳዊና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ የሉዊ ፡ ፲፬ኛና ፡ የኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ምኞትና ፡ አሳብ ፡ ለጊዜው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ተቋረጠ ።

※ ※ ※

እነዚህ ፡ የኢትዮጵያና ፡ የፈረንሳዊ ፡ ነገሥታት ፡ በዚሁ ፡ ባንድ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ሲገኙ ፡ የሁለቱ ፡ ሥራና ፡ ታላቅነት ፡ እንደዚሁም ፡ ያባቶቻቸውንና ፡ የአያቶቻቸው ፡ ሥራና ፡ ጠባይ ፡ ተጋጥሞ ፡ መገኘቱ ፡ አንባቢን ፡ ትንሽ ፡ ሳያስደንቅ ፡ አይቀርም ።

ሉዊ ፡ ፲፬ኛ ፡ በፈረንሳዊ ፡ አገር ፡ (በፈ.ሕ ፡ ፲፮፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተወልደው ፡ በተወለዱ ፡ በ፭ኛው ፡ ዓመት ፡ ነግሠው ፡ በፈ.ሕ ፡ ፲፯፻፲፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ፸፪ ፡ ዓመት ፡ ገዝተው ፡ ሲሞቱ ፡ በገዙበት ፡ ጊዜ ፡ በሠሩት ፡ የጦርነትና ፡ ያስተዳደር ፡ ምክንያት ፡ በጣም ፡ የገነኑ ፡ በዚሁም ፡ «ፀሐዩ ፡ ንጉሥ» ፡ ከመባላቸው ፡ በቀር ፡ ታላቁ ፡ ሉዊ ፡ እንደ ፡ ተባሉ ፤ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድም ፡ በዘመናቸው ፡ በሠሩት ፡ የጦርነትና ፡ ያስተዳደር ፡ ምክንያት ፡ ሕዝቡ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የሰጣቸው ፡ ስም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ተላልፎ ፡ «ታላቅ ፡ ኢያሱ» ፡ አሰኝቷቸዋል ። ታላቅነታቸውና ፡ ስመ ፡ ጥርነታቸውም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምዕራፍ ፡ ይዟል ። በግዛት ፡ ማስፋፋትና ፡ በጽሑፍ ፡ ማሻሻል ፡ የነበራቸው ፡ አካሄድም ፡ እንደ ፡ መጠኑ ፡ ይመሳሰላል ። በፈረንሳዊ ፡ አገር ፡ በሉዊ ፡ ዐሥራ ፡ አራተኛ ፡ ዘመን ፡ እነፎንቴን ፡ እነፓስካል ፡ . . . . ቢኖሩም ፡ በታላቁ ፡ ኢያሱ ፡ ጊዜም ፡ ቅኔ ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ የሚያጕርፉ ፡ እነ ፡ ክፍለ ፡ ዮሐንስ ፤ እንእዛኝ ፡ ከናፍሮ ፡ ነበሩ ፡ ብንል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የጥበቡም ፡ የሊቅነቱም ፡ መንገድና ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ ግዛታቸው ፡ ስፋት ፡ ቢሆን ፡ አናፍርም ። በፈረንሳዊ ፡ አገር ፡ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ቢጻፉ ፡ ለየብቻ ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱም ፡ ጊዜ ፡ ስንክሳር ፡ ከቀድሞው ፡ ተሻሽሎና ፡ ተብዝቶ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፤ ፊውሰ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ጠቢብ ፡ ጠበ.ባን ፤ መጽሐፈ

ሳዊሮስ ፡ ማኅበረ ፡ ማዕምራን ፡ ዜና ፡ እስክንድር ፡ ይኸን ፡ የመሳሰለው ፡ ግማሹ ፡ በቀደሙ ፡ ነገሥታት ፡ ዘመን ፡ ግማሹ ፡ በዘመናቸው ፡ መጻፉን ፡ ታሪካቸው ፡ ይነግረ ናል ። ይኸም ፡ ሲሆን ፡ በፈረንሳዊ ፡ አገር ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከነፓስካል ፡ ከነራሲን ፡ የተጻፉት ፡ መጻሕፍቶችና ፡ በገራችን ፡ እነዚህ ፡ የተጻፉት ፡ አብዛኞቹ ፡ የመንፈሳዊ ፡ መጻሕፍት ፡ በመጠናቸው ፡ በይነታቸው ፡ በቁም ፡ ነገራቸው ፡ ልዩነት ፡ እንዳላቸው ፡ አንዘነጋም ።

የሉዊ ፡ ፲፬ኛ ፡ አባት ፡ ፲፫ኛ ፡ ሉዊ ፡ «ጻድቁ ፡ ሉዊ» ፡ እንደ ፡ ተባሉ ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አባት ፡ ቀዳማዊ ፡ ዮሐንስ ፡ «ጻድቁ ፡ ዮሐንስ» ፡ መባላቸውን ፡ ባለፈው ፡ ታሪክ ፡ ከነሥራቸው ፡ ገልጸናል ፡ የሉዊ ፡ ፲፬ኛ ፡ አያት ፡ ሐንሪ ፡ አራተኛ ፡ በሃይማኖት ፡ ጦርነት ፡ የተጕዳችውን ፡ አገራቸውን ፡ ፈረንሳዊን ፡ መልሰው ፡ እንዳቋቋሙ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አያት ፡ ዐፄ ፡ ፋሲለደስ ፡ ባባታቸው ፡ በዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ጊዜ ፡ በካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ ጦርነት ፡ ምክንያት ፡ የታወከችውን ፡ አገራቸውን ፡ ኢትዮጵያን ፡ በዘመናቸው ፡ መልሰው ፡ እንዳቋቋሟት ፡ ታሪካቸው ፡ ይነግረናል ። ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ የሚገረመው ፡ ሐንሪ ፡ አራተኛ ፡ ካደን ፡ ሲመለሱ ፡ ንጉሥን ፡ ለማየት እፈልጋለሁ ፡ ብሎ ፡ በመንገድ ፡ የሚጠብቀውን ፡ ለማኝ ፡ ራሳቸው ፡ ንጉሥ ፡ መሆናቸውን ፡ ሳያስረዱ ፡ «እኔ ፡ ንጉሡን ፡ አሳይሃለሁ ፡ ብለው ፡ በፈረስ ፡ አፈናጠው ፡ መሄዳቸውና ፡ በኋላም ፡ መንገዳቸውን ፡ ከለማኙ ፡ ጋራ ፡ ሲቀጥሉ ፡ ንጉሡን ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ መለየት ፡ እችላለሁ ፡ ቢል ፡ „ሁሉ ፡ ባርሜጣውን ፡ እያወለቀ ፡ እጅ ፡ ሲነሣውና ፡ ንጉሡ ፡ ግን ፡ ባርሜጣውን ፡ እንዳደረገ ፡ ታገኘዋለኸ„ ፡ እንዳሉትና ፡ ይኸም ፡ በሐንሪ ፡ ታሪክ ፡ ተጽፎ ፡ እንደሚገኝ ፡ ባለፈው ፡ በምዕራፍ ፡ ፴፪ ፡ እንዳነበብነው ፡ ደግሞ ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አያት ፡ ዐፄ ፡ ፋሲልም ፡ ላደን ፡ በረሐ ፡ ሄደው ፡ መንገድ ፡ ጠፍቶባቸው ፡ ሲመለሱ ፡ ጌሾ ፡ ቈራጩን ፡ ቈለኛ ፡ አግኝተው ፡ በፈረሳቸው ፡ አፈናጠው ፡ ንጉሡን ፡ እኔ ፡ አሳይኻለሁ ፡ ካሉት ፡ ጋራ ፡ በፍጹም ፡ ይጋጠማል ፡ ስለዚህ ፡ በዝርዝርና ፡ በንዳንድ ፡ ነገር ፡ ቢለያይም ፡ በጠቅላላው ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ከሉዊ ፡ ፲፬ኛ ፡ ጋራ ፡ ያባታቸው ፡ የጻድቁ ፡ ዮሐንስ ከሉዊ ፡ ፲፬ኛ ፡ አባት ፡ ከሉዊ ፡ ፲፫ኛ ፡ ጋራ ፡ ያያታቸውም ፡ የዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ሥራና ፡ አስተዳደር ፡ ከሉዊ ፡ ፲፬ኛ ፡ አያት ፡ ከሐንሪ ፡ አራተኛ ፡ ጋራ ፡ መግጠሙና ፡ መመሳሰሉ ፡ በጣም ፡ ያስደንቃል ። ነገር ፡ ግን ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በ፳፬ ፡ ዓመት ፡ ሲወሰን ፡ ያ፲፬ኛ ፡ ሉዊ ፡ የግዛት ፡ ዘመን ፡ እስከ ፡ ፸፪ ፡ ዓመት ፡ ደርሶ ፡ በኛ ፡ ከዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ማልሳዊ ፡ ዳዊት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ፡ የ፯ት ፡ ነገሥታቶቻችንን ፡ ጊዜ ፡ ባንድ ፡ በራሱ ፡ ዘመን ፡ መጠቅለሉ ፡ ልዩነት ፡ አለው ።

## ምዕራፍ ፡ ፶፯ ።

### የዘመኑ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊ ፡–የንጉሦታቱ ፡ ደንበኛ ፡ ተግባር ፤ -የተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መሸፈት ።

ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ባለፉት ፡ ምዕራፎች ፡ ከተጻፉት ፡ በቀር ፡ አገር ፡ ላገር ፡ እየዞሩ ፡ የጐበኙት ፡ አገር ፡ የተሳለሙት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ ለማስገበር ፡ ያደረጉት ፡ ጦርነት ፡ ለማስተዳደሪያ ፡ ያወጡት ፡ ታላላቅም ፡ ጥቃቅንም ፡ ደንብና ፡ ዐዋጅ ፡ ብዙ ፡ ነው ። ይኸንንም ፡ በታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ በዚህ ፡ ቦታ ፡ ዋሉ ፤ ከዚህ ፡ አልፈው ፡ በዚህ ፡ ቦታ ፡ አደሩ ፡ ከእገሌ ፡ ጋራ ፡ ተዋጉ ፤ ከዚህ ተመልሰው ፡ በእገሌና ፡ በእገሌ ፡ መንደር ፡ ተጕዘው ፡ ጐንደር ፡ ገቡ ፡ የሚለውን ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ በዝርዝር ፡ ለመጻፍ ፡ ብንሞክር ፡ አንባቢን ፡ ከማታከት ፡ በቀር ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አናገኝለትም ። ያውም ፡ ቢሆን ፡ በዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ የተደረገው ፡ ዋና ፡ ዋናው ፡ ጕዞና ፡ ጦርነት ፡ ዐዋጁና ፡ ደንቡ ፡ የሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ባለፉት ፡ ምዕራፎች ፡ ተነግረዋል ። ታሪክ ፡ ነገሥታቸውን ፡ እነሐዋርያ ፡ ክርስቶስ ፤ እነአዛዥ ፡ ዘወልድ ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ሲጽፉ ፡ ብዙ ፡ የማጋነን ፤ የማሞገስ ፡ አጻጻፍ እየጨመሩ ፡ ጽፈውላቸዋል ።

የቀድሞ ፡ ጸሐፊዎች ፡ እራሳቸው ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሰዎች ፡ በመሆናቸው ፡ ታሪኩን ፡ ከመንፈሳዊ ፡ ቃልና ፡ ታሪክ ፡ ጋራ ፡ እያቀናጁ ፡ መጻፍ ፡ ልማዳቸው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አእላፍ ፡ ሰገድ ፡ ዮሐንስን ፡ ከወንጌላዊው ፡ ዮሐንስ ፡ ጋራ ፡ እያመሳሰሉ ፡ ለመጻፍ ፡ ሲዠምሩ ፡ «ንዌጥን ፡ ጽሒፈ ፡ ዜናሁ ፡ ዘይጥዕም ፡ እመ ዓር ፡ ወሶከር ፡ ወይትበደር ፡ እምወርቅ ፡ ወእምዕብነ ፡ ጳዝዮን ፡ . . . . . ለክቡር ፡ ወዐቢይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አእላፍ ፡ ሰገድ ፡ ዘተሰምየ ፡ በስመ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ወኀብረ ፡ ስሙ ፡ ምስለ ፡ ስሙ ፡ ወሃይማኖቱ ፡ ምስለ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ወምግባሩ ፡ ምስለ ፡ ምግባሩ ፡ . . . . . »እያሉ ፡ ይጽፉላቸው ፡ ነበር ፡ እንደዚሁም ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ የአድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱን ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊው ፡ ከኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፡ ጋራ ፡ ዠግንነታቸውንም ፡ አመራራቸውንም ፡ እያመሳሰለ ፡ ይተርክላቸዋል ። ሲዠምርም ፡ "ዝክረ ፡ ነገሩ ፡ ሠናይ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ወምክሐ ፡ ወራዙት ፡ ኢያሱ ፡ ዘይቀልል ፡ እምንስር ፡ ወይጸንዕ ፡ እምአንበሳ ፡ ወይትረአይ ፡ በቅድሜሁ ፡ ኵሉ ፡ ጥበብ ፡ ዘጠቢባን ፡ ከመ ፡ ነጥበ ፡ ጠል ፡ ወማሕየብ ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሰሎሞን ፡ ጠቢብ ፡ . . . . . . "እያለ ፡ ታሪካቸውን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ቃልና ፡ በዚያም ፡ ከሚገኙት ፡ ከመሳፍንት ፡ ከሐዋርያት ፤ ከሰማዕታት ፡ ጋራ ፡ እያነጻጸረ ፡ ይጽፍላቸዋል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በርግጥ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በግል ፡ ሕይወታቸው ፡ አንዳንድ ፡ ጕድለት ፡ ማድረጋቸው ፡ ባይቀር ፡ በጠቅላ

ላው ፡ እንዳባቶቻቸው ፡ እንደነዐፄ ፡ ካሌብ ፡ እንደነአልዐሜዳ ፡ እንደነገብረ ፡ መስቀል ፡ እንደነላሊበላ ፣ እንደነበዕደ ፡ ማርያም ፣ እንደነዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ እንደ ነሠርፀ ፡ ድንግል ፡ እንደነፋሲል ፡ የሚቆጠሩ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የተገኙ ፡ ትልቅ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መሆናቸው ፡ አይጠረጠርም ።

ምናልባት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛታቸው ፡ ውስጥ ፡ የሚገ ኘው ፡ የሸዋው ፣ ያማራው ፣ የትግሬው ፣ የላስታው ፣ የፈላሻው ፣ የጋላው ፣ የሻ ንቅላው ፣ ሕዝብ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቢገዛላቸውና ፡ ላዋሉት ፡ ሥራ ፡ ባንድ ፡ ልብና ፡ መንፈስ ፡ እየታዘዘ ፡ ቢውልላቸው ፡ ኖሮ ፡ በዚህም ፣ ላይ ፡ በፈረንሣዊ ፣ በእንግሊዝ ፣ በሆላንድ ፡ በቱርክ ፡ አገር ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ያለው ፡ የመሣሪያና ፡ የእጅ ፡ ጥበብ ፡ ፋብሪካ ፡ በገራቸው ፡ ቢሠራና ፡ ቢለመድ ፡ ኖሮ ፡ እነሉዊ ፡ ፲፬ኛ ፡ እነትልቁ ፡ ፍሬዴሪክ ፡ እነናፖሊዮን ፡ እንዳደረጉት ፣ የኢ ትዮጵያን ፡ ድንበር ፡ አልፈው ፡ ከቱርክ ፡ መንግሥት ፡ እየተዋጉ ፡ ኢትዮጵ ያን ፡ ትልቅ ፡ የቄሳር ፡ መንግሥት ፡ ሳያደርጓት ፡ አይቀርም ፡ ነበር ፡ የርሳቸውም ፡ የኢትዮጵያም ፡ ታሪክ ፡ ከጨለማ ፡ ወጥቶ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ደምቆ ፡ ሳይታይ ፡ አይቀርም ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ዕድል ፡ ላባቶቻቸውም ፡ ለል ጆቻቸውም ፡ እንዳልተከናወነ ፡ ርሳቸው ፡ በዚች ፡ በእስላም ፡ በተከበበችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብቻ ፡ በታላቅ ፡ ድካምና ፡ ጥረት ፡ ከመኖር ፡ በቀር ፡ ከዚያ ፡ የበ ለጠ ፡ ለማስፋፋት ፡ አልተከናወነላቸውም ።

የዚህም ፡ ሁሉ ፡ ዕንቅፋት ፡ «ወሬኛ» ፡ «አፈቻላ» ፡ እየተባለ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ በስድብ ፡ ስም ፡ የሚጠራው ፡ አንዳንድ ፡ ቀንደኛ ፡ ሰው ፡ ግማሹ ፡ አልጋ ፡ ለማግኘት ፣ የቀረው ፡ ነፃ ፡ ለመሆን ፣ ግማሹም ፡ ከብት ፡ ለመዝረፍ ፡ በየጊዜው ፡ የሚያደርገው ፡ ውሳጣዊ ፡ ጦርነት ፡ ነው ። የተ ነሣውም ፡ ቀንደኛ ፡ በተነሣ ፡ ቍጥር ፡ ከጋላ ፣ ከላስታ ፡ ከፈላሻ ፣ ወገን ፡ እን ደዚሁም ፡ በሹመት ፡ በደረጃ ፡ ከተቀየመ ፡ ያማራና ፡ የትግሬ ፡ መኰንን ፡ ውስጥ ፡ ተከታይ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ይገኝለት ፡ ነበር ። እርሱም ፡ በደንበኛው ፡ የንጉሡ ፡ ጦር ፡ ሲሸነፍ ፣ ሲማረክ ፣ ሲታሰር ፣ ሲገረፍ ፣ ሲሰቀል ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ልጁና ፡ የልጅ ፡ ልጁ ፡ ባባቱ ፡ የተደረገበትን ፡ ከታሪክ ፡ በመስማት ቂም ፡ ያድርበትና ፡ ይኸንኑ ፡ ለመቀበል ፡ በሻቱ ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ለጦርነት ፡ እንደገና ፡ ይነሣል ። ቢቀናውም ፡ ባይቀናውም ፡ የተቻለውን ፡ ለመሥራት ፡ የተለመደውን ፡ ጦርነት ፡ ይቀሰቅሳል ። በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አኳ ኋን ፡ እንደ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፡ ያሉ ፡ ኀያላንና ፡ ዐዋቂዎች ፡ የሆኑ ፡ ነገሥታት ፡ በየጊዜው ፡ ቢነሡም ፡ አሳባቸውንና ፡ ዕውቀታቸውን ፣ ኀግንናታቸ ውንና ፡ መሪነታቸውን ፡ ይህ ፡ አላይ ፡ ያልነው ፡ ያገር ፡ ውስጥ ፡ ዘመቻና ፡ አስ ገባሪነት ፡ ወጥሮ ፡ ዕረፍት ፡ ስለሚነሣው ፡ ነገሥታቱ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ውጭ ፡ አሳ ባቸውን ፡ አውጥተው ፡ ከሌላው ፡ ከሠለጠነው ፡ ዓለም ፡ ጋራ ፡ በጦርነትም ፡ በሰ ላምም ፡ ግንኙነት ፡ አድርገው ፡ ለመጠቀምና ፡ ለመጥቀም ፡ ይከለክላቸዋል ።

ስለዚህ ፡ እንደተለመደው ፡ በዚሁ ፡ ባገራቸው ፡ ያለውን ፡ ወሬኛንና ፡ ያመጠውን ፡ ወገን ፡ እየወጉ ፡ በማሳመን ፡ ቀባቶችንና ፡ ተዋሕዶዎችን ፡ በማከራከር ፡ የራሳቸውንና ፡ የሕዝቡንም ፡ ፍላጎት ፡ ለማስደሰት ፡ አዳዲስ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በማሳነጽ ፡ ርስትና ፡ ጕልት ፡ እየወሰኑ ፡ በማከፋፈል ፡ ሲሠሩ ፤ በግል ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜያቸውን ፡ ደግሞ ፡ መንፈሳውያት ፡ መጻሕፍት ፡ በመመልከት ፡ አደን ፡ በማደን ፡ ብቻ ፡ ያሳልፉ ፡ ነበር ።

※ ※ ※

ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድም ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሲሠሩ ፡ ቈይተው ፡ አሁን ፡ ሰውነታቸው ፡ ወደ ፡ መድከም ፡ ሊጠጋ ፡ ነው ምንም ፡ እንኳ ፡ ዕድሜያቸው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፤ ከሃምሳ ፡ ባይበልጥ ፡ እላይ ፡ ያልነው ፡ የጦርነትና ፡ ያስተዳደር ፡ ውዝዋዜ ፡ ከበሽታ ፡ ጋራ ፡ ሰውነታቸውን ፡ ወደ ፡ ማድከም ፡ አደረሰው ። በዚህም ፡ ላይ ፡ የባለቤታቸው ፡ የእቴጌ ፡ ወለተ ፡ ጽዮንና የቁባታቸው ፡ የወይዘሮ ፡ ቅድስቴ ፡ የልጆቻቸው ፡ የነፋሲል ፡ የነወይዘሮ ፡ ኢዮጳራቅስያ ፡ የነወይዘሮ ፡ ማርታ ፡ የብዙ ፡ ዘመዶቻቸውና ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ሞት ፡ በኀዘን ፡ ላይ ፡ ኀዘን ፡ በድካም ፡ ላይ ፡ ድካም ፡ እየጨመረባቸው ፡ ሄደ ።

ቢሆንም ፡ መንግሥትን ፡ ለልጃቸው ፡ እስኪ ፡ ለቁ ፡ ድረስ ፡ በሞቱትና ፡ በተሻሩት ፡ መኳንንቶቻቸው ፡ እግር ፡ አዳዲስ ፡ ሹማምንት ፡ እነደጃዝማች ፡ ሕዝቅያስን ፡ እነደጃዝማች ፡ ኢዮብን ፡ እነብላቴን ፡ ጌታ ፡ ባስልዮስን ፤ እነፀበኛ ፡ አምሳሌን ፤ እነደጃዝማች ፡ ቱሉን ፡ እነብላቴን ፡ ጌታ ፡ አሞንዮስን ፤ እነበጅሮንድ ፡ አብሬን ፡ እነጕጃም ፡ ነጋሽ ፡ አኖሬን ፡ እነፊታውራሪ ፡ ሕንፃ ፡ ክርስቶስን ፡ እነአዛዥ ፡ ዝክሮን ፤ እነጽራግ ፡ ማሰሬ ፡ ኪሮስን ፤ እነዐቃቤ ፡ ሰዓት ፡ አብራንዮስን ፤ እነቄስ ፡ ዐጼ ፡ ሚካኤልን ፡ እነ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ አካለ ፡ ክርስቶስን ፡ እየሾሙና ፡ እሥልጣን ፡ ላይ ፡ እያወጡ ፡ በቀድሞዎቹ ፡ እግር ፡ ከተተኩት ከነዚህ ፡ አዳዲስ ፡ ሹማምንቶች ፡ ጋራ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሥራቸውን ለመቀጠል ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ሞከሩ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሰውነታቸው ፡ ስለ ፡ ቀዘቀዘ ፡ ኀይላቸውም ፡ ስለ ፡ ተዳከመ ፡ ሹማምንቱም ፡ መኳንንቱም ፡ ርሳቸውን ፡ ችላ ፡ እያሉ ፡ ወደ ፡ ትልቁ ፡ ልጃቸው ፡ ወደ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በግልጽም ፡ በስውርም ፡ መጠጋት ፡ ዠመሩ ። ርሳቸውም ፡ ይኸንን ፡ በልባቸው ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡ በሺሕ ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ የመግሥቱን ፡ እንደራሴነት ፡ ለልጃቸው ፡ ለኒሁ ፡ ለተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የራስነት ፡ ማዕርግ ፡ ጨምረው ፡ ሰጥተው ይበልጥ ፡ ጊዜያቸውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመሳለምና ፡ ጸሎት ፡ በማዘውተር ፡ ያሳልፉ ፡ ዠመር ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ከባለቤታቸው ፡ ከእቴጌ ፡ መለኰታዊት ፡ የተወለዱት ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትና ፡ ከቁባቶቻቸው ፡ ከወይዘሮ ፡ ቅድስቴና ፡ ከወይዘሮ ፡ ማርያማዊት ፡ የተወለዱት ፡ ልጆች ፡ ዳዊትና ፡ በካፋ ፡ ዙፋኑን ፡ እኔ ፡ እወርሳለሁ ፡ በማለት ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይጣሉ ፡ ዠመር ። መኳንንቱም ፡ የንጉሡን

መሸምገልና ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖትንም ፡ ሙሉ ፡ ሰውነት ፡ ከሕግ ፡ ሚስታቸው ፡ የተወለዱ ፡ መሆናቸውንም ፡ በመመልከት ፡ የንጉሥነት ፡ ጊዜያቸውም ፡ እንደ ፡ ተቃረበ ፡ በመረዳት ፡ ከወይዘሮ ፡ ቅድስቲ ፡ ልጆች ፡ ይልቅ ፡ ለተክለ ፡ ሃይማ ኖት ፡ አድልተው ፡ ነበር ፤ ይልቁንም ፡ ገሚሶቹ ፡ ገና ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ሳይሞቱ፥ አሁኑን ፡ ንገሥና ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ በእጅኽ ፡ ያዝ ፡ እያሉ ፡ ስላደፋፈሯቸው ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በባታቸው ፡ ላይ ፡ ሸፈቱ ። ንጉሡም ፡ ይኽ ንኑ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ርግጠኛውን ፡ ለማወቅ ፡ እኔ ፡ አለሁበት ፡ ድረስ ፡ መጥ ተህ ፡ እንገናኝ ፡ ብለው ፡ ላኩባቸው ። ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ የትግሬውን ፡ ገዥ ፡ ራስ ፡ ፋሬስን ፡ የሰሜኑን ፡ ገዥ ፡ ደጃዝማች፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስንና ፤ ሌሎቹንም ፡ የጐጃምን ፡ ሹማምቶች ፡ ሰብስበው ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ መልክት ፡ ከባቴ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገ ሥቱ ፡ መጣብኝ ፡ ምን ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ አማከሯቸው ። እነሱም ፡ አንተን ፡ ወህኒ ፡ አምባ ፡ አሥረው ፡ ትንሹ ፡ ልጃቸውን ፡ ዳዊትን ፡ ለማንገሥ ፡ አስበው ፡ ይሆ ናልና ፡ በትሄድ ፡ ይሻላል ፡ እዚሁ ፡ ዝም ፡ ብለኽ ፡ ቅርና ፡ እኛ ፡ እናንግሥኽ ፡ ብለው ፡ መከሯቸው ። እርሳቸውም ፡ ይህን ፡ ምክር ፡ ተቀብለው ፡ ቀሩና ፡ በነ ዚህ ፡ ሰዎች ፡ ፈቃድ ፡ መንገሣቸው ፡ በዋጅ ፡ ተነገረ ። ይኽንንም ፡ ዐዋጅ ፡ ለተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከናገሩ ፡ በኋላ ፡ እነዚሁ ፡ መኳንንቶች ፡ እርስዎ ፡ እንደ ፡ አፄ ፡ ካሌብ ፡ መንግሥትን ፡ ንቀው ፡ መንነዋል ፡ ማለትን ፡ ስለ ፡ ሰማን ፡ የበኵር ፡ ልጅዎን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ አንግሠናል ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ መልክተኛ ፡ ላኩ ። ንጉሡም ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ሕይወቴ ፡ ሳለ፡ መንግሥቴን ፡ ሰልሰጠው ፡ በእንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ለመቀማት ፡ ካሰበ ፡ እዋጋለሁ፡ ብለው ፡ ጦር ፡ ሰብስበው ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከነጭፍራቸው ፡ ወዳሉበት ፡ ጉዞ፡ ገሠገሩ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ በመንገድ ፡ ድንግል ፡ በር ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ሲደርሱ፡ ስለ ፡ ታመሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምናልባት ፡ የመንግሥቴን ፡ ፍጻሜ ፡ አቅርቦ ፡ ልጄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲነግሥ ፡ ፈቅዶ ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ ለጦርነት ፡ የተከተላቸውን ፡ ሠራዊት ፡ አሰናብተው ፡ ባጠገባቸው ፡ ያሉትን ፡ የወይዘሮ ፡ ቅድ ስቴን ፡ ልጆች ፡ ለተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ላኩና ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ውጊያውንም ፡ መን ግሥታቸውንም ፡ ትተው ፡ ጣና ፡ አጠገብ ፡ ደቀ ፡ ማርያም ፡ ወደምትባለው ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ ሄደው ፡ እንደ ፡ መናኒ ፡ ተቀመጡ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የጐጃም ፡ መኳንንትና ፡ ሊቃውንት ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በሸፈቱበት ፡ ጊዜ ፡ ረድተዋቸው ፡ ነበርና ፤ ለዚሁ ፡ ርዳታቸው ፡ ውለታ ፡ ክርስ ቶስ ፡ በተዋሕዶ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ በቅብዐት ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ሆነ ፡ የሚል ፡ ዐዋጅ ፡ አስነግርልን ፡ ብለው ፡ ለመኗቸውና ፡ አስነገሩ ላቸው ፡ ይባላል ። በሌላ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ በጉባኤ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ተዋሕዶች ፡ ጋራ ፡ ተከራክራችሁ ፡ ሳታሸንፉ ፡ ዐዋጅ ፡ አል ነግርም ፡ ስላሏቸው ፡ በዚሁ ፡ ተቀይመው ፡ ሸፈቱ ፡ በኋላም ፡ ተዋግተው ፡ ድል፡ ሆኑ ይባላል ፡ የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በና

ታቸው ፡ በወይዘሮ ፡ መለኮታዊት ፡ በራስ ፡ ፋሬስና ፡ በደጃች ፡ ፍሥሐ ፡ ክር ልቶስ ፡ በኀቶቻቸው ፡ በጳውሎስና በዳርመን ፡ እየተረዱ ፡ ጐንደር ፡ ገብተው ፡ ስማቸውን ፡ ልዑል ፡ ሰገድ ፡ አሰኝተው ፡ በገሃድ ፡ ነገሡ ። በቅባት ፡ ሃይማ ኖት ፡ አልገባም ፡ እያለ ፡ ለዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ የሚያደላውንም ፡ እነራስ ፡ ፋሬስ፡ እየተፈላለጉ ፡ ሲይዙና ፡ ሲያስሩ ሰነበቱ ።

ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ በመንኑበት ፡ ቦታ ፡ ሆነው ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ፡ አዘኑ ፤ ቢሆንም ፡ ልጁ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ክፎዎች ፡ ገፋፍተውና ፡ መክረው ፡ ካላስካዱት ፡ ፀቀር ፡ እኔ ፡ ሳልሰጠው ፡ አልጋዬን ፡ በፈቃዱ ፡ ቀምቶ ፡ በግድ ፡ ለመንገሥ ፡ አያስብም ፡ ሲሉ ፡ ተጠራጠሩ ። ባጠገባቸውም ፡ አንለይም ፡ ብለው የተገኙ ፡ ደጃች ፡ ዮሐንስ ፡ ያማሩ ፡ (ማይንት) ፡ ገዥ ፡ እነፊታውራሪ ፡ ያዕቆብ እንደጃች ፡ አኖሬ ፤ እንደጃች ፡ ዮስጦስ ፤ እነአዛዥ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ነበሩ ፤ ነገር፡ ግን ፡ ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ በየጊዜው ፡ ወደነዚያ ፡ የዞሩ ፡ አሉ ። ስለዚህ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ደጃች ፡ ዮስጦስን ፡ ጠርተው ፡ ሂድና ፡ ልጄን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትንና ራስ ፡ ፋሬስን ፡ በኔ ፡ ቃል ፡ ይጠራችኋል ፡ ብለኸ ፡ አምጣልኝ ፡ ብለው ፡ ፪ኛ አዘዙት ። ዮስጦስም ፡ ሄዶ ፡ በነገራቸው ፡ ጊዜ ፡ በንግግሩ ፡ አፈዙበት ፡ እን ዲያውም ፡ እጁን ፡ ይዘው ፡ አሠሩት ። ዐፄ ፡ ኢያሱም ፡ አሁንም ፡ ትዕግሥታቸ ውን ፡ ሳይጨርሱ ፡ ሦስተኛ ፡ (1) ፡ በዛኸ ፡ ገላውዴዎስ ፡ እጅ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን፡ ቃል ፡ ለተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ላኩ ፡ ልጄ ፡ እንደ ፡ ሆንኸ ፡ ቤቴን ፡ ልቀቅ ፤ ከል ጋዬም ፡ ሙረድና ፡ ከነበርክበት ፡ ቤት ፡ ቈይ ፤ የሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ምክር ፡ ከመ ጕዳት ፡ በቀር ፡ አይጠቅምኸም ፤ ከኔ ፡ ፈቃድና ፡ ከኔ ፡ ሃይማኖት ፡ ካልወጣኸ ፡ አልጋው ፡ ካንተ ፡ አያልፍም ፣ ከኔ ፡ ፈቃድና ፡ ከኔ ፡ ሃይማኖት ፡ የወጣኸ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ እንኳን ፡ የመሬቱን ፡ ርስት ፡ ሰማያዊ ፡ ርስትም ፡ አታገኝም ።

ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ያባታቸውን ፡ ምክር ፡ ከመስማት ፡ ልባ ቸውን ፡ አጸኑ ፤ ባጠገባቸውም ፡ ካሉት ፡ መኳንንቶች ፡ ተመካከሩና ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ መልስ ፡ በድፍረት ፡ ላባታቸው ፡ ላኩ ።

‹ቤትዎንም ፡ አለቅ ፤ ከዙፋንዎ ፡ አልወርድ ፡ የመነነ ፡ ሰው ፡ አልጋ ፡ ምኑ ፡ ነው ? የመነነ ፡ ከዱር ፤ የሞተ ፡ ከመቃብር ፡ ይመለሳልን ? ዛሬ ፡ በርስዎ ፡ የተገዠ መረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ለምን ፡ መነንሁ ፡ ብለው ፡ ተጸጽተው ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ከመነኑበት ፡ ደሴት ፡ ይውጡና ፡ እንዋጋ ፡ ፈረስዎ ፡ ፈረሴ ፡ ሠራዊትዎ ፡ ሠራዊቴ ፤ ነው ፤ አማኞችዎ ፡ ደጃች ፡ አኖሪና ፡ ፊታውራሪ ፡ ያዕቆብ ፡ ሊያድኑዎ ፡ አይች ሉም› ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ዙሪያ ፡ ያሉት ፡ መኳንንትና ፡ ቀሳውስት ፡ ተክለ ሃይማኖትን ፡ ከዚህ ፡ ከደሴት ፡ ወጥተን ፡ እንዋጋ ፡ እያሉ ፡ ሲጐተጕቷቸው ፡ እር

(1) መልእክቱ ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ በመሆኑ ፡ ፈንታ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ ይኸውም የመዠመሪያው ፡ ፩ዱ ፡ ቀርቶ ፡ እንዚህ ፡ የመጨረሻዎቹ ፡ ፪ቱ ፡ ብቻ ።

ሳቸው ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ እንዲሆን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ ይሆናልና ፡ ተዉኝ ፡ ሲሉ ፡ እንቢ ፡ ብለው ፡ ምናኒያቸውን ፡ አጸኑ ። ባጠገባቸው ፡ ያሉትን ፡ እነዚህኑ ፡ መኳንንትና ፡ ቀሳውስትም ፡ እየመረቁ ፡ በምስጋና ፡ ወደያገራቸው ፡ አሰና በቷቸው ። ልጃቸውን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ብለው ፡ አረገሟ ቸው ። «ባባትኽ ፡ ክፉ ፡ እንደ ፡ መከርኽ ፡ ክፉ ፡ መከር ፡ ያውርድልህ ፡ ሹመትኽም ለባዕድ ፡ ይለፍ ፡ ሰውም ፡ አይገዛልኽ ፡ ዋተኽ ፡ ባክነህ ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ሙት» ።

ይኽን ፡ ሁሉ ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ የምናኔ ፡ የተ ባትዎ ፡ ሥራቸውን ፡ በዚሁ ፡ በደሴተ ፡ ደቅ ፡ ይቀጥሉ ፡ ዠመር ። ነገር ፡ ግን ፡ ተክለ ሃይማኖትና ፡ መኳንንቶቻቸው ፡ የርሳቸውን ፡ ከልብ ፡ ዙፋናቸውን ፡ ትተው ፡ መመ ነናቸውን ፡ አላመኑም ፡ ነበርና ፤ ኢያሱ ፡ ከደሴቱ ፡ ወጥተው ፡ እንዳይወጓቸው ፡ በደ ሴቱ ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ ታንኳ ፡ በእሳት ፡ አቃጥለው ፡ ደሴቱንም ፡ በዘበኛ ፡ ያስጠ ብቁት ፡ ዠመር ። ይኽም ፡ ሳይበቃ ፡ ቀርቶ ፡ በ፬ኛው ፡ ወር ፡ በሐምሌ ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ሺሕ ፡ ፮፻፺፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ደጃች ፡ ፍሥሐ ፡ ክርስቶስን ፤ ጳውሎስንና ፡ ዳርመ፡ንን ፡ አባ ፡ ሰይፈ ፡ ሚካኤልንና ፡ አባ ፡ ዘወልደ ፡ ማርያምን ፡ ፻፶ ፡ ጦር ፡ ጨምራችሁ ፡ ወደ ፡ ደሴተ ፡ ደቅ ፡ ሂዳችሁ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱን ፡ ከደቅ ፡ አውጥታችሁ ፡ ወደ ፡ ጨቅላ ፡ መንዘ ፡ ውሰዷቸው ፡ አልሄድም ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ግደሏቸው ፡ ብለው ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አዘዙ ፡ ይባላል ። እነዚህም ፡ እንደ ፡ ታዘዙ ፡ ወደ ፡ ደሴቱ ፡ ሄደው ፡ ባገኟዋቸው ፡ ጊዜ ፡ ይነሡና ፡ ወደ ፡ ጨቅላ ፡ መንዘ ፡ እንውሰድዎት ፡ አሏ ቸው ፤ እርሳቸውም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ እነዚሁ ፡ ባቀረቡላቸው ፡ ታንኳ ፡ መጓዝ ፡ ዠመሩ ። በጕዞ ፡ ላይም ፡ ጊዜው ፡ ቀትርም ፡ ሆኖ ። የፀሐይ ፡ ሙቀት ፡ ባቃጠላ ቸው ፡ ጊዜ ፡ ጥላ ፡ ቢለምኑ ፡ ከለከሏቸው ፡ ከዚያም ፡ በብዙ ፡ መጕላላት ፡ ወደ ፡ ተባለው ፡ ሥፍራ ፡ ወስደው ፡ አስቀመጧቸው ። ይኽን ፡ ሁሉ ፡ ግፍ ፡ ደጃች ፡ አኖ ሬና ፡ ፊታውራሪ ፡ ያዕቆብ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ተማምለው ፡ የጐጃምን ፡ ጦር ፡ አስከ ትተው ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱን ፡ ለመርዳት ፡ ጕዞ ፡ ዠምረው ፡ ነበር ፤ ይኽንንም ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ "እኔ ፡ ከባቴ ፡ ምሕረት ፡ ለምኜ ፡ ለመታረቅ ፡ አስቤ አለሁና ፤ በከንቱ ፡ ደም ፡ አታፍሱ ፡ የሚል ፡ የማታለያ ፡ ቃል ፡ ይዞኽ ፡ ሒደኽ አዘንግተኽ ፡ ደጃዝማች ፡ አኖሬንና ፡ ፊታውራሪ ፡ ያዕቆብን ፡ ያዝልኝ" ፡ ብለው ፡ ራስ ፡ ፋሬስን ፡ ላኩ ። ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱን ፡ በቶሎ ፡ ግደሉ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ጨከኞቹ ፡ ወደ ፡ ዳርመንና ፡ ወደ ፡ ጳውሎስ ፡ ወደ ፡ እልበተ ፡ ተስፋ ፡ ላኩ ፡ ይባላል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ እንደሚለው ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ በማግሥቱ ፡ ሊሞቱ ፡ ሌሊቱን ፡ ሕልም ፡ አይተው ፡ ነበርና ፡ እልበተ ፡ ተስፋ ፡ የሚ ባለው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ገብቶ ፡ በኃይለ ፡ ቃል ፡ ሊያነጋግራቸው ፡ ሲዠምር ፡ ኢያሱ ፡ አብረዋቸው ፡ የነበሩትን ፡ ካህናትና ፡ መነኰሳት ፡ ፍቱኝ ፡ ብለው ፡ ተናዘዙ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ካህናቱና ፡ መነኰሳቱ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይላቀሱ ፡ ዠመር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ «ኢሐመኑ ፡ ሥጋከ ፡ አመ ፡ ኰርዐከ ፡ አይሁድ ፤ ወአመ ፡ ቀሰፉከ ፡ ውስተ ፡ ዐውደ ፡ ምኵናን ፡ እስከ ፡ ይትረአያ ፡ አዕፅምቲከ ፤ ኢየኀዘነኑ ፡ ልብከ ፡ አመ ፡ ረገዙከ ፡ በኵናት ፤ ወቀነዉከ ፡ በቅንዋት ፡ ኀምስ ፡ . . . . . . . ተዘከረኒ እግዚኦ ፡ በውስተ ፡ መንግሥትከ ፡ በከመ ፡ ተዘከርኮ ፡ ለፈያታዊ ፡ ዘየማን ፡ . . . ፡

. . .» እያሉ ፡ ጸልየው ፡ ሲጨርሱ ፡ ሊገድሉ ፡ ከመጡት ፡ አንዱ ፡ የደረበ ፡ ወገን ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ገባ ። ኢያሱም ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ኋላፊውን ፡ መንግሥቴን በማያልፈው ፡ ለውጫለሁ ፡ በኔ ፡ ሞት ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚጠቀመው ፡ ምን ድነው ? ባጥንቴ ፡ ቤት ፡ አይሠራበት ፤ በደሜ ፡ ማር ፡ አይበቅልበት ፤ ሥጋዬም ፡ ለትል ነው ፡ የግፍ ፡ ብዛት ፡ ምን ፡ ይረባዋል ፡ አሉት ። ደረባም ፡ የንጉሡን ፡ ንግግር ፡ ሰምቶ ፡ በልቡ ፡ አዘነ ፡ ከዚያም ፡ መግደሉን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጣና ፡ እኔ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱን ፡ ገድዬ ፡ በእሥራኤል ፡ ልጆችና ፡ (1) በሜጫ ፡ ልጆች ፡ ዘለዓለ ማዊ ፡ ቂም ፡ አልተክልም ፡ ሲል ፡ ለወገኖቹ ፡ ተናገረ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከርሱ ፡ ልበ ቸው ፡ ደም ፡ ለማፍሰስ ፡ የጸናውና ፡ እርሳቸውን ፡ ገድለው ፡ በዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይ ማኖት ፡ መንግሥት ፡ ዘመናይ ፡ እንሆናለን ፡ ብለው ፡ የቸኰሉት ፡ ጳውሎስና ፡ ዳር መን ፡ መዜሬት ፡ የሚባሉት የርሱን ፡ ንግግር ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ በቍጣ ፡ ተነሥተው የደረቤን ፡ ጭፍራ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ገቡ ፤ በገቡም ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ መግደል ፡ አነሣቸውና ፡ አይሁድ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ላይ የእሥራኤል ፡ ንጉሥ ፤ ሰላም ፡ ይሁንልኽ እያሉ ፡ እንዳፌዙበት ፡ እነርሱም ፡ ዐፄ ኢያሱን ፡ ሊገድሉ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ «እንደ ፡ ገና ፡ ልናነግሥዎ ፡ ነው ፡ የመጣነው» ፡ ብለው ፡ አፌዙባቸው ፡ እርሳቸውም ፡ "ርግጥ ፡ በሰማይ ፡ ልታነግሡኝ ፡ እንደ ፡ መጣችሁ ፡ ዐውቃለሁ" ፡ ሲሉ ፡ መለሱላቸው ።

በዚህ ፡ መካከል ፡ አሁንም ፡ በገዳዮቹ ፡ መካከል ፡ ጥቂት ፡ ክርክር ፡ ተደረገ ፡ ግማ ሾቹ ፡ ደረቤዎች ፡ (ሜጫዎች) ፡ የሚባሉት ፡ አንገድልም ፡ ብለው ፡ እንቢ ፡ አሉ ። ግማሾቹ ፡ ማፌዝ ፡ ሳይሆን ፡ በቅብዐት ፡ ሃይማኖት ፡ ይግቡልንና ፡ በእርግጥ ፡ እንደ ገና ፡ እናነግሣቸው ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትንና ፡ መኳንንቱንም ፡ አስረን ፡ እንስጣቸው ፡ አሉ እርሳቸውንም ፡ ይኸንኑ ፡ ጠየቋቸው ? ፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ ከተዋሕዶ ፡ ሃይማኖቴ ፡ አልለወጥም ። ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሞቶ ፡ ቀባሪ ፡ ያጣል ፡ ሲሉ ፡ ትንቢት ፡ ተናግረው ፡ ሞቱን ፡ ለመቀበል ፡ ተዘጋጁ ፡ ይባላል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ይኸ ሁሉ ፡ ክርክር ፡ ለምንድነው ፡ ሲሉ ፡ ከቆሙት ፡ ጨካኞች ፡ ውስጥ ፡ አንዱን ፡ እስ ላም ፡ በጠመንዡ ፡ እንዲገድላቸው ፡ እነጳውሎስ ፡ አዘዙት ። እርሱም ፡ እንደታዘዘ ፡ አጠገባቸው ፡ ሆኖ ፡ በጥይት ፡ ቢመታቸው ፡ የጥይቱ ፡ ኀይል ፡ ከልጋ ፡ ላይ ፡ ገለበጣ ቸው ። ቀጥሎ ፡ የጳውሎስ ፡ ወንድም ፡ ዳርመን ፡ ይኸ ፡ ከሐዲ ፡ በቶሎ ፡ አይሞትም ብሎ ፡ በሁለት ፡ ጦር ፡ ወግቶ ፡ ጨረሳቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፤ ቤታቸውን ፡ አቃጥለው ፡ ዕቃቸውን ፡ ተከፋፍለው ፡ ገዳዮቹ ፡ ሲመለሱ ፡ ሚካኤል ፡ የተባለ ፡ ፩ ፡ ጎበዝ ፡ ሬሳቸውን ፡ ከእሳቱ ፡ ውስጥ ፡ ጎትቶ ፡ አወጣው ፤ ከዚያ ፡ የትግሬው ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የእናሪያው ፡ አባ ፡ አስበ ፡ አብ ፡ እየሮጡ ፡ መጥተው ፡ ገላቸውን ፡ አጥበው ፡ በወላንሳና ፡ በሰርፍ ፡ (መጎናጸፊያ) ፡ ከፈኑቸው ፤ (ገነዟቸው) ። የሞቱበት ንም ፡ ጦር ፡ አረር ፡ (ጥይት) ፡ ግፉን ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ እንዲመለከተው ፡ ብለው አብረው ፡ ከፈኑት ።

(1) የእሥራኤል ፡ ልጅ ፡ የሚለው ፡ ከእሥራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከሰሎሞን ፡ መወለዳቸውን ፡ በሜጫ ፡ ልጆች ፡ ማለቱም ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ የሜጫ ፡ ተወላጅ ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነዚሁ ፡ ገዳዮች ፡ ጳውሎስና ፡ ዳርመን ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ መገደላቸውን ፡ ለእህታቸው ፡ ለወይዘሮ ፡ መለኮታዊት ፡ ልከው ፡ ሴትዮዋም ፡ ለልጃቸው ፡ ለተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ላኩ ። ዳግመኛም ፡ ከነዚሁ ፡ ወገኖች ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱን፡ ሬሳ ፡ እባሕር ፡ ይጣል ፡ ያለ ፤ ግማሹም ፡ ተሰቅሎ ፡ አሞራ ፡ ይብላው ፡ ያለ ፡ አለ፤ ግማሾቹ ፡ ግን ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ግፍ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡ ብለው ፡ በመጨረሻ ፡ እንዲቀበሩ ፡ ስለ ፡ ተፈቀደ ፡ ቀሳውስቱና ፡ ካህናቱ ፡ የሚወዷቸው ፡ አንዳንድ ፡ መኳንንት ፡ ሆነው ፡ ሬሳቸውን ፡ በታላቅ ፡ ኀዘንና ፡ ፍታት ፡ ወስደው ፡ በምጽርሐ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቀበሯቸው ። የታላቁ ፡ የገናናው ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ሕይወት ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ መፈጸሙን ፡ ታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ ይነግረናል ፤ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ በሕዝብና ፡ በካህናት ፡ ዘንድ ፡ «ርጉም ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት» ፡ እንደ ፡ ተባሉ ፡ ጨምሮ ፡ ይገልጽልናል።

የንጉሡ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ መሞት ፡ በያገሩ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ኀዘንን ፡ ጸጸትን ቂምን ፡ በቀልን ፡ በያለበት ፡ ቀሰቀሰ ። ወንድሞቻቸው ፡ እነ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ለጊዜው ፡ ለመበቀል ፡ ባይችሉ ፡ የሚችሉበትን ፡ ጊዜ ፡ አጥብቀው ፡ ይጠባበቁ ፡ ዠመር ፤ ወዲያውም ፡ ለመዠመር ፡ አንዳንዶቹ ፡ መኳንንት ፡ ሸፈቱ ። ለመበቀል ፡ ዐቅም ፡ የሌላቸው ፡ ግን ፡ በለቅሶና ፡ በኀዘን ፡ እያማረሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አመለከቱ ። ይልቁንም ፡ በጐንደር ፡ ሕዝብና ፡ በተለይም ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴ ፡ ካህናት ፡ ዘንድ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ካህናቱም ፡ ሕዝቡም ፡ ለፍታትና ፡ ለለቅሶ ፡ ከያለበት ፡ ተሰበሰቡ ። የደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴ ፡ ካህናትና ፡ ቀሳውስት ፡ ንጉሡ ፡ በሕይወታቸው ፡ ሳሉ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ የሰጡትን ፡ አልባሳትና ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ አውጥተው ፡ ለሕዝቡ ፡ እያሳዩ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ፍታት ፡ እየፈቱ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሲያለቅሱ ፡ ሕዝቡ ፡ ወታደሩም ፡ ንጉሡን ፡ ይወዳቸው ፡ ነበርና ፡ ይኸንኑ ፡ እያየ ፡ ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ዕንባ ፡ በዕንባ ፡ እየተራጨ ፡ አለቀሰላቸው ። በዚህም ፡ ቀን ፡ የተገጠመላቸው ፡ የለቅሶ ፡ ግጥም ብዛቱ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ነው ፡ ይባላል ። እኔ ፡ ግን ፡ አንዱን ፡ እንኳን ፡ ለማግኘት ፡ አላጋጠመኝም ፡ ምናልባት ፡ እኔ ፡ ያላየሁት ፡ መጽሐፍ ፡ ወይም ፡ ያልተገናኘሁት ፡ ሽማግሌ ፡ ይተርከው ፡ ይሆናል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ኀዘኑ ፡ በጐንደር ፡ ከተማ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ ተደርጎ ፡ ሰነበተ ፤ እንደዚሁ ፡ ወደ ፡ ትግሬም ፡ ወደ ፡ ጐጃምም ወደ ፡ ሸዋም ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መርዶው ፡ ተላከና ፡ ኀዘንና ፡ ፍታት ፡ በየደብሩና ፡ በየገዳሙ ፡ ተደረገ ። የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ በየታሪኩ ፡ የሚገኘው ፡ ከሺሕ ፡ ፲፯፻፳፫ ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፲፯፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ ፳፬ ፡ ዓመት፡ መሆኑ ፡ ነው ።

በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድና ፡ በልጃቸው ፡ በተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ የደረሰው ፡ ታሪክ ፡ በዳዊትና ፡ በአቤሴሎም ፡ መካከል ፡ ከደረሰው ፤ እንደዚሁም ፡ በየመንግሥታቱ ፡ ንጉሣዊ ፡ ቤተሰብ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከሚደርሰው፡ ልዩነት ፡ የለውም ። አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ሲገዛ ፡ ኖሮ ፡ ወደ ፡ እርጅና ፡ ሲጠጋ ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ ከብዙ ፡ ሴቶች ፡ ብዙ ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ሲወልድ ፡ ከነርሱ ፡ መካ

ከል ፡ አንዱ ፡ ሲጐለምስ ፡ ጐልምሶም ፡ ያባቱን ፡ ዙፋን ፡ ለመውረስ ፡ ዘውዱን ፡ ለመጫን ፡ ሲቸኵል ፡ አባትዮውም ፡ እኔው ፡ ግዛቴን ፡ ልቀጥል ፡ ሲል ፡ ወይም ፡ ዘውዴን ፡ ለማንኛው ፡ ልጄ ፡ ልስጠው ፡ እያለ ፡ የማወላወልና ፡ የማማረጥ ፡ ነገር ፡ ባሳብም ፡ በሥራም ፡ ሲገለጥበት ፡ በልጆቹ ፡ መካከል ፡ ይልቁንም ፡ በደረሰው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ የመንፈስ ፡ ሁከት ፡ መፈጠሩ ፡ የማይቀር ፡ ነው ። እንደ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ያለውም ፡ ወገኑን ፡ ይዞ ፡ በገሃድ ፡ ለውጊያ ፡ ይነሣል ። በዚህ ፡ መካከልም ፡ እንደ ፡ ራስ ፡ ፋሬስ ፡ እንደ ፡ አፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ እንደራሴ ፡ እንደ ፡ አኪጦፌል ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ባለሟል ፡ ያሉት ፡ ካረጀው ፡ አባት ፡ ወደ ፡ ወጣቱ ፡ ልጅ ፡ መዞር ፡ ብልኅት ፡ የሚመስልና ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ነው ። የነጋሢ ፡ ልጆችም ፡ እንደ ፡ አቤሴሎም ፡ በዙፋን ፡ እኛ ፡ ብንቀመጥ ፡ ኖሮ ፡ ለሕዝብ ፡ ምንኛ ፡ በጠቀምን ፤ እንዴትስ ፡ በፈረድን ፡ እያሉ ፡ ሕዝብን ፡ መስበክና ፡ ማባበል ፡ የተለመደ ፡ ነው ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ በሕይወታቸው ፡ ገና ፡ ለልጃቸው ፡ ለተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የራስነት ፡ ማዕርግ ፡ ጨምረው ፡ እንደራሴ ፡ አድርገው ፡ የዙፋኑን ፡ ጐዳና ፡ ጠርገውላቸው ፡ ነበር ። ዕለት ፡ በለት ፡ ዘውድንና ፡ ዙፋንን ፡ ለመንጠቅ ፡ እንደምን ፡ ትዕግሥት ፡ አጠራቸው ? ፡ ምናልባት ፡ ዙፋንን ፡ አባቴ ፡ ለቴዎፍሎስና ፡ ለዳዊት ፡ ይሰጡብኝ ፡ ይሆናልና ፡ በቶሎ ፡ ብይዝ ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ ይሆናል ። ይኸም ፡ ቢሆን ፡ እመነኑበት ፡ ደሴትና ፡ በኋላም ፡ እየተዘዋወሩበት ፡ ሥፍራ ፡ ድረስ ፡ ጨካኞቹን ፡ ወታደሮች ፡ እየላኩ ፡ ባባታቸው ፡ ነፍስና ፡ ሕይወት ፡ መጫወታቸው ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ። ታሪክ ፡ ነገሥቱም ፡ በዚሁ ፡ «ርጉም ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት» የሚል ፡ ስያሜ ፡ ሰጥቶ ፡ ወደ ፡ ጊዜያችን ፡ እንዲተላለፍ ፡ ማድረጉ ፡ አልተሳሳተም ።

የማይጣላ ፡ የማይዋጋ ፡ የለም ። ሳኦልና ፡ ዳዊት ፤ ዳዊትና ፡ አቤሴሎም ፡ በዚሁ በዙፋን ፡ ተጣልተው ፤ ተዋግተዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሳኦልም ፡ አቤሴሎምም ፡ በደንበኛ ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ መሞታቸውን ፡ ዳዊት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ የሳኦልን ፡ ገዳይ ፡ አስገደለ ፡ እንጂ ፡ አልተደሰተም ። ስለ ፡ ልጁም ፡ ስለ ፡ አቤሴሎም ፡ ሞት ፡ "ልጄ ፡ ሆይ ፡ አቤሴሎም ፡ ምነው ፡ ያንተን ፡ ሞት ፡ ለኔ ፡ ባደረገው» ፡ እያለ ፡ መራራ ፡ ልቅሶ ፡ አለቀሰበት ። በዚህ ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ የልብ ፡ ጭካኔ ፡ የዳዊትን ፡ የልብ ፡ ርኅራኄ ፡ እንመለከታለን ።

## የንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

## ምዕራፍ ፡ ፵፫ ።

## ስለ ፡ ጐጃም ፡ ቅባቶች ፡ መታሰር ።

በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሞት ፡ አባታቸውን ፡ ካስገደሉ ፡ በኋላ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ "ልዑል ፡ ሰገድ„ ፡ ተብለው ፡ መንገሣቸው ፡ በገሃድ ፡ ታወቀ ። ነገር ፡ ግን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ባባታቸው ፡ ላይ ፡ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ ሕዝቡ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ከልብ አልተቀበለምና ፡ በየቤቱ ፡ በየጉባኤው ፡ ያማቸው ፡ ገሥመር ። ቀሳውስቱም ፡ "ለዚህ ፡ ለርጉም ፡ ንጉሥ ፡ አባቱን ፡ አስገዳይ ፡ የተገዛ ፡ ርጉም ፡ ይሁን" ፡ እያሉ ፡ ውስጡን ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ለሽፍትነት ፡ ይቀሰቅሱ ፡ ገሥመር ።

ርሳቸው ፡ ግን ፡ መንግሥትን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ለናታቸው ፡ ለእቴጌ ፡ መለከታዊት ፡ የእቴጌነት ፡ (የንግሥትነት ፡ ሥያሜ? ) ለራስ ፡ ፋሬስ ፡ የእንደራሴነት ፡ ሹመት፡ ለዳርመን ፡ ጐጃምን ፡ ለጳውሎስ ፡ በጌምድርን ፡ ለአምኃየስ ፡ በኸሮንድነትን ፤ ሰጥተው፡ ሹም ፡ ሽር ፡ አድርገው ፡ በነዚህ ፡ በወዳጆቻቸው፡ ደጋፊነት ፡ ኢትዮጵያን፡ ለመግዛት ፡ ሞከሩ ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ጊዜያቸውን ፡ ጦርነት ፡ ሁከት ፡ የሃይማኖት ፡ ክርክር ፡ ረኃብ፡ ስለ ፡ ከበባው ፡ በፍጹም ፡ እንዳበቶቻቸው ፡ ለመግዛት ፡ ጥቂትም ፡ ዕረፍትና ፡ ደስታ ፡ አላጋጠማቸውም ።

ባንዳንድ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ላይ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ራሳቸው ፡ ቅብዐት ሆነው ፡ የቅብዐት ፡ ካህናቶችንም ፡ በመደገፍ ፡ ርሳቸውና ፡ ባለሟላቸው ፡ ደጃች ፡ ዳርመን ፡ ተዋሕዶዎችን ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ እንደ ፡ ፊጁ ፡ እንዳሳደዱ ፡ ይገልጽልናል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በሌላው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥትና ፡ በነኵልበ ፡ በነጐይዲ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ልዩነት ፡ አለው ፤ ይኸውም ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ነው ።

መንግሥትን ፡ ለመያዝ ፡ ከረዷቸው ፡ ውስጥ ፡ አብዛኞቹ ፡ የጐጃም ፡ ቅባቶች ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ የረዱበት ፡ ምክንያት ፡ ንጉሡ ፡ መንግሥት ፡ ይዘው ፡ ቅብዐት ፡ ሲሆኑ ፡ እኛም ፡ ባለሟሎች ፡ ሆነን ፡ ባለጋሮቻችንን ፡ ተዋሕዶዎችን ፡ እናጠቃለን ፡ በማለት ፡ ነበር ። በዚሁ ፡ እምነትና ፡ ተስፋ ፡ አሁን ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መጡና ፡ «እንግዴህ ፡ ክርስቶስ ፡ በቅብዐተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው» ፡ የሚል ፡ ዐዋጅ ፡ ይነገርልን ፡ አሏቸው ፤ ንጉሡ ፡ ግን ፡ ጉባኤ ፡ ሰጥቼ ፡ ሳላከራክር ፡ በደረጋችሁልኝ ፡ ርዳታ ፡ ምክንያት ፡ በተዋሕዶ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ እስካሁን ፡ የቈየውን፡ ለማፍረስ ፡ አልችልም ፡ ብለው ፡ በግልጽ ፡ መለሱላቸው ። በዚህ ፡ መልስ ፡ ቅባትን ፡ የሚደግፉት ፡ መኳንንትና ፡ ካህናት ፡ መበሳጨት ፡ ጀመሩ ፤ ባለፊውም ፡ ርዳታቸው ፡ ይጸጸቱ ፡ ጀመር ። ቢሆንም ፡ ክርክሩን ፡ ለመቀጠል ፡ ጉባኤው ፡ ይዘርጋልን ፡ ብለው ፡ ስለአመለከቱ ፡ ንጉሡ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጳጳሱ ፡ አቡነ፡ ማርቆስ ፡ ባሉበት ፡ ክርክሩ ፡ ተጀመረ ። በክርክሩም ፡ ጊዜ ፡ ጳጳሱና ፡ ንጉሡ፡ ለተዋሕዶዎች ፡ እያደሉ ፡ ቅባቶችን ፡ ይጫኗቸው ፡ ነበር ። በመጨረሻም ፡ ተዋሕዶዎች ፡ ረቺ ፡ ቅባቶች ፡ ተረቺ ፡ ሆነው ፡ በሰላም ፡ ሊለያዩ ፡ ነበር ፤ ነገር፡ ግን ፡ በመካከሉ ፡ ጳጳሱ ፡ እነዚህን ፡ በተቀብዖ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ሆነ ፡ የሚሉትን ፡ ገዝቻለሁ ፡ ስላሉ ፡ ንጉሡም ፡ እነዚህኑ ፡ ለማሰር ፡ ምክንያት ፡ ይፈልጉ ኖሮ ፡ ወዲያው ፡ በርሳቸው ፡ ትእዛዝ ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ቅባቶች ፡ እነአበ ፡ ወልደ ትንሣኤ ፡ እየተያዙ ፡ ታሰሩ ፤ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ የጐጃም ፡ ቅባቶች ፡ ቂም ፡ እየበረከተ ፡ ሄደ ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፺፱ ።

## ጐጃሞች ፡ ዐምደ ፡ ጽዮንን ፡ እንግሠው ፡ የቀሰቀሱት ፡ ጦርነት ፤ የንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አሟሟት ።

የሃይማኖቱ ፡ ክርክር ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሲፈጸም ፡ ሌላው ፡ የርስ ፡ በርስ ፡
ጦርነት ፡ ደግሞ ፡ ከመቀጠል ፡ አላረፈም ። ድሆ ፡ የሚባለው ፡ የበጌምድር ፡ ተወ
ላጅ ፡ ብዙ ፡ጭፍራ ፡ እያስከተለ ፡ የጐንደርን ፡ ዙሪያ ፡ አገር ፡ ሲያውክና ፡ ሲዘ
ርፍ ፡ አራት ፡ ወር ፡ አለፈ ። በመጨረሻ ፡ ግን ፡ የንጉሡ ፡ ወገኖች ፡ አሸን
ፈው ፡ ራሱን ፡ ቈርጠው ፤ ለንጉሡ ፡ አሳዩዋቸው ፤ ቢሆንም ፡ በዚህ ፡ ያለው ፡ ሽፍ
ሲፈጸም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ በደጃች ፡ ዳርመን ፡ ግዛት ፡ በጐጃም ፡ ያለው ፡ ሽፍ
ትነት ፡ እየበረታ ፡ ሄደ ። የጐጃም ፡ መኳንንትና ፡ ባላባቶች ፡ ምክር ፡ አድርገው ፡
ዐምደ ፡ ጽዮን ፡ የተባለውን ፡ ወጣት ፡ የነጋሢነት ፡ ዘር ፡ ስለነበረው ፡ ርሱን ፡ አንግ
ሠው ፡ ለጦርነት ፡ ተሰለፉ ።

ከነሱም ፡ ጋራ ፡ በንጉሣቸው ፡ አሟሟት ፡ ያዘኑ ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አሮያም
ሰገድ ፡ የጥንት ፡ አሽከሮች ፡ የጐጃም ፡ ካህናትና ፡ ሊቃውንት ፡ አገሩን ፡ እያሳ
ደሙ ፡ አብረው ፡ ከጦሩ ፡ ጋራ ፡ ይጓዙ ፡ ነበር ። የሕዝቡም ፡ ብዛት ፡ በጐን
ደር ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሥጋት ፡ ሆነ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ንጉሡ ፡ የጦር ፡ አለቆ
ቻቸውን ፡ እነራስ ፡ ፋሪስን ፡ እነዳርመንን ፡ ጠርተው ፡ ጐጃሞችን ፡ እንዲወጉ ፡
አዘዟቸው ፤ እነርሱም ፡ ጐጃሞች ፡ ያነገሡትን ፡ ዐምደ ፡ ጽዮንን ፡ በመፈለግ ፡
ብዙ ፡ ሰው ፡ እየገደሉ ፡ ያገኙትንም ፡ ቤት ፡ እያቃጠሉ ፡ ብዙ ፡ አገር ፡ አጠፉ ።
በኋላም ፡ ይባበ ፡ ከሚባለው ፡ አገር ፡ በሺህ ፡ ፯፻፺፱ ፡ ዓ፡ ም፡ ላይ ፡ ተገናኙና፡
ትልቅ ፡ ጦርነት ፡ ተደረገ ። በዚህም ፡ ጦርነት ፡ ከሁለቱ ፡ ወገን ፡ ከታላላቆም ፡
ከታናናሹም ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ አለቀ ፤ የጐጃም ፡ ቀሳውስቶች ፡ ገሚሶቹ ፡ በጦርነት
ሞቱ ፤ በምርኮም ፡ የተያዙት ፡ ተገደሉ ። ድሉም ፡ የነዳርመን ፡ ሆነ ። ንጉሡም
ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይኸንኑ ፡ ያገኙትን ፡ ድል ፡ በከበሩበት ፡ ቀን ፡ አስቀድመው ፡
ታስረው ፡ በዕጃቸው ፡ የነበሩትን ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ታማኝ ፡ አሽከሮች ፡ የነበ
ሩትን ፡ ደጃዝማች ፡ አኖሬንና ፡ ያዕቆብን ፡ ከመሀኒ ፡ ቤት ፡ አስወጥተው ፡ በጥ
ይት ፡ አስደበደቧቸውና ፡ ጦርነቱ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ተፈጸመ ።

፨ ፨ ፨

ጐጃሞች ፡ በጦርነት ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ቢሸነፉ ፡ ቂማቸውን ፡ በልባቸው ፡
ይዘው ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ገብተው ፡ ተቀምጠው ፡ ንጉሡን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡
የሚገድሉበትን ፡ ምክንያት ፡ አጥብቀው ፡ ይፈልጉ ፡ ዠመር ፤ ንጉሡንም ፡ ከዙ
ፋን ፡ ለማውረድ ፡ ወይም ፡ ለመግደል ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በሚደረግ ፡ ዘመቻ ፡
ፈትነው ፡ ሳይሳካላቸው ፡ በቀረ ፡ ጊዜ ፡ በአገው ፡ ምድር ፡ ካሉ ፡ ከገበርማ ፡ ባላ

ባቶች ፡ ጋራ ፡ በስውር ፡ ተስማምተው ፡ ንጉሡን ፡ በብልኀት ፡ ለመግደል ፡ ዐድማ ፡ አደረጉ ።

ስለዚህ ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ በዳሞት ፡ የሸፈተባቸውን ፡ ደጃች ፡ ወልደ ፡ አቢብን ፡ ለመውጋት ፡ በመጡበት ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ አደን ፡ ወዳድ ፡ መሆናቸውን ፡ ያውቁ ፡ ነበርና ፡ «ባገራችን ፡ በአገው ፡ ምድር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አውሬ ፡ ስላለ ፡ መጥተው ፡ ቢያድኑ ፡ መልካም ፡ ነበር» ፡ ብለው ፡ በቀጥታ ፡ ሳይሆን ፡ በጐን ፡ በበለሟል ፡ በኩል ፡ አሳሰቧቸው ። ንጉሡም ፡ በውስጥ ፡ የተዘጋጀባቸውን ፡ አሽክላ ፡ ሳያውቁ ፡ በቅንነት ፡ ጥቂቶች ፡ አሽከሮቻቸውን ፡ ብቻ ፡ አስከትለው ፡ ለአደን ፡ ሄዱ ። እነዚያም ፡ ንጉሡ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ለመግደል ፡ የሚችሉትን ፡ ጠንካራ ፡ ሰዎች ፡ እነባላምባራስ ፡ ዮሐንስን ፡ አስቀምጠው ፡ ነበር ። በአዘና ፡ ምድር ፡ (አገው ፡ ምድር) ፡ ንጉሡ ፡ በመዠመሪያ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ጐሽ ፡ ገደሉ ። ቀጥሎም ፡ አንበሳና ፡ ዝኆን ፡ ለመግደል ፡ በጫካ ፡ ውስጥ ፡ በበቅሏቸው ፡ ተቀምጠው ፡ ሲተላለፉ ፡ ርሳቸውን ፡ ለመግደል ፡ የተመደቡት ፡ ሰዎች ፡ አውሬ ፡ የሚፈልጉ ፡ እየመሰሉ ፡ በቍጥቋጦ ፡ ውስጥ ፡ ሲያደቡ ፡ በኋላም ፡ አውሬ ፡ የሮጠ ፡ አስመስለው ፡ በፈረስ ፡ አውሬውን ፡ እንደሚያበሩ ፡ መስለው ፡ ባጠገባቸው ፡ ሲያልፉ ፡ አንደኛው ፡ ወራፍ ፡ (ገበርማ ፡ ከሣ? ፡) የሚባለው ፡ ጐበዝ ፡ በጠመንዣ ፡ መቷና ፡ ጣላቸው ፤ ሲወድቁም ፡ አንደኛው ፡ በጦር ፡ ስለወጋቸው ፡ የሞቱ ፡ መስላቸውና ፡ ጥለዋቸው ፡ ሸሹ ። የንጉሡ ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬም ፡ ለጌታው ፡ ሲከላከል ፡ አብሮ ፡ ተወጋ ፤ በኋላም ፡ ትተዋቸው ፡ ሸሽተው ፡ የነበሩት ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ተመልሰው ፡ አንሥተው ፡ በቃሬዛ ፡ አድርገው ፡ በቅራቢያው ፡ ወደሚገኘው ፡ አዘነ ፡ ሚከኤል ፡ ወደሚባል ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ወስደው ፡ አስተኝዋቸው ፡ ጥቂት ፡ እንደቈዩ ፡ ነፍስና ፡ ሥጋቸው ፡ ተለያየ ።

ምንም ፡ ቢሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ ቈይቶም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በቶሎ ፡ ለሰው ፡ የጁን ፡ ሥራ ፡ መስጠቱ ፡ አይቀርም ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ንጉሡ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አባታቸውን ፡ በጐታቸው ፡ እጅ ፡ በግፍ ፡ አስገድለው ፡ ነበርና ፡ ምናልባት ፡ ይህን ፡ የመሰለው ፡ ያልታሰበ ፡ አደጋ ፡ በእርሳቸው ፡ መድረሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያባታቸውን ፡ ደም ፡ ለመበቀል ፡ ያደረገው ፡ ይሆናል ። እኛም ፡ ግፍ ፡ ያልሠራ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይኸን የመሰለ ፡ አደጋ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይደርስበታልና ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ይሆናል ፡ እንላለን ። ነገር ፡ ግን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ በቀል ፡ ሲገኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ አደረገው ፡ ተብሎ ፡ ቢገመት ፡ ከስንፍና ፡ አይቈጠርም ።

የተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ፩ኛም ፡ ግዛት ፡ ከሺሕ ፡ ፰፻፺፫ ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፰፻ ፡ ዓ. ም. ድረስ ፡ ነው ። የእርሳቸውንም ፡ መሞት ፡ ራስ ፡ ፋሪስ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ናዖድ ፡ የሚባለውን ፡ የዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ያ፬ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ አነገሠ ። ነገር ፡ ግን ፡ ያ፬ ፡ ዓመት ፡ ሕፃን ፡ መንግሥት ፡ ሊይዝ ፡ አይችልም ፡ ብለው ፡ እነበዥሮንድ ፡ ዮስጦስ ፡ የዐፄ ፡ እያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድን ፡ ወንድም ፡ ቴዎፍሎስን ፡ ከወህኒ ፡ አምባ ፡ አውርደው ፡ አነገሡቸው ።

## የዐፄ ቴዎፍሎስ ዘመነ መንግሥት ።

### ም ዕ ራ ፍ ፡ ፳ ።

### ስለ ፡ ነገሥታት ፡ ልጆች ፡ እስራት ፡ ሹም ፡ ሽር ፤ — የእቴጌ ፡ መለኮታዊትና ፡ የነዳርማን ፡ መገደል ።

ዐፄ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ (ጻድቁ) ልጅ ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ወንድም ፡ መሆናቸውን ፡ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከብዙም ፡ ልጆች ፡ የበኵሩ ፡ ወይም ፡ አባቱ ፡ በኑዛዜው ፡ አውርሶት ፡ መንግሥት ፡ የያዘ ፡ እንደሆነ ፡ የቀሩት ፡ ተይዘው ፡ ወህኒ ፡ አምባ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ በዘበኛ ፡ እየተጠበቁ ፡ መቀመጣቸውን ፡ ባለፈው ፡ ጽፈናል ። ስለዚህ ፡ የዚያ ፡ ጊዜ ፡ የነገሥታት ፡ ልጆች ፡ የዛሬ ፡ ጊዜ ፡ ነገሥታት ፡ እንደሚያደርጉት ፡ የአውራጃ ፡ አገር ፡ በክፍል ፡ እየተሰጣቸው ፡ የእገሌ ፡ አገር ፡ መስፍን ፡ እየተባሉ ፡ በሹመት ፡ ተቀምጠው ፡ ደስታቸውን ፡ ከነጋሢው ፡ ወንድማቸው ፡ ጋራ ፡ ሊካፈሉ ፡ አይችሉም ። ምክንያቱም ፡ አንዱ ፡ ከወንድማማቾቹ ፡ ውስጥ ፡ ወንድማቸው ፡ የነገሠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እነሱ ፡ ደግሞ ፡ በራሳቸውም ፡ አሳብ ፡ ወይም ፡ ባንዳንድ ፡ መኳንንትና ፡ ነገድ ፡ እየተገፉ ፡ ዙፋን ፡ ለመያዝ ፡ በማሰብ ፡ የረጋውን ፡ መንግሥት ፡ ስለሚያሸብሩ ፡ ነው ። ከእገሌ ፡ ንጉሥ ፡ እንወለዳለን ፡ እያሉ ፡ በየጊዜው ፡ በተነሡ ፡ ዙፋን ፡ ተካራካሪዎች ፡ ምክንያት ፡ ጦርነት ፡ እየተቀሰቀሰ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ይበልጥ ? ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፈሰሰው ፡ ደም ፡ ብዙ ፡ ነው ።

እንደዚሁም ፡ ዐፄ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ በወንድማቸው ፡ በዐፄ ኢያሱና ፡ በወንድማቸው ፡ ልጅ ፡ በዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በወህኒ ፡ አምባ እስረኛ ፡ ሆነው ፡ (1) ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ባደሙባቸው ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ አገው ፡ ምድር ፡ ጫካ ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ አልጋቸውን ፡ የሚይዝ ፡ የደረሰ ፡ ልጅ ፡ ባለመኖሩ ፡ በጅሮንድ ፡ ዮስጦስ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎፍሎስን ፡ ከወህኒ ፡ አምባ ፡ አውርደው ፤ በሺሕ ፡ ፯፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሐምሌ ፡ ወር ፡ አነገሡዋቸው ፤ ስመ ፡ መንግሥታቸውም ፡ «አዕራር ፡ ሰገድ» ፡ ተባለ ።

እርሳቸውም ፡ መንግሥት ፡ ከያዙ ፡ በኋላ ፡ የማይስማሟቸውንና ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ለመግደል ፡ ዐድማ ፡ በማድረግ ፡ የተጠረጠሩትን ፡ ራስ ፡ ፋሪስን ፤ ሣጹን ፡ ዮሐንስን ፤ ቲጄን ፤ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኪዳኔን ፤ ራቅ ፡ ወዳለ ፡ አገር ፡ እየላኩ ፡ ገሚሶቹን ፡ በእስራት ፡ የቀሩትን ፡ በግዞት ፡ አስቀምጧቸው ። ወዳጆቻቸውንና ፡ እዙፋን ፡ ለመውጣት ፡ የረዷቸውን ፡ ግን ፡ አገር ፡ ግዛት ፡ እየሰጡ ፡ ባለሟል ፡ አድረጓቸው ። ከነዚሁም ፡ ውስጥ ፡ በጅሮንድ ፡ ዮስጦስን ፡ ራስ ፡ ብለው ፡ የስሜንና ፡ የትግሬን ፡ ግዛት ፤ ለደጃች ፡ ወልደ ፡ አቢብ ፡ የጐጃምን ፤ ለደጃዝማች ፡ ሕዝቅያስ ፡ የበጌ ፡ ምድርን ፡ ግዛት ፡ ሾሟቸው ።

(1) በወህኒ ፡ አምባ ፡ ሲቀመጡ ፡ ከዚያ ፡ ብቻ ፡ እንዳይወርዱ ፡ መጠበቅ ፡ እንጂ ፤ በሰንሰለት ፡ በግር ፡ ብረት ፡ መታሰር የለባቸውም ።

በዚህ ፡ ዐይነት ፡ አገሩ ፡ ሰላም ፡ ሆኖ ፡ ነበር ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ የነዚያው ፡ የቅባቶችና ፡ የተዋሕዶዎች ፡ (የካራዎች) ፡ ክርክር ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ በነ ገሠ ፡ ቍጥር ፡ እየተነሣ ፡ አስቸግሮ ፡ ነበር ። እነዚህንም ፡ ሁለት ፡ ወገኖች ፡ ማስታ ረቅ ፡ በፍጹም ፡ አልተቻለም ፤ ነጋሢውም ፡ ቅባቶችን ፡ ሲከተል ፡ ተዋሕዶዎች ፡ እየ ተቀየሙ ፤ ተዋሕዶዎችን ፡ ሲከተል ፤ ቅባቶች ፡ እየተቀየሙ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ትልቅ ፡ ችግር ፡ ሆኖበት ፡ ይኖር ፡ ነበር ። አሁንም ፡ ጉባኤ ፡ ይዘርጋልንና ፡ እንከራከር ፡ ሲሉ ፡ የተለመደ ፡ ጥያቄያቸውን ፡ አቀረቡ ።

ንጉሡ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ከሃይማኖት ፡ ክርክር ፡ በፊት ፡ የሚጠብቃቸው ፡ ሌላ ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ ነበርና ፤ ይኸንን ፡ አቈይተው ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድን ፡ ገዳዮች ፡ ዳርመንንና ፡ ጳውሎስን ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ የተባበሩትን ፡ በለቤታቸው ፡ የነበሩ ትን ፡ እቴጌ ፡ መለከታዊትን ፡ ከያሉበት ፡ አሲዘው ፡ እቴጌ ፡ መለከታዊትንና ፡ ጳውሎ ስን ፡ ባደባባይ ፡ አሰቀሏቸው ። ደጃች ፡ ዳርመንም ፡ ጐጃም ፡ ከደጃች ፡ ወልደ ፡ አቢብ ፡ ጋራ ፡ በኋላም ፡ ዳሞት ፡ መጥቶ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ተዋግቶ ፡ ከተሸነፈ ፡ በኋላ ፡ ደብረ ፡ መዊዕ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገብቶ ፡ ደወለ ። ዐፄ ፡ ቴዎፍሎስም ፡ «የከሐዲ ፡ መደበቂያ ፡ (መሸመጊ) ፡ ከምትሆኚ ፡ እመቤቴ ፡ አትቀየሚኝ ፡ የጭቃ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እኔ ፡ በኋላ ፡ በማንብና ፡ በኖራ ፡ አሠርቼ ፡ እደብር ሻለሁ» ፡ ብለው ፡ ተስለው ፡ በዕድሞው ፡ ላይ ፡ ሲተኩሱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሲቃ ጠል ፡ የዳርመን ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ተቃጥለው ፡ አለቁ ። ዳርመን ፡ ግን ፡ እብዙ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ቈሰለ ፡ ተያዘና ፡ ተፈርዶበት ፡ እርሱ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱን ፡ ለመግደል ፡ በጨከነበት ፡ በጦር ፡ ተገደለ ። በጦር ፡ መገደሉንም ፡ ርሱ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱን ፡ በጦር ፡ በትር ፡ የገደላቸውን ፡ ለመበቀል ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። የቀሩትንም ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱን ፡ በመግደል ፡ የተባበሩትን ፡ ሁሉ ፡ እያስያዙ ፡ ገሚሶቹን ፡ በሰይፍ ፡ ገሚሶቹን ፡ በጥይት ፡ እያስደበደቡ ፡ አስገደሏቸው ። ገበርማ ፡ ካሣ ፡ የተባለውም ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ በአገው ፡ ገድሎ ፡ የነበረው ፡ ሳይቀር ፡ እንደዚሁ ፡ ተገ ደለና ፡ ንጉሡ ፡ የወንድማቸውንና ፡ የወንድማቸውን ፡ ልጅ ፡ ደም ፡ በሚገባ ፡ ተበቀሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

## ስለ ፡ ቅባቶች ፤ –ስለ ፡ ጋሎች ፡ መሸነፍ ፤–ስለ ፡ ንጉሡ ፡ ዕረፍት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጉባኤ ፡ ይደረግና ፡ እንከራከር ፡ ብለው ፡ ቅባቶች ፡ እንደዚህ ፡ ቀደሙ ፡ አመለከቱ ።

ንጉሡ ፡ ግን ፡ ቅባቶችን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፤ ወይም ፡ ራሳቸው ፡ በዚሁ ፡ በቅባት ፡ ስላመኑ ፡ «ክርስቶስ ፡ በቅብዐተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የባሕርይ ፡ አም ላክ ፡ ሆነ» ፡ ብለው ፡ በጉባኤ ፡ ሳያከራክሩ ፡ ዐዋጅ ፡ አናገሩ ፡ ስለዚህ ፡ ቅባቶች ፡ ድል ፡ አረግን ፡ ብለው ፡ ደስ ፡ አላቸው ። ቤተ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚባሉት ፡

የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ቀሳውስቶች ፡ ግን ፡ በጣም ፡ አዘኑ ። ወዲያውም ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ቀርበው ፡ «ጉባኤ ፡ ተደርጎ ፡ መጽሐፍ ፡ ተዘርግቶ ፡ በክርክር ፡ ሳንረታ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ክርስቶስ ፡ በተቀብዖ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡ ዐዋጅ ፡ ያስነግራሉ» ፡ ብለው ፡ ጠየቋቸው ። እርሳቸውም ፡ ጐጃሞች ፡ ወዳጆቼ ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ እውነተኛውን ፡ መለሱላቸው ፡ ይባላል ። እነርሱም ፡ በንጉሡ ፡ መልስ ፡ ተስፋ ፡ በቈረጡ ፡ ጊዜ ፡ በያገሩ ፡ እየሰበኩ ፡ ብዙ ፡ አገር ፡ በሽፍትነት ፡ አሥነሡባቸው ። ይልቁንም ፡ ዋናው ፡ እንደራሴ ፡ ራስ ፡ ዮስጦስ ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ቀሳውስት ፡ ጋራ ፡ ተባብረው ፡ ኖሮ ፡ በዚሁ ፡ ተወንጅለው ፡ በግዞት ፡ ታሰሩ ። ደጃች ሕዝቅያስም ፡ ተሽሮ ፡ የሸዋ ፡ ገዥ ፡ (ምስለኔ) ፡ የነበረው ፡ ራስ ፡ ድሜጥሮስ ፡ በጌምድር ፡ ተሾመ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ግዞተኞች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተመልሰው ፡ ባለሟል ፡ ሆኑ ።

ቈጥሎ ፡ በግዞት ፡ ሄደው ፡ በሐማሴን ፡ ታስረው ፡ የነበሩት ፡ ሣጺነ ፡ ዮሐንስና ፡ ዘመዱ ፡ ማሞ ፡ ከእስራት ፡ ቤት ፡ አምልጠው ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ሸፍተው ፡ ለብቻው ፡ ናብሐና ፡ ዮሐንስ ፡ የተባለውን ፡ አንግሠናል ፡ ብለው ፡ በንጉሡ ላይ ፡ ሸፈቱ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ነጋሢው ፡ ብቻ ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ሲያመልጥ ፡ ሁለቱም ፡ ተይዘው ፡ ተሰቀሉ ።

ቱጂ ፡ የተባለው ፡ ግዞተኞች ፡ ከነበሩት ፡ አንደኛው ፡ ከግዞቱ ፡ ቦታ ፡ ንጉሡ ፡ ምሕረት ፡ አድርገውለት ፡ መጥቶ ፡ በጐንደር ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ በያለበት ፡ ሽፍታ ፡ መነሣቱን ፡ ተመልክቶ ፡ እሱም ፡ ከጐንደር ፡ ሊበን ፡ ጐንዳ ፡ የሚባሉቱን ፡ ጋሎች ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ይባባ ፡ መጥቶ ፡ ብዙ ፡ አገር ፡ አጠፋ ። ከዚያም ፡ ከአትሮንሰ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገብቶ ፡ ካህናቶቹን ፡ ገድሎ ፡ አልባሳቱን ፡ ዘረፈ፤ ብራንካሊዎን ፡ በሚባለው ፡ እጅ ፡ ተሥሎ ፡ የነበረውንም ፡ የእመቤታችንን ፡ ሥዕል ፡ አስጠፋው ።

ንጉሡ ፡ ግን ፡ መዠመሪያ ፡ ጋላ ፡ ባዘ ፡ ወደሚባሉት ፡ ሄደው ፡ ነበርና ፡ ቱጂ ፡ ብዙ ጋሎች ፡ ይዞ ፡ መጥቶ ፡ ይባባን ፡ አጠፋ ፡ ማለትን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ተመልሰው ፡ መጥተው ፡ ውጊያ ፡ ተዠመረ ። ቱጂም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተዋግቶ ፡ የመሸነፉን ፡ ቊርጥ ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ወታደሮቹን ፡ ትቶ ፡ ሸሽት ፡ ዠመረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሲሸሽ ፡ ባላገሮች ፡ እርሱ ፡ መሆኑን ፡ ዐውቀው ፡ አባረው ፡ ከሁለት ፡ ልጆቹ ፡ ጋራ ፡ ያዙት ። ከያዙትም ፡ በኋላ ፡ የሦስቱንም ፡ ራስ ፡ ቈርጠው ፡ ወደ ፡ ይባባ ፡ ለንጉሡ ፡ ላኩላቸውና ፡ ደስታ ፡ ሆነ ። የቀሩትንም ፡ ጭፍሮቹን ፡ ወታደርና ፡ ባላገር ፡ እየተከታተለ ፡ ፈጃቸው ።

ንጉሡም ፡ የሸፈቱባቸውን ፡ ጋሎች ፡ በእንዴዚህ ፡ ያለ ፡ የጭካኔ ፡ ቅጣት ፡ አጥፍተው ፡ ጐንደር ፡ ተመልሰው ፡ ገብተው ፡ እንደ ፡ ቈዩ ፡ ታመሙ ፡ ሕመማቸውም ፡ የወባ ፡ ትኩሳት ፡ ነው ፡ ይባላል ። ታመው ፡ ሳለ ፡ ባለቤታቸውና ፡ እንደራሴያቸው ፡ ራስ ፡ ዮስጦስ ፡ ያስታምሟቸው ፡ ነበር ። በሽታቸው ፡ ግን ፡ እየጠና ፡ ሄዶ ፡ በሺህ ፡ ፲፻፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥቅምት ፡ ወር ዐረፉ ።

# የንጉሥ ፡ ዮስጦስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

### የንጉሥ ፡ ዮስጦስ ፡ ዘር ፤–በንጉሥ ፡ ዮስጦስ ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ዐድማ።

የቀሩት ፡ ነገሥታት ፡ ከደንበኛና ፡ ከቃል ፡ ኪዳን ፡ ባለቤታቸው ፡ በቀር፡ ዘርና ፡ ወራሽ ፡ እንዳናጣ ፡ እያሉ ፡ በየሥፍራው ፡ ብዙ ፡ ቁባቶች ፡ ያስቀምጡ ፡ ነበር ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ አንደኛዪቱ ፡ መካን ፡ ብትሆን ፡ ሌላዪቱ ፡ ወላድ ፡ መሆኗ ፡ አይቀርምና ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ ይኖሯቸው ፡ ነበር ። ለምሳሌ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፡ ከባለቤታቸው ፡ ከእቴጌ ፡ ወለተ ፡ ጽዮን ፡ ባይወልዱ ፡ ከቁባቶቻቸው ፡ ከወይዘሮ ፡ መለኮታዊትና ፡ ከወይዘሮ ፡ ቅድስቴ ፡ ከወይዘሮ ፡ ማርያማዊት ፡ በመውለዳቸው ፡ ብዙ ፡ ወራሽ ፡ ለማግኘት ፡ ቻሉ ። ዐፄ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ግን ፡ ካንድ ፡ ሚስት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ቁባት ፡ ስላልነበራቸውና ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ባለቤታቸውም፡ መካን ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ሌላም ፡ እንዳይጨምሩ ፡ የክርስቲያንነት ፡ ሕግ ፡ መተላለፍ ፡ ስለ ፡ ሆነባቸው ፡ መንግሥታቸውን ፡ የሚይዝ ፡ ልጅ ፡ ፈጽሞ ፡ አልነበራቸውም ።

ስለዚህ ፡ እንደራሴያቸው ፡ ራስ ፡ ዮስጦስ ፡ መንግሥትን ፡ ለመያዝ ፡ ምንም ፡ የሚያስቸግራቸው ፡ ነገር ፡ ለጊዜው ፡ አለመኖሩን ፡ ስለ ፡ ተረዱ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ሲሞቱ ፡ ስመ ፡ መንግሥታቸውን ፡ «ፀሐይ ፡ ሰገድ» ፡ አሰኝተው ፡ ነገሡ ። እርሳቸውንም ፡ የነጋሢነት ፡ ዘር ፡ የላቸውም ፡ እያሉ ፡ አንዳንድ ፡ መጻሕፍት ፡ ሲናገሩ ፡ ሌሎች ፡ መጻሕፍትና ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ በእናታቸው ፡ በኩል ፡ ከዔ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ አባት ፡ ከጻድቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ጋራ ፡ መዛመዳቸውን ፡ ያረጋግጣል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ዝምድና ፡ ዙፋንን ፡ ለመውረስ ፡ የበቃ ፡ ባለመሆኑ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በኸርሮንድ ፤ በመጨረሻም ፡ ራስ ፡ እየተባሉ፡ ባዔ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድና ፡ ባዔ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ጊዜ ፡ በባለሟልነት ፡ ኖሩ፤ እንጂ ፤ ወራሽ ፡ የሌላቸው ፡ ዐፄ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ እስኪሞቱ ፡ ድረስ ፡ መንግሥትን ፡ ልያዝ ፡ ብለው ፡ በግልጽ ፡ ያደረጉት ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። ነጋሢዎቹ ፡ እነዐፄ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ እነተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ የነጋሢ ፡ ዘር ፡ ነውና ፡ ዙፋን ይፈልግ ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ ጠርጥረው ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ነጋሢ ፡ ዘሮች ፡ በወህኒ ፡ አምባ ፡ ማሰራቸውም ፡ አልተጻፈም ። እንዲያውም ፡ ያዔ ፡ ኢያሱ ፡ ልጅ ፡ ዐፄ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ባረፉ ፡ ጊዜ ፡ የበጌምድር ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ራስ ፡ ፋሪስ ፡ ናዖድ ፡ የሚባለውን ፡ ያ፬ ፡ ዓመት ፤ የሟቹን ፡ ንጉሥ ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ልጅ ፡ ሲያነግሡ ፡ ናዖድ ፡ ሕፃን ፡ ስለሆነ ፡ መንግሥት ፡ ለመያዝ ፡ አይችልም ፡ ብለው፡ ከወህኒ ፤ አምባ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎፍሎስን ፡ አውርደው ፡ ለመንግሥት ፡ ያበቁ ፡ ራስ ፡ ዮስጦስ ፡ ናቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እውነትና ፡ ሐሰቱ ፡ አይታወቅም ፡ እንጂ ፡ መንግሥትን ፡ ለመያዝ ፡ ሲሉ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ታመው ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ መድ

ኃኒት ፡ አብልተው ፡ የገደሏቸው ፡ ራስ ፡ ዮስጦስ ፡ ናቸው ፡ እየተባሉ ፡ ታምተዋል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ግማሹ ፡ በከፋ ፡ ይንገሥ ፡ የቀረው ፡ ዳዊት ፡ ይንገሥ ፡ እያሉ ፡ ሲመክሩ ፡ ርሳቸው ፡ በተሎ ፡ መንግሥት ፡ ይዘው ፡ አይነግሡም ፡ ያሏቸውን፡ እየተከታተሉ ፡ ቀጡ ። የቀድሞዎቹን ፡ መኳንንቶችም ፡ እየሻሩ ፡ የራሳቸውን ፡ ወገኖችና ፡ ታማኞቻቸውን ፡ ሾሙ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አደን ፡ አድናለሁ ፡ ብለው ፡ ከጐንደር ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ በላ ገር ፡ ሄደው ፡ ሳለ ፡ ርስዎን ፡ ከመንግሥት ፡ ለማውረድ ፡ በጐንደር ፡ ዐድማ ፡ ይደ ረጋል ፡ ማለትን ፡ ስለ ፡ ሰሙ ፡ አደኑን ፡ አቋርጠው ፡ በግሥጋሤ ፡ ጐንደር ፡ ገብ ተው ፡ የዚህኑ ፡ የዐድማውን ፡ ነገር ፡ በሰላይ ፡ ሲከታተሉ ፡ እነዚሁ ፡ ዐድመኞች ፡ እጓደኛቸው ፡ ቤት ፡ ተሰብስበው ፡ ሲማከሩ ፡ ተያዙና ፡ ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ የዐድ ማው ፡ ቀንደኞች ፡ የሆኑትን ፡ አስገድለው ፡ የቀሩትን ፡ ግን ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡ እንዲታሰሩ ፡ ፈረዱባቸውና ፡ አገሩ ፡ በሰላም ፡ ለንጉሡ ፡ ለዮስጦስ ፡ ይገዛ ፡ ዠመር ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

### ስለ ፡ ንጉሥ ፡ ዮስጦስ ፡ ሕመም ፡ -ዙፋን ፡ ለመያዝ ፡ የተደረገ ፡ ፍጅት ።

ዐፄ ፡ ዮስጦስ ፡ እንደቀሩት ፡ ነገሥታት ፡ ጐንደር ፡ የልደታን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ አሠሩ ። በዘመናቸውም ፡ አደን ፡ ማደን ፡ በጣም ፡ ይወዱ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብና ፡ ወታደር ፡ ሳያስከትሉ ፡ ወደ ፡ በረሃ ፡ እየሄዱ ፡ ዝኆን ፡ ጐሽ ፡ አውራሪስ ፡ ቀጭኔ ፡ ይገድሉ ፡ ነበር ። ይልቁንም ፡ ብልት ፡ እየመረጡ ፡ አነጣጥሮ ፡ የመምታት፡ ስጦታ ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ በንድ ፡ ጥይት ፡ አንዱን ፡ አውሬ ፡ ይጥሉት ፡ ነበር ፡ ይባ ላል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ፩ ፡ ዐመት ፡ ከራት ፡ ወር ፡ ያኽል ፡ ኢትዮጵያን ፡ እንደ ፡ ገዙ ። የአባ ፡ እንጦስን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመሳለምና ፡ ሥራውንም ፡ ለማየት ፡ በሄዱ በት ፡ ጊዜ ፡ ስለታመሙ ፡ ወዲያው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ተመልሰው ፡ ተኙ ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ ዮስጦስ ፡ የሞቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማን ፡ ይሆን ፡ ገዥ፡ እያለ ፡ የከተማው ፡ ሕዝብ ፡ ይጨነቅ ፡ ዠመር ።

ስለዚህ ፡ አገረ ፡ ገዥዎቹና ፡ መኳንንቶቹ ፡ ተሰብስበው ፡ ንጉሡ ፡ ስለ ፡ ታመሙ፡ ላዩን ፡ ለመጠየቅ ፡ አስመስለው ፡ ውስጡን ፡ ግን ፡ የይዞታቸውን ፡ ልክ ፡ ለማወቅና፡ አንድ ፡ ቊርጥ ፡ ነገር ፡ ለመውሰድ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ቤት ፡ መጡ ። ንጉሡም ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ተበራተው ፡ ከልጋቸው ፡ ተነሥተው ፡ ተቀመጡና ፡ መኳንንቶቹን፡ ተቀብለው ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ ጕዳይ ፡ ያነጋግሯቸው ፡ ዠመር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በሕ መም ፡ መድከማቸው ፡ በፊታቸው ፡ ላይ ፡ በገሃድ ፡ የታወቀ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ «ንጉሡ፡ ደክመዋልና ፡ ልጅዎን ፡ ፋሲልን ፡ ብናነግሠው ፡ ይሻላል» ፡ ብለው ፡ ነገሯቸው ። እነዚህም ፡ መኳንንቶች ፡ ንጉሥ ፡ ዮስጦስ ፡ ገሚሶቹን ፡ ከድኽነት ፡ እያነሱ ፡ ለማዕ ርግ ፡ ያበቋቸው ፡ የቀሩትም ፡ ወዳጆቻቸው ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ በእውነት ፡ አልጋውን ፡ ለልጃቸው ፡ ለመስጠት ፡ ያሰቡ ፡ ናቸው ፡ ይባላል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ሌሎች ፡ የነዐዬ ፡ ኢያሱ ፡ የጥንት ፡ መኳንንቶችና ፡ የከተማው፡ ሕዝብ ፡ ይልቁንም ፡ ወታደሩ ፡ ዐዬ ፡ ዮስጦስን ፡ ቀድሞም ፡ አልወደደም ፡ ነበርና፤ የዐዬ ፡ ዮስጦስን ፡ ልጅ ፡ ለማንገሥ ፡ የተስማሙትን ፡ እነዚህኑ ፡ መኳንንቶች ፡ ከን ጉሡ ፡ ዘንድ ፡ ሲወጡ ፡ ተጠባብቆ ፡ አገኘና ፡ ጥቂቶቹ ፡ ሲያመልጡ ፡ ሁሉንም፡ አደጋ ፡ ጥሎ ፡ አሰራቸው ፡ ዕንቢ ፡ ያሉትንም ፡ እየወጋ ፡ ገደላቸው ፡ ይባላል ።

የዚህ ፡ ሁሉ ፡ ወሬ ፡ ወህኒ ፡ አምባ ፡ በእስር ፡ ስም ፡ በተቀመጡት ፡ የነገሥ ታት ፡ ዘሮች ፡ ዘንድ ፡ ተሰማ ። እነሱም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ንጉሥ ፡ ዮስጦስ ፡ ሁላችንን ፡ አስሮ ፡ ከመከከላችን ፡ አንዳንዳችንን ፡ በአካል ፡ ቅጣት ፡ እየቀጣ ፡ አሠ ቃይቶናልና ፡ አሁን ፡ ደግም ፡ ልጁ ፡ የነገሠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁላችንንም ፡ ይጨርሰ ናል ፡ ብለው ፡ ወህኒ ፡ ጠባቂዎችን ፡ አሸንፈው ፡ ወጡ ። ከወህኒ ፡ አምባም ፡ በወ ረዱ ፡ ጊዜ ፡ ከነሱ ፡ መካከል ፡ አንዱን ፡ ለማንገሥ ፡ ከጐንደር ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ አምባ ፡ ከተላኩት ፡ ጋራ ፡ በመንገድ ፡ ተገናኙ ። በኋላም ፡ ከመከከላቸው ፡ የዐዬ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድን ፡ ልጅ ፡ ዳዊትን ፡ መርጠው ፡ አነገሡዋቸው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አቤቶ ፡ በካፋ ፡ ብቻቸውን ፡ ሆነው ፡ ሲያመልጡ ፡ የቀሩትን ፡ የነጋሢ ፡ ዘሮች ፡ ሁሉንም ፡ ሰብስበው ፡ ወደዚያው ፡ ቀድሞ ፡ ወደ ፡ ነበሩበት ፡ ወደ ፡ ወህኒ፡ አምባ ፡ መልሰው ፡ አስቀመጧቸው ።

## የዐዬ ፡ ዳዊት ፡ (ሣልሳዊ) ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

### ምዕራፍ ፡ ፳፬ ።

### በወልቃይት ፡ ስለ ፡ ተገኙት ፡ ሦስት ፡ ሚሲዮኖች ።

ዐዬ ፡ ዳዊት ፡ አቡነ ፡ ማርቆስና ፡ ዕጨጌ ፡ ዘሚካኤል ፡ ባሉበት ፡ ዘውድ ፡ ደፍ ተው ፡ በሺህ ፡ ፯፻፲ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነገሡ ። ስመ ፡ መንግሥታቸውም ፡ "አድባር ፡ ሰገድ» ፡ ተባለ(1) ። ዕድሜያቸውም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ፳፭ ፡ ዓመት ፡ ነው ። ዐዬ ፡ ዳዊት ፡ በነገሡ ፡ በ፱ኛው ፡ ቀን ፡ ንጉሥ ፡ ዮስጦስ ፡ ሞቱ ። የከተማውም ፡ ሰው ፡ በበሽታ፡ ሞቱ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ዐዬ ፡ ዳዊት ፡ መድኀኒት ፡ አድርገው ፡ ወይም ፡ አሳንቀው፡ ገደሏቸው ፡ እያለ ፡ አወራ ።

ዐዬ ፡ ዳዊት ፡ መንግሥትን ፡ ከያዙ ፡ በኋላ ፡ ፊታውራሪ ፡ አኘ ፡ ለሚባለው፡ ለእናታቸው ፡ ወንድም ፡ የቢቶደድነቱን ፡ ማዕርግ ፡ ሰጥተው ፡ ባለሟል ፡ አደረጉት ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ካህናት ፡ የምናመለክተው ፡ ጉዳይ ፡ አለንና ጉባኤ ፡ ይደረግልን ፡ ብለው ፡ ለንጉሡ ፡ አመለከቱ ። ንጉሡም ፡ ልመናቸውን ፡ ተቀ ብለው ፡ የካህናት ፡ ስብሰባ ፡ ተደረገ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አባ ፡ መዝሙረ ፡ የሚባሉት፡ ተነሥተው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ አመለከቱ ፡ "፫ ፡ የፈረንጅ ፡ ቄሶች ፡ ከባሕር፡

(1) ስመ ፡ መንግሥታቸውን ፡ «አብራክ ፡ ስገድ» ፡ ነው ፡ የሚሉም አሉ ።

አገር ፣ መጥተው ፣ በዐይነ ፣ እግዚእ ፣ (ወልቃይት) ፣ ተቀምጠዋል ። ያስመጧቸውም ፣ ዐፄ ፣ ዮስጦስ ፣ ናቸው ። ርሳቸው ፣ ወልቃይት ፣ ድረስ ፣ በስውር ፣ እየሄዱ ፣ የቄሶቹን ፣ ቅዳሴ ፣ ይሰሙ ፣ ነበር ፤ አሁን ፣ ግን ፣ የእግዚአብሔር ፣ ፈቃድ ፣ ሆኖ ፤ ዮስጦስ ፣ ከሞቱና ፣ ርስዎ ፣ ባባትዎ ፣ ባፄ ፣ ኢያሱ ፣ ዙፋን ፣ ከተቀመጡ ፣ እነዚህ ፣ ፈረንጆች ፣ ይምጡና ፣ ሃይማኖታቸው ፣ ምን ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ይጠየቅልን» ፣ አሉ ።

ንጉሡም ፣ መልክተኛ ፣ ልከው ፣ እነዚህኑ ፣ ፈረንጆች ፣ ካሉበት ፣ ሥፍራ ፣ እጉባኤው ፣ ድረስ ፣ አስመጧቸው ፤ ከነዚህም ፣ አንደኛው ፣ የነምሳ ፣ ፪ቱ ፣ የሮማ ፣ ተወላጅ ፣ ሆነው ፣ ፫ቱም ፣ የካቶሊክ ፣ ሚሲዮኖች ፣ ናቸው ። ያስመጧቸውም ፣ ዐፄ ዮስጦስ ፣ ናቸው ፤ ያስመጡበትም ፣ ምክንያት ፣ ከፈረንጅ ፣ አገር ፣ በነሱ ፣ አማካይነት ፣ የጦር ፣ መሣሪያና ፣ ዕቃ ፣ ለማግኘት ፣ በኢትዮጵያም ፣ ውስጥ ፣ በርሳቸው ፣ ላይ ፣ አገር ፣ ቢነሣባቸው ፣ የወታደር ፣ ርዳታ ፣ ለማስመጣት ፣ አስበው ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ እንደ ፣ አባ ፣ መዝሙረ ፣ አሳብ ፣ በሃይማኖት ፣ በኩል ፣ እንዲያገለግሏቸው ፣ አልነበረም ። ምናልባት ፣ ለዚሁ ፣ ጉዳያቸው ፣ ሲሉ ፣ ለሚሲዮኖቹ ፣ ነፃነትም ፣ ሰጥተው ፣ አንዳንድ ፣ ጊዜም ፣ እነሱን ፣ ለማስደሰት ፣ ሥርዓተ ፣ ቅዳሴያቸውንም ፣ ሰምተዋቸው ፣ ይሆናል ።

እነዚሁም ፣ ሚሲዮኖች ፣ እንደ ፣ መጡ ፣ በጕንደር ፣ የተቀመጡ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ በሃይማኖት ፣ ምክንያት ፣ ከጕንደር ፣ ሊቃውንት ፣ ጋራ ፣ ጠብና ፣ ክርክር ፣ እንደ ዚህ ፣ ቀደም ፣ እንዳይቀሰቀስ ፣ ብለው ፣ በወልቃይት ፣ በተለይ ፣ ዐይነ ፣ እግዚእ ፣ በተባለው ፣ ባንድ ፣ ሥፍራ ፣ ብቻ ፣ እንዲቀመጡ ፣ ንጉሡ ፣ ዮስጦስ ፣ አዘው ፣ ነበር ።

ስለዚህ ፣ ሚሲዮኖቹ ፣ ተጠርተው ፣ እጉባኤ ፣ በቀረቡ ፣ ጊዜ ፣ ሃይማኖታችሁ ፣ ምንድነው ፣ ብለው ፣ አባ ፣ መዝሙረ ፣ ዐረብኛ ፣ ያውቁ ፣ ኖሮ ፣ በረብኛ ፣ ቋንቋ ፣ ጠየቋቸው ፣ እነሱም ፣ በኬልቄዶንያ ፣ ጉባኤ ፣ እንደ ፣ ተለየው ፣ ካቶሊክ ችና ፣ የልዮን ፣ ተከታዮች ፣ ነን ፣ ብለው ፣ በድፍረት ፣ ተናገሩ ።

በዚህ ፣ ጊዜ ፣ በጉባኤው ፣ የነበሩት ፣ ሊቃውንት ፣ ከዚህ ፣ ቀደም ፣ ባፄ ፣ ሱስንዮስ ፣ ጊዜ ፣ መጥተው ፣ በሃይማኖት ፣ ምክንያት ፣ ያንን ፣ ያኽል ፣ ደም ፣ የፈሰሰው ፣ በእንደነዚህ ፣ ያሉት ፣ የተነሣ ፣ ነውና ፣ እነዚህን ፣ አሁኑን ፣ መግደል ፣ ይገባል ፣ እያሉ ፣ ተናገሩ ፤ ለሊቃውንቱም ፣ ወገን ፣ አፈ ፣ ጉባኤ ፣ የነበሩት ፣ ሊቁ ፣ አለቃ ፣ ክፍሌ ፣ ይኸንኑ ፣ ስለፈረዱ ፣ ንጉሡም ፣ ፈቃዳቸው ፣ ሆነና ፣ ወደ ፣ ቈላ ፣ አውርደው ፣ ገደሏቸው ፣ ይባላል ፤ የነዚህም ፣ የሚሲዮናውያኑ ፣ ስም ፣ ሳሙኤል ፣ ዳዊት ፣ ሚካኤል ፣ ነው ።

የካህናቱን ፣ ፈቃድ ፣ መቃወም ፣ አስቸግሯቸው ፣ ይሆናል ፣ እንጂ ፤ ዐፄ ፣ ዳዊት ፣ እነዚህን ፣ ሚሲዮናውያን ፣ ሳያስገድሉ ፣ ሸኚ ፣ ጨምረው ፣ ከኢትዮጵያ ፣ ግዛት ፣ ማስወጣት ፣ ብቻ ፣ ይበቃቸው ፣ ነበር ።

እነሱንም ፣ በወልቃይት ፣ ሳሉ ፣ ይጠብቋቸውና ፣ ያስተናግዷቸው ፣ የነበሩት ፣ ወደ ፣ ችሎትም ፣ ሲመጡ ፣ አብረው ፣ የመጡት ፣ አባ ፣ ጎርጎርዮስ ፣ እዚያው ፣

ስለ ፡ ነበሩ ፡ እርሳቸውንም ፡ አብሮ ፡ መግደል ፡ ይገባል ፡ ብሎ ፡ ጉባኤው ፡ ፍርድ ፡ ዠምሮ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ አባ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ «እኔ ፡ ንጉሥ ፡ የነበሩት ፡ ዐፄ ፡ ዮስጦስ ፡ ባልደረባ ፡ ሁናቸው ፡ ብለው ፡ ሲያዙኝ ፡ ዕንቢ ፡ ለማለት ፡ እችላለሁን ? ነገር ፡ ግን ፡ ሃይማኖቴን ፡ ሳለውጥ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ይፈረድብኛል ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳያችሁ» ፡ ብለው ፡ በኀዘን ፡ ቃል ፡ አመለከቱ ። ጉባኤውም ፡ ተመልሶ ፡ ነገራቸውን ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተቀበለና ፡ በነፃ ፡ እንዲሄዱ ፡ አደረገ ። የዚህም ፡ ጉዳይ ፡ ተፈጸመና ፡ ከያድባራቱ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ካህናት ፡ ተመልሰው ፡ ወደያገራቸው ፡ ሄዱ ።

## ም ዕ ራ ፍ ፳፫ ።

### ስለ ፡ ዐፄ ፡ በካፋ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መታሰር ፤–ብቅባቶችና ፡ በተዋሕዶዎች ፡ ምክንያት የተነሣው ፡ ክርክር ፤–ስለ ፡ አዘዞ ፡ መነኰሳት ፡ መገደል ።

ዐፄ ፡ ዳዊት ፡ በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ የቀሩት ፡ የነገሥታት ፡ ዘሮች ፡ ከመለጡ ፡ በኋላ ፡ ተመልሰው ፡ በወህኒ ፡ አምባ ፡ የታሠሩ ፡ ጊዜ ፡ አምልጠው ፡ የነበሩት ፡ ወንድማቸው ፡ አቤቶ ፡ በካፋ ፡ ካሉበት ፡ ተይዘው ፡ መጡና ፡ እዚያው ፡ ቀድሞ ፡ እነበሩበት ፡ እወህኒ ፡ አምባ ፡ ወጥተው ፡ ከዘመዶቻቸው ፡ ጋራ ፡ ተደባለቁ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በከተማው ፡ የፈንጣጣ ፡ በሽታ ፡ ተነሥቶ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ሲሞት ፡ በዚሁ ፡ ሕመም ፡ አጎታቸው ፡ የነበሩት ፡ ቢትወደድ ፡ አኛ ፡ ሞቱና ፡ ኀዘን ፡ ተደርጎ ፡ ሰነበተ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ የራስ ፡ አንስጣስዮን ፡ ልጅ ፡ ደጃዝማች ፡ ዘጊዮርጊስን ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ጊዜ ፡ ታስሮ ፡ በወህኒ ፡ አምባ ፡ ይኖር ፡ የነበረውን ፡ አምጥተው ፡ የጐጃም ፡ ገዥ ፡ አድርገውን ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከጐጃም ፡ አስመጥተው ፡ ቢትወደድ ፡ አሰኝተው ፡ እንደራሴነቱን ፡ ሰጥተው ፡ አጠገባቸው ፡ አስቀመጡት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስና ፡ በራስ ፡ ወልደ ጊዮርጊስ ፡ መከከል ፡ የሥልጣን ፡ ክርክር ፡ ተነሥቶ ፡ ችግር ፡ ሆኖ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በመጨረሻው ፡ ንጉሡ ፡ ለቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ አድልተው ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስን ፡ በግዞት ፡ አስቀመጡትና ፡ ዋናው ፡ በለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ ብቻ ፡ ሆነ ፡ እርሱም ፡ በጐጃም ፡ ሳለ ፡ ከካህናቱ ፡ ጋራ ፡ የጠበቀ ፡ ወዳጅነት ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በነሱ ፡ ስብከት ፡ እምነቱ ፡ እንደ ፡ ቅባቶች ፡ ነበር ።

ቅባቶችም ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ በለሙሉ ፡ ሥልጣንና ፡ እንደራሴ ፡ መሆኑን ፡ ስላወቁ ፡ ጊዜያችን ፡ አሁን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ክርስቶስ ፡ በተዋሕዶ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ሆነ ፡ ከሚሉት ፡ ከአዘዞ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖሶች ፡ ጋራ ፡ ጉባኤ ፡ ይደረግልንና ፡ እንከራከር ፡ ብለው ፡ ለዐፄ ፡ ዳዊት ፡ አመለከቱ ።

ንጉሡም ፡ ደግ ፡ ነው ፡ ጉባኤ ፡ ይደረግና ፡ ሊቃውንቱ ፡ ተሰብስበችሁ ተከራከሩ ፤ ስለኔም ፡ በጉባኤው ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ ይቀመጥ ፡ ብለው ፡ ነገሯቸው ። የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ተዋሕዶዎችም ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ ቅባት ፡ መሆኑን ፡ ያውቁ ፡ ነበርና ፡ ንጉሡ ፡ ይቀመጡልን ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አለዚያ ፡ በቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ ዳኝነት ፡ አንከራከርም ፡ ብለው ፡ አመለከቱ ።

ዐፄ ፡ ዳዊትም ፡ እንደ ፡ እንደራሴያቸው ፡ የቅባቶችን ፡ ሃይማኖት ፡ ይወዱ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ከጭቅጭቅ ፡ ለመዳን ፡ በሌላውም ፡ ወገን ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ የቤተ ፡ ክህነቱን ፡ የበላይ ፡ አለቃ ፡ ጳጳሱን ፡ በመሆኑ ፡ እንዲያውስ ፡ በአቡነ ፡ ማርቆስ ፡ እግር ፡ አሁን ፡ የመጡትን ፡ ጳጳስ ፡ አቡነ ፡ ክርስቶዶሉን ፡ ጠየቋቸው ፡ ብለው ፡ ለሁለቱም ፡ ወገን ፡ ነገሯቸው ። እነሱም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስን ፡ እንደ ፡ ዳኛ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ጳጳሱ ፡ ሄዱና ፡ የዚህኑ ፡ የሃይማኖት ፡ ነገር ፡ ጠይቋቸው ። ጳጳሱም ፡ የንጉሡ ፡ የዐፄ ፡ ዳዊትና ፡ የእንደራሴያቸው ፡ የቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ ሃይማኖት ፡ ቅባት ፡ መሆኑን ፡ ስላወቁ ፡ ክርስቶስ ፡ በተዋሕዶ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ሆን ፡ ብለው ፡ እንዳይመሰክሩ ፡ ፈሩና ፡ እንዲያው ፡ በደፈናው ፡ የኔ ፡ እምነት ፡ እንደ ፡ ሹመት ፡ አባቶቼ ፡ እንደነአቡነ ፡ ሲኖዳና ፡ እንደነአቡነ ፡ ማርቆስ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መለሱላቸው ። በዚህም ፡ ብልጠት ፡ ባለበት ፡ መልስ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ትርጕሙን ፡ ለየ ራሳቸው ፡ አድርገው ፡ ደስ ፡ ያላቸው ፡ ወደየሥፍራቸው ፡ ተመለሱ ።

ቤተ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚባሉት ፡ የአዘዞና ፡ የሞጊና ፡ (መጕና) ፡ ሊቃውንትም ፡ አቡነ ፡ ክርስቶዶሉ ፡ ሃይማኖቴ ፡ እንደ ፡ ቀድሞዎቹ ፡ ጳጳሶች ፡ እንደ ፡ አባ ፡ ማርቆስና ፡ እንደ ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡ ነው ፡ ማለታቸው ፡ ለኛ ፡ መመስከራቸው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ወደ ፡ አዘዞ ፡ ሄዱ ።

ቅባቶችም ፡ ከቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ተመልሰው ፡ ጳጳሱ ፡ የተናገሩትን ፡ ነገሯቸው ። ንጉሡም ፡ የአቡነ ፡ ማርቆስና የአቡነ ፡ ሲኖዳ ፡ ሃይማኖት ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ኖሯል ፡ ብለው ፡ ባጠገባቸው ፡ ያሉትን ፡ መኳንንትና ፡ ሊቃውንት ፡ ጠየቋቸው ፤ እነሱም ፡ ንጉሡንና ፡ እንደራሴውን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ የነዚህ ፡ የሁለቱም ፡ ጳጳሳት ፡ ሃይማኖት ፡ «ክርስቶስ ፡ በቅብዐተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ሆነ» ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ነገሯቸው ።

ንጉሡም ፡ «መልካም ፡ ነው ፡ ይኸንኑ ፡ ሄዳችሁ ፡ በደባባይ ፡ በዐዋጅ ፡ ንገሩ» ፡ ብለው አዘዟቸው ። እነሱም ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ሄደው ፡ «ክርስቶስ ፡ በቅብዐተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ሆነ ፡ የሚሉት ፡ ቅባቶች ፡ ረቱ ፤ በተዋሕዶ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ሆነ ፡ የሚሉት ፡ ተዋሕዶዎች ፡ ግን ፡ ተረቱ» ፡ ብለው ፡ ዐዋጅ ፡ ነግረው ፡ ተመለሱ ።

ይኸንንም ፡ ዐዋጅና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በጐንደር ፡ የተደረገውን ፡ ደስታ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ተዋሕዶዎች ፡ ሰጪጌያቸውን ፡ ይዘው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለመጠ

የቅ ፡ ወደ ፡ አቡነ ፡ ክርስቶዶሉ ፡ ዘንድ ፡ ሄዱና ፡ ይኸንኑ ፡ የቀድሞ ፡ ጥያ ቄያቸውን ፡ አድሰው ፡ ጠየቋቸው ። አቡኑም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቢትወደዱና ፡ አን ድም ፡ የቅባት ፡ ወገን ፡ ባጠገባቸው ፡ አለመኖሩን ፡ ተመለከቱና ፡ "ክርስቶስ ፡ በመዋሐዱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ሆነ ፡ በመቀባቱ ፡ ግን ፡ መሲሕ ፡ ሆነ ፡ ብለው" ፡ መለሱላቸው ። ይኸንንም ፡ ከጳጳሱ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አላቸውና ፡ ተመለሱ ። አዘዞም ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ በዕጨጌው ፡ ቤት ፡ ንሴብሖ ፡ እያሉ ፡ ዘመሩ ፤ ወረብም ፡ እየወረቡ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ አደረጉ ። ዕጨጌውም ፡ ጥላ ፡ ተይዞላቸው ፡ ታጅበው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ቤተ ፤ ክርስቲያን ፡ ሄደው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቀረቡ ። የዚህም ፡ ወሬ ፡ በጐንደር ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ዳዊትና ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ ተናደዱ ። የጃዊ ፡ ነገዶችን ፡ (የእስላምና ፡ የአረማውያንን ፡ የፈረሰኛ ፡ ወታደ ሮች) ፡ ሄዳችሁ ፡ የአዘዞን ፡ ሊቃውንት ፡ ፍጅዋቸው ፡ ብለው ፡ ሰደዷቸው ። እነሱም ፡ በግልቢያ ፡ ደርሰው ፡ ሊቃውንቱ ፡ በዕጨጌው ፡ ቤት ፡ እንዳሉ ፡ አገ ኟዋቸውና ፡ መነኰሳቱን ፡ ግማሾቹን ፡ እየሰለቡ ፡ የቀሩትንም ፡ እየገደሉ ፡ በጭ ካኔ ፡ ፈጁዋቸው ። እጨጌ ፡ ተክለ ፡ ሃማኖትም ፡ ዕራቍታቸውን ፡ እየጐተቱ ፡ ደበደቧቸው ፤ ወደ ፡ ማታ ፡ ግን ፡ ንጉሡ ፡ እንግዲህ፡ በቃችሁ፡ ብለው ፡ ላኩባቸውና፡ ተመለሱ ፡ ይባላል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከቅባቶች ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ ደብተራ ፡ በእ ጨጌውና ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ተዋሕዶዎች ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ የቀ ልድ ፡ ቅኔ ፡ ተቀኘ ። ሰላም ፡ እብል ፡ ለሰብለ ፡ አዘዞ ፡ ፀረ ፡ ቅባት ፡ ወእጨ ጌሆሙ፡ ፡ ዕጨጌነት ፡ ከሚስት ።

ሶበ ፡ እንቢ ፡ ለግዜር ፡ ይቤሉ ፡ ወእንቢ ፡ ለንጉሥ ፡ ዳዊት ።
ጃዊ ፡ ቀደደ ፡ ሆድ ፡ ሆዶሙ ፤ ወሰለቦሙ ፡ እስከ ፡ ጎንብርት ፤
ወበእንተዝ ፡ ይቤሉ ፡ በ፶ ፡ ዓመት ፡ ግዝረት ፡ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ዳዊት ፡ ጳጳሱን ፡ አቡነ ፡ ክርስቶዶሉን ፡ አስጠር ተው ፡ የቅባቶችን ፡ መርታትና ፡ የተዋሕዶዎችን ፡ መረታት ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ እንዲያውቀው ፡ ሄደው ፡ ባደባባይ ፡ ሀዋጅ ፡ ይንገሩ ፡ ብለው ፡ አዘዟቸው ። ጳጳሱም ፡ መንፈሳቸው ፡ ደካማና ፡ ሰውን ፡ ደስ ፡ ማሰኘት ፡ ብቻ ፡ ስለ ሚወዱ ፡ ምንም ፡ የፊት ፡ ለፊት ፡ ክርክር ፡ ሳያደርጉ ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ ሄደው ፡ "ክርስቶስ ፡ በቅብዐተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የባሕርይ ፡ አም ላክ ' ሆነ» ፤ ብለው ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ፡ ይባላል ።

በያገሩ ፤ በየደብሩ ፡ በየቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ የሚገኘው ፡ በግዕዝ ፡ ወይም ፡ ባማርኛ ፡ የተጻፈው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ አይስማማም ። የዚህም ፡ ምክንያት ፡ ጸሐፊው ፡ ቅባት ፡ ወይም ፡ ጸጋ ፡ ይልቁንም ፡ ተዋሕዶ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ አሳብ ፡ እያደላ ፡ በመጻፍ ፡ ይሆናል ።

አብዛኛው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥትና ፡ እርሱንም ፡ መሠረት ፡ እያደረጉ ፡ የሚጽፉት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ባፄ ፡ ዳዊት ፡ ዘመን ፡ የተደረገውን ፡ ይህን ፡ የቅባቶችንና ፡ የተዋሕዶዎችን ፡ ክርክር ፡ ይልቁንም ፡ የተዋሕዶዎችን ፡ አልቂት ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሲጽፉ ፡ አንዳንዱ ፡ የብራና ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ባጭሩ ፡ «ዕድሜዬ ፡ ይርዘም ፡ የምትል ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በኛ ፡ ሃይማኖት ፡ ግባ ፡ ዓርባ ፡ ዓመት ፡ ትገዛለኽ ፡ ብለው ፡ ቅባቶች ፡ ለዐፄ ፡ ዳዊት ፡ ላኩባቸው ፡ እርሳቸውም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ በቅብዐት ፡ አምነው ፡ ሳያከራክሩ ፡ ዐዋጅ ፡ ለቅባቶች ፡ አስነግረው ፡ ተዋሕዶዎችን ፡ አስፈጇዋቸው ፤ ጳጳሱም ፡ ቅባትነትዎን ፡ ትተው ፡ በባቶችዎ ፡ ሃይማኖት ፡ በተዋሕዶ ፡ ይርጉ ፡ ብለው ፡ ቢገዝቷቸው ፡ እንቢ ፡ አሉ» ፡ ብሎ ፡ ባጭሩ ፡ ይጨርሳል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በዚህም ፡ ቢሆን ፡ ባለፈውም ፡ አኳኋን ፡ ቢሆን ፡ በጠቅላላው ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ቅባቶች ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ የንጉሡ ፡ ባለሟል ፡ ሆነው ፡ በልበ ፡ ቅንነትና ፤ በእምነት ፡ ለንጉሡ ፡ ሲገዙ ፤ የተዋሕዶ ፡ ወገን ፡ የሆነው ፡ መኳንንቱም ፡ ሊቃውንቱም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በውጭ ፡ ሰውነቱ ፡ ደስ ፡ ያለው ፡ መስሎ ፡ ቢኖር ፡ በውስጠ ፡ መንፈሱ ፡ ግን ፡ ኀዘን ፡ እንደ ፡ ነበረበት ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ የአዘዞና ፡ የሞጊና ፡ (መጉና) ፡ ቀሳውስት ፡ በተዋሕዶ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ምክንያት ፡ በረመኔዎች ፡ እጅ ፡ በንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ መገደላቸውን ፤ የከበሩትም ፡ ዕጨጌ ፡ ዕራቍታቸውን ፡ እየተገሎተቱ ፡ መደብደባቸውን ፡ የሰማ ፡ ሁሉ ፡ በልቡ ፡ እያዘነ ፡ ንጉሡንና ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስን ፡ በየቤቱ ፡ ያሟቸው ፡ ዠመር ።

## ምዕራፍ ፳፮ ።

## የደጃች ፡ ለታ ፡ ዐድማ ፡–ስለ ፡ ዐፄ ፡ ዳዊት ፡ በጎ ፡ ተግባር ፤–የሰንበቴ ፡ ማኅበር ።

በዚህ ፡ መካከል ፡ ንጉሡ ፡ ዳዊት ፡ ታመሙና ፡ በጐንደር ፡ በንጉሡና ፡ በቢትወደድ ፡ ላይ ፡ ዐድማ ፡ ተደረገባቸው ። ዐድማውንም ፡ ያሥነሡ ፡ ደጃዝማች ፡ ለታና ፡ የታሳሪው ፡ የራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ነገሩንም ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ ስለ ፡ ሰማው ፡ የቀሩትን ፡ መኳንንቶች ፡ በቤቱ ፡ ሰብስቦ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፤ «ንጉሡ ፡ ዳዊት ፡ አምና ፡ ከፈረስ ፡ በወደቁት ፡ ምክንያት ፡ ታመዋል ፡ ማለት ፡ ሐሰት ፡ ነው ፤ የታመሙት ፡ ደጃዝማች ፡ ለታ ፡ መድኃኒት ፡ አድርጎባቸው ፡ ነው ፤ እሱም ፡ ንጉሡን ፡ ለመግደል ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ዐድማ ፡ አድርጓል ፡ በዐድማውም ፡ ውስጥ ፡ የራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ልጅ ፡ አብሮ ፡ አለ ። አሁን ፡ ግን ፡ ዐድማውን ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ሳያደርሱ ፡ በቶሎ ፡ ሁሉንም ፡ በድንገት ፡ እየያዙ ፡ ማሰር ፡ ይሻላል» ።

መኳንንቶቹም ፡ እሺ ፡ አሉና ፡ ዐድመኞች ፡ የተባሉት ፡ መያዝ ፡ ዠመሩ ፤ ደጃዝማች ፡ ለታ ፡ ግን ፡ ዠግና ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ሊይዙት ፡ ከመጡት ፡

ዘበኞች ፣ ውስጥ ፣ አንዱን ፡ በጦር ፡ ወግቶ ፣ ጣለው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የቀሩት ፡ መላልሰው ፡ ስለ ፡ ወጉት ፡ ከዚያ ፡ ደሙን ፡ እያንጠበጠበ ፡ ቅጥር ፡ ዘሎ ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፣ አገር ፡ ለማምለጥ ፡ መንገድ ፡ ዠምሮ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን በትሩ ፡ ከፉኛ ፡ ስለ ፡ ነበረና ፡ ሰውነቱ ፡ ስለ ፡ ደከመ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄዶ ፡ ተኛ ። ጥቂትም ፡ እንደ ፡ ቈየ ፡ ዘበኞቹ ፡ ደርሰው ፡ ያዙትና ፡ ወደ ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ ቤት ፡ ወስደው ፡ ዐይኑን ፡ አሳውረው ፡ ገደሉት ። የራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ልጅና ፡ የቀሩትም ፡ በዐድማው ፡ ሥራ ፡ የተገኙት ፡ እየተመረመሩ ፡ ኀጢአታቸው ፡ የቀለለው ፡ ታሰሩ ፤ ኀጢአታቸው ፡ የከበደው ፡ ተገደሉ ።

ዐፄ ፡ ዳዊት ፡ ግልሰዊ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ምንም ፣ እንኳን ፣ ቅባት ፡ ቢሆን ፡ ስለዚህም ፡ ሃይማኖት ፡ ቀናተኛ ፡ ሆነው ፡ በአዘዞ ፡ ሊቃውንትና ፡ በዕጨጌው ፡ ላይ ፡ ከቢትወደድ ዘጊዮርጊስ ፡ ጋራ ፡ ተባብረው ፡ የማይገባ ፡ ሥራ ፡ ቢሠሩም ፡ አንዳድም ፡ ታሪክ ፡ ዘፈን ፡ ይወዱ ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ (ዘፋኝ ፡ ዳዊት) ፡ እያለ ፡ ቢጠሩቸውም ፡ በቀረው ፡ ወገን ፡ በጊዜያቸው ፡ የተጻፈው ፡ ጽሑፍ ፡ እንደሚተርክላቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈሩ ፡ ደግነትንና ፡ መንፈሳዊነትን ፡ አጥባቂ ፡ ነበሩ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከግብርና ፡ ከእጅ ፡ መንሻ ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመንግሥቱ ፣ ሥራ ፡ መሥሪያ ፡ እያደረጉ ፡ ርሳቸው ፡ ግን ፡ የቁም ጽሕፈትና ፡ የድጕሰት ፡ ሙያ ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ በዚሁ ፡ ሙያቸው ፡ በሚያተርፉት ፡ ገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ሁል ፡ ጊዜም ፡ ከማዕዳቸው ፡ የሚተርፈውን ፡ እያወጣችሁ ፡ ለደኻ ፡ አብሉልኝ ፡ ይሉ ነበር ፡ ይባላል ።

፨ ፨ ፨

ደግሞ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን የሰው ገንዘብ ፡ ሳይደባልቅ ፡ ደክሞ ፡ ባፈራው ፡ ገንዘብ ፡ የሚኖር ፡ ማነው ፡ ብለው ፡ ጠየቁ ፤ ባጠገባቸውም ፡ ያሉ ፡ ባለሟሎች ፡ ገበሬ ፡ ነው ፡ ብለው መለሱላቸው ፤ ንጉሡም ፡ ከገበሬዎቹ ፡ ውስጥ ፡ ሽማግሌዎች ፡ የሆኑትን ፡ መርጣችሁ ፡ አምጡልኝ ፡ ብለው ፣ አመጡላቸውና ፡ ከነሱ ፣ ጋራ ፡ እሁድ ፡ እሁድ ፡ ሰንበቴ ፡ አብረው ፡ ይጠጡ ፡ ዠመር ።

ከሰንበታቶቹ ፡ በ፭ኛው ፡ ቀን ፡ ትኵስ ፡ ወተት ፡ የሚመስል ፡ ቡሌ ፡ የሚባለውን ፡ ኀይለኛ ፡ የጐንደር ጠላ ፡ ደጋግሞ ፡ ጠጥቶ ፡ በዚሁ ፡ መጠጥ ፡ አእምሮው ፡ የተነካ ፡ አንድ ፡ ማኅበረተኛ ፡ ተነሥቶ ፡ ንጉሡን ፡ በጥፊ ፡ መታቸው ። ሰውም ፡ እንምታው ፡ እያለ ፡ ሲጋበዝ ርሳቸው ፡ መጠጥ ፡ ቢያሸንፈው ፡ ነውና ፡ ተውት ፤ ይልቅስ ፡ እቤቱ ፡ ወስዳችሁ ፡ አስተኙት ፡ ብለው ፡ አዘዙና ፡ ወስደው ፡ አስተኙት ።

በማግስቱ ፡ ችሎት ፡ ተዘርግቶ ፡ በዚህ ፡ ሰውዬ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ተዠመረ ፤ መኳንንቱም ፡ ሊቃውንቱም ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ፈረዱበት ። እንዲህም ፡ አራቱ ፡ ሊቀ ፡ መጣኞች ፡ አዛገሮች ፡ (ባለፍትሐ ፡ ነገሥቶች)ዘያወርድ እዴሁ ፡ ዲበ ፡

መሲሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይትመተር ፡ እዴሁ ፡ (እግዘአብሔር ፡ ቀብቶ ፡ በነገሠው ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ የሚዘረጋ ፡ እጁ ይቈረጥ) ፡ የሚለውን ፡ ጠቅሰው ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ፈረዱበት ።

ንጉሡም ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ ከችሎት ፡ ወደ ፡ እልፍኛቸው ፡ ተመልሰው ፡ ገቡ ። በዚያም ፡ ሊቃውንቱንና ፡ መኳንንቱን ወንጀለኛውን ፡ ጭምር ፡ አስጠርተው ፡ በነሱ ፡ ፊት ፡ አንድ ፡ የአንበሳ ፡ ለማዳና ፡ የዝንጀሮ ፡ ለማዳ ፡ አስመጥተው ፡ አቆሙ ። ዝንጀሮውም ፡ አንበሳውን ፡ አይቶ ፡ በፍርሃት ፡ ይንቀጠቀጥ ፡ ዠመር ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በቈሬ ፡ ሙሉ ፡ ጠጅ ፡ አቀረቡላቸው ፡ ሁለቱም ፡ አብረው ፡ ጠጡ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዝንጀሮው ፡ ፍርሃቱ ፡ ተወገደለትና ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ ይቀናጣ ፡ ዠመር ፤ እንዲያውም ፡ በአንበሳው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ እየተዛና ፡ ተቀመጠ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ፊታቸውን ፡ ወደ ፡ መኳንንቱ ፡ አዞረው ፡ አሁንስ በማን ፡ ትፈርዳላችሁ ፡ ቀድሞውንም ፡ ከገበሬ ፡ ጋራ ፡ ማኅበር ፡ በመጠጣቴ ፡ ያጠፋሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ በማኅበርና ፡ በቦታ ፡ ባንገናኝ ፡ ኖሮ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ መቼ ፡ ይደፍረኝ ፡ ነበር ፡ ብለው ፡ ወደ ችሎት ፡ ተመልሰው ፡ ምሕረት ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ በሰላም ፡ ሰደዱት ፡ ይባላል ። በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ደግነትና ርኅራኄ ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ከገዙ ፡ በኋላ ፡ በሺሕ ፡ ፮፻፲፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በግንቦት ፡ ወር ፡ እሁድ ፡ ዐረፉና ፡ ወንድማቸው ፡ በካፋ ፡ በዙፋን ፡ ተቀመጡ ።

## የዐፄ ፡ በካፋ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፯ ።

ስለ ፡ ፀፄ ፡ በካፋ ፤ ስለ ፡ ንግሣቸው ፡ በርሣቸው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ያሉት ፡ የሹማምንት ፡

## ዝርዝር ።

ከዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ በፊት ፡ በጐንደር የነገሡት ፡ እነሠርፀ ፡ ድንግል ፡ እነ ሱስንዮስ ፡ እነፋሲል ፤ እነዮሐንስ ፡ ታላላቅ ፡ ነገሥታት ፡ ሆነው ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ በማግኘት ፡ ለጊዜው ፡ የሚስማማውን ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ ለኢያሱ ፡ አድ ያም ፡ ሰገድ ፡ መንግሥትን ፡ አቀበሉ ። ኢያሱም ፡ ከባቶቻቸው ፡ ቢበልጥ ፡ እንጂ ፡ በማያንስ ፡ አገዛዝና ፡ አያያዝ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ገዝተው ፡ አለፉ ። እርሳቸው ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ የነገሡት ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ልጃቸው ፤ ቴዎፍሎስ ፡ ወን ድማቸው ፤ ዮስጦስ ፡ መኰንናቸው ፤ ዳዊት ፡ ልጃቸው ፡ ከነዚያ ፡ ደከም ፡ ያሉ ፡ ሆነው ፡ እንደ ፡ ጥቃቅን ፡ ነገሥታት ፡ ይታያሉ ። የዚህም ፡ ምክንያት ፡ የግዛታቸው ዘመን ፡ አጭር ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ ባጭሩ ፡ ጊዜያቸው ፡ የሠሩት ፡ ሥራ በሕዝብ ፡ እንደበት ፡ ደምቆ ፡ ለመነገር ፡ ሳይመጥን ፤ ለጽሕፈትም ፡ ብዙ ፡ ምዕ ራፎች ፡ ሳያገኝ ፡ በመቅረቱ ፡ ነው ። አሁን ፡ ግን ፡ መንግሥትን ፡ ከወንድማቸው ፡

ከዳዊት ፡ የተቀበሉት ፡ በካፋ ፡ እንደ ፡ ታላላቆቹ ፡ ነገሥታት ፡ ለመቈጠር ፡ ባይ ቈጠሩም ፡ ወደነዚያው ፡ ቍጥር ፡ ለመጠጋት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አይቀራቸውም ፡ ስንል ፡ ታሪካቸውን ፡ በሚቀጥለው ፡ እንመልከት ።

፨ ፨ ፨

በካፋ ፡ የታላቅ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ልጅ ፡ ናቸው ። እናታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ማርያማዊት ፡ (ማርያም ፡ መዋዒት ?) ፡ ይባላሉ ። የእናታቸው ፡ አባት ፡ አቤቶ ፡ ሚካኤል ፡ አያታቸው ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ይባላሉ ።

ስለ ፡ በካፋ ፡ ልደትና ፡ እድገት ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዙ ፡ አዛዥ ፡ ሲኖዳ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ በታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ጽፎ ፡ ይገኛል ።

እንደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ልብሳቸውን ፡ በደም ፡ ያጠቡት ፡ እንደ ፡ ቂርቆስ ፡ በእሳት ፡ የተቃጠሉት ፡ እንደ ፡ ገላውዴዎስ ፡ በጦር ፡ የተወጉት ፡ (1) ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ከይበባ ፡ ወደ ፡ በካፋ ፡ እናት ፡ ወይዘሮ ፡ ማርያማዊት ፡ ርስት ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ዲማ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሄዱ ። በዚያም ፡ የማርያማዊትን ፡ መልክና ፡ ደም ፡ ግባት ፡ እንደዚሁም ፡ ንጽሕናቸውንና ፡ ጸሎት ፡ አዘውታሪነታቸውን አይተው ፡ ደስ ፡ አላቸው ። በኋላ ፡ ሴትዮዋ ፡ ድንግል ፡ ሳሉ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ቢገናኙዋቸው ፡ ጸንሰው ፡ በጊዜው ፡ በካፋን ፡ ወለዱ ። የበካፋን ፡ መወለድ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አላቸው ። እግዚአብሔርንም አመሰገኑ ። ወዲያውም ፡ "ይህ ፡ ሕፃን ፡ መንግሥቴን ፡ ይወርሳል ፡ በዘመኑም ፡ ሰላምና ፡ ደስታ ይሆናል ። , . . ." ብለው ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩላቸው ። እናትዮዋም ፡ «ታዐብዮ ፡ ነፍስየ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘርእየ ፡ ትሕትናሃ ፡ ለአመቱ ፡ እስመ ፡ ገብረ ፡ ሊተ ፡ ኀይለ ፡ ዐቢያተ ፡ . . . .» (2) ብለው ፡ ጸለዩ ።

በካፋንም ፡ አባታቸውና ፡ እናታቸው ፡ በጣም ፡ ይወዷቸው ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ በፍቅር ፡ በጥበብና ፡ በጸጋ ፡ አሳደጓቸው ። ዐሥር ፡ ዓመትም ፡ በሞላቸው ፡ ጊዜ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ በግቤ ፡ በኩል ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ እናሪያ ፡ ሲሄዱ ፡ ግስላ ፡ (የግስላ ፡ ለምድ ?) ፡ አልብሰው ፡ ጦር ፡ አሲዘው ፡ አስከትለዋቸው ፡ ሄዱ ። በመንገድም ፡ በካፋን ፡ ያዩ ፡ ካህናትም ፡ ባሕታውያንም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንደሚነግሡ ፡ ተነበዩላቸው ። እንደዚሁም ፡ ንጉሡ ፡ ኢያሱ ፡ ቱሉ ፡ ቁባ ፡ ሉባ ፡ በሚባለው ፡ የጋላ ፡ አገር ፡ ሲያልፉ ፡ ፩ ፡ ጋላ ፡ አግኝቶኝ ፡ እባክህ ፡ በካፋ ፡ የሚባለውን ፡ የጉሡን ፡ ልጅ ፡ አሳየኝ ብሎ ፡ ለምኖኝ ፡ ባሳየሁት ፡ በ፫ኛ ፡ ቀን ፡ ‹ተመልከት ፡ ይህ ፡ ሕፃን ፡ ልጅ ፡ በኋላ ፡ ይነግሥና ፡ ኀይለኛ ፡ ይሆናል ። ሜጫንና ፡

(1) እንዳርመን ፡ በገደሏቸው ፡ ጊዜ ፡ የተደረገባቸውን ፡ ግፍ ፡ ሲያስታውስ ፡ ነው ።

(2) ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ሲኖዳ ፡ በሉቃስ ፡ ወንጌል ፡ ምዕ ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፵፮—፶፭ ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ የጸለየችውን ፡ ወይዘሮ ፡ ማርያማዊት ፡ እንደ ፡ ጸለዩት ፡ አስመስሎ ፡ ራሱ ፡ ጽፎት ፡ እንደሆን ፡ ወይም ፡ ሴትዮዋ ፡ በርግጥ ፡ ጸልየውት ፡ እንደሆን ፡ አይታወቅም ።

ቱለማንም ፡ ደርቦ ፡ ይገዛል» ፡ ብሎ ፡ በሰፊው ፡ አጫወተኝ ፡ ሲል ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ሲኖዳ ፡ በታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ መዠመሪያ ፡ ላይ ፡ ይጽፋል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በከፋ ፡ አባታቸውም ፡ ባሕታውያኑም ፡ ጋላውም ፡ የተነበዩላቸው ፡ ትንቢት ፡ ተፈጽሞ ፡ እስኪነግሡ ፡ ድረስ ፡ እዚያው ፡ እነገሥታቱ ፡ ልጆች ፡ ደንበኛ ፡ ሥፍራ ፡ እወህኒ ፡ አምባ ፡ ወጥተው ፡ ተቀመጡ ፡ በዚያም ፡ ሳሉ ፡ ይበልጥ ፡ ጊዜያቸውን ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በስግደት ፡ ምጽዋት ፡ በመስጠት ፡ መጻሕፍት ፡ ቅዱሳትን ፡ በመመልከት ፡ ያሳልፉ ፡ ነበር ። እንዲያውም ፡ እንደ ፡ ባሕታውያን ፡ ምሳቸውን ፡ የሚበሉት ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ ይገልጻል ። የርሳቸውንም ፡ አያያዝ ፡ በመመልከት ፡ የተጠማ ፡ እንስሳ ፡ የውሃ ፡ ምንጭን ፡ ለማግኘት ፡ እንደሚናፍቅ ፡ እንደዚሁ ፡ መቼ ፡ ይሆን ፡ የሚነግሠው ፡ እያሉ ፡ በያለበት ፡ ያሉት ፡ ካህናትና ፡ ባሕታውያን ፡ ትልቁም ፡ ትንሹም ፡ ይናፍቅ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ጨምሮ ፡ ይገልጻል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ወንድማቸው ፡ ዐፄ ፡ ዳዊት ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ ገዝተው ፡ በ፹ሕ ፡ ፲፻፲፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ መኳንንቱን ፡ በቤቱ ፡ ሰብስቦ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ከወይዘሮ ፡ ማሚት ፡ (ነገላ) ፡ የወለዱት ፡ አቤቶ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ይንገሥ ፡ ሲል ፡ አማከራቸው ፤ የተሰበሰቡትም ፡ ሰዎች ፡ እንቢ ፡ እንዳይሉ ፡ አቤቶ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ የራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ የባለቤቱ ፡ ወንድም ፡ ስለሆነ ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ ራስ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ ኀይለኛና ፡ የሚፈራ ፡ ነውና ፡ ከልባቸው ፡ ሳይሆን ፡ ለጊዜው ፡ ደግ ፡ ነው ፡ እርስዎ ፡ እንዳሉት ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ይንገሥ ፡ ብለው ፡ መለሱለት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ ትእዛዝ ፡ ሊቁ ፡ ዮናታን ፡ በጭፍራ ፡ ታጅቦ ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ ወጣና ፡ «አቤቶ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ነግሠዋል» ፡ የሚል ፡ ዐዋጅ ፡ ነገረ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ውላጅ ፡ የሚባሉት ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ የልፍኝ ፡ ወታደሮች ፡ ከሌሎች ፡ መኳንንቶች ፡ ጋራ ፡ ለብቻ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሆነው ፡ በወህኒ ፡ አምባ ፡ ያሉት ፡ በካፋ ፡ እንዲነግሡ ፡ በምክር ፡ ቈረጡ ። በነዚህ ፡ ስብከት ፡ ተመርተው ፡ ከራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ወገን ፡ የነበሩት ፡ መኳንንቶችም ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ተገልብጠው ፡ ወደነዚህ ፡ መጡ ። ከዚህ በኋላ ፡ በካፋን ፡ ከወህኒ ፡ አምባ ፡ ለማውረድ ፡ ያንድ ፡ ክፍል ፡ ጭፍራ ፡ ተላከ ። እነሱም ፡ እተራራው ፡ ጥግ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በወህኒ ፡ አባ ፡ ያሉት ፡ የነጋሢ ፡ ዘሮች ፡ አልጋው ፡ ለኔ ፡ ይገባል ፡ በማለት ፡ ግማሹ ፡ በካፋ ፡ ኀይለኛና ፡ ጥብቅ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይጨቍነናልና ፡ አይነግሥም ፤ የሚነግሠውን ፡ ከመካከላችን ፡ እኛው ፡ መርጠን ፡ እንሰጣለን ፡ በማለት ፡ ፍጅት ፡ ሆኖ ፡ ጭቅጭቁ ፡ እዚያው ፡ እየተራራው ፡ ሥር ፡ እስከ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ቈየ ፡ ይባላል ። በተራራው ፡ ሥር ፡ ያሉት ፡ በካፋን ፡ ለማምጣት ፡ የተላኩት ፡ ግን ፡ መኳንንቱም ፡ ሕዝቡም ፡ በካፋን ፡ ነውና ፡ የመረጠው ፡

አሁን ፡ ከምታስቸግሩት ብትለቁት ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ መከሯቸው ፤ በዚህም ፡ ላይ ፡ የበጌምድሩ ፡ ደጃዝማች ፡ አምኃየስ ፡ ለበካፋ ፡ ለመርዳት ፡ ሠራዊት ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ጥግ ፡ መምጣቱ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ እነዚሁ ፡ በካፋን ፡ አናስወ ርድም ፡ ብለው ፡ የነበሩት ፡ የነጋሢ ፡ ዘሮች ፡ ቂም ፡ ይዘኸ ፡ በነገሥኸ ፡ ጊዜ ፡ እን ዳታጉላላን ፡ ቃል ፡ ግባልንና ፡ እንልቀቅኸ ፡ አሏቸው ። በካፋም ፡ ቃል ፡ ገቡላ ቸውና ፡ ተለቀው ፡ ከተራራው ፡ ወርደው ፡ ከሚጠብቋቸው ፡ ከነደጃዝማች ፡ አም ኃየስ ፡ ጋራ ፡ ተገናኙ ። የዚህንም ፡ ወሬ ፡ ብንያም ፡ የሚባለው ፡ ጐንደር ፡ ሄዶ ፡ ተናገረና ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ አምጥቶ ፡ የንጉሥ ፡ ልብስ ፡ በካ ፋን ፡ አለበሳቸው ፤ እንደ ፡ ለበሱም ፡ በእነርሱ ፡ ታጅበው ፡ ጐንደር ፡ ከተማ ፤ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ጳጳሱ ፡ አቡነ ፡ ክርስቶዶሉና ፡ ዕጨጌ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከሊቃ ውንቱ ፡ ጋራ ፡ ወታደሩም ፡ ሕዝቡም ፡ ባንድነት ፡ ሆኖ ፡ በደስታ ፡ ተቀበላቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጳጳሱ ፡ ጽራግ ፡ ማሰሬው ፡ እስመ ፡ በጻሕከ ፡ በበረከት ፡ ሠናይ ፡ ወአንበርከ ፡ አክሊለ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ፡ ዘእምዕንቍ ፡ ክቡር ፡ ......... የሚባ ለውን ፡ እየደገሙ ፡ ቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ ቀብተው ፡ ዘውዱን ፡ ደፋላቸውና ፡ ሥርዐተ ፡ ንግሣቸው ፡ በደንብ ፡ ተከበረ ፤ ስመ ፡ መንግሥታቸውም ፡ «መሲሕ ፡ ሰገድ» ፡ ተባለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪው ፡ ወጥቶ ፡ «ንጉሣችን ፡ ዳዊት ፡ ሞተዋል ፡ በርሳቸው ፡ እግር ፡ በካፋን ፡ አንግሠናል ፡ ጠላቶቻችን ፡ ይፈሩ ፡ ወዳ ጆቻችን ፡ ይደሰቱ› ፡ የሚል ፡ ዐዋጅ ፡ ነገረ ።

፨ ፨ ፨

ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስም ፡ አቤቶ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ለማንገሥ ሲል ፡ በዐፄ ፡ በካፋ ፡ ላይ ፡ የሠራውን ፡ ሁሉ ፡ ያውቃልና ፤ ዐፄ ፡ በካፋ ፡ ገና ፡ ከወህኒ ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ቤቱን ፡ ትቶ ፡ ከነቤተ ፡ ሰቡ ፡ ወደ ፡ አቡኑ ፡ ቤት ፡ መጥቶ ፡ ተማጥኖ ፡ ተቀመጠ ። በኋላም ፡ በአቡኑ አማላጅነት ፡ ተፈርዶበት ፡ የነበረው ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ቀረለትና ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጣ ። ንጉ ሡም ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ባላፈ ፡ ሥራው ፡ ጥቂት ፡ ከወቀሱት ፡ በኋላ ፡ በግዞት ፡ የምትቀመጥበትን ፡ ሥፍራ ፡ አንተው ፡ ምረጥና ፡ ከጐንደር ፡ ውጣልኝ ፡ አሉት ። ራስ ፡ ቢትወደድም ፡ በመጕና ፡ ብቀመጥ ፡ ይሻለኛል ፡ ብሎ ፡ ንጉሡን ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ሄደ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ሲደርስ ፡ ሊቃውንቱና ፡ ካህናቱ ፡ ተሰ ብስበው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ለቅባቶች ፡ አድልቶ ፡ የጃዊን ፡ ወታደር ፡ ልኮ ፡ ቀሳ ውስቱን ፡ ወንድሞቻችንን ፡ ያስፈጀና ፡ አባታችንን ፡ ዕጨጌ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ዕራቍታቸውን ፡ እያስጐተተ ፡ ያስደበደበ ፡ እርሱ ፡ አይደለምን ፡ ብለው ፡ ድንጊያ ፡ እየወረወሩ ፡ አባረሩት ። እርሱም ፡ ከዚያ ፡ ተመልሶ ፡ በንጉሡ ፡ ፈቃድ ፡ በአ ደጋት ፡ ቄላ ፡ ገብቶ ፡ ተቀመጠ ፤ የዐፄ ፡ በካፋም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ እስኪ ያልቅ ፡ ድምፁ ፡ አልተሰማም ፡ ይባላል ።

ዐፄ ፡ በካፋም ፡ የእንደራሴነቱን ፡ ሥራ ፡ በመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ለቢትወደድ ፡ ኢራቅሊስ ፡ የእንደራሴነት ፡ ማዕርግ ፡ ጨምረው ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ ፡ የቀረውንም ፡ የሥልጣን ፡ ሥፍራ ፡ በየክፍሉ ፡ በየደረጃው ፡ በሹም ፡ ሽር ፡ አከፋፍለው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ሥፍራቸውን ፡ ያስኬዱ ፡ ዠመር ።

ላንባቢም ፡ ሐሳብ ፡ ለመስጠት ፡ ያኽል ፡ በርሳቸው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ የነበሩትን ፡ የቀድሞና ፡ የቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የሊቃውንት ፡ የመኳንንት ፡ የሹማምትም ፡ ስም ፡ ከታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ለቅመን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ዘርዝረነዋል ።

ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ በበካፋ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት፡
በሞት ፡ በጠብ ፡ የተለዩ ፡ በሹም ፡ ሽር ፡ የተዘዋ
ወሩ ፡ አሉባቸው ።

## ቤተ ፡ ክህነት ።

ጳጳሱ ፡ አባ ፡ ክርስቶዶሉ ፡
ዕጨጌው ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ዕጨጌ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ከተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
በኋላ ፡
ዐቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ወልደ ፡ ሐዋርያት ፡
ቄስ ፡ ዐፄ ፡ ቀውስጦስ ፡
መልአከ ፡ ብርሃናት ፡ ፀሐየ ፡ ልዳ የልደታ ፡
አለቃ ፡

## ቤተ ፡ መንግሥት ።

ቢትወደድ ፡ ኢራቅሊስ ፡ (ከራስ ፡ አምኃየስ ፡ በፊትና ፡ ራስ ፡ አምኃየስ ፡ ከሸፈተ ፡ በኋላ ፡ የቢትወደድነት ፡ ሥፍራ ፡ ላጭጭር ፡ ጊዜ ፡ የወሰደ ፡ ይመስላል) ፡

ራስ ፡ አምኃየስ ፡ ከቢትወደድ ፡ ኢራቅሊስ ፡ በኋላ ፡ እንደራሴ ፡ የሆነ ፡

ደጃዝማች ፡ ኤፍሬም ፡ የበጌምድር ፡ አዝማች ፡

〃 ዮሐንስ ፡
〃 አሞንዮስ ፡
〃 ማሞ ፡ የዳሞት ፡ ገዥ ፡
〃 ዐዕሜ ፡
〃 ወዳጄ ፡
〃 ኮምቤ ፡ በጌምድር ፡ አዝማች ፡

» ተስፋ ፡ ኢየሱስ ፡ የቋራው ፡
" የማነ ፡ እብ ፡

" ለጋሥ ፡
" ርቱዕ ፡ (በሻ ፡ ርቱ) ፡

ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ሲኖዳ ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡
መዠመሪያ ፡ የቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡
በኋላ ፡ የቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ አለቃ ፡
ሆኖ ፡ መልአከ ፡ ገነት ፡ የተባለ ።
ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ድሚጥሮስ ፡ የቅዱስ ፡ ሩፋ
ኤልን ፡ አለቅነት ፡ ጭምር ፡ የያዘ ፡
ብላቴን፡ ጌታ ፡ ማሙዬ ፡ (የባለቤታቸው ፡ ወንድም)፡

» ወሰን ፡ ሰገድ ፡ (የዐፄ ፡ በከፋ ፡ እኅት)፡
» ኩቾ ፡
» ተስፋ ፡ ኢየሱስ ፡ (በኋላ ፡ ቢትወደድ፡
የተባለው ፡

አዛዥ፡ ብንያም ፡ የይባባው ፡
» ወልደ ፡ ትንሣኤ ፡ ወግና ፡ ሥርዓት ፡
የሚያውቀው ፡ ሊቅ ፡
» ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡
" ኢዮሴ ፡
ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ገብረ ፡ ልዑል ፡
ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ማርቆስ ፡
ሊጋባ ፡ ስምዖን ፡ (1)

» ዳዊት ፡

በዥሮንድ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ውስጥ ፡
አዛዥና ፡ ዳዊት ፡ ደጋሚ ፡

» ሕዝቅያስ ፡
» ማሞ ፡ ቆቅ ፡ አዳኝ ፡
» ጳውሎስ ፡
» ወልደ ልዑል ፡
ከንቲባ ፡ ናትናኤል ፡ የደንቢያው ፡

(1) የቀድሞ ፡ ሊጋባነት ፤ ጽሬግ ፡ ማሰሬ ፡ ወይም ፡ ሊቀ ፡ ዐቢያን ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ የሚሠራው ፡ ይመስል ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ቀርቶ ፡ በሊጋባ ፡ ስም ፡ መጠራት መዠመሩ ፡ ይሆንን ።

» ድርመ ፡ ገጭ ፡ አርሴ ፡
» አርሴኒ ፡
» ተስፋ ፡ ኢየሱስ ፡
ፊታውራሪ፡ አግናጥዮስ ፡
» ነጮ ፡
» ገብረ ፡ መድኅን ፡
» ጎራ ፡

ቀኛዝማች ፡ ጴጥሮስ ፡
ግራዝማች ፡ እልፍዮስ ፡ ጡጫ ፡
» ሀላዌ ፡ ክርስቶስ ፡ በኋላ ፡ ፊታውራሪ ፡
ቀጥሎ ፡ የስሜን ፡ ደጃዝማች) ፡
ግራዝማች ፡ ሥሙር ፡

ባላምባራስ ፡ ወልዴ ፡ ጊዮርጊስ ፡
» አይከል ፡ ባልደራስ ፡
ባሻ ፡ አርከለዲስ ፡ (በኋላ ፡ በጌምድር ፡ አዝማችነት ፡ የተሾመ( ፡

» ያዕቆብ ፡
» ወልዴ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቄለኛ ፡
» ምእናም ፡ ቆቅ ፡ አዳኝ ፡
- አደራ ፡ (ከአርከለዲስ ፡ በኋላ ፡ የተሾመ)፡
የሻለቃ ፡ ዕዱግ ፡ ኤፍሬም ፡
» ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
» በትሬ ፡ የቀሃ ፡ ገዥ ፡
» ጎሼ ፡ የቀሃ ፡ ገዥ ፡ ከበትሬ ፡ በኋላ ፡
» ዋልዋጆ ፡ የወሀኒ ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡
የሻለቃ ፡ ዘገብርኤል ፡ የጠጅ ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ (ሊቀ ፡ መያስያን) ፡

» ባልጋዳ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በኋላ ፡ ደጃዝማች ፡ የሆነ ፡

ሴ ቶ ች ።

ወይዘሮ ፡ ማርያማዊት ፡ እናታቸው ፡
እቴጌ ፡ አዋልደ ፡ ንግሥት ፡ ባለቤት ፡ (በቶሎ፡ የሞቱ) ፡
» ምንትዋብ ፡ ባለቤት ፡ የቋረኛ ፡ ኢያሱ ፡ እናት ፡

ዊዘሮ ፡ (ወይዘሮ) ፡ ወለተ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቍባት ፡
፡፡ ወለተ ፡ ሩፋኤል ፡ የንጉሡ ፡ እኅት ፡
፡፡ ሰበኔ ፡
፡፡ ብስለንትያ ፡
፡፡ ወለተ ፡ እስራኤል ፡ .....።

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

## የጃዊ ፡ ሽፍትነት ።

ዐፄ ፡ በካፋ ፡ ከነዚህ ፡ መኳንንትና ፡ ሹማምንት ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ የንጉሥነት ፡ ሥራቸውን ፡ በዠመሩ ፡ ባ፩ ፡ ዓመት ፡ ከ፰ ፡ ወር ፡ ባጼ ፡ ኢያሱ ፡ ጊዜ ፡ ከግቤ ፡ መጥተው ፡ በዐባይ ፡ ዳር ፡ የተቀመጡት ፡ የጃዊ ፡ ጋሎች ፡ (ጠለቃ ፡ ጃዊ) ፡ ሽፍተው ፡ ግብር ፡ ከለከሉ ፡ የሚሉ ፡ ወሬ ፡ መጣላቸው ። ስለዚህ ፡ የጐንደርን ፡ ከተማና ፡ ቤተ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ለቢትወደድ ፡ ኢራቅሊስ ፤ ሀብትና ፡ ገንዘባቸውን ፡ ለበኸሮንድ ፡ ማሞ ፡ እንዲጠብቁ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥተው ፡ ጳጳሱን ፡ አባ ፡ ክርስቶዶሉን ፤ የደብረ ፡ ሊባኖስን ፡ ዕጨጌ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፤ ዐቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ወልደ ፡ ሐዋርያትን ፡ ጸሎትና ፡ ምህላ ፡ እንዲይዙ ፡ አሳስበው ፡ በመኳንንትና ፡ በሠራዊት ፡ ታጅበው ፡ በጐንደር ፡ በወይና ፡ ዐረብ ፡ በምጽራሐ ፡ ማርያም ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ አሪንጎ ፡ ጕዞ ፡ ዠመሩ ። በዚያም ፡ ሲኀዙ ፡ ለዳሞት ፡ ገዥ ፡ ለደጃች ፡ ማሞ ፡ ፱ ፡ ነፍጥ ፡ (ጠመንዣ) ፤ ልከው ፡ በበኩሉ ፡ ጭፍራውን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ጃዊዎች ፡ ሔዶ ፡ እንዲዋጋ ፡ ላኩበት ። ርሳቸውም ፡ (ይበሳ) ፡ በሚባለው ፡ ፈረሳቸው ፡ ሆነው ፡ መኳንንቶቻቸውንም ፡ በፈረስ ፡ በፈረስ ፡ አስከትለው ፡ ከሠራዊቱ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ አሪንጎ ፡ ገቡ ። ሠራዊቱም ፡ ተጠናቆ ፡ እያደር ፡ በአሪንጎ ፡ ገብቶ ፡ ከከተተ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ሠንጋና ፡ ፍሪዳ ፡ አሳርደው ፡ በዚሁ ፡ በአሪንጎ ፡ ለመኳንንትና ፡ ለሠራዊት ፡ ትልቅ ፡ ግብር ፡ አድርገው ፡ ዋሉ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በጥር ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ሠራዊቱ ፡ በያለቃው ፡ ይሰብሰብና ፡ ሰልፉን ፡ አያለሁ ፡ ብለው ፡ በጥሩምባ ፡ ዐዋጅ ፡ አናገሩ ። ሠራዊቱም ፡ ከተሰበሰበ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ተሰበሰበበት ፡ ሥፍራ ፡ ሄደው ፡ በፈረሳቸው ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ የፈረሰኛውንም ፡ የእግረኛውንም ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ እየዞሩ ፡ ተመለከቱ (1) ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግራዝማች ፡ ህላዌ ፡ ክርስቶስ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሆኖ ፡ በፊት ፡ ለፊት ፡ ቀድሞ ፡ እንዲሄድ ፡ ታዘዘ ፤ ርሳቸውም ፡ ከአሪንጎ ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ ተነ

(1) እዚህ ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ ጸሓፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ሲኖዳ ፡ በካፋ ፡ በፈረስ ፡ ሆነው ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ሲመለከቱ ፡ የሰማይ ፡ መልአክ ፡ እንጂ ፡ ሥጋ ፡ የለበስ ፡ ሰው ፡ አይመስሉም ፡ ነበር ፡ ይላል ።
(2) የጃዊ ፡ ባላባቶችና ፡ አዝማቾች ፡ ይሆናሉ ።

ሥተው ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ሊቀ ፡ መኳስ  ገብረ ፡ ልዑል ፡ በፊት ፡ የቀረው ፡ ሠራዊት ፡ ከኋላ ፡ ሆኖ ፡ እያጀባቸው ፡ ዝማሒ ፡ ከሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ደርሰው ፡ ብዙ ፡ ገራ ፡ እባሻ ፡ ያሰቆብ ፡ ቤት ፡ አደሩ ። ከዚያ ፡ በማግሥቱ ፡ ተነሥተው ፡ በገንታ ፤ በአንዳቤት ፡ አድርገው ፡ ሲጓዙ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ግራዝማች ፡ እልፍዮስ ፤ ባሻ ፡ አርከለዲስ ፤ ቄለኛ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ነበሩ ። በኋላም ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማሙዬ ፤ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ገብረ ፡ ልዑል ፡ ሊጋባ ፡ ስምዖን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀርተው ፡ የነበሩት ፡ በዚህ ፡ ጊዜ፡ደርሰው ፡ የንጉሡ ፡ አጀብ ፡ በረከተ ። እንደዚህ፡ ሆኖ ፡ ጕዟቸውን ፡ ወደፊት ፡ ቀጥለው ፡ የዐባይን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግረው ፡ አጋም ፡ ውሃ ፡ አደሩ ። ከዚያም ፡ ተነሥተው ፡ ሲሄዱ ፡ በመንገድ ፡ የቤልማና ፡ የጋዴሳ ፡ የሴንጫ ፡ የጋላ ፡ ወታደሮች ፡ ሆ ፡ እያሉና ፡ እየዘፈኑ ፡ ንጉሡን ፡ ለመቀበል ፡ መጡ ። የነርሱም ፡ አቡሊዳስ ፡ የሚባለው ፡ አለቃቸው ፡ የግስላ ፡ ለምድ ፡ ለብሶ ፡ በቀይ ፡ ፈረሱ ፡ ተቀምጦ ፡ በጭፍሮቹ ፡ መካከል ፡ አምሮ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። እነዚህም ፡ ከነአለቃቸው ፡ ንጉሡን ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፡ ከተገናኙ ፡ በኋላ ፡ ከሠራዊት ፡ ተደባልቀው ፡ ጕዘው ፡ ቀጠለና ፡ ደብረ ፡ ጾት ፡ ደረሱ ፤ በዚያም ፡ ግብር ፡ አግብተው ፡ ዋሉ ። ከዚያም ፡ ተነሥተው ፡ ኬዋንዳ ፡ ደረሱ ። በዚህ ፡ ሥፍራ ፡ ሳሉ ፡ ከሸፈቱት ፤ ከጃዊ ፤ ወገኖች ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ዐርብ ፡ ለት ፡ መጥተው ፡ ከንጉሡ ፡ ተገናኙና ፡ በቀሩት ፡ የጃዊ ፡ ነገዶች ፡ ስም ፡ እንደዚህ ፡ ሲሉ ፡ አመለከቱ ። «ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ እኛ ፡ የርስዎና ፡ ያባትዎ ፡ ባሮች ፡ ነን ፡ አጥፍተንም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጥፋት ፡ ከኛ ፡ ምሕረት ፡ ከርስዎ ፡ ነውና ፡ ይማሩን» ።

ንጉሡም ፡ ይኽን ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ ደግነው ፡ ምሬያችኋለሁ ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሮጌንና ፡ ነጮ ፡ እምዬን ፡ (2) አምጡ ፤ «እነሱን ፡ እስከ ፡ ረቡዕ ፡ ድረስ ፡ እኔ ፡ አለሁበት ፡ ሳታመጡ ፡ የቀራችሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ ሳያመልጠኝ ፡ በሞት ፡ ቀጥቼ ፡ ሥጋውን ፡ ለሰማይ ፡ አሞራ ፡ ነው ፡ የምሰጠው» ፡ ሲሉ ፡ አስፈራርተውና ፡ አስጠንቅቀው ፡ ለቀቋቸው ። ንጉሡም ፡ ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ ቤአባ ፡ ጌራ ፡ በኩል ፡ ዋንዳ ፡ ደረሱ ። እዚህም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ የዚህን ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ ከብቱንም ፡ እህሉንም ፡ ወታደር ፡ እንዳይዘርፍ ፡ በዋጅ ፡ አስጠነቀቁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ዐዋጁን ፡ ጥሰው ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ መዝረፍ ፡ ዠመሩ ፤ እነዚህም ፡ ተይዘው ፡ እንጉሡ ፡ ፊት ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ ዦራቸው ፡ በሰይፍ ፡ እንዲቈረጥ ፡ ንጉሡ ፡ ፈርደው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ሲኖዳ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ቀርበ ፡ አማልዶ ፡ አስማራቸው ።

እነሮጌን ፡ ሊያመጡ ፡ የሄዱት ፡ የጃዊ ፡ መልክተኞች ፤ በተባለው ፡ ቀን ፡ ሳይመጡ ፡ ስለ ፡ ቀሩ ፡ ንጉሡ ፡ እነደጃዝማች ፡ ተስፋ ፡ ኢየሱስ ፡ እነደጃዝማች ፡ ማሞ ፤ እነአዛዥ ፡ ብንያም ፤ እነፊታውራሪ ፡ አግናጥዮስ ፡ ወደፊት ፡ ሄደው ፡ በዳሞትና ፡ በአገው ፡ በሊበንና ፡ በባሶ ፡ የሸፈቱትን ፡ ጋሎችና ፡ ጃዊዎች ፡ እንዲዋጉ ፡ ከብታቸውንም ፡ እኽላቸውንም ፡ እንዲዘርፉ ፡ አዘዟቸው ፡ ንጉሡም ፡ ከኋላ ፡ እየተከተሉ ፡ ጃዊን ፡ ይፈልጉ ፡ ዠመር ። ነገር ፡ ግን ፡ ጃዊ ፡ ቤተ ፡ ሰቡንና ፡ የቻለ

ውን ፡ ያኽል ፡ ከብቱን ፡ ዕቃውንና ፡ እኽሉን ፡ እየያዘ ፡ አገሩንና ፡ ቤቱን ፡ እየተወ ፡ በየደኑ ፡ በየተራራው ፡ እየወጣ ፡ ተደበቀ ። የጃዊ ፡ ሰዎች ፡ ከንጉሡና ፡ ከወታደሩ ፡ አደጋ ፡ ለማምለጥ ፡ ሲሉ ፡ በየተሸሸጉበት ፡ በየጫካው ፡ ሳሉ ፡ የዱር ፡ አውሬና ፡ ተንቀሳቃሹ ፡ እንስሳ ፡ እየነከሰ ፡ አደጋና ፡ ችግር ፡ አበረከተባቸው ፤ የያዙትም ፡ እኽል ፡ አለቀ ። በቤታቸው ፡ የቀረውን ፡ እኽልና ፡ በአዝመራ ፡ ላይ ፡ ያለውንም ፡ ሰብል ፡ የንጉሡ ፡ ወታደር ፡ እየበላ ፡ ለፈረስና ፡ ለበቅሎውም ፡ እያበላ ፡ ጨረሰው ። ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ የተነሣ ፡ የጃዊ ፡ ሕዝብ ፡ በጣም ፡ ተቸግረው ፡ የሚያደርጉት ፡ አጡ ። በመጨረሻ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጥተው ፡ ምሕረት ፡ ከመለመን ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መዳኛ ፡ እንደሌላቸው ፡ ተመካከረው ፡ ተረዱና ፡ ባላባቶቹና ፡ እነዚያ ፡ በፊት ፡ ሳይመጡ ፡ የቀሩት ፡ ተመርጠው ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጡ ። በተገናኙም ፡ ጊዜ ፡ እያለቀሱና ፡ እያስተዛዘኑ ፡ በራሳቸውና ፡ በቀሩት ፡ ስም ፡ «ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ አጥፍተናል ፤ በድለናል ፤ ይማሩን ፤ ቍጣዎን ከላያችን ፡ ይመልሱ ፤ ለዘለዓለምም ፡ አያጥፉን ? ከአረማውያን ፡ አገዛዝ ፡ አውጥተው ፡ ለጥምቀትና ፡ ለቍርባን ፡ ያብቁን ፤ ያባትዎ ፡ የአድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፡ ባሮች ፡ አይደለንምን ? እርስዎስ ፡ ገና ፡ ጥርስዎን ፡ ሳይነቅሉ ፡ ካባትዎ ፡ ጋራ ፡ ያመጡን ፡ አይደሉምን» ፡ ሲሉ ፡ አመለከቱ ። በንጉሡ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ያሉት ፡ መኳንንትና ፡ ሊቃውንትም ፡ ተነሥተው ፡ «ሰው ፡ ሆኖ ፡ ከተፈጠረ ፡ ምንጊዜም ፡ ጥፋተኛ ፡ ነው ። እርስዎ ፡ ግን ፡ እንዳባትዎ ፡ መሐሪ ፡ ነዎትና ፤ እነዚህን ፡ ጥፋተኞች ፡ አይበቀሏቸውም» ፡ ብለው ፡ አማለዱ ።

ንጉሥ ፡ ዐፄ ፡ በካፋ ፡ የጃዊን ፡ መልእክተኞች ፡ ልመና ፡ የመኳንንቱንም ፡ ምልጃ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ልባቸው ፡ አዘነ ። ቍጣቸውም ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ ተመልሶ ፡ ምሬያችኋለሁ ፡ አሏቸው ። ከነዚህም ፡ መካከል ፡ ገሚሶቹ ፡ ተመልሰው ፡ ለጃዊ ፡ ሕዝቦች ፡ በተናገሩ ፡ ጊዜ ፡ የጃዊ ፡ ሕዝብ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ አደረገ ። በዚህ ፡ የምሕረት ፡ ቃል ፡ ሁሉም ፡ በልቡ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ በተራራ ፡ በጫካ ፡ ከነቤተ ፡ ሰቡ ፡ ከነከብቱ ፡ የተደበቀው ፡ ሁሉ ፡ ወደየቤቱ ፡ ተመልሶ ፡ ደንበኛና ፡ ሰላማዊ ፡ ሥራውን ፡ ይቀጥል ፡ ጀመር ።

ንጉሡም ፡ ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ በጐድላ ፡ በኩል ፡ አልፈው ፡ ደልማ ፡ ገቡ ። በዚያም ፡ ሳሉ ፡ በይባባ ፡ በኩል ፡ ወይም ፡ በአሬንጎ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ መመለስ ፡ እንደሚሻል ፡ ከተከተሏቸው ፡ መኳንንት ፡ ከነአዛዥ ፡ ብንያም ፡ ከነግራዝማች ፡ ህላዌ ፡ ክርስቶስ ፡ ከነበዥሮንድ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከነባሻ ፡ አርከሌዲስ ፤ ከነደጃዝማች ፡ ዮሐንስ ፡ ከነደጃዝማች ፡ አሞንዮስ ፡ ጋራ ፡ ተማከሩ ። ግማሾቹ ፡ በአሬንጎ ፡ በኩል ፡ መሄድ ፡ ይሻላል ፡ ሲሉ ፡ አብዛኞቹ ፡ በይባባ ፡ በኩል ፡ መሄድ ፡ ይሻላል ፡ ስላሉ ፡ በዚሁ ፡ ተቈረጠና ፡ ከደልማ ፡ ተነሥተው ፡ በጐዴብ ፤ በዳንጉሌ ፡ በከር ፡ ነዋሪ ፡ አድርገው ፡ እግረ ፡ መንገዳቸውንም ፡ ያደጉበትን ፡ የናታቸውን ፡ አገር ፡ ጺማን ፡ ጐብኝተው ፡ ይባባ ፡ ገቡ ። በየመንገዳቸውም ፡ ለባላባትና ፡ ላገለገሉ ፡ ሰዎች ፡ ስጦታና ፡ ሽልማት ፡ እያደረጉ ፡ አልፈው ፡ በጀፍጃፉ ፡ በሦድ ፡ ገበያ ፤ በኰሸሽላ ፡ በኩል ፡ አድርገው ፡ በወጡ ፡ በ፱ ፡ ወር ፡ ከሦር ፡ ቀን ፡ ተመልሰው ፡ መጋቢት ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ሺሕ ፡ ፯፻፲፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እዋና ፡ ከተማቸው ፡ ጐንደር ፡ ገቡ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፱ ።

### የወይዘሮ ፡ ማርያማዊት ፡ ዕረፍት ፤–የወይዘሮ ፡ አዋልደ ፡ ንግሥትና ፡ የንጉሡ ፡ ጋብቻ ፤–ሹም ፡ ሽር ።

ዐፄ ፡ በካፋ ፡ ከጃዊ ፡ ጦርነት ፡ ጐንደር ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ የሠሩት ፡ ሥራ ፡ በታሪክ ፡ ነገሥታቸው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ አንዳንድ ፡ ጥቃቅን ፡ ሥራ ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

፩ኛ ፤ ውላጆችና ፡ ከኒሳዎች ፡ የሚባሉ ፡ የልፍኝና የወታደር ፡ ክፍሎች ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፤ ከከተማም ፡ ውጭ ፡ እየወጡ ፡ ልጃ ፡ ገረድ ፡ እያበላሹ ፡ የሰው ፡ ሚስት ፡ እያማገጡ ፡ አገር ፡ እየዘረፉ ፡ በነርሱ ፡ ምክንያት ፡ አገር ፡ ታውኮ ፡ ነበር ። እንዳይገቡም ፡ ከተከለከሉ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ገብተው ፡ አገር ፡ ዘርፈው ፡ ብዙ ፡ የዐመፅና ፡ የእብሪት ፡ ሥራ ፡ መሥራታቸው ፡ ስለ ፡ ታወቀ ንጉሡ ፡ ላሔን ፡ ማሞን ፡ ጠንቀኛ ፡ የተባለውን ፡ የጦር ፡ ጭፍራውን ፡ ይዞ ፡ እንዲወጋቸው ፡ አዘዙ ። እርሱንም ፡ አዛዥ ፡ ብንያም ፡ የኢልማና ፡ ዴንሳን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ እንዲያግዘው ፡ ተደረገና ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ አገር ፡ ያበጡትን ፡ እነዚህን ፡ ውላጆች ፡ ወግተው ፡ ግማሾቹን ፡ ገደሏቸው ። የቀሩትንም ፡ እያሰሩ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አመጧቸውና ፡ እስራት ፡ አስፈረዱባቸው ።

፪ኛ ፡ በሐምሌ ፡ ወር ፡ ከጦር ፡ አለቆቹ ፡ አንዱ ፡ በሻ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቋለኛ ፡ ሞቶ ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴ ፡ ተቀበረ ። በዚሁ ፡ ወር ፡ በሻ ፡ አርከለዲስ ፡ ተሽሮ ፡ የርሱ ፡ ሹመት ፡ ለበሻ ፡ አደራ ፡ ተሰጠ ። ለአርከለዲስም በኋላ ፡ የበጌምድር ፡ አዝማችነት ፡ ተሰጠው ። በነሐሴ ፡ ወር ፡ ንጉሡ ፡ ከሕዝብ ፡ ተለይተው ፡ ቀኖና ፡ ይዘው ፡ እስከ ፡ ፍልስታ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ቈዩ ።

፫ኛ ፡ በ፳፫ ፡ ነሐሴ ፡ የሚወዷቸው ፡ እናታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ማርያማዊት ፡ ሞተው ፡ በታላቅ ፡ ኀዘንና ፡ ፍታት ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴ ፡ ተቀበሩ ። ዐፄ ፡ በካፋም ፡ ስለ ናታቸው ፡ ሞት ፡ እስከ ፡ ዓርብ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ልብሳቸውን ፡ ከል ፡ አስነክረው ፡ በብርጊዳ ፡ ደሴት ፡ ሲያዝኑ ፡ ሲያለቅሱ ፡ ሰነበቱ ። ከዚያም ፡ ተመልሰው ፡ እንደ ፡ ሲኖዳ ፡ አጻጻፍ ፡ ለማንም ፡ ለሞቱ ፡ ነገሥታት ፡ ያልተደረገ ፡ ተዝካር ፡ ደግሰው ፡ ዓርባቸውን ፡ አወጡላቸው ።

የናታቸው ፡ ተዝካር ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ጸሐፌ ትእዛዝ ፡ ሲኖዳ ፡ ለዚሁ ፡ ኀዘን ፡ ማስረሻ ፡ የሚሆን ፤ «ድርሰተ ፡ መርስዔ ፡ ኀዘን„ ፡ የሚባል ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፎ ፡ ስላበረከተላቸው ፡ የወርቅ ፡ አንባር ፡ (አውቃፊ ፡ ወርቅ) ፡ ሸለሙት ።

፬ኛ ፤ ቄስ ፡ ዐዒ ፡ ቀውስጦስ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ በጥቅምት ፡ ወር ፡ መከከል ፡ ላይ ፡ የመኰናው ፡ አባ ፡ ዘወልደ ፡ ማርያም ፡ ሊቃውንትና ፡ ካህናት ፡ መሳፍንትና መኳንንት ፡ በሉበት ፡ ዐዒ ፡ በከፋ ፡ መጽሐፈ ፡ ተክሊል ፡ ተነበ ፡ ደንበኛ፡ የጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡ ተፈጽሞ ፡ ወይዘሮ ፡ አዋልደ ፡ ንግሥትን ፡ አገቡ ።

ንጉሡና ፡ ንግሥቲቱም ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ የሠርግ ፡ ልብሳቸውን ፡ ለብሰው ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፡ ንጉሡ ፡ የእቴጌነቱን ፡ አክሊል ፡ በአዋልደ ፡ ንግሥት ፡ ላይ፡ ማን ፡ ያስቀምጥ ? ብለው ፣ ሊቃውንቱን ፡ ጠየቁ ። ሊቃውንቱም ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ የዕጨጌውን ፡ የሹመት ፡ አክሊል ፡ ነገሥታቱ ፡ ይደፉላቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፤ አሁንም ፡ ለእቴጌዪቱ ፡ አክሊሉን ፡ እርስዎ ፡ ንጉሡ ፡ ይድፉላቸው ፡ ሲሉ ፡ መለሱ ። ስለዚህ ፡ ዐዒ ፡ በከፋ ፡ አክሊሉን ፡ ለሙሽራዪቱ ፡ ደፉላቸው። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እቴጌዪቱ ፡ ከወንበራቸው ፡ ላይ ፡ ተነሥተው ፡ አክሊላቸውን ፡ እንደ ፡ ደፉ ፡ ከኋላና ፡ ከፊት ፡ ጥሩንባና ፡ መለከት ፡ እየተነፋላቸው ፡ ባማረ፡ አጀብ ፡ ወደ ፡ ደንበኛው ፡ የእቴጌ ፡ አዳራሽ ፡ ሄዱ ። በዚያም ፡ ተቀምጠው ፡ ከማታ ፡ ዠምረው ፡ እስከ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ግብር ፡ ሲያበሉ ፡ አደሩ ። ዳሩ ፡ ትክክለኛው ፡ ምክንያት ፡ ሳይታወቅ በዚያኑ ፡ ሌሊት ፡ ታመው ፡ በጽኑ ፡ ደዌ ፡ አደሩና ፡ በማግሥቱ ፡ ጥቅምት ፡ ፴ ቀን ፡ ስላረፉ ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ ድንጋጤና ፡ መገረም ፡ ሆነ ። ርስቸውም ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በንጉሡ ፡ እናት ፡ በወይዘሮ ፡ ማርያማዊት ፡ መቃብር አጠገብ ፡ በክብር ፡ ተቀበሩ ።

፫ኛ ፡ በኅዳር ፡ ወር ፡ ባሻ ፡ አደራ ፡ በጥር ፡ ወር ፡ አዛዥ ፡ አርሴ ፡ ሞተው፡ ባሻ ፡ አደራ ፡ በቀሐ ፡ አዛዥ ፡ አርሴ ፡ በአዘዞ ፡ (ደብረ ፡ ሊባኖስ) ፡ ተቀበሩ ። በዚሁ ፡ በጥር ፡ ወር ፡ መጋቢ ፡ ወልደ ሐዋርያት ፡ የቅዱስ ፡ ሩፋኤልን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እልቅና ፡ ጨምሮ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝነት ፡ ተሾመ ፤ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ፡ ሲኖዳ ፡ በጸሐፌ ፡ ትእዛዝነቱ ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ የቅዱስ ፡ ሩፋኤልን ፡ እልቅና ፡ ትቶ ፡ የቅዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ እልቅና ፡ ተሾመ ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ ደጃች ፡ አምኃየስ ፡ የበጌምድርን ፡ ግዛት ፡ ይዞ ፡ የራስ ፡ ቢትወደድነቱን ፡ ሹመት ፡ ተሾመ። በመጋቢት ፡ ወር ፡ ዕጨጌ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ተሽረው ፡ በርሳቸው ፡ እግር ፡ ዕጨጌ ፡ ዮሐንስ ፡ ተሾሙ ። በዚሁም ፡ ወር ፡ በሹም ፡ ሽረቱ ፡ መከከል ፡ ወይ ዘሮ ፡ ሰበኔና ፡ ወይዘሮ ፡ ብስለንትያ ፡ የሚባሉት ፡ የንጉሡ ፡ እኅቶች ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ኀዘን ፡ ሆነ ።

## ምዕራፍ ፡ ፸ ።

## የራስ ፡ ቢትወደድ ፡ አምኃየስ ፡ ፍጻሜ—የላስቶችና ፡ የብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማሙዬ ፡ ጦርነት ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ሕመምም ፡ ጦርነትም ፡ እየ ተከታተለ ፡ እንደ ፡ ደረሰባቸው ፡ ከታሪካቸው ፡ ላይ ፡ ይነበባል ። ይኸም ፡ ሲሆን፡ በዚሁ ፡ ባዒ ፡ በከፋ ፡ ታሪክ ፡ በመዠመሪያው ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ገለጽ

ነው ፡ በካፋ ፡ በተወለዱ ፡ ጊዜ ፡ «በዘመኑ ፡ ሰላም ፡ ይሆናል ፡ . . . » ብለው ፡ አባታቸው ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ተናገሩ ፡ ሲል ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዙ ፡ የጻፈው ፡ ትንቢታዊ ፡ ቃል ፡ እንዳልተፈጸመ ፡ ይታወቃል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የዚህኑ ፡ የሕመማቸውንና ፡ የጦርነቱን ፡ ሁኔታ ፡ እንመልከት ።

ዐፄ ፡ በካፋ ፡ በበሽታ ፡ እንደ ፡ ወደቁ ፡ ድንገት ፡ እኔ ፡ የሞትኩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዙፋኑን ፡ ለመያዝ ፡ በነጋሢዎቹ ፡ መካከል ፡ ጭቅጭቅ ፡ ሲነሣ ፡ አገር ፡ ይታወካል ፡ ብለው ፡ ራሳቸው ፡ ወንድማቸውን ፡ ዮሐንስን ፡ ለማንገሥ ፡ አስበው ፡ ከወህኒ ፡ አምባ ፡ አስመጡና ፡ ባጠገባቸው ፡ አስቀመጧቸው ። በኋላ ፡ ግን ፡ ሞታቸው ፡ ወደ ፡ ደኅንነት ፡ ስለ ፡ ተመለሰ ፡ ሊነግሡ ፡ መጥተው ፡ የነበሩት ፡ ዮሐንስም ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ አምባቸው ፡ ተመለሱ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ከሕመማቸው ፡ ድነው ፡ ፍጹም ፡ ጤንነት ፡ ካገኙ ፡ በኋላ ፡ ያድማ ፡ ነገር ፡ በላያቸው ፡ እየተከታተለ ፡ ስለ ፡ ደረሰባቸው ፡ ሰላምና ፡ ደስታ ፡ አላገኙም ፡ ነበር ፤ በዚህም ፡ ላይ ፡ ቍባታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ጴጥሮስ ፡ በወሊድ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ኀዘን ፡ በኀዘን ፡ ተደረበባቸው ። ኀዘናቸውንም ፡ ሳይጨርሱ ፡ እኅታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ሩፋኤልና ፡ ልጃቸው ፡ አጼቆ ፡ ሱስንዮስ ፡ ሌሎች ፡ ዐድመኞች ፡ ጨምረው ፡ ሊገድሏቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በዙፋንና ፡ በሥልጣን ፡ የተቀመጠ ፡ ንጉሥ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ግቢና ፡ ውጭ ፡ ያለውን ፡ የሚነግረው ፡ አያጣምና ፡ የነወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ሩፋኤል ፡ ዐድማ ፡ ስለ ፡ ተሰማ ፡ ከዐድመኞቻቸውና ከስሜኑ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ጋራ ፡ ተይዘው ፡ ሁሉም ፡ በወልቃይት ፡ ታሰሩ ።

ቀጥሎም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በራስ ፡ ፋሪስ ፡ ርዳታ ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ ያ፬ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነውና ፡ መንግሥት ፡ አይችልም ፡ ተብሎ ፡ ተመልሶ ፡ የታሠረው ፡ ናዖድ ፡ የሚባለው ፡ ያፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ልጅ ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ በዕድሜ ፡ ስለ ፡ በሰለ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዕድሉን ፡ ለመፈተን ፡ ከወህኒ ፡ አምባ ፡ አምልጦ ፡ ወጣ ።

እንደ ፡ ወጣም ፡ ውስጡን ፡ ከእንደራሴው ፡ ከቢትወደድ ፡ አምኃየስ ፡ ጋራ ፡ ተስማማ ፡ ይባላል ፤ እነሱም ፡ ዐድማቸውን ፡ ጨርሰው ፡ ንጉሡን ፡ ከአልጋ ፡ እናወርዳለን ፡ እያሉ ፡ ሲያስቡ ፡ ሥራቸውን ፡ ከመገርመራቸው ፡ በፊት ፡ ንጉሡ ፡ እነሱን ፡ በመያዝና ፡ በማሰር ፡ ቀደሟቸው ፤ ናዖድም ፡ ተይዞ ፡ እግሩ ፡ ተቈርጦ ፡ ሞተ ፡ ቢትወደድ ፡ አምኃየስ ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ማደሙ ፡ በወሬ ፡ እንጂ ፡ በማስረጃ ፡ ስላልተገለጸ ፡ ከሹመቱ ፡ ተሽሮ ፡ ተጋዘ ፡ እንጂ ፡ አልተገደለም ።

በዚህም ፡ መካከል ፡ ዐፄ ፡ በካፋ ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ አምኃየስን ፡ ይቅርታ ፡ አድርገው ፡ በበጌምድር ፡ ግዛቱ ፡ መልሰው ፡ ሥራውን ፡ በደንብ ፡ መሥራት ፡ ገዞምሮ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ራስ ፡ አምኃየስ ፡ ከቢትወደድ ፡ ቀውስጦስና ፡ ይልቁንም ፡ ከንጉሡ ፡ አማች ፡ ከብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማሙዬ ፡ ጋራ ፡ በግዛትና ፡ በሥልጣን ፡ እየተ

ጣሉ ፡ አልተስማሙም ፡ ነበር ፤ የሦስቱም ፡ ጸብ ፡ ንጉሡንና ፡ የበታች ፡ መኳንንቶች፡ አስቸግሮ ፡ ነበር ። በመጨረሻ ፡ ግን ፡ ንጉሡ ፡ ሦስቱንም ፡ እፊታቸው ፡ ጠርተው ፡ ለኔ ፡ ስትሉ ፡ ታረቁ ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ ለመኗቸው ፡ ከልባቸው ፡ ሳይሆን ፡ የንጉሡን ፡ ቃል ፡ ለማክበር ፡ ብቻ ፡ ይቅር ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ተባብለው ፡ ተሳስመው ፡ ታረቁ ።

፨ ፨ ፨

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ከከተማቸው ፡ አየር ፡ ለመለወጥ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ በወጡበት ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቅያስ ፡ የተባለው ፡ የሚቼ ፡ የዐጼ ፡ ያዕቆብ ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ጐንደር ፡ ገብቶ ፡ ከንጉሡ ፡ ዘበኞች ፡ ጋራ ፡ ተዋጋና ፡ በመጨረሻ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ ተያዘ ። ንጉሡም ፡ ከሄዱበት ፡ ሲመለሱ ፡ እስረኛው ፡ ሕዝያቅስ ፡ ከነተከታዮቹ ፡ እፊታቸው ፡ ቀርቦ ፡ ተፈረደበትና ፡ ሁለት ፡ እጆቹን ፡ ተቈርጦ ፡ ሞተ ፤ ተከታዮቹም ፡ በደባባይ ፡ በጦርና ፡ በሰይፍ ፡ ተደብድበው ፡ ተገደሉ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባለፈው ፡ ያነሣነው ፡ የንጉሡ ፡ ባለሟልና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ የነበረው ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ አምኃየስ ፡ የቀድሞ ፡ ቂሙ፡ እያመረቀዘ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ በሺህ ፡ ፯፻፺፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሸፈተ ። ዋናው ፡ ጠቡም ፡ ከን ጉሡ ፡ ባለቤትና ፡ ከወንድማቸው ፡ ከብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማሙዬ ፡ ጋራ ፡ ነው ። በዚ ህም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሲኖዳ ፡ አጻጻፍ ፡ እንደራሴነት ፡ አንሶት ፡ መንግሥትን ፡ ከበከፋ፡ ቀምቶ ፡ ለመንገሥ ፡ አስቦ ፡ ነበር ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ንጉሡም ፡ በባለቤታቸው ፡ እየ ተመሩ ፡ ራስ ፡ አምኃየስን ፡ ስለ ፡ ተጫኑት ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ሸፈተ ። ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማሙዬም ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ዘበኛ ፡ ይዞ ፡ ሄዶ ፡ ራስ ፡ አምኃየስን ፡ ጦርነት ፡ ገጠመው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ጠንክረው ፡ ስለ ፡ ተዋጉ ፡ ድል፡ አድራጊው ፡ ሳይታወቅ ፡ ጦርነቱ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ጐተተ ፡ ንጉሡ ፡ ራሳቸው፡ በመስከረም ፡ ወር ፡ ከጐንደር ፡ በአሬንጎ ፡ በኩል ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ላስታ ፡ መጡ። ራስ ፡ አምኃየስም ፡ ብያዝም ፡ ሞት ፡ አይቀርልኝም ፡ ብሎ ፡ በላስታ ፡ ተራራ ፡ ላይ፡ እንዳለ ፡ ሊወጉት ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ የሚመጡትን ፡ ፊጃቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ባንድ፡ ወገን ፡ ከሚመጣው ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ እየተዋጋ ፡ ሲያሸንፍ ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ጦር ፡ እየመጣ ፡ በኋላው ፡ እየደረሰ ፡ ስለ ፡ ወጋው ፡ ራስ ፡ አምኃየስና ፡ አሽከሮቹ ፡ እጦርነቱ ፡ ላይ ፡ በዠግንነት ፡ ሲዋጉ ፡ ሞቱ ። ሲኖዳ ፡ ግን ፡ በግዕዙ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ላይ ፡ አምኃየስ ፡ ከጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ ሸሽቶ ፡ ባንዲት ፡ ግብፃዊት፡ ቤት ፡ ተደብቆ ፡ ሳለ ፡ ተወልደ ፡ ሕፃን ፡ የሚባል ፡ ወታደር ፡ አግኝቶ ፡ እንደገደ ለው ፡ ይጽፋል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ አምኃየስ ፡ ከነጭፍራው ፡ ተዋግቶ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የንጉሡ፡ ድንኳን ፡ ተተክሎ ፡ ዙፋናቸውም ፡ ተዘረጋና ፡ ተቀመጡ ። ተዋጊዎች ፡ ወታደሮ ቻቸውም ፡ በብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማሙዬ ፡ መሪነት ፡ ተሰልፈው ፡ ሆ ፡ እያሉና ፡ እየጨ ፈሩ ፡ መጡ ። የራስ ፡ አምኃየስንና ፡ ያባቱን ፡ የቆኒስን ፡ ያሽከሮቹንም ፡ የተቈረጠ ፡ ጭንቅላት ፡ በፊታቸው ፡ አስቀምጠው ፡ ፎከሩላቸውና ፡ የድሉ ፡ በዓል ፡ ተፈጸመ ።

ዐዌ ፡ በካፋም ፡ ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ተመለሱ ። የራስ ፡ አምኃየስ ፡ ሚስት ፡ ወይዘሮ ፡ እንጐሪና ፡ ያሽከሮቹም ፡ ባለቤቶች ፡ በምርኮኛነት ፡ ጐንደር ፡ ከተማ ፡ ከንጉሡ ፡ ጓዝ ፡ ጋራ ፡ ገብተው ፡ ተቀመጡ ።

※ ※ ※

ይህ ፡ ጦርነት ፡ በተደረገ ፡ ባመቱ ፡ ላስቶች ፡ ለጦርነት ፡ ተዘጋጅተዋል ፡ ማለት ፡ ተሰማ ። የላስታው ፡ ባላባት ፡ ጉባላም ፡ የራስ ፡ አምኃየስን ፡ ልጅ ፡ አግብቶ ፡ ውስጡንም ፡ ከራስ ፡ አምኃየስ ፡ ጋራ ፡ አስቀድሞ ፡ ተስማምቶ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በዚህም ፡ ላይ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማሙዬ ፡ ያለ ፡ ትእዛዝ ፡ ከገር ፡ ጋራ ፡ በመዋጋቱ ፡ ትልቅ ፡ ጦርነት ፡ ተቀሰቀሰ ። ስለዚህ ፡ ንጉሡ ፡ ከመድረሳቸው ፡ በፊት ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማሙዬ ፡ የራሱን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ እመኪና ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ከላስቶች ፡ ጋራ ፡ ትልቅ ፡ ጦርነት ፡ ዠመረ ። ላስቶችም ፡ በኃይለኛው ፡ ባላባታቸው ፡ በጉባላ ፡ እየተመሩ ፡ ከብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማሙዬ ፡ ጋራ ፡ ገጥመው ፡ ትልቅ ፡ ጦርነት ፡ ተደረገ ። በጦርነቱም ፡ ጊዜ ፡ ላስቶች ፡ ባገራቸው ፡ መውጫ ፡ መግቢያውን ፡ ያውቁት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ አዝማቹ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማሙዬና ፡ ጥቂት ፡ ወታደሮች ፡ ብቻ ፡ ሲያመልጡ ፡ ብዙዎቹ ፡ የጦር ፡ ሹማምቶች ፡ ከነወታደሮቻቸው ፡ በላስቶች ፡ እየተወጉ ፡ ወደቁ ። ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማሙዬም ፡ ለማምለጥ ፡ የቻለው ፡ የማዕርግ ፡ ልብሱን ፡ አውልቆ ፡ የረኛ ፡ ደበሎ ፡ ለብሶ ፡ ሳይታወቅ ፡ ነው ፡ ይባላል ፡

ንጉሡም ፡ የዚህን ፡ ወሬ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ እመኪና ፡ ሊሄዱ ፡ ተዘጋጁ ፡ የእመኪና ፡ ሥፍራ ፡ ገደልና ፡ ኰረኰንች ፡ ጫካ ፡ በመሆኑ ፡ ለጦርነት ፡ አይመችምና ፡ አይሂዱ ፡ ብለው ፡ ዐዋቂዎቹ ፡ የመከሯቸውን ፡ ምክር ፡ ሳይቀበሉ ፡ ወደዚያው ፡ ተጕዘው ፡ የጉባላን ፡ ጦር ፡ እየወጉ ፡ ወደ ፡ እመኪና ፡ ተጠጉ ።

የንጉሡ ፡ መምጣትም ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ በባላባቶቹ ፡ ዘንድ ፡ ድንጋጤ ፡ ሆነ ፤ ሽማግሌዎቹም ፡ ወደ ፡ ጉባላ ፡ ቀርበው ፡ አማላጅ ፡ ልከኽ ፡ ብትታረቅና ፡ ብትገባ ፡ ይሻላል ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ተዋግተኽ ፡ አትዘልቀውም ፡ ብለው ፡ መከሩት ። እሱም ፡ እንደ ፡ ተመከረ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ምሕረት ፡ ያድርጉልኝና ፡ እንታረቅ ፡ የራስ ፡ አምኃየስንም ፡ ልጅ ፡ (ሚስቱን) ፡ ልላክልዎት ፡ ከአዳል ፡ አገር ፡ ያስመጣኋቸውንም ፡ ሁለት ፡ የሚያማምሩ ፡ ወንበሮች ፡ ልላክ ፤ ግብሬንም ፡ ልገብር ፡ ሲል ፡ ላከ ፤ ንጉሡም ፡ ባለፈው ፡ ጦርነት ፡ ሰዋ[illegible]ው ፡ መድከሙን ፡ ያውቃሉና ፡ ምሕረት ፡ አድርገውለት ፡ በካፋም ፡ እያስገበሩ ፡ ጉባላም ፡ እየገበረ ፡ ሊኖር ፡ በመልክት ፡ ተራረቁ ።

ጉባላም ፡ ታርቆ ፡ በገባ ፡ በመቱ ፡ እልፍዮስ ፡ የሚባለው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በላስታ ፡ ሸፈተ ፤ እሱም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲዋጋ ፡ ኖሮ ፡ በመጨረሻ ፡ ተይዞ ፡ ጐንደር ፡ መጣና ፡ ባደባባይ ፡ ተሰቀለ ።

ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማሙዬም ፡ ፩ኛ ፡ በላስታ ፤ የመዠመሪያውን ፡ ጦርነት ፡ ከንጉሡ ፡ ሳይታዘዝ ፡ በመዠመሩ ፤ ፪ኛም ፡ የጦር ፡ አዝማች ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፤ ሠራዊቱን ፡ አጋፍጦ ፡ የማዕረግ ፡ ልብሱን ፡ አውልቆ ፡ እንደረኛ ፡ ደበሎ ፡ ለብሶ ፡

ከጦርነቱ ፡ ባመለጠበት ፡ ምክንያት ፡ እዚያው ፡ እተደበቀበት ፡ አቡኑ ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ መኳንንቱና ፡ ሊቃውንቱ ፡ ሄደው ፡ አቡነ ፡ ክርስቶዶሉ ፡ ጭምር ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማሙዬን ፡ ፈረዱበትና ፡ ከሹመቱ ፡ ተዋርዶ ፡ ወልቃዬት ፡ ታስሮ ፡ ሲኖር ፡ ባል ታወቀ ፡ አሟሟት ፡ ሞተ ፤ የርሱም ፡ ሹመት ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ተብሎ ፡ ለኩኙ ፡ ተሰጠ ።

እልፍዮስም ፡ ከተሰቀለ ፡ በኋላ ፡ ታርቆ ፡ የገባው ፡ ጉባላ ፡ በዐፄ ፡ ሱስን ዮስ ፡ ጊዜ ፡ ከአዳበ ፡ ዘማርያም ፡ ላይ ፡ ላስቶች ፡ ማርከውት ፡ የነበረውን ፡ የብ ረት ፡ ነጋሪት ፡ መጻሕፍትና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃ ፡ ከራሱም ፡ ብዙ ፡ ሠንጋ ፡ ጨምሮ ፡ ጐንደር ፡ በልጁ ፡ በኩል ፡ ላከ ። በመጨረሻም ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ መጥቶ ፡ ከንጉሡ ፡ ተገናኝ ፤ ንጉሡም ፡ ደስ ፡ እላቸውና ፡ ሽልማት ፡ ሰጥተው ፡ አገሩንም ፡ በደንብ ፡ መርቀው ፡ በደስታ ፡ ሰደዱት ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፸፩ ።

## የቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አከባበር ፤– ሹም ፡ ሽር ፡ – የሲኖዳ ፡ ሞት ፤– የደጃዝማች ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መከሰስ ።

የቀደሙት ፡ ነገሥታትና ፡ እቴጌዎች ፡ አንዳንድ ፡ መኳንንቶች ፡ በሥራቸው ፡ ላይ ፡ በዘመናቸው ፡ ከልብ ፡ ለሚወዱት ፡ ስለታችንን ፡ ያደርሳል ፡ ለሚሉት ፡ ታቦት ፡ እያስቀረጹ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እያሰነፁ ፡ ከመንግሥት ፡ ወይም ፡ ከግል ፡ ርስታ ቸው ፡ ለካህናትና ፡ ለቀሳውስት ፡ ርስት ፡ እየሰጡ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ታቦት ፡ እየተከሉ ፡ መደበር ፡ ልማዳቸው ፡ ነው ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ለምሳሌ ።

(ሀ) ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ተድባበ ፡ ማርያምን ፡ ባማራ ፡ ሣይንት ፤ ታቦተ ፡ ገላውዴዎስን ፡ (መካነ ፡ ሰማዕትን) በምድረ ፡ ደብር ።

(ለ) እቴጌ ፡ ማርያም ፡ ሥና ፡ የዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ባለቤት ፡ በግራርያ ፡ ማኅደረ ፡ ማርያምን ።

(ሐ) ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴን ፡ (ጐንደር) ፡

(መ) ዐፄ ፡ ዮስጦስ ፡ ልደታ ፡ ለማርያምን ፡ (ጐንደር) ።

(ሠ) ዐፄ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ደብረ ፡ መዊዕን ፡ ያሠሩት ፡ ፪ኛ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

እንደዚሁም ፡ ዐፄ ፡ በካፋ ፡ በዘመን ፡ መንግሥታቸው ፡ ለሚወዱት ፡ ለቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ ትልቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠርተው ፡ የታቦቱ ፡ አገባብ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ በታላቅ ፡ በዓል ፡ ተከበረ ። በተከበረበትም ፡ ቀን ፡ ጸሓፌ ፡ ትእዛዛቸው ፡ ሲኖዳ ፡ በቅኔ ፡ ማኅሌት ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ ሥላሴ ፡ ቅኔ ፡ ተቀኘ ።

ሩፋኤል ፡ በቤትከ ፡

ኅብስተ ፡ ርኁባን ፡ አመ ፡ በላዕከ ፡
ኢተረክበ ፡ ኀይል ፡ ዘይቤ ፡ እምአብያጺከ ፡ ኀይላት ፡

ሐሜት ፡ ዝንቱ ፡ ወዝንቱ ፡ ኅፍረት ፡
እመሰ ፡ ላዕሌከ ፡ ኢሀሎ ፡ እንተ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ሐሜት ፡፡
እንጻረ ፡ በክፉ ፡ በኵረ ፡ ነገሥት ፡
ድግምኬ ፡ በሊዐ ፡ ኅብስት ፡
ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ቤትከ ፡ እምርት ፡፡

የቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ በዓል ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ለሊቃውንት ፡ ለካህናት ፡ ለመኳንንትና ፡ ለወታደር ፡ ባለቀየው ፡ በጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ድሜጥሮስ ፡ ቤት ፡ ማግናቸውም ፡ ምግብና ፡ መጠጥ ፡ ከንጉሡ ፡ ቤት ፡ ተግዞ ፡ ትልቅ ፡ ግብር ፡ ተደረገ ፡፡

※ ※ ※

በሁለተኛው ፡ ዓመት ፤ ዐፄ ፡ በካፋ ፡ በግንቦት ፡ ወር ፡ መገርመሪያ ፡ ላይ ፡ የልደታን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጥሩን ፡ ማሳደሳቸውና ፡ ባጠገቡም ፡ ለራሳቸው ፡ እልፍኝ ፡ ማሠራታቸው ፡ ተጽፏል ፡፡ እንደዚሁም ፡ ለከንቲባ ፡ ናትናኤል ፡ የውስጥ ፡ አዛዥነት ፤ ለባላምበራስ ፡ ህላዌ ፡ ክርስቶስ ፡ በጌምድር ፡ አዝማችነት ፤ ለበልጋዳ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ስሜን ፡ አጋፋሪነት ፤ ለሊቀ ፡ መኳስ ፡ ማርቆስና ፡ ለኒቆላዎስ ፡ የጠንቀኛ ፡ (ያንድ ፡ ክፍል ፡ ወታደር) ፡ ሻለቅነት ፤ ለሊቀ ፡ መዘምራን ፡ ማሞ ፡ የደብረ ፡ ብርሃን ፡ሥላሴን ፡ እልቅና ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ ተብሎ ፤ ለመልአከ ፡ ብርሃናት ፡ ፀሐየ ፡ ልዳ ፡ የልደታን ፡ አልቅና ፤ ለምእናም ፡ የቆቅ ፡ አዳኝነትን ፡ ሹመት ፡ ሰጡ ፡፡

※ ※ ※

በዚህ ፡ መካከል ፡ ደግሞ ፡ ደጋግመን ፡ በጸሐፌ ፡ ትእዛዝነቱና ፡ በታሪክ ፡ ጸሐፊነቱ ፡ ስሙን ፡ ያነሣነው ፡ አዛዥ ፡ ሲኖዳ ፡ በነሐሴ ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ትልቅ ፡ ኀዘን ፡ ወደቀባቸው ፡፡ አዛዥ ፡ ሲኖዳ ፡ የሚባለው ፡ ለዐፄ ፡ በካፋ ፡ ባለሟል ፡ ሆኖ ፡ በብዙ ፡ ረገድ ፡ ያገለግላቸው ፡ ነበር ፡፡

(ሀ) እንዳዛገሮች ፡ ተቀምጦ ፡ በጉባኤ ይፈርዳል ፡፡

(ለ) ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ሆኖ ፡ ቃል ፡ ያስተላልፋል ፡፡

(ሐ) በታሪክ ፡ ጸሐፌነት ፡ ተመስግኖ ፡ የራሳቸውን ፡ የዐፄ ፡ በካፋን ፡ ታሪክ ፡ በጊቤ ፡ በጃዊና ፡ በላስቶች ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፡ ጦርነት ፡ ሁሉ ፡ ከጻፈ ፡ በኋላ ፡ ከአባታቸው ፡ ከዐፄ ፡ ኢያሱና ፡ ከያታቸው ፡ ከቀዳማዊ ፡ ዮሐንስ ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ ሰብስቦ ፡ ያደራጀ ፡ እርሱ ፡ ነው ፡፡

(መ) እንደ ፡ ሊቀ ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ እየተባለ ፡ የትልቁን ፡ ደብር ፡ የደብረ ብርሃን ፡ ሥላሴን ፤ በኋላም ፡ የቅዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ እልቅና ፡ ተሾሞ ፡ በሌላው ፡ አገልግሎቱ ፡ ላይ ፡ በቅኔ ፡ ማኅሌት ፡ የሚቀኘውን ፡ ቅኔ ፡ ባለፈው ፡ አንብበናል ፡፡

(ሠ) ለንጉሡ ፡ ልጆች ፡ መምህር ፡ ሆኖ ፡ መጻሕፍት ፡ ያስተምራል ፡፡

(ረ) ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ ድርሰተ ፡ መርስዔ ፡ ኅዘን ፤ የሰዋስው ፡ መጽሐፍ ፡

መዝሙረ ፡ ሐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ሰማዕት ፡ የሚባሉትን ፡ ድርሰቶች ፡ መጻፉን ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ይገልጻልና ፡ የሲኖዳ ፡ መሞት ፤ ንጉሡን ፡ ዐፄ ፡ በከፋን ፡ ቡብዙ ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ጐዳቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ከግብጽ ፡ የመጡ ፡ ድሜጥሮስና ፡ ጊዮርጊስ ፡ የሚ ባሉ ፡ ጥበበኞች ፡ እሳት ፡ ውላጅና ፡ አንጣጭ ፡ ማሞ ፡ ከሚባሉት ፡ ያገር ፡ ተወ ላጅ ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ አዋቂዎች ፡ ጋራ ፡ እየተመካከሩ ፡ በብርጊዳ ፡ የሠሩት ፡ የመርከብ ፡ ሥራ ፡ አልቋል ፡ ማለትን ፡ ሰሙ ፤ ስለዚህ ፡ የመርከቡን ፡ ሥራ ፡ ለማየት ፡ መኳንንቶቻቸውን ፡ አስከትለው ፡ ወደዚሁ ፡ ወደ ፡ ብርጊዳ ፡ ሄዱ ። በዚያም ፡ ሄደው ፡ የመርከቡን ፡ ሥራ ፡ በሠሪዎቹ ፡ አስረጅነት ፡ ውጭውንም ፡ ግቢውንም ፡ ዙሪያውንም ፡ አይተው ፡ ተደነቁ ። ከዚያም ፡ መርከቡ ፡ ወደ ፡ ጣና ፡ ባሕር ፡ ተላከና ፡ ንጉሡም ፡ ተመልሰው ፡ ጐንደር ፡ ገቡ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ጐንደር ፡ ሳሉ ፡ ባሻ ፡ ርቱዕ ፡ ደጃዝማች ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ስሜን ፡ አጋፋሪ ፤ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ የትግሬ ፡ ገዥ ፡ (ባልጋዳ) ፡ የነበረውን ፡ የውስጥ ፡ ብላቴናውን ፡ ርእሰ ፡ ቃልን ፡ በገንዘብ ፡ ገዝተኽ ፡ ንጉሡን፡ ሥራይ ፡ ልታበላና ፡ አንተ ፡ ለመንገሥ ፡ አስበኻል ፡ ሲል ፡ እንጉሡ ፡ ላይ ፡ ከሰ ሰው ። ንጉሡም ፡ ሁለቱን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ አቁመው ፡ የከሳሹን ፡ ንግግር ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ ተከሳሹን ፡ ደጃዝማች ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ እውነት ፡ ነውን ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ፡ እርሱም ፡ እንኳን ፡ የውስጥ ፡ ብላቴናን ፡ በገንዘብ ፡ ገዝቼ ፡ በእጅ ፡ አዞር ፡ ንጉሡን ፡ ጌታዬን ፡ ለማስገደል ፡ መነጋገር ፡ ይቅርና ፡ ይህ ፡ ርእሰ ፡ ቃል ፡ የተባለው ፡ የውስጥ ፡ ብላቴና ፡ እኔን ፡ ዐውቀዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ከመሰከረ ፡ ንጉሡ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ይፍረዱብኝ ፡ ሲል፡አመለከተ ። በዚሁም ፡ ከሳሹና፡ተከሳሹ፡ብዙ ፡ ንግግር ፡ ሲመላለሱ ፤ ሁከት ፡ አበዙ ፤ ስለዚህ ፡ ንጉሡ ፡ ቢትወደድ ፡ ተስፋ ፡ ኢየሱስን ፡ ጠርተው ፡ በርሱ ፡ ዳኝነት ፡ ተነጋገሩ ፡ ብለው ፡ አዘዟቸውና ፡ ቢትወደዱ ፡ ሁለቱን ፡ ባላጋሮች፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ ችሎት ፡ ወስዶ ፡ ማነጋገር ፡ ዠመረ ። በዚያም ፡ የውስጥ ፡ ብላቴ ናው ፡ ቀርቦ ፡ ከተጠየቀ ፡ በኋላ ፡ ዐዎን ፡ አውቀዋለሁ ፡ ላፋ ፡ ጥቍር ፡ እጀ ፡ ጠባ ብና ፡ ሱሪ ፡ ዝናርም ፡ እሰጥኻለሁ ፡ ብሎኝ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ እሱም ፡ አልሰጠኝ ፡ እኔም ፡ አልተቀበልሁ ፡ ሲል ፡ መሰከረ ። በርሱ ፡ ላይ ፡ ባሻ ፡ ርቱዕ ፡ ሌሎች ፡ ፲፩ ፡ ምስክሮች ፡ ቈጥሮ ፡ ነበርና ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፤ «ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የአድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፡ ልጅ ፡ ነኝና ፡ እነግሣለሁ ፡ ማለቱን ፡ ቀድሞም ፡ በላስታ ፡ ወሬኛን በንጉሥ ፡ ዮስጦስ ፡ ዘመን ፡ አንግሦ ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ቢትወደድ ፡ መባሉን ፡ በኋ ላም ፡ ወሬኛን ፡ በጐንደር ፡ አንግሼ ፡ እኔም ፡ በትግሬ ፡ እነግሣለሁ ፡ እያለ ፡ ብዙ ፡ ጥፋት ፡ ማጥፋቱን» ፡ ዕወቁልኝ ፡ አላቸው ። ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ባታውቁቡኝ ፡ ብሎ ፡ ከመለሰ ፡ በኋላ ፡ ምስክሮቹ ፡ አንዳንድ ፡ ጥፋት ፡ ቀድሞ ፡ ማጥፋቱን ፡ እናውቃለን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ሲባል ፡ በወሬ ፡ እንሰማለን ፡ እንጂ ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ያፄ ፡ ኢያሱ ፡ ልጅ ፡ ነኝና ፡ እነግሣለሁ ፡ ማለ ቱን ፡ ከፉ ፡ አልሰማንም ፡ ሲሉ ፡ መሰከሩ ፡ ደግሞ ፡ እንደገና ፡ ፭ ፡ መነኰሴ ፡ ከጉ

ባኤው ፡ ተንሥተው ፡ «እናቴ ፡ ከንጉሥ ፡ ወልጄዋለሁ ፡ ብላ ፡ ነግራኛለች ፡ ርሱም ፡ ራሱ ፡ ዐመፀኛ ፡ መሆኑን ፡ ዐውቃለሁ» ፡ ሲሉ ፡ በተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መሰከሩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ሳይሰጥ ፡ ጊዜው ፡ ስለመሸ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ የቢትወደዱ ፡ ዘበኞች ፡ አስረው ፡ ወሰዱትና ፡ ነገሩ ፡ አደረ ።

በማግሥቱ ፡ ደጃዝማች ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እንደገና ፡ እችሎት ፡ ቀርበ ፡ በመጀመሪያ ፡ በቢትወደድ ፡ ተስፉ ፡ ኢየሱስ ፡ ችሎትም ፡ ላይ ፡ "ብላቴናውን ፡ እን ኳን ፡ ላባብል ፡ ዐውቀዋለሁ ፡ ሲል ፡ የመሰከረብኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሞት ፍርድ ፡ ይፈረድብኝ» ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ነበረና ፡ ብላቴናውም ፡ ቀርበ ፡ ስለ፡ መሰከረበት፡ «ይሙት ፡ በቃ» ፡ ተፈርዶበት ፡ ነበር ። በኋላም ፡ እንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዐዌ ፡ በከፉ ፡ ችሎት ፡ ቀርበ ፡ ግማሾቹ ፡ መኳንንትና ፡ ሊቃውንት ፡ ባለፍትሐ ፡ ነገሥቶችም ፡ የሞቱን ፡ ፍርድ ፡ አጽንተው ፡ ነበር ፤ የቀሩት ፡ መኳንንትና ፡ ዳኞች ፡ ደግሞ ፡ እነዚያ ፡ ፲፩ ፡ ምስክሮች ፡ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ነኝና ፡ እነግሣለሁ ፡ ማለቱን ፡ በወሬ ፡ ሰማን ፡ ስላሉ ፡ በወሬ ፡ የሰሙትን ፡ መሠረት ፡ አድርገን ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ አንፈርድበትም ። በዚህም ፡ ላይ ፡ ደጃዝማች ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በትግሬ ፡ ያልተጣላሁትና ፡ ደም ፡ ያልተቃባሁት ፡ አይገኝምና ፤ እነዚህም ፡ በወሬ ፡ ሰምተናል ፡ ያሉት ፡ ምስክሮች ፡ ከጠላቶቼ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡ ስላለ ፡ ባይሆን ፡ ይታሰራል ፡ እንጂ ፡ አይሞትም ፡ ለሁሉም፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ያውቃሉ ፡ ብለው ፡ ፈረዱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የእስራት ፡ ወይም ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ሊፈርዱበት ፡ ነው ፡ እየተባለ ፡ ሲጠበቅ ፡ ከንጉሡ ፡ አንደበት ፡ "አንተም ፡ ወደ ፡ እናትህ ፡ ነዪ ፡ ብለህ ፡ ላክባት ፡ እኛም ፡ በበኩላችን ፡ እንልክባትና ፡ እንጠይቃታለን ፡ እርሷንም ፡ ከጠየቅንና ፡ ከተረዳን ፡ በኋላ ፡ የምንፈርደውን ፡ እንፈርዳለን' ፡ የሚል ፡ ድንገተኛ ፡ አዲስ ፡ ንግግር ፤ ስለ ፡ ወጣ ፡ ተቀማጩ ፡ ሁሉ ፡ በንጉሡ ፡ አስተዋይነት ፡ ተደነቀ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ እንዳለ ፡ ወደ ፡ እናቱ ፡ ልከ ፡ እናትዮዋ ፡ ወይዘሮ ፡ ክርስቶሳዊት ፡ በልጃቸው ፡ ጥሪ ፡ በንጉሡም ፡ ትእዛዝ ፡ ከመጡ ፡ በኋላ ፡ እንደዚህ ፡ ሲሉ ፡ መሰከሩ ፡ "ገና ፡ የሰባት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ሳለሁ ፡ ደጃዝማች ፡ ዘማርያም ፡ አግብቶ ፡ ትግሬ ፡ ወሰደኝ ፤ በዚያም ፤ ሳለሁ ፡ ፫ ፡ ልጆች ፡ ወለድሁለት ፤ ፬ኛም ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ በፀነስሁ ፡ በ፯ተኛው ፡ ወር ፡ ባለቤቴ ፡ ደጃዝማች ፡ ዘማርያም ፡ በጌምድር ፡ አምጥቶ ፡ አስቀመጠኝ ፡ በመጣሁ ፡ በሦስተኛ ፡ ወሩም ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ በበጌምድር ፡ ከወለድሁ ፡ በኋላ ፡ ደጃዝማች ፡ ዘማርያም ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ወስዶኝ ፡ በዚያም ፡ ፯ ፡ ልጆች ፡ ወለድሁለት ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባለቤቴ ፡ ዘማርያም ፡ ስለ ሞተ ፡ ከትግሬ ፡ መጥቼ ፡ ጐንደር ፡ ከተማ ፡ ተቀመጥሁ ፡ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ንጉሥ ፡ ኢያሱ ፡ ዐወቁኝ" ፡ ብለው ፡ መሰከሩ ።

ይህ ፡ ምስክርነት ፡ ከተሰማ ፡ በኋላ ፡ ግማሾቹ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ምንም ፡ ጥፋት ፡ የለበትምና ፡ ይለቀቅ ፡ አሉ ፡ ግማሾቹ ፡ እናትዮዋ ፡ ንጉሥ ፡ ኢያሱ ፡ ዐወቁኝ ፡ ካለች ፡ የሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ማድረጓ ፡ ነውና እንደ ፡

ገና ፡ ትመርመር ፡ ወይም ፡ ግዞት ፡ ይገባዋል ፡ አሉ ፡ ግማሾቹ ፡ ልጆቹን ፡ አገር፡ እንዳያውኩ ፡ ራሱ ፡ ይሰብስብ ፡ ሲሉ ፡ ተከራከሩ ። ንጉሡ ፡ ግን ፡ የምፈርደውን ፡ ነገ ፡ እፈርዳለሁ ፡ ብለው ፡ ተነሡና ፡ ጉባኤው ፡ ተበተነ ፡ ብሎ ፡ የግዕዙ ታሪክ ፡ ንገሥት ፡ የንጉሡን ፡ የመጨረሻ ፡ ፍርድና ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ የጥቃት ፡ ፍጻሜ፡ ሳይጽፍ ፡ ይተውና ፡ ይጨርሳል ። ይኸን ፡ የግዕዙን ፡ ታሪክ ፡ ትተን ፡ በፈረንሳዊ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈውን ፡ የዣን ፡ ባቲስት ፡ ኩልበን ፡ መጽሐፍ ፡ በ355 ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ስንመለከት ፡ ባሻ ፡ ርቱዕ ፡ በከሰሰው ፡ ክስ ፡ ምክንያት ፡ በንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ቀኝ ፡ እጁን ፡ ተቆረጠ ፡ ሲል ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፴፱

### የዐፄ ፡ በካፋና ፡ የእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ጋብቻ – የብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኩኙ ፡ ፍጻሜ ፡ የንጉሡ ፡ ዕረፍት ።

ዐፄ ፡ በካፋ ፡ ለአደን ፡ ወይም ፡ ግዛት ፡ ለማየት ፡ ወደ ፡ ስናር ፡ ድንበር ፡ ሄደው ሳለ ፡ የወባ ፡ በሽታ ፡ ስለ ፡ ታመሙ ፡ ቋራ ፡ በባላባቱ ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ ተኙ ። ንጉሥ ፡ መሆናቸውን ፡ ሳያውቅ ፡ ባላባቱ ፡ ተቀብሎ ፡ በቤቱ ፡ አስተኛቸው ፡ ይባላል ። የባላባቱም ፡ ውበት ፡ ያላት ፡ ሴት ፡ ልጁ ፡ ስታስታምማቸው ፡ ሰነበተች ፤ በዚያው ፡ በታመሙበት ፡ ጊዜ ፡ ድኜ ፡ ጐንደር ፡ ስገባ ፡ ይችን ፡ ልጅ ፡ አገባለሁ ፡ ብለው ፡ አሰቡ ። እንዳሰቡትም ፡ ከሕመማቸው ፡ ድነው ፡ ጐንደር ፡ ሲገቡ ፡ መኳንንቶቻቸውን ፡ ልከው ፡ ወጣቲቱን ፡ ሴት ፡ አምጥተው ፡ በጐንደር ፡ ታላቅ ፡ ድግስ ፡ ተደግሶ ፡ በሠርግ ፡ አገቡ ። እኝህም ፡ ሴት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የታወቁት ፡ ስመ ፡ ጥሩዪቱ ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ናቸው ። የክርስትና ፡ ስማቸው ፡ ወለተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተጨማሪ ፡ «ስማቸው ፡ ደግሞ ፡ ብርሃን ፡ ሞገሳ ? ይባላል ።

እቴጌይቱ ፡ በኋላ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ተብለው ፡ የነገሡትን ፡ ኢያሱን ፡ ለበካፋ ፡ ወለዱላቸውና ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ተደረገ ።

የእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ዘር ፡ ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ልጅ ፡ ከፊቅጦር፡ የመጣ ፡ ነው ፤ እንደዚሁ ፡ ከፖርቱጊዞች ፡ የወረደ ፡ ዘር ፡ አላቸው ፡ ሲሉ ፡ ብሩስ ፡ (Bruce) በሁለተኛ ፡ መጽሐፉ ፡ በ፫፻፲፩ ፡ ገጽ ፡ ባጂ ፡ (Budge) ፡ በ፬፻፵፫ ፡ ገጽ ፡ ይጽፋሉ ።

እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ በዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ነበሩት ፡ እንደ ፡ ዐፄ ፡ በዕደ ፡ ማርያም ፡ ባለቤት ፡ እንደ ፡ እቴጌ እሌኒ ፤ እንደ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ባለቤት ፡ እንደ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ በሕዝቡም ፡ ዘንድ ፡ የተከበሩና ፡ የተፈሩ ፡ ነበሩ ። ከባለቤታቸው ፡ ከዐፄ ፡ በካፋ ፡ ዠምሮ ፡ ይልቁንም ፡ በልጃቸው ፡ በቋረኛ ፡ እያሱ ፡ በልጅ ፡ ልጃቸው ፡ በኢዮአስ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ከዚያም ፡ እስከ ፡ ተፍጻሜተ ፡ መንግሥት ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዘመን ፡ ሲኖሩ ፡

አብዛኛውን ፡ ጊዜያቸውን ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ያዙ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፤ የር ሳቸውን ፡ ሥልጣን ፡ በመጨረሻ ፡ የራስ ፡ ሥዑል ፡ ሚካኤል ፡ መነሣት ፡ ሊያደ ናቅፈው ፡ ቻለ ፡ ይኸንንም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እናገኘዋለን።

⁂ ⁂ ⁂

ዐፄ ፡ በከፋ ፡ ዘጠኝ ፡ (፱) ፡ ዓመት ፡ ከገዙ ፡ በኋላ ፡ በዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ መገመሪያ ፡ ላይ ፡ ጠላትና ፡ ወዳጃቸውን ፡ ለመለየት ፡ ሳይታመሙ ፡ ታምሚያ ለሁ ፡ ብለው ፡ ተኙ ። ሊገናኙም ፡ የሚመጣውን ፡ ዐፄ ፡ ታመዋልና ፡ ማንንም ፡ ሊገናኙ ፡ አይችሉም ፡ እያሉ ፡ አሽከሮቻቸው ፡ መለሱት ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ በብላቴን ፡ ጌታ ፡ ማሙዬ ፡ እግር ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ የሆነው ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኩቾ ፡ ወታደሩን ፡ ሰበሰበና ፡ ከወህኒ ፡ አምባ ፡ የመረጠውን ፡ አውርዶ ፡ ለማን ገሥ ፡ ይሰናዳ ፡ ዠመር ። ወታደሩም ፡ ጠመንዠውን ፡ እያጐረሰ ፡ ጦሩን ፡ እየ ያዘ ፡ ተከተለው ፤ ከተማውም ፡ ሊሸበር ፡ ደረሰ ።

ንጉሡም ፡ ይህነን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከእልፍኛቸው ፡ ወጥተው ፡ በፈ ረስ ፡ ሆነው ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ አደባባይ ፡ በድንገት በታዩ ፡ ጊዜ ፡ መኳንን ቱና ፡ ሕዝቡ ፡ እየተገረመ ፡ ተገልብጦ ፡ መጣ ። ካህናቱም ፡ ንሴብሖ ፡ ለእግዚ አብሔር ፡ ስቡሐ ፡ ዘተሰብሐ ፡ እያሉ ፡ እየወረቡ ፡ ንጉሡ ፡ እፈረሳቸው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ሁሉም ፡ እየመጡ ፡ መሬት ፡ እየሳሙ ፡ ደስታቸውን ፡ ገለ ጡላቸው ፤ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኰቾም ፡ ሳይዋጋ ፡ ተመልሶ ፡ ገባ ።

ንጉሡም ፡ መኳንንቶቹን ፡ እናንተን ፡ ነገ ፡ ነው ፡ የማነጋግራችሁ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ወደየቤታችሁ ፡ ግቡ ፡ ብለው ፡ አሰናብተው ፡ ካህናቱን ፡ ግን ፡ በፍቅር ፡ ሲያ ነጋግሯቸው ፡ ዋሉ ፡ ይባላል ። በማግስቱም ፡ ልብሰ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ለብሰው ፡ ባደባባይ ፡ ተቀመጡ ፡ መኳንንቱም ፡ እየመጣ ፡ እጅ ፡ እየነሣ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ እንደ ፡ ማዕርጉ ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ «ለጥቂት ፡ ቀን ፡ ታምሜ ፡ ብተኛ ፡ በከተማ ፡ ሽብር ፡ ያስነሣችሁት ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው» ፡ ብለው ፡ ንጉሡ ፡ መኳንንቶቹን ፡ መውቀስ ፡ ዠመሩ ። መኳንንቶቹም ፡ እየተነሡ ፡ «እኛ ፡ ለጌታችን ፡ ሕይወት ፡ ከማሰብ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ የበደልነው ፡ ነገር ፡ የለም ፤ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ፡ የጦሩ ፡ አለቃ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኩቾና ፡ የንጉሡ ፡ እኅቶች ፡ ናቸው» ፡ ብለው ፡ ጥፋቱን ፡ ሁሉ ፡ በነ ዚሁ ፡ ጣሉባቸው ። ስለዚህ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኩቾና ፡ ሁለቱ ፡ የዐፄ ፡ በከፋ ፡ እኅቶች ፡ ተይዘው ፡ ተገደሉ ፡ ይባላል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ፩ ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ ቈዩ ፡ በሺሕ ፡ ፲፻፷፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ ታመሙና ፡ በመጨረሻ ፡ ሞቱ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሕዝቡ ፡ እንደዚህ ፡ ቀደሙ ፡ ሐሰት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ እያለ ያመነታ ፡ ነበር ። እቴጌ ፤ ምንትዋብም ፡ ከቋራ ፡ ፩ቱ ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ደጃች ፡ ወልደ ፡ ልዑል ፡ እሸቴ ፡ (ኤሽቴ) ፡ ጌታ ፤ አውሳብዮስ ፡ ነጮ ፤ እስኪመጡላቸው ፡ ድረስ ፡ የንጉሡን ፡ መሞት ፡ ደበቁ ። የተጠሩት ፡ ወንድሞቻቸውም ፡ ደርሰው ፡ በየ ሥልጣኑ ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ የንጉሡ ፡ የዐፄ ፡ በከፋ ፡ መሞት ፡ በይፋ ፡ ተነግሮ ፡ ኀዘን ፡ ተደረገ ።

ዐፄ ፡ በካፋ ፡ ዋና ፡ ዋናው ፡ በዘመናቸው ፡ የሠሩት ፡ ሥራ ፡ እንሆ ፡ ባለ ፈው ፡ የተጻፈው ፡ ነው ፡ አንዳንድ ፡ ሳንጽፍ ፡ የተውነውም ፡ ቢኖር ፡ ያንዳንድ፡ ሰው ፡ የመሸፈትና ፡ የመዋጋት ፡ ወዳንዳንድ ፡ አገር ፡ ያደረጉት ፡ ጉዞ ፡ ይኸን ፡ ከመሳሰለው ፡ በቀር ፡ የጐላ ፡ ነገር ፡ የቀረ ፡ ያለ ፡ አይመስለኝም ። የርሳቸውን ፡ ጠባይና ፡ ችሎት ፡ ደግነትና ፡ ርኅራኄ ፡ ጸሎትና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አዘው ታሪነታቸውን ፡ ጸሓፌ ፡ ትእዛዛቸው ፡ አዛዥ ፡ ሲኖዳ ፡ እያሳመረ ፡ ጽፎላቸዋል። በሌላ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ በጎነት ፡ በጊዜያቸው ፡ እንዳልሠሩ ፡ እን ዲያውም ፡ ሙያቸውን ፡ ካንድ ፡ ተዋነይ ፡ ከሚባል ፡ ከጐንጅ ፡ ደብተራ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ጥንቈላና ፡ ስለ ፡ አስማት ፡ ጉዳይ ፡ ሲጫወቱና ፡ ሲያስጠነቁሉ ፡ ይውሉ ፡ ነበር ፡ የሚል ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ።

ነገር ፡ ግን ፡ እውነተኛውን ፡ የፈለግን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዳባቶቻቸውም ፡ እንደ ፡ ልጆቻቸውም ፡ አንዳንድ ፡ ነገሥታት ፡ ባንድ ፡ ፊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲተክሉ ፡ ግብር ፡ ሲያበሉ ፡ ቅን ፡ ፍርድ ፡ ሲፈርዱ ፡ በሌላው ፡ ፊት ፡ ደግሞ ፡ ከሸፈተው ፡ ጋራ ፡ ሲዋጉ ፡ ሲማርኩ ፡ በጭካኔ ፡ ሲገድሉ ፡ ሲያስሩ ፡ ሲፈቱ ፡ መኖር ፡ እንዳለባቸው ፤ እንዲሁም ፡ መጪ ፡ ዕድላቸውን ፡ ለመርዳት ፡ ተስፋ ፡ እያደረጉ ፡ ዐው ቃለሁ ፡ ከሚል ፡ ደብተራ ፡ ለመጠየቅ ፡ ግንኙነት ፡ ማድረጋቸው ፡ አይቀርም ።

## የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

### ምዕራፍ ፡ ፴፫ ።

### እቴጌ ፡ ምንትዋብና ፡ ቋረኞች ፤ የራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ መሸፈት ፤ ዙፋን ፡ በሚ ፈልገው ፡ በሕዝቅያስና ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ጦር ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ውጊያ ።

ዐፄ ፡ በካፋ ፡ ሲሞቱ ፡ ልጃቸው ፡ ኢያሱ ፡ ስመ ፡ መንግሥታቸው ፡ «ብርሃን ፡ ሰገድ» ፡ (1) ፡ ተብሎ ፡ ነገሡ ፤ በእናታቸውም ፡ የቋራ ፡ ተወላጅ ፡ ስለ፡ ሆኑ ፡ "ቋረኛ ፡ ኢያሱ„ ፡ እየተባሉ ፡ ይጠራሉ ፤ ለአድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱም ፱ኛ ፡ በመሆናቸው ፡ „ዳግማዊ ፡ ኢያሱ" ፡ ይበላሉ ። በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ ዕድሜያ ቸው ፡ ያልበሰለ ፡ ስለሆነ ፡ በነገሡበት ፡ ቀን ፡ እናታቸው ፡ እቴጌ ምንትዋብ ፡ እንደ ፡ ንግሥት ፡ ዘውድ ፡ ጭነው ፡ በሞግዚትነት ፡ ነገሡ ። እቴጌይቱም ፡ ኃይ ለኛና ፡ ብልኅ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ከልጃቸው ፡ ከንጉሡ ፡ ይልቅ ፡ የርሳቸው ፡ ኃይልና ፡ ሥልጣን ፡ የገነነ ፡ ነበር ፤ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ባፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ ያደርጉት ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብም ፡ ከቋራ ፡ ወንድሞቻቸውንና ፡ የወንድሞ ቻቸውን ፡ ልጆች ፡ አስመጥተው ፡ ሥልጣኑን ፡ ሁሉ ፡ አሲዘዋቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ፡ በጊዜያቸው ፡ ሊደፈሩ ፡ አልቻሉም ነበር ።

(1) ፤ እንዳያታቸው ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ተብለዋል ፡ የሚሉ ፡ አሉ ። በዚህም ፡ ላይ ፡ (አገልድም ፡ ኢያሱ) ፡ ይባሉ ፡ ነበር ፡ አገልድም ፡ የተባሉበት ፡ ምክንያት ፡ አልገባኝም ።

ነገር ፡ ግን ፡ የቀድሞዎቹ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እነዚህን ፡ አዲስ ፡ እየመጡ ፡ በሥልጣን ፡ የተቀመጡትን ፡ ሿረኞችን ፡ በመጥላታቸው ፡ የወገን ፡ ልዩነት ፡ ሆኖ ፡ ይናናቁ ፡ ነበር ፤ ቢሆንም ፡ ሁሉም ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መገዛት ፡ ግድ ፡ ሆነበት ። ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ ብቻ ፡ በዚህ ፡ መለያየት ፡ ለመጠቀምና ፡ በቶሎ ፡ መንግሥቱን ፡ ለመገልበጥ ፡ ሞከረ ።

ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ በዐፄ ፡ በካፋ ፡ ጊዜ ፡ በወልቃይት ፡ በግዞት ፡ ተቀምጦ ፡ ሲኖር ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከወልቃይት ፡ ገሥግሦ ፡ መጥቶ ፡ በዐፄ ፡ በካፋና ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ ትእዛዝ ፡ ታስረው ፡ የነበሩትን ፡ በኀይል ፡ አስፈትቶ ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ አምባ ፡ ገሠገሠ ፤ በየመንገዱም ፡ ብዙ ፡ ተከታይ ፡ አገኘ ። የርሱም ፡ አሳብ ፡ እንደዚህ ፡ ቀደሙ ፡ የዐፄ ፡ በካፋን ፡ ወንድም ፡ አቤቶ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስን ፡ አውርዶ ፡ ለማንገሥ ፡ ነው ። ወደ ፡ ወህኒ ፡ አምባ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ወህኒ ፡ ቤቱን ፡ ይጠብቁ ፡ ከነበሩት ፡ ከእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ወንድም ፡ ከደጃች ፡ ወልደ ፡ ልዑል ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ገጠሙ ። ነገር ፡ ግን ፡ ወዲያው ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ አሸነፈና ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ወጥቶ ፡ ከአቤቶ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተገናኙ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከመውረዱ ፡ በፊት ፡ ከጐንደር ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ በደጃች ፡ ኒቆላዎስ ፡ መሪነት ፡ መጥተው ፡ ሸሽተው ፡ ከነበሩት ፡ ከነደጃች ፡ ወልደ ፡ ልዑል ፡ ጋራ ፡ ተገናኘ ። ደጃች ፡ ወልደ ፡ ልዑልም ፡ አዲስ ፡ የደረሰለትን ጦር ፡ ጨመርና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተመልሶ ፡ ተራራውን ፡ ከበው ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስን ፡ ውጊያ ፡ ገጠሙት ፤ እነዚህ ፡ ከሥር ፡ እነዚያ ፡ ከተራራው ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ሲዋጉ ፡ ጦርነቱ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ አዋለ ። በ፪ኛው ፡ ቀን ፡ ሲመሽ ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ ፡ ዘጊዮርጊስ ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ ከአቤቶ ፡ ወልደ ፡ ጊርዮጊስና ፡ ከተከታዮቻቸው ፡ ጋራ ፡ ተማረኩ ። አቤቶ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ብቻ ፡ ተመልሶ ፡ በዚያው ፡ በወህኒ ፡ አምባ ፡ በጥብቅ ፡ እንዲታሰር ፡ ሲፈረድበት ፡ የቀሩትን ፡ አምጥተው ፡ ጐንደር ፡ በእቴጌ ፡ ምንትዋብና ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ትእዛዝ ፡ በጭከኔ ፡ ገደሏቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ አገሩ ፡ በሰላም ፡ እንደ ፡ ቈየ ፡ በመጨረሻ ፡ የዐፄ ፡ በካፋ ፡ መኳንንቶች ፡ ከነበሩት ፡ አንዱ ፡ ተንሣይ ? ማሞ ፡ የሚባለው ፡ ከሥልጣኑ ፡ ተዋርዶ ፡ ባለሥልጣኖቹ ፡ ቋረኞች ፡ በመሆናቸው ፡ ሲናደድ ፡ ይኖር ፡ ነበርና ፤ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከጓደኞቹ ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ ወታደር ፡ ይዞ ፡ ወጥቶ ፡ ሕዝቅያስ ፡ የተባለውን የነጋሢ ፡ ዘር ፡ ከወህኒ ፡ አምባ ፡ አውርዶ ፡ ጐንደርን ፡ ከቦ ፡ አስጨነቀ ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ጳጳሱ ፡ አቡነ ፡ ክርስቶዶሉና ፡ ዕጨጌው ፡ በገሃድ ፡ ሳይሆን ፡ ውስጡን ፡ ዐድማቸውን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አድርገው ፡ ነበር ።

ዐፄ ፡ ኢያሱም ፡ የጐንደርን ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ወታደሮች ፡ ይዘው ፡ ከቅጥር ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ ለጦርነት ፡ ይዘጋጁ ፡ ዠመር ። የእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ወንድሞችም ፡ የጦርነቱ ፡ አነሣሥ ፡ አንዱም ፡ እነሱን ፡ በመጥላት ፡ መሆኑን ፡

ያውቃሉና ፡ ከሌሎቹ ፡ ለንጉሡ ፡ ከታመኑት ፡ መኳንንት ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ለሞትም ፡ ቢሆን ፡ ለሕይወትም ፡ ታጥቀን ፡ ከጌታችን ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ እንሞታለን ፡ ሲሉ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ በሥርዐተ ፡ ርእሱ ፡ ሥዕል ፡ (የጌታችን ፡ አክሊለ ፡ ሦክ ፡ ያለበት ፡ ሥዕል) ፡ ፊት ፡ መሐላ ፡ አቅርበው ፡ የጠርነቱን ፡ መዠመር ፡ ይጠባበቁ ፡ ዠመር ፡፡

ንጉሡም ፡ የራስ ፡ ኤልያስንና ፡ የጳጳሱን ፡ የዕጨጌውንም ፡ ከሽፍቶቹ ፡ ጋራ ፡ ዐድመዋል ፡ ማለትን ፡ ወሬ ፡ እንጂ ፡ ርግጡን ፡ አልተረዱም ፡ ነበርና ፡ ርግጡን ፡ ለማወቅ ፡ ሲሉ ፡ ሦስቱንም ፡ እኔ ፡ ድረስ ፡ በቶሎ ፡ መጥታችሁ ፡ እንድንገናኝ ፡ ብለው ፡ ላኩባቸው ፤ እነሱም ፡ መልክቱን ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ ዕጨጌው ፡ ብቻ ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ሲመጡ ፡ ጳጳሱና ፡ ራስ ፡ ኤልያስ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ ቀሩ ፡ መክዳታቸው ፡ ታወቀ ፡፡

ሽፍቶቹም ፡ የጐንደርን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከበው ፡ አስጨነቁት ፡፡ ሕዝቅያስንም ፡ ማንገሣቸውን ፡ የሚያስረዳ ፡ ዐዋጅ ፡ አደረጉ ፤ ብዙ ፡ ቤትም ፡ ማቃጠል ፡ ዠመሩ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ንጉሡን ፡ ለመርዳት ፡ ብዙ ፡ ጋሎች ፡ በፈረስ ፡ ከውጭ ፡ እየጋለቡ ፡ መጥተው ፡ በሽፍቶቹ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ጣሉባቸው ፡፡ ጋሎቹም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ገብተው ፡ እውስጥ ፡ ካለው ፡ ከንጉሡ ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ ተደባለቁ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በሽፍቶቹ ፡ መከከል ፡ ፍርሃት ፡ ተነዛ ፡፡

አቡኑ ፡ በውጭ ፡ ሆነው ፡ የንጉሡ ፡ ወገን ፡ ከውስጥ ፡ መበርታቱን ፡ ስለ ፡ ተመለከቱ ፡ በቶሎ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ተላልከው ፡ ገብተው ፡ የንጉሡን ፡ አሽከሮች ፡ «ስለ ንጉሣችሁ ፡ ብትሞቱ ፡ የሰማዕታትን ፡ ክብር ፡ ታገኛላችሁ» ፡ እያሉ ፡ ይሰብኩ ፡ ዠመር ፡፡ ራስ ፡ ኤልያስ ፡ ግን ፡ ከነዚሁ ፡ ከሽፍቶቹ ፡ ወገን ፡ ሆኖ ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጳጳሱ ፡ አሳቡን ፡ አለወጠም ፡፡

በውጭ ፡ ያለው ፡ አብዛኛው ፡ የከተማው ፡ ሕዝብና ፡ ካህናት ፡ ራስ ፡ ኤልያስንና ፡ ንገሠ ፡ የተባለውን ፡ ሕዝቅያስን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ሆ ፡ እያለ ፡ ጦርነቱን ፡ ያዳምቅ ፡ ነበር ፡፡ ጦርነቱም ፡ ካለፉት ፡ ቀኖች ፡ ይልቅ ፡ የመጨረሻው ፡ ቀን ፡ የባሰ ፡ ሆኖ ፡ ዋለ ፡፡ በውስጡም ፡ ያሉት ፡ የንጉሡ ፡ ወታደሮች ፡ ተዳከሙ ፡ ይልቁንም ፡ በቅጥሩ ፡ አጠገብ ፡ የነበረውን ፡ የጐተራና ፡ የጒድጓድ ፡ እኽል ፡ የውጭዎቹ ፡ ስለ ፡ ያዙባቸው ፡ እውስጥ ፡ ያሉት ፡ በፍጹም ፡ ተስፋ ፡ ቈርጠው ፡ ነበር ፡፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ አቡኑና ፡ ዕጨጌው ፡ ዐቃቤ ፡ ሰዓቱ ፡ የጠርነቱ ፡ ዕድል ፡ ለነራስ ፡ ኤልያስ ፡ ማድላቱን ፡ ስለ ፡ ተመለከቱ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ከንጉሡ ፡ ሰፈር ፡ ተለይተው ፡ ወደነራስ ፡ ኤልያስ ፡ መጡ ፡፡ ሲመጡም ፡ ንጉሡን ፡ ፪ኛ ፡ ከዳችሁ ፡ ወይም ፡ አወላወላችሁ ፡ ተብሎ ፡ እንዳይሳቀባቸው ፡ እኛ ፡ ወደናንተ ፡ ተመልሰን ፡ የመጣነው ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ እቴጌዩቱና ፡ ንጉሡ ፡ ኢያሱ ፡ ድሜጥሮስ ፡ (1) የተባለውን ፡ ካቶሊክ ፡ ባለሟል ፡

(1) ይህ ፡ ድሜጥሮስ ፡ በዐፄ ፡ በካፋ ፡ ጊዜ ፡ የመጣ ፡ የግብጽ ፡ ተወላጅ ፡ ነው ፡፡ በበካፋ ፡ ጊዜ ፡ በብርጌዳ ፡ በተሠራው ፡ መርከብም ፡ ውስጥ ፡ በሠራተኛነት ፡ ስሙ ፡ ተጠቅሱዋል ፡፡ ካቶሊክ ፡ መሆኑን ፡ ግን ፡ ጳጳሱ ፡ ለምክንያት ፡ የጣሉበት ፡ ይመስላል ፡ እንጂ ፤ እርሱ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡፡

አድርገው ፡ ስላስቀመጡት ፡ ከካቶሊክ ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ የለንም ፡ በማለት ፡
ነው ፡ ብለው ፡ አወሩ ። ሽፍቶቹንም ፡ በርቱና ፡ ተዋጉ ፡ እያሉ ፡ ያደፋፍሯ
ቸው ፡ ጀመር ። ነገር ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ ፊት ፡ ደግሞ ፡ ጳጳሱና ፡ ዕጨጌው ፡
ከዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ወደ ፡ ሽፍቶቹ ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ የተመላለሱት ፡
ውስጡን ፡ ክዳት ፡ ቢኖር ፡ ላዩን ፡ በማስታረቅ ፡ ስም ፡ ነው ፡ ይባላል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ የሽፍቶቹ ፡ ኀይል ፡ እየበረታ ፡
ሄደ ። በቅጥሩ ፡ አጠገብና ፡ ዙሪያ ፡ የሚገኘውን ፤ ቤት ፡ ሁሉ ፡ እሳት ፡ ለቀ
ቁበት ፤ ከተማውም ፡ በመላ ፡ ተሸበረ ። በውስጡም ፡ ያሉት ፡ ወታደሮች ፡
ምንም ፡ እንኳን ፡ ተስፋ ፡ ቢቈርጡ ፡ ተማርከን ፡ በሽፍቶቹ ፡ እጅ ፡ ከምንወ
ቃይ ፡ ስል ፡ ጌታችን ፡ በርትተን ፡ እየተዋጋን ፡ በከበሬታ ፡ ብንሞት ፡ ይሻላል ፡
ብለው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ባዲስ ፡ ኀይል ፡ ተቀሰቀሱ ። ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ጭንቅ ፡
በከበደበት ፡ ጊዜ ፡ በሰገነት ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ከብዙ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ከውጭ ፡
የሚመጣውን ፡ ርዳታ ፡ የሚጠብቀው ፡ የንጉሡ ፡ ዘበኛ ፡ ይኸው ፡ ደርሷልና ፡ በርቱ ፡
ብሎ ፡ ስለ ፡ ተናገረ ፡ ይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ የባሕርይ ፡ ጕልበት ፡ የሚጠነክረው ፡
በተስፋ ፡ ነውና ፤ የንጉሡ ፡ ተዋጊዎች ፡ ይኸን ፡ ወሬ ፡ ከተጠባበቂው ፡ በሰሙ ፡
ጊዜ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ባዲስ ፡ ኀይል ፡ ጦርነቱን ፡ ይቀጥሉ ፡ ጀመር ።

ቢሆንም ፡ ቊጥራቸው ፡ እያደር ፡ በማነሱ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ በርትተው ፡ ሲከ
ላከሉ ፡ ደጃች ፡ አርከለዲስ ፡ በሚዋጋበት ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ተሸነፉ ፡ ሽፍቶቹ ፡ እቅ
ጥሩ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ዕቃ ፡ መዝረፍ ፡ ቤት ፡ መበርበር ፡ ጀመሩ ፤ በየቤቱም ፡
ቢጋን ፡ ያገኙትን ፡ ጠጅና ፡ ጠላ ፡ እየጠጡ ፡ ይሰክሩ ፡ ጀመሩ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የተጠበቀው ፡ ደጃዝማች ፡ ወሬኛ ፡ የሚባለው ፡ የዳሞት ፡ አገረ
ገዥ ፡ ካዛዥ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ጋራ ፡ ሠራዊቱን ፡ ይዞ ፡ ንጉሡን ፡ ለመርዳት ፡ በግሥ
ጋሚ ፡ በሽፍቶቹ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ ይዋጋ ፡ ጀመር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጦርነቱ ፡ ተፋ
ፍሞ ፡ ታላቅ ፡ እልቂት ፡ ሆነ ። ከሽፍቶቹም ፤ ከንጉሡም ፡ አሽከሮች ፡ ብዙ ፡ ሰው
አለቀና ፡ የሰው ፡ ደም ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ጐረፈ ፡ ይባላል ። በመጨረሻ ፡ ግን ፡ በሁ
ለት ፡ ወገን ፡ ከውጭና ፡ ከግቢ ፡ እየተወጉ ፡ ከሽፍቶቹ ፡ ብዙዎቹ ፡ ስላለቁ ፡ ገሚ
ሶቹም ፡ ሰክረው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እየተደናበሩ ፡ ሲሸሹ ፡ አዲሱ ፡ ነጋሢ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተማ
ረከና ፡ ጦርነቱ ፡ ተፈጸመ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የንጉሡ ፡ የጦር ፡ ሹማምቶች ፡ ሕዝቅያስ ፡ መማረኩን ፡ ለዐፄ ፡
ኢያሱና ፡ ለእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ የምሥራቹን ፡ ልከው ፡ እነሱም ፡ እርሱንና ፡ ተከ
ታዮቹን ፡ አስረው ፡ ብዙም ፡ ሰለባ ፡ ይዘው ፡ ሆ ፡ እያሉ ፡ ንጉሡ ፡ ወዳሉበት ፡ ገቡ ።
ንጉሡና ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብም ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ሆነው ፡ በዙፋናቸው ፡ ተቀምጠው ፡
ይጠባበቁ ፡ ነበርና ፡ ምርኮኛውን ፡ ሕዝቅያስንና ፡ ተማራኪዎቹን ፡ አሽከሮቻቸውን ፡ ባዩ ፡
ጊዜ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ደስታ ፡ አደረጉ ፤ እቴጌ ፡ ምንትዋብም ፡ "በኢያሱ ፡ ቀኝ ፡
የዋልክ ፡ አምላክ ፡ አመሰግንሃለሁ" ፡ ብለው ፡ ለፈጣሪያቸው ፡ ከልብ ፡ የሆነ ፡ ምስ
ጋና ፡ አቀረቡ ፡ ይባላል ።

የጦርነቱ ፡ ቀስቃሽ ፡ የነበረው ፡ ትንሣይ ፡ ማሞም ፡ ድል ፡ መሆኑን ፡ በተረዳ ፡ ጊዜ ፡ ከጦርነቱ ፡ ሥፍራ ፡ ሸሽቶ ፡ ነበርና ፤ በወገራ ፡ በኩል ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ሸሬ ፡ ለመሄድ ፡ ሲያስብ ፤ በመንገድ ፡ ተያዘና ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጣ ፤ ከዚያም ፡ ተፈረደ በትና ፡ በደባባይ ፡ ተሰቀለ ። የቀሩትም ፡ ገሚሶቹ ፡ በሞት ፡ ገሚሶቹ ፡ በስራት ፡ ተቀጡ ። ሕዝቅያስ ፡ ግን ፡ የነጋሢ ፡ ልጅ ፡ አይገደልም ፡ ተባለና ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ካስ ጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ቀድሞ ፡ ወደ ፡ ነበረበት ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ አምባ ፡ ተላከ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሕዝቅያስንና ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱን ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ከድተው ፡ ይመ ላለሱ ፡ የነበሩት ፡ ጳጳሱና ፡ እጨጌው ፡ ይቅረቡ ፡ ተባለና ፡ ተጠርተው ፡ ቀረቡ ። እንደ ፡ ቀረቡም ፡ ‘በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ እኛን ፡ ገዝታችሁ ፡ ከሸፍቶች ፡ ጋራ ፡ ሆናችሁ ፡ ትወጉን ፡ የነበረው» ፡ ብለው ፡ ጠየቋቸው ። እነሱም ፡ «እኛ ፡ ድሜጥሮስና ፡ ጓደኞቹ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ግቢ ፡ ገብተው ፡ በተቀመጡ ፡ ጊዜ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ መሆናቸ ውን ፡ ሳናውቅ ፡ ካቶሊኮች ፡ መስለውን ፡ በዚህ ፡ ተቀይመን ፡ ነው ፤ አሁን ፡ ግን ፡ እኛም ፡ ግዝታችንን ፡ እንፍታ ፡ ንጉሡም ፡ ይቅርታ ፡ ያድርጉልን› ፡ ብለው ፡ አመለከቱ ፤ ንጉሡም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ኀይል ፡ ጳጳሱና ፡ እጨጌውም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ ክብር ፡ ያውቃሉና ፡ ይቅርታ ፡ አደረጉላቸው ። እነሱም ፡ ንጉሡ ንና ፡ ከንጉሡ ፡ ጐን ፡ ሆነኽ ፡ ሕዝቅያስን ፡ የወጋኽ ፡ ገዝተናል ፡ ብለው ፡ የነበረውን ግዝት ፡ ፈቱና ፡ ዕርቅና ፡ ሰላም ፡ ሆነ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፬ ።

### የክብራን ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ — ስለ ፡ ትምህርትና ፡ ጽሕፈት ፡ መስፋፋት ፤ — የጎዳር ፡ ቍስቋም ፡ በዋለችበት ፡ ቀን ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ያደረጉት ፡ ግብር ፡— ተንኰል ፡ ያለበት ፡ ያለቃ ፡ ኢሳይያስ ፡ ጥያቄ ።

ቋረኛ ፡ ኢያሱ ፡ ከእናታቸው ፡ ከእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ጋራ ፡ እየተመካከሩ ፡ ብዙ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተክለዋል ። በጣና ፡ ደሴት ፡ ውስጥ ፡ ዛሬ ፡ ያሉት ፡ ትልልቅ ፡ አድባራትና ፡ ገዳማት ፡ የተተከሉት ፡ በርሳቸው ፡ ጊዜ ፡ ነው ፤ ከነዚሁም ውስጥ ፡ ይበልጥ ፡ አምሮ ፡ የተሠራው ፡ የክብራን ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ ነው ። እርሱንም ፡ ንጉሡ ፡ ከኢየሩሳሌምና ፡ ከግብጽ ፡ ተላልከው ፡ ሠራ ተኛ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጠንካራ ፡ ዕንጨት ፡ አስመጥተው ፡ ባማረ ፡ ዕንጨትና ፡ በጡብ ፡ አሠርተውት ፡ ነበር ፤ ሥራውም ፡ አምሮ ፡ በመፈጸሙ ፡ ከንጉሡና ፡ ከእቴጌ ፡ ምን ትዋብ ፡ ጋራ ፡ እንዲሁም ፡ ተመልካችን ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አሰኘ ። በአለፉ ፡ በጣቍሳ ፡ በጭልጋም ፡ ብዙ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በኖራ ፡ ተሠሩ ።

በዚህም ፡ ላይ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ በዘመናቸው ፡ ትምህርት ፡ እንዲስፋፋና ፡ አስ ተማሪውም ፡ ተማሪውም ፡ እንዲነቃ ፡ ይጣጣሩ ፡ ነበር ፡ ስለዚህ ፡ ከመንግሥቱ ፡ ማድ ፡ ቤት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ እየወጣ ፡

ሀ) ለፊደል ፡ ቄጣሪ ፡ እንጀራና ፡ ወጥ ፡

ለ) ለዜማ ፡ ተማሪ ፡ እንጀራና ፡ ወጥ ፡ ከጠላ ፡ ጋራ ፡

ሐ) ለቅኔ ፡ ተማሪ ፡ እንጀራና ፡ ወጥ ፡ ከጠጅ ፡ ጋራ ፡

መ) እንዲሁም ፡ ለመጻሕፍት ፡ ተማሪ ፡ ከዚህ ፡ የተሻለ ፡ ድርጎ ፡ እንዲሰጥ ፡ ስለ ፡ አዘዙ ፡ የትምህርት ፡ ጉባኤ ፡ በሰፊው ፡ ተይዞ ፡ ነበር ።

መጻሕፍትንም ፡ ከዐረብኛ ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ በጊዜያቸው ፡ አስተርጒመዋል ። ለቁም ፡ ጸሐፊም ፡ ደመወዝና ፡ ቀለብ ፡ እየሰጡ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ እያስገለበጡ ፡ ለየቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ያድሉ ፡ ነበር ። ይልቁንም ፡ ለክብራን ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ገዳም ፡ የሰጡት ፡ መጻሕፍት ብዙዎች ፡ ናቸው ፡ ከብዛታቸውም ፡ የተነሣ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የማ ይታወቁ ፡ መጻሕፍት ፡ አሉ ፡ ይባላል ። ይኸውም ፡ ገዳም ፡ በመጻሕፍት ፡ በኩል ፡ ሀብታም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ የመጻሕፍት ፡ ቤት ፡ (ቢብሊዮቴክ) ፡ ይቈጠር ፡ ነበር ፤ ከሸዋና ፡ ከትግሬም ፡ የሚመጡት ፡ የጐንደርም ፡ ሊቃውንት ፡ ሥንቃቸ ውን ፡ እየያዙ ፡ በታንኳ ፡ እቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ገዳም ፡ እየገቡ ፡ መጻሕፍቱን ፡ በመመርመርና ፡ በመመልከት ፡ ዓመትና ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ይፈጁ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

ይህ ፡ ገዳም ፡ ሥራው ፡ የመዳብ ፡ የሆነ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነጋሪት ፡ ስላለው ፡ በጐን ደር ፡ የተደነቀ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ በሥራውና ፡ ባሳብ ፡ ደክመው ፡ ሳለ ፡ «ገዳም ፡ ነውና ፡ ሴት ፡ አትገባበትም» ፡ በመባሉ ፡ በጣም ፡ ሲያዝኑ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከርሱ ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ለሴቶች ፡ በተለይ ፡ የኪዳነ ፡ ምሕ ረት ፡ ገዳም ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ይህ ፡ የሴት ፡ ገዳም ፡ ቢኖራቸው ፡ ውጭውና ፡ ውስጡ ፡ ሥራው ፡ የሚያምረውን ፡ በሙሣሪያውም የተደነቀውን ፡ የቅዱስ ፡ ገብርኤልን ፡ ገዳም ፡ ለማየት ፡ ባለመቻላቸው ፡ ያዝኑ ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ከሴት ፡ ገዳም ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ እስከ ፡ ወንድ ገዳም ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ድረስ ፡ ስጋጃ ፡ አስነጥፌ ፡ ርሱን ፡ እየረገጥሁ ፡ ገብቼ ፡ ልይና ፡ ለዚሁም ፡ ለደፈርሁበት ፡ እንደ ፡ ካሳ ፡ እንዲቆጠርልኝ ፡ ሥጋጃውን ፡ በሙሉ ፡ ለቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ልልቀቅ ፡ ብለው ፡ ለልጃቸው ፡ ለዳግማዊ ፡ ኢያሱ ፡ አማ ክረዋቸው ፡ ነበረ ። ንጉሡ ፡ ግን ፡ እኛው ፡ ደንቡን ፡ ሠርተን ፡ መልሰን ፡ ራሳ ችን ፡ ስናፈርሰው ፡ ቅር ፡ ያሰኛል ፡ ሲሉ ፡ መለሱላቸው ። የዚህንም ፡ አሳብ ፡ ለሊቃውንቱ ፡ ቢልኩባቸው ፡ አልተስማሙባቸውም ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ እቴጌዪቱ ፡ በጣም ፡ የተከበሩና ፡ የተፈሩ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ በገሃድ ፡ ሊከለክላቸው ፡ የሚደፍር ፡ እንደሌለ ፡ በማወቅ ፡ በገዛ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ምንጣፉን ፡ ከሴት ፡ ገዳም ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ እስከ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ገዳም ፡ አስነጥፈው ፡ በዓሉ ፡ በሚውልበት ፡ በታኅሣሥ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ለመሄድ ፡ ጕዞ ፡ ዠመሩ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ገሚስ ፡ መንገድ ፡ እንዳደረጉ ፡ «ልማደ ፡ አንስት» ፡ ስለ ፡ አስደነገጣቸው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ተአምራት ፡ አድንቀው ፡ ወደ ፡ ኋላ ቸው ፡ ተመለሱ ። ይኸንንም ፡ ተአምራት ፡ የሠራ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ነው ፡

ሲሉ ፡ እንደ ፡ ተሳሉ ፡ ወደ ፡ ገዳሙም ፡ ሳይገቡ ፡ የተነጠፈውን ፡ ሥጋጃ ፡ ብዙ ፡
ወርቅ ፡ ጨምረው ለታቦቱ ፡ ሰጡ ፡ ይባላል ።

※ ※ ※

ከዚህ ፡ ሁሉ ጋራ ፡ ቋረኛ ፡ ኢያሱ ፡ የቤተ ፡ ክህነትን ፡ ሰው ፡ በጣም ፡
ያከብሩ ፡ ነበርና ፡ ሊቃውንቱን ፡ የወርቅ ፡ ጫማ እንዲያደርጉ ፡ ፈቀዱላቸው ። የሊቃው
ንቱም ፡ ልብስ ፡ እንዳያድፍ ፡ በከተማው ፡ ዙሪያ ፡ እንዶድ ፡ በብዙ ፡ ተተክሎ ፡
ካህኑ ፡ ሁሉ ፡ በዚያ ፡ ልብሱን ፡ እያጠበ ፡ ንጹሕ ፡ ይለብስ ፡ ነበር ። በዚያ ፡
ዘመን ፡ አዳፋ ፡ ልብስ ፡ የሚለብስ ፡ እንደ ፡ ነውረኛ ፡ ይቈጠር ፡ ነበር ፡
ይባላል ።

ደግሞ ፡ በደንቀዝ ፡ በታች በይፋግ ፡ በላይ ፡ ቃሮዳ ፡ የሚባለውን ፡ ያን
ዱን ፡ ደጃዝማች ፡ አገር ፡ በትእዛዝ ፡ በመላው ፡ ወይን ፡ አስተክለው ፡ ብዙ ፡
የወይን ፡ ፍሬ ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በጐንደር ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡
እንደ ፡ ውሃ ፡ እየተጠጣ ፡ ተድላና ፡ ደስታ ፡ በዝቶ ፡ ነበረ ፡ ይባላል ። እቴጌ ፡
ምንትዋብም ፡ እንደ ፡ ልጃቸው ፡ ካህናን ከመውደዳቸው ፡ የተነሣ ፡ እሑድ ፡
እሑድ ፡ ካህናን ፡ ብቻ ፡ ግብር ፡ ሲያበሉና ፡ የወይን ፡ ጠጅም ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡
ሲጠጣ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሊቃውንቱም ፡ በየተራ ፡ እየተነሡ ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋ
ብንና ፡ ንጉሡን ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱን ፡ እንዲሁም ፡ ካለፉት ፡ ነገሥታት ፡
ስመ ፡ ጥሩዎቹን ፡ የሚያሞግስ ፡ ቅኔ ፡ ሲቀኙ ፡ ወረብ ፡ ሲወርቡ ፡ ይውሉ ፡
ነበር ፡ ይባላል ።

እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ በጐንደር ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ከደኅቡሽ ፡ ቃጠሎ ፡ ተርፎ ፡
ፍራሹ ፡ የሚያስደንቀውን ፡ የቅድስት ፡ ቍስቋምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዘመ
ናቸው ፡ አሠሩ ። ለዚህም ፡ ሥራ ፡ ሺሕ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ከራሳቸው ፡ እን
ዳወጡ ፡ ይኸም ፡ የማይበቃ ፡ ቢሆን ፡ የጣታቸውን ፡ ቀለበት ፡ አውልቀው ፡
እንደጨመሩ ፡ ታሪካቸው ፡ ይገልጻል ። ሥራውም ፡ አልቆ ፡ የታቦቷ ፡ አገባ
ብና ፡ ክብረ ፡ በዓል ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ሁኔታ ፡ ተከበረ ።

ስለዚህ ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ የኅዳር ፡ ቍስቋም ፡ በዋለችበት ፡ ቀን ፡
በዚሁ ፡ በዓል ምክንያት ፡ የቍስቋምንና ፡ የሌላውንም ፡ አድባራትና ፡ ገዳማት ፡
ቀሳውስትና ፡ ካህናት ፡ ጠርተው ፡ ትልቅ ፡ ግብር ፡ ሲያበሉ ፡ ‹ሁል ፡ ጊዜ ፡
በንግግርም ፡ በመጠጥም ፡ ካህን ፡ ያሸንፈኛል ፡ ዛሬ ፡ ግን እኔ ፡ ሳላሸንፍ ፡ አል
ሰደውምና ፡ ዋናውንም ፡ የስርቆሹንም ፡ በር ፡ ደኅና ፡ አድርጋችሁ ፡ ዝጉ ፡ ለካ
ህኑም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እየደጋገማችሁ ፡ ስጡ› ፡ ብለው ፡ እቴጌ ፡ አሳላፊዎ
ቻቸውን ፡ አዘዙ ፡ ይባላል ።

ካህኑ ፡ ከበላ ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እየጠጣ ፡ ሽንቱ ፡ መጣበት ፤ እሥጋ
ጃቸው ፡ ላይ እንዳይሸና ፡ ብልግና ፡ ነው ፡ እንዳይወጣም ፡ በሩ ፡ ሁሉ ፡ በጥ

ብቅ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ ተዘጋ ፡ አልተቻለም ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ካህኑ ፡ እርስ ፡ በርሱ እየተጨነቀ ፡ የሚያደርገውን ፡ አጣ ። በዚህ ፡ መካከል ፡ ከተጨናቂዎቹ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ አለቃ ፡ ኢሳይያስ ፡ የሚባል ፡ ሊቅ ፡ እንዳደገደገ ፡ ተነሥቶ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንድጠይቅ ፡ ይፈቀድልኝ ፡ ብሎ ፡ እቴጌን ፡ ለመነ ። እቴጌም ፡ ተፈቅዶልኻልና ፡ ጠይቅ ፡ አሉት ፤ እሱም ፡ ፳፻ና ፡ ፳፻ ፡ ሲጋጠም ፡ ስንት ፡ ይሆናል ? ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። እሳቸውም ፡ ሺ ፡ ነዋ ፡ ብለው ፡ መለሱ ። አለቃ ፡ ኢሳይያስም ፡ ከእቴጌዩቱ ፡ ይህችን ፡ ቃል ፡ ሰምቶ ፡ ከነጠቀ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጓደኞቹ ፡ ወደ ፡ ካህናቱ ፡ ፊቱን ፡ አዙሮ ፡ ሺነዋ ፡ ብለውኻል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ የተቸገረው ፡ ሁሉ በየተቀመጠበት ፡ ምንጣፍ ላይ ፡ ሸና በት ። እቴጌዩቱም ፡ አለቃ ፡ ኢሳይያስ ፡ ባመጣው ፡ የነገር ፡ ብልኅት ፡ ተደንቀው ፡ ሸልመው ፡ ሰደዱት ፡ ይባላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፭፮ ።

የሸዋው ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አብዬ ፡ ግብር ፡ ስለ ፡ መከልከላቸው ፤ ‑ ከጐንደር ፡ በተላኩትና ፡ በመርድ ፡ አዝማች ፡ አብዬ ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ጦርነት ።

---

እዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ ስንደርስ ፡ በዝርዝር ፡ የሸዋን ፡ ባላባቶች ፡ ታሪክ ፡ ለመተረክ ፡ ምክንያት ፡ ነበረን ፤ ነገር ፡ ግን የጐንደሩን ፡ መንግሥት ፡ ታሪክ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ሳናደርስ ፡ በመካከሉ ፡ የሸዋን ፡ ታሪክ ፡ መገርመር ፡ ላጻጻፉ ፡ መልክ ፡ ላንባቢም ፡ ግልጽ ፡ ንባብ ፡ አይሰጠውም ፡ በማለት ፡ የሸዋን ፡ የባላባቶች ፡ ታሪክ ፡ ይኸን ፡ የያዝነውን ፡ በጐንደር ፡ ያሉትን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ ከጨረስን ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንጨምረዋለን ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ ጊዜ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አብዬ ፡ ግብር ፡ ከልክለው ፡ መዋጋታቸውን ፡ እንጠቅሳለን ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ አብዬ ፡ እንዳባቶቻቸው ፡ ለጐንደር ፡ ነገሥታት ፡ መገበርን ፡ እንቢ ፡ አሉ ፤ ምናልባት ፡ እኔም ፡ ከልብነ ፡ ድንግል ፡ ልጅ ፡ ከአቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ እወለዳለሁ ፡ በማለት ፡ ወይም ፡ የጐንደሩ ፡ መንግሥት ፡ መዳከሙንና ፡ የርሳቸውን ፡ መበርታት ፡ ተመልክተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አይታወቅም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ግብር ፡ መከልከላቸውን ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ አየሌ ፡ ወሰኑን ፡ ራስ ፡ ወዳጆን ፡ አጎታቸውን ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ልዑልን ፡ ጨምረው ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አብዬን ፡ እንዲወጉ ፡ በሺሕ ፡ ፯፻፴ ፡ ዓ ፡ ም ? ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ላኳቸው ፤ እነዚህም ፡ እንደ ፡ ተላኩ ለውጊያ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ መጡ ። አብዬም ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ባያታቸው ፡ በአቤቶ ፡ ነጋሢ ፡ ከተማ ፡ በተለይ ፡ በዐይኔ ፡ ላይ ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበርና ፤ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ጦርነት ፡ ገጥመው ፡ ወዲያው ፡ ድል ፡ አደረጓቸው ። ከጦርነቱም ፡ ራስ ፡ ወዳጆ ፡ ብቻ ፡ ሲያመልጡ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ልዑልና ፡ አየሌ ፡ ወሰኑ ፡ ከሞት ፡ ከተረፉት ፡ ጭፍሮቻቸው ፡

ጋራ ፡ ተማረኩ ። በዚህም ፡ ጦርነት ፡ ብዙ ፡ የጐንደር ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ መጣሪያ ፡ ድንኳኑና ፡ ሥራ ፡ ቤቱ ፡ ነጋሪትና ፡ መለከት ፡ እንቢልታና ፡ ጥሩምብ ፡ ከ፷፻ ፡ ጠመንዣ ፡ (ባለመጣቀሻ ፡ ነፍጥ) ፡ ጋራ ፡ ተማረከ ።

በኋላ ፡ ግን ፡ በመልክት፡ዕርቅ ፡ ተደርጎ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ልዑል ፡ ወደ ፡ ጐንደር ሲመለሱ ፡ የቀሩት ፡ የጐንደር ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ የጁ ፡ ብልኅት ፡ ያላቸው ፡ የፊላሻ ፡ ተወላጆች ፡ በፈቃዳቸው ፡ ሸዋ ፡ ከመርድ ፡ አዝማች ፡ አብዬ ፡ ማዕርግና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ እየተሰጣቸው ፡ ቀሩ ። ለአየሊ ፡ ወሰኑ ፡ የካራ ፡ መገን ፡ አበጋዝነት ፡ ተሰጠው ።

※ ※

ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ በሸዋ ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ የእምቢታ ፡ ሁኔታ ፡ ምንም ፡ ቢደርስ ፡ ርሳቸው ፡ ግን ፡ በጐንደር ፡ ሰላማዊ ፡ ሥራቸውን ፡ ይቀጥሉ ፡ ነበር ፤ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ የጐንደርን ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ ቅጥሩንም ፡ አሳደሱ ። በዙሪያውም ፡ ለዚያ ፡ ጊዜ ፡ ድንቅ ፤ የሆነውን ፡የአትክልት ፡ ሥፍራ፡አዘጋጁ ። ባትክልቱም ፡ ሥፍራ፡ ወይን ፡ ሌላም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሚሸት ፡ አትክልት ፡ አስተከሉ ፡ ይኸንንም ፡ ያዘጋጁ ፡ የነበሩት ፡ ከእስያ ፤ ከየመን ፤ ከግብጽ ፡ እየመጡ ፡ ጐንደር ፡ የተቀመጡት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ከገሩ ፡ ተወላጅ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ነው ፡ ይባላል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ዛሬ ፡ የሱዳን ፡ ግዛት ፡ ወደሚባለው ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ ሄደው ፡ ለማስገበርና ፡ ግዛታቸውን ፡ ለማስፋት ፡ ጕዞ ፡ ዠመሩ ። የዛሬውንም ፡ የኢትዮጵያን ፡ የግዛት ፡ ወሰን ፡ አትባራን ፡ አልፈው ፡ ስናር ፡ ከተማ ፡ በደረሱም ። ጊዜ ወታደሮቻቸው ፡ ከተማውን ፡ እያቃጠሉ ፡ ዘረፉት ፤ አገሬውም ፡ ገሚሱ ፡ ገበረ ፤ የቀረውም ፡ እየሸሸ ፡ ሄደ ። የስናርም ፡ ባላባት ፡ ባዲ ፡ ኢብን ፡ ሻሉክ ፡ ይባል ፡ ነበር ። ርሱም ፡ በመዠመሪያ ፡ እዋጋለሁ ፡ ብሎ ፡ ወታደሩን ፡ ይዞ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ጦር ፡ መጥቶ ፡ የስናርን ፡ ሜዳ ፡ ሲመላው ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ ፍርሃት ፡ አደረበት ፤ መግጠሙንም ፡ ትቶ ፡ ሸሸና ፡ ስናር ፡ ተበዘበዘ ።

በኋላ ፡ ግን ፡ የንጉሡ፡ጦር፡እሁለት ፡ ተከፍሎ ፡ ለየብቻው፡ሲሄድ ፡ በሩቅ ፡ ይመለከት ፡ የነበረው ፡ ሐማርስ ፡ የሚባለው ፡ የዳርፉር ፡ ባላባት ፡ ባንደኛው ፡ ወገን ፡ ግመሉንና ፡ ፈረሱን ፡ አስጭኖ ፡ ደረሰና ፡ ውጊያ ፡ ገጠመ ። ኢትዮጵያውያንም፡ መልሰው ፡ ይዋጉ ፡ ዠመር ፤ በመጨረሻም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከስናር ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ አፈገፈጉ ። ንጉሡ ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ ጦርነት ፡ ሳይመለከቱ ፡ ባንደኛው፡ ክፍል ፡ በጦር ፡ ሠራዊት ፡ ታጅበው ፡ ላይኛውን ፡ የአትባራን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግረው ፡ በሰቲት ፡ አልፈው ፡ ተከዜ ፡ ደረሱ ፤ ከዚያም ፡ ተመልሰው ፡ ጐንደር ፡ ገቡ ።

## ምዕራፍ ፳፯ ።

### ስለ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ሥዑል ፤-እቴጌ ፡ ምንትዋብና ፡ ምልምል ፡ ኢያሱ ፤ ስለ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ ዕረፍት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሺሕ ፡ ፯፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጳጳሱ ፡ አባ ፡ ክርስቶዶሉ ፡ ሲሞቱ፡ በርሳቸው ፡ ምትክ ፡ ጳጳስ ፡ ለማስመጣት ፡ መልክተኞች ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ተላኩ ። ከነ ንደርም ፡ ተነሥተው ፡ ምጥዋ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ቱርኮች ፡ ምጥዋ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ዕቃ ዘርፈው ፡ በታላቅ ፡ ችግር ፡ አሳለፏቸው ፡ ማለት ፡ ተሰማ ፤ እንዲሁ ፡ እስክንድርያ፡ ደርሰው ፡ ጳጳሱን ፡ ይዘው ፡ ሲመጡ ፡ ቱርኮች ፡ ጳጳሱን ፡ ጭምር ፡ አስረው ፡ አጉላሏቸው ።

ንጉሡም ፡ የዚህን ፡ ወሬ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ የትንቤኑን ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ሥዑልን ፡ የአርኪቆውን ፡ ናይብ ፡ (ገዥ) ፡ ውጋ ፡ ብለው ፡ ላኩባቸው ። ነገር ፡ ግን ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ውስጡን ፡ ከናይብ ፡ ጋራ ፡ ስምምነት ፡ ነበራቸውና ፤ እሺ ፡ ብለው፡ ነገ ፡ ተነገ ፡ ወዲያ ፡ እያሉ ፡ ጊዜ ፡ ያስረዝሙ ፡ ገመር ። ስለዚህ ፡ ንጉሡ ፡ ራሳ ቸው ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ጉዞ ፡ አደረጉ ፤ አሳባቸውም ፡ ቢቻል ፡ የራስ ፡ ሚካኤልን ፡ አኳኋን ፡ ለማወቅና ፡ ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ እሺ ፡ ቢሉ ፡ ከንጉሡ ፡ ርዳታ ፡ ተጨም ሮላቸው ፡ ሄደው ፡ ናይብን ፡ እንዲወጉ ፡ ለማድረግ ፤ እንቢ ፡ ቢሉም ፡ ራሳቸውን፡ ራስ ፡ ሚካኤልን ፡ ለመውጋት ፡ ነበር ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ በንድ ፡ ሥፍራ ፡ ተቀምጠው ፡ የራያና ፡ ያዘቦን ፡ ጋላ ፡ ውስጡን ፡ እየቀሰቀሱ ፡ የንጉሡን ፡ ጦር ፡ ለማስወጋት ፡ ይሰብኩ ፡ ገመር ። ጋሎቹም ፡ ዘረፋ ፡ ለማግኘት ፡ ጭምር ፡ በፈረስና ፡ በእግር ፡ እየመጡ ፡ ከንጉሡ ፡ ከንድ ፡ ክፍል ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ገምረው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ አፍታ ፡ ድል ፡ ሆኑና ፡ በመዝረፍ ፡ ፈንታ የእነሱ ፡ ከብትና ፡ እኽል ፡ ተዘረፈ ፡ የእንደርታውም ፡ ገዥ ፡ ወልዱ ፡ ከራስ ፡ ሚካ ኤል ፡ ጋራ ፡ ውጊያ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አብሬ ፡ እዋጋለሁ ፡ ብለው ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ አብረው ፡ ነበሩ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ንጉሡ ፡ ደም ፡ ከማፍሰስ ፡ በፊት ፡ ምና ልባት ፡ ጥሪዬን ፡ ሰምቶ ፡ ይመጣ ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ መጥተኽ ፡ እንድንገናኝ ፡ ብለው ፡ ለራስ ፡ ሚካኤል ፡ ላኩባቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ለመልክቱ ፡ ምንም ፡ መልስ ሳይሰጡ ፡ እሳቸውም ፡ ሳይመጡ ፡ ስለ ፡ ቀሩ ፡ እንቢተኛነታቸው ፡ ታወቀና ፡ ንጉሡ ከነሠራዊታቸው ፡ ወደ ፡ ዐድዋ በተጠጉ ፡ ጊዜ ፡ ከያለበት ፡ የንጉሡ ፡ ጦር ፡ ተጠ ራቅሞ ፡ ዐድዋ ፡ ላይ ፡ ተሰበሰበና ፡ ታላቅ ፡ ሰልፍ ፡ ተደረገ ።

ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ዠግንነታቸው ፡ የታወቀ ፡ ቢሆን ፡ እንደ ፡ አሸዋ ፡ የበረከተውን ፡ የንጉሡን ፡ ጦር ፡ ለመመለስ ፡ ዐቅማቸው ፡ እንደማይፈቅድ ላቸው ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡ ሁሉን ፡ ትተው ፡ ገንዘብና ፡ ቤት ፡ ሰባቸውን ፡ ይዘው ፡ ከጥቂት ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ሰማያት ፡ ወደሚባለው ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ወጥ ተው ፡ ተቀመጡ ።

የንጉሡም ፡ ጦር ፡ አራት ፡ ላይ ተከፍሎ ፡ ባራት ፡ መንገድ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ መጠጋት ፡ መገርመሩን ፡ ስለ ፡ ተመለከቱ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ፍጻሜያቸው ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ ያኽል ፡ ቄጠሩት ። ውጊያውንም ፡ አቁመው ፡ ታርቄ ፡ ልግባ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አማላጅ ፡ ላኩ ፡ አማላጆቹም ፡ እንዲገቡ ፡ ፈቅደውልዎታል ፡ ብለው ፡ ነገሯቸው ። ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ ባንገታቸው ፡ ደንጊያ ፡ አስረው ፡ መጡና ፡ ተገዥነታቸውን ፡ ለንጉሡ ፡ ለዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ አምነው ፡ ገቡ ።

ንጉሡም ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ በርሳቸው ፡ ቀስቃሽነት ፡ በራያ ፡ ጋላና ፡ በንጉሡ ፡ ወታደሮች ፡ መከከል ፡ የፈሰሰው ፡ ደም ፡ በርሳቸው ፡ ሕይወት ፡ ለመበቀል ፡ አስበው ፡ ሊያስገድሏቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ታላላቆቹ ፡ ሰዎች ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ዠግና ፡ ላንድ ፡ ቀን ፡ የሚሆን ፡ ነውና ፡ አይገደልም ፡ ብለው ፡ ለንጉሡ ፡ ልመና ፡ አቀረቡላቸው ። ንጉሡም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ሞቱ ፡ ቀረና ፡ ታሰሩ። ጥቂትም ፡ ወራት ፡ እንደ ፡ ታሰሩ ፡ ከእሥራታቸው ፡ ተፈቱና ፡ እንዲያውም ፡ ከትግሬ ፡ ወደ ፡ ጎንደር ፡ መጥተው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የንጉሡ ፡ አማካሪና ፡ ባለሟል ፡ ሆነው ፡ ኖሩ ።

፨ ፨ ፨

እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ዐፄ ፡ በካፋን ፡ አግብተው ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱን ፡ እንደ ፡ ወለዱ ፡ በወጣትነታቸው ፡ ጊዜ ፡ ባለቤታቸው ፡ ዐፄ ፡ በካፋ ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ደንበኛ ፡ ባል ፡ ሳያገቡ ፡ በልጃቸው ፡ በ፲ኛው ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ንግሥት ፡ ሆነው ፡ ከልጃቸው ፡ ጋራ ፡ ይገዙ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ደንበኛ ፡ ባል ፡ ባይኖራቸው ፡ የታላቅ ፡ ወለተ ፡ እስራኤልን ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ እንደ ፡ ምልምል ፡ አስቀምጠውት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ከዚሁ ፡ የተነሣ ፡ የሁለቱን ፡ ግንኙነት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ስላወቀ ፡ ኢያሱን ፡ «ምልምል ፡ ኢያሱ» ፡ እያሉ ፡ እያሽሟጠጡ ፡ ይጠሩት ፡ ዠመር ። እቴጌዪቱም ፡ ይኸንኑ ፡ ስለ ፡ ሰሙ ፡ "ምልምል ፡ ኢያሱ" ፡ ተብሎ ፡ እንዳይጠራ ፡ የግራዝማችነት ፡ ማዕርግ ፡ ሰጡት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ "ምልምል ፡ ኢያሱ" ፡ ሲለው ፡ ይገኛል ። በዚህ ፡ ዐይነት ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብና ፡ ምልምል ፡ ኢያሱ ፡ በይፋ ፡ ሳይሆን ፡ በድብቅ አብረው ፡ ሲኖሩ ፡ ሦስት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ወለዱ ፡ ስማቸውም ፡ ወይዘሮ ፡ አልጣሽ ፡ ወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ እስራኤል ፡ (ዳግሚት) ፡ ይባላል ፡ እነዚህም ፡ ሦስቱ ፡ እንደናታቸው ፡ እንደ ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ በመልካቸው ፡ ቅርጽና ፡ በውበታቸው ፡ በጣም ፡ የተደነቁ ፡ ነበሩ ፡ ይባላል ። ከሦስቱም ፡ የወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ ቁንጆና ፡ የተደነቀ ፡ መሆኑን ፡ ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ በ፪ኛው ፡ ቮሊዩም ፡ ከገጽ ፡ ፪፻፲-፪፻፳ ፡ ባለው ፡ ውስጥ ፡ እያለፈ ፡ ይጠቅሳል ። እርሱም ፡ በዘመኑ ፡ የነበረ ፡ ያይን ፡ ምስክር ፡ የሆነ ፡ ጸሐፊ ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ መገርመሪያ ፡ አዝማች ፡ ነጮን ፡ ፪ኛ ፡ ራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያውን ፡ ፫ኛ ፡ ራስ ፡ ሥዑል ፡ ሚካኤልን ፡ ማግባታቸውን ፡ ይጽፋል ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ለምልምል ፡ ኢያሱ ፡ የእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ባለቤት ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አባት ፡ ዐፄ ፡ በካፋ ፡ አጎት ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ የእቴጌንና ፡ የምልምል ፡ ኢያሱን ፡ ግንኙነት ፡ የሚያውቅ ፡ ሁሉ ፡ እያወራው ፡ ትልቅ ፡ ሐሜት ፡ ተነሥቶ ፡ ነበር ፡ (1) ። ዐፄ ፡

(1) እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ በዚሁ ፡ ሥራቸው ፡ ሱባኤ ፡ ገብተው ፡ በብረት ፡ ውሃ ፡ ወደ ፡ እመቤታችን ፡ እየጸለዩ ፡ ንስሐ ፡ ተቀብለው ፡ እመቤታችንም ፡ በራእይ ፡ መርቆሬዎስን ፡ ባልደረባ ፡ እንደ ፡ ሰጠቻቸውና ፡ እንደ ፡ ማረቻቸው ፡ ከዘርሽም ፡ አልጋ ፡ የሚወርስ ፡ አላሳጣሽም ፡ እንዳለቻቸው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ ይናገራል ።

ኢያሱም ፡ ከዚሁ ፡ የተነሣ ፡ ከእናታቸው ፡ ጋራ ፡ ተቀያየሙ ፡ ከምልምል ፡ ኢያሱም ፡ የከረረ ፡ ጠብ ፡ አደረጉ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በጠቡ ፡ መከከል ፡ ገላጋይ ፡ እየገባ ፡ ያስታርቃቸው ፡ ነበር ። ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ግን ፡ ቂማቸውን ፡ አልተዉ ፡ ኖሮ ፡ ከዕለታት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ምልምል ፡ ኢያሱን ፡ አስከትለው ፡ ዓሣ ፡ ወዳለበት ፡ ባሕር ፡ ለሽርሽር ፡ አስመስለው ፡ ወሰዱት ፤ እባሕሩ ፡ ዳርም ፡ በቆሙ ፡ ጊዜ ፡ ባሪያቸውን ፡ አዘው ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ አስገፍተው ፡ ጣሉትና ፡ አስገደሉት ። ሬሳው ፡ ግን ፡ በሌላ ፡ ቀን ፡ ከባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ ወጥቶ ፡ ተቀበረ ። ይኸውም ፡ የምልምል ፡ ኢያሱ ፡ አሟሟት ፡ እንዳይታወቅ ፡ በጥብቅ ፡ ተከልክሎ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የምልምል ፡ ኢያሱ ፡ እኅት ፡ በትክክል ፡ ዐውቃ ፡ ኖሮ ፡ የወንድሟን ፡ ደም ፡ ለመበቀል ፡ ጊዜ ፡ ትጠብቅ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ከምልምል ፡ ኢያሱ ፡ የተወለዱትን ፡ እነዚህን ፡ ሦስቱንም ፡ እኅቶቻቸውን ፡ በዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ እንገዛም ፡ ብለው ፡ ላስቸገሯቸው ፡ ባላባቶች ፡ እየዳሩ ፡ ለማስታገሻና ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ለመመሥረት ፡ መሣሪያ ፡ አድርገዋቸው ፡ ነበር ። ከነዚህም ፡ ዋነኛው ፡ ደጃች ፡ ዮሴዴቅ ፡ የሚባለው ፡ የጐጃም ፡ ባላባት ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ ከንጉሡ ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ አድርጓቸው ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ከሦስቱ ፡ እኅቶቻቸው ፡ አንዷቱን ፡ ወለተ ፡ እስራኤልን ፡ ዳሩለት ፡ ከነርሱም ፡ የጐጃሙ ፡ ታላቁ ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተወለዱ ። የቀሩትንም ፡ አልጣሽን ፡ ለስሜን ፡ ባላባት ፡ አስቴርን ፡ ለትግሬ ፡ ባላባት ፡ ለራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያቸው ፡ ዳሯቸውና ፡ በነርሱ ፡ ጋብቻ ፡ ብዙ ፡ ጠላት ፡ ዐረፈላቸው ፡ ይባላል ።

ራሳቸውም ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ እንደ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ አጻጻፍ ፡ ከወሎ ፡ ባላባት ፡ (1) የሚወለዱትን ፡ ውቢት ፡ የሚባሉትን ፡ ክርስትና ፡ አስነሥተው ፡ የክርስትና ፡ ስማቸውን ፡ ወለተ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ አሰኝተው ፡ ስላገቧቸው ፡ ከወሎና ፡ ከየጁም ፡ በዚሁ ፡ ጋብቻ ፡ ለመዛመድ ፡ ቻሉ ፡ ከወሎና ፡ ከየጁም ፡ ብዙዎቹን ፡ እያመጡ ፡ በሥልጣን ፡ ላይ ፡ አስቀመጡ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የጐንደር ፡ ሰው ፡ ጋላዋን ፡ አገባት ፡ እያለ ፡ ሐሜታ ፡ ከማብዛቱ ፡ የተነሣ ፡ ጋብቻውና ፤ የባልና ፡ የሚስቱ ፡ ኑሮ ፡ ኢያሱ ፡ እስኪሞቱ ፡ ድረስ ፡ ገሃድ ፡ ሳይሆን ፡ በድብቅ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ዐፄ ፡ ኢያሱም ፡ ከኝሁ ፡ ከወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ (ውቢት) ፡ ኢዮአስን ፡ ወለዱ ።

ስለዚህ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ በነዚህ ፡ ጋብቾቻቸው ፡ ባላባቶቻቸው ፡ በነደጃች ፡ ዮሴዴቅ ፡ ባኅቶቻቸው ፡ በነራስ ወልደ ፡ ልዑል ፡ እንደዚሁም ፡ በቅርቡ ፡ ከትግሬ ፡ አስመጥተው ፡ ባለሟልና ፡ መከር ፡ ባደረጓቸው ፡ በነራስ ፡ ሥዑል ፡ ሚካኤል ፡ ተከብረውና ፡ ተፈርተው ፡ ኢትዮጵያን ፡ በንጉሥ ፡ ነገሥትነት ፡ ፳፭ ፡ ዓመት ፡ ገዙ ። በዘመናቸውም ፡ መጨረሻ ፡ እነናቡቱ ፡ እነተስፋ ፡ ማሞ ፡ ቢነሡባቸው ፡ ከዙፋን ፡ ሊገለብጧቸው ፡ አልቻሉም ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ የሕይወታቸውን ፡ ፍጻሜ ፡ እግዚአብሔር ፡ በንዲት ፡ ሴት ፡ እጅ ፡ ሊፈጽመው ፡ ፈለገ ። ይህችም ፡ ሴት ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አስገደሉት ፡ የተባለው ፡ የምል ምል ፡ ኢያሱ ፡ እኅት ፡ ነች ። እርሷም ፡ የወንድሟን ፡ ደም ፡ ለመበቀል ፡ ከመብል ፡ ጋራ፡መርዝ ፡ ጨምራ ፡ ዐፄ ኢያሱን ፡ አብልታ ፡ ገደለቻቸውና ፡ በሺሕ ፡ ፲፻፺፯ ፡ ዓ፡ ም፡ ሞቱ ። በመንግሥታቸውም ፡ ልጃቸው ፡ ኢዮአስ ፡ ተተኩ ።

## የዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

### ምዕራፍ ፡ ፳፮ ።

### ዐፄ ፡ ኢዮአስና ፡ ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ቤርሳቤሕ ፤ –የቋረኞችና ፡ የወሎዎች ፡ ክርክር ።

ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ በሺሕ ፡ ፲፻፺፯ ፡ ዓ፡ ም፡ ሲሞቱ ፡ ከወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ (የቀድሞ ፡ ስማቸው ፡ ውቢት) ፡ የተወለዱት ፡ ልጃቸው ፡ ኢዮአስ ፡ መንግሥትን ፡ ያዙ ። ርሳቸውም ፡ መንግሥትን ፡ በያዙ ፡ ጊዜ ፡ እናታቸው ፡ ወለተ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ቀድሞ ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ጊዜ ፡ በሽሽግ ፡ ይቀመጡ ፡ የነበረውን ፡ አሁን ፡ ልጃቸው ፡ ስለ ፡ ነገሡ ፡ በገሃድ ፡ እየወጡ ፡ እየገቡ ፡ በመንግሥቱም ፡ ሥልጣን ፡ መግባት ፡ ፈለጉ ። እንዲያውም ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ጊዜ ፡ ወይዘሮ ፡ ምንትዋብ ፡ እቴጌ ፡ ተብለው ፡ ከልጃቸው ፡ ከኢያሱ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ንግሥት ፡ ይገዙ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አሁንም ፡ እኔ ፡ የእቴጌነት ፡ ማዕርግ ፡ ተሰጥቶኝ ፡ ከልጄ ፡ ከኢዮአስ ፡ ጋራ ፡ ልግዛ ፡ የሚል ፡ አሳብ ፡ አደረባቸው ፡ በዚህ ፡ ይዞታቸው ፡ በሌላውም ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ በመሾም ፡ በመሻሩም ፡ ሥልጣን ፡ ልግባ ፡ ስላሉ ፡ ከልጃቸው ፡ አያት ፡ ከእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ጋራ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጠብና ፡ ክርክር ፡ ተገርመረ ።

አማትና ፡ ምራት ፡ በሆኑት ፡ በሁለቱ ፡ ጠብ ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ተቸገሩ ፤ ቢሆንም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሁለቱም ፡ ወገን ፡ እየሆኑ ፡ ይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ለናታቸው ፡ ለወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ማድላታቸው ፡ አልቀረም ። የሆነ ፡ ሆኖ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብና ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ቋረኞች ፡ በንድ ፡ ወገን ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስና፡ እናታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ ሆነው ፡ የሚያደርጉት፡ ጠብና ፡ ክርክር ፡ በየቀኑ ፡ የበረታ ፡ ሆነ ፤ ካሁን ፡ አሁን ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች፡ሊዋጉ፡ ነው ፡ እየተባለም ፡ ይፈራ ፡ ዠመር ። ስለዚህ ፡ በወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ቤርሳቤሕና ፡ በዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ጥሪ ፡ የወለተ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ወንድሞች ፡ ልበና ፤ ብርሌ ፡ የሚባሉት ፡ ሺሕ ፡ ፈረሰኛ ፡ አስከትለው ፡ ጦርነት ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለእኅታቸው ፡ ለመርዳት ፡ ከወሎ ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ጐንደር ፡ ገብተው ፡ ተቀመጡ ። እን

(1) የውጭ ፡ አገር ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ውቢትን ፡ ከየጁ ፡ ቶሎማ ፡ ከሚባለው ፡ የነገድ ፡ ባላባት ፡ እንደሚወለዱ ፡ አንዳንዶቹም ፤ ከራያ ፡ አዘቦ ፡ እንደሚወለዱ ፡ ይጽፋሉ ፡ ምናልባት ፡ ታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ የጁን ፡ ወይም ፡ ራያን ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ ግዛት ፡ ደባልቆ ፡ በጠቅላላው ፡ ወሎ ፡ ብሎ ፡ ጠቅሶት ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ እኛም ፡ ባሁኑ ፡ ጽሑፋችን ፡ ውቢትንም ፡ ወንድሞቻቸውንም ፡ ወሎዎች ፡ እያልን ፡ ጽፈነዋል ።

ደዚሁም ፡ እያደር ፡ የፈረሰኛም ፡ የእግረኛም ፡ የጋላ ፡ ወታደር ፡ በያለቃው ፡ እየሆነ፡ ከወሎም ፡ ከየጁም ፡ ከራያም ፡ እየመጣ ፡ የጐንደር ፡ ከተማ ፡ በጋሎች ፡ ተመላ ፡ እነብርሌ ፡ እነልበ ፡ ከባታቸው ፡ ከአሚዞ ፡ ጋራ ፡ በሹመትና ፡ በሥልጣን ፡ እየገቡ ተደላደሉ ። የከተማውም ንግግር ፡ አብዛኛው ፡ ወደ ፡ ጋልኛ ፡ ቋንቋ ፡ ለመዞር፡ቀረበ። ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስም ፡ ያባታቸውን ፡ የኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድን ፡ ወገን፡ ያማርኛውን ፡ ቋንቋ ፡ ችላ ፡ እያሉ ፡ ንግግርና ፡ ጨዋታቸውን ፡ በናታቸው ፡ ወገኖች፡ ቋንቋ ፡ በጋልኛ ፡ አደረጉ ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ የተመለከተ ፡ ለጥንቱ ፡ ሃይማኖትና ፡ ቋንቋ ፡ ልማድና ፡ ሥርዓት ፡ ቀናተኛ ፡ የሆነው ፡ የጐጃም፡ የጐንደር ፡ የስሜን ፡ የትግሬ ፡ መኳንንትና ፡ ሊቃውንት ፡ በዐፄ ፡ ኢዮአስ፡ ላይ ፡ አንጐራጐረ ፡ ገሚሶቹም ፡ አሁኑኑ ፡ እንበለውና ፡ የኢዮአስን ፡ መንግሥት ፡ ከነጋሎቹ ፡ ገልብጠን ፡ የፋሲልን ፡ የኢያሱን ፡ የበካፋን ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ጥንት ፡ ልማድ ፡ መልሰን ፡ እናቋቁም ፡ የማለት ፡ አሳብ ፡ መጣባቸው ። አሳባቸውን ፡ ግን ፡ በቶሎ ፡ ለመፈጸም አልቈረጡም ። ስለዚህ ፡ ለጊዜው ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ዘቻና፡ ቂማቸውን ፡ በልባቸው ፡ ይዘው ፡ ውስጡን ፡ እየተማሙ ፡ ላዩን ፡ አብረው ፡ እየኖሩ ፡ በጊዜው ፡ ለተቀባው ፡ ንጉሥ ፡ እየታዘዙ ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብና ፡ ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ቤርሳቤሕንም ፡ በየበኩላቸው ፡ እያከበሩ ፡ ቈዩ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ውስጡን፡ የሥልጣን ፡ የደረጃ ፡ ሽሚያና ፡ የመንፈስ ፡ ጦርነት ፡ በመካከላቸው ፡ አልጠፋም ፡ ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ የእንደራሴነቱን ፡ ሥፍራ ፡ ለመያዝ ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ ጥረት፡ ተደርጓል ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ከወሎዎቹ ፡ አንዱ ፡ የወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ወንድም ፡ የዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ አጎት ፡ ብርሌ ፡ እንዲይዝ ፡ ታስቦ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን፡ የጐንደር ፡ መኳንንት ፡ ነገሩን ፡ ስላልተቀበለው ፡ ይልቁንም ፡ የትልቋ ፡ እመቤት፡ የእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ድምፅና ፡ ፈቃድ ፡ ኀይል ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ የእንደራሴነቱ ፡ ሥልጣን ፡ ከእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ወንድም ፡ ከራስ ፡ ወልደ፡ ልዑል ፡ እጅ ፡ እስኪሞቱ ፡ ድረስ ፡ አልወጣም ። ራስ ፡ ወልደ ፡ ልዑልም ፡ እንኳ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ በእቴጌ ፡ ምንትዋብና ፡ በቋረኞች ፡ አሸናፊነት ፡ (ተጫኝነት) ፡ የራስ ፡ ወልደ ፡ ልዑል ፡ እንደራሴነት ፡ ለታናሽ ፡ ወንድማቸው ፡ ለራስ ፡ ኤሽቴ ፡ (1) ተላለፈ፡ ኤሽቴም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የዳሞት ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ነበረ ።

ኤሽቴ ፡ የዳሞት ፡ ገዥና ፡ በኋላም ፡ እንደራሴ ፡ በተባለበት ፡ ዘመን ፡ ጃዊ ፡ የሚባሉት ፡ የበረና ፡ ጋሎች ፡ ስለ ፡ ሸፈቱ ፡ እነሱን ፡ ለመውጋት ፡ የደጃች ፡ ወሬኛን፡ ልጅ ፡ ፋሲልን፡ ይዞ፡ ጋሎቹን ፡ ሊወጋ ፡ ሄደ፤ የፋሲልም፡ ዘር ፡ ጋላ፡ በመሆኑ፡ ምንም ፡ እንኳ፡ ራስ ፡ ኤሽቴን ፡ ተከትሎ ፡ ጋሎቹን ፡ ለመውጋት ፡ ቢሄድ ፤ ጋሎቹ ፡ በራስ ፡ ኤሽቴ፡ ጦር ፡ እንዲሸነፉ ፡ አይፈልግም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ውስጡን ፡ ከጋሎቹ ፡ ጋራ ፡ እየተላላከ ፡ ለራስ ፡ ኤሽቴ ፡ የሚያደርገውን ፡ የጦርነት ፡ ርዳታ ፡ በልግም ፡ ይዞት ፡ ነበር ፡ ይባላል ፡ እነብርሌም ፡ ራስ ፡ ኤሽቴን ፡ የሚገድሉ ፡ ወታደሮች ፡ በስውር ፡

(1) ስሙ ፡ እሸቴ ፡ እስቴ ፡ ኤሽቴ ፡ እየተባለ ፡ በመለያየት ፡ በብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፎል ፡ ሳቤሊ ፡ ኤስቴ ፡ ሲል ፡ ብሩስ ፡ ኤሽቴ ፡ ስለሚል ፡ በዘመኑ ፡ አቅራቢያ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ይታመን ይሆናል ።

ልከው ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ ጦርነቱ ፡ ተዠምሮ ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡
ጋሎቹ ፡ አሸንፈው ፡ ራስ ፡ ኤሽቴን ፡ ሲገድሉ ፡ ፋሲልን ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ተዉት ፡
ይባላል ። አንዳንዶቹም ፡ ኤሽቴ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ከጦርነቱ ፡ መልስ ፡ የወታደሩን ፡
ሰልፍ ፡ ሲመለከት ፡ እንብርሌ ፡ የላኩት ፡ ፩ ፡ ወታደር ፡ አዘንግቶ ፡ ገደለው ፡ ይላሉ ።
የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ራስ ፡ ኤሽቴ ፡ ሞቶ ፡ የዚህን ፡ ሁኔታ ፡ ከጦርነቱ ፡ መልስ ፡ ዐፄ ፡ ኢዮ
አስ ፡ ስለ ፡ ሰሙ ፡ በጣም ፡ ተናደዱ ። ራስ ፡ ኤሽቴንም ፡ እርሱ ፡ በትንኰል ፡ እንዳ
ስገደለ ፡ እኔም ፡ ፋሲልን ፡ ገድዬ ፡ የሟቹን ፡ ደም ፡ መበቀል ፡ አለብኝ ፡ ብለው ፡
ቈረጡ ። ነገር ፡ ግን ፡ የቋረኛው ፡ የራስ ፡ ኤሽቴ ፡ ሞትና ፡ የጋሎቹ ፡ ማሸነፍ ፡ ደስ ፡
የሚላቸው ፡ ወሎዬዎቹ ፡ ብርሌና ፡ ልበ ፡ በመካከል ፡ ገብተው ፡ "እሱ ፡ አልገደ
ለም ። በምን ፡ ምክንያት ፡ ያላገባብ ፡ ይገደላል» ፡ ብለው ፡ ንጉሡን ፡ አባብለው ፡
አስማሩት ። እንዲያውም ፡ የቀድሞ ፡ ያባቱን ፡ ግዛት ፡ ዳሞትን ፡ አስመርቀው ፡
ወደ ፡ ግዛቱ ፡ ሰደዱት ።

እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ሁኔታ ፡ ቋረኞችን ፡ እንደሚያሳዝናቸው ፡ የታወቀ ፡
ነው ። የቋረኞች ፡ መሪዎችና ፡ ትምክህቶች ፡ እነራስ ፡ ወልደ ፡ ልዑል ፡ እነራስ ፡
ኤሽቴ ፡ ሲሞቱ ፡ የወደ ፡ ፊቱ ፡ ጥቃት ፡ እንደ ፡ ተቃረበ ፡ ይሰማቸው ፡ ዠመር ፡
አሁንም ፡ ቢሆን ፡ እንደራሴነቱ ፡ ከቋረኞች ፡ እጅ ፡ ወጥቶ ፡ ለወሎዎች ፡ አይተላ
ለፍም ፡ ለማለት ፡ የእንደራሴነቱ ፡ ሥፍራ ፡ ለእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ልጅ ፡ ለወይዘሮ ፡
አስቴር ፡ ባል ፡ ለራስ ፡ ማርያም ፡ በሪያው ፡ ተላለፈ ። እሳቸውም ፡ አሳባቸውንም ፡
አገልግሎታቸውንም ፡ ወደነእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ስላደረጉና ፡ ከንጉሡ ፡ ከዐፄ ፡
ኢዮአስ ፡ ጋራ ፡ ሳይስማሙ ፡ ስለ ፡ ቀሩ ፡ ተሻሩ ። በመጨረሻም ፡ በንጉሡ ፡
ፈቃድ ፡ አጎታቸው ፡ ብርሌ ፡ ስለ ፡ ተሾመ ፡ መጨረሻውን ፡ ወሎዎች ፡ እንዳሸ
ነፉ ፤ ቋረኞች ፡ እንደ ፡ ተሸነፉ ፡ ተቈጠረ ። ቢሆን ፡ በመጨረሻ ፡ ሁሉንም ፡ አሸ
ንፈው ፡ የእንደራሴነቱን ፡ ሥልጣን ፡ የሚይዙ ፡ ነገዳቸው ፡ ከሁለቱ ፡ ወገን ፡ ያል
ሆኑት ፡ የትግሬው ፡ የራስ ፡ ሚካኤል ፡ የእንደራሴነት ፡ ጊዜ ፡ በመድረሱ ፡ ቋረ
ኞች ፡ አማሮቹ ፤ ወሎዎች ፡ ጋሎቹ ፡ በሥልጣን ፡ ምክንያት ፡ የሚያደርጉት ፡ ጠብና ፡
ክርክር ፡ የመጨረሻውን ፡ ውድቀት ፡ አግኝቶ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ በሽረት ፡ ዕረፍ
ታቸውን ፡ ሊያገኙ ፡ ነው ። መንፈሳቸው ፡ እንኳ ፡ ለማረፍ ፡ ባይችል ፡ እነራስ ፡
ጐሹ ፡ እነደጃች ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ እተነሡበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የራስ ፡ ሚካኤል ፡
ኀይለኝነትና ፡ ጥብቅነት ፤ ዘዴኛነትና ፡ አስተዳዳሪነት ፡ ጨቍኖ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡
የሥልጣን ፡ እጃቸውን ፡ መልሰው ፡ በገሃድ ፡ እንዳያገቡ ፡ ከለከላቸው ።

ራስ ፡ ሚካኤል ፡ (ሥሁል) ፡ ከዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ ጊዜ ፡ ዠም
ረው ፡ ጐንደር ፡ መጥተው ፡ አብረው ፡ ቢኖሩም ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ መቀመጫቸው ፡
በዚያው ፡ በግዛታቸው ፡ በትግሬ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ በአያታቸው ፡
በእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ወገኖች ፡ በቋረኞችና ፡ በናታቸው ፡ ወገኖች ፡ በወሎዎቹ ፡
መካከል ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አኳኋን ፡ ጠቡና ፡ ክርክሩ ፡ መብዛቱን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡
ከትግሬ ፡ ራስ ፡ ሚካኤልን ፡ አስመጥተው ፡ እንደራሴነቱን ፡ ሾመው ፡ በእር

ርሳቸው ፡ ቋረኞችን ፡ ለማስጠቃት ፡ አሰቡ ። እንደ ፡ መጡም ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስና ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ አዛዥና ፡ ታዛዥ ፡ ሆነው ፡ በባለሟልነት ፡ ሥራቸውን ፡ ጀምረው ፡ ነበር ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ በሁለቱ ፡ መከከል ፡ ቅርታ ፡ እንዲገባና ፡ ሁለቱ ፡ እንዲጣሉ ፡ ደግሞ ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ በስውርና ፡ በብልኀት ፡ ከመጣጣር ፡ አላረፉም ። እቴጌዪቱም ፡ በሡሩት ፡ የብልኀት ፡ (የዲፕሎማሲ) ፡ ሥራ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ከዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ተጣሉና ፡ ከእቴጌዪቱ ፡ ወዳጅ ፡ ሆኑ ፡ እንዲያውም ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ቋረኞችን ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ አስጠቃለሁ ፡ ያሉት ፡ አሳብ ፡ ወደ ፡ ራሳቸው ፡ ላይ ፡ ተመለሰና ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስን ፡ እስከ ፡ መግደል ፡ ደረሱ ፤ የዚህንም ፡ ምክንያት ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ምዕራፍ ፡ ያስረዳናል ። ቢሆንም ፡ የእቴጌዪቱ ፡ ጥረት ፡ ቋረኞች ፡ እንዳይጠቁ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ የልጅ ፡ ልጃቸውን ፡ ኢዮአስን ፡ ዐውቀው ፡ ለማስገደል ፡ የሡሩት ፡ ዘዴ ፡ አልነበረም ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

### ስለ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፤–የራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያውና ፡ የዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ፍጻሜ ።

ራስ ፡ ሚካኤል ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ ዘመን ፡ በትግሬ ፡ አገር ፡ የታወቁ ፡ ሆነው ፡ በጠረፍ ፡ ካሉ ፡ ቱርኮችም ፡ እየተስማሙ ፡ መሣሪያም ፡ ሀብትም ፡ አደርጅተው ፡ ነበር ፤ በዚህም ፡ ላይ ፡ የተጣራ ፡ ፳፪ ፡ ሺህ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ነበራቸው ። በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ጊዜ ፡ መላውን ፡ ትግሬና ፡ ስሜንን ፡ ጨምረው ፡ ሲገዙ ፡ አሁን ፡ በዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ጥሪ ፡ ከነወታደራቸው ፡ ጐንደር ፡ መጥተው ፡ የእንደራሴነቱን ፡ ሥልጣን ፡ ይዘው ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ያስተዳድሩ ፡ ጀመር ። እንቢተኛውንም ፡ በደንብ ፡ እየቀጡ ፡ ፍርድ ፡ ለጉደለበትም ፡ ዳኝነት ፡ እያዩ ፡ ሁሉንም ፡ ደስ ፡ ስላሰኙ ፡ የጐንደር ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ራሴነታቸውን ፡ ከልብ ፡ ተቀበለው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያው ፡ የቀድሞ ፡ የእንደራሴነት ፡ ሥልጣናቸው ፡ በመቅረቱ ፡ አዝነው ፡ ነበርና ፡ ከላስታው ፡ ባላባት ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ በዐፄ ፡ ኢዮአስና ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ ላይ በሽፍትነት ፡ ተነሡባቸው ። ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ የላስታውን ፡ ባላባት ፡ በመልክት ፡ አባብለው ፡ ከራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያው ፡ ተለይቶ ፡ እንዲገባ ፡ አደረጉት ፡ ባላባቱም ፡ ራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያውን ፡ ትቶ ፡ ጐንደር ፡ ስለመጣ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ በደስታ ፡ ተቀበሉት ። ነገር ፡ ግን ፡ ንጉሡ ፡ ቀድሞውኑ ፡ ከራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያው ፡ ጋራ ፡ ለምን ፡ በሽፍትነት ፡ ተደረበ ፡ ብለው ፡ በንድ ፡ አገዛሪ ፡ እጅ ፡ አስገደሉት ። ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ እኔ ፡ አባብዬ ፡ ያስገባሁትን ፡ እንዴት ፡ አስገደሉብኝ ፡ ብለው ፡ ተናደዱ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ርሳቸውም ፡ ገዳዩን ፡ በስውር ፡ አስገድለው ፡ የባላባቱን ፡ ደም ፡ ተበቀሉለት ፡ ይባላል ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በንጉሡ ፡ በአፄ ፡ ኢዮአስና ፡ በእንደራሴው ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡

መከከል ፡ ውስጠ ፡ ቅያሜ ፡ ተመሠረተ ፤ ቢሆንም ፡ ሁለቱም ፡ ቅያሜያቸውን በየልባቸው ፡ ይዘው ፡ አዛዥና ፡ ታዛዥ ፡ ሆነው ፡ ሥራቸውን ፡ በስምምነት ፡ የሚቀጥሉ ፡ መስለው ፡ ለመታየት ፡ ተጣጣሩ ።

ስለዚህ ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ራስ ፡ ሚካኤልን ፡ አስከትለው ፡ ራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያውን ፡ ለመውጋት ፡ ሄዱ ። ከራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያውም ፡ ጋራ ፡ በጌምድርና ፡ ላስታ ፡ ወሰን ፡ ነፋስ ፡ ሙሳ ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ተገናኝተው ፡ ተዋጉና ፡ ራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያው ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ሲሸሹ ፡ ጋሎች ፡ ማርከው ፡ ለንጉሡ ፡ ሰጧቸው ። ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ ራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያውን ፡ ከሞት ፡ ለማዳን ፡ ሲሉ ፡ እባክዎ ፡ ባይሆን ፡ ይታሰር ፡ እንጂ ፡ አይገደል ፡ ብለው ፡ ንጉሡን ፡ ለምነዋቸው ፡ ነበር ፤ ንጉሡ ፡ ግን ፡ የራስ ፡ ሚካኤልን ፡ ልመና ፡ ሳይቀበሉ ፡ በጭካኔ ፡ በጥይት ፡ አስደበደቧቸው ። ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ በቀድሞ ፡ ቅያሜ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ስለ ፡ ተጨመረ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ቂማቸው ፡ እየባሰ ፡ ሄደ ።

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስሙን ፡ ያነሣነው ፡ የዳሞቱ ፡ ገዥ ፡ ፋሲል ፡ የጐንደርን ፡ እንደራሴነት ፡ ባለማግኘቱ ፡ በበኩሉ ፡ ተቀይሞ ፡ ኖሮ ፡ አሁን ፡ ንጉሡና ፡ እንደራሴው ፡ ከራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያው ፡ ጋር ፡ በሚዋጉበት ፡ ሰዓት ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ያገኘ ፡ ስለ ፡ መሰለው ፡ ከዳሞት ፡ መጥቶ ፡ በጌምድርን ፡ ወረረ ። ባንድ ፡ ወገንም ፡ ራስ ፡ ሚካኤልን ፡ እንዲያጠቃላቸውና ፡ እንደራሴነቱን ፡ እንዲይዝ ፡ ተስፋ ፡ ሰጥተው ፡ በስውር ፡ ያሥነሡት ፡ ራሳቸው ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። ይኸውም ፡ እውነት ፡ መሆኑ ፡ ወደፊት ፡ ይገለጻል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በገሃድ ፡ የታወቀው ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ለንጉሡ ፡ እንደራሴ ፡ መሆናቸው ፡ ፋሲልም ፡ መሸፈቱ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያውን ፡ እንደ ፡ ወጋን ፡ እንዲሁም ፡ ፋሲልን ፡ አብረን ፡ ሄደን ፡ እንውጋው ፡ ወይም ፡ ጦርዎ ፡ በሙሉ ፡ ይሰጠኝ ፡ ብለው ፡ ለንጉሡ ፡ አመለከቷቸው ። ንጉሡ ፡ ግን የራስ ፡ ሚካኤል ፡ እንደራሴነትና ፡ አያያዛቸው ፡ ከብዷቸውና ፡ ቀኗቸው ፡ ስለ ፡ ነበር ፤ ራሳቸውም ፡ አለመሄዳቸውን ፡ ጦርም ፡ ለመስጠት ፡ አለመፍቀዳቸውን ፡ ገልጸው ፡ ሄደኽ ፡ አንተው ፡ ብቻኽን ፡ ውጋው ፡ ብለው ፡ አሰናበቷቸው ። ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ ቂማቸውን ፡ በልባቸው ፡ ይዘው ፡ ከንጉሡ ፡ ተሰናብተው ፡ ፋሲል ፡ ከጐንደር ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ተቀመጠበት ፡ ወደ ፡ አዘዞ ፡ ለመዋጋት ፡ መጡ ፡ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ከንተ ፡ ጋራ ፡ አልሄድም ፡ ማለት ፡ ሳይበቃቸው ፡ ቀርቶ ፡ የገዛ ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ከነፋሲል ፡ ተደባልቀው ፡ ራስ ፡ ሚካኤልን ፡ እንዲወጉ ፡ በስውር ፡ ላኳቸው ፥ የዚህንም ፡ ምሥጢር ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ከእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ አገኙት ። ሁለቱም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወዳጅ ፡ ሆኑ ፡ ይባላል ።

ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ በመጨረሻ ፡ ወታደራቸውን ፡ ይዘው ፡ ከፋሲል ፡ ጋራ ፡ ተዋጉና ፡ በቶሎ ፡ ድል ፡ አደረጉ ። ፋሲልም ፡ ከጥቂት ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ ሸሽቶ ፡ ወዳገሩ ፡ ወደ ፡ ዳሞት ፡ ተመለሰ ። እርሱ ፡ ሸሽቶ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡

እምርክ ፡ ላይ ፡ ውስጡን ፡ ከንጉሡ ፡ ታዘው ፡ የመጡት ፡ የዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ አሽከሮች ፡ አብረው ፡ ተገኝተው ፡ ተማረኩ ። በዚህ ፡ ንጉሡ ፡ ለፋሲል ፡ መር ዳታቸው ፡ በገሃድ ፡ ታወቀ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ በድል ፡ አድ ራጊነት ፡ ከጦርነቱ ፡ ተመልሰው ፡ ጐንደር ፡ ገቡ ። ወዲያውም ፡ ንጉሡን ፡ ለማ ናደድ ፡ ሲሉ ፡ ከጦርነቱ ፡ ተመልሰው ፡ በገቡበት ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ የጐንደርን ፡ ከተማ ፡ አቃጠሉት ። ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ እንደገቡ ፡ በቶሎ ፡ ሊቃ ውንቱና ፡ መኳንንቱን ፡ ሰብስበው ፡ “በንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ የሸፈተውን ፡ ልወጋ ፡ ሄጄ ፡ ንጉሡ ፡ እኔን ፡ በመርዳት ፡ ፈንታ ፡ ለሽፍታው ፡ ርዳታ ፡ የገዛ ፡ አሽከ ሮቻቸውን ፡ ላኩ ። በዚህም ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ንጉሡ ፡ አዘውት ፡ ፩ ፡ ሰው ፡ ተደብቆ ፡ ጥይት ፡ ተኵሶ ፡ ሊገድለኝ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በኔ ፡ ፈንታ ፡ ባጠገቤ ፡ ቆሞ ፡ ጭራ ፡ ይዞ ፡ ይከለክል ፡ የነበረው ፡ አሽከሬ ፡ ሞተ ። ይኸንኑም ፡ ሁሉ ፡ እናንተ ፡ የተሰበሰባችሁ ፡ ታውቃላችሁና ፡ ፍረዱኝ ፡” ብለው ፡ ተናገሩ ።

በዚያም ፡ ከቆሙት ፡ ገሚሶቹ ፡ ንጉሥ ፡ ባይሆን ፡ ይታሰራል ፡ እንጂ ፡ አይገደ ልም ፡ አሉ ። የቀሩት ፡ ራስ ፡ ሚካኤልን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ከሆነ ፡ ንጉሡ ፡ ይገደላሉ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ። በመጨረሻም ፡ አንድ ፡ ራስ ፡ ሚካኤልን ፡ የማ ይወድ ፡ የትግሬ ፡ ደብተራ ፡ ‹ንጉሥ ፡ ከገደሉ ፡ ግዛት ፡ አይገባቸውም ፡ ለማሰኘት› ፡ ሲል ፡ ንጉሥ ፡ በጠመንዣ ፡ አይገደልም ፡ እንጂ ፡ በሻሽ ፡ ታንቆ ፡ ይሞታል ፡ ብሎ ፡ ፈረደ ፡ ይባላል ። ስለዚህ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ በደል ፡ ቢበዛባቸው ፡ ከትግሬ ፡ አስመጥ ተው ፡ እንደራሴ ፡ ያደረጓቸውን ፡ ንጉሣቸውን ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስን ፡ በሻሽ ፡ አሳንቀው ፡ በሺሕ ፡ ፯፻፷፩ ፡ ዓ. ም. ገደሏቸው ። ሬሳቸውም ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ባንድ ፡ ጕድጓድ ፡ ተጥሎ ውሎ ፡ ካደረ ፡ በኋላ ፡ በሌላ ፡ ቀን ፡ ከዚያ ፡ ወጥቶ ፡ ጐንደር ፡ በቅዱስ ፡ ሩፋ ኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተቀበረ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ስለ ፡ ጋሎች ፡ መውደቅ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ከራስ ፡ ሚካኤል ፡ ጋራ ፡ ቢተባበሩ ፡ ስለ ፡ ልጅ ፡ ልጃቸው ፡ ስለ ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ሕይወት ፡ አስቀድመው ፡ ተጨንቀው ፡ ነበር ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ለማዳን ፡ ሳይችሉ ፡ ቀር ተው ፡ በሞቱም ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ አዘኑ ፡ ይባላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፱ ።

## ስለ ፡ ነገሥታቱ ፡ ሥልጣን ፡ መውደቅ ።

በአኵስም ፡ ተከታትለው ፡ የመጡትን ፡ የነገሥታት ፡ ዘሮች ፡ ዮዲት ፡ (ይሁዳዊት) የምትባለዋ ፡ ኃይለኛ ፡ የፈላሻ ፡ ሴት ፡ በ፰፻፵፫ ፡ ዓ. ም. ላይ ፡ እንዳጠፋቻቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ሁሉ ፡ የሚገኝ ፡ ነው ። በርሷም ፡ ዠማሪነት ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ዛጔዎች ፡ ከ፱፻፩ ፡ ዠምረው ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፪፻፷፫ ፡ ዓ. ም. ፡ ድረስ ፡ አኵስ ምና ፡ ሸዋ ፡ በነበሩበት ፡ ነገሥታት ፡ መካከል ፡ ገብተው ፡ ላስታ ፡ ሆነው ፡ ኢትዮጵ ያን ፡ መግዛታቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በነርሱ ፡ መጨረሻ ፡ ከይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጊዜ ፡ (ከሺሕ ፡ ፪፻፶፱ ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፭፻ ፡ ዓ. ም.) ድረስ ፡

ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ተነሥቶ ፡ በታወቀው ፡ ኃይሉ ፤ ፀሬ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ አሸንፎ ኢትዮጵያን ፡ ለመውረር ፤ የርሱም ፡ ተከታይ ፡ ኑር ፡ መሐመድ ፤ ፀሬ ፡ ገላው ዴዎስን ፡ አሸንፎ ፡ እስከ ፡ መግደል ፡ መድረሱን ፡ ባለፈው ፡ አንብበናል ፤ ከነዚህ ፡ በቀር ፡ የነገሥታቱን ፡ ዘውድ ፡ ቀምቶ ፡ ሥልጣናቸውን ፡ የገፈፈ ፤ እነርሱንም ፡ ያዋረደ ፡ በታሪኩ ፡ ውስጥ ፡ የሚታወሰን ፡ የለም ። የራስ ፡ ዘሥላሴ ፡ በገዛ ፡ እጅ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ መንገሥ ፣ የራስ ፡ ዮስጦስም ፡ ወደ ፡ ዙፋን ፡ መውጣት ፡ መንገዱ ፡ የተለየ ፡ ጊዜውም ፡ ያጠረ ፡ ነው ።

ረዥም ፡ ጊዜ ፡ ባለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ነገሥታቱ ፡ በሕዝቡም፡ በመኳንንቱም ፤ በካህኑም ፡ በሊቃውቱም ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ የመፈራት ፤ የመከበር ፤ የማዘዝ ፡ ሥልጣንና ፡ ችሎታቸውም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ነገሥታቱ ፡ በምድር ፡ የእግዚአብሔር ፡ እንደራሴ ፡ በመሆናቸው ፡ ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፤ መሲሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ እየተባሉ ፡ ሕዝቡ ፡ የሚሰጣቸው ፡ ግምት ፡ ልዩ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ በቤተ ክህነቱም ፡ ላይ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ። ቢሾሙ ቢሽሩ ፤ ቢያስሩ ፤ ቢፈቱ ፡ በበላይ ፡ ያለው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከመፍራት ፡ በቀር ፡ በምድር ፡ ጠያቂ ፡ የለባቸውም ፤ መኳንንቱና ፡ ሕዝቡ ፡ ካህኑም ፡ ይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ የነርሱ ፡ አገልጋይና ፡ ታዛዥ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ጠያቂአቸው ፡ ተከራካሪያቸው ፡ አይደለም ። በነርሱ ፡ ላይ ፡ እጁንም ፡ አንደበቱንም ፡ ያነሣውን ፡ ምላሱና ፡ እጁ ፡ ይቈረጥ ፡ ብሎ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ የወሰነው ፡ ደኅና ፡ አንድርጎ ፡ ተመሥርቷል ። ስለዚህ ፡ ያው ፡ ልንገሥ ፤ አትንግሥም ፡ እየተባባሉ ፡ በሚከታተሉበት ፡ ጊዜ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ነገሥታቱ ፡ ይገዳደላሉ ፡ እንጂ ፡ ከሕዝቡና ፡ ከተርታው ፡ መኳንንት ፡ ወገን ፡ ንጉሡን ፡ የመድፈር ፡ ነገር ፡ አይታይም ፤ ቢታይም ፡ በብርቅ ፡ ነው ፡ ነገሥታቱ ፡ ግን ፡ የጥፋቱ ፡ አኳኋን ፡ እንደ ፡ ታያቸው ፡ ወይም ፡ ሰውዮውን ፡ በሚፈሩትና ፡ በሚጠረጥሩት ፡ ዓይነት ፡ ሲዋጋ ፡ ከሞተው ፡ በቀር ፡ ሳይሞት ፡ የተማረከውን ፤ እጅና ፡ እግር ፡ ምላስ፡ እያስቈረጡ ፤ በሰይፍ ፡ እያስመቱ ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ እያሰቀሉ ፡ ይገድላሉ ። ለዚህም ፡ ፍርድ ፡ ሲፈልጉ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አዘርግተው ፡ በጉባኤ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ያለፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ሲገድሉ ፡ መኖራቸውን ፡ በየታሪኩ ፡ በየዘመኑ ፡ አንብበናል ። ይኸም ፡ ከ፲፰ኛ ፡ ዓ. ም. በፊት ፡ በመካከላቸውና ፡ በጥንቱ ፡ የዘመን ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ዛሬ የሠለጠኑት ፡ የአውሮፓ ፡ ነገሥታት ፡ ከእንግሊዞች ፡ በቀር ፡ ባገራቸው ፡ ይሠሩት ፡ በነበረው ፡ የሚመሳሰል ፡ እንጂ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብቻ ፡ የተደረገ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይዶለም ።

የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፤ መሲሐ ፡ እግዚአብሔር ፤ ወይም ፡ ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የመባል ፡ ስያሜ ፡ ለሁሉም ፡ በየጊዜያቸው ፡ እንዳላቸው ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ ዘውድ ፡ ደፍተው ፡ ለንጉሥነት ፡ የተቀበሉት ።

አንበሳ ፡ ሰገድ ፤ አንበሳ ፡ የሰደገለት ፤ ፀሐይ ፡ ሰገድ ፡ ፀሐይ ፡ የምትሰግድለት ፡ እየተባሉ ፡ በመጠሪያ ፡ ስማቸው ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ ስም ፡ እንደሚሰጣቸው ፡ እነሆ ፡ አንብበናል ። እንደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አለቃ ፡ ብፁዕና ፡ ቅዱስ ፡ የሚባሉበት ፡ መንገድ ፡ አይጠፉም ።

ይኸን ፡ በመሰለ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ክብርና ፡ ግርማ ፤ ሥልጣንና ፡ መፈራት ፡ የዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ አባቶች ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፤ ዐፄ ፡ በካፋ ፡ መሲሕ ፡ ሰገድ ፤ ዐፄ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፤ . . . . . ገዝተው ፡ እንዳለፉ ፡ እንደዚሁ ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ዝምረው ፡ ነበር ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ መጨረስ ፡ አልሆነላቸውም ። ከገበሬም ፡ ቢሆን ፡ ከነ ጋዴ ፤ ከካህንም ፡ ቢሆን ፡ ከእጅ ፡ ጥበበኛ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስፈሪውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በድንገት ፡ ይለውጠዋል ። እግዚአብሔር ፡ ኀይሉን ፡ እንኳን ፡ በወንድ ፡ በሴት ፡ በኩል ፡ ለመግለጽ ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወንዶች ፡ ሁሉ ፡ በሴትዮዋ ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ ለመመከት ፡ ጉብዝና ፡ ይነሣቸዋል ። ባለፈው ፡ የጠቀስና ትን ፡ የዮዲትን ፡ ታሪክ ፡ ከመዠመሪያው ፡ ምዕራፍ ፡ ስናነብ ፡ ነገሩን ፡ መገንዘብ ፡ እን ችላለን ።

በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ከትግሬ ፡ መጥተው ፡ ጐንደር ፡ መዠመሪያ ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አማካሪ ፡ ቀጥሎ ፡ ለልጃቸው ፡ ለዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ እንደራሴ ፡ ሲሆኑ ፡ ይኸን ፡ የመጨረሻ ፡ የድፍረት ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ ለእንደራሴነት ፡ ያስመጧቸውን ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስን ፡ በሻሽ ፡ አሳንቀው ፡ ይገድላሉ ፡ ብሎ ፡ የገመተ ፡ መቼም ፡ አልነበ ረም ። በሕታውያኑ ፡ በሕልም ፤ ደብተሮቹ ፡ በቍጥር ፡ አስቀድሞ ፡ ዐውቀውት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አናውቅም ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፤ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ድፍረትና ፡ ችሎት ፡ ንጉሡን ፡ ካስገደሉ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ ለስሙ ፡ ዘውድ ፡ የጫነ ፡ ንጉሥ ፡ ማስቀመጣቸው ፡ ባይቀር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ የነበረውን ፡ ሥልጣን ፡ ይዘው ፡ ያስተዳድሩ ፡ ዠመር ፤ አዲሱ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትም ፡ የሚደረገውን ፡ ሹም ፡ ሽርና ፡ አስተዳደር ፡ ወሬውን ፡ እየሰማ ፡ ባዳራሹ ፡ ሆኖ ፡ ከመታዘብ ፡ በቀር ፡ ያለፉት ፡ ነገሥታት ፡ እንደራሴዎቻቸውን ፡ እንደ ፡ ዕቃ ፡ ይለዋውጡ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ እንኳን ፡ ለመለወጥና ፡ ለመሻር ፡ ይህ ፡ ለምን ተደረገ ፡ ብሎ ፡ ለመከራከርና ፡ ለመቈጣት ፡ ዐቅም ፡ አላገኙም ።

ይኸም ፡ የደረሰበትን ፡ ምክንያት ፡ ከታሪክ ፡ ነገሥት ስንፈላለግ ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ነገሥታቱ ፡ በጐንደር ፡ ተድላና ደስታ ፤ ጨዋታና ፡ እብሬት ፡ ስለ ፡ አበዙ ፡ የነዚያን ፡ ግፍ ፡ ቈጥሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ራስ ፡ ሚካኤልን ፡ በአፄ ፡ ኢዮአስና ፡ በልጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ አስነሣባቸው ፡ ሲል ፡ ሁኔታውንም ፡ ከአኵስም ፡ ነገሥታትና ፡ ከዮዲት ፡ ጋራ ፤ ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልና ፡ ከግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ጋራ ፡ እያገናኘ ፡ ሲያመጣው ፡ እንመለከታለን ። ስለዚህ ፡ ነገሥታቱ ፡ ቢበድሉ ፡ እነራስ ፡ ሚካኤልን ፤ እነራስ ፡ ዐሊ ፡ ትልቁን ፡ አስነሣ ፤ መሳፍንቱ ፡ ቢበድሉ ፡ ደግሞ ፤ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ አስነሣ ፡ ማለት ፡ የተለመደና ፡ የሚመስል ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ይኸም ፡ ታሪክነቱ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን በሥልጣን ፡ ላይ ፡ የወጣውን ፤ ገና ፡ የሚወጣውን ፡ ለማስጠንቀቂያ ፡ ጭምር ፡ ይረዳል ፡ ተብሎ ፡ የመጣ ፡ ሳይሆንም ፡ አይቀርም ።

## የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ፬ኛ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

### ምዕራፍ ፡ ፺ ።

### ንጉሡ ፡ የተቀኙዋቸው ፡ ቅኔዎች -የንጉሡ ፡ አሟሟት ፤-የጀምስ ፡ ብሩስ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መምጣት ።

ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስን ካስገደሉ በኋላ ፡ ለራሳቸው ፡ የሚስማሚቸውን ፡ በወህኒ ፡ አምባ ፡ ከሚቀመጡት ፡ ነጋሥያን ፡ ውስጥ ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድን ፡ ልጅ ፡ የዐፄ ፡ በካፋን ፡ ወንድም ፡ ዮሐንስን ፡ አውርደው ፡ በዙፋን ፡ አስቀመጧቸው ።

ዐፄ ፡ ዮሐንስም ፡ ከወህኒ ፡ አምባ ፡ ወርደው ፡ ሲነግሡ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ እጃቸው ፡ ቈራጣ ፡ ነበር ፤ ስለዚህ ፡ ስማቸውም ፡ አንድ ፡ እጁ ፡ ዮሐንስ ፡ ይባላል ። ያስቈረጧቸውም ፡ ዙፋንን ፡ ቢቀናቀኗቸው ፡ ዐፄ ፡ በካፋ ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። ዐፄ ፡ በካፋ ፡ በዘመናቸው ፡ ቢታመሙ ፡ እኔ ፡ የሞትሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ርሱ ፡ ይነግሣል ፡ ብለው ፡ ከወህኒ ፡ አምባ ፡ አውርደው ፡ ባጠገባቸው ፡ ያስቀመጧቸው ፡ ርሳቸው ፡ ናቸው ፡ ገጽ ፡ ፻፺፵፪–፻፺፵፫ ፡ ተመልከት ።

ሕዝቡና ፡ መኳንንቱም ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሊነግሥ ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ ክርክር ፡ አቅርቦ ፡ ነበር ። አንድ ፡ እጁ ፡ ዮሐንስ ፡ በወህኒ ፡ አምባ ፡ ሲኖሩ ፡ ዕድሜያቸውን ፡ ቅኔና ፡ መጻሕፍትን ፡ በመማር ፡ ስለ ፡ አሳለፉ ፡ እንዳንድ ፡ ሊቅ ፡ መጻሕፍትና ፡ ቅኔ ፡ ዐዋቂ ፡ ነበሩ ፤ ስለዚህ ፡ የጎዳር ፡ ሚካኤል ፡ ዕለት ፡ አእላፍ ፡ ከሚባለው ፡ አጣጣሚ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገብተው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ሥላሴ ፡ ቅኔ ፡ ተቀኙ ፡ ይባላል ።

መንክረ·ተ ፡ ግብጽ ፡
ሙሴ ፡ ረሰየ ፡ ከመ ፡ ፈቀደ ፤
አምጣነ ፡ ለሙሴ ፡ መልአኩ ፡ ወመድኃኔ ፡ ገጹ ፡ እምገጽ ፡
ዘባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ ሚካኤል ፡ አንቀጽ ።
እመኒ ፡ በዕፅ ፡ ሥጡቱ ፤ ወአመ ፡ ርፍአቱ ፡ በዕፅ ፡
ለባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ ልብሰ ፡ ተግሣጽ ፡
መቅረፁ ፡ ይእቲ ፡ በትሩ ፡ ዘግብጽ ፡
ወመርፍኡ ፡ ይእቲ ፡ መቅረፅ ።

ትርጓሜው ።

የግብጽን ፡ ድንቅ ፡ ነገሮች ፡ ሙሴ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ አደረገ ፤
ለሙሴ ፡ መልክተኛውና ፡ የፊቱ ፡ አዳኝ ፡ የኤርትራ ፡ በር ፡ ሚካኤል ፡ ነውና ።
የተግሣጽ ፡ ልብስ ፡ የኤርትራ ፡ ባሕር ፡ መቀደዱና ፡ መሰፋቱ ፡ በዕንጨት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ የግብጽ ፡ በትር ፡ መቀሱ ፡ ናት ፤
መቀሲቱም ፤ መርፌው ፡ ናት ።

ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ግን ፡ ቅዱስ ፡ ሚከኤል ፡ የኤርትራን ፡ ባሕር ፡ ከፍሎ ፡ ሙሴን ፡ እንዳሻገረውና ፡ የእስራኤል ፡ መሪ ፡ እንዳደረገው ፤ ሥዑል ፡ ሚከኤልም ፡ ወህኒ ፡ አምባን ፡ ከፍተው ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ፪ኛን ፡ ንጉሥ ፡ ማድረጋቸውን ፡ ያሳያል ።

በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ እኳ ፡ ስለሌላቸው ፡ ሰዉ ፡ ይንገሥ ፡ አይንገሥ ፡ እያለ ፡ ሲጨቃጨቅ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ ብለው ፡ ተቀኙ ፡ ይባላል ።

. . . . . ጊዜያትሂ ፡ አእላፊ ፡ እመ ፡ መከሩ ፡ አእላፍ ፤
አንተ ፡ ዘኃለይከ ፡ ወዘወሰንከ ፡ ኢይተርፍ ።

የትርጓሜውም ፡ አሳብ ፡ ብዙ ፡ ሺህ ፡ ሰው ፡ የመከረውን ፡ ቢመክር ፡ አንተ ፡ (እግዚአብሔር ) ፡ ካስብኸውና ፡ ከወሰንኸው ፡ አያልፍም ፡ ማለት ፡ ነው ።

በውነትም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ ሆነና ፡ ሕዝቡም ፡ አልቀበልም ፡ እንዳይል ፡ ራስ ፡ ሚከኤልን ፡ በመፍራት ፡ የዮሐንስን ፡ ንጋሢነት ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ተቀበለ ። ራስ ፡ ሚከኤልም ፡ እኅታቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ሥላሴን ፡ ለንጉሡ ፡ ዳሩላቸውና ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ራስ ሚከኤል ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሆኑ ። ከዐፄ በካፋ ፡ ዠምሮ ሥልጣናቸው ፡ ገኖ ፡ ይኖር ፡ የነበረው ፡ የእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ሥልጣን ፡ ተወሰነ ። የቀድሞ ነገሥታት ፡ ይሠሩት ፡ የነበረውም ፡ ቀረና ፡ አሁን ፡ እንደራሴው ፡ ራስ ፡ ሚከኤል ፡ በፈቃዳቸው ፡ በያገሩ ፡ ታማኞቻቸውንና ፡ ዘመዶቻቸውን ፡ ሾሙበት ፡ ለልጃቸውም ፡ ጐጃምን ፡ ሰጡት ። እቴጌ ምንትዋብም ፡ ዕድሜያቸውም ፡ ስለ ፡ ጸና ፡ በራስ ሚከኤል ፡ አያያዝ ፡ ተስፋ ፡ ቈርጠው ፡ ሁሉንም ፡ ትተው ፡ ባሠሩት ፡ በቍስቋም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ በጸሎት ፡ በሰጊድ ፡ ተቀመጡ ።

በዚህም ፡ ዘመን ፡ በሺህ ፡ ፯፻፷፪ ፡ ዓመት ፡ (እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ አቈጣጠር ፡ ፲፯፻፷፱ ፡ ) ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ የሚባለው ፡ እንግሊዛዊ ፡ ጐንደር ፡ መጣና ፡ ከራስ ፡ ሚከኤልና ፡ ከዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ተገናኝቶ ፡ በጐንደር ፡ ተቀመጠ ። ርሱም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተቀምጦ ፡ ወዳገሩ ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፤ BRUCE'S TRAVEL የብሩስ ፡ ጕዞ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ በ፭ ፡ ቮሊም ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሁኔታና ፡ ስለ ፡ ታሪኳ ፡ ጽፏል ። ያባይንም ፡ የምንጭ ፡ መነሻ ፡ ያገኘሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ብሏል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይኸኛው ፡ በሙሉ ፡ አልታመነለትም ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዳሞት ፡ ሸፍቶ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ያስቸገረው ፡ ፋሲል ፡ አሁንም ፡ አልገባም ፡ ነበርና ፡ ራስ ፡ ሚከኤል ፡ ርሱን ፡ ለመውጋት ፡ ይዘጋጁ ፡ ዠመር ።

ዝግጅቱም ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡን ፡ አብረን እንሂድና ፡ ፋሲልን ፡ እንውጋ ፡ ብለው ፡ አማከሯቸው ። ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ግን ፡ በወህኒ ፡ አምባ ፡ ሲኖሩ ፡ ጸሎትና ፡ ስግደት ፡ በማዘውተር ፡ ኖሩ ፡ እንጂ ፡ የጦርነት ፡ ነገር ፡ ሞክረውት ፡ አያውቁም ፡ ነበርና ፡ «አልችልም ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ ሽምግያለሁ» ፡ ብለው ፡ እምቢ ፡ አሏቸው ። ቢያባብሏቸውም ፡ ባትፈልግ ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ አምባዬ ፡ መልሰኝ ፡ እንጂ ፡ አልሄ

ድም ፣ አሉ ፣ ይባላል ፤ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ግን ፡ አሁን ፡ እንቢ ፡ ማለታቸው ፡ እኔ ፡ እልፍ ፡ ስል ፡ ሌላ ፡ እንደራሴ ፡ ለማድረግ ፡ አስበው ፡ ይሆናል ፡ ሲሉ ፡ ተጠራጥረው ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ ንጉሡን ፡ ከመብል ፡ ጋራ ፡ መርዝ ፡ አብልተው ፡ አስገደሏቸው ፡ ይባላል ። የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ፪ኛም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ ፩ ፡ ዓመት ፡ ብቻ ነው ፡ የሞቱትም ፡ በሺሕ ፡ ፯፻፷፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነው ።

## የዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

## ምዕራፍ ፡ ፹፩ ።

## የፋሲል ፡ ሽፍትነት ፤–የራስ ፡ ሚካኤል ፡ ጭካኔ ፡ –የራስ ፡ ጐሹ ፡ ሥልጣን ፡ መያዝ ፡ – የእቴጌ ፡ ምንትዋብና ፡ የራስ ፡ ሚካኤል ፡ ፍጻሜ ።

ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ የኋህኑ ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስን ፡ ልጅ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ስመ ፡ መንግሥታቸውን ፡ «ኀያል ፡ ሰገድ» ፡ አሰኝተው ፡ አነገሧቸው ። ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ሲነግሡ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ነበር ። ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ከነገሡ ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡ ፡ በደስታ ፡ እንዲያብርላቸው ፡ ንጉሡን ፡ ይዘው ፡ የዳሞቱን ፡ ፋሲልን ፡ ለመውጋት ፡ በሺሕ ፡ ፯፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ ሄዱ ። ፋሲልም ፡ የዳሞትን ፡ የአገውን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ፋጊት ፡ ከሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበርና ፡ በዚሁ ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ጦርነቱ ፡ ተዠመረ ። ብዙ ፡ ሰዓት ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በኀይል ፡ ሲዋጉ ፡ ቈዩ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ ፲ ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ፋሲል ፡ ድል ፡ ሆነና ፡ በፈረስ ፡ ከጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ አመለጠ ። ፈረሰኞችም ፡ ቢከታተሉት ፡ ለማግኘት ፡ አልቻሉም ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከርሱ ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ የተማረኩትን ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ ትእዛዝ ገደሏቸው ። ከነዚህም ፡ ዋጩቃ ፡ የሚባል ፡ የፋሲል ፡ ተከታይ ፡ ይምሩኛል ፡ ብሎ ፡ እጁን ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ ጭፍሮቻቸው ፡ እርሱን ፡ ገድለው ፡ ቈዳውን ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ ገፈው ፡ እንደ ፡ ስልቻ ፡ ሰፍተው ፡ ገለባ ፡ ሞልተው ፡ ለራስ ፡ ሚካኤል ፡ አሳዩዋቸው ፡ ይባላል ። የዚህም ፡ ታሪክ ፡ በብዙ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ደራሲዎችና ፡ ባገራችንም ፡ ጽሑፍ ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ።

ሞት ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ዐይነት ፡ ሥጋ ፡ በለበሰውና ፡ የዚህም ፡ ሥቃይ ፡ ሊሰማው ፡ በሚችል ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ የአብሪትና ፡ የጭካኔ ሥራ ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ላይ ፡ ሲፈጽም ፡ አስደናቂ ፡ ነገር ፡ ነው ። የዚህ ፡ ዐይነትም ፡ ግዳይ ፡ የገዳዩቹን ፡ ልብ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ በኵራት ፡ እንደሚሞላ ፡ አይታወቅም ።

ይኸውም ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ብዙ ፡ መኳንንት ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ እንዲሸፍቱ ፡ ምክንያት ፡ ሆነ ። ከነዚሁም ፡ ውስጥ ፡ ያማራ ፡ ሣይንቱ ፡ ራስ ፡ ጐሹና ፡ የላስታው ፡ ደጃች ፡ ወንድ ፡ በወሰን ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት ፡ ታላላቅ ፡ መኳንንት ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለው ጨካኝ ፡ አንገዛም ፡ ብለው ፡ ሸፈቱባቸው ፤ ብዙም ፡ አባሪ ፡ አገኙ ።

ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ ከነዚህ ፡ አላይ ፡ ከተጠሩት ፡ በቀር ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ እንደተነ ሣባቸው ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ፡ ጐንደርን ፡ ትተው ፡ ንጉሡን ፡ ተክለ፡ ሃይማኖትን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ አኵስም ፡ ሄዱ ። አኵስም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ ትእዛዝ ፡ ለን ጉሡ ፡ የአኵስም ፡ ሕዝብ ፡ ብዙ ፡ ገጸ ፡ በረከትና ፡ መጥን ፡ አገባ ።

ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ጐንደርን ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ አኵስም ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣንነትና ፡ ኀይለኛነት ፡ ተስፋ ፡ ቈርጠው ፡ በጸሎትና፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ በማዘውተር ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ተወስኘለሁ ፡ ብለው ፡ የነበሩት ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ መራቅ ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሕፃኑን ፡ የሻኛቸን፡ የዐፄ ፡ ኢያሱን ፡ ልጅ ፡ ለስሙ ፡ አንግሠው ፡ ሥልጣኑን ፡ ለመያዝ ፡ አስበው ፡ ነበር። ዳሩ ፡ ግን ፡ መኳንንቱ ፡ የእቴጌዪቱን ፡ ፈቃድ ፡ ስላልተቀበሉ ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ በሄ ዱት ፡ በንጉሡ ፡ በተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ምትክ ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድን ፡ ልጅ ፡ ሱስንዮስ ፡ የሚባለውን ፡ አንግሠናል ፡ ብለው ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ።

ፋሲልም ፡ ከራስ ፡ ሚካኤል ፡ ተዋግቶ ፡ በተሸነፈ ፡ ጊዜ ፡ ሸሽቶ ፡ በዳሞት ፡ ነበ ርና ፡ ይኸንን፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከዳሞት፡ ተነሥቶ፡ ጐንደር ፡ ገብቶ ፡ የመንግሥቱን፡ ሥል ጣን ፡ ለመያዝ ፡ አሰበ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሦስቱ ፡ ታላላቅ ፡ መኳንንቶች ፡ ጐሹ፤ ያየኸ ይራድ ፤ ወንድ ፡ በወሰን ፤ አናስገባም ፡ ብለው ፡ ለጦርነት ፡ ተሰለፉት ። ፋሲልም ፡ አሳቡ ፡ እንዳልተሳካለት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እነሱን ፡ ለመጕዳት ፡ ሲል፡ አሳቡን፡ ያን ፡ ያኸል እየተጣላቸው ፡ ከተዋጋቸው ፡ ከንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትና ፡ ከራስ ፡ ሚካኤል፡ ጋራ፡ እደረገ ። ከነሱም ፡ ተላልኮ ፡ ታረቀ ፤ ፋሲልም ፡ በጊዜው ፡ በኀይለኛነት ፡ ስሙ ፡ የተጠራ ፡ ነውና ፡ ከንጉሡና ፡ ከራስ ፡ ሚካኤል ፡ መታረቁ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ ከነጐሹ፤ ከነወንድ ፡ በወሰን ፡እየከዳ ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ እየሄደ ፡ ለንጉሡ፡ ገባ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ንጉሣቸውን ፡ ይዘው ፡ ከዐረብ ፡ ሺሕ ፡ የሚ በልጥ ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ጕዞ ፡ ዠመሩ ። በጕዞውም ፡ ጊዜ ፡ እንግ ሊዙ ፡ ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ አብሮ ፡ ነበር ። በመንገድም ፡ ምንም ፡ ያኸል ፡ የተቋቋማ ቸው ፡ ሳያገኙ ፡ ጐንደር ፡ በሰልፍ ፡ ገቡ ። ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ነግሦ ፡ የነበረው ፡ ሱስን ዮስም ፡ ከጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ጐንደርን ፡ ለቆ ፡ ወደ ፡ ቋራ ፡ ሜካ ፡ ሸሸ ። ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትና ፡ ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ ጐንደር ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ እገሌ ፡ ንጉሡን ፡ አምቷል ፤ እገሌ ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ ክፉ ፡ መክሯል ፡ እየተባለ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ እየተ ያዘ ፡ በጥይትና ፡ በሰይፍ ፡ ተገደለ ።

በከተማ ፡ የተገኘውን ፡ ሕዝብ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅጣት ፡ ሲሣቅዩት ፡ ዋኖቹ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ የሸፈቱት ፡ መኳንንቶች ፡ ከነሠራዊታቸውና ፡ ከነጦር ፡ መሣሪያቸው፡ በውጭ ፡ ሆነው ፡ ጦር ፡ እያሳበሩ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ። እቴጌ ፡ ምንትዋብም ፡ ከነተ ከታዮቻቸው ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ፡ ኀይለኛውም ፡ ፋሲል ፡ እንደገና ፡ ከነዚሁ ፡ ጋራ፡ ተመልሶ ፡ ተደባለቀ ። የእነዚህም ፡ ወገን ፡ ኀይላቸው ፡ እየበረታ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ ከዋና፡ ሰፈራቸው ፡ ከደንቢያ ፡ እስከ ፡ ጐንደር ፡ ሜዳ ፡ እየሄዱ ፡ ከብትም ፡ መዝረፍ፡ ቤትም፡ ማቃጠል ፡ ዠመሩ ።

ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ወደ ፡ ሽምግልና ፡ ኀይላቸው ፡ ወደ ፡ ድካም ፡ የተቃረበ ፡ ቢሆን ፡ በከተማው ፡ ተቀምጠው ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ የሽፍትነት ፡ ሥራ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፤ ተናደው ፡ ጭፍሮቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ለውጊያው ፡ ተነሡ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከበጌምድርም ፡ ከጐጃምም ፤ ከላስታም ፡ እየሄደ ፡ ከሽፍቶቹ ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ተደባለቀ፡ ከራስ ፡ ሚካኤል ፡ ጦር ፡ የነደጃች ፡ ወንድ ፡ በወሰን ፡ ጦር ፡ ሁለት ፡ ዕጥፍ ፡ ይበልጥ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ የነበሩበት ፡ ሥፍራ ፡ ከጐንደር ፡ በደቡብ ፡ በኩል ስበር ፡ ቀኻዝ ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ነበርና ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ እዚሁ ፡ ሥፍራ ፡ ድረስ ፡ ሄደው ፡ በሺሕ ፡ ፲፯፻፷፬ ፡ ዓ፡ ም፡ በግንቦት ፡ ወር ፡ ጦርነት ፡ ተጋጠሟቸው ፤ ጦርነቱም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ሲግል ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ሲበርድ ፡ እስከ ፡ ስምንት፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ቈየ ፡ ይባላል ።

ውጊያውም ፡ የመሣሪያ ፡ ጦርነት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የዲፕሎማቲክም ፡ ጭምር ፡ ነበር ፡ ይኸውም ፡ ሽፍቶቹ ፡ ራስ ፡ ሚካኤልን ፡ ትተው ፡ ከኛ ፡ ጋራ ይሁኑና ፡ ዙፋንዎን ፡ እንደያዙ ፡ ይቀመጡ ፡ እያሉ ፡ ለንጉሥ ፡ ለዐፄ ፡ ተክለ፡ ሃይማኖት ፡ ይልኩባቸው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከዲፕሎማቲኩ ፡ ኀይል ፡ የልብ፡ ጦርነቱም ፡ ከነራስ ፡ ጐሹ ፡ ወገን ፡ በጣም ፡ ተጭኖ ፡ ስለነበር ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ከነሰዎቻቸው ፡ ንጉሡን ፡ እንደያዙ ፡ ከጦርነቱ ፡ ሥፍራ ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ተመለሱ እነዚያም ፡ እግር ፡ በእግር ፡ እየተከታተሉ ፡ ሄደው ፡ ጐንደርን ፡ ከበቡ ። ከመካከላቸውም ፡ ጐሹን ፡ ራስ ፡ ብለው ፡ የበላይ ፡ አዛዥ ፡ ስላደረጓቸው ፡ ነገሩ ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ ላይ ፡ እየከበደ ፡ ሄደ ። ከራስ ፡ ሚካኤል ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ትግሮችም ፡ አማሮችም ፡ እየከዱ ፡ መጥተው ፡ ከራስ ፡ ጐሹ ፡ ጋራ ፡ ተደባለቁ ። ስለዚህ ፡ በመጨረሻ ፡ እነራስ ፡ ጐሹ ፡ አሸነፉና ፡ ዠግናው ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ተማረኩና ፡ በእመኪና ፡ አምባ ፡ ታሠሩ ፤ ንጉሡን ፡ ግን ፡ እንዳሉ በዙፋናቸው ላይ ተዋቸው።

ራስ ፡ ጐሹም ፡ ከራስ ፡ ሚካኤል ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ በሻሽ ፡ ታንቀው ፡ በተገደሉት ፡ በዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ላይ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ የፈረዱትን ፡ ሰዎች ፡ በሰላይ ፡ እየያዙ ፡ አስገደሏቸው ።

እቴጌ ፡ ምንትዋብም ፡ ቀድሞ ፡ ወዳሠሩት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወደ ፡ ቍስቋም ፡ ተመልሰው ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ በጾምና ፡ በጸሎት ፡ እንደቈዩ ፡ ዐረፉና ፡ በዚሁ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ተቀበሩ ። ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በኋላም ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ፹፯ ፡ እንደግማሾቹ ፡ ፺ ፡ ዓመት ፡ በእንደራሴነት ፡ አንቀጥቅጠው ፡ እንደ ፡ ገዙ ፡ ሞቱ ።

ራስ ፡ ጐሹም ፡ ለስሙ ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ እንደ ፡ ቀድሞው በዙፋናቸው ፡ አስቀምጠው ፡ ሙሉውን ፡ ሥልጣን ፡ ግን ፡ እርሳቸው ፡ ብቻ ፡ ይዘው ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ያዙ ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ንጉሡና ፡ ጐሹ ፡ ጠብ ፡

አደረጉ ። ስለዚህ ፡ በሹመትም ፡ በሌላም ፡ ምክንያት ፡ የራስ ፡ ጐሹ ፡ ጓደኞች ፡ ከጐንደር ፡ በራቁ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ራስ ፡ ጐሹን ፡ አሲዘው ፡ አሠሯቸው ። የዚህም ፡ ወሬ ፡ ለነደጃች ፡ ወንድ ፡ በወሰን ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ወንድ ፡ በወሰን ፡ ጐንደር ፡ ገብተው ፡ ጓደኛቸውን ፡ ራስ ፡ ጐሹን ፡ ከታሠሩበት፡ በታ በኀይል ፡ ፈቱና ፡ እሥልጣናቸው ፡ መለሷቸው ፡ የሚሉ ፤ እርሳቸውም ፡ እራሳቸው፡ እንደራሴነቱን ፡ ይዘው ፡ ለመንገሥም ፡ አስበው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሳይሆንላ ቸው ፡ ፱ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ እንደገዙ ፡ ከፈረስ ፡ ወድቀው ፡ ሞቱ ፡ የሚሉም፡ አሉ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ከዙፋናቸው ፡ አወረዱቸውና ፡ በግዞት ፡ ወደ ፡ ዋልድባ ፡ ገዳም ፡ ላኳቸው ። ንጉሡም ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፤ እንደ ፡ ሰነበቱ ፡ በሺሕ ፡ ፯፻፸ ፡ ዓ፡ ም፡ ዐረፉ ። ከርሳቸውም ፡ በኋላ ፡ ሰሎሞን ፡ ሁለት ዓመት ፡ ነግሠው ፡ ነበር ። በመጨረሻ ፡ ግን ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ «ፍቁር፡ ሰገድ» ተብለው ፡ ነገሡ ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፪ ።

## የዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

በታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ እንደተጻፈው ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ኀይለኛ ፡ የሆነ ፡ የን ጉሥ አውራ ፡ ያም ፡ ቢቀር ፡ እንደ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ያለ ፡ ጥብቅ ፡ እንደራሴ በመጥፋቱ ፡ ሁሉም ፡ በያለበት ፡ እነግሣለሁ ፡ እያለ ፡ ተነሣ ። በያውራጃው ፡ ጦር ነት ፡ እያደረገ ፡ እልቂት ፡ ሆነ ። ለም ፡ የነበረው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሆነ ፤ የምስለኔውና ፡ የጭቃ ፡ ሹሙ ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ያባቱን ፡ በሬ ፡ እያረደ ፡ ወደ ዱር ፡ ገባ ። እንደዚሁም ፡ በጐንደር ፡ ያሉ ፡ ደብተሮች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በሃይማኖት ፡ በሰዋስው ፡ በቅኔ ፡ እየተጣሉ ፡ ሁሉም ፡ የያውራጃውን ፡ ቀንደኛ ፡ ባላበት ፡ እየተከፋፈለ ፡ አንተ ፡ ጺጋ ፡ ብትሆን ፡ ትነግሣለህ ፤ አንተ ፡ ከራ ፤ አንተ፡ ቅባት ፡ ብትሆን ፡ ዓርባ ፡ ዓመት ፡ ትገዛለኽ ፡ በራእይ ፤ በዐውደ ፡ ነገሥት ፡ ተረ ድተነዋል ፡ እያሉ ፡ ብዙውን ፡ መኳንንትና ፡ ሕዝብ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ አዋጉት ። በዚህ፡ ዐይነት ፡ የርስ ፡ በርሱ ፡ ጦርነት ፡ ሲቀጥል ፡ በመጨረሻ ፡ የዐጼ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ፡ የታላቅ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ መነሣት ፡ ጥቂት ፡ ሊያሻሽለው ፡ ቻለ ። ይኸውም ፡ ለመዠመ ሪያ ፡ ጊዜ ፡ እንጂ ፡ ፍጻሜ ፡ ያለው ፡ ሰላምና ፡ ጸጥታ ፡ በነሱም ፡ ጊዜ ፡ አልተገኘም።

ከሰሎሞን ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በሺሕ ፡ ፯፻፸ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነገሡ ። የርሳቸውም ፡ አነጋገሥ ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ነገሥታት ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሊሆን ፡ ተዠምሮ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን አልሆነም ። እንዲያውም ፡ ከርሳቸው ፡ ቀደም፡ ብሎ ፡ በዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ጊዜ ፡ የደከመው ፡ በርሳቸው ፡ ጊዜ ፡ በጭራሽ ፡ የነገሥ ታቱ ፡ ኀይል ፡ ስለ ፡ ወደቀና ፡ መሳፍንቱ ፡ ስለ ፡ ገነኑ ፡ ስማቸው ፡ "ተፍጻሜተ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ ፈጻሚ ፡ መንግሥት ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ„ ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የነገሥታቱ ፡ ኀይል ፡ ደከመ ፡ ለማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ "መንግሥቱ„ ፡ ምንም፡

መከከል ፡ ውስጠ ፡ ቅያሜ ፡ ተመሠረተ ፤ ቢሆንም ፡ ሁለቱም ፡ ቅያሜያቸውን በየልባቸው ፡ ይዘው ፡ አዛዥና ፡ ታዛዥ ፡ ሆነው ፡ ሥራቸውን ፡ በስምምነት ፡ የሚቀጥሉ ፡ መስለው ፡ ለመታየት ፡ ተጣጣሩ ።

ስለዚህ ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ራስ ፡ ሚካኤልን ፡ አስከትለው ፡ ራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያውን ፡ ለመውጋት ፡ ሄዱ ። ከራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያውም ፡ ጋራ ፡ በጌምድርና ፡ ላስታ ፡ ወሰን ፡ ነፋስ ፡ ሙሳ ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ተገናኝተው ፡ ተዋጉና ፡ ራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያው ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ሲሸሹ ፡ ጋሎች ፡ ማርከው ፡ ለንጉሡ ፡ ሰጧቸው ። ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ ራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያውን ፡ ከሞት ለማዳን ፡ ሲሉ ፡ እባክዎ ፡ ባይሆን ፡ ይታሰር ፡ እንጂ ፡ አይገደል ፡ ብለው ፡ ንጉሡን ፡ ለምነዋቸው ፡ ነበር ፤ ንጉሡ ፡ ግን ፡ የራስ ፡ ሚካኤልን ፡ ልመና ፡ ሳይቀበሉ ፡ በጭካኔ ፡ በጥይት ፡ አስደበደቧቸው ። ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ በቀድሞ ፡ ቅያሜ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ስለ ፡ ተጨመረ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ቂማቸው ፡ እየባሰ ፡ ሄደ ።

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስሙን ፡ ያነሣነው ፡ የዳሞቱ ፡ ገዥ ፡ ፋሲል ፡ የጐንደርን ፡ እንደራሴነት ፡ ባለማግኘቱ ፡ በበኩሉ ፡ ተቀይሞ ፡ ኖሮ ፡ አሁን ፡ ንጉሡና ፡ እንደራሴው ፡ ከራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያው ፡ ጋር ፡ በሚዋጉበት ፡ ሰዓት ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ያገኘ ፡ ስለ ፡ መሰለው ፡ ከዳሞት ፡ መጥቶ ፡ በጌምድርን ፡ ወረረ ። ባንድ ፡ ወገንም ፡ ራስ ፡ ሚካኤልን ፡ እንዲያጠቃላቸውና ፡ እንደራሴነቱን ፡ እንዲይዝ ፡ ተስፋ ፡ ሰጥተው ፡ በስውር ፡ ያሥነሡት ፡ ራሳቸው ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። ይኸውም ፡ እውነት ፡ መሆኑ ፡ ወደፊት ፡ ይገለጻል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በገሃድ ፡ የታወቀው ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ለንጉሡ ፡ እንደራሴ ፡ መሆናቸው ፡ ፋሲልም ፡ መሸፈቱ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ራስ ፡ ማርያም ፡ ባሪያውን ፡ እንደ ፡ ወጋን ፡ እንዲሁም ፡ ፋሲልን ፡ አብረን ፡ ሄደን ፡ እንውጋው ፡ ወይም ፡ ጦርዎ ፡ በሙሉ ፡ ይሰጠኝ ፡ ብለው ፡ ለንጉሡ ፡ አመለከቷቸው ። ንጉሡ ፡ ግን የራስ ፡ ሚካኤል ፡ እንደራሴነትና ፡ አያያዛቸው ፡ ከብዷቸውና ፡ ቀኝቸው ፡ ስለ ፡ ነበር ፤ ራሳቸውም ፡ አለመሄዳቸውን ፡ ጦርም ፡ ለመስጠት ፡ አለመፍቀዳቸውን ፡ ገልጸው ፡ ሄደኽ ፡ አንተው ፡ ብቻኽን ውጋው ፡ ብለው ፡ አሰናበቷቸው ። ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ ቂማቸውን ፡ በልባቸው ፡ ይዘው ፡ ከንጉሡ ፡ ተሰናብተው ፡ ፋሲል ፡ ከጐንደር ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ተቀመጠበት ፡ ወደ ፡ አዘዞ ፡ ለመዋጋት ፡ መጡ ፡ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ከንተ ፡ ጋራ ፡ አልሄድም ፡ ማለት ፡ ሳይበቃቸው ፡ ቀርቶ ፡ የገዛ ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ከነፋሲል ፡ ተደባልቀው ፡ ራስ ፡ ሚካኤልን ፡ እንዲወጉ ፡ በስውር ፡ ላኳቸው ፡ የዚህንም ፡ ምሥጢር ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ከእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ አገኙት ። ሁለቱም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወዳጅ ፡ ሆኑ ፡ ይባላል ።

ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ በመጨረሻ ፡ ወታደራቸውን ፡ ይዘው ፡ ከፋሲል ፡ ጋራ ፡ ተዋጉና ፡ በቶሎ ፡ ድል ፡ አደረጉ ። ፋሲልም ፡ ከጥቂት ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ ሸሽቶ ፡ ወዳገሩ ፡ ወደ ፡ ዳሞት ፡ ተመለሰ ። እርሱ ፡ ሸሽቶ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡

እምርኮ ፡ ላይ ፡ ውስጡን ፡ ከንጉሡ ፡ ታዘው ፡ የመጡት ፡ የዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ አሽከሮች ፡ አብረው ፡ ተገኝተው ፡ ተማረኩ ። በዚህ ፡ ንጉሡ ፡ ለፋሲል ፡ መርዳታቸው ፡ በገሃድ ፡ ታወቀ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ሚከኤል ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ከጦርነቱ ፡ ተመልሰው ፡ ጐንደር ፡ ገቡ ። ወዲያውም ፡ ንጉሡን ፡ ለማናደድ ፡ ሲሉ ፡ ከጦርነቱ ፡ ተመልሰው ፡ በገቡበት ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ የጐንደርን ፡ ከተማ ፡ አቃጠሉት ። ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ እንደገቡ ፡ በቶሎ ፡ ሊቃውንቱና ፡ መኳንንቱን ፡ ሰብስበው ፡ "በንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ የሸፈተውን ፡ ልወጋ ፡ ሄጄ ፡ ንጉሡ ፡ እኔን ፡ በመርዳት ፡ ፈንታ ፡ ለሽፍታው ፡ ርዳታ ፡ የገዛ ፡ አሽከሮቻቸውን ፡ ላኩ ። በዚህም ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ንጉሡ ፡ አዘውት ፡ ፩ ፡ ሰው ፡ ተደብቆ ፡ ጥይት ፡ ተኩሶ ፡ ሊገድለኝ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በኔ ፡ ፈንታ ፡ ባጠገቤ ፡ ቆሞ ፡ ጭራ ፡ ይዞ ፡ ይከለክል ፡ የነበረው ፡ አሽከሬ ፡ ሞተ ። ይኸንኑም ፡ ሁሉ ፡ እናንተ ፡ የተሰበሰባችሁ ፡ ታውቃላችሁና ፡ ፍረዱኝ ፡" ብለው ፡ ተናገሩ ።

በዚያም ፡ ከቆሙት ፡ ግሚሶቹ ፡ ንጉሥ ፡ ባይሆን ፡ ይታሰራል ፡ እንጂ ፡ አይገደልም ፡ አሉ ። የቀሩት ፡ ራስ ፡ ሚከኤልን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ከሆነ ፡ ንጉሡ ፡ ይገደላሉ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ። በመጨረሻም ፡ አንድ ፡ ራስ ፡ ሚካኤልን ፡ የማይወድ ፡ የትግሬ ፡ ደብተራ ፡ «ንጉሥ ፡ ከገደሉ ፡ ግዛት ፡ አይገባቸውም ፡ ለማሰኘት» ፡ ሲል ፡ ንጉሥ ፡ በጠመንዣ ፡ አይገደልም ፡ እንጂ ፡ በሻሽ ፡ ታንቆ ፡ ይሞታል ፡ ብሎ ፡ ፈረደ ፡ ይባላል ። ስለዚህ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ በደል ፡ ቢበዛባቸው ፡ ከትግሬ ፡ አስመጥተው ፡ እንደራሴ ፡ ያደረጓቸውን ፡ ንጉሣቸውን ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስን ፡ በሻሽ ፡ አሳንቀው ፡ በሺሕ ፡ ፯፻፷፩ ፡ ዓ. ም. ገደሏቸው ። ሬሳቸውም ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ባንድ ፡ ጕድጓድ ፡ ተጥሎ ውሎ ፡ ካደረ ፡ በኋላ ፡ በሌላ ፡ ቀን ፡ ከዚያ ፡ ወጥቶ ፡ ጐንደር ፡ በቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተቀበረ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ስለ ፡ ጋሎች ፡ መውደቅ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ከራስ ፡ ሚካኤል ፡ ጋራ ፡ ቢተባበሩ ፡ ስለ ፡ ልጅ ፡ ልጃቸው ፡ ስለ ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ሕይወት ፡ አስቀድመው ፡ ተጨንቀው ፡ ነበር ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ለማዳን ፡ ሳይችሉ ፡ ቀርተው ፡ በሞቱም ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ አዘኑ ፡ ይባላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፱ ።

## ስለ ፡ ነገሥታቱ ፡ ሥልጣን ፡ መውደቅ ።

በአኵስም ፡ ተከታትለው ፡ የመጡትን ፡ የነገሥታት ፡ ዘሮች ፤ ዮዲት ፡ (ይሁዳዊት) የምትባለዋ ፡ ኃይለኛ ፡ የፈላሻ ፡ ሴት ፡ በ፰፻፵፯ ፡ ዓ. ም. ላይ ፡ እንዳጠፋቻቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ሁሉ ፡ የሚገኝ ፡ ነው ። በርሷም ፡ ዠማሪነት ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ዛጔዎች ፡ ከ፱፻ ፡ ዠምረው ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፪፻፷፫ ፡ ዓ. ም. ፡ ድረስ ፡ አኵስምና ፡ ሸዋ ፡ በነበሩበት ፡ ነገሥታት ፡ መካከል ፡ ገብተው ፡ ላስታ ፡ ሆነው ፡ ኢትዮጵያን ፡ መግዛታቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በነርሱ ፡ መጨረሻ ፡ ከይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጊዜ ፡ (ከሺሕ ፡ ፪፻፸ ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፭፻ ፡ ዓ. ም.) ድረስ ፡

ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ተነሥቶ ፡ በታወቀው ፡ ኃይሉ ፤ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ አሸንፎ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመውረር ፤ የርሱም ፡ ተከታይ ፡ ኑር ፡ መሐመድ ፤ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስን ፡ አሸንፎ ፡ እስከ ፡ መግደል ፡ መድረሱን ፡ ባለፈው ፡ አንብበናል ፤ ከነዚህ ፡ በቀር ፡ የነገሥታቱን ፡ ዘውድ ፡ ቀምቶ ፡ ሥልጣናቸውን ፡ የገፈፈ ፤ እነርሱንም ፡ ያዋረደ ፡ በታሪኩ ፡ ውስጥ ፡ የሚታወሰን ፡ የለም ። የራስ ፡ ዘሥላሴ ፡ በገዛ ፡ እጅ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ መንገሥ ፤ የራስ ፡ ዮስጦስም ፡ ወደ ፡ ዙፋን ፡ መውጣት ፡ መንገዱ ፡ የተለየ ፡ ጊዜውም ፡ ያጠረ ፡ ነው ።

ረዥም ፡ ጊዜ ፡ ባለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ነገሥታቱ ፡ በሕዝቡም ፡ በመኳንንቱም ፤ በካህኑም ፡ በሊቃውቱም ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ የመፈራት ፤ የመከበር ፤ የማዘዝ ፡ ሥልጣንና ፡ ችሎታቸውም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ነገሥታቱ ፡ በምድር ፡ የእግዚአብሔር ፡ እንደራሴ ፡ በመሆናቸው ፡ ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፤ መሲሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ እየተባሉ ፡ ሕዝቡ ፡ የሚሰጣቸው ፡ ግምት ፡ ልዩ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ በቤተ ክህነቱም ፡ ላይ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ። ቢሾሙ ቢሽሩ ፤ ቢያስሩ ፡ ቢፈቱ ፡ በበላይ ፡ ያለው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከመፍራት ፡ በቀር ፡ በምድር ፡ ጠያቂ ፡ የለባቸውም ፤ መኳንንቱና ፡ ሕዝቡ ፡ ካህኑም ፡ ይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ የነርሱ ፡ አገልጋይና ፡ ታዛዥ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ጠያቂአቸው ፡ ተከራካሪያቸው ፡ አይደለም ። በነርሱ ፡ ላይ ፡ እጁንም ፡ አንደበቱንም ፡ ያነሣውን ፡ ምላሱና ፡ እጁ ፡ ይቈረጥ ፡ ብሎ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ የወሰነው ፡ ደኅና ፡ አንድርጎ ፡ ተመሥርቷል ። ስለዚህ ፡ ያው ፡ ልንገሥ ፤ አትንግሥም ፡ እየተባባሉ ፡ በሚከታተሉበት ፡ ጊዜ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ነገሥታቱ ፡ ይገዳደላሉ ፡ እንጂ ፡ ከሕዝቡና ፡ ከተርታው ፡ መኳንንት ፡ ወገን ፡ ንጉሡን ፡ የመድፈር ፡ ነገር ፡ አይታይም ፤ ቢታይም ፡ በብርቅ ፡ ነው ፡ ነገሥታቱ ፡ ግን ፡ የጥፋቱ ፡ አኳኋን ፡ እንደ ፡ ታያቸው ፡ ወይም ፡ ሰውዮውን ፡ በሚፈሩትና ፡ በሚጠረጥሩት ፡ ዓይነት ፡ ሲዋጋ ፡ ከሞተው ፡ በቀር ፡ ሳይሞት ፡ የተማረከውን ፤ እጅና ፡ እግር ፡ ምላስ ፡ እያስቈረጡ ፡ በሰይፍ ፡ እያስመቱ ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ እያሰቀሉ ፡ ይገድላሉ ። ለዚህም ፡ ፍርድ ፡ ሲፈልጉ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ አዘርግተው ፡ በጉባኤ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ያለፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ሲገድሉ ፡ መኖራቸውን ፡ በየታሪኩ ፡ በየዘመኑ ፡ አንብበናል ። ይኸም ፡ ከ፲፰ና ፡ ዓ. ም. በፊት ፡ በመካከላቸውና ፡ በጥንቱ ፡ የዘመን ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ዛሬ የሠለጠኑት ፡ የአውሮፓ ፡ ነገሥታት ፡ ከእንግሊዞች ፡ በቀር ፡ ባገራቸው ፡ ይሠሩት ፡ በነበረው ፡ የሚመሳሰል ፡ እንጂ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብቻ ፡ የተደረገ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፤ መሲሐ ፡ እግዚአብሔር ፤ ወይም ፡ ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የመባል ፡ ስያሜ ፡ ለሁሉም ፡ በየጊዜያቸው ፡ እንዳላቸው ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ ዘውድ ፡ ደፍተው ፡ ለንጉሥነት ፡ የተቀበሉት ።

አንበሳ ፡ ሰገድ ፤ አንበሳ ፡ የሰደገለት ፤ ፀሐይ ፡ ሰገድ ፡ ፀሐይ ፡ የምትሰግድለት ፡ እየተባሉ ፡ በመጠሪያ ፡ ስማቸው ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ ስም ፡ እንደሚሰጣቸው ፡ እነሆ ፡ አንብበናል ። እንደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አለቃ ፡ ብፁዕና ፡ ቅዱስ ፡ የሚባሉበት ፡ መንገድ ፡ አይጠፋም ።

ይኸን ፡ በመሰለ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ክብርና ፡ ግርማ ፤ ሥልጣንና ፡ መፈራት ፡ የዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ አባቶች ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፤ ዐፄ ፡ በካፋ ፡ መሲሕ ፡ ሰገድ ፤ ዐፄ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፤ . . . . . ገዝተው ፡ እንዳለፉ ፡ እንደዚሁ ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ዠምረው ፡ ነበር ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ መጨረስ ፡ አልሆነላቸውም ። ከገበሬም ፡ ቢሆን ፡ ከነ ጋዴ ፤ ከካህንም ፡ ቢሆን ፡ ከእጀ ፡ ጥበበኛ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስፈሪውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በድንገት ፡ ይለውጠዋል ። እግዚአብሔር ፡ ኀይሉን ፡ እንኳን ፡ በወንድ ፡ በሴት ፡ በኩል ፡ ለመግለጽ ፡ የፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወንዶች ፡ ሁሉ፡ በሴትዮዋ ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ ለመመከት ፡ ጉብዝና ፡ ይነሣቸዋል ። ባለፈው ፡ የጠቀስና ትን ፡ የዮዲትን ፡ ታሪክ ፡ ከመዠመሪያው ፡ ምዕራፍ ፡ ስናነብ ፡ ነገሩን ፡ መገንዘብ ፡ እን ችላለን ።

በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ከትግሬ ፡ መጥተው ፡ ጐንደር ፡ መዠመሪያ ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አማካሪ ፡ ቀጥሎ ፡ ለልጃቸው ፡ ለዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ እንደራሴ ፡ ሲሆኑ ፡ ይኸን ፡ የመጨረሻ ፡ የድፍረት ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ ለእንደራሴነት ፡ ያስመጧቸውን ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስን ፡ በሻሽ ፡ አሳንቀው ፡ ይገድላሉ ፡ ብሎ ፡ የገመተ ፡ መቼም ፡ አልነበ ረም ። ባሕታውያኑ ፡ በሕልም ፤ ደብተሮቹ ፡ በቊጥር ፡ አስቀድሞ ፡ ዐውቀውት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አናውቅም ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፤ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ድፍረትና ፡ ችሎት ፡ ንጉሡን ፡ ካስገደሉ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ ለስሙ ፡ ዘውድ ፡ የጫኑ ፡ ንጉሥ ፡ ማስቀመጣቸው ፡ ባይቀር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ የነበረውን ፡ ሥልጣን ፡ ይዘው ፡ ያስተዳድሩ ፡ ዠመር ፤ አዲሱ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትም ፡ የሚደረገውን ፡ ሹም ፡ ሽርና ፡ አስተዳደር ፡ ወሬውን ፡ እየሰማ ፡ ባዳራሹ ፡ ሆኖ ፡ ከመታዘብ ፡ በቀር ፡ ያለፉት ፡ ነገሥታት ፡ እንደራሴዎቻቸውን ፡ እንደ ፡ ዕቃ ፡ ይለዋውጡ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ እንኳን ፡ ለመለወጥና ፡ ለመሻር ፡ ይህ ፡ ለምን ተደረገ ፡ ብሎ ፡ ለመከራከርና ፡ ለመቈጣት ፡ ዐቅም ፡ አላገኙም ።

ይኸም ፡ የደረሰበትን ፡ ምክንያት ፡ ከታሪክ ፡ ነገሥት ስንፈላለግ ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ነገሥታቱ ፡ በጐንደር ፡ ተድላና ደስታ ፤ ጨዋታና ፡ እብሬት ፡ ስለ ፡ አበዙ ፡ የነዚያን ፡ ግፍ ፡ ቈጥሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ራስ ፡ ሚካኤልን ፡ በአፄ ፡ ኢዮአስና ፡ በልጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ አስነሣባቸው ፡ ሲል ፡ ሁኔታውንም ፡ ከአኵስም ፡ ነገሥታትና ፡ ከዮዲት ፡ ጋራ ፤ ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልና ፡ ከግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ጋራ ፡ እያገናኘ ፡ ሲያመጣው ፡ እንመለከታለን ። ስለዚህ ፡ ነገሥታቱ ፡ ቢበድሉ ፡ እነራስ ፡ ሚካኤልን ፤ እነራስ ፡ ዐሊ ፡ ትልቁን ፡ አስነሣ ፤ መሳፍንቱ ፡ ቢበድሉ ፡ ደግሞ ፤ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ አስነሣ ፡ ማለት ፡ የተለመደና ፡ የሚመስል ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ይኸም ፡ ታሪክነቱ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን በሥልጣን ፡ ላይ ፡ የወጣውን ፤ ገና ፡ የሚወጣውን ፡ ለማስጠንቀቂያ ፡ ጭምር ፡ ይረዳል ፡ ተብሎ ፡ የመጣ ፡ ሳይሆንም ፡ አይቀርም ።

## የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ፬ኛ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

### ምዕራፍ ፡ ፹ ።

### ንጉሡ ፡ የተቀኙዋቸው ፡ ቅኔዎች -የንጉሡ ፡ አሟሟት ፤-የጀምስ ፡ ብሩስ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መምጣት ።

ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስን ካስገደሉ በኋላ ፡ ለራሳቸው ፡ የሚስማሚቻቸውን ፡ በወህኒ ፡ አምባ ፡ ከሚቀመጡት ፡ ነጋሥያን ፡ ውስጥ ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድን ፡ ልጅ ፡ የዐፄ ፡ በካፋን ፡ ወንድም ፡ ዮሐንስን ፡ አውርደው ፡ በዙፋን ፡ አስቀመጧቸው ።

ዐፄ ፡ ዮሐንስም ፡ ከወህኒ ፡ አምባ ፡ ወርደው ፡ ሲነግሡ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ፸ ፡ ዓመት ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ እጃቸው ፡ ቈራጣ ፡ ነበር ፤ ስለዚህ ፡ ስማቸውም ፡ አንድ ፡ እጁ ፡ ዮሐንስ ፡ ይባላል ፡ ያስቈረጧቸውም ፡ ዙፋንን ፡ ቢቀናቀኗቸው ፡ ዐፄ ፡ በካፋ ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። ዐፄ ፡ በካፋ ፡ በዘመናቸው ፡ ቢታመሙ ፡ እኔ ፡ የሞትሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ርሱ ፡ ይነግሣል ፡ ብለው ፡ ከወህኒ ፡ አምባ ፡ አውርደው ፡ ባጠገባቸው ፡ ያስቀመጧቸው ፡ ርሳቸው ፡ ናቸው ፡ ገጽ ፡ ፲፱፻፺፯–፲፱፻፺፰ ፡ ተመልከት ።

ሕዝቡና ፡ መኳንንቱም ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሊነግሥ ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ ክርክር ፡ አቅርቦ ፡ ነበር ። አንድ ፡ እጁ ፡ ዮሐንስ ፡ በወህኒ ፡ አምባ ፡ ሲኖሩ ፡ ዕድሜያቸውን ፡ ቅኔና ፡ መጻሕፍትን ፡ በመማር ፡ ስለ ፡ አሳለፉ ፡ እንዳንድ ፡ ሊቅ ፡ መጻሕፍትና ፡ ቅኔ ፡ ዐዋቂ ፡ ነበሩ ፤ ስለዚህ ፡ የኅዳር ፡ ሚካኤል ፡ ዕለት ፡ አእላፍ ፡ ከሚባለው ፡ አጣጣሚ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገብተው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ሥላሴ ፡ ቅኔ ፡ ተቀኙ ፡ ይባላል ።

መንክራተ ፡ ግብጽ ፡
ሙሴ ፡ ረሰየ ፡ ከመ ፡ ፈቀደ ፤
አምጣነ ፡ ለሙሴ ፡ መልአኩ ፡ ወመድኃኔ ፡ ገጹ ፡ እምገጽ ፡
ዘባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ ሚካኤል ፡ አንቀጽ ።
አመኒ ፡ በዕፅ ፡ ሥጠቱ ፤ ወአመ ፡ ርፍአቱ ፡ በዕፅ ፡
ለባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ ልብሰ ፡ ተግሣጽ ፡
መቅረፀ ፡ ይእቲ ፡ በትሩ ፡ ዘግብጽ ፡
ወመርፍኡ ፡ ይእቲ ፡ መቅረዕ ።

ትርጓሜው ።

የግብጽን ፡ ድንቅ ፡ ነገሮች ፡ ሙሴ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ አደረገ ፤
ለሙሴ ፡ መልክተኛውና ፡ የፊቱ ፡ አዳኝ ፡ የኤርትራ ፡ በር ፡ ሚካኤል ፡ ነውና ።
የተግሣጽ ፡ ልብስ ፡ የኤርትራ ፡ ባሕር ፡ መቀደዱና ፡ መሰፋቱ ፡ በዕንጨት ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ የግብጽ ፡ በትር ፡ መቀሱ ፡ ናት ፤
መቀሲቱም ፤ መርፌው ፡ ናት ።

ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ግን ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ የኤርትራን ፡ ባሕር ፡ ከፍሎ ፡ ሙሴን ፡ እንዳሻገረውና ፡ የእስራኤል ፡ መሪ ፡ እንዳደረገው ፤ ሥዑል ፡ ሚካኤልም ፡ ወህኒ ፡ አምባን ፡ ከፍተው ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ፩ኛን ፡ ንጉሥ ፡ ማድረጋቸውን ፡ ያሳያል ።

በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ ስለሌላቸው ፡ ሰዉ ፡ ይንገሥ ፡ አይንገሥ ፡ እያለ ፡ ሲጨቃጨቅ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ ብለው ፡ ተቀኙ ፡ ይባላል ።

. . . . . . ጊዜያትሂ ፡ አእላፈ ፡ እመ ፡ መከሩ ፡ አእላፍ ፤
አንተ ፡ ዘኃለይከ ፡ ወዘወሰንከ ፡ ኢይትርፍ ።

የትርጓሜውም ፡ አሳብ ፡ ብዙ ፡ ሺህ ፡ ሰው ፡ የመከረውን ፡ ቢመክር ፡ አንተ ፡ (እግዚአብሔር ) ፡ ካስብኸውና ፡ ከወሰንኸው ፡ አያልፍም ፡ ማለት ፡ ነው ።

በውነትም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ ሆነና ፡ ሕዝቡም ፡ አልቀበልም ፡ እንዳይል ፡ ራስ ፡ ሚካኤልን ፡ በመፍራት ፡ የዮሐንስን ፡ ንጋሢነት ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ተቀበለ ። ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ እኅታቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ሥላሴን ፡ ለንጉሡ ፡ ዳሩላቸውና ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ራስ ሚካኤል ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሆኑ ። ከዐጼ በካፋ ፡ ዠምሮ ሥልጣናቸው ፡ ገኖ ፡ ይኖር ፡ የነበረው ፡ የእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ ሥልጣን ፡ ተወሰነ ። የቀድሞ ነገሥታት ፡ ይሠሩት ፡ የነበረውም ፡ ቀረና ፡ አሁን ፡ እንደራሴው ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ በፈቃዳቸው ፡ በያገሩ ፡ ታማኞቻቸውንና ፡ ዘመ ዶቻቸውን ፡ ሹሙበት ፡ ለልጃቸውም ፡ ጐጃምን ፡ ሰጡት ። እቴጌ ምንትዋብም ፡ ዕድሜያቸውም ፡ ስለ ፡ ጸና ፡ በራስ ሚካኤል ፡ አያያዝ ፡ ተስፋ ፡ ቈርጠው ፡ ሁሉንም ፡ ትተው ፡ በሠሩት ፡ በቊስቋም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ በጸሎት ፡ በሰጊድ ፡ ተቀመጡ ።

በዚህም ፡ ዘመን ፡ በሺህ ፡ ፲፯፻፷፪ ፡ ዓመት ፡ (እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ አቈጣጠር ፡ ፲፯፻፷፱ ፡ ) ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ የሚባለው ፡ እንግሊዛዊ ፡ ጐንደር ፡ መጣና ፡ ከራስ ፡ ሚካኤልና ፡ ከዐጼ ፡ ዮሐንስ ፡ ተገናኝቶ ፡ በጐንደር ፡ ተቀመጠ ። ርሱም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተቀምጦ ፡ ወዳገሩ ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፤ BRUCE'S TRA VEL የብሩስ ፡ ጕዞ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ በ፭ ፡ ቮሊም ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሁኔታና ፡ ስለ ፡ ታሪኳ ፡ ጽፏል ። ያባይንም ፡ የምንጭ ፡ መነሻ ፡ ያገኘሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ብሏል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይኸኛው ፡ በሙሉ ፡ አልታመነለትም ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዳሞት ፡ ሸፍቶ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ያስቸገረው ፡ ፋሲል ፡ አሁ ንም ፡ አልገባም ፡ ነበርና ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ርሱን ፡ ለመውጋት ፡ ይዘጋጁ ፡ ዠመር ።

ዝግጅቱም ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡን ፡ አብረን እንሂድና ፡ ፋሲልን ፡ እንውጋ ፡ ብለው ፡ አማከሯቸው ። ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ግን ፡ በወህኒ ፡ አምባ ፡ ሲኖሩ ፡ ጸሎትና ፡ ስግደት ፡ በማዘውተር ፡ ኖሩ ፡ እንጂ ፡ የጦርነት ፡ ነገር ፡ ሞክረውት ፡ አያውቁም ፡ ነበርና ፡ «አልችልም ፡ በዚህም ፡ ላይ ‹ ሽምግያለሁ › ፡ ብለው ፡ እምቢ ፡ አሏቸው ። ቢያበብሏቸውም ፡ ባትፈልግ ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ አምባዩ ፡ መልሰኝ ፡ እንጂ ፡ አልሄ

ድም ፡ አሉ ፡ ይባላል ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ግን ፡ አሁን ፡ እንቢ ፡ ማለታቸው ፡ እኔ ፡ እልፍ ፡ ስል ፡ ሌላ ፡ እንደራሴ ፡ ለማድረግ ፡ አስበው ፡ ይሆናል ፡ ሲሉ ፡ ተጠራጥረው ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ ንጉሡን ፡ ከመብል ፡ ጋራ ፡ መርዝ ፡ አብልተው ፡ አስገደሏቸው ፡ ይባላል ። የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ፪ኛም ፡ ዘመን ፡ መንግሥታቸው ፡ ፩ ፡ ዓመት ፡ ብቻ ነው ፡ የሞቱትም ፡ በሺሕ ፡ ፯፻፷፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነው ።

## የዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

## ምዕራፍ ፡ ፹፩ ።

### የፋሲል ፡ ሽፍትነት ፤–የራስ ፡ ሚካኤል ፡ ጭካኔ ፡ –የራስ ፡ ጕሹ ፡ ሥልጣን ፡ መያዝ ፡ – የእቴጌ ፡ ምንትዋብና ፡ የራስ ፡ ሚካኤል ፡ ፍጻሜ ።

ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ የኝህን ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስን ፡ ልጅ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ስመ ፡ መንግሥታቸውን ፡ «ኀያል ፡ ሰገድ» ፡ አሰኝተው ፡ አነገሧቸው ። ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ሲነግሡ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ነበር ። ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ካነገሡ ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡ ፡ በደስታ ፡ እንዲያብርላቸው ፡ ንጉሡን ፡ ይዘው ፡ የዳሞቱን ፡ ፋሲልን ፡ ለመውጋት ፡ በሺሕ ፡ ፯፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ ሄዱ ። ፋሲልም ፡ የዳሞትን ፡ የአገውን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ፋጊት ፡ ከሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበርና ፡ በዚሁ ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ጦርነቱ ፡ ተዠመረ ። ብዙ ፡ ሰዓት ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በኀይል ፡ ሲዋጉ ፡ ቈዩ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ ፲ ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ፋሲል ፡ ድል ፡ ሆነና ፡ በፈረስ ፡ ከጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ አመለጠ ። ፈረሰኞችም ፡ ቢከታተሉት ፡ ለማግኘት ፡ አልቻሉም ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከርሱ ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ የተማረኩትን ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ ትእዛዝ ገደሏቸው ። ከነዚህም ፡ ዋጪቃ ፡ የሚባል ፡ የፋሲል ፡ ተከታይ ፡ ይምሩኛል ፡ ብሎ ፡ እጁን ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ ጭፍሮቻቸው ፡ እርሱን ፡ ገድለው ፡ ቈዳውን ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ ገፈው ፡ እንደ ፡ ስልቻ ፡ ሰፍተው ፡ ገለባ ፡ ሞልተው ፡ ለራስ ፡ ሚካኤል ፡ አሳዩዋቸው ፡ ይባላል ። የዚህም ፡ ታሪክ ፡ በብዙ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ደራሲዎችና ፡ ባገራችንም ፡ ጽሑፍ ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ።

ሞት ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ዐይነት ፡ ሥጋ ፡ በለበሰውና ፡ የዚህም ፡ ሥቃይ ፡ ሊሰማው ፡ በሚችል ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ የእብሪትና ፡ የጭካኔ ሥራ ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ሲፈጽም ፡ አስደናቂ ፡ ነገር ፡ ነው ። የዚህ ፡ ዐይነትም ፡ ግዳይ ፡ የገዳዩቹን ፡ ልብ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ በኵራት ፡ እንደሚሞላ ፡ አይታወቅም ።

ይኸውም ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ብዙ ፡ መኳንንት ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ እንዲሸፍቱ ፡ ምክንያት ፡ ሆነ ። ከነዚሁም ፡ ውስጥ ፡ ያማራ ፡ ሣይንቱ ፡ ራስ ፡ ጕሹና ፡ የላስታው ፡ ደጃች ፡ ወንድ ፡ በወሰን ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት ፡ ታላላቅ ፡ መኳንንት ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለው ጨካኝ ፡ አንገዛም ፡ ብለው ፡ ሸፈቱባቸው ፤ ብዙም ፡ አባሪ ፡ አገኙ ።

ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ ከነዚህ ፡ አላይ ፡ ከተጠሩት ፡ በቀር ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ እንደተነ ሣባቸው ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ፡ ጐንደርን ፡ ትተው ፡ ንጉሡን ፡ ተክለ፡ ሃይማኖትን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ አኵስም ፡ ሄዱ ። አኵስም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ ትእዛዝ ፡ ለን ጉሡ ፡ የአኵስም ፡ ሕዝብ ፡ ብዙ ፡ ገጸ ፡ በረከትና ፡ መጥን ፡ አገባ ።

ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ጐንደርን ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ አኵስም ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ በለሙሉ ፡ ሥልጣንነትና ፡ ኀይለኝነት ፡ ተስፋ ፡ ቈርጠው ፡ በጸሎትና፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ በማዘውተር ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ተወስኛለሁ ፡ ብለው ፡ የነበሩት ፡ እቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ መራቅ ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሕፃኑን ፡ የማቼን፡ የዐፄ ፡ ኢያሱን ፡ ልጅ ፡ ለስሙ ፡ አንግሠው ፡ ሥልጣኑን ፡ ለመያዝ ፡ አስበው ፡ ነበር። ዳሩ ፡ ግን ፡ መኳንንቱ ፡ የእቴጌዪቱን ፡ ፈቃድ ፡ ስላልተቀበሉ ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ በሄ ዱት ፡ በንጉሡ ፡ በተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ምትክ ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድን ፡ ልጅ ፡ ሱስንዮስ ፡ የሚባለውን ፡ አንግሠናል ፡ ብለው ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ።

ፋሲልም ፡ ከራስ ፡ ሚካኤል ፡ ተዋግቶ ፡ በተሸነፈ ፡ ጊዜ ፡ ሸሽቶ ፡ በዳሞት ፡ ነበ ርና ፡ ይኸንን፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከዳሞት፡ ተነሥቶ፡ ጐንደር ፡ ገብቶ ፡ የመንግሥቱን፡ ሥል ጣን ፡ ለመያዝ ፡ አሰበ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሦስቱ ፡ ታላላቅ ፡ መኳንንቶች ፡ ጐሹ፤ ያየኸ ይራድ ፤ ወንድ ፡ በወሰን ፤ አናስገባም ፡ ብለው ፡ ለጦርነት ፡ ተሳለፉት ። ፋሲልም ፡ አሳቡ ፡ እንዳልተሳካለት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እነሱን ፡ ለመጕዳት ፡ ሲል፡ አሳቡን፡ ያን ፡ ያኸል እየተጣላቸው ፡ ከተዋጋቸው ፡ ከንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትና ፡ ከራስ ፡ ሚካኤል፡ ጋራ፡ አደረገ ። ከነሱም ፡ ተላልኮ ፡ ታረቀ ፤ ፋሲልም ፡ በጊዜው ፡ በኀይለኝነት ፡ ስሙ ፡ የተጠራ ፡ ነውና ፡ ከንጉሡና ፡ ከራስ ፡ ሚካኤል ፡ መታረቁ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ ከነጐሹ፤ ከነወንድ ፡ በወሰን ፡እየከዳ ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ እየሄደ ፡ ለንጉሡ፡ ገባ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ንጉሣቸውን ፡ ይዘው ፡ ከዐርባ ፡ ሺሕ ፡ የሚ በልጥ ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ጕዞ ፡ ዠመሩ ። በጕዘውም ፡ ጊዜ ፡ እንግ ሊዙ ፡ ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ አብሮ ፡ ነበር ። በመንገድም ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ የተቋቋማ ቸው ፡ ሳያገኙ ፡ ጐንደር ፡ በሰልፍ ፡ ገቡ ። ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ነግሦ ፡ የነበረው ፡ ሱስን ዮስም ፡ ከጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ጐንደርን ፡ ለቆ ፡ ወደ ፡ ቋራ ፡ ጫካ ፡ ሸሸ ። ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትና ፡ ራስ ፡ ሚካኤልም ፡ ጐንደር ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ እገሌ ፡ ንጉሡን ፡ አምቷል ፤ እገሌ ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ ክፉ ፡ መክሯል ፡ እየተባለ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ እየተ ያዘ ፡ በጥይትና ፡ በሰይፍ ፡ ተገደለ ።

በከተማ ፡ የተገኘውን ፡ ሕዝብ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅጣት ፡ ሲሣቅዩት ፡ ዋኖቹ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ የሸፈቱት ፡ መኳንንቶች ፡ ከነሠራዊታቸውና ፡ ከነጦር ፡ መሣሪያቸው፡ በውጭ ፡ ሆነው ፡ ጦር ፡ እያሳበሩ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ። እቴጌ ፡ ምንትዋብም ፡ ከነተ ከታዮቻቸው ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ፡ ኀይለኛውም ፡ ፋሲል ፡ እንደገና ፡ ከነዚሁ ፡ ጋራ፡ ተመልሶ ፡ ተደባለቀ ። የእነዚህም ፡ ወገን ፡ ኀይላቸው ፡ እየበረታ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ ከዋና፡ ሰፈራቸው ፡ ከደንቢያ ፡ እስከ ፡ ጐንደር ፡ ጫፍ ፡ እየሄዱ ፡ ከብትም ፡ መዝረፍ፡ ቤትም፡ ማቃጠል ፡ ዠመሩ ።

ራስ ፡ ሚከኤልም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ወደ ፡ ሽምግልና ፡ ኀይላቸው ፡ ወደ ፡ ድካም ፡ የተቃረበ ፡ ቢሆን ፡ በከተማው ፡ ተቀ ምጠው ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ የሽፍትነት ፡ ሥራ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፤ ተናደው ፡ ጭፍሮቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ለውጊያው ፡ ተነሡ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከበጌምድርም ፡ ከጐ ጃምም ፤ ከላስታም ፡ እየሄደ ፡ ከሽፍቶቹ ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ተደበለቀ፡ ከራስ ፡ ሚከኤል ፡ ጦር ፡ የነደጃች ፡ ወንድ ፡ በወሰን ፡ ጦር ፡ ሁለት ፡ ዕጥፍ ፡ ይበልጥ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ የነበሩበት ፡ ሥፍራ ፡ ከጐንደር ፡ በደቡብ ፡ በኩል ስበር ፡ ቀኻ ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ነበርና ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ እዚሁ ፡ ሥፍራ ፡ ድረስ ፡ ሄደው ፡ በሺሕ ፡ ፲፯፻፷፬ ፡ ዓ፡ ም፡ በግንቦት ፡ ወር ፡ ጦርነት ፡ ተጋጠሟቸው ፤ ጦርነቱም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ሲግል ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ሲበርድ ፡ እስከ ፡ ስምንት፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ቈየ ፡ ይባላል ።

ውጊያውም ፡ የመሣሪያ ፡ ጦርነት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የዲፕሎማቲክም ፡ ጭምር ፡ ነበር ፡ ይኸውም ፡ ሽፍቶቹ ፡ ራስ ፡ ሚካኤልን ፡ ትተው ፡ ከኛ ፡ ጋራ ይሁኑና ፡ ዙፋንዎን ፡ እንደያዙ ፡ ይቀመጡ ፡ እያሉ ፡ ለንጉሡ ፡ ለዐፄ ፡ ተክለ፡ ሃይማኖት ፡ ይልኩባቸው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከዲፕሎማቲኩ ፡ ኀይል ፡ የልብ፡ ጦርነቱም፡ ከነራስ ፡ ጐሹ ፡ ወገን ፡ በጣም ፡ ተጭኖ ፡ ስለነበር ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ከነሰዋቸው ፡ ንጉሡን ፡ እንደያዙ ፡ ከጦርነቱ ፡ ሥፍራ ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ተመለሱ እነዚያም ፡ እግር ፡ በእግር ፡ እየተከታተሉ ፡ ሄደው ፡ ጐንደርን ፡ ከበቡ ። ከመ ካከላቸውም ፡ ጐሹን ፡ ራስ ፡ ብለው ፡ የበላይ ፡ አዛዥ ፡ ስላደረጓቸው ፡ ነገሩ ፡ በራስ ፡ ሚካ ኤል ፡ ላይ ፡ እየከበደ ፡ ሄደ ። ከራስ ፡ ሚካኤል ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ትግሮችም ፡ አማሮችም ፡ እየከዱ ፡ መጥተው ፡ ከራስ ፡ ጐሹ ፡ ጋራ ፡ ተደበለቁ ። ስለዚህ ፡ በመ ጨረሻ ፡ እነራስ ፡ ጐሹ ፡ አሸነፉና ፡ ዠግናው ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ተማረኩና ፡ በእመኪና ፡ አምባ ፡ ታሠሩ ፤ ንጉሡን ፡ ግን ፡ እንዳሉ በዙፋናቸው ላይ ተዋቸው።

ራስ ፡ ጐሹም ፡ ከራስ ፡ ሚካኤል ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ በሻሽ ፡ ታንቀው ፡ በተገደሉት ፡ በዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ላይ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ የፈረዱትን ፡ ሰዎች ፡ በሰላይ ፡ እየያዙ ፡ አስገደሏቸው ።

እቴጌ ፡ ምንትዋብም ፡ ቀድሞ ፡ ወዳሠሩት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወደ ፡ ቍስ ቋም ፡ ተመልሰው ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ በጾምና ፡ በጸሎት ፡ እንደቈዩ ፡ ዐረፉና ፡ በዚሁ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ተቀበሩ ። ከጥቂት ፡ ዓመታት፡ በኋላም ፡ ራስ ፡ ሚከኤል ፡ ፹፮ ፡ እንደግማሾቹ ፡ ፺ ፡ ዓመት ፡ በእንደራሴነት ፡ እንቀጥቅጠው ፡ እንደ ፡ ገዙ ፡ ሞቱ ።

ራስ ፡ ጐሹም ፡ ለስሙ ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ እንደ ፡ ቀድሞው በዙፋናቸው ፡ አስቀምጠው ፡ ሙሉውን ፡ ሥልጣን ፡ ግን ፡ እርሳቸው ፡ ብቻ ፡ ይዘው ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ያዙ ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ንጉሡና ፡ ጐሹ ፡ ጠብ ፡

አደረጉ ። ስለዚህ ፡ በሹመትም ፡ በሌላም ፡ ምክንያት ፡ የራስ ፡ ጐሹ ፡ ጓደኞች ፡ ከጐንደር ፡ በራቁ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ራስ ፡ ጐሹን ፡ አሲዘው ፡ አሠሯቸው ። የዚህም ፡ ወሬ ፡ ለነደጃች ፡ ወንድ ፡ በወሰን ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ወንድ ፡ በወሰን ፡ ጐንደር ፡ ገብተው ፡ ጓደኛቸውን ፡ ራስ ፡ ጐሹን ፡ ከታሠሩበት ፡ በቃ በኀይል ፡ ፈቱና ፡ እሥልጣናቸው ፡ መለሷቸው ፡ የሚሉ ፤ እርሳቸውም ፡ እራሳቸው ፡ እንደራሴነቱን ፡ ይዘው ፡ ለመንገሥም ፡ አስበው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሳይሆንላቸው ፡ ፱ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ እንደገዙ ፡ ከፈረስ ፡ ወድቀው ፡ ሞቱ ፡ የሚሉም ፡ አሉ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ከዙፋናቸው ፡ አወረዷቸውና ፡ በግዞት ፡ ወደ ፡ ዋልድባ ፡ ገዳም ፡ ላኳቸው ። ንጉሡም ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሰነበቱ ፡ በሺሕ ፡ ፲፻፸ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዐረፉ ። ከርሳቸውም ፡ በኋላ ፡ ሰሎሞን ፡ ሁለት ዓመት ፡ ነግሠው ፡ ነበር ። በመጨረሻ ፡ ግን ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ «ፍቁር ፡ ሰገድ» ተብለው ፡ ነገሡ ።

## ምዕራፍ ፡ ፹፪ ።

## የዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

በታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ እንደተጻፈው ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ኀይለኛ ፡ የሆነ ፡ የንጉሥ አውራ ፡ ያም ፡ ቢቀር ፡ እንደ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ያለ ፡ ጥብቅ ፡ እንደራሴ በመጥፋቱ ፡ ሁሉም ፡ በያለበት ፡ እነግሣለሁ ፡ እያለ ፡ ተነሣ ። በያውራጃው ፡ ጦርነት ፡ እያደረገ ፡ እልቂት ፡ ሆነ ። ለም ፡ የነበረው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሆነ ፤ የምስለኔውና ፡ የጭቃ ፡ ሹሙ ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ያባቱን ፡ በሬ ፡ እያረደ ፡ ወደ ዱር ፡ ገባ ። እንደዚሁም ፡ በጐንደር ፡ ያሉ ፡ ደብተሮች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በሃይማኖት ፡ በሰዋስው ፡ በቅኔ ፡ እየተጣሉ ፡ ሁሉም ፡ የያውራጃውን ፡ ቀንደኛ ፡ ባላበት ፡ እየተከፋፈለ ፡ አንተ ፡ ጸጋ ፡ ብትሆን ፡ ትነግሣለህ ፤ አንተ ፡ ካራ ፡ አንተ ፡ ቅባት ፡ ብትሆን ፡ ዓርባ ፡ ዓመት ፡ ትገዛለኽ ፡ በራእይ ፤ በዐውደ ፡ ነገሥት ፡ ተረድተነዋል ፡ እያሉ ፡ ብዙውን ፡ መኳንንትና ፡ ሕዝብ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ አዋጉት ። በዚህ ፡ ዐይነት ፡ የርስ ፡ በርሱ ፡ ጦርነት ፡ ሲቀጥል ፡ በመጨረሻ ፡ የዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የታላቅ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ መነሣት ፡ ጥቂት ፡ ሊያሻሽለው ፡ ቻለ ። ይኸውም ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እንጂ ፡ ፍጻሜ ፡ ያለው ፡ ሰላምና ፡ ጸጥታ ፡ በነሱም ፡ ጊዜ ፡ አልተገኘም ።

ከሰሎሞን ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በሺሕ ፡ ፲፻፸ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነገሡ ። የርሳቸውም ፡ አነጋገሥ ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ነገሥታት ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሊሆን ፡ ተዠምሮ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን አልሆነም ። እንዲያውም ፡ ከርሳቸው ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ጊዜ ፡ የደከመው ፡ በርሳቸው ፡ ጊዜ ፡ በጭራሽ ፡ የነገሥታቱ ፡ ኀይል ፡ ስለ ፡ ወደቀና ፡ መሳፍንቱ ፡ ስለ ፡ ገነኑ ፡ ስማቸው ፡ "ተፍጻሜተ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ ፈጻሚ ፡ መንግሥት ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ" ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የነገሥታቱ ፡ ኀይል ፡ ደከመ ፡ ለማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ "መንግሥቱ" ፡ ምንም ፡

መከፋፈል፡ ቢኖርበት ፡ በመሳፍንቱ ፡ እጅ ፡ ቀጥሏልና ፡ ተፍጻሜተ፡ መንግሥት፡ በማ ለት ፡ ፈንታ ፡ ፍጻሜ ነገሥት ፡ ማለት ፡ ይገባል ።

የዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስንም ፡ የዘመናቸውን ፡ አፈጻጸም ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንጽፋለን ። ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ እዙፋን ፡ ከወጡ ፡ በኋላ፡ ትልቁ ፡ ዐሊ ፡ ከየጁ ፡ መጥተው ፡ አሽከርነት ፡ አድረው ፡ በታማኝነት ፡ ስላገለገሉ፡ ንጉሡ ፡ የራስነት ፡ ማዕርግ ፡ ጨምረው ፡ እንደራሴነቱን ፡ ሰጧቸው ። ከራስ ሚከ ኤል ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ምንም ፡ የነገሥታት ፡ ውድቀት ፡ ሆን ፡ ቢባል ፡ ዐፄ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የቀድሞዎቹን ፡ ነገሥታት ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ሚያውቁ ፡ በነዚያው ፡ ባባቶቻቸው ፡ ዐይነት ፡ ለመግዛት ፡ ተጣጥረው ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ንጉሡና ፡ እንደራሴው ፡ ተስማምተው ፡ ሲኖሩ ፡ በመካከሉ ፡ በቀድሞ ፡ ነገሥታት ፡ ያልነበረውን ፡ የማርና ፡ የገንዘብ ፡ ግብር ፡ በባለ ፡ መሬቱ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተከሉበት ፡ የጕንደር ፡ ሹማምትና ፡ ባለመሬት ፡ ተሰብስቦ ፡ በሰማይ ፡ የለ ፡ ዱር ፡ በጕንደር ፡ የለ ፡ ግብር ፡ የበጌምድር ፡ ሕዝብ ፡ ደረቱን ፡ ለጦር ፡ እግ ሩን ፡ ለጠጠር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚሰጥ ፡ አሁንም ፡ ዐፄ ፡ ሆይ ፡ እንዳባቶችዎ ፡ ደንብ ፡ ያሳድሩን ፡ ብሎ ፡ ቢያመለክታቸው ፡ ጥያቄውን ፡ ሳይቀበሉ ፡ ግብሩን ፡ ስላስገደዷቸው ፡ በዚሁ ፡ መኳንንቱ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ተመካክሮ ፡ እርሳቸውን ፡ ሽሮ ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ እንደ ፡ ሾመ ፤ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስም ፡ ከዚሁ ፡ የተነሣ ፡ ሰዉንም ፡ አገሩንም ፡ እንደ ፡ ረገሙ ፡ ሰፉ ፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ያለው ፡ ፳፩ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ያስረዳናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

## ዘመነ ፡ መሳፍንት ።

እንደ ፡ ዛሬ ፡ መንግሥታት ፡ አኳኋን ፡ በደንብ ፡ የተቀመጠ ፡ ባንድ ፡ አዛዥና ፡ መንፈስ ፡ የሚመራ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ባለመኖሩ ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ የመገናኛ ፡ መንገድና ፡ ስልክ ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ ስለሌለ ፡ በያውራጃው ፡ ባሉት ፡ ገዥዎችና ፡ ባላ ባቶች ፡ ላይ ፡ ጕንደር ፡ ያሉት ፡ ነገሥታት ፡ የበቃ ፡ ምርመራ ፡ ለማድረግ ፡ ባለ መቻላቸው ፡ በየጊዜው ፡ የተደረገውንም ፡ ለጧት ፡ ለማታ ፡ የሚያስረዳ ፡ የእንተሊ ጃንስ ፡ ሰርቪስ ፡ (የስለላ ፡ ሥራ) ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ በሚገባ ፡ ባለመኖሩ ፡ ምክንያት ፡ የነገሥታቱ ፡ ኀይላቸው ፡ እየደከመ ፡ ሄደ ። ቀድሞ ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ ሥዑል ፡ ጊዜ ፡ ቀዝቅዞ ፡ የነበረው ፡ የነገሥታቱ ፡ የነዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ የነዮሐንስ ፡ የነተክለ ፡ ሃይማኖት ፤ ሥልጣን ፡ በዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ጊዜ ፡ በሥልጣንና ፡ በግዛት ፡ ረገድ ፡ በፍጹም ፡ ወደቀ ። ሁሉም ፡ በያውራጃው ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ሆኖ ፡ አን ዱም ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ አግኝቶ ፡ ሊያዘው ፡ አልቻለም ። በበጌምድር ፡ ትልቁ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ በዳሞት ፡ ራስ ፡ ክፍለ ፡ አዳም ፡ በትግሬ ፡ ራስ ፡ ክፍለ ፡ ኢየ

ሱስ ፡ በፊት ፡ ቀጥሎ ፡ ልጃቸው ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ይገዙ ፡ ዠመር ፡ ሸዋም ፡ ገና ፡ አስቀድሞ ፡ ከዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ ተነጥሎ ፡ በዚህም ፡ ዘመን ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ መዠመሪያ ፤ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ተከትለው ፡ ራሳቸ ውን ፡ ችለው ፡ ሸዋን ፡ ያስተዳድሩ ፡ ነበር ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የታወቀው ፡ መደብነቱ ፡ ይኸው ፡ ጐንደር ፡ ስለሆነ ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ ለስሙም ፡ ቢሆን ፡ ዘውድ ፡ የደፉና ፡ የተቀቡ ፡ ነገሥታት ፡ ስላሉበት ፡ በጐንደር ፡ የሚቀመጠው ፡ መስፍን ፡ እየተባለ ፡ ከቀሩት ፡ ሁሉ ፡ የበላይ ፡ ሆኖ ፡ መታየቱ ፡ አልቀረም ። በጐንደርም ፡ ተቀምጠው ፡ በነገሥ ታቱ ፡ ስም ፡ ሆነው ፡ በበላይነት ፡ እስከ ፡ ትንሹ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ድረስ ፡ የገዙ ፡ ዝር ዝራቸው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ነው ።

ራስ ፡ ዐሊ ፡ ትልቁ ፡ ከሺሕ ፡ ፲፯፻፸፯ ፡ ፡-ሺሕ ፡ ፲፯፻፹፩ ።

ራስ ፡ ዐሊጋዝ ፡ ከሺሕ ፡ ፲፯፻፹፩ ፡-ሺሕ ፡ ፲፯፻፺፮ ።

ራስ ፡ ዓሥራትና ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ ከሺሕ ፡ ፲፯፻፺፮ ፡-ሺሕ ፡ ፲፯፻፺፱ ፡

ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ከሺሕ ፡ ፲፯፻፺፱ ፡-ሺሕ ፡ ፲፰፻፲፯ ።

ራስ ፡ ይማም ፡ ከሺሕ ፡ ፲፰፻፲፯ ፡-ሺሕ ፡ ፲፰፻፳ ።

ራስ ፡ ማርዬ ፡ ከሺሕ ፡ ፲፰፻፳ ፡-ሺሕ ፡ ፲፰፻፳፫ ።

ራስ ፡ ዶሪ ፡ ፫ ፡ ወር ።

ራስ ፡ ዐሊ ፡ ትንሹ ፡ ከሺሕ ፡ ፲፰፻፳፫-ሺሕ ፡ ፲፰፻፵፭ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ።

## የትልቁ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ የምስፍንና ፡ ዘመን ።

## ምዕራፍ ፡ ፹፬ ።

## ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አዲስ ፡ ግብር ፡ ስላመጡ ፡ ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ ከዳቸውና ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ እንዳቀፊ ።

ትልቁ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ትውልዳቸው ፡ በዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመንና ፡ በግ ራኝ ፡ ወረራ ፡ ዘመን ፡ የብር ፡ ዘንግና ፡ ርኮት ፡ ይዞ ፡ መጥቶ ፡ በየጁ ፡ ከተቀመ ጠው ፡ ከሸህ ፡ ዑመር ፡ የወረደ ፡ መሆኑን ፡ መጻሕፍት ፡ ተስማምተውበታል ። አባ ታቸው ፡ የዚሁ ፡ የሸህ ፡ ዑመር ፡ ፲ኛ ፡ ትውልድ ፡ ሴሩ ፡ ጓንጉል ፡ ናቸው ። እና ታቸውም ፡ የላስታና ፡ የሰላዋው ፡ ባላባት ፡ የራስ ፡ ፋሪስ ፡ ልጅ ፡ ወይዘሮ ፡ ገለቡ ፡ ናቸው ። እሳቸውም ፡ በየጁ ፡ ሲኖሩ ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ በኋላ ፡ ከየጁ ፡ መጥተው ፡ ለዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ታማኝነትና ፡ አገልግሎት ፡ ስላሳዩ ፡ በበጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ እንደራሴነትን ፡ ንጉሡ ፡ ሰጧቸው ። ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ እንደ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ አጻጻፍ ፡ በበጌምድር ፡ ከርሳቸው ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ነገ

ሥታት ፡ ያልተከሉትን ፡ ግብር ፡ መትከል ፡ ስለ ፡ ዝመሩ ፡ የበጌምድር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስቦ ፡ ለዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ «በበጌምድር ፡ የለ ፡ ግብር ፤ በሰማይ ፡ የለ ፡ ዱር ፡ በጌምድር ፡ ደረቱን ፡ ለጦር ፤ እግሩን ፡ ለጠጠር ፡ መስጠት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የማር ፡ የገንዘብ ፡ ግብር ፡ የለበትምና ፡ እርስዎም ፡ እንዳባቶችዎ ፡ እንደ ፡ ፋሲል ፡ እንደ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፡ ያሳድሩን ፤ እኛም ፡ እንዳባቶቻችን ፡ አልጋዎን ፡ ደግፈን ፡ እንኑር" ፡ ብለው ፡ አመለከቱ ፡ ንጉሡም ፡ በኔ ፡ ሥልጣን ፡ አስተዳድራለሁ ፡ እንጂ ፡ እናንተ ፡ እንዳላችሁት ፡ ከሆነ ፡ ምን ፡ አልጋ ፡ አለኝ ፡ አሁንም ፡ የምለውን ፡ ፈጽሙ ፡ አሏቸው ፡ ይባላል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መልስ ፡ ሆነና ፡ ደጃች ፡ እሸቴ ፡ ኀይሉ ፡ የሚባሉ ፡ የስቴ ፡ ባላባት ፡ በጌምድር ፡ እንደ ፡ ባሪያ ፡ እስትንገዛ ፡ ነው ፡ የምናየው ፡ አገራችንን ፡ የምናሳድርበት ፡ እንምከር ፡ ብለው ፡ ለጓደኞቻቸው ፡ ተናገሩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በጌምድር ፡ ከጨጨሆ ፡ በታች ፡ ከመተማ ፡ በላይ ፡ በ፪ ፡ ቀን ፡ ተሰብስቦ ፡ ንጉሣችን ፡ ያገርን ፡ አስተዳደር ፡ ከለወጡብን ፡ እኛም ፡ ገዥ ፡ እንለውጥ ፡ አልጋችን ፡ በእጃችን ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ ሆኖ ፡ መክሮ ፡ የተፍጻሜት ፡ መንግሥት ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስን ፡ እንደራሴ ፡ የጁዬውን ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ ከጐንደር ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ይምጡ ፡ ብሎ ፡ ላከባቸው ። ራስ ፡ ዐሊም ፡ ቶሎ ፡ መጡ ። የበጌምድርም ፡ ሹማምት ፤ ከኛ ፡ ፈቃድ ፡ ይወጣሉን ፡ ወይስ ፡ አይወጡም ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ አገሩ ፡ ኃይለኛ ፡ መከር ፡ መሆኑን ፡ ስላወቁ ፡ ከናንተ ፡ ፈቃድ ፡ ወጥቼ ፡ ብቻዬን ፡ ምን ፡ ለማድረግ ፡ እችላለሁ ፡ ከፈቃዳችሁ ፡ ውስጥ ፡ እንዳንድ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ ብለው ፡ መለሱ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የሰጡዎን ፡ እንደራሴነት ፡ ይተውና ፡ በኛ ፡ በኩል ፡ እንደራሴ ፡ አድርገንዎታል ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ በመስፍን ፡ እንጂ ፡ በንጉሥ ፡ እንገዛም ፡ አልጋ ፡ ግን ፡ ከገራችን ፡ እንዳይጠፋ ፡ ወይዛዝር ፡ ከሚባሉት ፡ ከነገሥታት ፡ ዘር ፡ ዐፄ ፡ እያልን ፡ አንዱን ፡ እያነገሥን ፡ እናስቀምጣለን ። ለሱም ፡ ማደሪያ ፡ ወይና ፡ ደጋ ፡ የሚባለውን ፡ ከጐንደር ፡ ራስጌ ። ያለውን ፡ አገር ፡ እንሰጣለን ፡ ብሎ ፡ አስቀድሞ ፡ በምክር ፡ የወሰነውን ፡ ቢነግራቸው ፡ ከተቀመጡበት ፡ ተነሥተው ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፡ አገሩን ፡ መርቀው ፡ ተቀበሉ ።

ወዲያውም ፡ እንግዴህ ፡ ጐንደር ፡ ሂጂ ፡ ባንድ ፡ ምክንያት ፡ ከንጉሡ ፡ ተሰናብቼ ፡ የጁ ፡ ወጥቼ ፡ ጦር ፡ አስከትቼ ፡ ልምጣ ፡ ብለው ፡ ካገር ፡ ተሰናብተው ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ተመለሱ ። ወዲያውም ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ገብተው ፡ እናቴ ፡ በጭንቅ ፡ ታመውብኛልና ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ስንብት ፡ ይስጡኝ ፡ አሏቸው ። ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስም ፡ ውስጡን ፡ የተደረገባቸውን ፡ ዐድማ ፡ ሳያውቁ ፡ ስንብት ፡ ሰጧቸው ። ራስ ፡ ዐሊም ፡ የንጉሥ ፡ የጕዞ ፡ መስፈሪያ ፡ በነበረው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ምሪት ፡ ያስቀመጡት ፡ ፈረስ ፡ ነበራቸውና ፡ ከጐንደር ፡ ተነሥተው ፡ ፍርቃ ፡ በር ፤ ከፍርቃ ፡ በር ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፤ ከደብረ ፡ ታቦር ፡ ክምር ፡ ደንጊያ ፡ ከክምር ፡ ድንጊያ ፡ ገረገራ ፤ ከገረገራ ፡ አገራቸው ፡ የጁ ፡ ፈረስ ፡ እያቀያየሩ ፡ ባንድ ፡ ቀንና ፡ ባንድ ፡ ሌሊት ፡ ገብተው ፡ አደሩ ፡ ይባላል ። ወዲያው ፡ ሰባት ፡ ቤት ፡ ወሎ ፡ መል

ክተኛ ፡ ልከው ፡ የወሎን ፡ የየጁን ፡ ጦር ፡ አስከትተው ፡ ባምስተኛው ፡ ቀን ፡ ተመ
ልሰው ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ገብተው ፡ ከበጌምድር ፡ ባላባቶች ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተማማ
ሉት ፡ አገሩንና ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣኑን ፡ በጌምድር ፡ ለኔ ፡ ሰጥቶኛልና ፤ እርስዎ ፡
ዝም ፡ ብለው ፡ ከግንብዎ ፡ ይቀመጡ ፡ ብለው ፡ ለዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ላኩ
ባቸው ። ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስም ፡ ክዳቱ ፡ ያንድ ፡ ወይም ፡ የሁለት ፡ ሳይሆን ፡
ያገር ፡ መሆኑን ፡ ስላወቁ ፡ «በጌምድር ፤ ከኔ ፡ ከወንድምኽ ፡ የየጁ ፡ ጋላ ፡ ከተሻለኽ ፡
ደግ ፡ ነዋ» ፡ ብለው ፡ አኵስም ፡ ሄደው ፡ ተቀመጡ ፡ ይባላል ።

በተረፈ ፡ በሌላው ፡ ረገድ ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ደግነት ፡ የበዛባቸው ፡
ንጉሥ ፡ ነበሩ ፡ ይባላል ። ስለዚህ ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ . . . . . ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡
ዓለም ፡ በይነ ፡ ዘኀለፈ ። እምተስፋሁ ፡ ልበ ፡ ሰብአ ፡ አዕረፈ ።—ትርጓሜ ፤ ተክለ ፡
ጊዮርጊስ ፡ ዓለም ፡ ስለ ፡ አለፈ ፡ (ስለ ፡ ሞተ) ፡ ከሰው ፡ ልብ ፡ ላይ ፡ ተስፋ ፡ ተቋረጠ ፡
ሲል ፡ በለቅኔ ፡ ተቀኙላቸው ፡ ይባላል ።

የሆኖ ፡ ሆኖ ፡ ይህን ፡ የመሰለው ፡ መንግሥትን ፡ የመልቀቅ ፡ ሥራ ፡ የኑቁን ፡
ትተን ፡ በቅርቡ ፡ በዐፄ ፡ ሠርጸ ፡ ድንግል ፡ ልጅ ፡ በዐፄ ፡ ያዕቆብ ፡ ጊዜ ፡ ዘሦ ፡
በጁ ፡ ነግሦ ፡ በተባለው ፡ በራስ ፡ ዘሥላሴ ፡ ተዠምሮ ፡ እንዲሁም ፡ በራስ ፡ ሥዑል ፡
ሚካኤል ፡ ጊዜ ፡ ደርሶ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ቀጥሎ ፡ የሚነሣው ፡ ንጉሥ ፡ እየተከ
ላከለ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሥልጣኑን ፡ ማቈየት ፡ ችሎ ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ ግን ፡
በራስ ፡ ሀሊ ፡ ጊዜ ፡ የተዠመረው ፡ የመሳፍንቱ ፡ ኀይል ፡ የነገሥታቱ ፡ ድካም ፡
እስከ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ ረግቶ ፡ ቈየ ። ከዚህ ፡ ዘመን ፡
ዠምሮ ፡ ነገሥታቱ ፡ ቀድሞ ፡ የነበራቸው ፡ ሥልጣን ፡ በትክክል ፡ ወደ ፡ እንደ
ራሴዎቹ ፡ ዞረ ። ሿሚ ፤ ሻሪ ፡ አሳሪ ፤ ፈቺ ፡ እንደራሴዎቹ ፡ ሆኑ ፡ ነገሥታቱ ፡ በመሳፍ
ንቱ ፡ ፈቃድ ፡ እየነገሡ ፡ ዘውዳቸውን ፡ ደፍተው ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ የዐፄነት ፡
ስማቸውን ፡ ብቻ ፡ ይዘው ፡ ተቀመጡ ።

※ ※ ※

በምድር ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ወይም ፡ ታሪክ ፡ ተመ
ልሶ ፡ ይደገማል ፡ እንደሚባለው ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ጥንት ፡ በ፯ኛው ፡ መቶ ፡
ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ በፈረንሳዊ ፡ አገር ፡ ደርሶ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ታሪክ ፡ ይነግረናል ።

ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ በዛሬው ፡ በፈረንሳዊ ፡ አገር ፡ ባምስተኛው ፡ መቶ ፡
ዓ ፡ ም ፡ ላይ ፡ እነክሎቢስ ፡ እነክሎቴር ፡ የምዕራብ ፡ መንግሥት ፡ የሚባል ፡ ትልቅ ፡
መንግሥት ፡ አቁመው ፡ ነበር ፤ ይኸም ፡ መንግሥት ፡ «የሜሮቢንጂያ ፡ ሥርወ ፡ መን
ግሥት» ፡ ይባላል ። በዚህም ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ እላይ ፡ ስማቸውን ፡ የጠራናቸው ፡
ክሎቢስና ፡ ልጁ ፡ ክሎቴር ፡ የተከፋፈለውን ፡ ሕዝብና ፡ ነገድ ፡ ባንድነት ፡ ሰብስበው ፡
ባንድ ፡ ዙፋን ፡ ሥር ፡ ውስጥ ፡ አግብተው ፡ ይገዙት ፡ ነበር ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ ክሎቴር ፡
፩ኛ ፡ ሲሞት ፡ ልጆቹ ፡ ትልቁን ፡ የምዕራብ ፡ መንግሥት ፡ እሁለት ፡ ከፍለው ፡ ይገ
ዙት ፡ ዠመር ። ይኸም ፡ እሁለት ፡ የተከፈለው ፡ መንግሥት ፡ አንዱ ፡ የነስትሪ ፡ መን

ግሥት ፡ ሁለተኛው ፡ የአውስትራዚ ፡ መንግሥት ፡ ይባላል ። ስለዚህ ፡ ከራተኛው ፡ መቶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዠምረው ፡ እነዚሁ ፡ ነገሥታት ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሲገዙ ፡ በበታቻቸው ፡ የኛዎቹ ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ፡ እያሉ ፡ እየሾሙ ፡ ይገዙ ፡ እንደ ፡ ነበረ፤ እነሱም፡ «Maire du palais የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከንቲባ» ፣ (1)እያሉ ፡ ይሾሙ ፡ ነበር፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ መጣና ፡ እስከ ፡ ሦስተኛው ፡ ቲዬሪ ፡ (Thierry III) ደረሰ ። በርሱ ፡ ዘመን ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱ፡ ሥልጣን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ከንቲባ ፡ ዞረ ። በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ቲዬሪ ፡ ፫ኛ ፡ በኛ ፡ እንደ ፡ ተፍጻሜተ ፡ መንግሥት ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ከርሱ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ሺልዴሪክ ፡ ፫ኛ ፡ Childeric III) ፡ ድረስ ፡ (675-751 ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ ሜር፡ዱ፡ፓሌ፡ በሚባሉት ፡ በእንደራሴዎቹ ፡ እጅ ፡ ዞሮ ፡ አገሩንና ፡ መንግሥቱን ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ያስተዳድሩ ፡ ዠመር ። ነገሥታቱንም ፡ የሚሽሩ ፡ የሚሾሙ ፡ እነርሱ ፡ ሆኑ ። ዘውድ ፡ ለስሙ ፡ ጭነው ፡ የሚቀመጡት ፡ ነገሥታት ፡ በኛ ፡ ዘንድ ፡ "ወይዘዝር ፡ ወይም ፡ ግንብ ፡ ጠባቂ» ፡ እንደ ፡ ተባሉ ፡ ለነዚህም ፡ የፈረንሳዮች ፡ ነገሥታት ፡ «ምንም ፡ ለመሥራት ፡ የማይችሉ ፡ ሰነፎች ፡ ነገሥታት ፡ -Rois Faineants,, ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ ወጣላቸው ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከነዚሁ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ከንቲባዎች ፡ መከከል ፡ ታላላቅና ፡ የታሪክ ፡ ሰው ፡ ተገኝቶባቸዋል ። ለምሳሌ ፤ በፑዋቲዬ ፡ በ732 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ላይ ተዋግቶ ፡ ዐረቦችን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ አውሮፓን ፡ ከእስልምና ፡ ያዳነው ፡ ሻርል ፡ ማርቴል ፡ ከነዚሁ ፡ አንዱ ፡ ነበር ።

በኋላ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ማስማማቱ ፡ ባይሆንላቸው ፡ መሳፍንቱን ፡ አሸንፈው ፡ የንጉሡ ፡ ንጉሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ያዙት ፡ እንደ፡ ዐፄ፡ ቴዎድሮስ ፡ በዚያም ፡ ከነስትሪ ፡ ውስጥ ፡ ስሙ ፡ የታወቀው ፡ ሻርለማኝ ፡ 742-814 ፡ ላይ ፡ ተነሥቶ ፡ የወደቀውን ፡ የነገሥታት ፡ ኀይል ፡ መልሶ ፡ አቆመው ። ከቀድሞው፡ ግዛትም ፡ እያለፈ ፡ ብዙ ፡ መንግሥታት ፡ እየወጋ ፡ እያሸነፈ ፡ በሙሉ ፡ የምዕራብ ፡ አውሮፓ ፡ ላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለመሆን ፡ ቻለ ። ስለዚህ ፡ ታሪክ ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ዐይነት ፡ አኳኋን ፡ በያገሩ፡ መድረሱን ፡ ተመልክተን ፡ አሁን ፡ ወደዚሁ ፡ ወዳገራችን፡ ታሪክ ፡ እንመለስ ።

፨ ፨ ፨

ራስ ፡ ዐሊ ፡ የጐንደርን ፡ ምስፍንና ፡ በያዙ ፡ ጊዜ ፡ በእንደርታ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፤ በተንቤን ፡ ከራስ ፡ ሚካኤል ፡ ሥዑል ፡ በኋላ ፡ የተነሡት ፡ ራስ ፡ ገብረ፡ መስቀል ፡ የሥልጣን ፡ ተወዳዳሪዮቻቸው ፡ ሆነው ፡ ያስቸግሯቸው ፡ ነበር ፤ ከነዚህም፡ ከሁለቱ ፡ የትግሬ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አንደኛው ፡ ራስ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ ለማጥቃት ፡ እንዲመቻቸውና ፡ ሕዝብም ፡ እንዲያብርላቸው ፡ ዐፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምን፡

(1) የዚህ ፡ ሹመት ፡ መዠመሪያ ፡ እንደልፍኝ ፡ አስከልካይ ፡ ነበር ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ እያደር ፡ የንጉሥ ፡ እንደራሴ ፡ እስከ ፡ መሆን ደረሰ ፤ በኛ ፡ በጐንደሩ ፡ መንግሥት ፡ ራስ ፡ ቢቶደድ ፡ እንደሚባለው ፡ ነው ።

አንግሠው ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፤ ራስ ፡ ዐሊና ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ ራስ ፡ ገብረ ፡ መስቀልና ፡ ዐፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ከሌላው ፡ ወገን ፡ ሆነው ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲዋጉ ፡ በመጨረሻ ፡ ጠቅላላ ፡ ሥልጣን ፡ ለመያዝ ፡ ተስፋ ፡ አድርገው ፡ እዳር ፡ ሆነው ፡ ሁለቱንም ፡ ወገኖች ፡ በነገረ ፡ ሠሪ ፡ ይገፋፏቸው ፡ ነበር ፡ ይባላል ። እንደ ፡ ታሰበውም ፡ ራስ ፡ ዐሊና ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ካንድ ፡ ወገን ፡ እንዲሁም ፡ ራስ ፡ ገብረ ፡ መስቀልና ፡ ዐፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ከሌላው ፡ ወገን ሆነው ፡ ጦርነት ፤ ተደረገና ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ዐፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ገደሏቸው ።

በርሳቸውም ፡ ፈንታ ፡ ቀድሞ ፡ ነግሠው ፡ የነበሩትን ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስን ፡ መልሰው ፡ እዙፋን ፡ አወጧቸው ። ራስ ፡ ገብረ ፡ መስቀልም ፡ ከዚሁ ፡ ጦርነት ፡ ሸሽተው ፡ ከመለጡ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ጦር ፡ አደራጅተው ፡ መጥተው ፡ በዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ሥፍራ ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ አንግሻለሁ ፡ ብለው ፡ አዋጅ ፡ አናገሩ ፤ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ በንጉሥነት ፡ ከዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ እንደ ፡ ቈዩ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ከበጌምድር ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ከእንደርታ ፡ ተስማምተው ፡ በራስ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ላይ ፡ ተነሡባቸው ። ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴም ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ባሳብ ፡ እንደ ፡ ተስማሟቸውና ፡ ከኋላቸው ፡ (ከበጌምድር) ፡ ምንም ፡ አደጋ ፡ እንደማይደርስባቸው ፡ በተረዱ ፡ ጊዜ ፡ ተንቤን ፡ ሄደው ፡ ከራስ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ጋራ ፡ ተዋጉና ፡ ድል ፡ አደረጉ ። በመላውም ፡ ትግሬ ፡ ላይ ፡ የበላይነታቸውን ፡ ሥልጣን ፡ በይፋ ፡ አረጋገጡ ፤ ራስ ፡ ዐሊም ፡ በበኩላቸው ፡ ጐንደር ፡ ከተማ ፡ ገብተው ፡ ራስ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ አንግሠዋቸው ፡ የነበሩትን ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ አባረው ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱን ፡ ልጅ ፡ ዐፄ ፡ ሕዝቅያስን ፡ አነገሡ ። ራስ ፡ ዐሊ ፡ በምስፍንና ፤ ዐፄ ፡ ሕዝቅያስም ፡ በዙፋን ፡ ሆነው ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ ገዙ ። ይኸውም ፡ ግዛት ፡ ዋናው ፡ የመሾም ፡ የመሻር ፡ ሥልጣን ፡ በእንደራሴው ፡ በራስ ፡ ዐሊ ፡ እጅ ፡ ሆኖ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጥንቱ ፡ ነገሥታት ፡ ንጉሡ ፡ ዘውዱን ፡ ጭኖ ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፡ ከመገኘት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ሥልጣን ፡ አልነበረውም ።

ይኸውም ፡ ሆኖ ፡ ታላቅ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ በመጀመሪያ ፡ በዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቀጥሎም ፡ በዐፄ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ጊዜ ፤ ቀጥሎም ፡ ራስ ፡ ዐሊጋዝ ፡ በምስፍንና ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ መግዛታቸው ፡ በጐጃም ፡ በትግሬ ፡ በስሜን ፡ በላስታ ፡ ባላባቶች ፡ ዘንድ ፡ ቅርታን ፡ ፈጥሮ ፡ ነበር ። የነዚህም ፡ ቅርታና ፡ ጠብ ፡ ቀድሞ ፡ በዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ቋረኞችና ፡ ወሎዎች ፡ ከተጣሉበት ፡ ምክንያት ፡ ጋራ ፡ የተያያዘ ፡ ነው ። ራስ ፡ ዐሊ ፡ ከየጁ ፡ የመጡ ፡ የጋላ ፡ ዘር ፡ በመሆናቸው ፡ የምስፍንናው ፡ ሥፍራ ፡ በራሳቸው ፡ በመያዙ ፡ በሌሎቹ ፡ ዘንድ ፡ ቅናትንና ፡ ቍጭትን ፡ ፈጠረ ።

ከነዚሁም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ያነሣናቸው ፡ የእንደርታው ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ የተንቤኑ ፡ ራስ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ የጐጃሙ ፡ ታላቅ ፡ ራስ ፡ ኀይሉ ፤ ይልቁንም ፡

ራስ ፡ ዓሥራትና ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ያማራና ፡ የትግሬ ፡ ዘሮች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እየተባበሩ ፡ እንደ ፡ ባዕድ ፡ የሚያዩዋቸውን ፡ እነራስ ፡ ዐሊን ፡ እነራስ ፡ ዐሊጋዝን ፡ ለማጥቃት ፡ ሲነሡ ፡ ደግሞ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደራሴነቱን ፡ ራሳቸው ፡ ለየግላቸው ፡ ለመያዝ ፡ እየፈለጉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይጣሉ ፡ ነበር ። እስከ ፡ መዋጋትም ፡ እየደረሱ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ያሸነፈው ወገን ፡ በቶሎ ፡ አንዱን ፡ የነጋሢ ፡ ዘር ፡ ይይዝና ፡ እንደራሴ ፡ መሆኑን ፡ ያውጃል ። በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ታላቅ ፡ ራስ ፡ ኀይሉ ፡ የዐፄ ፡ ኢዮአስን ፡ ልጅ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱን ፤ ራስ ፡ ዓሥራት ፡ ዐፄ ፡ ሕዝቅያስን ፤ ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ ዐፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፤ እንደዚሁም ፡ እነራስ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፤ እነራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ አንዳንድ ፡ የነጋሢ ፡ ዘር ፡ እያነገሡ ፡ እንደራሴነት ፡ ይዘናል ፡ እያሉ ፡ ዐውጀዋል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በየተራ ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ባንድ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ በያውራጃው ፡ ሥልጣን ፡ ሲይዙ ፡ አንዱ ፡ አንግሦት ፡ የነበረውን ፡ ፩ኛው ፡ እየመለሰ ፡ ያነግሠው ፡ ነበር ። አንዱ ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፡ ቀድሞ ፡ ይዞ ፡ አንግሥ ፡ እንደራሴነትን ፡ ያዝሁ ፡ ሲል ፤ ሌላው ፡ ተሽቀዳድሞ ፡ ሰሎሞንን ፡ ወይም ፡ ሕዝቅያስን ፡ አንግሼ ፡ እንደራሴነትን ፡ ይዤአለሁ ፡ ብሎ ፡ እያወጀ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ሲዋጋ ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ ሲያልቅ ፡ ብዙ ፡ ባላገር ፡ ብዙ ፡ መንደር ፡ ሲዘረፍ ፡ ኖረ ።

ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ጳጳሱንና ፡ ዕጨጌውን ፡ የኔን ፡ ንጉሥ ፡ ቀብታችሁ ፡ አንግሡ ፤ የእገሌን ፡ አትቀቡ ፤ ነግሻለሁ ፡ ብሎም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገዝቱት ፡ እያሉ ፡ እነዚሁ ፡ ኀያላን ፡ መኳንንቶች ፡ ሲያታክቱዋቸው ፡ ሲያስጨንቋቸው ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

ነጋሢዎቹ ፡ እንደ ፡ ጥንቱ ፡ እንደራሴያቸውን ፡ እየለዋወጡ ፡ በሠሾም ፡ በመሻር ፡ ፈንታ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንደራሴው ፡ እነሱን ፡ ሲሾማቸው ፡ ሲሽራቸው ፡ እዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ሲያወጣቸው ፡ ሲያወርዳቸው ፡ እንደ ፡ ሙሽራ ፡ በያለበት ፡ እንደራሴነት ፡ ያማረው ፡ ባላባት ፡ ሁሉ ፡ ሲናጠቃቸው ፡ ኖረ ። እነሱም ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ያሸነፈው ፡ ወገን ፡ ወስዶ ፡ ሲያነግሣቸው ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ። ስለ ዚህ ፡ የጐንደር ፡ ሕዝብ ፡ ከዚሁ ፡ የተነሣ ፡ «ወይዛዝር ፤ ግንብ ፡ ጠባቂ» ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ አወጣላቸው ።

የነጋሢዎቹ ፡ ሥልጣን ፡ መዠመሪያ ፡ በዐፄ ፡ ኢዮአስ ፤ ሁለተኛም ፡ በዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተፍጻሜተ ፡ መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ወደቀ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነትን ፡ ሥልጣን ፡ መልሶ ፡ ለማንሣት ፡ የእንደራሴነትን ፡ ሥልጣን ፡ ለመጣል ፡ እንደ ፡ ቀድሞዎቹ ፡ እንደ ፡ ሠርጸ ፡ ድንግል ፡ እንደ ፡ ፋሲል ፡ እንደ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ያሉ ፡ ኀይለኞችና ፡ ዐዋቂዎች ፡ ነገሥታት ፡ ለመነሣት ፡ አልቻሉም ። ቢነሡም ፡ ነገሩ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ከሥሩ ፡ ስለ ፡ ተበላሸ ፡ የእንደራሴ ፡ መሣሪያ ፡ ከመሆን ፡ በቀር ፡ ሊከናወንላቸው ፡ አልቻለም ። ኢዮአስ ፡ መዠመሪያ ፡ ሥልጣናቸው ፡ በእንደራሴያቸው ፡ በራስ ፡ ሚካኤል ፡ እንዳይወረስ ፡ ጥረው ፡ ነበር ። ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፤ ተክለ ፡ ጊዮርጊስም ፡ ይኸን ፡ ሥልጣን ፡ መልሰው ፡ ለማግኘት ፡ ሞክረው ፡ ነበር ፡ አልቻሉም ። ስለዚህ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ ትንንቅ ፡ ለንጉሠ ፡

ነገሥትነት ፡ በመሆን ፡ ፈንታ ፡ ሥልጣን ፡ ያለበትን ፡ የእንደራሴነቱን ፡ ሥፍራ ፡ ለማግኘት ፡ ብቻ ፡ ሆነ ። ይኸንንም ፡ ለማግኘት ፡ እላይ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ከማሮቹና ፡ ከትግሮቹ ፡ በኩል ፡ ብዙዎቹ ፡ ጣሩ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ዓሥራትና ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ በጐንደር ፤ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ራስ ፡ ገብረ መስቀል ፤ ራስ ፡ ገብሬ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከጐንደር ፡ ውጭ ፡ ቢይዙም ፡ የእንደራሴነቱ ፡ ሥፍራ ፡ ከትልቁ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ እስከ ፡ ትንሹ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ድረስ ፡ ከሴሩ ፡ ጓንጉል ፡ ዘር ፡ አልወጣም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እነርሱም ፡ ቢሆን ፡ እንደራሴነቱን ፡ በሙሉ ፡ ይዘው ፡ ሲገዙ ፡ በግድ ፡ ከሰሎሞናዊው ፡ ዘር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ስም ፡ ተቀብቶ ፡ ዘውድ ፡ ደፍቶ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ እንዲቀመጥ ፡ አስፈላጊነቱን ፡ ተረድተዋል ።

## ምዕራፍ ፡ ፹፩ ።

የራስ ፡ ኃይሉና ፡ የራስ ፡ መርድ ፡ ቤት ፡ ግብር ፤—የራስ ፡ መርድና ፡ የራስ ፡ ወልደ ፡

## ገብርኤል ፡ ጦርነት ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ በላስታ ፤ በስሜን ፤ በትግሬ ፤ በበጌምድር ፤ በአማራ ፡ ሣይንት ፡ በዳሞት ፤ በጐጃም ፡ የተነሡት ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ዎች ፡ ናቸው ።

እርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ያደረጉት ፡ ጦርነት ፤ ጦርነቱም ፤ የተነሣበት ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ነው ። ጊዜውም ፣ ምክንያቱም ፡ የጦርነቱም ፡ ቦታ ፡ ዘመኑም ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ የተወሳሰበ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የዚህ ፡ ዘመን ፡ ታሪክ ፡ የሰዎቹም ፡ ስም ፡ ቦታውኑ ፡ ጊዜውን ፡ ምክንያቱን ፡ ሁሉ ፡ አጣርቶ ፡ ለመጻፍ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በደንብ ፡ ተጽፎ ፡ የተቀመጠ ፤ ባለመኖሩ ፡ ከውራጅ ፡ ወዳውራጅ ፡ ከሽማግሌ ፡ ወደ ፡ ሽማግሌ ፡ ለመዞርና ፡ ለመጠየቅ ፡ ረዥም ፡ ጊዜ ፡ ያስፈልጋል ። አሁን ፡ ግን ፡ የሆነውን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ከንዳንድ ፡ ሽማግሌ ፡ የሰማነውን ፡ በመጽሐፍ ፡ ለጊዜው ፡ በመጠኑ ፡ ያገኘነውን ፡ ብቻ ፡ ለወደ ፡ ፊት ፡ ጸሐፊ ፡ መነሻ ፡ የሚሆነውን ፡ ባጭሩ ፡ በመጻፍ ፡ እንወስናለን ።

፨ ፨ ፨

በስሜን ፡ ራስ ፡ ገብሬ ፤ በላስታ ፡ ደጃች ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፤ በዳሞት ፡ ደጃች ፡ ዘውዴ ፡ ይልቁንም ፡ ከራስ ፡ ዐሊ ጋዝ ፡ በኋላ ፡ እንደራሴነት ፡ የያዙት ፡ ወንድማማቾቹ ፡ ራስ ፡ ዓሥራትና ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፤ ከላስታ ፡ ተነሥተው ፡ እንደራሴነትን ፡ ከመያዛቸው ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ጐጃምን ፡ ከዐፄ ፡ በካፋ ፡ የእኅት ፡ ልጅ ፡ ከምልምል ፡ ኢያሱ ፡ የሚወለዱት ፡ ታላቁ ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ያስተዳድሩት ፡ ነበር ። ታላቅ ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ በጣም ፡ ርስት ፡ ይወዱ ፡ ነበር ፡ ይበላል ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ርስታቸውን ፡ ባ፳፬ ፡ ጥንድ ፡ በሬ ፡ እያሳረሱ ፡ ብዙ ፡ እኽል ፡ እያስመረቱ ፡ ግብራቸው ፡ እንደ ፡ ስሜኑ ፡ ራስ ፡ ገብሬ ፡ ሰፊ ፡ ነበር ፡

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ መኳንንትና ፡ ወታደር ፡ ይወዷቸው ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በዘመናቸውም ፡ ሕዝቡን ፡ ከነመኳንንቱ ፤ ከህኑን ፡ ከነሊቃውንቱ ፡ ግብር ፡ እያገቡ ፡ ማብላት ፤ ማጠጣት ፡ ይወዱ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በርሳቸው ፡ ጊዜ ፡ አንዳንድ ፡ መኳንንት ፡ ግብሩን ፡ ለመብላት ፡ እየከሩ ፡ የመንቀባረር ፡ ነገር ፡ ያሳዩ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሥጋው ፡ የምን ፡ ከብት ፡ እንደ ፡ ሆነ ሳናውቅ ፡ አንበላም ፡ እያሉ ፡ ሲያስቸግሩ ፤ ራስ ፡ ኀይሉም ፡ እንግዲያው ፡ መንጋው ፡ እፊታችሁ ፡ እየቀረበ ፡ ይታረድ ፡ ሲሏቸው ፡ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ የቋሚ ፡ ሹም ፡ አይደለንም ፡ ይሉ ፡ ነበር ፤ ደግሞ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሥጋው ፡ የበሬ ፡ ቢሆንም ፡ በደባባይ ፡ ተቀምጠን ፡ ደጅ ፡ እየጠናን ፡ የምንበላው ፡ ስለምንድነው ፡ እያሉ ፡ ራስ ፡ ኀይሉንም ፡ አስተናባሪዎቻቸውንም ፡ ሲያስቸግሩ ፡ ልጅ ፡ መርድ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ በባታቸው ፡ በራስ ፡ ኀይሉ ፡ ቤት ፡ ተቀምጠው ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ታላቅ ፡ ራስ ፡ ኀይሉ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ገዝተው ፡ ከሞቱና ፡ በደብር ፡ ኢየሱስ ፡ ከተቀበሩ ብኋላ ፡ ልጅ ፡ መርድ ፡ የራስነት ፡ ማዕርግ ፡ ጨምረው ፡ በባታቸው ፡ አልጋ ፡ ተቀመጡ ። እንደ ፡ ተቀመጡም ፡ መኳንንቱ በግብር ፡ ጊዜ ፡ በባታቸው ፡ ላይ ፡ የዋሉትን ፡ የመንቀባረር ፡ ጡር ፡ መመለስን ፡ የመዠመሪያ ፡ ሥራቸው ፡ አደረጉት ። ራስ ፡ መርድ ፡ ግብር ፡ አሠርተው ፡ ሲጨርሱ ፤ መኳንንቱና ፡ ወታደሩ ፡ እንደየማዕርጉ ፡ እንዲገባ ፡ ያዛሉ ። መኳንንቱ ፡ ሲገባ ፡ ወደ ፡ ግብር ፡ ሳይመጣ ፡ የቀረውን ፡ ከጋፋሪዎቻቸው ፡ እየጠየቁ ፡ በእግረ ፡ሙቅ ፡ እያሰሩም ፡ እየገረፉም ፡ ይቀጡት ፡ ዠመር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በመኳንንቱ ፡ ታላቅ ፡ ድንጋጤ ፡ አደረበት ። የታላቅ ፡ ራስ ፡ ኀይሉም ፡ ጡር ፡ ደረሰብን ፡ እያለ ፡ እርስ ፡ ብርሱ ፡ ይወያይ ፡ ዠመር ። ስለዚህ ፡ መኳንንቱም ፡ ወታደሩም ፡ ሊቃውንቱም ፡ በራስ ፡ መርድ ፡ አዳራሽ ፡ ግብሩ ፡ ሲዘረጋ ፡ እንኳን ፡ እየተጠራ ፡ ሳይጠራም ፡ ቀድም ፡ ብሎ ፡ እየመጣ ፡ ባዳራሹ ፡ በራፍ ፡ እየኰለኰለ ፡ ደጅ ፡ እየጠና ፡ ይበላ ፡ ዠመር ። በዚህም ፡ ላይ ፡ ከባላገር ፡ ደጅ ፡ የደረሰውን ፡ መኳንንትና ፡ ወታደር ፡ ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ እቀጣዋለሁ ፡ የሚል ፡ በጐጃም ፡ ስላወጁ ፡ በግብሩ ፡ አኳኋንና ፡ ከዚህም ፡ ዐዋጅ ፡ የተነሣ ፡ መኳንንትና ፡ ወታደር ፡ ራስ ፡ መርድን ፡ በልቡ ፡ ጠላቸው ፤ ባላገር ፡ ግን ፡ ከልቡ ፡ ወደዳቸው ። በዚህ ፡ ዘመን ፡ የራስ ፡ መርድ ፡ እኅት ፡ የወይዘሮ ፡ ድንቅነሽ ፡ ባል ፡ የዳሞቱ ፡ ደጃች ፡ ዘውዴ ፡ ጉልበት ፡ ተሰምቷቸው ፡ ነበርና ፡ በዳሞት ፡ ላይ ፡ ጐጃምን ፡ ደርበው ፡ መግዛት ፡ አማራቸው ። ራስ ፡ መርድም ፡ ይኸንን ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ለፊት ፡ ጦርነት ፡ በመግጠም ፡ ፈንታ ፡ በብልኀት ፡ ደጃች ፡ ዘውዴን ፡ ይዘው ፡ ለማሰር ፡ አሰቡ ። እንዳሰቡም ፡ እኅቴ ፡ ድንቅነሽ ፡ ናፍቃኛለችና ፡ ይዘኻት ፡ መጥተኸ ፡ ምሳ ፡ እንድንጋበዝ ፡ መልስ ፡ ጠርቼኻለሁ ፡ ብለው ፡ ላኩባቸው ። ደጃች ፡ ዘውዴም ፡ ነገሩ ፡ ሳይገባቸው ፡ ሚስታቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደራስ ፡ መርድ ፡ ቤት ፡ መጡ ። እንደ ፡ መጡም ፡ እኅታቸውን ፡ አስቀርተው ፡ የደጃች ፡ ዘውዴን እጃቸውን ፡ አስያዙና ፡ አስረው ፡ በቀራንዮ ፡ ዋሻ ፡ አስቀመጧቸው ።

ደጃች ፡ ዘውዴም ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ቃሰሩ ፡ ናፍቃኛለችና ፡ ሚስቴን ፡ ድንቅነሽን ፡ ይላኩልኝ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ መርድ ፡ ላኩ ፤ ራስ ፡ መርድ ፤ ዘበኛ ፡ ጨምረው ፡ ድንቅነሽን ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ ዘውዴ ፡ ላኳቸው ፤ በዚያም ፡ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ የሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ አድርገው ፡ ኖሮ ፡ ደጃች ፡ ጕሹ ፡ ተፀንሰው ፡ በጊዜው ፡ ተወለዱ ። ደጃች ፡ ጕሹም ፡ የደጃች ፡ ተሰማ ፡ አባት ፤ የንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አያት ፡ መሆናቸው ፡ ነው ።

※ ※ ※

በዚህ ፡ ዘመን ፡ ራስ ፡ ዓሥራትና ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ ባንድነት ፡ እንደራሴነት ፡ ይዘው ፡ ሲያስተዳድሩ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተጣሉ ። ራስ ፡ ገብሬና ፡ ደጃች ፡ እሸቴ ፡ ለራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ አንገብርም ፡ ብለው ፡ ራስ ፡ መርድን ፡ ጨምረው ፡ ከራስ ፡ ዓሥራት ፡ ጋራ ፡ ሆኑ ፤ ራስ ፡ ጕግሳና ፡ ወንድማቸው ፡ ደጃች ፡ አሉላ ፡ ደግሞ ፡ ለራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ ሆኑ ። በመከከሉም ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ እሸቴ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ እስቴ ፡ ጦር ፡ ሰደዱ ። ደጃች ፡ እሸቴም ፡ ሸሽተው ፡ ቀራንዮ ፡ ከራስ ፡ መርድ ፡ ግዛት ፡ ገብተው ፡ ተቀመጡ ። ይኸንንም ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እጁን ፡ ይዘኸ ፡ ላክልኝ ፡ የሚል ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ጨምረው ፡ ላኩ ፤ ራስ ፡ መርድም ፡ ደጃች ፡ እሸቴን ፡ አልሰድም ፡ ብለው ፡ ከራስ ፡ ዓሥራት ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤልን ፡ ለመዋጋት ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ ተጓዙ ። በዚያም ፡ የበጌምድር ሊቃውንት ፡ ተሰባሰቡና ፡ ከደጃች ፡ እሸቴ ፡ ግዛት ፡ ቈርጠው ፡ እስከ ፡ ርብ ፡ ድረስ ፡ ራስ ፡ መርድ ፡ ለራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ ሊለቁ ፡ ተራርቀው ፡ ተመለሱ ። እንደ ፡ ተመለሱም ፡ ይኸንኑ ፡ ለደጃች ፡ እሸቴ ፡ ቢነግሯቸው ፡ «ይህ ፡ የፈሪ ፡ ዕርቅ ፡ ነው» ፡ ብለው ፡ ለራስ ፡ መርድ ፡ ነገሯቸው ፡ ይባላል ። ስለዚህ ፡ ራስ ፡ መርድ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተጸጽተው ፡ የተቀበሉትን ፡ ዕርቅ ፡ አፍርሰው ፡ እንደ ፡ ጥንቱ ፡ ከተከዚ ፡ ወዲያ ፡ ርጋ ፡ ከዚያ ፡ አልፈኸ ፡ እመጣለሁ ፡ ያልኸ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መጣሁ ፡ ቃጠቅና ፡ ቈየኝ ፡ ብለው ፡ ለራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ ላኩ ፡ ይባላል ።

ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤልም ፡ ይኸን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ለአዝማሪ ፡ ቀኖሎ ፡ ያለውን ፡ ነገሩ ፡ ይባላል ።

እረ ፡ ምነው ፡ ይሆን ፡ ዕርቁ ፡ የፈረሰ ፤<br>
የሚሞት ፡ ሰው ፡ አለ ፡ ቀኑ ፡ የደረሰ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ መርድና ፡ ራስ ፡ ገብሬ ፤ ከራስ ፡ ዓሥራት ፡ ጋራ ፡ ተላልከው ፡ ተገናኙና ፡ ወገራ ፡ ላይ ፡ ለጦርነት ፡ ይጠባበቁ ፡ ገመሩ ። ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤልም ፡ ራስ ፡ ጕግሳንና ፡ የትግሬን ፡ ያ፴፩ ፡ ነጋሪት ፡ አገር ፡ መኳንንትና ፡ ወታደር ፡ ይዘው ፡ ነጋሪታቸውን ፡ እያስጐሸሙ ፡ ከትግሬ ፡ ወደ ፡ ወገራ ፡ መጡ ።

እንደመጡም ፡ ጦርነቱም ፡ ተገሠመረና ፡ ወታደርና ፡ ወታደር ፡ መኳንንትና፡ መኳንንት ሲዋጉ ፡ ራስ ፡ መርድ ፡ «ከጠላቱ ፡ ተሰላፊ ፤ ጠላቱን ፡ አሰላፊ ፡ መርድ፡ የኀይሉ ልጅ ፡ . . . . . » ብለው ፡ ፎክረው ፡ እፈረሳቸው ተጋብተው ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ ጋለቡ ። ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤልም ፡ በፈረሳቸው፡ ሆነው ፡ ፎክረው ፡ በመጨረሻም «የዕርቅ ፡ አምላክ ፡ ፍረድ» ፡ ብለው ፡ ሰይ ፋቸውን መዘው ፡ ሁለቱ ፡ አለቆች ፡ በፈረስ ፡ ሆነው ፡ ተጋጥመው ፡ በሰይፍ፡ እየተማቱ ፡ ቈይተው ፡ ሁለቱም ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ከፈረሶቻቸው ፡ ላይ ፡ ወደቁ። ራስ ፡ መርድም ፤ ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤልም ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ቈዩ ፡ ሞቱ፡ ቢሆንም ፡ የጦርነቱ ፡ ድል ፡ ለራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ ሆነ ። ራስ ፡ ዓሥ ራትም ፡ ሸሹ ፤ ራስ ፡ ገብሬም ፡ በመካከሉ ፡ ሸሽተው ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ስሜን ፡ ሄደው ፡ ተቀመጡ ።

አንዳንዱም ፡ ሰው ፡ ሲተርክ ፡ የራስ ፡ መርድን ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ያደርግና፡ ራስ ፡ ዓሥራትና ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ አንድነት ፡ ሲገዙ ፡ ቈይተው ፡ በመጨረሻ ፡ ተጣሉ ፤ በተጣሉም ፡ ጊዜ ፡ እነዚህን ፡ መኳንንት ፡ ይዘው ፡ ሊዋጉ ፡ ሲሉ ፡ በመካከሉ ፡ ገላጋይ ፡ ገብቶ ፡ አስታረቃቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ድንኳኑን ፡ መገሠመሪያ ፡ እሱ ፡ ነቅሎ ፡ ይሂድ ፤ እኔ ፡ አልነቅልም ፡ አንተ ፡ መገሠመሪያ ፡ ንቀል ፡ በመባባል ፤ እንደ ፡ ገና ፡ ዕርቁ ፡ ፈርሶ ፡ ጦርነቱ ፡ ተደ ረገ ፡ ብለው ፡ ይተርካሉ ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤልና ፡ ራስ ፡ መርድ ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ራስ ፡ ዓሥራትና ፡ ራስ ፡ ገብሬም ፡ ስለ ፡ ሸሹ ፡ በመካ ከሉ ፡ የእንደራሴነቱ ፡ ሥፍራ ፡ ባዶ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በወንድማቸው ፡ በደጃች ፡ አሉላ ፡ (የትንሹ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ አባት) ፡ ደጋፊነት ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ የእንደራሴ ነቱን ፡ ሥፍራ ፡ ያዙ ። ይኸም ፡ የእንደራሴነቱ ፡ ሥፍራ ፡ በመካከል ፡ ራስ ፡ ዓሥራትና ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ ጣልቃ ፡ ገብተው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመገሠመሪያም ፡ የአጎቶቻቸው ፡ የትልቁ ፡ ራስ ፡ ዐሊና ፡ የራስ ፡ ዐሊጋዝ ፡ ነበርና ፤ አሁን ፡ ከሴሩ ፡ ጓንጉል ፡ ዘር ፡ ወደ ፡ ላስታ ፡ ወደነራስ ፡ ወልደ፡ ገብርኤል ፡ ዘሮ ፡ የነበረውን ፡ መልሰው ፡ ተረከቡት ፡ ማለት ፡ ነው ።

## የራስ ፡ ጉግሳ ፡ የምስፍንና ፡ ዘመን ።

## ምዕራፍ ፡ ፹፪ ።

### ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ከራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴና ፡ ከራስ ፡ ገብሬ ፡ ጋራ ፡ ያደረጉት ፡ ጦርነት ።

እንግዴህ ፡ መገሠመሪያ ፡ ታላቅ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፤ ቀጥሎ ፡ ወንድማቸው ፡ ራስ ፡ ዐሊጋዝ ፡ ከዚያ ፡ ወንድማማቾቹ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤልና ፡ ራስ ፡

ዓሥራት ፡ በእንደራሴነት ፡ ሲገዙ ፡ ቈይተው ፡ በለፈው ፡ ጦርነት ፡ ራስ ፡
ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ ሞተው ፡ ራስ ፡ ዓሥራትም ፡ ከሸሹ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡
ያኸል ፡ ጊዜ ፡ ስላልቈዩ ፡ እንደራሴነቱን ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ያዙ ። ርሳቸውም ፡
የታላቅ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ እኅት ፡ የወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ልጅ ፡ የታናሽ ፡ ራስ ፡
ዐሊ ፡ አኅት ፡ ናቸው ። ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ወይዘሮ ፡ ኂሩትን ፡ ወልደው ፡ ወይ
ዘሮ ፡ ኂሩት ፡ ደጃች ፡ ብጡልን ፤ ደጃች ፡ ብጡልም ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱን ፡ ይወ
ልዳሉ ።

ራስ ፡ ጉግሳ ፡ በሺህ ፡ ፯፻፺፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እንደራሴነትን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡
እንደ ፡ ተለመደው ፡ የዐፄ ፡ሕዝቅያስን ፡ ልጅ ፡ ዐፄ ፡ ዕጓለ ፡ ጽዮንን ፡ አነገ
ሡና ፡ ርሳቸው ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ያስተዳድሩ ፡ ዠመር ። በጐጃምም ፡ ባባ
ታቸው ፡ በራስ ፡ መርድ ፡ እግር ፡ ልጃቸው ፡ ደጃች ፡ ኃሉ ፡ ተተክተው ፡ ነበ
ርና ፤ የራስ ፡ ጉግሳን ፡ እንደራሴነት ፡ ደጃች ፡ ኃሉ ፡ ተቀበሉ ። ነገር ፡ ግን ፡
ከትግሬው ፡ ከራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ጋራ ፡ በዘመናቸው ፡ ጠብና ፡ክርክር ፡ ሆነ።
ቢሆንም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ እንዳደረጉት ፡ እራስ ፡ ጉግሳ ፡ ከኗሁ ፡
ከራስ ፡ ወልደ ፤ ሥላሴ ፡ ጋራ ፡ ስምምነት ፡ ዠመሩ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ አንደኛው ፡
የበላይ ፡ ሳይሆን ፡ ትክክል ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ ራሶች ፡ ተስማምተው ፡ ለመግ
ዛት ፡ አይችሉምና ፤ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ መጠራጠርና ፡ ወገን ፡ መፈለግ ፡ አልቀ
ረም ። ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴም ፡ የንጉሡን ፡ የዐፄ ፡ ዕጓለ ፡ ጽዮንን ፡ ልብ ፡
በጋብቻ ፡ ለመማረክ ፡ ሲሉ ፡ በሸመገለ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ዘመን ፡ ምንትዋብ ፡
የምትባለዋን ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ የሆነችውን ፡ የንጉሡን ፡ ልጅ ፡ ለምነው ፡ አገቡ።

ራስ ፡ ጉግሳም ፡ ንጉሡና ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ በጋብቻና ፡ በፍቅር ፡
ተገናኝተው ፡ በርሳቸው ፡ ላይ ፡ እንዳይነሡባቸው ፡ የንጉሡ ፡ ልብ ፡ ከራስ ፡
ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ እንዲከፈል ፡ ሲሉ ፡ እኅታቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ኢየሱ
ስን ፡ በግዴታም ፡ በፍቅርም ፡ አድርገው ፡ ለንጉሡ ፡ ዳሩላቸው ። ስለዚህ ፡
ንጉሡ ፡ አንደኛው ፡ አማታቸው ፤ አንደኛው ፡ አማቻቸው ፡ ከሆኑት ፡ ከነዚህ፡
ከሁለቱ ፡ ራሶች ፡ በተለይ ፡ ለማናቸው ፡ ለማድላት ፡ ይቸገሩ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ላዩን ፡ ከራስ ፡ ጉግሳ ፡ ወዳጅ፡
ቢመስሉ ፡ ውስጡን ፡ መቀናናትና ፡ መቀያየም ፡ አልቀረምና ፡ ድንገት ፡ ጠብ ፡
ተነሥቶ ፡ ከራስ ፡ ጉግሳ ፡ ቢዋጉ ፡ እንዲረዷቸው ፡ ሲሉ ፡ ከስሜኑ ፡ ገዥ ፡
ከደጃች ፡ ውቤ ፡ አያት ፡ ከራስ ፡ ገብሬ ፡ ጋራ ፡ ወዳጅነት ፡ ዠመሩ ።

በዚህም ፡ ዘመን ፡ የነበሩት ፡ ጳጳስ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ እኔ ፡ የሞትሁ ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ የሊቀ ፡ ጵጵስናው ፡ ሥፍራ ፡ ባዶውን ፡ እንዳይቀመጥ ፡ ብለው ፡
ለእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ የሚሰጠውን ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ሰብስበው ፡ ፳፻ ፡
ወቄት ፡ የሚሆን ፡ ወርቅ ፡ በቤታቸው ፡ አስቀምጠው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ራስ፡
ጉግሳ ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ወርቅ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ይገባል ፡ እንጂ ፡

ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ለምን ፡ ይላካል ፡ ብለው ፡ በግድ ፡ ጳጳሱን ፡ ቀሟቸው፡ ይባላል ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ በራስ ፡ ጉግሳ ፡ ላይ ፡ ለመነሣት፡ ምክንያት አገኙ ። በራስ ፡ ጉግሳም ፡ ላይ ፡ የጋላና ፡ የስላም ፡ ዘርነታቸውን ፡ እየጠቀሱ ፡ ለምን ፡ ጳጳስ ፡ ይመጣል ፡ ብሎ ፡ ይኸውና ፡ የጳጳሱን ፡ ማምጫ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ቀማ ፡ ብለው ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ አስነሡባቸው ።

ሕዝቡም ፡ የጳጳሱንና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መደፈር ፡ አይወድምና ፡ ለራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ አበረላቸው ።

ይኸንንም ፡ ወርቅ ፡ ያልመለሱ ፡ እንደሆነ ፡ እንዋጋለን ፡ ብለው ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ከትግሬ ፤ ራስ ገብሬ ፡ ከስሜን ወደ ፡ በጌምድር ፡ ገሠገሡ ። ራስ ፡ ጉግሳም ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ በችግር ፡ ላይ ፡ ሆኑ ፤ በላያቸው ፡ ላይ ፡ ከብዶ ፡ የመጣውንም ፡ ጦር ፡ ለመመለስ ፡ ኀይላቸውን ፡ ተጠራጥረው ፡ ይኸ ንኑ ፡ የወሰዱትን ፡ ወርቅና ፡ እንደ ፡ ካሣ ፡ ከራሳቸውም ፡ ገንዘብ ፡ ጨምረው፡ በዕርቅ ፡ መለሱ ። ስለዚህ ፡ ጦርነቱና ፡ ክርክሩ ፡ ቆመና ፡ ገንዘቡ ፡ ተልኮ ፡ ከእስክንድርያ ፡ አቡነ ፡ ማርቆስ ፡ ፫ኛ ፡ ተመርጠው ፡ መጡ ።

ራስ ፡ ጉግሳም ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ በራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴና ፡ በራስ፡ ገብሬ ፡ ላይ ፡ ቂማቸው ፡ እየበረከተ ፡ ሄደ ።

የተለመደውንም ፡ የጦር ፡ መላ ፡ በመከተል ፡ ሁለቱን ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ከመዋጋት ፡ እየነጠሉ ፡ ለመውጋት ፡ የሚችሉበትን ፡ መንገድ ፡ ያስቡ ፡ ዠመር። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የየጁን ፤ የራያንና ፡ የአዘቦን ፡ ሕዝብ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ያለውን ፡ ተወላጅነቱን ፡ በመጥቀስ ፡ ገንዘብም ፡ በመስጠት ፡ አባብለው ፡ በራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ላይ ፡ አስነሡባቸው ። በኋላም ፡ የተከዚ ፡ ወንዝ ፡ ሞልቶ ፡ ራስ ፡ ወልደ፡ ሥላሴና ፡ ራስ ፡ ገብሬ ፡ ሊገናኙ ፡ በማይችሉበት ፡ በክረምት ፡ ወራት ፡ በሺሕ፡ ፲፯፻፺ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዓርባ ፡ ሺሕ ፡ የእግረኛ ፡ ወታደር ፤ ፳ ፡ ሺሕ ፡ ፈረሰኛ ፡ ይዘው ፡ ራስ ፡ ገብሬን ፡ ለመግጠም ፡ ሄዱ ። ራስ ፡ ገብሬም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ የጦር ፡ ጓደኛቸው ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ መጥተው ፡ ሊረዱ ቸው ፡ አለመቻላቸውን ፤ ባንድ ፡ ወገን ፡ የራስ ፡ ጉግሳን ፡ ጦር ፡ የሚወዳደር ፡ ወታደር ፡ እንደሌላቸው፡ ስለ ፡ ተረዱ ፡ እሜዳ ፡ ወርደው ፡ በፊት ፡ ለፊት ፡ ጦርነት ፡ ከማድረግ ፡ ይልቅ፡ ብዙውን ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ አሰናብተው ፡ ምርጥ ፡ የሆኑትን ፡ ወታደሮች፡ ብቻ ፡ ይዘው ፡ አምባ ፡ ግሼን ፡ ተራራ ፡ ላይ መሽገው ፡ መከላከልን ፡ መረጡ ።

በዚህም ፡ ራስ ፡ ገብሬ ፡ በመሸጉበት ፡ ተራራ ፡ ጥግ ፡ የራስ ፡ ጉግሳ ፡ ጦር፡ ደርሶ ፡ ይዋጋ ፡ ዠመር ። ነገር ፡ ግን ፡ እተራራው ፡ ላይ ፡ የመሸጉት ፡ የስሜን ፡ ወታደሮች ፡ በናዳም ፡ በነፍጥም ፡ እየወጉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እያሸነፉ ፡ ስለ ፡ መለ ሷቸው ፡ የተራራው ፡ ጦርነት ፡ በፍጹም ፡ የማይበገር ፡ መሆኑ ፡ በራስ ፡ ጉግሳ ፡ ወታደሮች ፡ ዘንድ ፡ የተረጋገጠ ፡ ሆነ ፤ ስለዚህ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ጦርነቱን ፡

አቁመው ፡ የራስ ፡ ጉግሳም ፡ ጦር ፡ ከተራራው ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡
ሊጠባበቁ ፡ ቆዩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የተከዚ ፡ ወንዝ ፡ መጉደል ፡ ሲዠምር ፡ ራስ፡
ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ተከዚን ፡ ተሻግረው ፡ ወደ ፡ ስሜን ፡ ጭፍራ ፡ ይዘው ፡ ራስ፡
ገብሬን ፡ ለመርዳት ፡ ጉዞ ፡ ማድረጋቸው ፡ ተሰማ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የራስ ፡
ገብሬ ፡ ጭንቀትና ፡ ችግር ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ዞረ ።

ስለዚህ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳሰቡት ፡ የስሜንና ፡ የትግሬን፡
ጦር ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ወግተው ፡ ለመመለስ ፡ ስላልቻሉ ፡ ከጦሩ ፡ ግንባር ፡ ከነሠ
ራዊታቸው ፡ መመለስ ፡ ዠመሩ ። ወዲያውም ፤ ከራያና ፡ ከአዘቦ ፡ ባላባቶች ፤
ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ አጥቅተዋቸው ፡ ከሚኖሩበት ፡ ከትግሬ ፡ ባላባቶች ፡ ጋራ፡
ተላልከው ፡ በራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ላይ ፡ ተስማሙ ። ለነሱም ፡ «ከወዲህ ፡ እኔ ፡
አለሁ ፡ ከወዲያ ፡ እናንተ ፡ ግጠሙ» ፡ እያሉ ፡ የፈረሰኛ ፡ መላክተኛ ፡ በግልቢያ ፡
እያከታተሉ ፡ ላኩባቸው ። እነዚህም ፡ የተንቤን ፤ የራያ ፤ የአዘቦ ፤ ባላባቶች ፡
ባንድነት ፡ ተነሥተው ፡ የራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴን ፡ ዋና ፡ ግዛት ፡ ዐድዋን ፡ ወረራ፡
ዠመሩ ። ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴም ፡ ከስሜን ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ዐድዋ ፡ መጡ።
ከሽፍቶቹም ፡ ገሚሶቹ ፡ የክዳት ፡ ሥራቸውን ፡ በልባቸው ፡ አኑረው ፡ ይማሩን፡
ብለው ፡ ቃርቀው ገቡላቸው ። የቀሩትንም ፡ አስቃርቀን ፡ እናስገባለን ፡ እያሉ ፡
ተስፋ ፡ እየሰጡ ፡ እውጭ ፡ ከሉት ፡ ሽፍቶች ፡ ጋራ ፡ [stain]ተላላኩ ፡ ሲስማሙ ፡
ሰነበቱ ። በመጨረሻም ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ሌሊት ፡ ራስ ፡ ወ[stain] ፡ ሥላሴ ፡ የሰፈሩበ
ትን ፡ መንደር ፡ አቃጠሉት ። በተለይም ፡ ራስ ፡ ወልደ [stain]ሥላሴ ፡ ተኝተውበት ፡
የነበረውን ፡ ሲያቃጥሉት ፡ አብሯቸው ፡ የነበረ ፡ ፒርስ ፡ (Pearce) ፡ የሚባለው፡
የእንግሊዝ ፡ ተወላጅ ፡ (የሒንሪ ፡ ሳልት ፡ ጓደኛ) ፡ ቀስቅሶ ፡ ባያሥነሣቸው ፡ ኖሮ፡
በእልፍኛቸው ፡ እንዳሉ ፡ ሊቃጠሉ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡
ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ መጨረሻቸውን ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፤ እነዚ
ህን ፡ ለመርዳት ፡ ወደ ፡ ዐድዋ ፡ አልሄዱም ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡
ሥላሴ ፡ እነዚህኑ ፡ ሽፍቶችና ፡ ሌሎቹንም እርሳቸውን ፡ ለመግደል ፡ ዐድማ ፡
ያደረጉትን ፡ ሽፍቶች ፡ እየተከታተሉ ፡ በወታደር ፡ አስፈጁዋቸው ።

ጉጂ ፡ የሚባለው ፡ የራያና ፡ ያዘቦ ፡ ባላባት ፡ ግን ፡ ከጦርነት ፡ በኋላ ፡ በድ
ርድር ፡ ቃርቆ ፡ በሰላም ፡ ወዳገሩ ፡ ተመለሰ ። በአጋሜም ፡ ተነሥተውባቸው ፡
ለነበሩት ፡ ለሹም ፡ አጋሜ ፡ ወልዱ ፡ (ለደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ አባት) ፡ የአጋሜን፡
ግዛት ፡ መርቄልኻለሁ ፡ ብለው ፡ ባዋጅ ፡ ስላስታወቁ ፡ ለጊዜው ፡ ሰላም ፡ ሆነ ።
በኋላ ፡ ግን የሹም ፡ አጋሜ ፡ ወልዱ ፡ ልጆች ፡ እያደጉ ፡ ስለ ፡ ሄዱ ፡ ከነሱም ፡
ውስጥ ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ እያደር ፡ ኀይል ፡ ስለ ፡ ተሰማቸው ፡ በሙሉ ፡ የትግ
ሬን ፡ ግዛት ፡ ከራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ለመቀማት ፡ አሰቡ ። ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴም
ወንድማማቾቹን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ አጣልቼ ፡ በደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ላይ ፡
አሥነሥቼ ፡ እነሱ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲፋጁ ፡ እኔ ፡ በሰላም ፡ ዘመኔን ፡ እገፋ
ለሁ ፡ ብለው ፡ ወንድማማቾቹን ፡ ለማጣላት ፡ መሞከራቸው ፡ አልቀረም ። ነገር ፡

ግን ፡ በተወለዱ ፡ በሰማንያ ፡ ዓመት ፡ በሺሕ ፡ ፰፻፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመጋቢት ፡ ወር፡ ዐረፉና የደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ኀይል ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እየገነነ ፡ ይሄድ ፡ ዠመር ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የስሜኑ ፡ ራስ ፡ ገብሬ ፡ በዚያው ፡ በስሜን ፡ ግዛታቸው ፡ ስለተወሰኑ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴም ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስም ፡ ገና፡ ስማቸው ፡ ስላልታወቀ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ እንደ ፡ ልባቸው ፡ እስከ ፡ ትግሬም ፡ እስከ ፡ ስሜንም ፡ ገዥነታቸውን ፡ ለማጽደቅ ፡ ተመቻቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፹፯ ።

የዳሞቱ ፡ ደጃች ፡ ዘውዴ ፤ ከደጃች ፡ ጓሉና ፡ ከደጃች ፡ ኤልያስ ፤ ከራስ ፡ ጉግሳ ፡ ጋራ ፡ ያደ

## ረጉት ፡ ጦርነት ።

ይህ ፡ ያለፈው [illegible]ራፍ ፡ ከዋናው ፡ ከተማ ፡ ከጐንደር ፡ በስሜን ፡ በትግሬ ፡ በኵል ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ ሲያሳየን ፡ ያሁኑ ፡ ደግሞ ፡ በጐጃምና ፡ በዳሞት ፡ በአገው ፡ ምድር ፡ በኵል ፡ ያለውን ፡ ያመለክተናል ። ወሎና ፡ የጁ ፡ ራያና ፡ አዘቦ ፡ በዙሪያው ፡ ያለው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ በዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ዠመረው ፡ በዘርና ፡ በትውልድ ፡ በጋብቻ ፡ ከራስ ፡ ጉግሳ ፡ ጋራ ፡ በመገናኘቱ ፡ ከሌላው ፡ ይበልጥ ፡ ለራስ ፡ ጉግሳ ፡ የሚገዛ ፡ ሕዝቡና ፡ ወታደሩም፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ላዋሉት ፡ ጉዳይ ፡ የሚውል ፡ በመሆኑ ፡ በዘመኑ ፡ አገልግሏል ። ሸዋ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ ጊዜ ፡ ከጐንደር ፡ መንግሥት ፡ ተነጥሎ ፡ ራሱን ፡ እንደ ፡ ቻለ ፡ ነው ፤ በተፍጻሜተ ፡ መንግሥት ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ጊዜ ፡ ለማስገበርም ፡ ቢሞከር ፡ አልተቻለም ። ባሁኑም ፡ ዘመን ፡ መዠመሪያ ፡ በወሰን ፡ ሰገድ ፤ ቀጥሎም ፡ በልጃቸው ፡ በሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ እየተመራ ፡ በሸዋ ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ የጋላ ፡ አገር ፡ እያ ቀና ፡ በሰላም ፡ ተቀምጧል ።

ስለዚህ ፡ አሁን ፡ በጐጃምና ፡ በዳሞት ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ እንመልከት ። በጐጃም ፡ ራስ ፡ መርድ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ልጃቸው ፡ ደጃች ፡ ጓሉ ፡ ተተኩ ። ደጃች ፡ ጓሉም ፡ አባታቸውን ፡ ራስ ፡ መርድን ፡ ወታደር ፡ እንደ ፡ ጠላቸውና፡ ከራስ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤልም ፡ የተዋጉለት ፡ ለግሞ ፡ እንዳጋለጣቸው ፡ ስላወቁ ፡ ባላገርን ፡ ትተው ፡ ወታደርን ፡ ማፍቀርና ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ማስደሰት ፡ ዠመሩ ።

ስለዚህ ፡ ወታደር ፡ በደጃች ፡ ጓሉ ፡ ጊዜ ፡ ተመችቶት ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ የባላገርን ፡ በሬና ፡ ላም ፤ በግና ፡ ፍየል ፡ እያረደ ፡ ይበላ ፡ ዠመር ። በዚህም ፡ ሳይወሰን ፡ የባላገሩን ፡ ሚስት እየቀማ አስለቀሰው ። ራስ ፡ መርድ ፡ ባላገርን ፡ አፍቅረው ፡ ዶሮውንና ፡ እርጎውን ፡ ሳይቀር ፡ በወታደር ፡ በማስጠበቃቸውም ፡ እያፈዘ ።

እንዴት ፡ ነሽ ፡ ርጎ ፡ የመርድ ፡ ማደጎ ፤ እንዴት ፡ ነሽ ፡ ዶሮ ፡ የመርድ ፡ ወይዘሮ ፡ እያለ ፡ እየዘፈነ ፡ በየባላገሩ ፡ ቤት ፡ እየገባ ፡ ዶሮውን ፡ እያረደ ፡ በሙብላት ፤ ርጎውን ፡ እየደፋ ፡ በመጠጣት ፡ አስቸገረው ፤ ቢጮኽም ፡ ተቀባይ ፡ አላገኘም ፡ ይባላል ።

ለደጃች ጓሉም ፡ በዘመናቸው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስማቸውን ፡ ያነሣናቸው ፡ ያክስታቸው ፡ የወይዘሮ ፡ ድንቅነሽ ፡ ባል ፡ የዳሞቱ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ደጃች ፡ ዘውዴ ፡ ባላንጣና ፡ ባላጋራቸው ፡ ነበሩ ። ስለዚህ ፡ ደጃች ፡ ጓሉ ፡ ደጃች ፡ ዘውዴን ፡ ለማጥቃት ፡ ሲሉ ፡ ለራስ ፡ ጉግሳ ፡ በፍጹም ፡ ወዳጅና ፡ ታዛዥ ሆነ ። ከአገው ፡ ምድር ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ከደጃች ፡ ኤልያስም ፡ ወዳጅነታቸውን ፡ አጸኑ ፤ ደጃች ፡ ጓሉ ፡ ከጐጃም ፤ ደጃች ፡ ኤልያስም ፡ ከአገው ፡ ምድር ፡ ሆነው ፡ ዳሞትን ፡ ለመግዛትና ፡ ደጃች ፡ ዘውዴን ፡ ለማስገበር ፡ ከበቡ ። ደጃች ፡ ዘውዴ ፡ ምንም ፡ የታወቁ ፡ ዠግና ፡ ቢሆኑ ፡ የከበቧቸውን ፡ እነዚህን ፡ ሁለት ፡ ደጃዝማቾች ፡ በንድ ፡ ጊዜ ፡ ተዋግተው ፡ መመለስ ፡ እንደማይሆንላቸው ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡ ጦርነቱን ፡ ትተው ፡ ደምበጫ ፡ ሚካኤል ፡ ገብተው ፡ ደወሉ ። ከዚያም ፡ በሊቃውንቱና ፡ በቀሳውስቱ ፡ ምልጃ ፡ ግማሽ ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸውን ፡ አስረክበው ፡ ታርቀው ፡ ወዳገራቸው ፡ ተመለሱ ። እንደ ፡ ተመለሱም ፡ ቂማቸውን ፡ በልባቸው ፡ ይዘው ፡ ባገራቸው ፡ በዳሞት ፡ የሚገኘውን ፡ ያማራ ፡ የጋላ ፡ ጦር ፡ ሰብስበው ፡ ደጃች ፡ ኤልያስን ፡ ለመውጋት ፡ ወደ ፡ አገው ፡ ምድር ፡ ገሠገሡ ፤ ደጃች ፡ ኤልያስም ፡ ፺ ፡ ቤት ፡ የአገውን ፡ የሚጫንና ፡ የአቸፈርን ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ይጠብቁ ፡ ዠመር ። ደጃች ፡ ዘውዴም ፡ ወታደራቸውን ፡ ይዘው ፡ በመግጠም ፡ ፈንታ ፡ በብልኀት ፡ የደጃች ፡ ኤልያስን ፡ ጦር ፡ ለመፍጀት ፡ አስበው ፡ ፴ ፡ ቊርበት ፡ ከ፴ ፡ ግልገል ፡ በቅሎ ፡ ጋር ገዝተው ፡ ቊርበቱን ፡ በግልገሎቹ ፡ ላይ ፡ አስረው ፡ ሌሊት ፡ በደጃች ፡ ኤልያስ ፡ ሰፈር ፡ ለቀቁበት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግልገሎቹ ፡ በቅሎዎች ፡ ቈዳቸውን ፡ እያንኳኩ ፡ ደንብረው ፡ በደጃች ፡ ኤልያስ ፡ ሰፈር ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ሲራወጡ [illegible]ች ፡ ኤልያስ ፡ ወታደር ፡ ሌሊት ፡ ምን ፡ መጣ ፡ ብሎ ፡ ደንግጦ ፡ እየተፏፈረ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ ተላለቀ ፤ ግማሹም ፡ ሲሸሽ ፡ በየጕድጓዱ ፡ በየገደሉ ፡ እየገባ ፡ ሞተ ። የቀረውም ፡ በቊጥቋጦ ፡ ውስጥ ፡ ተደብቆ ፡ ሳለ ሊነጋ ፡ ሲል ፡ ደጃች ፡ ዘውዴ ፡ በፈረሳቸው ፡ ከነወታደራቸው ፡ ገብተው ፡ የተረፈውን ፡ የደጃች ፡ ኤልያስን ፡ ጦር ፡ ፈጁት ፡ ይባላል ፤ ደጃች ፡ ኤልያስም ፡ ተማረኩ ። ከዚያም ፡ ደጃች ፡ ዘውዴ ፡ ጐጃምን ፡ ለመውጋት ፡ ሲጓዙ ፡ ደጃች ፡ ጓሉ ፡ በብላታ ፡ ኰላሊት ፡ መሪነት ፡ አስቀድመው ፡ ወታደር ፡ ሰደዱ ፤ ብላታ ፡ ኰላሊት ፡ ግን ፡ የደጃች ፡ ዘውዴን ፡ ባለቤት ፡ ወይዘሮ ፡ ድንቅነሽን ፡ ከሉበት ፡ ከደምበጫ ፡ ይዞ ፡ ሳይዋጋ ፡ ፈርቶ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ሸሸ ። ደጃች ፡ ዘውዴም ፡ የደጃች ፡ ጓሉን ፡ ጦር ፡ ለመውጋት ፡ ይጓዙ ፡ ዠመር ፤ በመንገድም ፡ በሜዳ ፡ ያገኙትን ፡ ጊደርና ፡ ወይፈን ፡ ሰብስበው ፡ በፈረሰኛ ፡ አስከብበው ፡ ነፍጠኛውን ፡ (ባለጠመንዣውን) ፡ በማኽል ፡ አድርገው ፡ ጐጃሞቹ ፡ ወዳሉበት ፡ ወደ ፡ ሰንተራ ፡

ሜዳ ፡ ሲመጡ ፡ ጕጃሞቹ ፡ ብዛቱን ፡ አይተው ፡ በሩቅ ፡ ደንግጠው ፡ ሳይዋጉ ፡ ሸሹ ፤ ስለዚህ ፡ ደጃች ፡ ዘውዴ ፡ በብልኅት ፡ አገዎችን ፡ በቍርበት ፤ ጕጃሞችን ፡ በሜዳ ፡ ከብት ፡ አሸነፉቸው ፡ እየተባለ ፡ እየተሣቀ ፡ ተወራ ፡ ይባላል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሰንተራ ፡ ሜዳ ፡ ተመልሰው ፡ ብላታ ፡ ኵላሊት ፡ ሚስታቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ድንቅነሽን ፡ ይዘ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ዘንድ ፡ ሄዶ ፡ መቀመጡን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በጌምድር ፡ ሄደው ፡ ከራስ ፡ ጉግሳ ፡ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ አሰቡ ። በግብርም ፡ ጊዜ ፡ ጦር ፡ ግድግዳ ፡ ሆኖ ፡ በሾተል ፡ (በሰይፍ) ፡ ቢማገር ። ሳላየው ፡ አልቀርም ፡ የድንቂቱን ፡ አገር ፡ ብለው ፡ ላዝማሪ ፡ ነገሩ ፡ ይባላል ።

ቀጥሎም ፡ መኰንንስ ፡ ቢሆን ፡ ከቤቱ ፡ ባልወጣ ፡ . . . ብለው ፡ አንዱን ፡ የግጥም ፡ ሐረግ ፡ ዝምረው ፡ ሁለተኛውን ፡ ሳይሞሉ ፡ ደብዳቤ ፡ ጨምረው ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ ለዋናው ፡ እንደራሴ ፡ ለራስ ፡ ጉግሳ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ላኩ ። ራስ ፡ ጉግሳም ፡ ወረቀቱን ፡ አንብበው ፡ ተዝምሮ ፡ ሳይጨረስ ፡ የቀረውን ፡ ግጥም ፡ ምክንያቱ ፡ ስላልገባቸው ፡ ብላታ ፡ ኵላሊትን ፡ ጠየቁት ፤ እርሱም ፡ አይቶ ፡ ስላልገባው ፡ የባሏን ፡ ምሥጢር ፡ ሚስቱ ፡ አታጣውም ፡ ብሎ ፡ ለወይዘሮ ፡ ድንቅነሽ ፡ አሳለፈው ። ወይዘሮ ፡ ድንቅነሽም ፡ መርምረውና ፡ አስተውለው ፡ መኰንንስ ፡ ቢሆን ፡ ከቤቱ ፡ ባልወጣ ፡ . . . . ያለው ።

ንጉሥ ፡ የመሰለ ፡ ዘውዴ ፡ ጫኑ ፡ (ዘውድ ፡ የጫነ) ፡ መጣ ፡ ማለቱ ፡ ነውና ፤ ይልቅስ ፡ ለጦርነት ፡ ብትዘጋጁ ፡ ይሻላችኋል ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ይባላል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ጦራቸውን ፡ አስከትተው ፡ ሲጠብቁ ፡ ደጃች ፡ ዘውዴም ፡ የዳሞትን ፡ ጦር አስከትተው ፡ መጥተው ፡ ጦርነቱ ፡ ተዠመረ ። እንደ ፡ ተዠመረም ፡ ደጃች ፡ ዘውዴ ፡ «ዘውዴ ፡ ሥልጣን ፡ የሐመር ፡ ጌታ» ፡ እያሉ ፡ እየፎከሩ ፡ በፈረሳቸው ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ በዠግንነት ፡ ተዋጉ ፡ ይባላል ። በመጨረሻ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ኀይለኛ ፡ የራስ ፡ ጉግሳ ፡ ወታደር ፡ አነጣጥሮ ፡ ፈረሳቸውን ፡ መታና ፡ ጣላቸው ፡ ወታደርና ፡ ወታደርም ፡ ሲዋጋ ፡ የራስ ፡ ጉግሳ ፡ ወታደሮች ፡ አሸነፈው ፡ የደጃች ፡ ዘውዴም ፡ ወታደሮች ፡ ሸሸት ፡ ዠመሩ ። ደጃች ፡ ዘውዴም ፡ ከጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ በድንግል ፡ በር ፡ አድርገው ፡ ሸሹ ። ከዚያ ፡ በራስ ፡ ጉግሳ ፡ ትእዛዝ ፡ የሚጫው ፡ ገዥ ፡ ደጃች ፡ ወልደ ፡ ሩፋኤል ፡ አባረው ፡ ደጃች ፡ ዘውዴን ፡ ማረኳቸውና ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ አመጧቸው ። ራስ ፡ ጉግሳም ፡ በጣና ፡ ውስጥ ፡ ጨቅላ ፡ መንዞ ፡ ከሚባለው ፡ ደሴት ፡ ይታሰር ፡ ብለው ፡ ስላዘዙ ፡ በዚያው ፡ እንደ ፡ ታሰሩ ፡ ሞቱ ።

የደጃች ፡ ዘውዴን ፡ መሸነፍና ፡ መማረክ ፤ መታሰራቸውንና ፡ መሞታቸውንም ፡ ወይዘሮ ፡ ድንቅነሽ ፡ በየጊዜው ፡ ሰሙ ፤ በጣምም ፡ አዝነው ፡ አለ

ቀሱ ፡ ይባላል ። ይኸ ፡ ሁሉ ፡ የደረሰበት ፡ በኔ ፡ በሚስቱ ፡ የተነሣ ፡ ነውና ፤ እኔም ፡ ክርሱ ፡ ወዲያ ዓለም ፡ ይቅርብኝ ፡ ብለው ፡ ማኅበረ ፡ ሥላሴ ፡ ገዳም ፡ ገብተው ፡ መንኰሰው ፡ ገዳሙን ፡ እያገለገሉ ፡ ተቀመጡ ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወርደው ፡ የጌታችንን ፡ መቃብር ፡ ተሳልመው ፡ በዚያው ፡ ሞቱ ፡ ይባላል ።

ደጃች ፡ ዘውዴ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ በዳሞት ፡ ግዛት ፡ ደጃች ጐሹ ፡ ተተኩ ። በጐጃም ፡ ግን ፡ አሁንም ፡ እኛው ፡ የራስ ፡ ጉግሳ ፡ ወዳጅ ፡ ደጃች ፡ ኀሉ ፡ ናቸው ። ደጃች ፡ ኀሉ ፡ ከቀድሞ ዠምረው ፡ ለዋናው ፡ እንደራሴ ፡ ቃማኝነታቸውን ፡ ገልጠው ፡ በጠጅቸውም ፡ ጊዜ ፡ እሺ ፡ እያሉ ፡ እስከ ፡ ጐንደር ፡ እስከ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ድረስ ፡ እየሄዱ ፡ ይገናኙ ፡ ነበር ።

የዳሞት ፡ ገዥ ፡ ግን ፡ ከውሃና ፡ ከየሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አይታወቅም ፤ ከቀድሞ ፡ ዠምሮ ፡ በላባቶቹ ፡ አገረ ፡ ገዥዎቹ ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ ኀይለኞች ፡ እየሆኑ ፡ ለጐንደር ፡ ነገሥታት ፡ እንኳ ፡ አንገዛም ፡ እያሉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይሸፍቱ ነበር ። በደጃች ፡ ወሬኛ ፡ በፋሲልም ፡ ጊዜ ፡ የተደረገውን ፡ ጦርነት ፡ ያሁኑንም የደጃች ፡ ዘውዴን ፡ እንሆ ፡ አንብበናል ፤ አሁንም ፡ በራስ ፡ ጉግሳ ፡ ጥሪ ፡ የጐጃሙ ገዥ ፡ ደጃች ፡ ኀሉ ፡ ሲሄዱ ፤ የዳሞቱ ፡ ገዥ ፡ ደጃች ፡ ጐሹ ፡ እንቢ ፡ ብለው ፡ ቀሩ ።

ራስ ፡ ጉግሳ ፡ የደጃች ፡ ጐሹን ፡ እንቢታ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ የጐጃሙን ፡ ገዥ ደጃች ፡ ኀሉን ፡ መሪ ፡ አድርገው ፡ ከበጌምድር ፡ ወደ ፡ ዳሞት ፡ መጡ ። ደጃች ፡ ጐሹም ፡ መሣሪያቸውንና ፡ ዕቃቸውን ፡ ቤተ ፡ ሰባቸውን ፡ ከወታደር ፡ ጋራ ፡ በጅበላ ተራራ ፡ ትተው ፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እራቾ ፡ ዘሮች ፡ (ጋሎች) ፡ ዘንድ ፡ ሄደው ፡ ተደበቁ ። ራስ ፡ ጉግሳም ፡ ይኸን ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ጐበና ፡ በሚባሉ ፡ በባጅቶ ፡ ምስለኔ ፡ የሚመራ ፡ ጦር ፡ ትተው ፡ ወደበጌምድር ፡ ተመለሱ ። የርሳቸውን ፡ መመለስ ፡ ደጃች ፡ ጐሹ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከሉበት ፡ ሥፍራ ፡ ወጥተው ወታደራቸውን ፡ ይዘው ፡ ደጃች ፡ ጐበናን ፡ ወግተው ፡ አሸንፋና ፡ በግዛታቸው ፡ በዳሞት ፡ እንደገና ፡ ተደላደሉ ። እንዲያውም ፡ በዚያው ፡ ዘመን ፡ የጐጃሙ ፡ ገዥ ፤ ደጃች ፡ ኀሉ ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ከልጃቸው ፡ ከይመር ፡ ኀሉ ፡ ጐጃምን ፡ ቀምተው ፡ ወደራሳቸው ፡ ግዛት ፡ ደረቡት ። ራስ ፡ ጉግሳም ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ለደጃች ፡ ጐሹ ፡ ተመቻቸው ፤ ባይሞቱ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ዘምተው ፡ ደጃች ፡ ጐሹን ፡ መውጋታቸው ፡ አይቀርም ፡ ነበር ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፲፫ ።

### የራስ ፡ ጉግሣ ፡ ትልቅነትና ፡ ዕድል ።

በጐንደር ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ከነበሩት ፡ መሳፍንት ፡ ወይም ፡ እንደራሴ ፡ ከምንላቸው ፡ ውስጥ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ በጣም ፡ የታደሉ ፡ ነበሩ ። ከሌሎቹም ፡ የበለጠ ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ነበራቸው ፡ ፳፪ ፡ ወይም ፡ ፳፫ ፡ ዓመት ፡ የግዛት ፡ ዘመን ፡ አግኝተው ፡ አማራንና ፡ ጋላን ፤ እስላምንና ፡ ክርስቲያንን ፡ በተ

ቻለ ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ እያስማሙ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ገዙ ። እንቢ ፡ ያለውንም በሚወጉበት ፡ ጊዜ ፡ የድል ፡ አድራጊነት ፡ ዕድል ፡ ነበራቸው ።

ለርሳቸውም ፡ ወይዘሮ ፡ አስቴር ፤ ወይዘሮ ፡ ኂሩት ፤ ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ተክሌ፡ የሚባሉ ፡ ሦስት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ነበሯቸው ። ከነዚሁም ፡ ወይዘሮ ፡ አስቴርን፡ ለትግሬው ፡ ለደጃች ፡ ገብሬ ፡ ሚካኤል ፤ ወለተ ፡ ተክሌን ፡ ጠበኛቸው ፡ ለነበሩት ፡ ለደጃች ፡ ማሩ ፤ ወይዘሮ ፡ ኂሩትን ፡ ለራስ ፡ ገብሬ ፡ ልጅ ፡ ለደጃች ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ አጋቧቸው ። ሌላም ፡ አራተኛ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ነበረቻቸው ፡ ይባላል ። ከነዚህ ፡ ውስጥ ፡ ወይዘሮ ፡ ኂሩት ፡ የደጃች ፡ ብጡል ፡ እናት ፡ የእቴጌ ጣይቱ ፡ አያት ፡ መሆናቸውን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ገልጸናል ።

እንደዚሁም ፡ ወንዶች ፡ ልጆቻቸው ፡ ራስ ፡ ማርዬ ፤ ራስ ፡ ይማም ፡ ራስ ፡ ዶሪ ፡ ይባላሉ ። እነዚህም ፡ ከርሳቸው ፡ ቀጥለው ፡ ላጪጭር ፡ ዘመን ፡ እንደራሴነት ፡ ይዘዋል ። የመጨረሻውም ፡ እንደራሴ ፡ ትንሹ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ የወንድማቸው ፡ የደጃች ፡ አሉላ ፡ ልጅ ፡ ናቸው ።

የራስ ፡ ጉግሣም ፡ ባለቤት ፡ ከእቴጌ ፡ ምንትዋብ ፡ የሚወለዱት ፡ የዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ፍቅርት ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ የርሳቸው ፡ ሚስትነት ፡ ከመገርመሪያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ መሆኑን ፡ መውለድ ፡ አለመውለዳቸውንም ፡ ለመመርመርና ፡ ለመግለጥ ፡ ጊዜ ፡ አላገኘሁም ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ በተጻፉት ፡ ምዕራፎች ፡ እንዳስረዳነው ፡ እንደራሴው በሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሲገዛ ፡ በግድ ፡ በራሱ ፡ ምርጫ ፡ አንድ ፡ የነጋሢ ፡ ዘር ፡ ለስሙም ፡ ቢሆን ፡ በበላዩ ፡ ማስቀመጥ ፡ እንዳለበት ፡ እንደዚሁም ፡ ራስ ፡ ጉግሣ ፡ በዚሁ ፡ በረዥም ፡ የግዛት ፡ ዘመናቸው ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ ነገሥታት ፡ በየተራ ፡ በዙፋን ፡ አስቀምጠዋል ። ስማቸውም ፡ የመገርመሪያው ፡ ዐፄ ፡ ጊጋር ፤ የ፪ኛው ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስ ፤ የ፫ተኛው ፡ ዐፄ ፡ ጓሉ ፡ (ዕጓለ ፡ ጽዮን ፡) ነው ። እነዚህም ፡ ሦስቱ የመገርመሪያው ፡ አባት ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉት ፡ ልጅ ፤ ቀጥለው ፡ የነገሡትም ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ናቸው ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ ረዥም ፡ የግዛት ፡ ዘመንም ፡ ቢኖረው ፡ ካንድም ፡ ከብዙ ፡ ሴትም ፡ ብዙ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ቢወልድም ፡ ዘሩ ፡ የትንሽ ፡ ወይም ፡ የትልቅ ፡ ወገን ፡ ቢሆንም ፡ በዘመኑ ፡ በገርግንነትና ፡ ባስተዳደርም ፡ የተመሰገነ ፡ በሕዝብም ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ቢሆንም ፡ ሁሉም ፡ ተጠራቅሞ ፡ እንኳን ፡ ከሞት ፡ አደጋ ፡ ሊከለል ፡ እስከ ፡ ጊዜው ፡ ከሕመም ፡ እንኳ ፡ ለማዳን ፡ አለመቻሉ ፡ ለሰው ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

ስለዚህ ፡ ትልቁ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ በሰላምም ፡ በጦርነትም ፡ ኢትዮጵያን ፡ ፳፮ ፡ ዓመት ፡ አስተዳድረው ፡ በሺሕ ፡ ፲፰፻፲፯ ፡ ዓ፡ ም፡ በግንቦት ፡ ወር ፡ ሞተው ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ተቀበሩ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፱ ።

## የራስ ፡ ይማም ፡ የምስፍንና ፡ ዘመን ።

ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ሲሞቱ ፡ ልጃቸው ፡ ራስ ፡ ይማም ፡ በባታቸው ፡ እግር ፡ ተተክተው ፡ ያስተዳድሩ ፡ ገዦመር ። ከነጋሚዎችም ፡ ውስጥ ፡ አዲስ ፡ ፈልጎ ፡ በማስቀመጥ ፈንታ ፡ አባታቸው ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ አንግሠዋቸው ፡ የነበሩትን ፡ ዐፄ ፡ ጊጋርን ፡ ርሳቸውም ፡ መልሰው ፡ አነገሡዋቸው ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ቀድሞ ፡ በነገሥታቱ ፡ ጊዜ ፡ ከስሜን ፣ ከላስታ ፣ ከዳሞት ፡ ከሌላውም ፡ አውራጃ ፡ አንዳንድ ፡ ባላባት ፡ እየተነሣ ፡ ያውከቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በቅርቡም ፡ በራስ ፡ ጉግሳ ፡ ጊዜ ፡ ከዳሞት ፡ እነደጃች ፡ ዘውዴ ፣ እነደጃች ፡ ጐሹ ፣ ከትግሬም ፡ እነራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ አንገዛም ፡ እያሉ ፡ ያውኳቸው ፡ እንደነበረ ፡ አንገዛም ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እነሱም ፡ ምስፍንናን ፡ እንደ ፡ ባላንጣ ፡ እየተሻሙ ፡ ይፎካከሯቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፤ አሁንም ፡ ራስ ፡ ይማም ፡ በዘመናቸው ፡ የስሜኑ ፡ ባላባት ፡ የራስ ፡ ገብሬ ፡ ልጅ ፡ ደጃች ፡ ኃይሉ ፡ ማርያም ፡ አልገዛም ፡ ብለው ፡ አወኳቸው ። እንዲያውም ፡ ደጃች ፡ ኃይሉ ፡ ማርያም ፡ በበኩላቸው ፡ ዐፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፡ አንግሸለሁና ፡ ምስፍንና ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ተነሡ ። በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ራስ ፡ ይማምና ፡ ደጃች ፡ ኃይሉ ፡ ማርያም ፡ መጀመሪያ ፡ ዋልባ ፡ ላይ ፡ ቀጥሎ ፡ ጕንደር ፡ አጠገብ ፡ ተዋጉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ራስ ፡ ይማም ፡ ድል ፡ አደረጓቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በመቱ ፡ ደግሞ ፡ ደጃች ፡ ኃይሉ ፡ ማርያም ፡ ሞተው ፡ ልጃቸው ፡ ወጣቱ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ስለ ፡ ተተኩ ፡ እንዳባታቸው ፡ ለራስ ፡ ይማም ፡ አልገዛም ፡ ብለው ፡ በተራቸው ፡ ለጦርነት ፡ ተሰለፉ ፤ ጦርነቱም ፡ ወገራ ፡ ላይ ፡ ተደረገ ። በዚያም ፡ ጦርነት ፡ አሁንም ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ወዳገራቸው ፡ ተመለሱ ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚዋጉት ፡ ያንዲት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዘር ፡ ከመሆናቸው ፡ በቀር ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ያላቸው ፡ የሥጋ ፣ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ በጣም ፡ የቀረበ ፡ ነው ። ደጃች ፡ ኃይሉ ፡ ማርያም ፡ ባለቤታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ኂሩት ፡ የራስ ፡ ጉግሳ ፡ ልጅ ፡ የራስ ፡ ይማም ፡ እኅት ፡ ናቸው ፤ ራስ ፡ ጉግሳም ፡ በዘመናቸው ፡ ልጃቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ኂሩትን ፡ ለደጃች ፡ ኃይሉ ፡ ማርያም ፡ አባት ፡ ለራስ ፡ ገብሬ ፡ መዳራቸው ፡ በዚህ ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ አንድነት ፡ ተመሥርቶ ፡ በስሜንና ፡ በበጌምድር ፡ ጸጥታና ፡ ሰላም ፡ እንዲገኝ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ኃይል ፡ አግዶት ፡ ጉልበት ፡ ተቀንሶበት ፡ ካልተቸገረ ፡ በቀር ፡ ዘውድንም ፣ ምስፍንናንም ፣ በጠቅላላው ፡ ገዥነትን ፡ ለሌላው ፡ መተው ፡ አይችልም ። ወንድም ፡ ለወንድሙ ፣ አባትም ፡ ለልጁ ፣ እማትም ፡ ለምራቱ ፡ ገዥነትን ፡ በፈቃዱ ፡ ለመልቀቅ ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ ለመገዛት ፡ ቅር ፡ ይለዋል ። ስለዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ነገሥታቱ ፡ አሁንም ፡ መሳፍንቱ ፡ እኅቶቻቸውን ፡ ልጆቻቸውን ፡ ከየባላባቱ ፡ ሲያጋቡ ፣ ሲያፋቱ ፣ ራሳቸውም ፡ ከሌላው ፡ ባላባት ፡ ልጅ ፡

ወይም ፡ እኅት ፡ መርጠው ፡ ሲያገቡ ፡ ይኖራሉ ። በምርጫውም ፡ ጊዜ ፡ የሚጠ
የቀውና ፡ የሚመረመረው ፡ የሴትዮዋ ፡ መልክና ፡ ጠባይ ፡ ሳይሆን ፡ ያባቷ ፤
ወይም ፡ የወንድሟ ፡ ኃይሉና ፡ ደጋፊነቱ ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ማለት ፡ ድን
ገት ፡ ጦርነት ፡ ከሌላው ፡ ጋራ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ተከታዩና ፡ የነገዱ ፡ የጭ
ፍራው ፡ የመሣሪያው ፡ ሁሉ ፡ ብዛትና ፡ ዐይነት ፡ እግምት ፡ ውስጥ ፡ ይገባል፡
ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንደዚህ ፡ ተመራርጦ ፡ ስሜኑ ፡ ከጐጃም ፤ ትግሬው ፡ ከወሎ ፤
ጐጃም ፡ ከዳሞት ፡ ባላባት ፡ ከባላባቱ ፤ መስፍን ፡ ከመስፍኑ ፡ ቢጋባም ፡ ቢዋ
ለድም ፡ ግዛትና ፡ ሥልጣን ፡ በመፈለግ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ መዋጋታቸው ፡ አይቀ
ርም ። እንዲያውም ፡ ከሌላው ፡ ይበልጥ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ መጣላት ፡ መዋጋት ፡
የሚታየው ፡ በነዚሁ ፡ በተጋቡትና ፡ በተዛመዱት ፡ መካከል ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የግዛት ፡ ምኞት ፡ የፍቅርና ፡ የዝምድና ፡ ጠላት ፡
መሆኑን ፡ ከተመለከትን ፡ በኋላ ፡ አሁን ፡ የዚህን ፡ ጕዳይ ፡ ትተን ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡
አሳባችን ፡ እንመለስ ።

## ምዕራፍ ፡ ፺ ።

## የራስ ፡ ማርዬ ፡ የምስፍንና ፡ ዘመን ።

ራስ ፡ ይማም ፡ በሺህ ፡ ፲፻፳ ዓ፡ ም፡ ሲሞቱ ፡ ወንድማቸው ፡ ራስ ፡ ማርዬ ፡
በጐንደር ፡ ምስፍንና ፡ ተከተሏቸው ። ባባታቸው ፡ በራስ ፡ ጉግሳ ፡ ጊዜ ፡ በትግሬ ፡
ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፤ በዳሞት ፡ ደጃች ፡ ዘውዴ ፡ አንገዛም ፡ እያሉ ፡ ያውኳ
ቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ወንድማቸውንም ፡ ራስ ፡ ይማምን ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡
እንደ ፡ ገለጽን ፡ የስሜኑ ፡ ደጃች ፡ ኀይለ ፡ ማርያም ፡ ተነሥተው ፡ እንደ ፡ ተፎከ
ከሯቸው ፡ አሁንም ፡ በራስ ፡ ማርዬ ፡ ጊዜ ፡ የአጋሜው ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፤
የጐጃሙ ፡ ደጃች ፡ ጐሹ ፡ አንገብርም ፡ አንገዛም ፡ ብለው ፡ እንቢ ፡ አሉ ።
ደጃች ፡ ጐሹ ፡ የታላቅ ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ የወይዘሮ ፡ ድንቅነሽ ፡
ልጅ ፡ የንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አያት ፡ መሆናቸውን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ጽፈ
ናል ። እርሳቸውም ፡ የባላምባራስ ፡ ዕንቈን ፡ ልጅ ፡ አግብተው ፡ ደጃች ፡ ተሰማን ፡
ወልደዋል ። ደጃች ፡ ተሰማ ፡ የንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አባት ፡ መሆናቸው ፡
ነው ፡ ከሌሎችም ፡ ሴቶች ፡ ብዙዎች ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ወልደዋል ።
ስማቸውም ፡ የወንዶቹ ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፤ ደጃች ፡ ኤሌምቱ ፤ ደጃች ፡ ንጉሤ ፤ ልጅ ፡
ይማም ፤ ልጅ ፡ ይልማ ፤ የሴቶቹ ፡ ወይዘሮ ፡ ድንቅነሽ ፤ ወይዘሮ ፡ ሁሉ ፡ አገርሽ ፤
ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ጊዮርጊስ ፤ ወይዘሮ ፡ መነጥር ፡ ይባላሉ ።

ይህ ፡ ከታላቅ ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ በልጃቸው ፡ በወይዘሮ ፡ ድንቅነሽ ፡ በኩል ፡
የመጣው ፡ ዘር ፡ ሲሆን ፡ ደግሞ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ የታላቅ ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ልጅ ፡
ራስ ፡ መርድ ፡ ደጃች ፡ ኃሉን ፡ መውለዳቸውን ፡ ባለፈው ፡ ገልጸናል ። ደጃች ፤
ኃሉ ፡ ደግሞ ፡ በጊዜያቸው ፡ ደጃች ፡ ይመርን ፤ ደጃች ፡ ተድላን ፤ ደጃች ፡ ተሰማን ፡

ልጅ ፡ አዳልን ፤ ወይዘሮ ፡ ምንትዋብን ፡ ይወልዳሉ ። ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ደጃች ፡
ተድላ ፡ ጓሉ ፡ የነደጃች ፡ ንጉሤ ፡ የነራስ ፡ ደስታ ፡ አባ ቀማው ፡ አበት ፡ መሆ
ናቸው ፡ ነው ። የነዚህም ፡ ዘር ፡ እንደዚያው ፡ እንደ ፡ ደጃች ፡ ጐሹ ፡ ዘር ፡
በጣም ፡ የበረከተ ፡ እስከዛሬም ፡ ድረስ ፡ ተወላጆቻቸው ፡ በብዙ ፡ የሚገኙ ፡ ስለ ፡
ሆነ ፡ የዘሩን ፡ ቈጠራ ፡ ትተን ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ታሪክ ፡ እንመለስ ።

እንግዴህ ፡ ደጃች ፡ ጐሹ ፡ ጐጃምን ፡ በሚገዙበት ፡ ጊዜ ፡ በበጌምድር ፡ ራስ ፡
ማርዬ ፡ የዋናውን ፡ መንግሥት ፡ እንደራሴነቱን ፡ ስለ ፡ ያዙ ፡ እንዲገብሩላቸው ፡
ለደጃች ፡ ጐሹ ፡ ላኩባቸው ፡ ደጃች ፡ ጐሹም ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ አልገብርም ፡
ብለው ፡ ላኩ ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የደጃች ፡ ጐሹ ፡ ልጅ ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ እሙሉ ፡
ሰውነት ፡ ደርሰው ፡ ራስ ፡ ማርዬን ፡ ለመውጋት ፡ ከባታቸው ፡ ጋራ ፡ ተባብረው ፡ ተሰ
ልፈው ፡ ነበር ።

ራስ ፡ ማርዬ ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ለማስገበር ፡
መጡ ። ከሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ የበጌምድር የወሎ ፡ የየጁ ፡ የራያ ፡ ጦር ፡
ሠራዊት ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ነበር ። የያዘውም ፡ መሣሪያ ፡ በብዛቱና ፡ በዓይነቱም ፡
ከጐጃሞቹ ፡ ይበልጥ ፡ ስለነበረ ፡ ደጃች ፡ ጐሹና ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡
ለመግጠም ፡ መድፈር ፡ አቃታቸው ። ስለዚህ ፡ ደጃች ፡ ጐሹ ፡ ጅብላ ፡ ተራራ ፤
ልጃቸው ፡ ደጃች ፡ ብሩም ፡ ሰማ ፡ አምባ ፡ ገብተው ፡ ተቀመጡ ። ራስ ፡ ማርዬም ፡
ወደ ፡ ተራራው ፡ ለመውጣት ፡ ተራራው ፡ ብርቱና ፡ የማይደፈር ፡ መሆኑን ፡ ተገን
ዘቡ ፤ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ወርደውም ፡ ይገጥሙኛል ፡ ብለው ፡ ቢጠብቁ ፡ እነዚያ ፡ ሳይ
መጡላቸው ፡ ቀሩ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እያሉ ፡ በጐጃም ፡
ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከቈዩ ፡ በኋላ ፡ የጐጃምን ፡ ግዛት ፡ ለለጋስ ፡ ቃሲም ፤ የዳሞትን ፡
ግዛት ፡ ለደጃች ፡ ማዕጠንቱ ፡ ሰጥተው ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡
ተመለሱ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደጃች ፡ ጐሹ ፡ ከጅብላ ፡ ተራራ ፡ ወርደው ፡ ልጃቸውን ፡
ደጃች ፡ ብሩን ፡ ሳይጨምሩ ፡ ደጃች ፡ ማዕጠንቱን ፡ ለመውጋቸ ፡ ይሰናዱ ፡ ዠመር ፤
በሚሰናዱበትም ፡ ጊዜ ።

ተጠናከር ፡ ጐጃም ፤ ተጠናከር ፡ ዳሞት ፡
እኛ ፡ አይተንም ፡ አናቅ ፡ ባረፉ ፡ነጋሪት
አሉ ። ይኸንንም፡ ደጃች ፡ ማዕጠንቱ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ።
በል ፡ አንዳችም ፤ በል ፡ አንዳችም ፤
እግዜር ፡ ከሰጠ፡ ሰው ፡ አይነሣም ፡

ብለው ፡ መለሱ ፡ ይባላል ።

ግጥሙን ፡ ከተመላለሱ ፡ በኋላ ፡ ደጃች ፡ ጐሹና ፡ ደጃች ፡ ማዕጠንቱ ፡
ቢሁኝ ፡ ሰበካ ፡ ሰበዝ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ውጊያውን ፡ ዠመሩ ። በውጊያውም ፡ ደጃች ፡
ጐሹ ፡ ተሸነፉና ፡ ተይዘው ፡ ቋሚ ፡ ጨርቅ ፡ ዋሻ ፡ ታሰሩ ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ የደጃች ፡
ጐሹ ፡ ልጅ ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ ይኸንኑ ፡ ሰምተው ፡ ጦር ፡ አስከትተው ፡ በግሥ
ጋሚ ፡ ወደ ፡ ጨርቅ ፡ ዋሻ ፡ መጥተው ፡ አባታቸውን ፡ በጦር ፡ ኀይል ፡ አስፈ

ትተው ፡ ከዚህም ፡ አልፈው ፡ ሰጐዲት ፡ ከሚባለው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ከደጃች ፡ ማዕጠንቱ ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ አሸነፉ ፡፡ ደጃች ፡ ማዕጠንቱም ፡ ከተሸነፉ ፡ በኋላ ፡ ከዳሞት ፡ ወደ ፡ ስሜን ፡ ሄደው ፡ ከደጃዝማች ፡ ውቤ ፡ ጋራ ፡ ተቀመጡ ፡፡ በጐጃም ፡ ላይ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ተሾሞ ፡ የነበረው ፡ ለጋስ ፡ ቃሲምም ፤ በዳሞት ፡ ተሾመው ፡ የነበሩት ፡ ደጃች ፡ ማዕጠንቱ ፡ ተሸንፈው ፡ ከሸሹ ፡ በኋላ ፡ የደጃች ፡ ጐሹና ፡ የብሩ ፡ ሰዎች ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ከበቡት ፡፡ ጦሩም ፡ በከበደው ፡ ጊዜ ፡ ላገሬ ፡ እብቃኝ ፡ ብሎ ፡ ለዛብች ፡ ኢየሱስ ፡ ስለት ፡ አድርጎ ፡ ሌሊቱን ፡ በግልቢያ ፡ ከጐጃም ፡ ተነሥቶ ፡ በበረንታ ፡ በኩል ፡ አድርጎ ፡ ወዳገሩ ፡ ተመለሰ ፡ ይባላል ፡፡

በጐጃም ፡ በኩል ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሲፈጸም ፡ በስሜን ፡ በኩል ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ለራስ ፡ ማርዬ ፡ አልገዛም ፡ ብለው ፡ በጠገባቸው ፡ ያሉትን ፡ ደጃች ፡ ማዕጠንቱን ፡ ይዘው ፡ ዕንጨት ፡ ካብ ፡ እሚባለው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ተዋግተው ፡ ነበር ፡፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ተሸንፈው ፡ ተመለሱ ፤ ደጃች ፡ ማዕጠንቱም ፡ የዚሁ ፡ ጦርነት ፡ ለት ፡ ሞቱ ፡፡ ቢሆንም ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ለራስ ፡ ማርዬ ፡ እገብራለሁ ፡ ብለው ፡ ሲስማሙ ፡ የአጋሜው ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ (ሱብአ ፡ ጋዲስ ፡) ብቻ ፡ እንቢ ፡ ብለው ፡ በመጨረሻም ፡ ራስ ፡ ማርዬን ፡ በልጃቸው ፡ እጅ ፡ እስከ ፡ ማስገደል ፡ ደረሱ ፡፡

## ምዕራፍ ፡ ፺፩ ፡፡

## የራስ ፡ ማርዬና ፡ የደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ (ሱብአ ፡ ጋዲስ ፡) ጦርነት ፡፡

ከዚህ ፡ ዘመን ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በአጋሜ ፡ ውስጥ ፡ በራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ጊዜ ፡ ሹም ፡ አጋሜ ፡ ወልዱ ፡ ተነሥተው ፡ ኀይለኛና ፡ አስፈሪ ፡ ሆነው ፡ ነበር ፡፡ ርሳቸውም ፡ በሸዋ ፡ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ያደርጉት ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ በያለበት ፡ ብዙ ፡ ቍባት ፡ አስቀምጠው ፡ እስከ ፡ ዓርባ ፡ የሚደርሱ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ነበሯቸው ፡ ይባላል ፡፡ ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ዋና ፡ ሆነው ፡ የተነሡት ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ናቸው ፡፡ ርሳቸውም ፡ በጦርነት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ባስተዳደር ፡ ጭምር ፡ ይበልጥ ፡ ይመሰገኑ ፡ ነበር ፡፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከአጋሜ ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ከሸዋ ፡ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ባስተዳደርና ፡ በሰላማዊ ፡ ሥራ ፡ ይመሰገኑ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፤ እንኳን ፡ ባገራችን ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ጽሑፍ ፡ ሁሉ ፡ ይገኛል ፡፡

ደጃች ፡ ሰባጋዲስም ፡ ከርሳቸው ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ነበሩት ፡ እንደ ፡ ራስ ፡ ሥዑል ፡ ሚካኤል ፡ ካንድ ፡ አውራጃ ፡ ከአጋሜ ፡ ተነሥተው ፡ ገዥግንነትንም ፡ አስተዳዳሪነትንም አጣምረው ፡ እያሳመሩ ፡ የመላው ፡ ትግሬና ፡ የሐማሴን ፡ የበላይ ፡ ገዥ ፡ ነበሩ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ከራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ጊዜ ፡ ዠምረው ፡ ሲገዙ ፡ በመጨረሻ ፡ ከራስ ፡ ማርዬ ፡ ተጣሉ ፡፡ በበጌምድር ፡ ዋናው ፡ የመንግሥቱ ፡ እንደ ራሴ ፡ ራስ ፡ ማርዬ ፡ ስለሆኑ ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ገብርልኝ ፡ ብለው ፡ ለደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ላኩ ፡፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስም ፡ አልገብርም ፡ ብለው ፡ በገሃድ ፡ እንቢታቸውን ፡ አስታወቁ ፡፡

ቀድሞ ፡ በራስ ፡ ጉግሳና ፡ በራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ጠብና ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ የስሜኑ ፡ ራስ ፡ ገብሬ ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ሆነው ፡ እንደ ፡ ጊዜውና ፡ ያገራቸው ፡ ያስተዳደር ፡ ዘዴ ፡ (ፖሊቲክ) ፡ እንደ ፡ ፈቀደላቸው ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ላንደኛው ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡ ለ፪ኛው ፡ ወገን ፡ ሲሆኑ ፡ እነዚያም ፡ የትግሬና ፡ ያማራ ፡ ገዥዎች ፡ ወደየ ራሳቸው ፡ ወገን ፡ ለመሳብ ፡ ይጥሩ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በመጨረሻም ፡ ራስ ፡ ገብሬ ፡ ከራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ባለፈው ፡ ተጽፏል ። እንደዚሁም ፡ በደጃች ፡ ማርዬና ፡ በደጃች ሰባጋዲስ ፡ ጊዜ ፡ የራስ ፡ ገብሬን ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ የደጃች ፡ ኃይለ ፡ ማርያምን ፡ ልጅ ፡ የስሜኑን ፡ ገዥ ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ አሁንም ፡ ወደየራሳቸው ፡ ለመሳብ ፡ ሁለቱ ፡ የሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ አስቀድሞ ፡ አባቶቻቸው ፡ ካደረጉት ፡ ሁኔታው ፡ መልኩን ፡ አለወጠም ።

ወይዘሮ ፡ ኂሩት ፡ የራስ ፡ ጉግሳ ፡ ልጅ ፡ የራስ ፡ ማርዬ ፡ እኅት ፡ ለደጃች ፡ ውቤ ፡ አባት ፡ ለደጃች ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ባለቤት ፡ ሲሆኑ ፤ ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ የደጃች ፡ ሰባጋዲስን ፡ ልጅ አግብተው ፡ አማች ፡ ሆነው ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ራስ ፡ ማርዬና ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ የተዋጉ ፡ እንደሆነ ፡ ባይሆን ፡ ያስታ ርቁ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ለማንኛውም ፡ አይረዱም ፡ እየተ ባለ ፡ ይወራ ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ከልጃቸው ፡ ከደጃች ፡ ሐጐስ ፡ ጋራ ሆነው ፡ ራስ ፡ ማርዬን ፡ ጦርነት ፡ ለመግጠም ፡ በተሰናዱ ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ ሳይታሰብ ፡ በድንገት ፡ ከራስ ፡ ማርዬ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ የሚስታቸውን ፡ አባት ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስን ፡ ለመውጋት ፡ ተሰለፉ ። ራስ ፡ ማርዬም ፡ እንዳሁኑ ፡ አያያዛችን ፡ ድንገት ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆነን ፡ ደጃች ፡ ሰባጋ ዲስን ፡ ድል ፡ ብናደርግ ፡ መላውን ፡ የትግሬን ፡ ግዛት ፡ እሰጥኻለሁ ፡ ብለው ፡ ለደ ጃች ፡ ውቤ ፡ ቃል ፡ ገቡላቸው ፡ ይባላል ። በሌላ ፡ ታሪክ ፡ ከዚያውም ፡ በኩልበ ፡ ጽሑፍ ፡ ደግሞ ፡ ጦርነቱን ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስና ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ገምረው ፡ ሳለ ፡ ራስ ፡ ማርዬ ፡ ለደጃች ፡ ውቤ ፡ እርዳታ ፡ ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ ደረሱ ፡ ሲል ፡ ይገኛል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ራስ ፡ ማርዬና ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ጦራቸውን ፡ ባንድነት ፡ ደምረው ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስን ፡ ለመውጋት ፡ ጉዞ ፡ ገሠገሡ ።

ደጃች ፡ ሰባጋዲስም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጦር ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡ መምጣቱን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከትግሬ ፡ ወደ ፡ ተከዚ ፡ አልፈው ፡ ማይ ፡ እስላማይ ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ መጥተው ፡ በሺህ ፡ ፲፰፻፳፬ ፡ ዓ፡ ም፡ በጥር ፡ ወር ፡ ተጋጠሙ ፡ ጦርነቱም ፡ በጋለበት ፡ ሰዓት ፡ የደጃች ፡ ሰባጋዲስን ፡ ጦር ፡ ከራስ ፡ ማርዬ ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ ፈረሰኛው ፡ በግልቢያ ፡ ሊጥሰው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ትግሬዎቹ ፡ ምቹ ፡ ሥፍራ ፡ ይዘው ፡ እየተታኰሱ ፡ በጠመንጃ ፡ ብርታት ፡ አገዱቸው ፡ ይባላል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ በኩል ፡ ያለ ፡ ጦር ፡ ስለ ፡ ላላ ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ተሸንፈው ፡ ተማረኩ ። የዚህን ፡ ወሬ ፡ ልጃቸው ፡ ደጃች ፡

ሐጐስ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ማርዬ ፡ ገሥግሠው ፡ ሄደው ፡ በ፪ ፡ አፍ ፡ ጠመንጃ ፡ ተኵሰው ፡ ራስ ፡ ማርዬን ፡ ገደሏቸው ። በዚያው ፡ ሰዓት ፡ ደግሞ ፡ የነራስ ፡ ማርዬ ፡ ወገኖች ፡ እንአዛዥ ፡ ውብሸት ፡ በጐራዴ ፡ ደብድበው ፡ ደጃች ፡ ሐጐስን ፡ ገደሏቸው ።

የዚህንም ፡ ወሬ ፡ አባታቸው ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ በእስር ፡ ስም ፡ እተቀመጡ በት ፡ ሆነው ፡ ሌሊቱ ፡ ሊነጋ ፡ ሲል ፡ ሰምተው ፡ «ሐጐስ ፡ ሞተን ፡ ሌሊቱስ ፡ ነጋን»?፡ ብለው ፡ መራራ ፡ ጸጸት ፡ ተናግረው ፡ ወዲያው ፡ የራስ ፡ ማርዬ ፡ ወገኖች ፡ ርሳቸ ውንም ፡ ገደሏቸውና ፡ የጦርነቱ ፡ ድል ፡ የደጃች ፡ ውቤና ፡ የራስ ፡ ማርዬ ፡ ወገኖች ፡ ሆነ።

ከያንዳንዱ ፡ ሽማግሌ ፡ ወይም ፡ መጽሐፍ ፡ የሚገኘው ፡ ታሪክ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አይጋጠምም ። የደጃች ፡ ሰባጋዲስንና ፡ የራስ ፡ ማርዬን ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ ግማሹ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጻፈው ፡ ዐይነት ፡ ሲተርከው ፡ ግማሹ ፡ ደግሞ ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ በራስ ፡ ማርዬ ፡ ከተማረኩ ፡ በኋላ ፡ ሐጐስ ፡ የራስ ፡ ማርዬ ፡ አሽከር ፡ መስለው ፡ ተጠ ግተው ፡ ራስ ፡ ማርዬን ፡ አዘንግተው ፡ ገደሏቸው ። ከገደሏቸውም ፡ በኋላ ፡ ሐጐስ ፡ በገዛ ፡ እጃቸው ፡ ቈስለው ፡ ከጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ በፈረስ ፡ አምልጠው ፡ ሄዱ ። ያሟሟ ታቸው ፡ ሁኔታ ፡ አልታወቀም ፡ የሚሉ ፡ አሉ ፡ የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሁሉም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ረኀርም ፡ ጊዜ ፡ ሲገኝ ፡ የሚጣራ ፡ ነው ።

የራስ ፡ ማርዬ ፡ ምስፍንና ፡ በጐንደር ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ ነው ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ፲፬ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ትግሬንና ፡ ሐማሴንን ፡ ገዝተዋል ። እንግዴህ ፡ ይህ ፡ ጦርነት ፡ በደጃች ፡ ውቤ ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ ተፈጸመ ። ርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ መሣሪያና ፡ ምርኰኞቻቸውን ፡ ይዘው ፡ በደስታ ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ተመለሱ ፤ ከዚ ያም ፡ ከስሜን ፡ አልፈው ፡ ትግሬንና ፡ ሐማሴንን ፡ ማስተዳደር ፡ ገሠመሩ ።

## ምዕራፍ ፡ ፺፪ ።

## የራስ ፡ ዶሪ ፡ የምስፍንና ፡ ዘመን ።

ራስ ፡ ማርዬ ፡ ተከዚ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ከደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ጋራ ፡ ሲዋጉ ፡ ወንድማቸው ፡ ራስ ፡ ዶሪ ፡ አብረው ፡ እየተዋጉ ፡ ይረዷቸው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ራስ ፡ ማርዬ ፡ በደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ልጅ ፡ በሐጐስ ፡ እጅ ፡ ተመተው ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ የተረፈውን ፡ ጦር ፡ ሰብስበው ፡ ራስ ፡ ዶሪ ፡ በዛኸ ፡ ውብሸት ፡ ርዳታ ፡ ጭምር ፡ ከጦርነቱ ፡ ሥፍራ ፡ ተመልሰው ፡ ጐንደር ፡ ከተማ ፡ ገብተው ፡ የከተማውን ፡ ጸጥታ ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ። ከጥቂት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ የበጌምድርን ፡ እንደራሴነት ፡ ለራሳቸው ፡ አስቀርተው ፡ የትግሬን ፡ ግዛት ፡ እንደ ፡ ወንድማቸው ፡ እንደ ፡ ራስ ፡ ማርዬ ፡ ቃል ፡ ለደጃች ፡ ውቤ ፡ ለቀቁላቸው ። ደጃች ፡ ውቤም ፡ በስሜን ፡ በትግሬ ፡ ላይ ፡ ተስፋፍ ተው ፡ ከዚያም ፡ አልፈው ፡ እስከ ፡ ምጥዋና ፡ ኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ ድረስ ፡ ግዛታ ቸውን ፡ አሰፉ ። ቢሆንም ፡ የደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ልጆች ፡ እነደጃች ፡ ካሳይ ፡ በየጊ ዜው ፡ እየተነሡ ፡ ማስቸገራቸው ፡ አልቀረም ።

ራስ ፡ ዶሪ ፡ እንደራሴነት ፡ መያዝ ፡ እንደ ፡ ዠመሩ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ዳሞትንና ፡ ጐጃ ምን ፡ ለማስገበር ፡ መጥተው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አመዳሚት ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ደጃች ፡ ጐሹና ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ ወግተው ፡ መለሷቸው ። ሲመለሱም ፡ ኢልማና ፡ ዴንሳን ፡ ዘርፈው ፡ ተመለሱ ፡ ይባላል ። በርሳቸውም ፡ ዘመን ፡ ለስሙ ፡ የነገሡት ፡ ዐፄ ፡ ሰሎሞን ፡ ይባላሉ ፤ ራስ ፡ ዶሪ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ብቻ ፡ በምስፍንና ፡ ገዝተው ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ በርሳቸው ፡ ምትክ ፡ ትንሹ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ተተኩ ።

## ምዕራፍ ፡ ፺፫ ።

## የእንግሊዝና ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥታት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ያደረጉት ፡ ግንኙነት ።

በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ስለ ፡ ዓለም ፡ ታሪክ ፡ አከፋፈል ፤ በምዕራፍ ፳ ፡ ስለ ፡ ፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፤ በምዕራፍ ፡ ፯ ፡ ስለ ፡ ዐረቦችና ፡ ስለ ፡ ቱርኮች ፡ አነሣሥ ፤ በምዕራፍ ፡ ፴፰ ፡ ስለ ፡ ኤስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ ገናናነት ፡ በምዕራፍ ፡ ፶፫ ፡ ስለ ፡ ዓለም ፡ ሁኔታና ፡ ስለ ፡ ፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ትልቅነት ፡ እስከ ፡ ሉዊ ፡ ፲፬ኛ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፯፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግድም ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ በጭር ፡ ባጭሩ ፡ በጠቀስንበት ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ በየጊዜው ፡ ያገ ናኛቸውን ፡ ምክንያት ፡ ሳንጠቅሰው ፡ አላለፍንም ።

አሁንም ፡ ከአድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፤ ወዲህ ፡ እስከ ፡ ትንሹ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ በዓለም ፡ የሆነውን ፡ ጠቅሰን ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ውስጥ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ የተደረገውን ፡ ግንኙነት ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ጣልቃ ፡ አግብተን ፡ እናስታውሳለን ።

በ፲፮ኛው ፡ በ፲፯ኛውና ፡ በ፲፰ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ውስጥ ፡ በኢትዮጵያ ፡ እነ ሠርፀ ፡ ድንግል ፤ እነሱስንዮስ ፤ እነፋሲል ፤ እነኢያሱ ፡ እነበካፋ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ያለ ፈው ፡ ታሪክ ፡ በገለጸልን ፡ ዐይነት ፡ በሚያስተዳድሩበት ፡ ጊዜ ፡ በኤውሮፓ ፡ ደግሞ ፡ የነፖርቱጋል ፡ የነኤስፓኝ ፡ ኀያልነት ፡ ወደ ፡ መቀዝቀዝ ፡ ሲሄድ ፡ የእንግሊዝ ፡ የፈ ረንሳዊ ፡ የቱርክ ፡ የነምሳ ፡ (አትሪሽ) ፡ የጀርመን ፡ የመስኮብ ፡ መንግሥታት ፡ ኀይል ፡ ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ እያደገ ፡ እየሰፋ ፡ ሄደ ። በጥንት ፡ ወራሪዎችም ፡ ተይዘው ፡ የነ በሩ ፡ አገሮች ፡ ነፃነታቸውን ፡ እያገኙ ፡ የመንግሥታት ፡ ቍጥር ፡ እየበረከተ ፡ ሄደ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ይመለከቱ ፡ የነበሩ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ህንድን ፡ ወይም ፡ ግብጽን ፡ የያዙ ፡ አገሮች ፡ ፖርቱጋል ፡ ቱርክ ፡ እንግሊዝና ፡ ፈረ ንሳዊ ፡ ሆላንድ ፡ . , . . . . . ናቸው ፡ ባለፈው ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ ቱርክ ፡ ግብጽን ፡ ስለ ፡ ያዘ ፡ ከደቡብ ፡ ወገን ፡ ግራኝን ፡ አስነሥቶ ፡ ክርስቲያኑን ፡ መንግ ሥት ፡ ለማስወረርና ፡ በዚያው ፡ በኩል ፡ ጥቅሙን ፡ ለማግኘት ፡ ፈለገ ፤ ፖርቱጋል ፡ ደግሞ ፡ ህንድን ፡ በሚገዛበት ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በረዳትነት ፡ ገብቶ ፡ የግራኝን ፡ ኀይል ፡ አጥፍቶ ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ክብሩንና ፡ ጥቅሙን ፡ ለማረጋገጥ ፡ አሰበ ።

ኤስፓኝም ፡ ፖርቱጋል ፡ በተለመው ፡ እግር ፡ ገብቶ ፡ ሚሲዮኖችም ፡ አገር ፡ መርማ ሪዎችም ፡ ልክ ፡ በዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ጊዜ ፡ ከሃይማኖት ፡ የተነሣ ፡ ያን ፡ ያህል ፡ ደም ፡ ፈሰሰ ።

ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ደግሞ ፡ የሆላንድ ፡ መንግሥት ፡ በቀዳማዊ ፡ ዮሐንስና ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ጊዜ ፡ በሺሕ ፡ ፮፻፺፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ላይ ፡ በህንድ ፡ አገረ ፡ ገዥው ፡ በኩል ፡ ደብዳቤና ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ (ትልቅ ፡ ደወል) ፡ ልክ ፡ ከቱርክ ፡ እየ ተፎካከረ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጠረፍ ፡ ለመግባት ፡ ምኞት ፡ ነበረው ። ነገር ፡ ግን ፡ ባ፲፰፡ ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ላይ ፡ ሁሉም ፡ በየምክንያቱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ማሰባቸው ሲቋረጥ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ለማድረግ ፡ አጥብቀው ፡ የተነሡት ፡ እንግሊዝና ፡ ፈረንሳዊ ፡ ሆነው ፡ ተገኙ ። ቤልጅክም ፡ ትንሽ ፡ ሞክሮ ፡ ነበር ፤ አላስፋፋውም ። ቱርክ ፡ ግን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጠረፍ ፡ በምጥዋ ፡ ወይም ፡ በአርኪቆ ፡ እንደ ፡ ተመሠረተ ፡ መኖሩን ፡ አንዘነጋም ።

ስለዚህ ፡ አሁን ፡ የሁሉንም ፡ ትተን ፡ ዋንኞቹ ፡ የእንግሊዝና ፡ የፈረንሳዊ ፡ መን ግሥታት ፡ ያደረጉትን ፡ ግንኙነት ፡ እንመልከት ።

የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፤ የኤስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ወደቀ ፡ ተነሥቶ ፡ ከፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ እየተፎካከረ ፡ አሜሪካንን ፡ ከናዳን ፡ ሲገዛ ፡ ከዚያ ፡ ደግሞ አሜሪካን ፡ በነዋሽንግቶን ፡ በነላፋዬት ፡ መሪነት ፡ ተዋግቶ ፡ እንግሊዞችን ፡ ከስወጣ ፡ በኋላ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በህንድ ፡ ግዛት ፡ ላይ ፡ ተመሠረተ ፤ ከጦር ፡ ሠራ ዊቱ ፡ ይልቅ ፡ የባሕር ፡ ኀይሉም ፡ እያደር ፡ በረታ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ በዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጊዜ ፡ ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ ወደ ኢትዮጵያ ፡ ገብቶ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ስለ ፡ ዐባይ ፡ ወንዝ ፡ ሁኔታ ፡ ባምስት ፡ ቦሊም ፡ የተከፈለ ፡ ትልቅ ፡ መጽሐፍ ፡ በእንግሊዝ ፡ ቋንቋ ፡ በጻፈ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጆች ፡ (አገር ፡ መርማሪዎችና ፡ ሚሲዮኖች) ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፤ በጣም ፡ ማሰብ ፡ ጀመሩ ።

ቀጥሎ ፡ ደግሞ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ትግሬን ፡ ሲገዙ ፡ (በሺሕ ፡ ፯፻፺፯ ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፰፻፲፮) ፡ ቢስኮንት ፡ ገርሻ ፡ ባለንቲያ ፡ የሚባለው ፡ የጦር ፡ መር ከብ ፡ ሹም ፡ ከራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ጋራ ፡ ደብዳቤ ፡ መላላክ ፡ ጀመረ ። ከዚያም ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ የመናገሻ ፡ ከተማ ፡ ጐንደር ፡ ሔደው ፡ ለንጉሡ ፡ ለዕጓለ ፡ ጽዮን ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ አቅርበው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ወዳጅነት ፡ ለመመሥረት ፡ ሐንሪ ፡ ሳልት ፡ (Henry Salt) ፡ ናትናኤል ፡ ፒርስ ፡ (Nathaniel Pearce) ና ፡ ኮፊ ፡ (Coffin) የሚባሉት ፡ ተልከው ፡ ከምጥዋ ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ መጡ ። ከዚያም ፡ በእን ደርታ ፡ በተለይ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ወደሚገኙበት ፡ ወደ ፡ እንጣሎ ፡ መጥ ተው ፡ ተገናኙ ። ከእንጣሎም ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ጉዟቸውን ፡ ቀጥለው ፡ የያዙትን ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ለነበሩት ፡ ንጉሥ ፡ ለዐፄ ፡ ዕጓለ ፡ ጽዮን ፡ ለማስረ ከብ ፡ ምኞት ፡ ነበራቸው ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ እንባቢ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ተመልሶ ፡ እንደሚያስታውሰው ፡ በዚህ ዘመን ፡ የነገሥታቱ ፡ ኀይል ፡ ወድቆ ፡ መሳፍንት ፡ በያለበት ፡ አይለው ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚዋጉበት ፡ ጊዜ ፡ ስለሆነ ፡ ዐፄ ፡ ዕጓለ ፡ ጽዮንም ፡ እንደ ፡ ወይዘሮ ፡ በግንብ ፡ ውስጥ ፡ ዐፄ ፡ እየተባሉ ፡ መቀመጥ ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ነበረባቸው ፡ በዚህም ፡ ዘመን ፡ ዋናው ፡ እንደራሴ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ የትግሬውም ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ለጐንደሩ ፡ እንደራሴ ፡ ለራስ ፡ ጉግሳ ፡ አልገዛም ፡ ብለው ፡ ለብቻቸው ፡ ሆነው ፡ የሚከራከሩበት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ሳልት ፡ ከጓደኞቹ ፡ ጋራ ፡ የያዘውን ፡ ገጸ ፡ በረከትና ፡ መጣሪያ ፡ ለራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ማስረከብ ፡ ግድ ፡ ሆነበት ፡ መጣሪያውንና ፡ ገጸ ፡ በረከቱንም ፡ ካስረከበ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱን ፡ ጓደኞቹን ፡ ለራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ትቶ ፡ ወዳገሩ ፡ ተመለሰ ። እንደ ፡ ተመለሰም ፡ «በሺሕ ፡ ፲፰፻፱ና ፡ በሺሕ ፡ ፲፰፻፲ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተደረገ ፡ ጉዞና ፡ በገር ፡ ውስጥም ፡ የመዘዋወር ፡ ሥራ፡- A Voyage to Abissinia and travel into the interior of that country executed in the years 1809 and 1810» የሚል ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፎ ፡ በሺሕ ፡ ፲፰፻፲፬ ፡ ዓ፡ ም ፡ አወጣ ።

ከራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴም ፡ ጋራ ፡ የቀሩት ፡ ፒርስና ፡ ከፊ ፡ በእንደርታ ለራስ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ አማካሪና ፡ ባለሟል ፡ ሆነው ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ ተቀመጡ ። ከዚያም ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ሞተው ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ በተነሡበት ፡ ጊዜ ፡ መከከል ፡ ብዙ ፡ ሚሲዮናውያንና ፡ አገር ፡ ተመልካቾች ፡ እየመጡ ፡ በደስታ ፡ ተቀመጡ ። ፒርስና ፡ ከፊም ፡ ካዲሱ ፡ ገዥ ፡ ከደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ጋራ ፡ ወዳጅችና ፡ አማካሪዎች ፡ ሆኑ ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስም ፡ በነርሱ ፡ ሥራና ፡ ምክር ፡ ደስ ፡ ስላላቸው ፡ በእንቲጮ ፡ ውስጥ ፡ የሚቀመጡበት ፡ ሰፊና ፡ የሚያምር ፡ ጕልት ፡ ሰጧቸው ፡ ይባላል ። ከዚያም ፡ ከፊ ፡ ከህንድ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ጋራ ፡ ተላልኮ ፡ ፳፬ ፡ ጠመንዣ ፡ ለደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ አስመጣላቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ጠመንዣው ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ከራስ ፡ ማርዬና ፡ ከደጃች ፡ ውቤ ፡ ተዋግተው ፡ ስለሞቱ ፡ በእጃቸው ፡ ሊገባላቸው ፡ አልቻለም ። ምናልባት ፡ ይህ ፡ አዳዲስ ፡ ፳፬ ፡ ጠመንዣ ፡ ከደረሰላቸው ፡ በኋላ ፡ ተዋግተው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ በመማረክና ፡ በመሞት ፡ ፈንታ ፡ ድል ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ጠመንዣው ፡ ምጥዋ ፡ ስለደረሰ ፡ ከደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ በኋላ ፡ የትግሬ ፡ ገዥ ፡ የሆኑት ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ለኔ ፡ ስጠኝ ፡ ብለው ፡ አባበሉት ። እርሱ ፡ ግን ፡ አልሰጥም ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዳሞ ፡ ሸሸ ፡ ይባላል ። በዚያም ፡ የደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ልጅ ፡ እስኪነሣ ፡ ድረስ ፡ አልተመለሰም ።

ቢሆንም ፡ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ በደጃች ፡ ወልደ ፡ ሥላሴና ፡ በደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ከዚያም ፡ በደጃች ፡ ውቤ ፡ ጊዜ ፡ በየጊዜው ፡ ጎባት ፡ (Gobat) ኢዘንበርግ ፡ (Isenberg) ዎልፍ ፡ (Walf) ብሉናር ፡ (Blunard) ክራፍ ፡ (Krapf) የሚ

በሉ ፡ ሚሲዮናውያን ፡ እንደዚሁም ፡ ሩፔል ፡ (Ruppel) ቤክ ፡ (Beck) ቤል ፡ (Bell) (1) ብሎውደን ፡ (Blawden) (2) ማንፌዩልድ ፡ (Manfield) ፓርኪንስ ፡ (Parkyns) የሚባሉ ፡ አገር ፡ መርማሪዎች ፡ እየመጡ ፡ በያገሩ ፡ እየተበተኑ ፡ የወንጌልም ፡ ሥራ ፡ ያገር ፡ ምርመራም ፡ የጥቅምም ፡ የፖለቲካም ፡ ጉዳያቸውን ፡ ከይሮና ፡ ምጥዋ ፡ ከሚቀመጡት ፡ ከዋና ፡ ቆንሲሎቻቸው ፡ እየተላላኩ ፡ ያከናውኑ ፡ ዠመር ። የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በስሜን ፡ በኩል ፡ ገብቶ ፡ ይኸን ፡ ሲያደርግ ፡ እንደዚሁም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በዝርዝር ፡ የምናገኘውን ፡ ሜዠር ፡ ሐሪስን ፡ ሸዋ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ልኮ ፡ የንግድና ፡ የወዳጅነት ፡ ውል ፡ ተዋዋለ ።

የእንግሊዝን ፡ መንግሥት ፡ በቅኝ ፡ አገርም ፡ በሀብትም ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ተወዳድሮታል ። ፈረንሳዊና ፡ እንግሊዝ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት፡ በፊት ፡ ከሮማውያን ፡ መነሣት ፡ በፊት ፡ ሁለቱም ፡ ያልሠለጠኑ ፡ መንግሥታት ፡ ሆነው ፡ በያገራቸው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ሮማውያን ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡ ዩልዮስ ፡ ቄሣር፡ ሁለቱንም ፡ ስላስገበራቸው ፡ በሮማውያን ፡ ግዛት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ሦስተኛው ፡ መቶ ፡ ዓ፡ ም፡ ድረስ ፡ ይቸገሩ ፡ ነበር ። የሮማን ፡ የምዕራብ ፡ ግዛት ፡ ከሰሜን ፡ የወጡት ፡ ድብልቅ ፡ የጀርመን ፡ ዘሮች ፡ (ከጣሉት ፡ በኋላ ፡ ፍራንኮች) ፡ በ፱ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ፡ ም፡ ላይ ፡ ሻርለማኝ ፡ የምዕራብ ፡ ኤውሮፓ ፡ በተለይ የፈረንሳዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እንግሊዞችን ፡ ሳያስጨንቅ ፡ አልቀረም ። ነገር ፡ ግን ፡ ርሱና ፡ ተከታዮቹ ፡ አልፈው ፡ እንግሊዞች ፡ ደግሞ ፡ ከ፲፫ኛው እስከ ፡ ፲፭ኛው ፡ ዓ፡ ም፡ ድረስ ፡ እየሉና ፡ የፈረንሳዊን ፡ ዘውድ ፡ ከመቀማትና ፡ ከማጥቃት ፡ ደረሱ ። በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ባ፲፯ኛውና ፡ ባ፲፰ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ፡ ፈረንሳዊና ፡ እንግሊዝ ፡ ይነስ ፡ ይብዛ ፡ ኀይላቸው ፡ ተመዛዝኖና ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ መዋጋትን ፡ ችላ ፡ ብለው ፡ ሌላውን ፡ አገር ፡ በመውረርና ፡ ግዛት ፡ በማስፋፋት ፡ ሀብት ፡ በመሰብሰብ ፡ እየተሻሙ ፡ ተፎካካሪ ፡ ሆነው ፡ እስከዚህ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ፲፱ነኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ይቀጥሉ ፡ ዠመር ።

በዚህ ፡ መካከል ፡ በአሜሪካና ፡ በአፍሪካ ፡ በቅኝ ፡ ግዛት ፡ እየተጣሉም ፡ እየታረቁም ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ።

የውስጥ ፡ አስተዳደርንም ፡ በማሻሻል ፡ ዕውቀትንም ፡ በማስፋፋት ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ እየሆኑ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ እየተተካከሉ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ እየቀደመው ፡ ይራመዱ ዠመር ።

የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ አስቀድሞ ፡ ገበሬው ፡ በግብር ፤ በዓሥራት ፡ በርቦ ፤ በጉልበት ፡ ሥራ ፤ ነጋዴው ፡ በቀረጥ ፤ አማካሪውና ፡ የሕዝብ ፡ ወኪሉ ፡ ባመካከሩ ፤ ጸሐፊው ፡ በጽሕፈቱ ፤ ሊቁ ፡ ባገላለጡ ፡ ጭቈና ፡ ነበረበት ። በኋላ ፡ ግን ፡ የማተሚያ ፡ መኪና ፤ የመጻፊያ ፡ ወረቀት ፡ ከተገኘ ፡ ወዲህ ፡ ማናቸውም ፡ ዕውቀት ፡ ስለ ፡ ተራ

(1) ያዒ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ሆኖ ፡ ከጋረድ ፡ የተዋጉ ፡ ጊዜ ፡ የሞተው ።
(2) ባዒ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጊዜ ፡ ቆንሲል ፡ ሆኖ ፡ ሲኖር ፡ በኋላ ፡ ሽፍቶች ፡ የገደሉት ።

ባና ፡ የሰው ፡ አእምሮ ፡ ወደ ፡ መብሰል ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ በሺ.ሕ ፡ ፲፮፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ላይ ፡ በክሮምዌል ፡ መሪነት ፡ የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ ኅብር ፡ አንሥቶ ፡ አስተዳደርን ፡ አሻሽሎ ፡ የዲሞክራሲ ፡ አገዛዝ ፡ እንዲቆም ፡ አደረገ ። በዚሁ ፡ ይዞታ ፤ ደግሞ ፡ ፈረንሳዮች ፡ በሺ.ሕ ፡ ፲፯፻፹፱ ፡ እስከ ፡ እንደ ፡ ኤው ፡ ቀ ፡ ሺ.ሕ ፡ ፲፯፻፺፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ላይ ፡ ኅብር ፡ አንሥተው ፡ የሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ አቆሙ ፤ ይኸንንም ፡ የቆመውን ፡ የሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ናፖሊዎን ፡ ኸሮ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተብሎ ፡ መካከልና ፡ ደቡብ ፡ አውሮፓን ፡ ወረረ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ጋራ ፡ ግን ፡ ፈረንሳዊ ፡ በመሬት ፡ እንግሊዝ ፡ በባሕር ፡ እየተፎካከሩ ፡ ከመኖር ፡ በቀር ፡ አንደኛው ፡ ሁለተኛውን ፡ ሊደመስሰው ፡ አልቻለም ።

እንግዴህ ፡ ናፖሊዎን ፡ በዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡ በሺ.ሕ ፡ ፲፰፻፬ ፡ እስከ ፡ ሺ.ሕ ፡ ፲፰፻፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ በኛ ፡ የነገሥታቱ ፡ ሥልጣን ፡ ወድቆ ፡ እንደራሴዎቹ ፡ እነራስ ፡ ጉግሣ ፡ በበጌምድር ፡ በትግሬም ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ በፊት ፤ ቀጥሎ ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፤ በሸዋ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ የነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፤ በጐንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ለስሙ ፡ ዘውድ ፡ ደፍተው ፡ የነገሡት ፡ ግን ፡ ዐፄ ፡ ዕጓለ ፡ ጽዮን ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ፈረንሳዊ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ያደረግችውን ፡ ግንኙነት ፡ እንመልከት ።

※ ※ ※

እንግሊዝና ፡ ፈረንሣዊ ፡ በአሜሪካና ፡ በእስያ ፡ ግዛት ፡ አስቀድሞ ፡ ግለኛ ፡ ሰው ፡ እየላኩ ፡ ከነርሱ ፡ በተገኘው ፡ የማስታወሻ ፡ ጽሑፍ ፡ እየተመሩ ፡ ግዛትን ፡ እየተፎካከሩ ፡ እንደሚይዙ ፡ እንደዚሁም ፡ በፍሪካ ፡ በግብጽ ፡ ግዛት ፡ መሻማታቸው ፡ አልቀረም ። ግብጽ ፡ ግን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የቱርክ ፡ ተገዥ ፡ ስለነበረች ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ ለጊዜው ፡ ምንም ፡ ማድረግ ፡ አልተቻለም ። እንግሊዝ ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡ ተገለጸው ፡ በትግሬ ፡ በኩል ፡ ሰዎቹን ፡ እየላከ ፡ እጁን ፡ ሲያገባ ፡ በሉዊ ፡ ፊሊፕ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ በናፖሊዎን ፡ ፫ኛ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የሚመራው ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አልተመለከተም ፡ ስለዚህ ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ለፌብር ፡ (Lete bvre) ፤ ድሪዮ ፡ (Drillon) ፌሬ (Ferret) ፡ ጋሊኒዮ ፡ (Galinier) ፡ ኮምብ ፡ (Combes) ታሚዚዬ ፤ (Tamisier) ፡ አንቷን ፡ዳባዲ ፡ (Antoine-d'Abbadie) ፡ አርኖ ፡ ዳባዲ ፤ (Arnauld-d'Abbadie) ፤ የሚባሉት ፡ የፈረንሣዊ ፡ ዜጎች ፡ መጥተው ፡ በትግሬ ፡ በበጌምድር ፡ በጐጃም ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ግማሾቹ ፡ የንግድና ፡ የወዳጅነት ፡ የጥቅም ፡ ግንኙነት ፡ የሚደረግበትን ፡ ዘዴ ፡ ያጠኑ ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከሚገኙት ፡ ከጐጃሙ ፡ ከደጃች ፡ ጐሹ ፡ ከበጌምድሩ ፡ ከራስ ፡ ዐሊ ፡ (ትንሹ) ፡ ከስሜኑና ፡ ከትግሬው ፡ ገዥ ፡ ከደጃች ፡ ውቤ ፡ ጋራ ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ እያደረጉ ፡ አንዳንድ ፡ ውል ፡ ማድረግ ፡ ጀመሩ ። ወደ ፡ ሸዋም ፡ ሮሼ ፡ ደሪኩር ፡ (Roetd'cheHicourtr) ፡ የሚባለው ፡ መጥቶ ፡ ከንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ጋራ ፡ የወዳጅነት ፡ ውል ፡ ተዋዋለ ። ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ በቀጥታ ፡ በፖለቲክና ፡ በሥራ ፡ የሚገናኘው ፡ ወገን ፡ ይኸን ፡

የመሰለውን ፡ የውል ፡ ነገር ፡ ሲሠራ ፡ ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ወንድማማቾቹ ፡ አንቷንና፡ አርኖ ፡ ዳባዲ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የወታደርነትና ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ባህል ፡ ደኅና ፡ አድር ገው ፡ የመመርመር ፡ ሥራቸውን ፡ ያከናውኑ ፡ ነበር ።

አንቷን ፡ ዳባዲ ፡ መዠመሪያ ፡ ከመጣ ፡ ወዲህ ፡ አገሪቱን ፡ አይቶ ፡ ወደ ፡ ፈረን ሣዊ ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ ከዚያም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መሣሪያና ፡ ገንዘብ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተመልሶ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪካዊ ፡ የሆነውን ፡ የላሊበላን ፡ (ላስታ፡) ሕንፃ፡ በደንብ ፡ መረመረ ፡ ከላስታ ፡ ወደ ፡ ጣና ፡ ባሕር ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ አድባራትና ፡ ገዳማት ፡ እየተዘዋወረ ፡ የቤተ ፡ ክህነታችንን ፡ ሥርዓት ፤ የዜማና ፡ የቅ ኔያችንን ፤ የታሪክና ፡ የመንፈሳዊ ፤ ያስማትና ፡ የጥንቈላ ፡ ጽሑፋችንን ፡ ሳይቀር ፡ በደንብ ፡ እያጠና ፡ መረመረው ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ደብተራ፡ ለብሶ ፡ ባማርኛ ፡ እየተናገረ ፡ ውሎው፡ ከመነኰሳትና ፡ ከደብተሮች ፡ ጋራ ፡ ነበር ፤ ይባ ላል ። ከጐጃም፡ አልፎ ፡ ጉዱሩን ፡ ኖኖን ፡ እናሪያን ፤ ከፋን ፡ ሁሉ ፡ ጐበኘ ።

ከዚያ ፡ ተመልሶ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በግዥና ፡ በስጦታ ፡ ያጠራቀማቸውን ፡ የብራና፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ወስዶ ፡ ለፓሪስ ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ አበረከታ ቸው ። እሱም ፡ የወሰዳቸው ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ መጻሕፍት ፡ የፓሪስን ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ ጠቅመውታል ። ብዙ ፡ ጸሐፊዎችም ፡ ወደዚያው ፡ እየሄዱ ፡ በመመልከት ፡ ተጠቅመ ዋል ። ፕሮፌሰር ፡ ኢኖሲዮ ፡ ጉይዲ ፡ የዮሐንስንና ፡ የኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድን ፡ የበካፋን ፡ ታሪክ ፡ በግዕዝ ፡ ያሳተሙት ፡ አንቷን ፡ ዳባዲ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወስዶ ፡ ፓሪስ፡ ካስቀመጠው ፡ አግኝተው ፡ ይመስላል ። እርሱም ፡ ባየውና ፡ በተረዳው ፡ መጠን ፤ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ጽፏል ።

ወንድሙ ፡ አርኖ ፡ ዳባዲ ፡ ደግሞ ፡ ዝንባሌው ፡ ወደ ፡ ወታደርነት ፡ ስለ ፡ ነበረ፡ የኢትዮጵያ ፡ የወታደራዊ ፡ ልብስ ፡ እየለበሰ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የወታደርነትን ፤ የጦር ነትን ፡ የቤተ ፡ መንግሥትን ፡ ሥርዓት ፡ ጐጃም ፡ ከደጃች ፡ ጐሹ ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ አጠና፡ ይባላል ። እነዚህም ፡ በግላቸው ፡ በኩል ፡ ሲሠሩ ፡ እላይ ፡ ስማቸውን ፡ የጠራነው ፡ ፈረንሣዮች ፡ ከተከፋፈሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዥዎች ፡ ሲወዳጁ ፡ ሲዋዋሉ ፡ ቈይ ተው ፡ በመጨረሻ ፡ የፈረንሣዊ ፡ መንግሥት ፡ በዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጊዜ ፡ ለዠን ፡ (Legean) ፡ የሚባለውን ፡ እንደ ፡ ቆንሲል ፡ አድርጎ ፡ ላከው ። ሚሲዮኖቹ ፡ መያዝ ፡ ሲጀምሩ ፤ ለዠንም ፡ አምልጦ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ በናፖሊዮን ፡ ፫ኛ ፡ ዘመነ ፡ መንግ ሥት ፡ ከደጃች ፡ ውቤ ፡ ተከታይ ፡ ከደጃች ፡ ንጉሤ ፡ ጋራ ፡ መላላክና ፡ መዋዋል ፡ ዠምረው ፡ ነበር ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ አልተቃናም ። ይኸንንም ፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ የምናገኘው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አሁን የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ትተን ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ታሪክ ፡ እንመለስና ፡ የራስ ፡ ዐሊን ፡ እንደ ራሴነት ፡ እንቀጥል ።

## የትንሹ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ የምስፍንና ፡ ዘመን ።

### ምዕራፍ ፡ ፺፬ ።

ደጃች ፡ ጐሹና ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ ከራስ ፡ ዐሊ ፡ ሹማምንት ፡ ጋራ ፡ ያደረጉት ፡ ጦርነት ፡ ፤—የደጃች ፡ ብሩና ፡ የደጃች ፡ ጐሹ ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ውጊያ ፤—የራስ ፡ ዐሊ ፡ ያስተዳደር ፡ ዘዴ ።

ትንሹ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፤ የትልቁ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ወንድም ፤ የደጃች ፡ አሉላ፡ ልጅ ፡ ናቸው ። እናታቸው ፡ ከወሎ ፡ ይማሞች ፡ የሚወለዱት ፡ ወይዘሮ ፡ መነን ፡ ይባላሉ ። ራስ ፡ ዐሊ ፡ ከራስ ፡ ዶሪ ፡ በኋላ ፡ እንደራሴነትን ፡ በያዙ ፡ ጊዜ ፡ ዐፄ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስን ፡ ከምጽርሐ ፡ ማርያም ፡ አስመጥተው ፡ አነገሡዋቸው ። ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ዐፄ ፡ ሣህሉን ፡ (ሣህለ ፡ ድንግልን) ፡ ከሣህሉ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ፫ኛ ፡ የተባሉትን ፡ አንግሠው ፡ አስቀመጡ ። እናታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ መነንም ፡ እኺህኑ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስን ፡ አግብተው ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ተባሉ ።

የእናታቸው ፡ የእቴጌ ፡ መነን ፤ ያባታቸው ፡ የደጃች ፡ አሉላ ፡ ደንበኛ ፡ መቀመጫ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ስለነበረ ፡ ራስ ፡ ዐሊም ፡ የልጅነታቸውን ፡ ዘመን ፡ ያሳለፉት ፡ በዚሁ ፡ አቅራቢያ ፡ ጉና ፡ ስማራ ፡ በሚባለው ፤ ሥፍራ ፡ ነው ፡ ይባላል ። እንደራሴነትንም ፡ ከያዙ ፡ በኋላ ፡ ከጐንደር ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ እየሄዱ ፡ ይቀመጡ ፡ ስለ ፡ ነበረ በርሳቸው ፡ ዘመን ፡ የደብረ ፡ ታቦር ፡ ከተማ ፡ እየደመቀና ፡ እየታወቀ ፡ ሔደ ።

እንግዴህ ፡ የሴሩ ፡ ኀንጐል ፡ ዘር ፡ በጐንደር ፡ እንደራሴ ፡ በሆነ ፡ ቍጥር ፡ እርሱም ፡ የመረጠውን ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ዐፄ ፡ እያሰኘ ፡ በነገሠ ፡ ቍጥር ፡ አንገዛም ፡ የሚለው ፡ የእንቢታና ፡ የጦርነት ፡ ድምፅ ፡ ሁል ፡ ጊዜ የሚሰማው ፡ ከስሜንና ፡ ከትግሬ ፡ ከዳሞትና ፡ ከጐጃም ፡ በኩል ፡ ነው ። ወሎና ፡ የጁ ፡ ቤተኛ ፡ በመሆኑ ፡ ለሴሩ ፡ ኀንጐል ፡ ዘር ፡ ረዳትና ፡ ተከታይ ፡ ነው ። ሸዋ ፡ ደግሞ ፡ ገና ፡ አስቀድሞ ፡ በመነጠሉ ፡ «ግባ ፡ ገብር» ፡ የሚለው ፡ ጠፍቶ ፡ ርሱም ፡ ጐንደር ፡ ሂጄ ፡ ተዋግቼ ፡ ልግዛ ፡ ሳይል ፡ ከጭቅጭቅ ፤ ራሱን ፡ አድኖ ፡ ከዙሪያው ፡ ጋላ ፡ ጋራ ፡ ብቻ ፡ እየተዋጋና ፡ አገር ፡ እያቀና ፡ ተቀምጧል ።

ስለዚህ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ እንደራሴነትን ፡ እንደያዙ ፡ ለነዚሁ ፡ ለተከራካሪዎች ፡ ወገኖች ፡ ለደጃች ፡ ውቤም ፡ ለደጃች ፡ ጐሹም ፡ ለልጃቸው ፡ ለደጃች ፡ ብሩም ፡ ገብሩ ፡ እያሉ ፡ ላኩ ። እነዚህም ፡ እንደተለመደ ፡ እንቢታቸውን ፡ አስታወቁ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ለደጃች ፡ ጐሹ ፡ ዳሞት ፡ ለደጃች ፡ ብሩ ፡ ጐጃም ፡ እንዲገቡ ፡ ልከው ፡ እንቢ ፡ ካሏቸው ፡ በኋላ ፡ ደጃች ፡

ሥዩም ፡ በቃኸኝን ፡ ከበጌምድር ፤ ደጃዝማች ፡ አዶዬ ፡ ባቡንና ፡ ደጃዝማች ፡ መሸሻ ፡ ባቡን ፡ ከየጁ ፡ ጠርተው ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ አድርገው ፡ ላኳቸው ፡ የሹም፡ ሽረቱም ፡ ድልድል ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ለደጃዝማች ፡ ሥዩም ፡ በቃኸኝ ፡ ጐጃምን ።
ለደጃዝማች ፡ መሸሻ ፡ ባቡ ፡ ዳሞትን ፡
ለደጃዝማች ፡ አዶዬ ፡ ባቡ ፡ አገው ፡ ምድርን ፡ ተሰጠ ።

እነዚህም ፡ ከበጌምድርና ፡ ከየጁ ፡ ያስከተሉትን ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ በደጋ ፡ ዳሞት ፡ በኩል ፡ መጡ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አባትዮው ፡ ደጃች ፡ ጐሹ ፡ ዳሞትን ፤ ልጅዮው ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ ጐጃምን ፡ ይገዙ ፡ ነበርና ፡ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ደጃዝማቾች ፡ በገዛ ፡ አገራቸው ፡ ተሾመው ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ እነሱም ፡ በበኩላቸው ፡ ጦር ፡ አከማችተው ፡ በደረቤ ፡ ሜዳ ፡ ስኩት ፡ በሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ለውጊያ ፡ ይጠባበቋቸው ፡ ነበር ። በኋላም ፡ እዚሁ ፡ እተባለው ፡ ሥፍራ ፡ ሁለቱ ወገኖች ፡ ተገናኝተው ፡ ውጊያውን ፡ ገጠሙ ፤ በውጊያውም ፡ ጊዜ ፤ እንግዳና ፡ ባላገር ፡ ምንም ፡ ዠግንነቱ ፡ አንድ ፡ ቢሆን ፡ እኩል ፡ አይዋጋምና ፡ ባላገሮቹ ፡ ደጃች ፡ ጐሹና ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ አዲስ ፡ መጪዎቹን ፡ እነደጃች ፡ ሥዩም ፡ በቃኸኝን ፡ አሸነፏቸው ። በዚህ ፡ ጦርነት ፡ ምንም ፡ አገሩንና ፡ መውጫ ፡ መግቢያውን ፡ ባያውቁት ፡ ደጃች ፡ ሥዩም ፡ በቃኸኝ ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ያሳዩት ፡ የዠግንነት ፡ ሥራ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ጓደኞቻቸው ፡ እነደጃች ፡ መሸሻ ፡ ባቡ ፡ መገመሪያ ፡ ተዋግተው ፡ በኋላም ፡ መሸነፋቸውን ፡ አውቀው ፡ ሲሸሹ ፡ ደጃች ፡ ሥዩም ፡ ለጠላቴ ፡ ዠርባዬን ፡ አላሳይም ፡ ብለው ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ተዋግተው ፡ እጦርነቱ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ በዠግንነት ፡ ወድቀው ፡ ሞቱ ። ዠግንነታቸውን ፡ እንኳን ፡ ወገኖቻቸው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በጠላትነት ፡ የሚመለከቷቸው ፡ ጐጃሞቹ ፡ ሳይቀሩ ፡ እያደነቁላቸው ፡ ዠግንነታቸውን ፡ የሚገልጥ ፡ ግጥም ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ተገጠመ ፡ ይባላል ።

መሸሻ ፡ ባቡ ፤ አዶዬ ፡ ባቡ ፡ ያስነሡበቱ ፡
ሥዩም ፡ በቃኸኝ ፡ የሞቱበቱ ፡
ሣር ፡ አልበቀለም ፡ ስኩት ፡ መሬቱ ።
የውሃም ፡ አይደለ ፡ የሥዩም ፡ ደም ፡ ነው ፡
ስኩት ፡ መሬቱ ፡ ሣሩ ፡ ለምለም ፡ ነው ።
ሥዩም ፡ በቃኸኝ ፡ የወረደበት ፡
፳፱ ፡ ላም ፡ የተነዳበት ።
ሥዩም ፡ በቃኸኝ ፡ የሞተው ፡ ዝናን ፡
ጦር ፡ መጣ ፡ በሉ ፡ ይነሣ ፡ እንደሆን ።

የዚህ ፡ የጠነነት ፡ ድል ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ በራስ ፡ ዐሊ. ፡ ዘንድ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ጸጸትንም ፡ ቊጣንም ፡ ቀስቅሶ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የበላይ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ለጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ የለቱን ፡ ሳይሆን ፡ ነገ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ማመዛዘን ፡ በትእግሥትም ፡ ሌላ ፡ ያስተዳደርና ፡ የመውጫ ፡ ዘዴ ፡ መፍጠር ፡ እንዳለበት ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በዚሁ ፡ መንገድ ፡ ራስ ፡ ዐሊም ፡ የጭፍሮቻቸውን ፡ መሸነፍ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ጦር ፡ መላክና ፡ መበቀል ፡ የሚቸግራቸው ፡ አልነበረም ። እርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ ፫ኛ ፡ ጊዜ ፡ ቢዋጉ ፡ ኖሮ ፡ ምናልባት ፡ የነደጃች ፡ ጐሹ ፡ ጦር ፡ በመጨረሻ ፡ ተዳክሞ ፡ ወደ ፡ መሸነፍ ፡ ሳያዘነበል ፡ አይቀርም ፡ ነበር ። ነገር ግን ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ በትልቁ ፡ ከተማ ፡ በጐንደር ፡ ምቀኛን ፡ በያለበት ፡ እስኪቀሰቅስ ፡ ድረስ ፡ ምስፍንናን ፡ ያረጋገጠላቸውን ፡ ኃይላቸውን ፡ በዳሞትና በጐጃም ፡ ሲፈጁ ፡ በስሔን ፡ በኩል አንድ ፡ ደስታ ፡ የሚሰማቸው ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ እንዳሉ ፡ በራስ ፡ ዐሊ ፡ አእምሮ ፡ ውስጥ ፡ አልተዘነጋም ። እኚህም ፡ ሰው ፡ የስሜንና ፡ የትግሬ ፡ የሐማሴን ፡ ገዥ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ናቸው ። ርሳቸውም ፡ ሲመቻቸው ፡ እየተዋጉ ፡ ሳይመቻቸው ፡ ለራስ ፡ ዐሊ ፡ እየገበሩ ፡ የተቀመጡ ፡ ናቸው ። በቀጥታም ፡ ከእንግሊዝና ፡ ከፈረንሣዊ ፡ መንግሥታት ፡ መልክተኞች ፡ እየተነጋገሩ ፡ መወዳጀትና ፡ መዋዋል ፡ መሣሪያም ፡ ማደርጀት ፡ ገምረዋል ፤ የመንግሥም ፍላጎት ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ ከእስክንድርያ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተላልከው ፡ አባ ፡ ሰላማን ፡ አስመጥተው ፡ ባጠገባቸው ፡ አስቀምጠዋል ። የሚነግሡበትን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሳይቀር ፡ እስከ ፡ ማሠራት ፡ ደርሰዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይኸን ፡ ሁሉም ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ አላጡትም ።

ስለዚህ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ኃይላቸውን ፡ በጐጃም ፡ ጨርሰው ፡ ለደጃች ፡ ውቤ ፡ ምቾትና ፡ ዘዴ ፡ መሣሪያ ፡ እንዳይሆኑና ፡ እንዳይመቹ ፡ እልከቸውን ፡ ጨክነው ፡ ወደ ፡ ትዕግሥት ፡ የለወጡት ፡ ይመስላል ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ደጃች ፡ ጐሹና ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ ፫ቱን ፡ ደጃዝማቾቻቸውን ፡ አሸንፈው ፡ በገደሏቸው ፡ ጊዜ ፡ ጦርነቱን ፡ አቁመው ፡ ሌላ ፡ የዕርቅና ፡ የሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ ማድረግ ፡ ገመሩ ። በመገመሪያም ፡ በብልኀት ፡ ደጃች ፡ ጐሹን ፡ አቀረቧቸው ፤ ደጃች ፡ ጐሹም ፡ በልጃቸው ፡ በደጃች ፡ ብሩና ፡ በርሳቸው ፡ መካከል ፡ ቅርታ ፡ ስለ ፡ ገባ ፡ ለብቻቸው ፡ ከራስ ፡ ዐሊ ፡ ጋራ ፡ ታረቁ ። ያለፈውም ፡ የጦርነት ፡ ቂም ፡ ከፀቱም ፡ ልብ ፡ እንዲጠፋ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ልጃቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ የውብዳርን ፡ ለደጃች ፡ ብሩ ፡ ዳሩላቸው ፤ ቢሆንም ፡ የዚህ ፡ የዕርቅና ፡ የተገኘነት ፡ ሁኔታ ፡ ደጃች ፡ ብሩን ፡ አላስደሰታቸውም ። በዚህም ፡ ላይ ፡ አባትየው ፡ ደጃች ፡ ጐሹ ፡ ወደ ፡ ሽምግልና ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ ወደ ፡ ሙሉ ፡ ሰውነት ፡ በመድረሳቸው ፡ ይልቁንም ፡ ደጃች ፡ ጐሹ ፡ ከርሳቸው ፡ ሳይስማሙ ፡ የተለየ ፡ ስምምነት ፡ ከራስ ፡ ዐሊ ፡ ጋራ ፡ ማድረጋቸው ፡ ቅር ፡ ስላላቸው ፡ ከባታቸው ፡ ጋራ ፡ ተጣሉ ፡ እንዲያውም ፡ ዳሞትን ፡ ይልቀቁልኝና ፡ እኔ ፡ ከጐጃም ፡ ጋራ ፡ ደርቤ ፡ ላስተዳድረው ፡



ራስ ፡ ዐሊ ፡ ትንሹ ፡ (ከአባ ፡ ማስያስ ፡ መጽሐፍ) ። ፬፻፲፯

እርስዎ ፡ ግዛት ፡ ይብቃዎ ፡ ብለው ፡ ላኩባቸው ። ካባታቸውም ፡ መልሱን ፡ ሳይ ጠብቁ ፡ በደገሞና ፡ በማቻከል ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ አደረጉበት ፡ ይባላል ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የራስ ፡ ዐሊ ፡ ጠላቶች ፡ የነበሩት ፡ ያባትና ፡ የልጁ ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ጠብ ፡ በገሃድ ፡ ታወቀ ፤ ዘመድም ፡ ሽማግሌም ፡ በመካከላቸው ፡ ገብቶ ፡ ለማስታረቅ ፡ ቢፈትን ፡ አልሆነለትም ። ደጃች ፡ ብሩም ፡ ያባቴን ፡ ግዛት ፡ ካል ደረብሁ ፡ ብለው ፡ ያቀረቡትን ፡ ክርክር ፡ አጥብቀው ፡ ያዙት ።

ስለዚህ ፡ በመጨረሻ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ሙቼስ ፡ ምን ፡ ይደረግ ፡ እርስዎ ፡ ይሸነ ፉልንና ፡ ይልቀቁለት ፡ እርሱ ፡ ጉልበቱ ፡ እንደ ፡ ፈቀደለት ፡ ያስተዳድር ፡ ብለው ፡ ደጃች ፡ ጐሹን ፡ ለመኗቸው ። ደጃች ፡ ጐሹ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ግዛቴን ፡ ያለፈቃዴ ፡ እርሱ ፡ ለመቀማት ፡ ከፈለገና ፡ ሰው ፡ ካልዣቀበት ፡ ይምጣና ፡ በኀይል ፡ ይውሰድ ፡ እንጂ ፡ በፈቃዴ ፡ አልሰጠውም ፤ በፈቃዴ ፡ ዳሞትን ፡ ከሰጠሁት ፡ በኋላ ፡

ወልጄው ፡ እርስዎ ፡ ልለው ፡ ነውን ።

ወይስ ፡ ጭፍራ ፡ ሆኜ ፡ ጋሻ ፡ አንግቤ ፡ አንተ ልለው ፡ ነውን ።

አላደርገውም ፡ ብለው ፡ ለሽማግሌዎቹ ፡ የመጨረሻ ፡ መልሳቸውን ፡ አስታ ወቁ ። ሽማግሌዎቹም ፡ እንግዴህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለወደደው ፡ ይርዳ ፡ ብለው ወደየቤታቸው ፡ ተመለሱ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሁለቱም · ወገን ፡ የጦርነት ፡ ድርጅት ፡ ይደረግ ፡ ዠመር ። በሁለቱም ፡ ዘንድ ፡ ግብር ፡ ለወታደሮች ፡ ሲደረግ ፤ በግብርም ፡ ላይ ፡ እኔ ፡ የብሩ ፡ አሽከር ፡ . . . ፡ እኔ ፡ የጐሹ ፡ አሽከር ፡ . . . ፡ እየተባለ ፡ ሲፎከር ፡ ሰነበተ ። ፊታ ውራሪ ፡ ፈልፈሉ ፡ (ፍልፍሉ) ፡ የሚባሉ ፡ የደጃች ፡ ጐሹ ፡ አሽከርና ፡ አማካሪ ፡ በተራቸው ፡ ሲፎክሩ ፡ «እንበለው ፡ ይኸን ፡ ዲቃላ ፡ እኔ ፡ ፈልፈሉ ፡ እጁን ፡ አም ጥቼ ፡ ሰለባ ፡ እጥለዋለሁ ፡ . . . ።» ፡ ብለው ፡ በጌታቸው ፡ ፊት ፡ ፉከራቸውን ፡ ደቀ ደቁት ፡ ይባላል ።

የዚህንም ፡ ወሬ ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ተናደዱና ፡ «የምትሰለፍበ ትን ፡ ቦታ ፡ መርጠኽ ፡ ላክብኝ» ፡ ብለው ፡ ለፊታውራሪ ፡ ፈልፈሉ ፡ ላኩባቸው ። ርሳቸውም ፡ «እንጋጣ ፡ ከሚባለው ፡ ቦታ ፡ በስተቀኝ ፡ በኩል ፡ ተሰልፌ ፡ ጊደር ፡ የሰበረ ፡ አንበሳ ፡ መስዬ ፡ እጠብቅኻለሁ» ፡ ብለው ፡ መለሱ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደዚሁ ፡ ሥፍራ ፡ ጉዞ ፡ ዠመሩ ። በጉ ዞም ፡ ላይ ፡ አባቴን ፡ ደጃች ፡ ጐሹን ፡ ያገኘ ፡ ወታደር ፤ ወይም ፡ ሹም ፡ ይማ ርክ ፡ እንጂ ፡ እንዳይገድል ፡ ብለው ፡ አስጠነቀቁ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱም ፡ ተገ ናኝተው ፡ ውጊያው ፡ ተዠመረና ፡ የደጃች ፡ ጐሹ ፡ ጦር ፡ ተሸነፈ ። ደጃች ፡ ጐሹም ፡ ወደ ፡ አጋምና ፡ ጊዮርጊስ ፡ ሸሸት ፡ ዠመሩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ማን ፡ ይከታተላ ቸው ፡ እያሉ ፡ እዚያው ፡ እጦሩ ፡ ሜዳ ፡ ሲጠያየቁ ፡ የለም ፡ ርሳቸውን ፡ ትታ ችሁ ፡ ያን ፡ እጁን ፡ አምጥቼ ፡ ሰለባ ፡ እጥለዋለሁ ፡ ብሎ ፡ የፎከረብኝን ፡ ፈልፈ ሉን ፡ ተከታትላችሁ ፡ ያዙልኝ ፡ ብለው ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ አሽከሮቻቸውን ፡ አዘዙ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፊታውራሪ ፡ ፈልፈሉ ፡ በፈረስ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ አገ

ራቸው ፡ ሲሸሹ ፡ አባራሪውም ፡ በፈረስ ፡ ሆኖ ፡ ሲያባርራቸው ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ ቆዩ ፡ በመጨረሻ ፡ ግን እንደምንም ፡ ሽምጥ ፡ ጋልቦ ፡ አባራሪው ፡ በፊታ ውራሪ ፡ ፈልፈሉ ፡ ደረሰባቸውና ፡ «ይማረኩ ፡ የኔታ ፡ ፊታውራሪ ፡ ፈልፈሉ ፡ እኔ ፡ እሻልዎታለሁኝ» ፡ አላቸው ፤ እርሳቸው ፡ ደግሞ ፡ የሽምጥ ፡ ግልቢ ያቸውን ፡ እየቀጠሉ ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ዘወር ፡ ብለው ፡ «ከቤቴ ፡ ከየ ብራኄ ፡ ከሚስቴ ፡ ከሐረን ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አትሻለኝምና ፡ ይልቅስ ፡ እኔን ፡ ማባረ ሩን ፡ ትተኽ ፡ ተመለስ» ፡ ብለው ፡ መለሱለት ፤ እርሱም ፡ እንቤታቸውን ፡ በወቀ ፡ ጊዜ ፡ ተከታትሎ ፡ ሊገድላቸው ፡ ግልቢያውን ፡ አበረታ ፡ ሊገድላቸው ፡ መቆረ ጡን ፡ ፊታውራሪ ፡ ፈልፈሉ ፡ በበኩላቸው ፡ በተረዱት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ የሚበረውን ፡ ፈረሳቸውን ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መልሰው ፡ አባራሪውን ፡ በጦር ፡ ወግተው ፡ ከመሬት ፡ ጋራ ፡ ደባልቀው ፡ ገደሉት ። ከዚያም ፡ ግልቢያቸውን ፡ ቀጥ ለው ፡ እቤታቸው ፡ ደርሰው ፡ እንደ ፡ ቈዩ ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ የደጃች ፡ ብሩ ፡ አሽ ከሮች ፡ አዘንግተው ፡ በሌሊት ፡ ከቤታቸው ፡ ይዘዋቸው ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ ወሰዷቸውና ፡ ሰማ ፡ አምባ ፡ ታሰሩ ። በደረቁም ፡ ጠኵራቸውን ፡ ላጩዋቸው ፡ ይባላል ።

※ ※ ※

እንግዴህ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ባለፈው ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ሦስቱን ፡ ደጃዝማቾች ፡ ልከው ፡ እነዚያንም ፡ የተላኩትን ፡ ደጃች ፡ ጐሹና ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ ተባብረው ፡ በወጓቸውና ፡ ሦስቱንም ፡ በገደሏቸው ፡ ጊዜ ፡ ራሳቸው ፡ ሄደው ፡ ከነዚህ ፡ ከሸና ፊዎቹ ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ድል ፡ ቢሆኑም ፡ ድል ፡ ቢያደር ጉም ፡ ያስተዳደራቸውን ፡ ዘዴ ፡ የሚያጠፋብቸው ፡ መሆኑን ፡ ተገነዘቡና ፡ ከደጃች ፡ ጐሹ ፡ ታረቁ ፤ ከታረቁ ፡ በኋላ ፡ ደጃች ፡ ጐሹ ፡ ከደጃች ፡ ብሩ ፡ ሲዋጉ ፡ የራስ ዐሊ ፡ ፖሊቲክ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ይኽን ፡ የመሰለውን ፡ የራስ ፡ መታረቅና ፡ ሌላውን ፡ የማዋጋት ፡ ዘዴ ፡ የኢትዮጵያም ፡ የኤውሮፓም ፡ መሪዎች ፡ እንደ ፡ መጠኑ ፡ በየጊዜው ፡ ሠርተው ፡ ተጠቅመውበታል ። የዚህም ፡ ዐይነት ፡ ያስተዳደር ፡ ብልኀት ፡ «አለያይተኽ ፡ ግዛ» ፡ ከተባለው ፡ ከሮማውያን ፡ ያገዛዝ ፡ ፍልስፍና ፡ ጋራ ፡ የሚገናኝ ፡ ነው ።

ራስ ፡ ዐሊ ፡ በዚህ ፡ በዕርቅ ፡ ፈንታ ፡ በጐጃም ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ ቢሆኑ ፡ ኖሮ ፡ የስሜንና ፡ የትግሬ ፡ ገዥ ፡ ተሮከካሪያቸው ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ቍልቍል ፡ መጥ ተው ፡ የጐንደርን ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ ቢይዙ ፡ የሚቋቋማቸው ፡ ይጠፋ ፡ ነበር ። ድል ፡ ቢያደርጉና ፡ ቢመለሱም ፡ በጦርነትና ፡ በጕዞ ፡ የደከመው ፡ ጦራ ቸው ፡ አዲሱን ፡ የደጃች ፡ ውቤን ፡ ጦር ፡ ተዋግቶ ፡ ለመመለስ ፡ ሳያዳግተው ፡ አይቀርም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ሁሉንም ፡ አመዛዝነው ፡ በዕርቅና ፡ በጋብቻ ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ማቀዝቀዛቸው ፡ ዘዴኛነታቸውን ፡ ያስረዳል ።

ቢሆንም ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክና ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እምባቦ ፡ ላይ ፡ ተዋግተው ፡ ንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ በሸነፉ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ከመቀሌ ፡ ወደ ፡ ወረይሉ ፡ መጥተው ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክን ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ እንደያዝህ ፡ ና ፡ ብለው ፡ እንደጠሯቸው ፤ ራስ ፡ ዐሊም ፡ የደጃች ፡ ጐሹንና ፡ የልጃቸውን ፡ የደጃች ፡ ብሩን ፡ ውጊያ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከደብረ ፡ ታቦር ፡ ተነሥተው ፡ በግሥጋሤ ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ መጡ ።

ዐዴት ፡ ከሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ሰፈራቸውን ፡ በዚያ ፡ አድርገው ፡ «እንድትመጡ» ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ ለደጃች ፡ ጐሹና ፡ ለደጃች ፡ ብሩ ፡ ላኩ ። መልክቱ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ መምጣት ፡ ስላልፈለጉ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ መዋጋትም እንደማይችሉ ፡ ተገንዝበው ፡ ሶማ ፡ አምባ ፡ ገብተው ፡ ተቀመጡ ። ደጃች ፡ ጐሹ ፡ ግን ፡ ከዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ታማኝነታቸውን ፡ በዕርቅ ፡ ገልጸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የራስ ፡ ዐሊን ፡ ጥሪ ፡ አክብረው ፡ ሄዱ ። በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክንና ፡ ንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ በመዋጋታቸው ፡ እንደ ፡ ወቀሷቸው ፡ አሁንም ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ «ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ደጃዝማችነቴን ፡ ሾሜ ፡ ብልክ ፡ ገደላችኋቸው ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ሁለታችሁ ፡ አባትና ፡ ልጁ ፡ መዋጋታችሁ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው» ፡ ብለው ፡ ተቈጥተው ፡ ደጃች ፡ ጐሹን ፡ በሰንሰለት ፡ አሰሯቸው ። ይኸ ፡ የራስ ፡ ዐሊ ፡ ቁጣ ፡ በውነቱ ፡ የደጃች ፡ ጐሹና ፡ የደጃች ፡ ብሩ ፡ መዋጋትና ፡ በከንቱ ፡ ደም ፡ መፋሰስ ፡ ለራስ ፡ ዐሊ ፡ ያሳዘናቸው ፡ ይመስላል ? ፤ አይመስልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ባሁን ፡ ጊዜ ፡ ይኸን ፡ መናገርና ፡ ማሰር ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ዘዴ ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ልጃቸው ፡ ደጃች ፡ ተሰማ ፡ (የንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አባት) ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ሄደው ፡ እኔን ፡ በርሳቸው ፡ ምትክ ፡ ይሰሩኝና ፡ አባቴን ፡ ደጃች ፡ ጐሹን ፡ እባክዎ ፡ ይፍቱልኝ ፡ ብለው ፡ ለራስ ፡ ዐሊ ፡ ልመና ፡ አቀረቡ ። ራስ ፡ ዐሊም ፡ ደጃች ፡ ተሰማን ፡ ከልብ ፡ አመስግነው ፡ ለጊዜው ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ደጃች ፡ ተሰማን ፡ አሰሩና ፡ ደጃች ፡ ጐሹን ፡ በቶሎ ፡ ፈተው ፡ ለቀቋቸው ። ደጃች ፡ ጐሹ ፡ ደግሞ ፡ በተራቸው ፡ ስለ ፡ ልጃቸው ፡ እስራት ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ ደጅ ፡ ጠንተው ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ ጊዜ ፡ ሳይቆዩ ፡ አስፈቱና ፡ በአገውና ፡ በቡሬ ፡ ላይ ፡ የደጃዝማችነት ፡ ማዕርግ ፡ አሰጥተው ፡ አሾሟቸው ። ቢሆንም ፡ ስላባታቸው ፡ ተተክተው ፡ ልታሰር ፡ ማለታቸውን ፡ የሰማ ፡ ሁሉ ፡ እያደነቀ ፡ ደጃች ፡ ተሰማን ፡ አመሰገናቸው ።

ግጥምም ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ተገጠመ ።
እኛ ፡ የተማርነው ፡ ሊቃውንቱ ፡ ሳናውቅ ፡
ተሰማ ፡ ላባቱ ፡ ተሠዋ ፡ እንደ ፡ ይሥሐቅ ።

ደጃች ፡ ጐሹ ፡ በዳሞት ፤ ልጃቸው ፡ ደጃች ፡ ተሰማ ፡ በአገውና ፡ በቡሬ ፡ ለራስ ፡ ዐሊ ፡ ታማኝ ፡ ሆነው ፡ ሳሉ ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ ብቻ ፡ በሶማ ፡ አምባ ፡

ሆነው ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ እየተዋጉ ፡ የራስ ፡ ዐሊ ፡ የግዛት ፡ ዘመን ፡ ፱ዐ፪ ፡ ቴዎ ድሮስ ፡ እስኪወድቅ ፡ ድረስ ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ ሲያስቸግሩ ፤ በኋላም ፡ ዐፄ ፡ ቴዎ ድሮስን ፡ ሲያውኩ ፡ ኖሩ ።

ራስ ፡ ዐሊም ፡ ከጐጃም ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ከተማቸው ፡ ተመልሰው ፡ የማ ስተዳደር ፡ ሥራቸውን ፡ ይቀጥሉ ፡ ጀመር ። ብዙ ፡ ቀንም ፡ በሰላም ፡ ከተቀመጡ በኋላ ፡ የስሜንና ፡ የትግሬ ፡ ገዥ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳልነው፡ ለራስ ፡ ዐሊ ፡ ሳይገዙ ፡ ራሳቸው ፡ መግዛት ፡ ስለ ፡ ፈለጉ ፡ ጦር ፡ አደራጅተው፡ መጥተው ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ ለመውጋት ፡ ይዘጋጁ ፡ ጀመር ። የዚህንም ፡ ጦር ነት ፡ ሁኔታ ፡ ወደፊት ፡ ባለው ፡ ምዕራፍ ፡ እንረዳለን ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፺፫ ።

## በዓለምና ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሥርወ ፡ መንግሥት ፡ መለዋወጥ ፤—በዘመነ ፡ መሳፍንት ሰበብ ፡ እንጂ ፡ እውነተኛነት ፡ የሌለው ፡ የጦርነት ፡ ምክንያት ።

በሮማውያን ፡ ዘመን ፡ ከዩልዮስ ፡ ቄሣር ፡ ጀምሮ ፡ በርሱ ፡ መሥራችነት ፡ (የዩልዮስ ፡ ክሎዲ ፡ ቤት) ፡ ከሚባለው ፡ ዘር ፡ ሳይወጣ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከገዛ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ እንደ ፡ ኤሊጋባሉስ ፡ (1)ያሉት ፡ የምሥራቅ ፡ የዐረብ ፡ ዘሮች ፡ በትልቁ ፡ በሮማ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ዙፋን ፡ መቀመጥና ፡ መግዛት ፡ ችለው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፤ ከዚያም ፡ በፊት ፡ በግብጽ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የግሪኩ ፡ የፕቶሎሚዉስ ፡ በፈረንሳዊ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የኤስ ፓኙ ፤ በኤስፓኙም ፡ ቦርቦን ፡ የሚባለው ፡ የፈረንሳዊ ፡ አብስቡርግ ፡ የሚባለው ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፤ ደግሞ ፡ ከስዊስ ? ፈልቆ ፡ በኋላ ፡ በኦትሪሽ ፡ የቄሣር ፡ ግዛት ፡ በደንብ ፡ ተመሥርቶ ፡ ከዚያም ፡ በኤስፓኝ ፡ በሆንግሪ ፡ በሆላንድ ፡ የነጋ ሢነት ፡ ዘሩን ፡ በገዥነት ፡ አጽድቆ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንደዚሁም ፡ ከተራ ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ በየጊዜው ፡ እየተነሡ ፡ ዘሩ ፡ ተያይዞ ፡ የመጣውን ፡ ገዥ ፡ እየጣሉ ፡ ላጭ ርም ፡ ለረዥምም ፡ ጊዜ ፡ ራሳቸውንና ፡ ዘራቸውን ፡ የመተካታቸው ፡ ታሪክ ፡ በዓ ለም ፡ በየመንግሥታቱ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ደርሷል ።

በኢትዮጵያም ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣውን ፡ ሰሎሞናዊ ፡ ነጋሢ ፡ ከት ግሬ ፤ ከጋላ ፤ ከአማራ ፤ ከሱማሌ ፡ አንዳንድ ፡ ኀይለኛ ፡ እየተነሣ ፡ ዙፋን ፡ ለመቀ ማት ፡ የታገለው ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ የተከናወነለት ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ ነው ፤ እስበው ፡ ያል ተከናወነላቸውን ፡ ብዙዎቹን ፡ ትተን ፤ ጥቂቶች ፡ የተከናወነላቸው ፡ እነማን ፡ መሆ ናቸውን ፡ ስናስብ ፡ ፈላሻዋ ፡ ዮዲት ፤ ላስታዎቹ ፡ ዛጌዎች ፤ እስላሙ ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ በመሳፍንትነት ፡ የሚገዙት ፡ የሴሩ ፡ ጓንጉል ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ።

1 ኤሊዮጋባሉስ ፡ የሮማ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከመሆኑ ፡ በፊት ፡ በሶርያ ፡ የብዔል ፡ ዜቡል ፡ (የዐሐይ) ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ነበረ ።

እንደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የበላይ ፡ ገዥ ፡ ለመሆን ፡ እየተነሡ ፡ ተዋግተው ፡ ሳይ ሆንላቸው ፡ እየቀረ ፡ በዚህ ፡ ፈንታ ፡ ስደት ፤ እስራት ፤ እጅ ፡ መቈረጥ ፤ ስቅላት ፡ የደረሰባቸውን ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ዘርዝሮ ፡ ለማሳየት ፡ ብዙ ፡ ምዕራፍ ፡ የሚፈጅ ፡ ነው ። በአኵስም ፤ በላስታ ፤ በሸዋ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ ሺ.ሕ ፡ ዓመት ፡ ግድም ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ዠምሮ ፡ ይኽ ፡ ያሁኑ ፡ መጽ ሐፍ ፡ መጻፍ ፡ እስከ ፡ ዠመረበት ፡ እስከ ፡ ሺ.ሕ ፡ ፰፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ እስከ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ድረስ ፡ በመካከሉ ፡ መንግሥትን ፡ ለመምራት ፡ ወይም ፡ ከመንግሥት ፡ ለመነጠል ፤ «ገብር ፡ አልገብርም ፡ ግባ ፡ አልገባም» ፡ በመባባል ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የፈሰሰውን ፡ ደም ፡ ለመገመት ፡ ያኽል ፡ ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ አን ሥቶ ፡ እስካሁን ፡ እስከ ፡ መሳፍንት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ በተጻፈው ፡ መጽ ሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ ይረዳናል ። ይህ ፡ ሁኔታ ፡ በኢትዮጵያ ውያን ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የበረታ ፡ የገዥነት ፡ መንፈስና ፡ የነፃነት ፡ ፍቅር ፡ ሊያሳየንና ፡ ሊያስደስተን ፡ ሲሞክር ፡ በዚህ ፡ ኵራትና ፡ ነፃነት ፤ ምኞትና ፡ እንቢታ ፡ ምክንያት ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ያለቀውን ፡ በዚህም ፡ የመንግሥቱና ፡ የሕዝቡ ፡ ኃይ ልና ፡ ቊጥር ፡ ወደ ፡ ድካምና ፡ ወደ ፡ መጕደል ፡ መዘቅዘቁን ፡ ስንመለከት ፡ መልሶ ፡ ያሳዝነናል ።

※ ※ ※

በዚህ ፡ ዘመን ፡ (ሺ.ሕ ፡ ፯፻፹—ሺህ ፡ ፰፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም) ፡ ያለው ፡ የጦርነት ዋናው ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ ከዐረብ ፡ አገር ፡ በግራኝ ፡ ጊዜ ፡ የመጣው ፡ ሸሕ ፡ ዑመር ፡ ከየጁ ፡ ጋላ ፡ መወለዳቸው ፤ የርሳቸውም ፡ ዘር ፡ በትልቁ ፡ ከተማ ፡ በጐ ንደር ፡ ተቀምጦ ፡ በእንደራሴነት ፡ ወይም ፡ በመስፍንነት ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይገዛ ፡ የሚባለው ፡ ምክንያት ፡ ነው ። እንደ ፡ መስቀል ፡ ጦርነት ፡ ዐይነት ፡ በዚህና ፡ በሌላውም ፡ በግል ፡ ምኞታቸው ፡ እየተቀሰቀሱ ፡ እነዚህን ፡ የሴሩ ፡ ጓንጕልን ፡ ዘሮች ፡ ከጐደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ለማስለቀቅ ፡ ከትግሬ ፡ እነራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ እነደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ከጐጃም ፡ እነራስ ፡ መርድ ፤ እነደጃች ፡ ዘውዱ ፤ እነደጃች ፡ ጐሹ ፤ ከስሜን እነራስ ፡ ገብሬ ፡ እነደጃች ፡ ኀይሉ ፡ ማርያም ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ እየተነሡ ፡ ሲመቻቸው ፡ እየተዋጉ ፡ ሳይመቻቸው ፡ እየታረቁ ፡ በቃላቅ ፡ የጦርነት ፡ ግድያና ፡ የነገር ፡ ክርክር ፡ ኖሩ ። የሴሩ ፡ ጓን ንጕል ፡ ዘሮች ፡ እነራስ ፡ ዐሊ ፤ እነራስ ፡ ጉግሳ ፡ እነራስ ፡ ማርዬም ፡ ያገሩን ፡ ልማድና ፡ ሥርዐት ፡ ሳይሽሩ ፡ ክርስቲያንነታቸውንም ፡ እንደያዙ ፡ ውጊያውን ፡ በውጊያ ፤ ሰላማዊውን ፡ በሰላም ፤ ዘዴኛውን ፡ በዘዴ ፡ እየመለሱ ፡ በጐንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ያላቸውን ፡ የገዥነት ፡ ሥልጣን ፡ አደላድለውና ፡ አጠንክ ረው ፡ ያዙ ።

እውነቱን ፡ መርምረን ፡ ለመረዳት ፡ የፈለግን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የጦርነቱ ፡ እውነተኛ ፡ ምክንያት ፡ የነራስ ፡ ዐሊ ፤ የነራስ ፡ ጉግሳ ፡ ከየጁ ፡ ጋላ ፡ ወይም ፡ ከዐረብ ፡ የመወለዳቸው ፡ ምክንያት ፡ ሳይሆን ፡ እኔ ፡ ልግዛ ፡ የማለት ፡ ምኞት ፡

እንደ ፡ ሆነ ፡ ለመረዳት ፡ መንገዱ ፡ ቀላል ፡ ነው ። እነራስ ፡ ዐሊን ፡ ለማስለቀቅ ፡ የሚታገሉት ፡ የስሜኖቹ ፡ የነራስ ፡ ገብሬ ፤ የትግሬዎቹ ፡ የነራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፤ የጐጃሞቹ ፡ የነራስ ፡ መርድ ፡ ዘራቸው ፡ ጥንት ፡ የመጣበት ፡ አገር ወዴት ፡ ነው ? ። ካረብ ፡ አገር ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ተሻግረው ፡ የመጡት ፡ የነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ወገኖች ፡ ያው ፡ ዐረቦች ፡ አይደሉምን ፤ የዘሩ ፡ ኑስ ፡ ደንበኛ ፡ ወራሽ ፡ ሰሎሞናዊው ፡ ነጋሢ ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ አይደለምን ፤ ሁሉም ፡ ከዐረብና ፡ ከእስራኤል ፡ ከህንድ ፡ በጠቅላላው ፡ ከምሥራቅ ፡ የመጣ ፡ ሲሆን ፡ ሁሉንም ፡ ያስመከውና ፡ ያኰራው ፡ ክርስቲያንነቱ ፡ አይደለምን ፤ የሸሕ ፡ ዑመር ፡ ዘሮችስ ፡ ክርስትናን ፡ ገና ፡ በፊት ፡ ከሴሩ ፡ ጓንጉል ፡ ዠምረው ፡ ተቀብለው ፡ የለምን ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ነገሩን ፡ በጕልህ ፡ እማሳጣት ፡ ያደረሰው ፡ ትግሬዎቹና ፡ አማሮቹም ፡ ለመነሻ ፡ ምክንያት ፡ ያጋጠማቸው ፡ የሸሕ ፡ ዑመር ፡ ካረብ ፡ አገር ፡ አመጣጡ ፡ ቀረብ ፡ ባለ ፡ በግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ጊዜ ፡ በሺሕ ፡ ፭፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ሲሆን ፡ የነገደ ፡ ዮቅጣኖች ፡ አመጣጥ ራቅ ፡ ካለ ፡ ጊዜ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ከሺሕ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ በየጊዜው ፡ በመሆኑና ፡ አስቀድሞ ፡ የገባው ፡ እንደ ፡ ባላገር ፤ በኋላ ፡ የመጣው ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፤ በመቈጠሩ ፡ ይሆናል ።

እንግዴህ ፡ ለማናቸውም ፡ ነገር ፡ ሰበብ ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ እነዚህም ፡ ያማራና ፡ የትግሬ ፡ ታላላቅ ፡ መኳንንቶች ፡ መሳፍንቱን ፡ ለማስለቀቅ ፡ በተዋጉበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የነዚህን ፡ የጋላና ፡ የዐረብ ፡ ዘርነታቸውን ፡ የሚጠቅሱት ፡ ተከታይና ፡ አባሪ ፡ ለማግኘት ፡ እንዲረዳቸው ፡ መሆኑን ፡ እንገነዘባለን ። እነራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፤ እነራስ ፡ መርድ ፡ የተነሡት ፡ «እኔ ፡ ልግዛ» ፡ በሚባል ፡ ምኞት ፡ ሳይሆን ፡ በነዚህ ፡ የዘር ፡ ልዩነት ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ከትልቁ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ምስፍንና ፡ በፊት ፡ ነገሥታቶቹ ፡ ከላስቶች ፡ ከጋሎች ፡ ጋራ ፡ ይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ወሬኛ ፡ እየተባለ ፡ ከያውራጃው ፡ ከየከተማው ፡ ከሚነሣው ፡ ጋራ ፡ ያን ፡ ያኽል ፡ አይዋጉም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ የጦርነቱ ፡ ሁሉ ፡ ሥረ ፡ ነገር ፡ «እኔ ፡ ልግዛ» ፡ የሚባለው ፡ የራስን ፡ መውደድና ፡ ራስን ፡ አኵርቶ ፡ ለመገኘት ፡ የመመኘት ፡ መንፈስ ፡ መሆኑን ፡ ለዘለቄታ ፡ እንገንዘብ ። ምናልባት ፡ «እገሌ ፡ ከሚገዛኝ ፡ እገሌ ፡ ቢገዛኝ ፡ ይሻላል ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ የሼህ ፡ ዑመር ፡ ዘር ፡ ከሚገዛን ፡ የሰሎሞን ፡ ዘር ፡ ቢገዛን ፡ ይሻላል» ፡ በሚል ፡ መንፈስ ፡ ተመርተው ፡ አማሮቹና ፡ ትግሬዎቹ ፡ ቀድሞ ፡ በነጋሢዎቹ ፡ ጊዜ ፡ አቀዝቅዘው ፡ የያዙትን ፡ ምኞታቸውን ፡ አሁን ፡ በሴሩ ፡ ጓንጉል ፡ ጊዜ ፡ በጋለ ፡ መንፈስ ፡ ተነሥተውበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የምርጫ ፡ ጕዳይ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ተመርጠው ፡ የነገሡትም ፡ በሚያስተዳድሩበት ፡ በነሠርፀ ፡ ድንግል ፤ በነኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፤ በነበካፋም ፡ ጊዜ ፡ ሙሉ ፡ ጸጥታና ፡ ሰላም ፡ እንዳልነበረ ፡ ባለፈው ፡ ታሪክ ፡ ሁሉ ፡ ተረድተነዋል ።

አሁን ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ትተን ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ደግሞ ፡ ከዋናው፡
እንደራሴ ፡ ከራስ ፡ ዐሊ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚያደርጉትን ፡ ጦርነት ፡ ከመመ
ልከታችን ፡ በፊት ፡ ከደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ዘሮች ፡ ጋራ ፡ ያደረጉትን ፡ ውጊያ ፡
እንመልከት ።

## ምዕራፍ ፡ ፺፪ ።

## ደጃች ፡ ውቤ ፡ ከደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ወራሾች ፡ ጋራ ፡ ያደረጉት ፡ ጦርነት ።

ደጃች ፡ ውቤ ፡ ከራስ ፡ ማርዬ ፡ ጋራ ፡ ሁነው ፡ ከታወቁትና ፡ በመላ ፡ የትግሬ ፡
ገዥ ፡ ከነበሩት ፡ ከደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ጋራ ፡ ከተዋጉና ፡ ደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡
ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ዶሪ ፡ የጐንደር ፡ ምስፍንናን ፡ ሲይዙ ፡ ደጃች ፡ ውቤ፡
ከባት ፡ ግዛታቸው ፡ ከስሜን ፡ አልፊው ፡ ትግሬን ፡ ማስተዳደር ፡ ዠመሩ ።
በዚህ ፡ ጊዜ የደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ ልጆች ፡ እኛ ፡ በሕይወት ፡ እያለን ፡ አባቶ
ቻችን ፡ በቈዩን ፡ በትግሬና ፡ በሐማሴን ፡ ግዛታችን ፡ ከስሜን ፡ ባዕዱ ፡ ደጃች
ውቤ ፡ መጥተው ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይግዙን ፡ የማለት ፡ ጸጸትና ፡ ቍጭት ፡ አደ
ረባቸው ። እነዚህም ፡ የአጋሜው ፡ ደጃች ፡ ካሣይ ፡ የተንቤኑ ፡ ደጃች ፡ ገብረ ፡
ሩፋኤል ፡ (1)የሐማሴኑ ፡ ከንቲባ? ኀይሉ ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ከየክፍላቸው ፡
ጦራቸውን ፡ ሰብስበው ፡ የደጃች ፡ ውቤ ፡ እንደራሴ ፡ ወደ ፡ ነበረበት ፡ ወደ ፡
ዐድዋ ፡ ተጓዙ ። ደርሰውም ፡ ወግተው ፡ ከዐድዋ ፡ አባረሩትና ፡ ደጃች ፡ ካሣይ ፡
በዐድዋ ፡ ተቀምጠው ፡ ማስተዳደር ፡ ዠመሩ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በሺሕ ፡ ፰፻፴፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ የክረምትን ፡
ወራት ፡ ለማሳለፍ ፡ ወዳገራቸው ፡ ወደ ፡ ስሜን ፡ ሄደው ፡ ነበርና ፡ ይኸን ፡
በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ጦራቸውን ፡ ሲያደራጁ ፡ ከርመው ፡ በመጨረሻ ፡ ፰ ፡ ሺሕ ፡
ጦር ፡ አስከትለው ፡ ዐድዋ ፡ ደረሱ ። ደጃች ፡ ካሣይ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዐድዋን ፡
ትተው ፡ ወደ ፡ ፈረስ ፡ ማይ ፡ ሄዱ ። ደጃች ፡ ገብረ ፡ ሩፋኤልም ፡ ወደ ፡
ግዛታቸው ፡ ወደ ፡ ተንቤን ፡ ሄደው ፡ ሰላማዊ ፡ መስለው ፡ ተቀመጡ ። ደጃች ፡
ካሣይና ፡ ኀይሉ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ብለው ፡ ፴ ፡ ሺሕ ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡
እዚሁ ፡ ፈረስ ፡ ማይ ፡ ከሚባለው ፡ (ቄሪ ፡ አጠገብ) ፡ ከፍተኛ ፡ ሥፍራ ፡
ፊት ፡ ለፊት ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ በሺሕ ፡ ፰፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ገጠሟቸው ።
ጦርነቱም ፡ ከሁለት ፡ ወገን ፡ በብርታት ፡ ስለ ፡ ተያዘ ፡ ከጧቱ ፡ ዠምሮ ፡
እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ አቈየ ፡ ይባላል ።

ደጃች ፡ ውቤም ፡ ሠራዊቱ ፡ ተደባልቆ ፡ በሚዋጋበት ፡ ጊዜ ፡ የደጃች ፡
ኃይሉ ፡ መመላለሻ ፡ የሆነውን ፡ በር ፡ ይዘው ፡ ክቢ ፡ ለመሥራት ፡ አሰቡ ።
ነገር ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ አሳብ ፡ ኀይሉ ፡ በቶሎ ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፡ ጓደኛቸውን ፡
ካሣይን ፡ ለብቻቸው ፡ ትተው ፡ መንገድ ፡ የያዙትን ፡ የደጃች ፡ ውቤን ፡ ወታደ
ሮች ፡ በውጊያ ፡ ጥሰው ፡ ወደ ፡ ሐማሴን ፡ ተመለሱ ።

(1) ኩልቦ ፡ በ፲ኛው ፡ ቮሊም ፡ በገጽ ፡ ፫፻፹፱ ፡ ላይ ፡ ወልደ ፡ ሩፋኤል ፡ ይላል ።

ደጃች ፡ ካሣይም ፡ የራሳቸው ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ደከመ ፡ ጓደኞቻቸውም ፡ ትተ
ዋቸው ፡ ስለ ፡ ሄዱ ፡ እርሳቸውም ፡ ጦርነቱን ፡ አቁመው ፡ በግሥጋሤ ፡ ወዳገ
ራቸው ፡ ወዳጋሜ ፡ ገብተው ፡ ተቀመጡ ።

ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ኀይሉ ፡ ከሐማሴን ፤ ካሣይም ፡ ከአጋሜ ፡ ለደጃች ፡
ውቤ ፡ ለመገበርና ፡ ታርቆ ፡ ለመግባት ፡ በሽማግሌ ፡ ይላላኩ ፡ ጀመር ። ደጃች ፡
ውቤም ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ጢትና ፡ ማታ ፡ ጦርነት ፡ በማድረግ ፡ ጦሬ ፡ የደከመ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ በኋላ ፡ በራስ ፡ ዐሊ ፡ መጠቃት ፡ ይመጣብኛል ፡ ሲሉ ፡ እገብራ
ለሁ ፡ ካሉ ፡ እታረቃቸዋለሁና ፡ ይምጡ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ በሽማግሌዎቹ ፡ በኩል፡
ለሁለቱም ፡ ላኩባቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኀይሉ ፡ በመጀመሪያ ፤ ቀጥሎም ፡ ካሣይ ፡ ምሕረት ፡ ለም
ነው ፡ ከደጃች ፡ ውቤ ፡ ጋራ ፡ ዕርቅ ፡ አደረጉ ። ደጃች ፡ ውቤም ፡ በያባት ፡
አገራቸው ፡ እየሾሙ ፡ ደስ ፡ አሰኝተዋቸው ፡ ስለ ፡ ሰደዷቸው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡
ጊዜ ፡ የሰላም ፡ መልክ ፡ አሳይቶ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ያባታቸው ፡ አገር ፡
ተመረቀላቸው ፡ ሲባል ፡ በደጃች ፡ ውቤ ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ ለደጃች ፡ ውቤ ፡
እየገበሩ ፡ እንዲኖሩ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ነፃ ፡ ለመሆን ፡ ወይም ፡ ንጉሥ ፡ ከነእ
ንደራሴው ፡ ላለበት ፡ ለጐንደሩ ፡ መንግሥት ፡ እንኳ ፡ ለመገበር ፡ አልተቻላቸ
ውምና ፡ ቂማቸውን ፡ ከልብ ፡ አልተዉም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ከነዚህ ፡ ከሁለቱ፡
ደጃች ፡ ካሣይ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሸፍተው ፡ ተማረኩና ፡ በአምባ ፡ ፊዛን ፡ ታስ
ረው ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ እስኪማርኳቸው፡
ድረስ ፡ በዚሁ ፡ አምባ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

※ ※ ※

ደጃች ፡ ውቤ ፡ በሰሜን ፡ እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ጦርነት ፡ ሲታወኩ ፡ በበጌም
ምድር ፡ ለራስ ፡ ዐሊ ፡ የሰላም ፡ ግዛት ፡ ሆኖላቸው ፡ ሕዝቡ ፡ በመላው ፡
እስከ ፡ ወሎ ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ በጸጥታና ፡ በፍራት ፡ ይገዛላቸው ፡ ነበር ።
ዳሞትና ፡ ጐጃምም ፡ ተገዥነቱን ፡ አምኖ ፡ ሰላም ፡ ሆኗል ። በዙፋኑም ፡ ላይ ፡
ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ ጊጋር ፡ በራስ ፡ ማርዬ ፡ ጊዜ ፤ ኢያሱ ፡
፩ኛ ፡ በራስ ፡ ዶሪ ፡ ጊዜ ፡ ነበሩ ። ኢያሱም ፡ እንደዚሁ ፡ በራስ ፡ ዐሊ ፡ ጊዜ፡
ጥቂት ፡ ዘመናት ፡ ቈይተው ፡ ነበር ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ልንገሥ ፡ በመባባል ፡ በሕይወት ፡ ባሉት ፡ የነገ
ሥታት ፡ ዘር ፡ መከከል ፡ ክርክርና ፡ ብጥብጥ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በመጨረሻ ፡ ዐፄ
ሣህሉ ፡ (ሣህለ ፡ ድንግል) ፡ ነገሡና ፡ ከተማው ፡ መርጋት ፡ ጀምሮ ፡ ነበር ፤
ነገር ፡ ግን ፡ የአዘዞ ፡ መነኰሳት ፡ (ተዋሕዶዎች) ፡ አልወደዷቸውም ፡ ነበርና ፡
ራስ ፡ ዐሊን ፡ ለምነው ፡ ከዙፋን ፡ እንዲወርዱ ፡ አደረጓቸው ። ራስ ፡ ዐሊም ፡
ከመነኰሳቱ ፡ ተመከክረው ፡ ጣና ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ በምጽራሐ ፡ ይቀመጡ ፡

የነበሩትን ፡ ዐፄ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስን ፡ አምጥተው ፡ አነገሡዋቸው ። ርሳቸውም፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ስለ ፡ አጠረ ፡ በነገሡ ፡ በ፫ኛው ፡ ወር ፡ ሞቱ ። በዙፋኑም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ነግሠው ፡ የነበሩት ፡ ሣህለ ፡ ድንግል ፡ እንደገና ፡ ወጥተው ፡ ተቀመጡ ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ዕጓለ ፡ አንበሳ ፡ የተባለ ፡ መነኵሴ ፡ በቀሃ ፡ ወንዝ ፡ በኩል ፡ መጥቶ ፡ ጥሩምባ ፡ እያስነፋ ፡ ነግሻለሁ ፡ ሲል ፡ ዐዋጅ ፡ ነገረ ፤ ስሜም፡ ቴዎድሮስ ፡ ነው ፤ ግዛቴም ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ ይደርሳል ፤ ዘመነ ፡ መንግሥቴም ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ያስወራ ፡ ጀመር ። እንደዚህም ፡ እያለ ፡ ጐንደር ፡ ከተማ ፡ ገባ ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ ንጉሡ ፡ ሣህለ ፡ ድንግል ፡ አሲዘው ፡ በጉባኤ ፡ በሰይፍ ፡ አንገቱን ፡ አስቈረጡት ፡ ይባላል ። በሌላው ፡ ግዛትና ፡ አስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ የሌላቸው ፡ ዐፄ ፡ ሣህለ ፡ ድንግል ፡ ዙፋን ፡ ተከራክረያቸውን ፡ መነኵሴ ፡ ብቻ ፡ ለመግደል ፡ ሥልጣን ፡ አገኙ ። ከዐፄ ፡ ሣህሉ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ዮሐንስ ፡ ፫ኛ ፡ ነገሡ ፡ ርሳቸውም ፡ የራስ ፡ ዐሊ ፡ እናት ፡ የእቴጌ ፡ መነን ፡ ባለቤት ፡ መሆናቸው ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፺፪ ።

## የራስ ፡ ዐሊና ፡ የደጃች ፡ ውቤ ፡ ጦርነት ።

በራስ ፡ ዐሊ ፡ ምስፍንና ፡ ዘመን ፡ በሸዋ ፡ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፤ በጐጃምና ፡ በዳሞት ፡ ደጃች ፡ ጐሹና ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፤ በደንቢያ ፡ ደጃች ፡ ክንፉ፡ በስሜንና ፡ በትግሬ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ የየግል ፡ አገራቸውን ፡ ያስተዳድራሉ ። ከነዚህ ፡ ውስጥ ፡ ዋናው ፡ የመንግሥቱ ፡ እንደራሴ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ በግዛትና ፡ በሥልጣን ፡ ይጣሉ ፡ የነበሩት ፡ ከደጃች ፡ ውቤ ፡ ጋራ፡ ነበር ። ራስ ፡ ዐሊ ፡ ዋና ፡ የመንግሥቱ ፡ እንደራሴ ፡ እንደ ፡ መሆናቸው ፡ መጠን ፡ ከነራስ ፡ ማርዬ ፡ ጀምሮ ፡ የተላለፈ ፡ የወሎ ፡ የየጁ ፡ የራያና ፡ ያዘቦ ፡ ይልቁንም ፡ የበጌምድር ፡ የተደራጀ ፡ ደንበኛ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ነበራቸው ። ደጃች ፡ ውቤ ፡ ደግሞ ፡ በበኩላቸው ፡ ክባት ፡ ግዛታቸው ፡ ከስሜን፡ ያዘጋጁት ፡ ጦር ፡ አዲስ ፡ ከሚገዙት ፡ ያፄ ፡ ነጋሪት ፡ አገር ፡ ከሚሆነው ፡ ከትግሬና ከሐማሴን ፡ የሰበሰቡት ፡ ጦር ፡ የሚያኰራቸው ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ በናይብ ፡ ግዛትና ፡ በምጥዋ ፡ በኩል ፡ ባሸከራቸው ፡ በብላታ ፡ ኮከቤ ፡ አማካይነት ፡ ከቱርኩ ፡ ናይብ ፡ ግንኙነት ፡ እያደረጉ ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ ሽቀጥ፡ ስለሚያገኙ ፡ በሀብትም ፡ በጦር ፡ መሣሪያና ፡ በወታደርም ፡ በኩል ፡ ስለ ፡ ደረጁ ፡ የራስ ፡ ዐሊን ፡ ሥልጣን ፡ ለመቃወም ፡ ብርቱ ፡ ባላጋራ ፡ ሆነው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተገኝተው ነበር ።

ከራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴና ፡ ከትልቁ ፡ ራስ ዐሊ ፡ ጀምሮ ፡ ትግሬዎቹም፡ አማሮቹም ፡ የሴሩ ፡ ኀንጕልን ፡ ዘር ፡ ከጐንደር ፡ ሥልጣን ፡ አስጥተው ፡ ለመ

ያዝ ፡ የሚያደርጉትን ፡ የጦርነት ፡ ክርክር ፡ ርሳቸው ፡ እፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ ነበራቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ምኞታቸው ፡ በትልቅ ፡ ጦር ነትና ፡ በመጨረሻ ፡ በሚገኝ ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ እስኪረጋገጥ ፡ ድረስ ፡ ለራስ ፡ ዐሊ ፡ እንደ ፡ ታዛዥ ፡ እየገበሩ ፡ እንደ ፡ ዘመድም ፡ ልጃቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ኂሩትን ፡ ድረው ፡ የወዳጅነትና ፡ የመተማመን ፡ መልክ ፡ እያሳዩ ፡ ቈዩ ። በሌላው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ የጐንደርን ፡ እንደራሴነት ፡ ለመቀማት ፡ የሚ ችሉበትን ፡ ዘዴ ፡ ማዘጋጀታቸውን ፡ ይቀጥሉ ፡ ነበር ። እንዲያውም ፡ አሳባቸው፡ በእንደራሴነት ፡ ብቻ ፡ ሳይወሰን ፡ ዘውድ ፡ ጭነው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለመ ሆን ፡ ምኞት ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ አለቃ ፡ ሀብተ ፡ ሥላሴን ፡ ወደ ፡ ካይሮ ፡ ልከው ፡ የሚቀበሎዋቸውን ፡ ጳጳስ ፡ አቡን ፡ ሰላማን ፡ አስመጡ ። የሚነግሡበት ንም ፡ የደርስጌ ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስኪምፔር ፡ ዊልሔልም ፡ (Schimper Wilhelm) ፡ በሚባል ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መሐንዲስ ፡ መሪነት ፡ ባማረ፡ ሥራ ፡ አሠሩ ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሥራና ፡ ምኞት ፡ ከራስ ፡ ዐሊ ፡ ዠሮና ማስተ ዋል ፡ ሊያመልጥ ፡ አልቻለም ፡ ቢሆንም፡ የሚስታቸውን ፡ አባት ፡ በዚህም፡ላይ፡ የበቃ፡ ምክንያት ፡ ሳያገኙ ፡ በግንጋኜ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ሊዋጉ ፡ አልፈለጉም ። ስለዚህ ፡ በበኩላቸው ፡ የጦር ፡ ወታደራቸውንና ፡ መሣሪያቸውን ፡ ብቻ ፡ እያደራጁ ፡ ሁለቱም ፡ በውስጥ ፡ እየተጠራጠሩ ፡ ላዩን ፡ እየተዛመዱ ኑሯቸውን ፡ ቀጠሉ ። በመ ጨረሻ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ኃይላቸውን ፡ ሲተማመኑ ፡ ጠነርቱን ፡ ለመዠመር ፡ ምክን ያት ፡ በመፈለግ ፡ የተለመደውን ፡ ግብር ፡ ከለከሉ ። ልጅንም ፡ ኂሩትን ፡ ላክልኝ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ መልእክት ፡ ላኩ ፤ ራስ ፡ ዐሊም ፡ አልክም ፡ ብለው ፡ መልስ ፡ ሰጡ ። በዚህ ፡ መካከል ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ የደጃች ፡ ውቤን ፡ ወገኖች ፡ እነደጃች፡ መርሶንና ፡ ከትግሬ ፡ ባላባቶችም ፡ ውስጥ ፡ ለማስከዳት ፡ ይጥሩ ፡ ዠመር ። ደጃች ፡ ውቤ ፡ ደግሞ ፡ ከራስ ፡ ዐሊ ፡ ጋራ ፡ ያሉትን ፡ የጐጃሙን ፡ ገዥ ፡ ደጃች ፡ ጐሹን ፡ ከራስ ፡ ዐሊ ፡ ነጥለው ፡ ወደ ፡ ራሳቸው ፡ ለመሳብ ፡ ተጣጣሩ ። ከራስ ፡ ዐሊ ፡ ተለይ ተኸ ፡ ወደኔ ፡ ብትመጣ ፡ ልጄን ፡ ኂሩትን ፡ ከራስ ፡ ዐሊ ፡ ነጥቄ ፡ ላንተ ፡ ነው ፡ የም ድራት ፡ ከበጌምድርም ፡ ግዛት ፡ በያዝኸው ፡ በጐጃም ፡ ላይ ፡ ትጨምራለኽ ፡ እያሉ ፡ በምልክት ፡ ያባብሏቸው ፡ ዠመር ። ከብዙ ፡ ማባበልም ፡ በኋላ ፡ ደጃች ፡ ጐሹ ፡ ልባ ቸውን ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፤ ሰውነታቸውን ፡ ከራስ ፡ ዐሊ ፡ ጋራ ፡ አድርገው ፡ ብዙ፡ ቀን ፡ በማመንታት ፡ ሰነበቱ ። የእቴጌ ፡ መነን ፡ ባለቤት ፡ የነበሩት ፡ ንጉሥ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስም ፡ በራስ ፡ ዐሊና ፡ በናታቸው ፡ በእቴጌ ፡ መነን ፡ ሥልጣን ፡ ብዛት ፡ በርሳቸው ማነስ ፡ ቅርታቸውን ፡ በልባቸው ፡ ይዘው ፡ኖሮ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ አሳባቸውን ፡ ከደ ጃች ፡ ውቤ ፡ ጋራ ፡ አደረጉ ። እንደዚህም ፡ ሆኖ ፡ የፖለቲካው ፡ ዘዴ ፡ ሥራውን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከቀጠለ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ያስመጧቸውን ፡ ጳጳስ ፡ አቡነ ፡ ሰላማን ፡ አስከትለው ፡ በሺሕ ፡ ፲፰፻፴፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ መጡ ። መምጣታቸውንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡

ውስጡን ፡ ከደጃች፡ውቤ ፡ ጋራ፡የተስማሙት ፡ ደጃች ፡ ጐሹ ፡ ዘረው ፡ ለደጃች፡ውቤ ገቡ ። ንጉሡም ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አዳራሽ ፡ አምልጠው ፡ ለደጃች ፡ ውቤ ፡ ገቡ ፤ (1) ስለዚህ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ደጃች ፡ ጐሹንና ፡ ንጉሡን ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስን ፡ እንደዚሁም ፡ ጳጳሱን ፡ አባ ፡ ሰላማን ፡ ይዘው ፡ መነሣታቸው ፡ ራስ ፡ ዐሊንና ፡ ወገኖቻቸውን ፡ እሥጋት ፡ ላይ ፡ መጣሉ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ቢሆንም ፡ ደጃች ፡ ሙቤና ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ ደንበኛውን ፡ ጦርነት ፡ ገጠሙ ። አቡነ ፡ ሰላማም ፡ ከራስ ፡ ዐሊ ፡ ጋራ ፡ ሆነኽ ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ የወጋኽ ፡ ገዝቻለሁ ፡ ስላሉ ፡ በራስ ፡ ዐሊ ፡ ወገን ፡ በሥጋት ፡ ላይ ፡ ሥጋት ፡ ተጨመረ። ቢሆንም ፡ ከራስ ፡ ዐሊ ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ ግዝትና ፡ ስብከት ፡ የማይፈታው ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ ከደጃች ፡ ውቤ ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ ገጥሞ ፡ በዠግንነት ፡ ይዋጋ ፡ ዠመር ። የደጃች ፡ ውቤም ፡ የስሜንና ፡ የትግሬ ፡ ጦር ፡ በርትቶ ፡ እየተዋጋ ፡ ብዙ፡ ሰዓት ፡ መከተ ፤ የደጃች ፡ ውቤም ፡ ጦር ፡ በፍጹም ፡ በእግረኛ ፡ ጦር ፡ የማይበገር ፡ መሆኑም ፡ ስለ ፡ ታወቀ ፡ ከኋላ ፡ ተጠባባቂ ፡ የነበረው ፡ የራስ ፡ ዐሊ ፡ የፈረሰኛ ፡ ጦር ፡ ተደባልቆ ፡ ይዋጋ ፡ ዠመር ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የደጃች ፡ ውቤ ፡ ጦረኛ፡ የራስ ፡ ዐሊን ፡ የፈረሰኛ ፡ ወታደር ፡ በነፍጥ ፡ እየመታ ፡ ሲጥለው ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ይመለከቱ ፡ ነበርና ፡ ከእንግዴህ ፡ ወዲያ ፡ ምን ፡ ተስፋ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ከጦርነቱ ፡ ቦታ፡ ሸሽተው ፡ ወደ ፡ ላስታ ፡ ሄደው ፡ በዋድላ ፡ ገዳም ፡ ገብተው ፡ ተቀመጡ ።

ደጃች ፡ ውቤም ፡ የራስ ፡ ዐሊ ፡ ፈረሰኛ ፡ ወታደር ፡ የርሳቸውን ፡ ጦር ፡ በነፍጥም ፡ በጐራዴም ፡ እየመታ ፡ ሲጥለው ፡ እያዩ ፡ ይኸንኑ ፡ እመሰለ ፡ ሥጋት ፡ ላይ፡ ነበሩና ፡ ድል ፡ የሆኑ ፡ መስሏቸው ፡ ሸሹ ። እነዚህም ፡ ሁለቱ ፡ ታላላቅ፡ ሰዎች ፡ የጦርነት ፡ ድል ፡ ወደ ፡ ማን ፡ መሆኑን ፡ ፍጻሜውን ፡ ለመጠበቅ ፡ እቅቷቸው ፡ መሸሻቸውን ፡ የሰማ ፡ ሁሉ ፡ ሳቀባቸው ። በኋላ ፡ ግን ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ የራስ ፡ ዐሊን ፡ መሸሽ ፡ እርግጠኛውን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እንስራርተው ፡ አጠገባቸው ፡ ያለውን ፡ ጥቂት ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ተመለሱና ፡ ከራስ ፡ ዐሊ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው፡ ድል ፡ አደረጉ ። የደብረ ፡ ታቦርንም ፡ ከተማ ፡ ያዙ ። በራስ ፡ ዐሊም ፡ አዳራሽ ፡ ገብተው ፡ ካቡነ ፡ ሰላማና ፡ ከመኳንንቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ ደስታ ፡ ሲያደርጉ ፡ ዐሊጋዝ፡ የተባለው ፡ ደፋር ፡ የራስ ፡ ዐሊ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ጭፍሮቹን ፡ አስከትሎ ፡ እጁን ፡ ለመስጠት ፡ መሣሪያውንም ፡ ለማስረከብ ፡ የመጣ ፡ አስመስሎ ፡ አዘነጋና ፡ በደጃች፡ ውቤ ፡ አደጋ ፡ ጥሎ ፡ ማረከና ፡ አሰራቸው ። ዐሊጋዝም ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ እንዳሰረ፡ ለመንገርና ፡ ለማስረከብ ፡ የበላዩን ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ ቢፈልግ ፡ ቢያስፈልግ ፡ እርሳቸው ፡ በዋድላ ፡ ገዳም ፡ ስለ ፡ ተደበቁ ፡ ሊያገኛቸው ፡ አልቻለም ። በዚሁም ፡ ነገር ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ያልተገረመና ፡ ያልሣቀ ፡ አለመኖሩን ፡ ከዚህ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ የ፪ ፡ ሰዎች ፡ ንግግር ፡ ያስረዳናል ።

የዚህን ፡ የጦርነት ፡ ወሬ ፡ ያልሰማ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የሰማውን ፡ ሰውዬ ፡ እመንገድ ፡ አግኝቶ ፤

(1)ኩልበ ፡ በ፪ኛው ፡ ቮሊ.ም ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፬ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፫ ።

እባክኽ ፡ የራስ ፡ ዐሊና ፡ የደጃች ፡ ውቤ ፡ ጦርነት ፡ በምን ፡ አለቀ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

—ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ተማርከው ፡ ታሰሩ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ደግሞ፡ ሸሹ ፡ ሲል ፡ መለሰለት ።

–እረ ፡ እባክኽ ፡ በወግ ፡ (በሚገባ) ፡ አድርገኽ ፡ አውራኝ ፡ ብሎ ፡ እንደገና ፡ ቢጠይቀው ፡ –እነሱ ፡ ራሳቸው ፡ በወግ ፡ ያልሆኑት ፡ እኔ ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ በወግ፡ ላውራኽ ፡ አለውና ፡ እየሣቀበት ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ፤ ያኛውም ፡ እየተገረመ፡ ሄደ ፡ ይባላል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዐሊጋዝ ፡ ጌታው ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ያሉበትን ፡ አሰልሎ ፡ ድሉ ፡ የኛ፡ ነው ፡ ጠላትዎንም ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ማርኬ ፡ በእጄ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ልኮ ፡ ነበርና ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ይኸን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከተደበቁበት ፡ ከዋድላ ፡ ገዳም ፡ ተነሥተው ፡ በወጡ ፡ ባ፲፫ኛው ፡ ቀን ፡ ተመልሰው ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ገቡና ፡ ከሚስታቸው ፡ ከወይዘሮ ፡ ጓሉት ፡ ተገናኙ ። የጐጃሙ ፡ ደጃች ፡ ጐሹ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ በሸሹበትና ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ በገቡበት ፡ መካከል ፡ ከደጃች ፡ ውቤ ፡ ጋራ ፡ ቀድሞ ባገኙት ፡ ተስፋ ፡ መሠረት ፡ ከወይዘሮ ፡ ጓሉት ፡ ተገናኝተው ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በኋላ ፡ ግን ፡ የራስ ፡ ዐሊ ፡ ጦር ፡ በዐሊጋዝ ፡ እየተመራ ፡ መጥቶ፡ በደጃች ፡ ውቤ ፡ ያጥቂነት ፡ ሥራ ፡ መፈጸሙን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ የነገሩ ፡ አያያዝ ፡ ስላላማራቸው ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ትተው ፡ አገራቸው ፡ ጐጃም ፡ ገብተው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ተቀመጡ ።

እንግዴህ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ከዋድላ ፡ መጥተው ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ እስረኛውን ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ይገድሏቸዋል ፡ ወይም ፡ ያስሯቸዋል ፡ እየተባለ ፡ ሲፈራ ፡ አሸናፊው ፡ ራስ ፡ ዐሊና ፡ ተሸናፊው ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ በድርድር ፡ መታረቃቸው ፡ ተሰማ ፤ ዕርቁም ፡ የተፈጸመው ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

ሀ–ደጃች ፡ ውቤ ፡ ሊያነግሡዋቸው ፡ ከግብጽ ፡ አገር ፡ ያስመጧቸውን ፡ ጳጳሱን፡ አቡነ ፡ ሰላማን ፡ ለራስ ፡ ዐሊ ፡ ለመተው ።

ለ–ወደ ፡ ግዛታቸው ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ የተለመደውን ፡ ግብር ፡ ሊልኩ ።

ራስ ፡ ዐሊ ፡ ይኸን ፡ ግዴታ ፡ በሽማግሌ ፡ ፊት ፡ ካስገቡ ፡ በኋላ ፡ የቀድሞ ፡ ግዛታቸውን ፡ በሙሉ ፡ መርቀው ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ በሰላም ፡ አሰናበቷቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ መርሶ ፡ የሚባሉ ፡ የደጃች ፡ ውቤ ፡ ወንድም ፡ (1) የስሜንን፡ ባላገር ፡ ለጦርነት ፡ ቀስቅሰው ፡ አላስገባም ፡ ብለው ፡ ውጊያ ፡ ገጠሙ ፤ ራስ ፡ ዐሊም፡ ቢልኩባቸው ፡ እምቢ ፡ አሉ ። ስለዚህ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ግዛታቸውን፡ መርቀው ፡ መላክ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ያንኑ ፡ የታወቀውን ፡ የጦር ፡ አለቃቸውን ፡ ዐሊጋዝን ፡ ልከው ፡ ደጃች ፡ መርሶን ፡ አስወግተው ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ በቀድሞ ፡ ግዛታቸው ፡ ገብተው ፡ እንዲደላደሉ ፡ ረዷቸው ። ደጃች ፡ መርሶም ፡ ተሸንፈው ፡ በዋልድባ ፡ ገዳም ፡ ገብተው ፡ ተቀመጡ ።

(1)ደጃች ፡ መርሶ ፡ ባባታቸው ፡ በደጃች ፡ ኀይሉ ፡ ማርያም ፡ በኩል ፡ የደጃች ፡ ውቤ ፡ ወንድም ፡ እናታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ጓሉት ፡ ናቸው ። ደጃች ፡ ውቤ ፡ ግን የተወለዱት፡ ከንዲት ፡ ከጃናሞራ ፡ (ወገራ)፡ ሴት፡ ነው ።

እከተማቸው ፡ እደብረ ፡ ታቦር ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ ጠብ ፡ አጫሪ ፡ ሆነው ፡ ወግተው ፡ እመሸሽ ፡ ያደረሷቸው ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ በእጃቸው ፡ ከወደቁላቸው ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ቸርነት ፡ ማሳየታቸው ።

የልብ ፡ ደግነት ፡ ነውን ።

ወይስ ፡ ባለቤታቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ኂሩትን ፡ ለማስደሰት ፡ ብለው ፡ ይሆን ፤

ወይስ ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ባስር ፡ ወይም ፡ ብገድል ፡ የትግሬና ፡ የስሜን ፡ ባላባቶች ፡ በያለበት ፡ እየተነሡ ፡ ከርሳቸው ፡ የበለጠ ፡ ማስቸገራቸው ፡ አይቀርምና ፤ ብዙውን ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ እያስገዙ ፡ ዝም ፡ ለማሰኘት ፡ ይሆን ፤ ፍርዱን ፡ ላንባቢ ፡ እንተዋለን ።

በጠቡ ፡ ጊዜ ወደ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ተደርበው ፡ የነበሩትን ፡ የናታቸውን ፡ ባለ ቤት ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስንም ፡ መልሰው ፡ በዙፋናቸው ፡ እንዲቀመጡ ፡ ፈቀዱላቸው ። ደጃች ፡ ጐሹ ፡ ግን ፡ ቀርበው ፡ ባለፈው ፡ ጥፋታቸው ፡ ይቅርታ ፡ ጠይቀው ፡ ሳይታ ረቁ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ አገራቸው ፡ ገብተው ፡ በመቀመጣቸው ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ደብረ ፡ ታቦርን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ዋድላ ፡ በሄዱበት ፡ ጊዜ ፡ ባለቤታቸ ውን ፡ ወይዘሮ ፡ ኂሩትን ፡ አገባሁ ፡ ብለው ፡ በመድፈራቸው ፡ ምክንያት ፡ ቢወጉ ፡ ይገባቸዋል ፡ ተባለና ፤ በዚሁ ፡ ዓመት ፡ በሺሕ ፡ ፰፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጦር ፡ ሄዶ ፡ ሲወ ጋቸው ፡ ከረመና ፡ ርሳቸውም ፡ በመጨረሻ ፡ ታረቁና ፡ ሰላም ፡ ሆነ ።

ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ደጃች ፡ ውቤና ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ በሰላም ፡ እስከ ፡ ፰ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ኖሩ ። ባ፰ኛው ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ጦርነት ፡ ቀስቅሰው ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ዓመት ድረስ ፡ የደፈጣ ፡ ጦርነትና ፡ ግጭት ፡ ሲያደርጉ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ሲታረቁ ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፰፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ደረሱ ። ራስ ፡ ዐሊ ፡ የበላይ ፤ ደጃች ፡ ውቤ ፡ የበታች ፡ መስለው ፡ እኝህም ፡ ቢያስገብሩ ፤ እኛም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢገብሩ ፡ ሁለቱም ፡ ኀይለኞች ፡ በመሆናቸው ፡ አንዱ ፡ አንዱን ፡ ሊያሸንፈውና ፡ ለዘለቄታ ፡ ሊደመስሰው ፡ አልቻለም ። በመካከሉ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ሆነና ፡ ካሣ ፡ (ቴዎድሮስ) ፡ ተነሥተው ፡ ሁለቱንም ፡ አጥፍተው ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ እነራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፤ እነደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ እነራስ ፡ መርድ ፤ እነደጃች ፡ ዘውዴ ፡ ደክመው ፡ ያል ሆነላቸውን ፡ ዘመነ ፡ ምስፍና ፡ አስወግደው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትን ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ገና ፡ በጥንቱ ፡ በነኢያሱ ፡ በነበካፋ ፡ ዐይነት ፡ መሥርተው ፡ አዲስ ፡ የታሪክ ፡ ጊዜ ፡ ከፈቱ ። የራሳቸውንም ፡ የጦርነት ፡ እርምጃ ፡ ከትግሬም ፤ ከጐጃምም ፤ ከበጌምድርም ፡ ከሸዋም ፡ የተነሣው ፡ የጦር ፡ መሪ ፡ ሊያግደው ፡ አልቻለም ። ስለዚህ ፡ የርሳቸውን ፡ ታሪክ ፡ ለማስታወስ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ወደ ፡ ተጻፈው ፡ «ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ» ፡ ወደ ፡ ሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ከመተላለፋችን ፡ በፊት ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ጣልቃ ፡ እየገባ ፡ ሳይጻፍ ፡ የቀ ረውን ፡ የሸዋን ፡ መሳፍንት ፡ ታሪክ ፡ አሁን ፡ በመደዳው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰን ፡ እንመልከት ።

## ምዕራፍ ፡ ፺፫ ።

## የሸዋ ፡ ባላባቶች ።

አንዳንድ ፡ ንጉሥ ፡ በገናንነት ፡ ወይም ፡ በዕድል ፡ አንድ ፡ ለታሪክ ፡ መነሻ የሚሆን ፡ ሥራ ፡ ራሱ ፡ ሲሠራ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ አጋጣሚ ፡ በጊዜው ፡ በራሱ ፡ ሲደርስበት ፡ ስሙ ፡ የታሪክ ፡ መነሻና ፡ መክፈያ ፡ ሆኖ ፡ ይቀራል ። ለኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ከሦር ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ከሰሎሞን ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክን ፡ ወልዳ ፡ ከርሷ ፡ ወዲህ ፡ የወንድ ፡ ንጉሥ ፡ ሆኖ ፡ በመገመሩ ፡ ሰሎሞን ፡ እንደ ፡ መገመሪያ ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ነገሥታት ፡ የዘር ፡ ግንድ ፤ ለኢትዮጵያ ፡ የሥርወ ፡ መንግሥት ፡ ገማሪ ፡ በመሆኑ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የተከተሉትን ፡ «የሰሎሞን ፡ ተከታዮች ፤ ሰሎሞናዊ ፡ ዘሮች» ፡ መባል ፡ ተለመደ ።

ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ሺሕ ፡ ፪፻፸ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ላይ ፡ መንግሥት ፡ ከተዘዋወረበት ፡ ከዛጔ ፡ ዘር ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ስለ ፡ ተቀበለና ፡ በሸዋ ፡ መሬት ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ለገዙት ፡ ተከታዮቹ ፡ ለነዐምደ ፡ ጽዮን ፡ ለነሰይፈ ፡ አርዓድ ፡ ለነዳዊት ፤ ለነዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ አባት ፡ ሆኖ ፡ በመገኘቱ ፡ የይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ስም ፡ የታወቀ ፡ ሆነ ።

በመጨረሻ ፡ በዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ተነሥቶ ፡ ከሸዋ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ አሸንፎ ፡ ካባረረ ፡ በኋላ ፡ ግራኝ ፡ ደግሞ ፡ ባፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ልጅ ፡ ባፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ተሸንፎ ፡ ከጠፋ ፡ በኋላ ፡ የዐፄ ፡ ልብነ ድንግል ፡ ዘሮች ፡ የጐንደርንም ፡ የሸዋንም ፡ የጐጃምንም ፡ ነጋሢነት ፡ ይዘው ፡ ስላስተዳደሩ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ አባት ፡ በመሆናቸው ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ የግራኝ ፡ ወረራ ፡ በዘመናቸው ፡ ስለተፈጸመ ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ስማቸው ፡ የታወቀ ፡ ሆኖ ፡ ቀረ ።

፨ ፨ ፨

እንግዲህ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የቈየው ፡ የጽሑፉም ፡ የቃሉም ፡ ታሪክ ፡ እንደሚነግረን ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በግራኝ ፡ ጦር ፡ ተሸንፈው ፡ በሺሕ ፡ ፭፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግድም ፡ ሸዋን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ አማራ ፡ ሣይንት ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ ቀጥሎ ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ቤተ ፡ ሰባቸውን ፡ ይዘው ፡ ሲሄዱ ፡ ያዕቆብ ፡ የሚባሉትን ፡ አንደኛውን ፡ ልጃቸውን ፡ መንዝ ፡ ላይ ፡ በተለይ ፡ ገሆር ፡ ከሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ባላጋሮቹን ፡ አደራ ፡ ብለው ፡ ልብሰ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ሰጥተው ፡ ትተዋቸው ፡ ሄዱ ።

ስለዚህ ፡ ያዕቆብ ፡ እስፈሪው ፡ የግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ጦርነት ፡ በዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ጊዜ ፡ ተሸንፎ ፡ እስኪወገድ ፡ ድረስ ፡ የዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ልጅ ፡ መሆናቸውን ፡ ሳይገልጹ ፡ በሰላይም ፡ እንዳይያዙ ፡ በመንዝ ፡ ውስጥ ፡ ከንዱ ፡ ወረዳ ፡ ወደ ሌላው ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ። በመንዝም ፡ ሳሉ ፡ ከጐንደር የመጣችውን ፡ ንግሥተ ፡ አዜብ ፡ የምትባለዋን ፡ አግብተው ፡ አቤቶ ፡ ወይም ፡ ገራም ፡ ፋሲልን ፡ አቤቶ ፡ ሥግው ፡ ቃልን ፤ አቤቶ ፡ ተዝካረ ፡ ቃልን ፤ ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ማርያምን ፡ ወለዱ ።

በጐንደር ፡ መንግሥት ፡ በቀጥታ ፡ ከዔ፡ ልብነ ፡ ድንግል፡ የሚወለዱት፡ በፊት ፡ ገላውዴስ ፡ ቀጥሎ ፡ ሚናስ ፡ ከዚያም ፡ የሚናስ ፡ ልጅ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ከርሳቸውም ፡ በኋላ ፡ ዘድንግልና ፡ ያዕቆብ ፡ (የሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ልጅ ፡ )ነገሡ ። በመጨረሻ ፡ ደግሞ ፡ በምዕራፍ ፡ ፳፺ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደተጻፈው ፡ የኳሁ ፡ የልብነ ፡ ድንግል ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጅ ፡ ገራም ፡ ፋሲል ፡ ከጐጃሟ ፡ ባላባት ፡ ከወይዘሮ ፡ ሐመልማል ፡ ሱስንዮስን ፡ ወልደው ፡ የርሳቸው ፡ ዘር ፡ ከሱስንዮስ ፡ ዠምሮ ፡ እየተከታተለ ፡ በጐንደር ፡ እስከ ፡ ተፍጻሜተ ፡ መንግሥት ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ድረስ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ መግዛቱን ፡ ባለፉት ፡ ምዕራፎች፡ የተጻፈው ፡ ሁሉ ፡ ያስረዳል ።

የፋሲል ፡ እናት ፡ ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ማርያምም ፡ ለጐጃም ፡ ባላባት ፡ ግንድ፡ ናቸው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ከገራም ፡ ፋሲልና ፡ ከወይዘሮ ፡ ሐመልማል ፡ የሚወለዱ ፡ ወንዶችም ፡ ሴቶችም ፡ በጐጃምና ፡ በዳሞት ፡ እየገቡ ፡ ዘራቸውን ፡ የመትከላቸው ፡ ታሪክ ፡ ብዙ ፡ ነው ። ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ እነታላቅ ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ መውረዳቸው ፡ ከርሳቸውም ፡ ራስ ፡ መርድና ፡ ወይዘሮ ፡ ድንቅነሽ ፡ መወለዳቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

አሁን ፡ ደግሞ ፡ ለዚህ ፡ ለያዝነው ፡ ለሸዋ ፡ ባላባቶች ፡ ምዕራፍ ፡ መነሻ ፡ የሚሆነው ፡ የአቤቶ ፡ ፋሲልና ፡ የአቤቶ ፡ ተዝካረ ፡ ቃል ፡ የወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ማርያም፡ ወንድም ፡ አቤቶ ፡ ሥግወ ፡ ቃል ፡ ነው ። እርሱም ፡ አቤቶ ፡ ወረደ ፡ ቃልን ፤ አቤቶ፡ ወረደ ፡ ቃልም ፡ አቤቶ ፡ ልብሰ ፡ ቃልን ፤ አቤቶ ፡ ልብሰ ፡ ቃልም ፡ የአጋንቻውን የደጃች ፡ ፋሬስን ፡ ልጅ ፡ ወይዘሮ ፡ ሰንበልትን ፡ አግብቶ ፡ አቤቶ ፡ ነጋሢን ፡ ይወልዳል ። አቤቶ ፡ ነጋሢም ፡ ለሸዋ ፡ መሳፍንት ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ መዠመሪያ ፡ ምሥራች፡ የሚቈጠሩት ፡ ናቸው ።

ቢሆንም ፡ ይህ ፡ የዘሩን ፡ አወራረድ ፡ ይገልጽልናል ፡ እንጂ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ የአቤቶ ፡ ሥግወ ፡ ቃል ፡ ተከታዮች ፡ በጊዜያቸው ፡ በየሥፍራቸው ፡ ከመቀመጥ በቀር ፡ በያለበት ፡ ያሉትን ፡ የሸዋን ፡ ባላባቶች ፡ ባንድነት ፡ ሰብስበው ፡ ለመግዛት ፡ አልቻሉም ። ሸዋ ፡ ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ የበላይ ፡ አለቃ ፡ ስለሌለው ፡ በያውራጃው ፡ ባላባቶችና ፡ ቀንደኞች ፡ እየተነሡ ፡ አገሩን ፡ ለብቻ ፡ ተከፋፍለው ፡ በወሰንና ፡ በርስት ፡ እየተጣሉ ፡ እየተዋጉ ፡ ኖሩ ። የነዚህንም ፡ ዝርዝር ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በምዕራፍ ፡ ፺፩ ፡ ውስጥ ፡ ጠቅሰነው ፡ የነበረውን ፡ አሁንም ፡ ሥፍራው ፡ ስለሆነ ፡ ደግመን ፡ አገሩንና ፡ የመዠመሪያዎቹን ፡ ባላባቶች ፡ ስም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንጠቅሳለን ።

፩ ፤ በአንጾኪያ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ ዘሚካኤል ፡ (ዘሚ)
፪ኛ ፤ በኤፍራታ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ።
፫ኛ ፤ በግድም ፡ ለታ ፡
፬ኛ ፤ በመንዝ ፡ ማማ ፡
፭ኛ ፤ በግማሹ ፡ መንዝ ፡ ባላምባራስ ፡ ላሎ ፡

፮ኛ ፡ በግሼ ፡ አውሳብዮስ ፡
፯ኛ ፡ በዶባ ፡ ጌታቸው ፡
፰ኛ ፡ በደብብ ፡ ጺጋ
፱ኛ ፡ በምሑይ ፡ አዛዥ ፡ መሒዲ ፡
፲ኛ ፡ በመርሐ ፡ ቤቴና ፡ በክራ ፡ ወልዱ ፡
፲፩ኛ ፡ በሞረት ፡ ጥዱ
፲፪ ፡ በተጉለት ፡ ይገባዋል ፡
፲፫ ፡ በወግዳ ፡ ሕርያቆስ ፡ ናቸው ።

እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ባላባቶች ፡ አብዛኞቹ ፡ ከነጋሢ ፡ በፊት ፡ ጥቂቶቹ ፡ ከነጋሢ ፡ በኋላም ፡ የነበሩ ፡ ናቸው ፤ እነዚህ ፡ የበላይ ፡ ሳይኖርባቸው ፡ ለየብቻ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እየተዋጉ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ የሚል ፡ በየመጽሐፉ ፡ ይገኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ ባለፈው ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በምዕራፍ ፡ ፴፱ የወሬኛ ፡ ይሥሐቅ ፡ አሸፋፈት ፡ በተተረከበት ፡ ውስጥ ፡ ይኸው ፡ ወሬኛ ፡ ይሥሐቅ ፡ በጐጃም ፡ ከተሸነፈ ፡ በኋላ ፡ ከጐጃም ፡ በደራ ፡ በኩል ፡ ተሻግሮ ፡ ሸዋ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ የሸዋው ምስለኔ ፡ ደጃች ፡ ድሜጥሮስ ፡ በብልኀት ፡ ወሬኛ ፡ ይሥሐቅን ፡ ያዘው ፡ ሲል ፡ የዐፄ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ አዛዥ ፡ ሐዋርያ ፡ ክርስቶስ ፡ በታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ ጽፎ ፡ ከዚያም ፡ አዛዥ ፡ ሲኖዳ ፡ ከዐፄ ፡ በካፋ ፡ ታሪክ ፡ ጋራ ፡ ደምሮ ፡ ያዘጋጀውን ፡ የግዕዝ ፡ ታሪክ ፡ አንቷን ፡ ዳባዲ ፡ በፓሪስ ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ያስቀመጠውን ፡ ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ጕይዲ ፡ በማኅተም ፡ ካሳተመው ፡ ውስጥ ፡ እናነባለን ። ስለዚህ ፡ ከዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ በፊት ፡ ባሉት ፡ የጐንደር ፡ ነገሥታት ዘመን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የሸዋ ፡ ባላባቶች ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተከፋፍለው ፡ ቢኖሩ በበላያቸው ፡ ለነገሥታቱ ፡ ምስለኔ ፡ ወይም ፡ ወኪል ፡ ሆኖ ፡ ከጐንደር ፡ የመጣ ፡ አንድ ፡ ደጃዝማች ፡ ወይም ፡ የሸዋ ፡ ጸሐፊ ፡ ላም ፡ የሚል ፡ በበላይ ፡ የነበራቸው ፡ ይመስላል ። ርሱም ፡ በጐንደር ፡ ነገሥታትና ፡ በባላባቱ ፡ መካከል ፡ አማካይ ፡ ሆኖ ፡ ከሸዋ ፡ ከየባላባቱ ፡ የሠንጋና ፡ የላም ፡ ግብር ፡ እየተቀበለ ፡ ለነገሥታቱ ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ የሚልክ ፡ ይመስላል ።

፨ ፨ ፨

እንግዴህ ፡ ባላባቶቹ ፡ ለየብቻ ፡ ሲኖሩ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያነሣናቸው ፡ የአጋንቻው ፡ አቤቶ ፡ ነጋሢ ፡ (ነጋሢ ፡ ክርስቶስ) ፡ ከልብነ ፡ ድንግል ፡ በመወለዳቸው ኀይል ፡ ስለተሰማቸው ፡ ለሸዋ ፡ የበላይ ፡ መስፍን ፡ ነኝ ፡ ሲሉ ፡ በሺሕ ፡ ፯፻፺፫ ዓ ፡ ም ፡ መንዝ ፡ በተለይ ፡ መዘዋ ፡ በሚባለው ፡ ኰረብታ ፡ ላይ ፡ በነጋሪት ፡ አሳወጁ ። ይኸንንም ፡ ዐዋጅ ፡ የፈሩት ፡ ወገኖች ፡ ሲቀበሉት ፡ ግማሾቹ ፡ ማን ፡ ከማን ይበልጣል ፡ በማለት ፡ ተጣሉና ፡ የዘወትር ፡ ውጊያ ፡ በሰፊው ፡ ተዠመረ ፡ ይባላል ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ርሳቸውም ፡ ቢሆኑ ፡ የጐንደሩን ፡ ንጉሥ ፡ ምናልባት ፡ የምስለኔውንም ፡ የበላይነት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ለመቃወም ፡ አልቻሉም ።

በያቅራቢያቸው ፡ ካለው ፡ ባላባት ፡ ሲዋጉ ፡ በመካከሉ ፡ ካሥር ፡ ዓመት ፡ በኋላ ነጋሚ ፡ ጌራን ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ የበላይነታቸውን ፡ አጸደቁበት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ነጋሚ ፡ በሌሎቹ ፡ ላይ ፡ የመፈራትና ፡ የመከበር ፡ መልክ ፡ አገኙ ። ነገር ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የፈሩትም ፡ ያልፈሩትም ፡ ጦርነት ፡ በየጊዜው ፡ እያነሡ ፡ ውጊያው ፡ በመበርከቱ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በጎንደር ፡ የሚቀመጡት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ በምዕራፍ ፡ ሧ፩ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ በመ ዠመሪያው ፡ ደብዳቤ ፡ አስቀድመው ፡ ቀጥሎ ፡ እነዚህን ፡ የሸዋ ፡ መኳንንት ፡ ለማስ ማማት ፡ በሺሕ ፡ ፲፯፻፹፫ ፡ ዓ ፣ ም ፡ ከጎንደር ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ መጥተው ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ደረሱ ።

ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መድረሳቸው ፡ ሲሰማ ፡ ባላባቱ ፡ ሁሉ ፡ መጥቶ ፡ በየተራ ፡ ሲገናኝ ፡ አቤቶ ፡ ነጋሚም ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፡ ተገናኙና ፡ የዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘር ፡ መሆናቸውን ፡ ተናገሩ ። ሌሎችም ፡ ሰዎች ፡ የጉብዝናቸውን ፡ የከፍተኝነታቸውን ፡ ሁኔታ ፡ ለዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አስረዱላቸው ፡ ይባላል ። ስለዚህ ፡ አቤቶ ፡ ነጋሚ ፡ ከሌሎቹ ፡ ይልቅ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ አገኙ ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የአርጎባው ፡ ወላስማ ፡ መጥቶ ፡ ከንጉሡ ፡ ተገናኝቶ ፡ ነበርና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ማኽል ፡ ሸዋ ፡ ገብቶ ፡ በወረራ ፡ ያስፈራውን ፡ የጋላ ፡ ነገድ ፡ እየተዋጉ ፡ አገር ፡ እንዲያቀኑ ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አቤቶ ፡ ነጋሚን ፡ አዘዟቸው ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በምዕራፍ ፡ ፷ ፡ ስለ ፡ ጋሎች ፡ አነሣሥ ፡ ጽፈናል ። በዚያው ፡ መሠረት ፡ ጋሎች ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ እንደሚሉት ፡ በዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጊዜ ፡ አዲስ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡ ፡ ሳይሆን ፡ ከደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በልብነ ፡ ድንግል ፡ ጊዜና ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ባለው ፡ በነገላውዴዎስ ፡ በነሱስንዮስ ፡ ጊዜ ፡ ከደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በብዛት ፡ እየተጓዙ ፡ ያማራውን ፡ አገር ፡ ስለ ፡ ወረሩ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከጋላ ፡ እየተዋጉ ፡ አገር ፡ ማቅናትና ፡ ማስመለስ ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ ይቈጠር ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ነጋሚን ፡ ከጋላ ፡ ጋራ ፡ እየተዋጋህ ፡ አገር ፡ አቅና ፡ ብለው ፡ ያዘዙበት ፡ ምክንያት ።

ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ሸዋን ፡ ጐብኝተው ፡ ጠበኞቹን ፡ አስማምተው ፡ ከሸዋ ፡ ወደ ፡ ዋና ፡ ከተማቸው ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ አቤቶ ፡ ነጋሚ ፡ ከጋሎች ፡ ጋራ ፡ እየተዋጉ ፡ እስከ ፡ ጣርማ ፡ በርና ፡ እስከ ፡ ሮቢ ፡ በጋላ ፡ የተወረረውን ፡ አገር ፡ አስመለሱ ፤ የዓይኔንም ፡ ከተማ ፡ ቈረቈሩ ። በከተማውም ፡ የእመቤታችንን ፡ የቅድስት ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ። በጅጌና ፡ በደብ ፡ ባላገሩን ፡ እየሰበሰቡ ፡ ብዙ ፡ መሬት ፡ እያሳረሱ ፡ እኽል ፡ በማምረት ፡ በማብላት ፡ በማጠጣት ፡ ወታደር ፡ መሰብሰብ ፡ የክፍል ፡ አገራቸውን ፤ በደንብ ፡ ማስተዳደር ፡ ዠመሩ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ የሚጠሩበት ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ከወዳጃቸው ፡ ሲጻጻፉ ፡ የበታቻቸውን ፡ ሲያዙ ፡ የሚያትሙበት ፡ ማኅተም ፡ ስለሌላቸው ፡ በዚሁ ፡ ያዝኑ ፡ ኖሮ ፡ ይኸንኑ ፡ የማዕርግ ፡ ስምና ፡ ማኅ

ቶም ፡ ለመቀበል ፡ የደንቡንም ፡ ግብር ፡ ለመስጠት ፡ ጐንደር ፡ ሄደው ፡ ሳሉ ፡ ማኅተሙንና ፡ የማዕርጉን ፡ ስም ፡ ተቀብለው ፡ ወዳገራቸው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ሳይመለሱ ፡ መንገዱ ፡ ሁሉ ፡ በጋሎች ፡ ጦር ፡ ተዘጋባቸው ። በመካከሉም ፡ እዚያው ፡ ጐንደር ፡ እንዳሉ ፡ ታመው ፡ሞቱና ፡ ፊት ፡ አበ ፡ ተቀበሩ ።

## ምዕራፍ ፡ ፺፱ ።

## አቤቶ ፡ ስብስቴ ፡ (ስብስትያኖስ) ።

ነገሢ ፡ ጐንደር ፡ ሆነው ፡ በሽታቸው ፡ እየባሰባቸው ፡ መሄዱን ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ፡ የጦር ፡ መሣሪያዎን ፡ የብር ፡ ካራዎን ፡ ጦሬንና ፡ የወርቅ ፡ ቅብ ፡ ጋሻዎን ፡ ለስብስቴ ፡ አልጋዎን ፡ (የግዛት ፡ ሹመቴን) ፡ ለአካዋ ፡ ገንዘቤንና ፡ ርስቴን ፡ ለቀሩት ፡ ልጆቼ ፡ አውርሻለሁ ፡ ብለው ፡ ተናዘው ፡ ኖሮ ፡ በኑዛዜው ፡ መሠረት ፡ አካዋ ፡ ባባቱ ፡ ሹመት ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዳጋጣሚ ፡ እርሱ ፡ ያባቱን ፡ ሹመት ፡ በያዘበት ፡ ዓመት ፡ ዝናም ፡ ጠፍቶ ፡ አዝመራ ፡ ሳይሆን ፡ ስለ ፡ ቀረ ፡ መኳንንቱ ፡ የአካዋ ፡ ገድ ፡ አልሆነንም ፡ ብለው ፡ ርሱን ፡ ትተው ፡ ዳኛ ፡ የተባለውን ፡ ሌላውን ፡ የነጋሢን ፡ ልጅ ፡ አስቀመጡት ፡ ይባላል ።

በጐንደር ፡ በነገሥታቱ ፡ ዘር ፡ መካከል ፡ በዙፋን ፡ የተነሣ ፡ ጭቅጭቅና ፡ ጦርነት እንደሚሆን ፡ በዚህ ፡ በሸዋም ፡ አልጋ ፡ ሰባት ፡ የሚሆኑ ፡ የነጋሢ ፡ ልጆች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ባልጋ ፡ የሚቀመጠው ፡ ያው ፡ ሕዝብ ፡ የመረጠው ፡ ቢሆን ፡ እነሱ ፡ ግን ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ መከራከራቸው ፡ አልቀረም ፡ ነበር ፡ ስብስቴ ፡ ግን ፡ ሁሉንም ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ መራቤቴ ፡ ሄደው ፡ በጊዜው ፡ ለነበሩት ፡ ለመራቤቴው ፡ ገዥ ፡ ለመዘምር ፡ አሽከርነት ፡ አደሩ ፡ በዚያም ፡ ሳሉ ፡ በደንም ፡ በሌላውም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የበረቱ ፡ ሆኑ ። መጨውን ፡ እናውቃለን ፡ የሚሉ ፡ መነኰሳትም ፡ የዚህ ፡ የስብስቴ ፡ ዘር ፡ ያንተን ፡ ዘር ፡ ቀጥቅጦ ፡ ይገዛል ፡ እያሉ ፡ ለመዘምር ፡ ነገሯቸው ። መዘምርም ፡ ከመነኰሳቱ ፡ የሰሙትንና ፡ ስብስቴ ፡ በየጊዜው ፡ የሚያሳዩትን ፡ የጐብዝና ፡ ሥራ ፡ ሲያመዛዝኑ ፡ ትንቢቱ ፡ ይፈጸም ፡ ይሆናል ፡ ሲሉ ፡ ሥጋትም ፡ ቅናትም ፡ አደረባቸው ፡ አሲዘውም ፡ ሊገድሏቸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ዘመዶቻቸውን ፡ ከወዲህ ፡ የጋላ ፡ ወረራ ፡ ስላሰለቻቸው ፡ ከዘመዶቻቸው ፡ እናትኽ ፡ ታማለችና ፡ ድረስ ፡ የሚል ፡ የሐሰት ፡ መልክት ፡ መጣባቸው ። በሰሙም ፡ ጊዜ ፡ ከመዘምር ፡ ሳይሰናበቱ ፡ ከመራቤቴ ፡ ወዳባታቸው ፡ ወደ ፡ ነጋሢ ፡ ግዛት ፡ ተመለሱ ። ከተመለሱም ፡ በኋላ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እያሉ ፡ ሰው ፡ እያሳበሩ ፡ ለብቻቸው ፡ ከጥሙጋና ፡ ከብቹ ፡ ጋላ ፡ ጋራ ፡ እየተዋጉ ፡ ያባርሩ ፡ ዠመር ። በዚህም ፡ ጦርነት ፡ ባገኙት ፡ አሸናፊነት ፡ ዝናቸው ፡ በያለበት ፡ መሰማትና ፡ መድመቅ ፡ ዠመረ ፡ ይልቁንም ፡ ከጋሎቹ ፡ የማረኩት ፡ ከብትና ፡ ገንዘብ ፡ ክብረት ፡ ስላተረፈላቸው ፡ በዚህ ፡ የምርኮም ከብትና ፡ ገንዘብ ፡

ብዙ ፡ ተከታይ ፡ ስላገኙ ፡ በነጋሚ ፡ አልጋ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በተቀመጠው ፡ ወንድ ማቻቸው ፡ በዳኛ ፡ ዘንድ ፡ ምቀኝነትን ፡ ሥጋትን ፡ ፈጠረባቸው ። ባለሟሎችም ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ ዘንድ ፡ እየቀረቡ ፡ «ምን ፡ ስትሆን ፡ ነው ፡ የምትመለከተው ፡ ስብስቴን ፡ አሁኑን ፡ ወግተኽ ፡ ካላጠፋኽ ፡ በኋላ ፡ አትችለውምና ፡ አሁኑኑ ፡ አስብበት » ፡ እያሉ ፡ ይመክሩት ፡ ዠመር ። ዳኛም ፡ ካሽከሮቹ ፡ ጋራ ፡ መክሮ ፡ «ግዳዩና ፡ ቀቤው ፡ ይበቃኻል ፡ ከጋላ ፡ የማረክኸውን ፡ ከብትና ፡ ገንዘብ ፡ ወደኔ ፡ አግባ» ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ ለስብስቴ ፡ ላከባቸው ። ስብስቴም ፡ አላደርገውም ፡ ብለው ፡ መለሱ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ የየግል ፡ ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ ተሰልፈው ፡ ተዋጉና ፡ ስብስቴ ፡ አሸነፉና ፡ ባባታቸው በነጋሚም ፡ አልጋ ፡ ተቀመጡ ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ (1) ፡ ስለ ፡ ስብስቴ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ተገጠመላቸው ፡ ይባላል ፡ ይኸንንም ግጥም ፡ ግማሹን ፡ ካንዳንድ ፡ የሸዋ ፡ ሽማግሌ ፡ ከሰማሁት ፡ በኋላ ፡ በሙሉ ፡ ተጠራቅሞ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ አሳትመው ፡ ሳይጠረዝ ፡ በተበታተነው ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ስላገኘሁት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ጽፌዋለሁ ፡ ይህም ፡ ግጥም ፡ እንደጐጃሞች ፡ ምሥጢርና ፡ ሰምና ፡ ወርቅ ፡ ሳይኖረው ፡ ስብስቴ ፡ በመራቤቴ ያሳለፉትን ፡ የሕይወት ፡ ታሪካቸውን ፡ ባንድ ፡ የጦር ፡ ውርወራ ፡ ፩ ፡ ጉሽ ፤ መግደላቸውን ፡ ከዚያ ሊያዙ ፡ ሲሉ ፡ ከመራቤቴ ፡ አምልጠው ፡ ዐይኔ ፡ መሄዳቸውን ፡ በዚያም ፡ ወንድማቸውን ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ያባታቸውን ፡ አልጋ ፡ ማግኘታቸውን ፡ በተርታ ፡ አገጣጠም ፡ ይገልጣል ።

ግጥሙም ፡ ይህ ፡ ነው ።

የነጋሚ ፡ ልጆች ፡ አልተስማሙም ፡ ከቶ ፡
አባታቸው ፡ ቢሞት ፡ ፲ ፡ ልጆች ፡ ትቶ ፡
አንዱን ፡ አንዱ ፡ ጠላው ፡ ሁከት ፡ አስነሥቶ
ስብስቴም ፡ ለቀቀ ፡ ሄደ ፡ ካገር ፡ ወጥቶ ።
ከወንድሞቹ ፡ ጋር ፡ መጋደልን ፡ ጠልቶ ።
ወደ ፡ ቄላ ፡ ወርዶ ፡ አደረ ፡ ለጌታ ፤
ጌታውም ፡ ወደደው ፡ ሰጠው ፡ ከበሬታ ።
አደን ፡ ሄዶ ፡ ጌታው ፡ ሠራዊት ፡ ሲፈታ ፡

(1) በግጥሙ ፡ ውስጥ ፡ "ፈጽሞ ፤ . . . . በዚህ ፡ ምክንያት ፡ . . . ." የሚል ፡ ንግግር ፡ እያለፈ ፡ ይገኛል ፡ ስለዚህ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ንግግር ፡ በስብስቴ ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ አይመስልምና ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የተገጠመ ፡ ይመስላል ።

ባንድ ፡ ውርወራ ፡ አስቀረው ፡ ጕሹን በቴማታ ። (1)
የጐሽ ፡ ሰንበር ፡ በላ ፤ ቀኝ ፡ እጁም ፡ በረታ ።
ለጌታው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ትንቢት ፡ ቢነግረው ፡
የርሱን ፡ ዘር ፡ ስብስቴ ፡ ኋላ ፡ እንዲገዛው ፡
በወደደው ፡ ፈንታ ፡ ፈጽሞ ፡ ጠላው ፤
ሊያስረውም ፡ ፈለገ ፤ ደግሞም ፡ ሊገድለው ።
ጋላ ፡ አስቸግሯቸው ፡ እጅግ ፡ ተጨንቀው ፡
ዘመዶቹ ፡ ላኩ ፡ ምክንያት ፡ አርገው ፤
እናትኽ ፡ ታመዋል ፡ ድረስ ፡ ና ፡ ብለው ፡
የቅንነት ፡ አምላክ ፡ ክሞት ፡ አዳነው ።
ሊታሰር ፡ ተመክሮ ፡ ሲሉ ፡ ነግ ፡ ሣልስት ፡
እናትኽ ፡ ታመዋል ፡ ብለው ፡ ቢነግሩት ፡
ደንግጦ ፡ ተነሣ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፤
ፈጥኖ ፡ አገሩ ፡ ሄደ ፡ ሳይሰናበት ።
ፈልጎ ፡ ቢያጣው ፡ ላከ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡
ያ ፡ ቈለኛው ፡ ጌታው ፡ ሆነበት ፡ ጸጸት ።
እያለ ፡ ተከዘ ፡ ምነው ፡ በሞትሁት ፤
ምነው ፡ በደለማ ፡ በፊት ፡ በያዝሁት ፡
አመለጠኝ ፡ ብሎ ፡ ነደደ ፡ እንደ ፡ እሳት ።
የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ ያስቀረ ፡ መስሎት ፡
አምላክ ፡ የፈቀደው ፡ ያሰበው ፡ ከጥንት ፡
ምን ፡ ቢሆን ፡ አይቀርም ፡ በሌላ ፡ ብልኀት ።
በከንቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዲያው ፡ መታከት ፤
በትእዛዝ ፡ አይሆንም ፡ አልጋና ፡ መንግሥት ፡
ከላይ ፡ ካልፈቀደ ፡ አምላክ ፡ ጸባዖት ።
ንጉሢም ፡ አዘዘ ፡ አልጋውን ፡ ላካዋ ፡
ዝናም ፡ አልዘንም ፡ አለ ፡ በግዛቱ ፡ ሸዋ ፡
አምላክ ፡ በይፈቅድለት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ጠላዋ ።
ዳኛም ፡ ግንባር ፡ አጣ ፡ አላገኘም ፡ ግርማ ፡
በስብስቴ ፡ ጕልበት ፡ አልጋውን ፡ ተቀማ ።
ስብስቴ ፡ ተመርጦ ፡ አምላክ ፡ ፈርዶለት ፡
ለልጅ ፡ ልጁ ፡ ሆነ ፡ የሸዋ ፡ መንግሥት ።

(1) የመራቤቴ ፡ ገዥ ፡ መዘምር ፡ ለአደን ፡ ወደ ፡ ቈላ ፡ ወርዶ ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ ጕሽ ፡ እየሮጠ ፡ መጥቶ ፡ መዘምርን ፡ ሊገድል ፡ ሲል ፡ ሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ ፈርቶ ፡ ሸሸ ፤ ስብስቴ ፡ ግን ፡ ቈርማው ፡ ስብስቴ ፡ ብለው ፡ ፎክረው ፡ ጠራቸውን ፡ በኀይል ፡ ነዝረው ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ውጋ ፡ ጕሹን ፡ ገድለው ፡ መዘምርን ፡ ከሞት ፡ ማዳናቸውን ፡ ሲጠቅስ ፡ ነው ፡

(2) ይህ ፡ ሁሉ ፡ አገር ፡ በይፋት ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

እንግዴህ ፡ ስብስቴ ፡ ወንድማቸውን ፡ ዳኛን ፡ አሸንፈው ፡ በባታቸው ፡ በነጋሢ ፡ አልጋ ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋላ ፡ ላባቴ ፡ ለነጋሢ ፡ ሞት ፡ ውሎ ፡ አደርጋለሁና ፡ ወዳጅ ፡ ዘመዴ ፡ የሆንኽ ፡ ሁሉ ፡ ሾላ ፡ ሜዳ ፡ ድረስ ፡ ተሰብስበኽ ፡ አላቅሰኝ ፡ ሲሉ ፡ በያለበት ፡ መልክት ፡ ላኩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሚስታቸው ፡ ወገኖች ፡ ዶቦች ፡ ያያታቸው ፡ የወይዘሮ ፡ ሰንበልት ፡ ወገኖች ፡ መላ ፡ አራድማ ፡ የልጃቸው ፡ የአብዬ ፡ ሚስት ፡ ወገኖች ፡ እነአፍሮ ፡ አይገባ ፡ ተሰብስበው ፡ መጡ ። ከነዚህም ፡ በቀር ፡ የይፋት ፡ ወላስማ ፡ ከነሰው ፡ የላሎ ፡ ምድር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ መጥቶ ፡ የውሎው ፡ ለቅሶ ፡ ተለቅሶ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ «ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የማዕርግ ፡ ስሜ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ ነውና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ ስብስቴ ፡ ብሎ ፡ ያልጠራኝን ፡ እቀጣዋለሁ» ፡ ብለው ፡ በዚያው ፡ ሳሉ ፡ ዐዋጅ ፡ አስነገሩ ፡ ይባላል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ ስብስቴ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ በቀረጥ ፡ አምባ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ራሳቸው ፡ በቈረቈሩት ፡ በዶቃቂት ፡ (2) ፩ ፡ ጊዜ ፡ ባባታቸው ፡ ከተማ ፡ በዐይኔ ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ሲቀመጡ ፡ በይፋት ፡ ከገባው ፡ ከከረዩ ፡ ጋራ ፡ እየተዋጉ ፡ ሲያስወጡ ፡ በመካከሉ ፡ ከልጃቸው ፡ ከአብዬ ፡ ጋራ ፡ ጠብ ፡ አበቀሉ ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ ስብስቴ ፡ ከዶባ ፡ ባላባት ፡ ወገን ፡ ከሚወለዱት ፡ ሴት ፡ አብዬን ፡ ወለዱ ። አብዬም ፡ ተወልደው ፡ እንዳደጉ ፡ ከመንዝ ፡ የማማን ፡ ልጅ ፡ ታጉንስጥያን ፡ አግብተው ፡ ሲኖሩ ፡ በኋላ ፡ እሙሉ ፡ ሰውነት ፡ ደርሰው ፡ ጭፍራም ፡ አበጅተው ፡ በኑሯቸውም ፡ ከባታቸው ፡ ተለይተው ፡ በዶቃቂት ፡ መቀመጥ ፡ ዠመሩ ። ታቦት ፡ ለመትከል ፡ ግን ፡ ቢያስቡ ፡ በግራኝ ፡ ወረራ ፡ ምክንያት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናቱ ፡ ተቃጥለው ፡ ታቦት ፡ ስላጡ ፡ ተቸገሩ ። ስለዚህ ፡ አባታቸው ፡ ካሉበት ፡ ከተማ ፡ ከዐይኔ ፡ የቅዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ ታቦት ፡ ሰርቀው ፡ ወደ ፡ ዶቃቂት ፡ ወሰዱ ፡ ይባላል ።

ይኸም ፡ የአብዬ ፡ ሁኔታ ፡ በስብስቴ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ መሸፈት ፡ ያኽል ፡ ተቈጠረና ፡ ስብስቴ ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ዶቃቂት፡ሄዱ ። አብዬ ፡ ግን ፡ ከባታቸው ፡ ጋራ ፡ መዋጋትን ፡ ሳያስቡ ፡ በሰላም ፡ ቆመው ፡ ሲጠብቁ ፡ ስብስቴ ፡ አብዬን ፡ ከሰዎቻቸው ፡ ለይተው ፡ ሊመቱ ፡ ሲተናነቁ ፡ ቆመው ፡ ይመለከቱ ፡ ከነበሩት ፡ ከአብዬ ፡ አሽከሮች ፡ አንዱ ፡ ስብስቴን ፡ ወግቶ ፡ ገደላቸው ። አብዬ ፡ ደግሞ ፡ ገዳዩን ፡ በማመስገን ፡ ፈንታ ፡ ቢሆን ፡ ትገላግል ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ለምን ፡ አባቴን ፡ ገደልኽ ፡ ብለው ፡ መልሰው ፡ አሽከራቸውን ፡ ገደሉት ፡ ይባላል ።

ይህን ፡ የመሰለው ፡ ታሪክ ፡ በብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ተፈጽሟል ። ለምሳሌ ፡ ዳዊትና ፡ ሳኦል ፡ በሚዋጉበት ፡ ጊዜ ፡ የዳዊት ፡ አሽከር ፡ ጌታውን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ ሌሊት ፡ ሳኦል ፡ ወደ ፡ ተኛበት ፡ ሰፈር ፡ ሄዶ ፡ ቢገድለው ፡ ዳዊት ፡ እግዚአብሔር ፡ በቀባው ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ እጅኽን ፡ እንደምን ፡ ዘረጋኽ ፡ ብሎ ፡ አሽከሩን ፡ ገድሎታል ።

ትልቁ ፡ እስክንድርና ፡ ዳርዮስ ፡ ሲዋጉ ፡ ዳርዮስ ፡ ተሸንፎ ፡ ሲመለስ ፡ እስ ክንድርን ፡ ደስ ፡ ያሰኘሁ ፡ መስሎት ፡ አንድ ፡ የፋርስ ፡ መኰንን ፡ ንጉሡን ፡ ዳር ዮስን ፡ ቢገድለው ፡ እስክንድር ፡ ገዳዩን ፡ ይዞ ፡ ለዳርዮስ ፡ ወንድም ፡ በፈቀድኸው ፡ ዐይነት ፡ አሠቃይተኸ ፡ የወንድምኽን ፡ ጠላት ፡ ግደለው ፡ ብሎ ፡ አሳልፎ ፡ አስገ ድሎታል ።

ይኸም ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ምርኮኛን ፡ እንዳንገድል ፡ በዘመ ዳሞችም ፡ መካከል ፡ ጦርነት ፡ ቢደረግ ፡ አንደኛውን ፡ ለማስደሰት ፡ የወደቀውን ፡ እንዳናጠቃ ፡ ለመጠንቀቅ ፡ ሲረዳን ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ጠላት ፡ ሆኖ ፡ የወደቀም ፡ ቢሆን ፡ «ንጉሥ» ፡ የተባለው ፡ በማንም ፡ እጅ ፡ ሲገደል ፡ በኛም ፡ ይኸው ፡ ነው ፡ በማለትና ፡ ንጉሣዊ ፡ አካልን ፡ ለማስከበር ፡ ሲሉ ፡ የተሸነፉት ፡ ነገሥታቶች ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ እንዲመቱና ፡ እንዲገደሉ ፡ አሸናፊዎች ፡ ነገሥ ታቶች ፡ የማይፈቅዱ ፡ መሆናቸውን ፡ ያስረዳል ።

## ምዕራፍ ፡ ፲ ።

## መርድ ፡ አዝማች ፡ አብዬ ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ አብዬ ፡ (የክርስትና ፡ ስማቸው ፡ ቀዳሜ ፡ ቃል ፡) ባባታ ቸው ፡ አልጋ ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋላ ፡ ከዶቃቂት ፡ አልፈው ፡ የሐር ፡ አምባን ፡ ከተማ ፡ ቈርቍረው ፡ የቅዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ። አባታቸው ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ ስብስቴ ፡ እስከ ፡ ዐዋዲ ፡ እያሳረሱ ፡ ያለሙትን ፡ እርሳቸው ፡ ደግሞ ፡ እስከ ፡ አይራራ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ እያሳረሱ ፡ ብዙ ፡ ያልታረሰ ፡ መሬት ፡ አለሙ ።

በዘመናቸው ፡ ለጐንደሩ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለዳግማዊ ፡ ኢያሱ ፡ (ብርሃን ፡ ሰገድ) ፡ ግብር ፡ ከልክለው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በራስ ፡ ወልደ ፡ ልዑል ፡ በራስ ፡ ወዳጆ ፡ በአየሌ ፡ ወሰኑ ፡ የሚመራ ፡ ጦር ፡ ተልከባቸው ፡ የተላኩትን ፡ አሸንፈው ፡ እነራስ ፡ ወልደ ፡ ልዑልን ፡ (የእቴጌ ፡ ምንትዋብን ፡ ወንድም) ፡ እነአየሌ ፡ ወሰኑን ፡ ከ፺፱ ፡ ጠመንዣ ፡ ጋራ ፡ መማረካቸው ፡ በኋላም ፡ በርቅ ፡ ራስ ፡ ወልደ ፡ ልዑልን ፡ መልሰው ፡ ለአየሌ ፡ ወሰኑ ፡ ሹመት ፡ ሰጥተው ፡ ማስቀረታቸው ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በተተረከበት ፡ በምዕራፍ ፡ ፳፫ ፡ ውስጥ ፡ በሰ ፊው ፡ ተዘርዝሯል ። ይኸውም ፡ ድል ፡ የአብዬን ፡ የጕብዝና ፡ ወሬ ፡ በያለበት ፡ አስፋፋ ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ አብዬ ፡ በዚህ ፡ ጦርነት ፡ ከተማረኩ ፡ በኋላ ፡ በፈቃዳቸው ፡ ሸዋ ፡ በቀሩት ፡ ጐንደሬዎች ፡ የጐንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሥርዓትና ፡ ልማድ ፡ በሸዋ ፡ በግዛታቸው ፡ እንዲለመድ ፡ አደረጉ ። እንደዚሁም ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ የሚያ ውቁትን ፡ ፈላሾች ፡ እየለዩ ፡ ማረሻ ፡ ዶማ ፡ ወገል ፡ እያሠሩ ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ በሰ ፊው ፡ እንዲለማ ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡ አንካሴ ፡ ጐራዴ ፡ ሰይፍ ፡ እያሠሩ ፡ የጦር ፡ መሣ ሪያ ፡ ለወታደሮቻቸው ፡ እንዲዘጋጅ ፡ አደረጉ ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ባብዬ ፡ ዘመን ፡ የወታደርነትና ፡ የግብርና ፡ ሥራ ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሥርዓት ፡ ከቀድሞው ፡ ይበ ልጥ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ነበር ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ አብዬም ፡ ከሐር ፡ አምባ ፡ ሔደው ፡ ያንኮበርን ፡ ከተማ ፡ ቈረቈሩ ። በዚህም ፡ ሥፍራ ፡ ትኖር ፡ የነበረች ፡ አንኮ ፡ የምትባል ፡ ሴት ፡ ዛሬ ፡ በርሷ ፡ ስም ፡ ተጠራ ፡ ከሚባለው ፡ ካንኮበር ፡ አብዬን ፡ በመፍራት ፡ ከብቷን ፡ ነድታ ፡ ወደ ፡ ከረዩ ፡ ተሰደደች ፡ እየተባለ ፡ ይወራል ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ አብዬ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ፳፰ ፡ ዓመት ፡ ሸዋን ፡ ከገዙ ፡ በኋላ ፡ በየካቲት ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ሺሕ ፡ ፯፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዐረፉና ፡ ራሳቸው ፡ ባሠሩት ፡ በሐር ፡ አምባ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በክብር ፡ ተቀበሩ ።

## ምዕራፍ ፡ ፶፩ ።

## መርድ ፡ አዝማች ፡ አምኃየስ ፡—የወሰን ፡ ሰገድ ፡ ዜና ፡ ልደት ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ አምኃየስ ፡ ደግሞ ፡ በባታቸው ፡ አልጋ ፡ ከተቀመጡ ፡ ወዲህ ፡ አባታቸው ፡ ይደክሙበት ፡ የነበረውን ፡ ያገር ፡ ማቅናት ፡ የግብርና ፡ ሥራ ፡ ማስፋፋትን ፡ የከተማ ፡ ቍርቈራን ፡ ሥራ ፡ አላቋረጡም ። ባባታቸው ፡ ጊዜ ፡ የሸዋ ፡ ግዛት ፡ እስከ ፡ ሚጣቅ ፡ እስከ ፡ ጐላ ፡ የደረሰውን ፡ ርሳቸው ፡ ደግሞ ፡ በጊዜያቸው ፡ ከዚያ ፡ አሳልፈው ፡ ጠራን ፤ ቡልጋን ፤ ምንጃርን ፡ ከጋሎች ፡ እየተዋጉ ፡ አቀኑ ። እስከ ፡ ቀወትና ፡ እስከ ፡ ምንጃር ፡ ያለውም ፡ አገር ፡ ከቀና ፡ በኋላ ፡ በደግነታቸው ፡ ምክንያት ፡ የቸር ፡ አምኃየስ ፡ አገር ፡ ይባል ፡ ዠመር ።

ከዚያም ፡ አንኮበር ፡ ተቀምጠው ፡ ጭፍራ ፡ እየላኩ ፡ ያብቹንና ፡ የሜራውን ፡ ጋላ ፡ እየወጉ ፡ ተቈርጦ ፡ ለብቻው ፡ የነበረውን ፡ የተጐለትን ፡ ሕዝብ ፡ ከቡልጋና ፡ ከጠራ ፡ ተገናኝቶ ፡ ከርሳቸው ፡ ጭፍራ ፡ ጋራ ፡ እንዲያብርና ፡ የሜራውን ፡ ጋላ ፡ እንዲወጋ ፡ አደረጉ ። በመርድ ፡ አዝማች ፡ አምኃየስ ፡ ጊዜ ፡ የጎንደር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ነበሩ ፡ ርሳቸውንም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ እንደራሴያቸው ፡ ራስ ፡ ሥዑል ፡ ሚካኤል ፡ በሻሽ ፡ አሳንቀው ፡ ገደሏቸው ፡ ማለትን ፡ ሰምተው ፡ በጣም ፡ አዘኑ ፡ ይባላል ። ቢሆንም ፡ ከማዘን ፡ በቀር ፡ ራሳቸው ፡ ወይም ፡ አዝማችና ፡ ጦር ፡ ልከው ፡ የሟቹን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ደም ፡ ለመበቀል ፡ አልሞከሩም ። ስለዚህ ፡ በነገሩ ፡ እየተገረሙና ፡ እየተቈጩ ፡ በዚሁ ፡ ባገራቸው ፡ በሸዋ ፡ የማስተዳደር ፡ ሥራቸውን ፡ ቀጠሉ ።

ያንኮበርን ፡ ከተማ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የቀረቈሩት ፡ አባታቸው ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አብዬ ፡ ቢሆኑ ፡ የቅዱስ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አዲስ ፡ ተክለው ፡ አንኮበርን ፡ ከቀድሞው ፡ እንዲደምቅ ፡ ያደረጉት ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አምኃየስ ፡ ናቸው ።

፨ ፨ ፨

በዘመናቸው ፤ ከእዘዞ ፡ (ጎንደር) ፡ መጥተው ፡ በመንዝ ፡ አውራጃ ፡ የሚቀመጡ ፡ ቢዛን ፡ ወልዱ ፡ የሚባሉ ፡ የቅኔና ፡ የመጻሕፍት ፡ ሊቅ ፡ ነበሩ ። የርሳቸውም ፡ የሊቅነት ፡ ዝና ፡ እስከ ፡ አምኃየስ ፡ ገሮ ፡ ደርሶ ፡ ተሰምቶ ፡ ነበርና

አምኃየስ፡ልጃቸውን፡አስፋ፡ወሰንን፡ቅኔ፡እንዲማሩ፡ከራት፡አሽከሮች፡ጋራ፡
ወደ፡ቢዛን፡ወልዱ፡ላኳቸው። አስፋ፡ወሰን፡መንዝ፡ሔደው፡ከኝሁ፡መም
ህር፡ቅኔ፡ተምረው፡ከስመረቁ፡በኋላ፡ከመንዝ፡ተነሥተው፡ወደ፡አንኮበር፡
ለመምጣት፡ወደራ፡(የጐላ፡ወደራ፡ማርያም፡አይደለም)፡ላይ፡ሲደርሱ፡ጊዜ፡
መሸባቸውና፡የአምኃየስ፡ቍባት፡በሆኑት፡በወይዘሮ፡አትሞች፡ሆይ፡ቤት፡
አሳድሩኝ፡ብለው፡አደሩ። በዚያም፡ሳሉ፡አስፋ፡ወሰን፡የአምኃየስ፡ልጅ፡
መሆናቸውን፡ሴትዮዋም፡የአምኃየስ፡ቍባት፡መሆናቸውን፡ሳይገላለጡ፡በሌ
ላውም፡ወገን፡የአስፋ፡ወሰን፡የወጣትነት፡ጊዜና፡የመልካቸው፡ቍንጅና፡ለወይ
ዘሮዪቱ፡ደስ፡ስላሰኛቸው፡የአስፋ፡ወሰንን፡ጓደኞች፡እሌላ፡ቤት፡አሳድረው፡
ወይዘሮ፡አትሞች፡ሆይና፡ወጣቱ፡አስፋ፡ወሰን፡ባንድነት፡አደሩ። በዚህ፡
ባንድ፡ሌሊት፡ግንኙነት፡ሴትዮዋ፡ፀንሰው፡በኋላ፡ወሰን፡ሰገድን፡ወለዱ፡
ይባላል።

አስፋ፡ወሰን፡ወደራ፡አድረው፡አንኮበር፡ከተማ፡በገቡ፡ጊዜ፡አባታ
ቸው፡በናፍቆት፡ስመው፡ተቀበሏቸው። አባትና፡ልጁም፡በፍቅር፡አንድነት፡
ሲኖሩ፡ወይዘሮ፡አትሞች፡ሆይ፡ካስፋ፡ወሰን፡ወሰን፡ሰገድን፡መውለዳቸው፡
ተሰማ፡አስፋ፡ወሰንም፡የሆኑትን፡ሥራ፡ስለሚያውቁና፡ሴትዮዋም፡ያባታ
ቸው፡ቍባት፡መሆናቸውን፡ስለሰሙ፡አባታቸውን፡ፈርተው፡ከንኮበር፡ሸሽ
ተው፡እንደ፡መነኰሴ፡ቆብ፡ደፍተው፡ዳባ፡ደርበው፡ፍርኰታ፡ገዳም፡ገቡ፡
ይባላል።

መርድ፡አዝማች፡አምኃየስም፡በልጃቸው፡መጥፋት፡ተጸጽተው፡በየገዳ
ማቱና፡በየአድባራቱ፡ጧፍ፡ዕጣን፡ምጽዋት፡እየላኩ፡አትርሱኝ፡ብለው፡
ኖሮ፡ለፍርኰታ፡ገዳምም፡ድርሻው፡ሲመጣ፡በዚህ፡መንገድ፡አስፋ፡ወሰን፡
ያባታቸውን፡መጨነቅ፡ሊገነዘቡ፡ቻሉ፡ይባላል። ከዚህ፡በኋላ፡ምሥጢራቸ
ውን፡ለገዳሙ፡መምህር፡በዝርዝር፡አስረዱና፡ተፈላጊው፡ያምኃየስ፡ልጅ፡
ርሳቸው፡መሆናቸውን፡አስረዱ። መምህሩም፡ልጅዎ፡አስፋ፡ወሰን፡በዚህ፡
በፍርኰታ፡ገዳም፡አለ፡ብለው፡ወዳንኮበር፡ለአምኃየስ፡ላኩ። ቀጥለውም፡
ራሳቸው፡ይዘው፡ሔደው፡አባትና፡ልጁን፡አገናኝተው፡አስታረቋቸውና፡
ደስታ፡ሆነ። ነገር፡ግን፡ይህ፡ነገር፡ለተርታው፡ሰው፡አልተገለጸ፡ኖሮ፡መም
ህሩና፡አስፋ፡ወሰን፡የመነኰሴ፡ልብሳቸውን፡ሳይለውጡ፡አምኃየስ፡ግብር፡
አግብተው፡ሲያበሉ፡ሲያጠጡ፡አንዱ፡የአምኃየስ፡አሽከር፡ተነሥቶ፡አይገቡ
ገብቼ፡የጌታዬን፡ልጅ፡አስፋ፡ወሰንን፡አመጣለሁ፡ብሎ፡ቢፎክር፡አምኃየስ፡
«ተው፡አንተ፡እንደዚህ፡አትናገር፡ሳይሆንልኽ፡የቀረ፡እንደሆነ፡እናባ፡ይታ
ዘቡኻል»፡አሉት፡ይባላል። ይህ፡ንግግር፡ከማሣቁ፡በቀር፡መርድ፡አዝማች፡
አምኃየስ፡የንግግር፡ዘዴ፡እንደነበራቸው፡ያስረዳል።

በኋላ ፡ ግን ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ አምኃየስ ፡ የገዳሙን ፡ መምህር ፡ አሰና ብተው ፡ የአስፋውን ፡ ወሰንን ፡ የምንኵስና ፡ ልብስ ፡ አሶልቀው ፡ የሚገባቸውን ፡ ያማረ ፡ ልብስ ፡ አስለብሰው ፡ ለመኳንንቱም ፡ ለወታደሩም ፡ አስተዋወቋቸው ። የተወለደውንም ፡ ልጅ ፡ ከወደራ ፡ አስመጥተው ፡ ስሙን ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ብለው ፤ ሠየሙት ፡ ይባላል ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ አምኃየስ ፡ ሐር ፡ አምባና ፡ አንኮበር ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ፴፬ ፡ ዓመት ፡ ከገዙ ፡ በኋላ ፡ ፲፯፻፸፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥር ፡ ወር ፡ ሞተው ፡ ራሳ ቸው ፡ ባሠሩት ፡ ባንኮበር ፡ በቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተቀበሩ ።

## ምዕራፍ ፡ ፻፱ ።

## መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፤ - የሞረት ፡ ጥዱ ፡ እንደ ፡ ገበረ ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ባ፲፯፻፸፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ባባታቸው ፡ አልጋ ፡ ተቀመጡ ። በርሳቸውም ፡ ዘመን ፡ በጐንደር ፡ መንግሥት ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማ ኖት ፡ በመዠመሪያ ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተፍጻሜተ ፡ መንግሥት ፡ በመ ጨረሻ ፡ የነበሩትና ፡ ታላቁ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ እንደራሴ ፡ የነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ባባታቸው ፡ አልጋ ፡ ከተቀመጡ ፡ ወዲህ ፡ ያንኮበርን ፡ ከተማ ፡ ከቀድሞው ፡ አሻሻሉ ። አባታቸው ፡ አምኃየስ ፡ የቅዱስ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠርተው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንዲሁም ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ በጊዜያቸው ፡ የቅድስት ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ፡ ግዛታቸውንም ፡ አሰፉ ። ካባታቸው ፡ ቀብት ፡ ከወይዘሮ ፡ አትሞች ፡ ሆኖ ፡ የተወለዱትም ፡ ልጃቸው ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ለጦርነት ፡ ስለ ፡ ደረሱ ፡ በጠ ባያቸው ፡ የጉብዝናና ፡ የተዋጊነት ፡ መንፈስ ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ ባባታቸው ፡ ውስጥ ፡ እየታዘዙ ፡ ግድምን ፡ ኤፍራታን ፤ አንጾኪያንና ፡ ግሼን ፤ ሞረትንና ፡ መራ ፡ ቤቱን ፡ እየተዋጉ ፡ አቀኑ ። በነጋሢ ፡ ዘመን ፡ ተከፋፍለው ፡ ይኖሩ ፡ ከነ በሩት ፡ ባላባቶች ፡ ውስጥ ፡ የሞረት ፡ ጥዱን ፡ ለማስገበር ፡ የሚያስፈራሩበት ፡ ጊዜ ፡ ነበርና ፡ ከሞረት ፡ ከጥዱ ፡ ወገን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ግጥም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ተገጠመ ፡ ይባላል ።

አስፋ ፡ ወሰን ፡ ይፋት ፡ ጠንክረው ፡ ይረሱ ፤
ሞረት ፡ ጥዱል ፡ ብለው ፡ ከመመላለሱ ።
በሞረት ፡ ጥዱ ፡ አለና ፡ ላስገብረው ፡ ከምትል ፡ ዝም ፡ ብለኽ ፡
  እረስ ፡ ማለት ፡ ነው) ።

የአስፋ ፡ ወሰን ፡ መልስ ።

ለሞፈር ፡ ለቀንበር ፡ የሚሆነኝን ፤
ሳልቆርጠው ፡ አልቀርም ፡ (ሳልገዛው ፡ አልቀርም ፡ ማለት ፡ ነው) ፡
  ዘንድሮ ፡ ጥዱን ።

የጥዱ ፡ መልስ ።

ያባቴ ፡ አገር ፡ ሞረት ፡ ሴቱን ፡ ያሳምራል ።
ወንዱን ፡ ያደረጃል ።
ምንጨን ፡ ያመነጫል ፡
ጠበሉን ፡ ያፈልቃል ፡
ቢለመልም ፡ እንጂ ፡ ጥዱ ፡ መች ፡ ይደርቃል ።
(ቢገዛ ፡ እንጂ ፡ መቼ ፡ ይገዛል ፡ ማለት ፡ ነው) ።

ነገር ፡ ግን ፡ ለግጥም ፡ መልስ ፡ ሲያገኙ ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ለማስገበር ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ የርሳቸውን ፡ ጦር ለመመለስ ፡ የበቃ ፡ ኃይል ፡ ስላልነበራቸው ፡ ላስፋ ፡ ወሰን ፡ በግዴታ ፡ ገበሩ ።

በዚህ ፡ መካከል ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ከወሰን ፡ ሰገድ ፡ ሌላ ፡ ከመንዝ ፡ ባላ ባት ፡ ከምትወለድ ፡ ሴት ፡ ኢዮአስ ፡ የሚባል ፡ ልጅ ፡ ወልደው - ነበርና ፡ አን ዳንድ ፡ መኳንንቶች ፡ አባት'ክ ፡ አንተን ፡ ትተው ፡ ለኢዮአስ ፡ አልጋውን ፡ ሳያወርሱ ፡ አይቀሩም ፡ ብለው ፡ ለወሰን ፡ ሰገድ ፡ ነገሯቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ባባታቸው ፡ ላይ ፡ ሸፍተው ፡ ሲሄዱ ፡ አባትዮው ፡ ከኋላ ፡ ገሥግሠው ፡ ፀጥንት ፡ መስበሪያ ፡ ላይ ፡ ደርሰው ፡ ጥቂት ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ያዟቸውና ፡ በሻሽ ፡ አስረዋቸው ፡ ወዳንኮበር ፡ መልስ ፡ ሆነ ። በሻሽ ፡ ያሰሩበትም ፡ ምክንያት ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ በብረት ፡ ይሞታል ፡ የሚሉ ፡ ንግር ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የብረት ፡ ሰንሰለት ፡ ያገባሁበት ፡ እንደሆነ ፡ ልጄ ፡ ይሞትብኛል ፡ ብለው ፡ ነው ፡ ይባላል ። በኋላም ፡ የሸፈቱበትን ፡ ምክንያት ፡ ቢጠይቋቸው ፡ ከርስዎ ፡ ሕይወት ፡ በኋላ ፡ አልጋዎን ፡ ለኢዮአስ ፡ ሊያወርሱት ፡ አስበዋል ፡ ማለትን ሰምቼ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የልባቸውን ፡ ገለጹላቸው ። አስፋ ፡ ወሰንም፡ ይኸን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ሕይወቴ ፡ ሳለ ፡ አልጋዬን ፡ የፈለግኸ ፡ መሰ ሎኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከኔስ ፡ በኋላ ፡ ካንተ ፡ በቀር ፡ አልጋዬን ፡ ለሌላ ፡ አላወርስም ፡ ብለው ፡ ቃል ፡ ገቡላቸው ፡ ወሰን ፡ ሰገድም ፡ ባባታቸው ፡ ዘመን ፡ አልጋ ፡ ላይፈልጉ ፡ ምለው ፡ ተራረቁ ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ መንዝ ፡ ሄደው ፡ የተማሩትን ፡ ቅኔ ፡ በሸዋ ፡ አልጋ ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋላ ፡ ሲመቻቸው ፡ ራሳቸው ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በቅኔ ፡ ማኅሌት ፡ እየተገኙ ፡ ለተመሪው ፡ እየነገሩ ፡ ይቀኙ ፡ ነበር ። በሥራ ፡ ምክንያት ፡ ሳይመቻቸው ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ቅኔውን ፡ ጽፈው ፡ በበዓል ፡ ቀን ፡ ወደየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ እየላኩ ፡ ተመሪው ፡ ጽሑፉን ፡ እያየ ፡ ያዜመው ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

አስፋ ፡ ወሰን ፡ በዘመናቸው ፡ አንድ ፡ ባሕታዊ ፡ መነኰሴ ፡ ዕድሜኸ ፡ አጭር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ነገራቸው ፡ ያለውን ፡ የመንግሥቻቸውንም ፡ የራ ሳቸውንም ፡ ገንዘብ ፡ ለየገዳማቱና ፡ ለየአድባራቱ ፡ እዘኑልኝ ፡ እያሉ ፡ በማከ

ኍፈል ፡ ግምጃ ፡ ቤታቸው ፡ ባዶ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ርሳቸው ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ከመንግሥታቸው ፡ በፊት ፡ ያለውን ፡ ዕድሜያቸውን ፡ ለመወሰን ፡ ቢቸግረን ፡ በግዛት ፡ ብቻ ፡ ፴፫ ፡ ዓመት ፡ ከሦት ፡ ወር ፡ ገዝተው ፡ ሞቱ ፡ የተቀበሩበትም ፡ ራሣቸው ፡ ባሠሩት ፡ ባንኮበር ፡ ቅድስት ፡ ማርያም ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፻፫ ።

## መርድ ፡ አዝማች ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ።

መርድ ፡ አዝማች ፡ ወሰን ሰገድ ፡ ካባታቸው ፡ ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘር ፡ የመጡ ፡ ሲሆኑ ፡ እናታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ አትሞችሆኖ ፡ ደግሞ ፡ ከዋየት ፡ በመለስ ፡ እስከ ፡ ተከዜ ፡ ላለው ፡ አገር ፡ ባላባት ፡ ከሆኑት ፡ የሚወለዱ ፡ የባላባት ፡ ዘር ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። ከባላባትነቱም ፡ ይልቅ ፡ ከአቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ሲያያዝ ፡ ከመጣው ፡ ከጐንደር ፡ ነገሥታት ፡ ዘር ፡ ይወለዳሉ ፡ ይባላል ።

ነገሥታትና ፡ ባላባቶች ፡ ሁሉ ፡ አባታቸው ፡ የተከለውን ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ የቈረቈረውን ፡ ከተማ ፡ እየተው ፡ ስማቸው ፡ የሚጠራበት ፡ አዲስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መትከልና ፡ አዲስ ፡ ከተማ ፡ መቈርቈር ፡ የተለመደ ፡ ሥራቸው ፡ ነው ፡ እንደዚሁ ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ የቁንዲን ፡ ከተማ ፡ ከተመው ፡ የጊዮርጊስን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተከሉ ።

በደብረ ፡ ብርሃንም ፡ የሥላሴን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ። እስከ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስም ፡ ሄደው ፡ ግራኝ ፡ ያቃጠለውን ፡ የእመቤታችንን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከዜጋመል ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሄደው ፡ ጫካውን ፡ መንጥረው ፡ መቃኞ ያቆሙና ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ጽላት ፡ ያስገቡ ፡ እርሳቸው ፡ ናቸው ፡ ይባላል ።

ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ልጅ ፡ ከያዕቆብ ፡ እስከ ፡ ነጋሢ ፡ ያሉት ፡ "አቤቶ" ፡ ከልጃቸው ፡ ከስብስቴ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ያሉት ፡ «መርድ ፡ አዝማች» ፡ እየተባሉ ፡ ይጠሩ ፡ ነበሩ ። አሁን ፡ ግን ፡ በወሰን ፡ ሰገድም ፡ ባባቶቻቸውም ፡ ዘመን ፡ የሸዋ ፡ ግዛት ፡ በጣሙ ፡ ስለተስፋፋ ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ከነገሥታት ፡ የምወለድ ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ አማራና ፡ ጋላውን ፡ ባዋጅ ፡ አንጐለላ ፡ ድረስ ፡ ሰብስበው ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ የማዕርግ ፡ ስሜ ፡ 'ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ' ፡ ነውና ፡ በዚሁ ጥሩኝ ፡ ይኸን ፡ ዐዋጅ ፡ አፍርሶ ፡ "መርድ ፡ አዝማች" ፡ የሚለኝ ፡ ሰው ፡ ቢገኝ ፡ በብርቱ ፡ ይቀጣል ፡ የሚል ፡ ዐዋጅ ፡ አናገሩ ። ከዚህም ፡ እኔ ፡ የነጋሢው ፡ ልጅ ፡ እያለሁ ፡ አንተን ፡ ጋላውን ፡ ባባቶቼ ፡ አልጋ ፡ ማን ፡ አስቀመጠኽ ፡ አሁንም ፡ ጦር ፡ ይገፍ ፡ መምጣቴ ፡ ነውና ፡ እሚዳ ፡ ላይ ፡ ተሰልፈኽ ፡ ጠብቀኝ ፡ ብለው ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ለነበሩት ፡ ለጐንደሩ ፡ መስፍን ፡ ለራስ ፡ ጉግሳ ፡

መልክት ፡ ልከውባቸው ፡ ነበር ፡ ይባላል ፤ (1) ዳሩ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡
ወሰን ፡ ሰገድ ፡ እስከ ፡ ጐንደር ፡ ሄደው ፡ ራስ ጉግሳን ፡ አሸንፈው ፡ የኢትዮ
ጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለመሆን ፡ ቢያስቡ ፡ ይኸን ፡ አሳብ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡
ያለበት ፡ መሆኑን ፡ በመገመት ፡ ሹማምቶቹ ፡ ሊከተሏቸው ፡ አልቻሉም ፡ ነበ
ርና ፡ አሳባቸውን ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ሳያደርሱ ፡ በመካከሉ ፡ ሞት ፡ ቀደማቸው ።

መኳንንቱም ፡ በዚህ ፡ የዘመቻ ፡ አሳብና ፡ በሌላም ፡ የተቀየሙበት ፡ ምክ
ንያት አልጠፋም ፡ ነበረና ፡ የወሰን ፡ ሰገድን ፡ ባሪያ ፡ በገንዘብ ፡ ገዝተው ፡
በ፲፻ ፡ ፰፻፳ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አስገደሏቸው ፡ ይባላል ። ሌሎች ፡ ግን ፡ አሽሟሻታ
ቸውን ፡ በሚስታቸው ፡ ምክንያት ፡ ሎሌያቸው ፡ ገደላቸው ፡ ይላሉ ። ከሞቱ ፡
በኋላ ፡ በዚያው ፡ ሬሳቸው ፡ ባሠሩት ፡ በቁንዲ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ ተቀበሩ ። ግዛታቸውም ፡ ፬ ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪፬ ።

## ስለ ፡ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፤— (2) ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ መዋዋላቸው ።

ከነጋሢ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ያሉት ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡
ሥራቸው ፡ ያንዱ ፡ ካንዱ ፡ እየበረታ ፡ መሄዱን ፡ ያለፈው ፡ የያንዳንዳቸው ፡
ታሪክ ፡ አስረድቶናል ። «ራስን ፡ መውደድ» ፡ ኃጢአት ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡
ባንድ ፡ ወገን ፡ ግን ፡ «ከሌላው ፡ ለመብለጥ ፡ መታገል» ፡ ላገር ፡ አስተዳደር ፡
ለጥበብና ፡ ለዕውቀት ፡ መስፋፊያ ፡ ድጋፍ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ የሸዋ ፡ ገዥዎች ፡
አባታቸው ፡ ባቀናው ፡ አገር ፤ በከተመው ፡ ከተማ ፡ ተቀምጠው ፡ ያባታቸውን ፡
ጉብዝናና ፡ ሥራ ፡ እያደነቁ ፡ አልተቀመጡም ። ነገር ፡ ግን ፡ በጊዜያቸው ፡
እነሱ ፤ አዲስ ፡ ቀኝ ፡ አገር ፡ በማቅናት ፡ አዲስ ፡ ከተማ ፡ በመቈርቈር ፡ አዲስ ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመትከል ፡ በተቻላቸው ፡ በሥራ ፡ ከባታቸው ፡ ለመብለጥ ፡
መጣጣራቸው ፡ ያስመስግናቸዋል ።

ነጋሢ ፡ የዐይኔን ፤ ስብስቴ ፡ የዶቃቂትን ፤ አብዬ ፡ የሐር ፡ አምባን ፤ አም
ኃየስ ፡ ያንኮበርን ፤ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ የቁንዲን ፡ ከተማ ፡ ከተሙ ። በየከተማቸ
ውም ፡ መኖሪያ ፡ ቤትም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ተከሉ ። እነሱም ፡ በየተራ ፡
በሕይወት ፡ በነበሩበት ፡ ዘመን ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በመበላለጥ ፡ የሠሩት ፡ ሥራ ፡
በጠቅላላው ፡ የሸዋን ፡ ሕዝብ ፡ ጠቀመ ፡ እንደዚሁም ፡ እየቀጠለና ፡ ያንዱ ፡

(1) መርድ ፡ አዝማችንትን ፡ ንቀው ፡ ራስ ፡ መባልን ፡ የመረጡትም ፡ ከራስ ፡ ጉግሳ ፡ ለመፎካከር ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።
(2) ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ከመንገሣቸው ፡ በፊት ፡ ምኒልክ ፡ ይባሉ ፡ ነበር ። ሊነግሡ ፡ በተቃረበበት ፡ ጊዜ ፡
በዚህ ፡ በምኒልክ ፡ ስም ፡ የነገሥኸ ፡ እንደሆን ፡ መንግሥትኸ ፡ አይጸናም ፡ ብሎ ፡ የበቃ ፡ ባሕታዊ ፡ ስለ ፡
ነገራቸው ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ተብለው ፡ ምኒልክነትን ፡ እርሳቸውም ፡ በሕልም ፡ እንዳዩት ፡ ለልጅ ፡ ልጃቸው ፡
ለዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ስጧቸው ፡ ሲሉ ፡ እንማገሩ ፡ ሐሪስ ፡ ጽፈዋል ።

ሥራ ፡ ከሌላው ፡ እየበረታ ፡ ሲሄድ ፡ በወሰን ፡ ሰገድ ፡ ዘመን ፡ ይልቁንም ፡ አሁን ፡ ታሪካቸውን ፡ በምንጠቅሰው ፡ በንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ጊዜ ፡ ቀድሞ ፡ ይገበርለት ፡ የነበረውን ፡ የጐንደርን ፡ መንግሥት ፡ ለመጠቅለል ፡ እስከ ፡ ማስፈራራት ፡ ደረሰ ።

ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ በተወለዱ ፡ በ፲፰ ፡ ዓመታቸው ፡ ንጉሥ ፡ ተብለው ፡ በባታቸው ፡ አልጋ ፡ ተቀመጡ ። በዘመናቸውም ፡ ወታደር ፡ እያዘጋጁ ፡ ገና ፡ በግራኝ ፡ ጊዜ ፡ ተነጥሎ ፡ የቀረውን ፡ ያማራውን ፡ አገር ፡ ለመመለስ ፡ በመቶ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ በጋሎች ፡ ላይ ፡ ይኸንኑ ፡ የተባለውን ፡ አገር ፡ ለማቅናት ፡ ዘመቻ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ። በጦርነትም ፡ ካስገበሯቸው ፡ በቀር ፡ የቀሩትም ፡ ያብቹ ፡ ጋሎች ፡ መልካም ፡ ገዥና ፡ አስተዳዳሪ ፡ መሆናቸውን ፡ ከጎረቤቶቻቸው ፡ በመስማት ፡ በፈቃዳቸው ፡ እየመጡ ፡ ተገዙላቸው ። አብቹም ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ተጠግቶ ፡ ከገበረ ፡ በኋላ ፡ ያብቹ ፡ ባላንጣ ፡ ገላን ፡ በግድም ፡ በውድም ፡ ለሣህለ ሥላሴ ፡ ገበረላቸው ። በዘመናቸው ፡ ያንኮበር ፡ ሚካኤልን ፡ ያፈር ፡ ባይኔ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ አሠሩ ። በባታቸው ፡ በመርድ ፡ አዝማች ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ጊዜ ፡ የተተከለውን ፡ የመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዘመኑ ፡ እንደሚያስደንቅ ፡ አሳደሱት ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ዙሪያ ፡ ያለውም ፡ የየካ ፡ ሚካኤልና ፡ የአቃቂ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ትክል ፡ የርሳቸው ፡ ነው ።

ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ዘመን ፡ ነገሥታትና ፡ መሪዎች ፡ አገር ፡ የሚለማው ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ የሚያገለግሉ ፡ መሣሪያዎች ፡ በማዘጋጀትና ፡ መሣሪያውንም ፡ በመሥራት ፡ መሆኑን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ተረድተው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የግንብ ፡ ያናጢነት ፡ የሸማኔነት ፡ የብረት ፡ ቅጥቀጣ ፡ ሥራ ፡ እንዲስፋፋ ፡ ራሳቸው ፡ ሥራውን ፡ በየግንባሩ ፡ እየተከታተሉ ፡ ያሠሩ ፡ ነበር ። ሠራተኛውንና ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ ራሳቸው ፡ እመሥሪያው ፡ ድረስ ፡ ሄደው ፡ እየተመለከቱ ፡ እያንዳንዱን ፡ ሠራተኛ ፡ በንግግር ፡ ደስ ፡ እያሰኙ ፡ ያበረታቱት ፡ ነበር ። እያሳመረ ፡ ለሚሠራው ፡ ጉርሻም ፡ ዳረጐትም ፡ ሽልማትም ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ። ለእጁም ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ ለመስጠት ፡ ከሠራተኞቹ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንዶቹን ፡ ባለሟል ፡ ስላደረጓቸው ፡ በውነትም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከብረት ፡ ከብር ፡ ከናስ ፡ ከቀንድ ፡ ከዝኆን ፡ ጥርስ ፡ እየተሠራ ፡ የሚወጣው ፡ መሣሪያና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጌጥ ፡ ለዚያ ፡ ጊዜ ፡ አስደነቀ ፡ ይባላል ። መሣሪያውም ፡ ሲገኝ ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ ግብርናውም ፡ የቤቱም ፡ ሥራ ፡ የልብስ ፡ አለባበሱም ፡ የጌጡም ፡ እኳኋን ፡ በመጠኑ ፡ እንደሚያምር ፡ የታወቀ ፡ ነው ። የጠመንዣ ፡ ባሩድም ፡ መሥራት ፡ የተዠመረው ፡ በርሳቸው ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ርሳቸውም ፡ "ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ሸዋ ፡ ወጋላ ፡ ወአዳል" ፡ የሚል ፡ ማኅተም ፡ አሠርተው ፡ በሚልኩበት ፡ ደብዳቤ ፡ በሚዋዋሉት ፡ ውል ፡ በሚያውጁት ፡ ዐዋጅ ፡ ያትሙ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሣዊ ፡ አስተዳደራቸው ፡ ቅርጽና ፡ መልክ ፡ አበጀ ።

በምዕራፍ ፡ ፺፫ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ዝናቸውን ፡ በመስማት ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘትም ፡ ከፈረንሳዊና ፡ ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የሚመጡትን ፡ የወንጌልና ፡ የመንግሥትን ፡ መልክተኞች ፡ እነሻርል ፡ ኢዜንቤርግን ፤ እነሌውስ ፡ ክራፍን ፤ እነክምብን ፤ እነቃሚዚዬን ፤ እነበርቶገን ፡ እነዶክተር ፡ ቤክን ፡ እነኮኔዋልን ፤ እነዡህስቶንን ፤ እነካፒቴን ፡ ሐሪስን ፡ እነሮሼ ፡ ዴሪኮሪን ፡ በደንብና ፡ በሥርዓት ፡ እየተቀበሉ ፡ ስላነጋገሯቸው ፡ የሸዋ ፡ ሰው ፡ ቀርቶ ፡ እነዚሁ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎችም ፡ የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴን ፡ ሥራቸውንም ፡ ጠባያቸውንም ፡ ሁሉም ፡ እያመሰገኑ ፡ በየመጽሐፋቸው ፡ ይጠቅሷቸዋል ። ከነዚህም ፡ በቀር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ የተቀመጡት ፡ ሞንሲኞር ፡ ደ ፡ ጃኮቢስ ፡ (አባ ፡ ያዕቆብ) ፡ ስለ ፡ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ «ኢትዮጵያና ፡ ሐዋርያ» ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ 122 ፡ ገጽ ፡ ሲጽፉ ፡ «ከብልሆች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሦች ፡ ውስጥ ፡ ዋነኛው ፡ (ቅን) ፡ ብልህ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ናቸው» ፡ ማለታቸውን ፡ ጓደኛቸው ፡ ጃን ፡ ባቲስት ፡ ኩልቦ ፡ «የኢትዮጵያ ፡ የሃይማኖትና ፡ የፖሊቲክ ፡ ታሪክ» ፡ በሚለው ፡ መጽሐፍ ፡ በ፪ኛው ፡ ቮሊም ፡ በገጽ ፡ 375 ፡ ጠቅሰው ፡ አስረድተዋል ።

በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ የፈረንሳዊ ፡ ንጉሥ ፡ ሉዊ ፡ ፊልጶስ ፡ (የፊሊጶስ ፡ ኤጋሊቴ ፡ ልጅ) ፡ ሙሴ ፡ ሮሼ ፡ ዴሪኩርን ፡ (Rocher d' hericourt) የእንግሊዝ ፡ ንግሥት ፡ ቪክቶርያ ፡ ካፒቴን ፡ ውሊያም ፡ ሐሪስን ፡ (W. Harris) ፡ ልከው ፡ ከንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ መተዋወቅ ፡ ዠመሩ ።

እነዚህም ፡ መልክተኞች ፡ መጥተው ፡ ከተነጋገሩና ፡ ከተለማመዱ ፡ በኋላ ፡ የሸዋ ፡ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፤ የንግሥት ፡ ቪክቶርያ ፡ ወኪል ፡ ካፒቴን ፡ ሐሪስ ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ ሆነው ፡ ባንኮለላ ፡ ከተማ ፡ ኅዳር ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወዳጅነትና ፡ የንግድ ፡ ውል ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ተዋዋሉ ።

የውሉ ፡ አሳብ ።

ከ፩–፫ ፡ ያለው ፡ አንቀጽ ፤—የሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ነገሥታት ፡ ወይም ፡ የነገሥታቱ ፡ መልክተኞች ፡ የሚወዳጁበትንና ፡ በክብር ፡ የሚቀባበሉበትን ፡ አሳብ ፡ ይገልጻል ።

ከ፬–፲፫ ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ አንቀጽ ፤—የሁለቱ ፡ አገር ፡ ነጋዴዎች ፡ ከብትና ፡ ሌላም ፡ ሸቀጥ ፡ አንደኛው ፡ ባንደኛው ፡ አገር ፡ እየተለዋወጠ ፡ እንዲነግድ ፤ የንግዱም ፡ ቀረጥ ፡ በመቶ ፡ አምስት ፡ ሆኖ ፡ ይኸንኑ ፡ በገንዘብ ፡ ወይም ፡ በከብት ፡ ብቻ ፡ እንዲከፍልና ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ እየተዘዋወረ ፡ ሲነግድ ፡ የሁለቱም ፡ አገር ፡ ነገሥታት ፡ በማናቸውም ፡ እንዳይደግፉትና ፡ የነጋዴዎቹን ፡ ችግር ፡ ለማቃለል ፡ የሚቻላቸውን ፡ እንዲያደርጉ ፤ ከባሕር ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ማኽል ፡ ሸዋ ፡ ድረስ ፡ መንገድ ፡ እንዲከፍቱ ፡ የሚገልጽ ፡ ነው ።

ከ፲፬–፲፰ ፡ ያለው ፡ አንቀጽ ፡ የሁለቱ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፣ ለንግድ ፡ ሳይሆን ፡ ለግላቸው ፡ ባመጡት ፡ ዕቃ ፡ ቀረጥ ፡ እንዳይጠየቁ ፤ የሁለቱ ፡ አገር ፡ ሕዝቦች ፡ ከሸዋ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፤ ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ቢመጡ ፡ ካውራጃም ፡ ወዳውራጃ ፡ እንደ ፡ ልባቸው ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ሲመጡ ፡ ማናቸውንም ፡ በመካከላቸው ፡ ጠብና ፡ ቂም ፡ የሚፈጥረውን ፡ ነገር ፡ እያስወገዱ ፡ በፍፍቅር ፡ ሀይን ፡ እየተያዩ ፡ እየተደጋገፉ ፡ እንዲኖሩ ፡ የሚያስጠነቅቅና ፡ የሚያስገድድ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

## በንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴና ፡ በፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ውል፤ የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ አሳብ ።

በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ አዲስ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ለማግኘት ፤ የምርመራ ፡ ነገር ፡ ተስፋፍቶ ነበር ። በዚሁ ፡ ምርመራ ፡ የግሪክና ፡ የሮማ ፡ ታላቅነት ፡ ያልደረሰበት ፡ የተደበቀውን ፡ ያሜሪካንን ፡ አገር ፡ ክሪስቶፎሮስ ፡ ኮሎምብ ፡ የሚባለው ፡ በ፲፬፻፺፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቍጥር ፡ በኤስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ ደጋፊነት ፡ ካገኘ ፡ ወዲህ ፡ በ፲፮ኛውና ፡ በ፲፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ላይ ፡ የኤስፓኝና ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ባሜሪካ ፤ በእስያ ፡ እየተፎካከሩ ፡ አገር ፡ ይይዙ ፡ ነበር ። ከ፲፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ የእነዚህን ፡ ፍለጋ ፡ በመከተል ፡ ከነዚህም ፤ ከቱርክም ፡ እየተከላከሉ ፡ ባሜሪካ ፤ በእስያ፤በአፍሪካ ፡ መርማሪ ፡ እየላኩ ፡ ለመመከት ፡ በጣም ፡ የሰነፈውን ፡ ቅኝ ፡ አገር ፤ አስቸጋሪነቱን ፡ ወይም ፡ ጥቅሙ ፡ መካከለኛ ፡ የሆነውን ፡ ጠባቂ ፤ ኀይለኛና ፡ የማይበገር ፡ የሆነውን ፡ በስምምነት ፡ ወዳጅ ፡ እያደረጉ ፤ የያንዳንዳቸውን ፡ መንግሥት ፡ በብርና ፡ በወርቅ ፡ ሀብታም ፡ እያደረጉ ፡ የባሕርና ፡ የመሬት ፡ ወታደራቸውን ፡ እያደራጁ ፡ የፈረንሳዊና ፡ የእንግሊዝ ፡ መሪዎች ፡ በፉክክር ፡ ይሽቀዳደሙ ፡ ነበር ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ እሽቀድድሙ ፡ ሲያጋጭ ፡ እየተዋጉ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ በሉዊ ፡ ፈሊፕና ፡ በናፖልዮን ፡ ጊዜ ፡ በግብጽና ፡ በምሥራቅ ፡ እስያ ፡ ምክንያት ፡ ባሜሪካንም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ተዋግተዋል ። በውጊያውም ፡ መጨረሻ ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ ጠላት ፡ እየፈጠረ ፡ ያዋጋው ፡ ነበር ። ለምሳሌ ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ በዋሽንግቶን ፡ ጊዜ ፡ አሜሪካኖችን ፡ እየረዳ ፡ በእንግሊዞች ፣ ደግሞ ፡ ጀርመንን ፡ በቢስማርክ ፡ ጊዜ ፡ በፈረንሳዮች ፡ ላይ ፡ ማስነሣታቸው ፡ ይታወሰናል ፤ የዚህም ፡ የፉክክራቸውን ፡ ሁኔታ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በተጻፈው ፡ በምዕራፍ ፡ ፲፪ ፡ አስረድተናል ።

ስለዚህ ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በወንጌል ፡ መልክተኞቹ ፡ አማካይነት ፡ የሸዋንና ፡ የንጉሡን ፡ የሣህለ ፡ ሥላሴን ፡ ዝና ፡ ሰምቶ ፡ በካፒቴን ፡ ሐሪስ ፡ በኩል ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያመለከትነውን ፡ ውል ፡ ከተዋዋለ ፡ በኋላ ፡ ባላንጣው ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አልተመለከተም ።

ከፒቴን ፡ ሐሪስና ፡ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ በተዋዋሉ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ የፈረንሳዊ ፡ መንግሥት ፡ ሙሴ ፡ ሮሼ ፡ ዲሪኩርን ፡ ልኮ ፡ እንደ ፡ ተፎ ከከረው ፡ የንግድና ፡ የወዳጅነት ፡ ውል ፡ ባ፲፰፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በግንቦት ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ተዋዋለ ።

በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ከተዋዋሉት ፡ ውስጥ ።

ከ፩-፫ ፡ ያለው ፡ አንቀጽ ፡-ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ መቃረብ ፡ በሸዋ ፡ ላይ ፡ የሚነ ሣው ፡ ጠላት ፡ በፈረንሳዊ ዘንድ ፡ የተጠላ ፡ እንደሚሆን ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በፈረን ሳዊ ፡ ጥላ ፡ ውስጥ ፡ የምትተዳደር ፡ በመሆኗ ፡ የሸዋ ፡ ሰዎች ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያሉት ፡ የፈረንሳዊ ፡ ሹማምቶች ፡ በመልከም ፡ እን ዲጠብቋቸው ፡ እንደዚሁም ፡ ፈረንሳዮች ፡ በሸዋ ፡ ሲኖሩ ፡ ከሌላው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የከፍታ ፡ መብት ፡ እንደሚያገኙ ፡ ያረጋግጣል ።

ከ፬—፳ ፡ ያለው ፡ አንቀጽ ፡—የፈረንሳዊ ፡ ተወላጅ ፡ በሸዋ እንደ ፡ ልቡ ፡ እየተዘዋወረ ፡ ሲነግድ ፡ ቀረጡ ፡ ከመቶ ፡ ሦስት ፡ መሆኑን ፡ ያረጋግጣል ።

፯ኛው ፡ አንቀጽ ፡-የፈረንሳዊ ፡ ተወላጅ ፡ ቤትም ፡ ምድርም ፡ በሸዋ ፡ ሲገዛ ፡ የገዛውንም ፡ ቢሸጥ ፡ ቢለውጥ ፡ ችግር ፡ እንዳያገኘው ፡ ንጉሡ ፡ እንደሚጠብ ቁት ፡ ይናገራል ።

፺ኛው ፡ አንቀጽ ፡-ስለ ፡ ውሉ ፡ ግልባጭ ፡ መለዋወጥ ፡ ብቻ ፡ ይናገራል ። በውሉ ፡ ግርጌም ፡ እንደዚሁ ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ የሙሴ ፡ ሮሼ ፡ ፊርማና ፡ የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ማኅተም ፡ ተደርጓል ። ከካፒቴን ፡ ሐሪስም ፡ ከሙሴ ፡ ሮሼም ፡ በተዋዋሉት ፡ ሰሌዳ ፡ በአርእስቱ ፡ መካከል ፡ የሦስቱ ፡ ሥላሴ ፡ በቀኝ ፡ የአንበሳ ፡ በግራ ፡ የርግብ ፡ ሥዕል ፡ አለበት ፡ ይባላል ።

በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለመሆን ፡ የቀራቸው ፡ አባታው ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ አስበውት ፡ ሳይፈጽሙት ፡ የቀረውን ፡ የጐንደርን ፡ መስፍን ፡ ራስ ፡ ዐሊን ፡ የትግሬንና ፡ የስሜንን ፡ ገዥ ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ የጐጃሙን ፡ ደጃች ፡ ጐሹን ፡ ሄደው ፡ ተዋግተው ፡ ማሸነፍና ፡ ጳጳስ ፡ አስመጥተው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ መቀባት ፡ ነበር ። ምናልባት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ቢዘምቱ ፡ ሰዋቸው ፡ እንደነዚያ ፡ በርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ ያልደከመና ፡ የደረጀ ፡ በመሆኑ ፡ ሳይቀናቸው ፡ አይቀርም ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ለመገመት ፡ አስቸጋሪ ፡ አይደለም ። እርሳቸውም ፡ ይኸንኑ ፡ ለመፈጸምና ፡ ተቀብቶ ፡ ለመንገሥ ፡ ጳጳስ ፡ ለማስመጣት ፡ ተላልከው ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ነገር ግን ፡ ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ ይበ ልጥ ፡ በጥንቃቄ ፡ ለመደርጀት ፡ ሲያስቡ ፡ በመካከሉ ፡ ምኞታቸውን ፡ ሳይፈጽሙ ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ የርሳቸውን ፡ ምኞት ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ፈጸሙትና ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ማዕርግ ፡ ለልጅ ፡ ልጃቸው ፡ ለዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በኋላ ፡ ደረሰ ።

ንጉሥ ፡ ሣህለ ። ሥላሴ ፡ ፴፫ ፡ ዓመት ፡ ከምስት ፡ ወር ፡ ሸዋንና ፡ የሸዋን፡ የጋላ ፡ አገር ፡ በሙሉ ፡ በውቀትና ፡ በመወደድ ፡ ሲያስተዳድሩ ፡ ኖሩ ። በዚህ ፡ መከከል ፡ የጦር ፡ አበጋዛቸው ፡ አቶ ፡ መተኮ ፡ የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴን ፡ ልጅ ፡ ለልጁ ፡ ለጃራ ፡ ለምኖ ፡ ስለ ፡ ከለከሉት ፡ በዚሁ ፡ ተናዶ ፡ ሊገድላቸው፡ ሲል ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ደብድበው ፡ ገደሉት ፡ ይባላል ፤ ርሳቸው ፡ ግን ፡ በእ ግዚአብሔር ፡ በሽታ ፡ ታመው ፡ ከቈዩ ፡ በኋላ ፡ በሺሕ ፡ ፳፻፵ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥቅምት ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ ከተማ ፡ ዐረፉ ። ሬሳቸውም ፡ አንኮበር ፡ ሄዶ ፡ ራሳቸው ፡ ባሠሩት ፡ በቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካህኑ ፡ መሐይምኑ ፡ ገበሬው ፡ ወታደሩ ፡ ተላቅሶ ፡ በክብር ፡ ቀበራቸው ።

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ቅኔ ፡ ዐዋቂ ፡ ደብተራ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን፡ የኀዘን ፡ ቅኔ ፡ ተቀኘላቸው ፡ ይባላል ።

ዕዝል ፡ ዕጣነ ፡ ሞገር ።

ደብረ ፡ ሚካኤል ፡ ብክዩ ፡ በላዕለ ፡ እንብዕኪ ፡ ደመ ፤
ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ተስፋኪ ፡ እስመ ፡ ተፈጸመ ።
ወኀልቀ ፡ ለዝሉፉ ፤ ወኢይትመየጥ ፡ ዳግመ ።
ወልበ ፡ ግፉዓን ፡ አስተሐመመ ፤
ፈታሒ ፡ በጽድቅ ፡ ልሳኑ ፡ አምጣነ ፡ በሞት ፡ ተኀትመ ፤
ወእምተናግሮ ፡ አፉሁ ፡ አርመመ ።
ከመ ፡ ሕልመ ፡ ሌሊት ፡ ሞትከ ፡ ይመስለኒ ፡ ንጉሠ ፡ መግበ ፡ ዓለመ ፤
ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ልብከ ፡ ሀላዊ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳመ ።
በደዌ ፡ ኀይልከ ፡ እምድኅረ ፡ ደከመ ፤
እንዘ ፡ ትብልሂ ፡ አሐውር ፡ እምጌሠም ፡ ጌሠመ ፤
ከመ ፡ ዐውሎ ፡ ሞትከ ፡ ቀደመ ።

ትርጓሜ ።

የሚካኤል ፡ ደብር ፡ በንባሽ ፡ ላይ ፡ ደምን ፡ (የደም ፡ እንባን) ፡ አልቅሽ ፤
ተስፋሽ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ተፈጽሟልና ።
ለዘወትርም ፡ አልቋልና ፤ ዳግመኛም ፡ አይመለስምና ።
የተገፉ ፡ (ሰዎችም) ፡ ልብ ፡ አሰበ ፡ (አዘነ ፡ ተቈረቈረ) ፤
በውነት ፡ ፈራጅ ፡ አንደበቱ ፡ በሞት ፡ ተዘግቷልና ፤
አፉም ፡ ከመናገር ፡ ዝም ፡ ብሏልና ።
ልብኽ ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ የሚኖር ፡ ዓለምን ፡ የመመገብ ፡ ንጉሥ ፡
ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ሞትኽ ፡ እንደ ፡ ሌሊት ፡ ሕልም ፡ ይመስለኛል ።
ኀይልኽ ፡ በበሽታ ፡ ከደከመ ፡ በኋላ ፡
ከነገ ፡ ነገ ፡ እሄዳለሁ ፡ ስትል ፡
እንዳውሎ ፡ (ነፋስ ፡ ሞትኽ ፡ ቀደመ ።

## ምዕራፍ ፡ ፻፳ ።

## ስለ ንጉሥ ፡ ኀይለ ፡ መለከት ።

ከክርስትና ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ ያለውን ፡ ትተን ፤ ከክርስትና ፡ ወዲህ ፡ በእስያ ፤ በታናሽ ፡ እስያ ፤ በአፍሪካ ፡ ያሉት ፡ እስላሞች ፡ በገሃድ ፡ እስከ ፡ አራት ፡ ሚስት ፡ ድረስ ፡ ሲያገቡ ፡ ከቈስጠንጢኖስ ፡ ወዲህ ፡ በቊስጥንጥንያ ፡ ያሉት ፡ የክርስቲያን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቶች ፤ የእስያ ፤ የታናሽ ፡ እስያ ፡ የክርስቲያን ፡ ነገሥታቱም ፡ መሳፍንቱም ፡ የወንጌሉን ፡ ቃል ፡ ለመጠበቅ ፡ ያኽል ፡ አንድ ፡ ደንበኛ ፡ ሚስት ፡ በሰማንያ ፡ አግብተው ፡ የቀሩትን ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ቊባት ፡ በያለበት ፡ ማስቀመጥ ፡ በምሥራቃውያን ፡ ነገሥታትና ፡ መኳንንት ፡ ዘንድ ፡ የተለመደ ፡ ነው ። ይኸም ፡ ሥራ ፡ ከወንጌል ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ በለመስማማቱ ፡ ለሰማይ ፡ መንግሥት ፡ ኑሮ ፡ የሚያመጣውን ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ አድርገን ፡ ለዚህ ፡ ለመሬት ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ መጥቀሙን ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ እንጠቅሳለን ።

፩ኛ ፤ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ሚስቱ ፡ መካን ፡ ሆና ፡ በልጋው ፡ የሚተካ ፡ ወራሽ ፡ ያሳጣችው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሌላዋ ፡ ቊባቱ ፡ ልጅ ፡ ማግኘቱ ፡ አይቀርምና ፡ የመንግሥቱ ፡ አልጋው ፡ ለባዕድ ፡ ከመሄድ ፡ ይድናል ።

፪ኛ ፤ አንዱ ፡ ንጉሥ ፡ ከሌሎች ፡ መሳፍንትና ፡ ባላባት ፡ ከሚወለዱት ፡ ጋራ ፡ ሲቻል ፡ በሚስትነት ፡ ሳይቻል ፡ በቊባትነት ፡ የተዛመደ ፡ ወይም ፡ የወለደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መንግሥቱን ፡ ወይም ፡ ራሱን ፡ የሚቃወመው ፡ ጠላት ፡ ሲመጣበት ፡ ዘሩንና ፡ ጋብቻውን ፡ ጠቅሶ ፡ ርዳታ ፡ ለማግኘትና ፡ ጠላቱን ፡ ለማጥቃት ፡ ይመቸዋል ።

በዚህ ፡ ዐይነት ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፤ ወሰን ፡ ሰገድን ፡ ከባታቸው ፡ ቊባት ፡ መውለዳቸውና ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴም ፡ የወሰን ፡ ሰገድ ፡ ልጅ ፡ መሆናቸው ፡ ባለፈው ፡ ተጽፏል ።

ስለዚህ ፡ በዚሁ ፡ እላይ ፡ ባመለከትነው ፡ መሠረት ፡ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በያለበት ፡ ከባላባት ፡ ወገን ፡ የሚወለዱ ፡ ብዙ ፡ ቊባቶች ፡ ማስቀመጣቸው ፡ ባይቀር ፡ ደንበኛ ፡ የታወቁ ፡ የሕግ ፡ ሚስታቸው ፡ ግን ፡ ከኩራ ፡ ወለዱና ፡ ከሞረት ፡ ጥዱ ፡ የሚወለዱት ፡ ወይዘሮ ፡ በዛብሽ ፡ ነበሩ ።

እርሳቸውም ፡ በሺሕ ፡ ፲፰፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አግብተው ፡ አቤቶ ፡ ኃይለ ፡ መለኮትን ፤ አቤቶ ፡ ሰይፉን ፤ ወይዘሮ ፡ በለጥሻቸውን ፡ ወልደው ፡ ከነዚህም ፡ ኀይለ ፡ መለኮትን ፡ ተከታይ ፡ ወራሽ ፡ አድርገዋቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ በሸዋ ፡ አልጋ ፡ ንጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡ ተተኩ ። እርሳቸውም ፡ ባባታቸው ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ የቀናው ፡ አገር ፡ አምጦ ፡ ነበርና ፡ ለገሚሱ ፡ የጦር ፡ ወታደራቸውን ፡ እየላኩ ፡ ለገሚሱም ፡ ራሳቸው ፡ እየሄዱ ፡ አሳመኑ ፤ እስከ ፡ አሩሲም ፡ ድረስ ፡ ዘምተው ፡ ነበር ።

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ከተመለከቷቸው ፡ ውስጥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ አቋቋማቸው መጠነኛ ፡ ሰውነታቸው ፡ ጥንክር ፡ ቈዳቸው ፡ ልስልስ ፡ የፊታቸው ፡ ቅርጽ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝና ፡ ተወዳጅ ፡ መልክ ፡ እንዳላቸውና ፡ ግራ ፡ ዐይናቸው ፡ ላይ ፡ የጣለባቸው ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ (1) ሲያመለክቱ ፤ ኀይለ ፡ መለኮትን ፡ ደግሞ ፡ የተ መለከተ ፡ ያገራችን ፡ ሰው ፡ ግዙፍና ፡ ኀይለኛ ፡ ያደርጋቸዋል ። ለዚሁም ፡ ማስረጃ ፡ ሲሰጥ ፡ ሥጋ ፡ የሚበሉበትን ፡ ቤላዋ ፡ ጠምዘው ፡ እንደ ፡ ቀለበት፡ ማድረጋቸውን ፤ ፊጋ ፡ በሬ ፡ ለመቃረድ ፡ ቀንዱን ፡ በጕሽ ፡ ጠፍር ፡ ታስሮ ፡ ሊወድቅ ፡ ሲል ፡ ለኔ ፡ ስጡኝ ፡ ብለው ፡ ሳለ ፡ በርሳቸውና ፡ በበሬው ፡ ኀይል፡ ተስበ ፡ ጠፍሩ ፡ መበጠሱና ፡ ግማሹ ፡ ጕማጅ ፡ በእጃቸው ፡ ግማሹ ፡ ግን ፡ በበሬው ፡ ቀንድ ፡ ላይ ፡ መቅረቱን ፡ ይተርካሉ ፤ ከሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ ይላማ ፡ ሲተኰሱ ፡ የጠመንዣው ፡ ባሩድና ፡ የተደቀደቀው ፡ ጨርቅ ፡ ፈንድቶ ፡ ጠመ ንዣው ፡ እሁለት ፡ ላይ ፡ ቢቈረጥ ፡ ደንግጠው ፡ ከእጃቸው ፡ ሳይጥሉት ፡ ሁለ ቱን ፡ ጕማጅ ፡ አንዱን ፡ ባንደኛው ፡ ሁለተኛውን ፡ በሁለተኛው ፡ እጃቸው ፡ ይዘው ፡ መቆማቸው ፡ ይነገራል ። ከዚህ ፡ የተረፈውን ፡ የንጉሥ ፡ ኀይለ ፡ መለ ኮትን ፡ ታሪክ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በተጻፈው ፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፤ እስከ ፡ ቀዳ ማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በሚለው ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እንቀጥላለን ። ስለዚህ ፡ ስለ ፡ ተጻፈው ፡ የሸዋ ፡ ባላባቶች ፡ ታሪክ ።

፩ኛ ፤ ጸሓፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ ጽፈውት ፤ አባ ፡ ተስፋ ፡ ሥላሴ ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ተርጕመው ፤ በኢትዮጵያ ፡ ሚኒስትር ፡ የነበሩት ፡ ሙሴ ፡ ሞሪስ ፡ ደኮፔ ፡ አሻሽለው ፡ ባሳተሙት ፡ የዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፤ ከ፩ኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ከገጽ ፡ ፶፬ ፡ እስከ ፡ ፹፩ ፡ ውስጥ ።

፪ኛ ፤ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ አሳትመውት ፡ ሳይጠረዝ ተበታትኖ ፡ በሚገ ኘው ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ።

በተረፈ ፡ በነኵልበ ፡ በነካምብ ፡ በነሮሺ ፡ ዴሪኩር ፡ በነማገር ፡ ሐሪስ ፡ በሌ ሎቹም ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ በየክፍሉ ፡ ይገኛል ።

## ምዕራፍ ፡ ፻፺ ።

## በሥልጣንና ፡ ያለሥልጣን ፡ የነገሡት ፡ የነገሥታት ፡ ዝርዝር ።

አሁን ፡ ያለነው ፡ ሺሕ ፡ ፲፱፻፵ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ ዐፄ ፡ ቴዎ ድሮስ ፡ ሊነሡ ፡ የቀረበበት ፡ የጊዜ ፡ ዋዜማ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ርሳቸው ፡ መገርመሪያ ፡ የራስ ፡ ዐሊ ፡ አሽከር ፡ ሆነው ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ልጃ ቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ተዋበችን ፡ አግብተው ፡ ያንኑ ፡ ያሽከርነት ፡ ሥራቸውን ፡ ይቀጥላሉ ።

(1) ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ግራ ፡ ዐይናቸው ፡ የተሰናከለው ፡ በጉግስ ፡ ጨዋታ ፡ ነው ፡ ይባላል ።

ባለፈው ፡ በምዕራፍ ፡ ፺፺ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ሁሉ ። በበጌምድር ፡ ዋና ፡ የመንግሥቱ ፡ እንደራሴ ፡ ትንሹ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፤ በጐጃም ፡ ደጃች ፡ ጐሹ ፤ በዳሞት ፡ ደጃች ፡ ብሩ ፡ በስሜንና ፡ በትግሬ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ደጋግመን ፡ ስማቸውን ፡ ያነሣናቸው ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ እንዳሉ ፡ ናቸው ። በሸዋም ፡ ንጉሥ ፡ ኀይለ ፡ መለኮት ፡ ለብቻቸው ፡ ሸዋን ፡ የሚገዙበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። በጐንደር ፡ ዙፋን ፡ የተቀመጡት ፡ የራስ ፡ ዐሊ ፡ እናት ፡ የእቴጌ ፡ መነን ፡ ባለቤት ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ፫ኛ ፡ ናቸው ። እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ በመጨረሻው ፡ ምዕራፍ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰን ፡ ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዠምሮ ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣንና ፡ በደከመ ፡ ሥልጣን ፡ የገዙትን ፡ ከዚያም ፡ ያለሥልጣን ፡ በዙፋን ፡ የተቀመጡትን የነገሥታት ፡ ዝርዝር ፡ ከዚህ ፡ ግርጌ እንጽፋለን ።

## በሙሉ ፡ ሥልጣን የገዙ ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ኛ ፤ ዐፄ ፡ ልብነ ድንግል ፡ ስመ ፡ መንግሥታቸው (1)ወናግ ፡ (አንበሳ) ፡ ሰገድ። | | | |
| ፪ኛ ፤ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ | ። | » | አጽናፍ ፡ ሰገድ ። |
| ፫ኛ ፤ ዐፄ ፡ ሚናስ ፡ | ። | » | አድማስ ፡ ሰገድ ። |
| ፬ኛ ፤ ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ | » | » | መለክ ፡ ሰገድ ። |
| ፭ኛ ፤ ዐፄ ፡ ያዕቆብ ፡ | " | " | ? |
| ፮ኛ ፤ ዐፄ ፡ ዘድንግል ፡ | › | " | አጽናፍ ፡ ሰገድ ። |
| ፯ኛ ፤ ዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ | » | " | ሥልጣን ፡ ሰገድ ። |
| ፰ኛ ፤ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ | › | » | ዓለም ፡ ሰገድ ። |
| ፱ኛ ፤ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ፩ኛ ፡ | › | " | አእላፍ ፡ ሰገድ ። |
| ፲ኛ ፤ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ታላቁ ፡ | " | " | አድያም ፡ ሰገድ ። |
| ፲፩ኛ ፤ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ | " | » | ልዑል ፡ ሰገድ ። |
| ፲፪ኛ ፤ ዐፄ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ | " | " | አፅራር ፡ ሰገድ ። |
| ፲፫ኛ ፤ ዐፄ ፡ ዮስጦስ ፡ | " | " | ፀሓይ ፡ ሰገድ። |
| ፲፬ኛ ፤ ዐፄ ፡ ዳዊት ፡ | " | " | አድባር ፡ ሰገድ ። |
| ፲፭ኛ ፤ ዐፄ ፡ በካፋ ፡ | " | " | መሲሕ ፡ ሰገድ ። |
| ፲፮ኛ ፤ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ፪ኛ ፡ (2) | " | » | ብርሃን ፡ ሰገድ ። |

## በደከመ ፡ ሥልጣን ፡ የገዙ ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፲፯ኛ ፤ ዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡ | ስመ ፡ መንግሥታቸው ፡ | | ? |
| ፲፰ኛ ፤ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ፪ኛ | ። | ። | አድማስ ፡ ሰገድ ። |
| ፲፱ኛ ፤ ዐፄ ፡ ተክለ፡ ሃይማኖት ፡ ፪ኛ ፡ | | ። | ኀያል ፡ ሰገድ ። |
| ፳ኛ ፤ ዐፄ ፡ ሰሎሞን ፡ (3) | ። | ። | ጥበብ ፡ ሰገድ ። |
| ፳፩ኛ ፤ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ | ። | ። | ፍቁር ፡ ሰገድ ። |

(1) ስመ ፡ መንግሥት ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ መጠሪያ ፡ ስም ፡ ዕጣነ ፡ ድንግል ፡ የሚሉም ፡ አሉ ። (2) እንዳያታቸው ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፤ ነው ፡ የሚሉም ፡ አሉ ። (3) ሰሎሞን ፡ ጊዜያቸው ፡ አጭር ፡ ሆኖ ፡ ብዙ ፡ ታሪክ ፡ ስለሌላቸው ፡ ምዕራፍ ፡ አላገኘም ።

## በዘመነ ፡ መሳፍንት ፡ ያለሥልጣን ፡ ለስሙ ፡ የነገሡ ።

፺፪ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ፫ኛ ፡ ስመ መንግሥታቸው በዓለ ፡ ጽጋብ ።
፺፫ኛ ፡ ዐፄ ፡ ሕዝቅያስ ፡
፺፬ኛ ፡ ዐፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ፪ኛ ፡
፺፭ኛ ፡ ዐፄ ፡ ሰሎሞን ፡
፺፮ኛ ፡ ዐፄ ፡ ዮናስ ።
፺፯ኛ ፡ ዐፄ ፡ ድሜጥሮስ ፡
፺፰ኛ ፡ ዐፄ ፡ ጓሉ ፡ ዕጓለ ፡ ጽዮን) ፡
፺፱ኛ ፡ ዐፄ ፡ ኢዮአስ ፡
፻ኛ ፡ ዐፄ ፡ ጊጋር ፡
፻፩ኛ ፡ ዐፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ፫ኛ ፡
፻፪ኛ ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ፬ኛ ፡
፻፫ኛ ፡ ዐፄ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡
፻፬ኛ ፡ ዐፄ ፡ ሣህሉ ፡ (ሣህለ ፡ ድንግል) ፡
፻፭ኛ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ፫ኛ ፡ ናቸው ።

የነዚህን ፡ የመጨረሻዎቹን ፡ ነገሥታት ፡ በመሳፍንቱ ፡ በታላቅ ፡ እራስ ፡ ዐሊ ፡ በነራስ ፡ ጉግሳ ፡ በነራስ ፡ ማርዬና ፡ በቀሩትም ፡ ዘመን ፡ ያነጋገሣቸውን ፡ ሁኔታ፡ በመጠኑ ፡ በምዕራፍ ፡ ፸፱–፹፫–፹፱ ፡ ገልጸናልና ፡ እንመለስበትም ፡ ብንመለስበት ያንኑ ፡ የተባለውን ፡ ደግመን ፡ ለማስታወስ ፡ ነው ። በመዠመሪያ ፡ ራስ ፡ ሚካ ኤል ፡ ከዚያም ፡ እነታላቅ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ እነራስ ፡ ጉግሳ ፡ እንደራሴ ፡ ሆነው ፡ የነገሥታቱን ፡ ሥልጣን ፡ በነጠቁበት ፡ ጊዜ ፡ እንደራሴዎቹ ፡ ራሳቸው ፡ ዘውድ ፡ ደፍተው ፡ ለመንግሥት ፡ እንደራሴነታቸውን ፡ እንኳን ፡ ከልብ ፡ ያልተቀበለውን ፡ ሕዝብ ፡ ስለፈሩ ፡ የሕዝቡን ፡ እነሣሥ ፡ ለማስታገሻ፡ ሲሉ ፡ እነርሱ ፡ የመረጡትን ፡ ፩ ፡ ነጋሢ ፡ ከወህኒ ፡ አምባ ፡ ወይም ፡ ከሚገኝበት ፡ ደሴትና ፡ ገዳም ፡ እያስመጡ ፡ ለስሙ ፡ እያነገሡ ፡ ሲያስቀምጡ ፡ ሲጠሏቸውም ፡ መልሰው ፡ ከዙፋን አውርደው ፡ ሌላውን ፡ ልባቸው ፡ የፈቀደውን ፡ አውጥተው ፡ ሲያነግሡ ፡ መስፍንነትን ፡ ለማግኘት ባንድ ፡ ዘመን ፡ የሚከራከሩት ፡ ደግሞ ፡ በየበኩላቸው ፡ ባንድ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ዐፄ ፡ እያሉ ፡ ብዙ ፡ ነገሥታት ፡ ያነግሡ ፡ ነበር ። ከነዚህም ፡ ባንድ ፡ ዘመን ፡ ነግ ሠው ፡ ከነበሩት ፡ የሚታወሱት ፡ ዐፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምና ፡ ዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ናቸው ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ቀድሞ ፡ ነግሦ ፡ የነበረው ፡ ሲስማማቸውም ፡ በራሳቸውም ፡ ጊዜ ፡ እንዲቀጥል ፡ ሲፈቅዱለት ፡ ወይም ፡ አንዱ ፡ አንግሦ ፡ ሌላው ፡ ያበረረውን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አንደኛው ፡ ሲመልሰው ፡ ኖረ ። በዚህ ዓይነት ፡ ዐፄ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ (1)ዐፄ ፡ ሣህሉ ፡ ፪ ፡ ጊዜ ፡ ዐፄ ፡ ጊጋ ርን ፡ ፪ ፡ ጊዜ ፡ እያወጡ ፡ እያነገሡ ፡ እያወረዱ ፡ እየሻሩ ፡ መሳፍንቱ ፡ ነገሥታቱን ፡

(1)፮ ፡ ጊዜ ፡ የሚሉም ፡ አሉ ።

ተጫውተውባቸዋል ። የሚነግሡበትንና ፡ የሚሻሩበትን ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ያንዳንዶቹ ፡ ረዘም ፡ ሲል ፡ የግማሾቹ ፡ በወርና ፡ በቀን ፡ በሚቈጠር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይለውጧቸዋል ።

በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ከነዚያ ፡ ካሰፈሪዎቹ ፡ ከነሠርፀ ፡ ድንግል ፤ ከነፋሲል ፤ ከነኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ የወረዱት ፡ እነዚህ ፡ ነገሥታት ፡ እንደ ፡ ዕቃ ፡ እንደ ሻጕሊት ፡ ለመሳፍንት ፡ መጫዎቻ ፡ ሆነው ፡ ከሺሕ ፡ ፲፻፹ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፲፻፵ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ ሲኖሩ ፡ ራሳቸውም ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ ይኸን ፡ ግፍ ፡ የሚበቀልና ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነትን ፡ ሥልጣን ፡ መልሶ ፡ ለነርሱ ፡ የሚሰጥ ፡ ወይም ፡ ለራሱ ፡ የሚይዝ ፡ አልተገኘም ። የጎጃሙም ፤ የትግሬውም ፤ የላስታውም ፡ ባላባቶች ፡ ቢዋጉ ፡ ቢታገሉ ፡ አልሆነላቸው ። የሸዋውም ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ቢዝቱ ፡ ዛቻቸውን ፡ እፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ አሞካከራቸው ፡ ሳይታይ ፡ ሞት ፡ ቀደማቸው ፤ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴም በዚያ ፡ ሁሉ ፡ ድርጅት ፡ ሳይሞክሩ ፡ በሰላም ፡ በሸዋ ፡ ንጉሥነት ፡ ብቻ ፡ ሞቱ፡ ከመጨረሻው ፡ መስፍን ፡ ከትንሹ ፡ ራስ ፡ ዐሊ ፡ ቤት ፡ ቋረኛው ፡ ደጃች ፡ ካሣ ፡ ብቻ ሳይታሰቡ ፡ ሳይገመቱ ፡ ተነሥተው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነትን ፡ ወይም ፡ መስፍንነትን ፡ ለመውሰድ ፡ በያለበት ፡ ያቄበቄበውን ፡ ሁሉ ፡ በየተራ ፡ አጥፍተው ፡ በጊዜው ፡ የነበሩትን ፡ መስፍንና ፡ ንጉሥ ፡ አሰግደው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነትን ፡ ዘውድ ፡ ለራሳቸው ፡ ተቀዳጁትና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ታሪክ ፡ ያለበት ፡ ሥራ ፡ ለራሳቸው ፡ ማስቀረት ቻሉ ። ይህን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ዘውድ ፡ የማግኘቱ ፡ ነገር ፡ ለነዚያ ፡ ያቃታቸውን ፡ ርሳቸው ፡ አገኙት ። ፀጥታና ፡ ሰላም ፡ ሰጥቶ ፡ ሙሉ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የማስማማቱ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ቢወጡ ፡ ቢወርዱ ፡ ቢዋጉ ፡ ድል ፡ ቢያደርጉ ፡ ቢራሩ ፡ ቢጨክኑ ፡ ለጊዜው ፡ ሳይቻል ፡ ቀረና ፡ የዚሁ ፡ ሁኔታና ፡ ጠንቅ ፡ ራሳቸውን ፡ በራሳቸው ፡ እስከ ፡ መግደል ፡ አደረሳቸው ። የዚህን ፡ ታሪክ ፡ «ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ» ፡ ወደሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ተሻግረን ፡ እንመልከት ።

የዚህኛው ፡ ታሪክ ፡ ተፈጸመ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይድረሰው ።

# ማረሚያ ።

| ገጽ ፡ | መሥመር | ግድፈት፡ | እርም ፡ |
|---|---|---|---|
| ፩፻፵፱ | ፳፰ | His-Torl | Historla |
| ፩፻፹፬ | ፫ | ጸሓፊ፡ ትእዛዝ ፡ ወልደ ፡ ሃይማኖት ፡ ሐዋርያ ፡ ክርስቶስ ፡ | ጸሓፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ሐዋርያ ፡ ክርስቶስ ፡ |
| ” | ፳፱ | ደጃዝማች ፡ ድሜጥሮስ ፡ የሸዋ ፡ ገዥ ፡ | የሸዋ ፡ ምስለኔ ፡ |
| ፩፻፹፱ | ፳፩ | ለሸዋ ፡ ገዥ ፡ | ለሸዋ ፡ ምስለኔ ፡ |
| ፩፻፺፭ | ፭ | መዠመሪያ፡ ቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ ሁለተኛ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ | መዠመሪያ፡ የደብረ፡ ብርሃን፡ ሥላሴ፡ በኋላ፤ የቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ እልቅና ፡ |
| ” ” | ፲፱ | የዐፄ ፡ በካፋ ፡ እኅት ፡ | የዐፄ ፡ በካፋ ፡ የናታቸው ፡ ዘመድ ፡ |
| ፩፻፸፱ | ፲፱ | የሐፄ፡ ስሌ ፡ የሚለው ፡ ለክፍል ፡ ሳይሆን ፡ በጠቅላላው ፡ የመንግሥት፡ ወታደር ፡ እንደ፡ ሆን ፡ ማንበብ ፡ ነው ። | |
| ፪፻፮ | ፲፫ | በትረ ፡ ያሬክ ፡ ያለው ፡ ካማራ ፡ ማይንት ፡ ደጃዝማች ፡ የዐድዋው ፡ ደጃዝማች ፡ ክንቡረ ፡ እዱ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ልዩነት ፡ የለውም ፡ ምክንያቱም ፡ ያማራ ፡ ማይንት ፡ ምስለኔ ፡ በትረ ፡ ያሬክነትን ፡ የዐድዋው ፡ ደጃዝማች ፡ ንቡረ ፡ እድነትን ፡ ደርበ ፡ ይይዛል ። | |
| ፪፻፰ | ፳፮ | አቤሴሎምና ፡ ዳዊት ፡ በደንበኛ ፡ ጦርነት ፡ ሲል ፡ ጠቡ ፡ በገሃድ ፡ መሆኑን ፡ ለማመልከት ፡ እንጂ ፡ አቤሴሎም ፡ ሲሸሽ ፡ መሞቱ ፡ አልተዘነጋንም ። | |
| ፪፻፶፭ | ፳፱ | ዐፄ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ደብረ ፡ መዊእን ፡ ያሠሩት ፡ ፪ኛ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። | |
| ፪፻፷፫ | ፩ | ምዕራፍ ፡ ፸፰ ፡ | ምዕራፍ ፡ ፸፮ ። |
| ፪፻፷፱ | ፫ | ምዕራፍ ፡ ፸፮ ፡ | ምዕራፍ ፡ ፸፯ ። |

## የሥዕል ፡ ዝርዝር ።

1- ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ።

2- ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ።

3- መሐመድ ፡ ግራኝና ፡ ክርስቶፎሮስ ፡ ደጋማ ፡ (በመላ ፡ የተሣለ) ።

4- የዓፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ፍራሽ ፡ (በጐጃም ፡ ደብረ ፡ መዊዕ ፡ አዴት ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም) ፡ (ከአናራቶሬ ፡ መጽሐፍ) ።

5- ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ሸዋ ።

6- ራስ ፡ ዐሊ ፡ ትንሹ ።